# አደፍርስ




ልቦለድ

ከዳኛቸው ወርቁ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY




... ለምሳሌ ጎሊናን የሚያነቁ ሁኔታዎችን ባህላዊ ሙዚቃን - ቅረርቶ ፉከራ ... የመሳሰሉትን ሲሰማ ልቡስ ጥላ ጀኛው ...

# ልቦለድ

ከዳኛቸው ወርቁ

ሠዐሊ - አቶ ታዬ ወልደ መድኅን

የእጅ ጽሑፌን ስርዝና ድልዝ አስተካክላ በመኪና በመጻፍ ለእትም እንዲቀርብ ያበቃችው ወይዘሮ ትዕግሥት ወርቁ።

# መታሰቢያ

ለልዑል ራስ መኰንን ወልደ ሚካኤል

ለራስ አርአያ (አጼ ዮሐንስ አጐት)

ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ

ለደጃዝማች ባልቻ ሣፎ

እና

ለራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በ፴፱ኛው ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፷፪ ዓ.ም

በንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ።

# ፩

# አደፍርስ

ቁንዲ፥ አንገቷን አስግጋ ቃፊርነት የቆመች መስላለች። የዓዋዲና የጀውሃ ጅረቶች ደረታቸውን ለፀሐይ ሰጥተው ይምቦገቦጋሉ። ሰማይና ምድር የተገናኘበት ሕይወት ያሸለበችበት የሚመስለውን በስተግርጌ የሚታይ ሜዳ አቧራ ረግቶበታል። በየስርጓጡ በየሸለቆው፥ በየተረተሩ በየሸንተረሩ - ጉርጅ ወፍ ዋሻ፥ ዋንዛበረት ጃናቦሬ የልቶኪ መጢ፥ ዲዒያውዲያምባ፥ ዓዋዲ፥ ጨኖ አጋምበር ዋይሎ፥ ደብረ ሲና፥ አርማኒያ ሽረሽር ወይን ውሃ፥ ማንያምባ አብዲላቅ፥ ማፉድ ግልዲማ ካሴ አገረ ራሳ፥ መዘዞ አያበርቅ ቀወት፥ ወጃ፥ ጠማሚት ሾተል አምባ.....በየከፍተኛዎቹ ጉባዎች - ግፍት ሚካኤል ራምሴ ሚካኤል ማኒያምባ ሚካኤል፥ የልቶኪ ሚካኤል፥ ዋይሎ ሚካኤል ሐራምባ ሚካኤል ማፉድ ሚካኤል፣ ዋጃ ሚካኤል፣....የይፋትና ጥሙጋ አውራጃን ጣርማበር ተራራ ላይ ሆኖ ሲመለከቱት እግዚአብሔር ዓለምን ሠርቶ ሲያበቃ የተረፈውን ትርክምክም ያጐረበት እቃ ቤቱ ይመስላል። ሸለቆው ጉባው፥ ተራራው ገመገሙ ጭጋጉ አቧራው ሕይወትን አፍኗት ተኝታለች። ያቺ በሌላው አገር የምትጣደፈው የምትፍለቀለቀው የምትቦለቦለው ሕይወት እዚህ እፎይ ብላለች - በርጋታ በዝግታ ታማምለች፤ በተገማሸረ መስክ ውስጥ እንደሚብሰከሰክ ውሃ ..... ሰኞ ማክሰኞ፥ ረቡዕ....ልደታ - (ራጉኤል) - አባ ጉባ - በዓታ - ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ - አቡይየ ጻድቁ - የሱስ ክርስቶስ - ሥላሴ - አርባዕቱ እንስሳ - ቶማስ ሰማዕት - መስቀለ የሱስ - ቅድስት ሐና - ቅዱስ ሚካኤል - እግዚአብሔር አብ - (ሩፋኤል) - አቡነ አረጋዊ - (ገብረ ክርስቶስ) - ሕፃኑ ቂርቆስ - ኪዳነ ምሕረት - እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት - ኤዎስጣቴዎስ ጻድቅ - ገብርኤል - ህንፀታ - ማርያም - ሐዋርያት - ጊዮርጊስ - ተክለ ሃይማኖት - መርቆሬዎስ - ዮሴፍ - መድኅኔ ዓለም - አማኑኤል - በዓለ እግዚእ - ቅዱስ ማርቆስ - ደመራ - መስቀል ቅዱስ ዮሐንስ - ገና - ጥምቀት - ፋሲካ - ትፈስሳለች - ታምማለች፣ ሕይወት በተገማሸረ መስክ ውስጥ እንደሚብሰከሰክ ውሃ..... ወገብ በመዛወር - በመናፈስ - በማሽራሸት - በመዋጥ - በማድቀቅ - በማኘክ - በመጉረስ - በመጋገር - በማቡካት - በመከርተፍ - በመሰለቅ - በመጐተር - በመጐድጐድ - በመቆፈር - በመጐልጐል - በመትለም - በማረስ - በመጨፈቅ - በመጥረግ - ከብት በማሠማራት - የከብት ራት በማስገባት - ማምሻ እንጨት በመልቀም ታልፋለች፥ ትፈስሳለች ታምማለች፥ ሕይወት በተገማሸረ መስክ ውስጥ እንደሚብሰከሰክ ውሃ። በፋሲካ - በፍልሰታ - በገሐድ - በነነዌ - በሑዳዴ - በጾመ

ሐዋርያት - ባርብ ሮብ ትደለላለች፥ ትደከማለች.....በታናሽ (ሹልዳ) - በታላቅ - በጭቅና - (ሰብራዳ) - በሽንጥ - በፍርምባ - በማህል አገዳ - (ጡንቻ) - ወርች - (ነብሮ) - በጐድን ተዳቢት (ቤተ ሳልገኝ) - በምላስና ሰምበር - በልብ - በጉበት - በኩላሊት - በጨጓራ - በሽምፍላ - በቅንጣቢ - በነጭ ጤፍ - በጥቁር ጤፍ - ነጭ ጤፍ - በማሽላ - ዘንጋዳ - ጨረቂት - በባቄላ - በሽምብራ - በቀይ ወጥ - በአልጫ - በጠጅ - በብርዝ - በጠላ - ቅራሪ እንደገናም ደግሞ ቲፍ ብላ ትሞላለች - ትፈስሳለች - ትፈስሳለች - ታምማለች ሕየት በተገማሸረ መስከ ወስጥ እንደሚብሰከሰክ ውሃ። - ኤዛና - ዐምደ ጽዮን - ዘርአ ያዕቆብ - ሱስንዮስ - አምኀየስ - አብዬ - መሳንት - ዮሐንስ - ቴዎድሮስ - ምኒልክ - ደለሏን ትተዋለች - አዝብጤ - ጫልቱ - ለጼሳ - ጐንጤ - ሐዳስ - ቀመሩ - አዛለች - ወርዶፋ - አርያም - ጨቡዴ - አያንቱ - ገብሬ - ተዋበች - ነስሩ - መገርቱ - ቢራቱ - ለተሚካኤል - እርገጤ - አያንቱ - ሐጐስ - ኩሬ - ጉድባ - ጉድባ - ኩሬ - ክትር - ክትር - ጉድባ - ጉድጓድ - ኩሬ - ክትር - ጐለንታ - መስኖ - በርጋታ - በዝግታ - ትገስሳለች - በሌላ አገር የምትጣደፈው - የምትፍለቀለቀው - የምትምቦለቦለው ይችው ሕይወት.....

«እግዚአብሔር ሩቁን የማያይ ይመስልሃል? ተሳስተሃል ወንድሜ፤ እግዚአብሔርን ርቀትና ቅርበት አይወስነውም። እግዚአብሔር እዚህ እዚያ እሁሉ ቦታ ነው - አሁን ከኛ ጋራ ነው ስንነጋገር - ሁሉን ይሰማል - ሁሉን ያያል - ሁሉን ያውቃል። አዎ፥ አንዳንዴ የማያይ የማይሰማ፥ የማያውቅ መስሎ፥ መታየትን ይመርጣል። የበደሉትን ሰዎች እግሮች ተምበርክኮ ያጥባል - እንደፈለጋችሁ - እንደምላዳችሁ - እንደስሜታችሁ፥ ኑሩ የሚል ይመስላል ለብልኀቱ። አንድ ቀን የሱን ትልቅነት የሱን ወሰን የለሽነት የሱን አይመረመሬነት ዘንጋ ያልን ጊዜ ድራሻችንን ሊያጠፋ። ሊያመጣው ውርጅብኙን። ሥልጣናችሁን በሚገባ አልተጠቀማችሁበትም - ለክብሬ የሚገባኝን አላቀረባችሁልኝም - ከየምታገኙት ገንዘብ ጥቂት ጥቂት እያነሣችሁ - ጧፍና ዕጣን ጋድና ሻማ፥ መገበሪያና ጃንጥላ በማቅረብ ፈንታ በሙሉ ተጫወታችሁበት - ጠጅ መሰርገቢያና መገሰቢያ አደረጋችሁት - ስለዚህ እኔም፥ የምሠራውን ዐውቃለሁ ሲለን - መጠጡ ራሳችሁን እያብረጀረጀ ከሳንቃ ጉበን እንዲደስማችሁ አንበጣ አመዳይና ቸነፈር የምትበሉትን አሳጥተው ችጋር እንዲነዙባችሁ - ተጓባቢውን ጐረምሳ፥ ጥጋብ የነፋውን በዱላ፥ የሚመላጐደውን ዱለኛ ለባለርስቱ ለባላባቱ የማይታዘዘውን ገበሬ አንገሩን ሰብረው ጭራውን እንደ ውሻ እንዲሸጉብ እስኪያደርጉት ድረስ - ሊለን! ሊያመጣው የጭቃ ጅራፉን.....» ይላሉ ወይዘሮ አሰጋሽ ለአንዱ ጭሰኛቸው -

«ገባኝኮ አሁን፥ ገባኝ» ይመልሳል ጭሰኛው

«አዎ ይኸውልህ አሁን ገባህ.... ለምን እንደ ገባህ ታውቃለህ.....?» ይቀጥላሉ ወይዘሮ አሰጋሽ «እግዚአብሔር ከእመቤትህ ስለተመሳጠረብህ፥ ግርማ ሞገሱን ከትከሻህ ላይ ስለገፈፈብህ ሀብትህ ስለሚሰሰ ነው። እርሻህ ተጐናዝሎ ብዙ አምርተህ ቢሆን ኖሮ ኩራት እንደነፋህ ትኖር ነበር....

«ይገባኛል.....

«ቆይ ቆይ ልጨርስ! እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ማስታወሻ ነገር ይልካል ለሚረሱት ሁሉ። ማጉረምረም የለብንም - ለኛ ሲል ነው የሚያደርገው - እንዲገባን ያሻል። አስቀድሞን አስታውሰነው በነበር እሱም፥ በበትረ መንግሥቱ ባልረሳን፤ የፈለግነውን በሰጠን ነበር - ጤፍ - ስንዴ - ገብስ - ማሽላ - ባቄላ - ጨረቂት - ያውልህ የፈለግህን ያህል ባለን ነበር። አሁን ግን ይኸውልህ - የእጅህን ፈለግ የእግርህን ንቃቃት፥ የለበስከውን ቡትቶ.....

«ምንኮ አላጣሁትም....

«እግዚአብሔርን መፍራት የመጀመሪያው ጥበብ ነው። ከዚያም የበላዮችህን ማክበር - ባለርስቶችን የንጉሣቸው፥ ልግሥና የእግዚአብሔር ቸርነት ያልተለያቸውን....አዎ ‹ዝምብ ቢጠራቀም ቋጫ አይከፍትም....

«ዐውቃለሁ እመየቴ!»

«ምናልባት ታውቀው ይሆናል፤ ግን አዙረህ ብትመለከት ሥራ ላይ እንዳልዋለ ልትረዳ ትችላለህ። አሁን ለምሳሌ ትንሽ ማሽላ ልትበደር መጣህ። እርግጥ ነው የዛሬን፥ አያድርገውና አክባሪዬና መልካም ሰው ነበርህ። ነገር ግን አምና ትዝ ይልህ እንደሁ ትዝ ይልሃል ርግጠኛ ነኝ ላጨዳና ለውቂያ እንድታግዘኝ ብጠይቅህ ምን ብለህ ነበር የመለስህልኝ? «ደኅና ዋል ስልቻ ፍሬውን ከትቻለሁ› ....የራሴን አላጨድሁ - የራሴንም አልወቃሁ፤ እኔም የሚረዳኝ እፈልጋለሁ! አላልከም? ለመንግሥትኮ ግብር ከፋይ ነኝ፤ ግዳጅ የለብኝም እስከዚህ አላልከም? አምቧት ረህብን ነበርኮ በል - ታዥረህብን ነበር! ‹ዝናብ ባይመጣ ሁሉ ቤት እንግዳ ባይመጣ ሁሉ ሴት!› አዎ ርግጥ ነው ግዳጅ የለብህም......ግን እየው.....እየው......ጊዜው ባይሆንልህ እንዲህ ሱልል ብለህ ጭራህን እንደ ቡችላ ስታወናውን - ! ‹የወደዱትን ቢያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ!› በኔ በኔ ላይ ተዣርረህብኝ ነበር.....

« ‹ጠጉራም ውሻ፥ አለ ሲሉት በራብ ይሞት› የለም....?

«በጣም ኩሩ ነህ፤ ስለዚህ ነው ችግር የጐለሰሰህ..... ግን ታደርግ ‹አውራ ዶሮ በየፍጉ ክምር ላይ ቆሞ ይጮሃል›.....እኔን ተመልከተኝ ለምሳሌ - አዎ እግዜር ሞገስን ንጉሥ ነገሥቴ ክብርህን አልነሡኝም። ሆኖም አልኮራም እንዴት ልኮራ እችላለሁ? ማነኝና! ትል ለራሴ! ትንሽ ፍጥረት - ምናምን! ግን እንደምታየው ራሴን ዝቅ ዝቅ በማድረጌ እግዜርና ንጉሤ ከፍ ከፍ አደረጉኝ በፊታቸው.....በሰማያዊ ኃይል የጐለበተ እንዲህ ነው ይኸውልህ.....እግዜር ሞገሱን ሰጥቶ በንጉሤ ፊትም ሞገስ፥ እንዳገኝ አደረገኝ.....

«የዱሮ ጊዜ ይሻል ነበር እመየቴ፤ እንዲህ እንደ ዛሬው ሳይሆን ባላባትና ገበሬ የሚተሳሰቡበት.....

«እንዴታ ምን ጥርጥር አለው፤ እንዲህ እንደዛሬ የጌታና አሽከር መንገራበብ ያልነበረበት - በየጊዜው የሚያፈጠፍጥ ክፉ፥ ዐመል.....ጥሩው ጊዜ አለፈ ዓለማችሁን ያያችሁበት - አደንጓሬው በቆሎው፥ ደንጐሎው ጨረቂቱ፥ ዘንጋዳው፥.....ምን ያረጋል ብቻ ያለፈውን ቢያስታውሱት? አሁን ማስታወሱ አይበጅም። ዱሮ ዱሮ ነው - ስለ ዱሮው የረሳሁትን......! ‹ፍላጻ ባየር ውስጥ አልፎ ፍለጋ አይተውም!› እና፥ አሁን ታዲያ የመጣኸው ትንሽ ዘንጋዳ ለመበደር ነው አልክ.....?

«ነበራ እመየቴ ማስቸገሬ ባይሆን.....

«ለመግዛት ነው የምትፈልገው.....»

«ከየቴ እመየቴ፤ ብሩ ከየት ተገኝቶ? በዚያው ባይነቱ ለመክፈል ነው እንጂ በትሣሥ.....

«ነገር ግን ማሞድሞድ ገንዘብ አይሆንም ይኸውልህ! ‹ለቀንዳም በሬ በኢት አትከልክለው ቀንዱ ይከለክለዋል!› ነው»

«መቼምኮ የሚሉት ሳይገባኝ ቀርቶ አይደለም..... ብቻ እንዲያው ሰኔና ሰኞ......

«አዎ ካጡ ወዲያ ማንኛውም ነገር አይያምር ‹በሰም የተጣበቀ ጥርስ ቢስቁበት አይደምቅ ቢበሉበት አያደቅ......!›

«ታዲያ ምን ተሻለኝ ይመስልዎታል አሁን.....?

«መከልከሌ አይደለምኮ ‹ሰው ሆኖ የማይብስ እንጨት ሆኖ የማጨስ!›..... ‹ሰው ከስሕተት ብረት ከዝገት.....›

«ታዲያ ያሉትን ብለውኝ ብሄድ.....

« ‹ብረት ካልፈላ አይላላ› - እንዲህ ልክ ገባህ ይኸውልህ......

«ዱሮምኮ ቢሆን.....እንዲያው ባንጣጣም ይሆናሊ.....

«ያልፈው አለፈ፣ አሁን አንድ ልልህ የምፈልገው.....

ምን ነበር እቴ! አዎ ለሁሉ እግዚአብሔርን.....ማለቴ ከሆነ፥ ወዲያ ‹ደሞ ማልቀስ ድንጋይ መንከስ› አያስፈልግም..... ‹ወረቱን እንደ ተቀማ እንጋዴ ዋግ እንደመታው ስንዴ› መሟሰስ የወንድ ልጅ ተግባር አይደለም..... ያሁኑ ወራት ስሕተትን ማረሚያ ነው። ‹ከዝንጀሮ ጋሜ ያንበሳ መላጣ› መሻሉን መገንዘቢያህ.....እድኒያ ተንዠባረህብኝ የነበረው ሰውዬ ቢኖረኝ ነው የመጣኸው ‹.....ተስካር ያየ ተማሪ ሽቀጣ ያየ አጣሪ......›

«የመሄጃ እጦት ነው እመየቴ.....

«ግርምቢጠኛነትህን ትንሽ አብርዶልሃል፤ መቼስ ጨርሶም ባይጠፋ። አዎ ለወደፊቱ መንገድ ስንገናኝም ቢሆን ከፊለፊቴ ሽረር ብለህ መንገዱን ብትለቅልኝ ነውር የለውም.....አንዳንዲኤት እንደሚማልግ ነብር አንዳንዴ እየተፍገረገረ እንደሚለማመጥ ድመት መሆን ያስተዛዝባል.....አዎ ፊት ማጭገግ ወይም መሰንገጭም በኔ አይደለም.....ከግምባርህ ትሕትናን አታጥፋ.....

«እመየቴ መቼም፥ ከዚህ በፊት አላስቸገርኩዎትም....

«እንዴት አዝን ይመስልሃል እንዲህ ተቆራምደህ ሳይ.....

«ታዲያ ታዝኑ......

«እንዴታ! በርግጥ ታሳዝነኛለህ፥ ነገር ግን ወዲያ ወዲህ ሆኖብኝ ነው እንጂ ‹እህል ያለው ፈርዛዛ ገንዘብ ያለው ቀበዝባዛ›..... የተቻለኝን ባደረግሁልህ.....እንደምታውቀው ግን ዘንጋዳው ተወዷል ዘንጋዳ.....እንደ ዘንድሮ ሆኖም አያውቅ......ምን ይመስልሃል ታዲያ......? ደግሞስ ደግሞስ ሰማሆይ መረዳዳትን የመሰለ ምን ዓለም አለ? መረዳዳቱ አይከፋም.....ዛሬ ባበድርህ ነገ ደግሞ እኔ አበድረኝ ልልህ እመጣ ይሆናል.....

«ይሆን ይሆን እመየቴ......መቼስ.....

«አይ ይሆናል እንኳ ብዬ አይደለም.....ያልጠረጠረ ለማለት ያህል ነው..... እና ታዲያ አሁን የምትፈልገው አሥራምስት ቁና መሆኑ ነው.....?

«አዎ እመየቴ ፈቃድዎ ከሆነ......

«ጥሩ ነው.....አሥራምስት ቁና.....ዘጠኝ ቁና እሰጥሃለሁ ማለት ነው፤ በትሣሥ አሥራምስት አድርገህ ትመልሳለህ......

«አይ እኔ እንኳን.....

«እንደምታየው ወለድ አልፈልግም፤ ያው ዓይነት ባይነቱ ነው፤ በብዛት አምርተህ ከምታገባው። አዎ ብዙ አይደለም። ደግሞ በደንብ እየተንቸረፈፈ ይሰፈርልሃል ‹ወዶ የዋጡት ቅልጥም ከፍርምባ ይጥም›

«ትንሽ አልበዛም እመየቴ.....?

«በዛ? አይ እንግዲያው ከበዛ ሌላ ሰው ብትጠይቅ ይሻላል። እኔ እስከዚዊህ የምጓጓለት ነገር አይደለም፤ ስላዘኔታዬ ነው የማበድርህ - አንተ መጣህብኘ እኔ አልመጣሁብህም.....

«መቼም እመየቴ አዘኔታዎን አልኩ እንጂ.....

«አዘኔታ አልተለየህም......ደግሞም ነገር ቢዘበዝቡት ምን ያደርጋል......

«እርግጥ ነው ብቻ የምመልሰው ትንሽ የበዛ መሰለኝ.....

«አይ አይ አይ እንግዲህ በነገር አትጐሽምጠኝ። መንግሥት ከፈቀደልኝ በላይ የምወስድብህ አራጣ በሊታ ማድረግህ ነው? አጉል ተናገርክ። እኔ ደሞ ጠንካር ሰው ስትመስለኝ ወስዋሳና ተልካሻ ወጣህ ልበል.....?

«ዋ እመየቴ መቼም ያላቅሜ......

«ምነው ቢገባህ! እኔስ በምን ልኑር ትላለህ? ስንት መሰለህ የሚተኮሰው ጉዳዬ.....የየቁረንጮው ግብር ራሴን ሊያዞረው ነው። በዚያ ላይ የሮማን ሠርግ ደርሷል.....የየመነኮሳቱ ድርጐ አለብኝ.....ስንቱን ልበልህ.....አዎ ባይሆን ለወደፊቱ በየቦታው ከማዘጥዘጥ ጠንከር ብሎ መሥራት ይኖርብሃል። ‹ወስፌ ቢለግም ቅቤ አይወጋም›.....

«መቼስ ምን ይደረጋል ይሁና ከጨከኑ......

«ጭካኔ! የምን ጭካኔ ጭካኔን ምን አመጣው......? አይ አድራጐቴ ጭካኔ ከመሰለህ ብትተወው ይሻላል.....

«ማለቴኮ እመየቴ.....

«ሰማሁኮ ያልከውን......

«ይሁና እንግዲያው መቼስ ምን አደጋለሁ.....

«አዎ እንዲያ ይሻላል.....ዘንድሮ አምናን አይደለም፤ የምታደርገው ነገር የለም.....በነገራችን ላይ እኔ ላንተ አንድ ነገር ስውልልህ አንተም ለኔ መዋል ሳይኖርብህ አይቀርም.... የክርስቲያን ምልክቱ ነው.....

«ምን ከፍቶኝ የሚሆን ከሆነ.....

«ክርስቲያን ምልክቱ ሲውሉለት መዋል ነው ትልቁ ትምርት፤ እና ታዲያ እዚያ አንተ አዋሳኝ ያለውን ድርቆሼን ብታስተጫጭደኝ......እንደምታየው ወለድ አልጠየቅሁህም......ማለቴ እንደውለታ! ውለታ እንዳይከብድህ.....እኛ ስንረዳዳ እግዜር ይረዳናል ደስ ይለዋል ቁልቁል ሲመለከተን....ደግሞም ላንተ ያን ድርቆሽ ማጨድ ምንም አይጐዳህም፤ እኔ ግን ለወደፊትህ ውለታህን አልረሳም..... ገር ሰው ነኝ እንደምታውቀው.... እርምጃህ ታዲያ ቅድም እንዳነሣሁልህ ትንሽ ተፋጥኗል ‹ሲሮጡ ያሠሩት ሲሮጡ ይፈታል›..... ትንሽ ልጓም አብጅለት.....አዎ አፍንጫ መስቀሉን ትደርስበታለህ። እኔም ብሆን ባንደዜ ብቻዬን አይምሰልህ እዚህ ደረጃ ለመድረስ የቻልኩት፤ አያት ቅድም አያቶቼ ጠጅ የሚያጠጣ ርስት በማቆየታቸው ነው፤ ሸንተውበት ስላላለፉ። አዎ ሰው እንደቤቱ እንጂ እንደ ጐረቤቱ አይኖርም......ድርቆሹን እንግዲኢህ ካጨድኸው በኋላ......አንድ ሰማኒኢያ ሸክም ቢሆን ነው.....እያመጣህ እደጄ እንድትከምረው.....መንገዱ ትንሽ ይርቅሃል.....ስለዚህ አላቻኩልህም - ባሥራምስት ቀንም ቢሆን በወር ልትጨርሰው ትችላለህ......

«እንግዲህ እመንገዴ ልግባ እመየቴ ላይን ሳይዝብኝ.....ጀምበሯ መጥለቋ ነው......

«አዎ ስለ ዘንጋዳው አታስብ፤ ቲፍፍ እየተደረገ ይሰፈርልሃል.....

«ላይን ሳይዝ ቢሰፈርልኝ.....

ጊዜው የከብቶች ከሥምሪት መመለሻ ሰዓት ስለ ነበረ የቀንድ ከብቶች ባንድ ፊት በጐችና ፍየሎች ባንድ ፊት የጋማ፥ ከብቶች ባንድ ፊት የቤታቸውን አቀበት ተያይዘውታል። አፌን ጣው ስርሲርታ የዝንቡ ዝዝታ የንቦቹ እምምታ በዙሪያ ጉብታው ያስተጋባል። አውራ ዶሮ አልፎ አልፎ ይኮኩላል። እውሃ መቅጃው ኩሬ የእንቁራሪቶች ሥርግና ምላሽ ሆኗል። ላሞች ያምቡዋሉ ጥጆች ያስተጋባሉ ያምቧርቃሉ፤ ያ ጭር ብሎ የሚውለው ቀዬ ላንድ አፍታ በሕይወት መምቦልቦል ይጀምራል። እያደር በሚጣደፈው ጭለማ ታፍኖ ሊጠፋ.....

«ሮማን....

«ማነህ አንተ?» ድንግጥ ብላ የሽምጡን አጥር ተገን በመያዝ።

«ሮማን አይዞሽ እኔ ነኝ....

«ማ....

«እኔ.....

«ማ፥ አብዬ.....» ድንጋጤዋ በረድ ባለ መንፈስ።

«የለም፤ ጐርፉ ነኝ.....ዋንዛ ይዝልሻለሁ.....

«እኔ ዋንዛ አልፈልግም.....

«ቅሞም ብትፈልጊ አለኝ.....

«የለም አልፈልግም.....

«ኮሽምስ?

«አልፈልግም! ደግሞ ያልገባኝ አይምሰልህ የመጣህበት.....

«ኮክስ?

«አትቀልድ እባክህ.....

«ቀጋስ፥ ሎሚስ?

«አልፈልግም አልኩህ እንግዲህ.....

«እውነትሽን ነው አሁን?

«እንዴታ! እውነቴን ነው.....

ጐርፉ የሰዓቱን አስባታሊነትና አጣድፊኝነት የከብቶቹን፥ መውጣት መግባት፥ የፍየሎቹንና የበጐቹን መሯሯጥና ትርምስ የጀምበሯንም ጥላ እየዘፈቃት መሄድ በመተማመን ነበር እንደልማዱ የመጣው፤ ገበሮችና እረኞች እንዳያዩት ቆም እያለ ዙሪያውን እየማተረ ስላች ስላች መንገድ እየመረጠ። ቁመናው ጥምጥም ያለ እግሮቹ የሚያጉጧቸውን አፈናጥረው አረጋገጣቸው የተዝናና የተደላደለ ልቡ በዝቅተኝነት መንፈስ ያልተበረዘ.....ፍልጥ ፍልጥ ጥርሶቹን በከትከታ መፋቂያው ሚዣቅ ሚዣቅ አድርጐ በረጅሙ ጢቅ ያለ እንደሆነ ኩራቱን ለመገመት የሚቻል - ገንጋኝ ጠርጣሪ ከፈለገበት ግብ ለመድረስ ታጥቆ የተነሣ የባላገር ቃንቄ ነው። - ያዳል ጫማ አድርጓል

- ቀጭን ሱሪ ታጥቋል - እጀ ጠባብ አጥልቋል - የሳርያን ኮት ደርቧል - ቀጭን ኩታ ሸው አድርጓል - በግራ ትከሻው የተወለወለ አጭር አልቤን አንግቷል። - አጭር ነው - ቀጭን ነው - ጠይም ነው - ግምባረ ሰፊ ጭንቅላተ ገምናና ፊተ፥ ኮስታራ ነው። ጺወኔን እናቲቱ ፈቃዳቸውን ቢሆን ባገር ደንብ መሠረት እንዲድሩለት ደጅ የሚጠና፥ ፈቃዳቸው የማይሆን ቢሆን ደግሞ ጠልፎ ለመውሰድ ቁርጥ ሐሳብ ያደረገ ነው።

«እንጆሪ አትፈልጊም?» ቀጥሏል ማባበሉን። -

«እንጆሪ?!

«አዎ አንጆሪ......

«እንጆሪ......

«አዎ አንድ ነገር ብቻ ካደረግሽልኝ.....

«ምን.....

«ጺወኔን ወደህ ብቅ ብታሰኘልኝ.....

«ጺወኔን....ጺወኔን!..... አይ ጺወኔ ደክሚታል፥ ኮሶ ጠጥታ.....

«ታዲያ የኮሶ ራት አትሻም? ማለቴ ተሰናብቸሃለሁ ብላኝ ነበር!

«ባላገሯን ልፈልግና አታል፥ እባክህ ቀድሞ የት አገኘችህና ነው የምትሰናበትህ? ደግሞስ ጺወኔ ነች አንተን የምታነጋግር..... ረሳኸው በቀደም እዚያ፥ ውሃ መቅጃ እንዴት እንዳስደነጥኸን.....

«ለመሆኑ አንችኮ ኮሶ ጠጥተሽ የለም እንዴ......?

«እኔማ እንዲያውም በትልቅ ዋንጫ ነው፤ ግን እንደምታየው ንክችም አላረገኝ.....እንጆሪውን ያመጣህላት ለኮሶ ራቷ ነው.......?

«አይ እንጆሪውስ ላንቻ ነው.....

«መቼ ተሰናበትሁህና ቀልደኛ ነህ ለካ! ሮማንን አታልላለሁ ማለት ዘበት ነው ዕወቀው.....

«እምልሽ አንድ ነገር እንደሚጠይቅ ጠርተሻት ብቅ ብታሰኘልኝ..... የያዝኩትን እንጆሪ በሙሉ እሰጥሻለሁ.....

«ባንተ ቤት የሚታለልልህ አግኝተሃል..... ይልቅ አብዬን ጠርቼ ማጣፊያው እንዲያጥር ብትሄድ ይሻልሃል......

«እሱን እንኳን እርሸው፤ ያንቺን አባት የሚፈራ የለም..... ይልቅ የጠየቅሁሽን አድርጊልኝ......

«የኔን አባት አትፈራም? የኔን አባት አትፈራም.....

«ቆይ ቆይ ነይ እባክሽ! ቀልዱን እንድምር ታድርጊው.....

«አልፈራውምኮ ብለሃል.....

«በቀደም እጉድባ ውሃ ስትቀዱ ደንገጣችሁ ለካ......?

«መደንገጥ ይነሰን.....

«እባክሽ ጺወኔን ብቅ አሰኚልኝ ሮማን.....

ሮማን ከኋላዋ ኮሽታ ትሰማና ዘወር ትላለች «መጣችልህ እንዲያውም! እስኪ እስከዚህ የቀሠፍሽኝ ለምን እንደ ሆነ እናያለን» ጐርፉ ወደ አጥሩ ጠጋ ብሎ በመሽሽግ የጺወኔን መምጣት ይጠባበቃል። አንገቷን ውዝ ውዝ እያደረገች ወደ ዋናው አጥር በር ታመራለች፤ አህያ ኖራለች ለካ፤ በጀርባዋ ላይ አንድ ስልቻ ተጭኖባታል። ባለቤቷ ጭሰኛው ዱላውን እትከሻው ላይ ጣል አድርጐ ራቅ ብሎ ተከትሏታል።

«ተጫወትትሽብኝኮ ሮማን! ተጫወትሽብኝ!» ይላታል ሮማንን አህያና ጭሰኛ ካለፉ በኋላ።

«እኔኢ አላወቅሁም፤ መሰለኝ.....

«አህያዋ የእመቤትሽን ልጅ መሰለችኝ.....?

«ካልክስ ጭሰኛውም አብዬ ወርዶፋን መስሎኝ ነበር። ለመሆኑ ቢሆን ኖሮ ምን ታደርግ ነበር? እንዲያ ዱላውን አንግቦ ሲመጣብህ.....?

«እሸሽ ነበራ.....

«መሣሪያ ይዘህ ትሸሻለህ.....?

«አሾፍሽብኝኮ ሮማን፥ አሾፍሽብኝ.....ለመሆኑ ብቅ አታሰኝልኝም ማለት ነው እንግዲህ......?

«እንዴት ያለኸው ነህ፥ ለመሆኑ? እመየቴስ ያዩ እንደሆን ምን መልስ ይኖረኛል፤ ታልፍልኛለህ አንተ.....? አትቀልድ እባክህ......!» በእስኪ - እሞክራለሁ - ተሆነልኝ አስተያየት አየት ታደርገውና ዞር ብላ ወደ ቤት ታመራለች።

# ፪

# አደፍርስ

ለዓይን እየያዘ እየጠየመ፥ እየጠየመ ሲሄድ ጐራው.... በየጉባው በየተራራውና በየሸንተረሩ ላይ በመትጐልና በመብነን ላይ ያሉት ደመናዎች ቦታቸውን ለጥቁሩ ሰማይ ይለቃሉ በመጣደፍ። - የሳት ክብ የመሰለች ጨረቃ ትወጣለች። - ጀምበሯ ጨርሶ ትጠልቃለች አድማሱን በሁለት የብርሃን ስለቶች በስተቀኝ፥ ዝቅ ብሎ በሚታየው ሰማያዊ በስተግራ ከፍ ብሎ በሚታየው አብረቅራቂ ሐምራዊ ወትራ ደብዘዝ ያሉ ወርቅማ መሥመሮችንና ገርጣ ያሉ ብጫ ቀለሞችን እያፈለቀች። ቀዬውም ቀስ በቀስ ጸጥታውን መመለስ ይጀምራል። ላሞቹ ከጥጆቻቸው ሲገናኙ ዝም ይላሉ፤ በጐችና ፍየሎች ሞቃት ጥጋታቸው ሲታሠሩ ዝም ይላሉ፤ ንቦች እየቀፏቸው ሲሠርጉ ዝም ይላሉ ዝንቦች እየጣራው እየሥርቻው ሲሰገስጉ ዝም ይላሉ። የከብቶች ራት ተሰጠ ማምሻ እንጨት በየቤቱ ውስጥ መንቀልቀል ጀመረ። - ገበሮች አሹቃቸውን ቃቅመው ራት መብላታቸውን ከብቶች ሣር ወይም ጭዳቸውን ገርደፍ ገርደፍ እያደረጉ ማጠራቀማቸውን ጨርሰው ማመንዠካቸውን ቀጥለዋል - ሸከም - ሸከም - እንካ! - ሸከም - ሸከም እንካ! እያለ የሚያምምና እንደስርቅታ እንደሀቅታ አልፎ አልፎ የሚቋቁር የፌንጣና የእንቁራሪቶች ቁር ቁርታ ብቻ ቀርቷል።

«ምነው ዝም ዝም ሆነ አትነጋገርም?» ትለዋለች ጺወኔ ጐርፉን።

«እነጋገራለሁኮ......! ኮሶ ተጣብቶሽ ነበር መሰለኝ.....?

«ኤዲያ እንዲያው ያው ነህ ምንም አልተለወጥህም» ለራሷ የምትናገር ይመስል «......ስማ የጠለፍኳቸውን ጥቅሶች ላሳይህ.....? ደብረሲና ከወጣሁኮ ብዙ ነገር ተምሪያለሁ.....

አብዛኞቹ ገበሬዎችና እረኞች ጋደም ጋደም ለማለት ይዘገጃጃሉ። ልማዱን ሳያደርስ የማይተኛው ወርዶፋ ደግሞ፥ የምሽቱን ጸጥታ ጥጾ ዋሽንቱን ማሰማት ይጀምራል። - አልፎ አልፎ የሚያፏጭ ነፋስ የነፍሳል። እርስ በርሳቸው

የሚመሰጣጠሩት ቅርንጫፎች ራሳቸውን እዚህና እዚያ ያጓጉናል። - ሰማዩን የተጠጉ የሚመስሉት በሩቅ የሚታዩት ደመናዎች በሩጫ ይበራረራሉ፤ ጨረቃንም አልፎ አልፎ በመሸፈን ሠፈሩን በየድንገቱ በተመሳሰለ ጥላ ሥር ያሳርፉታል።

«ምነው ምን ሆነሃል? የከፋህ ትመስላለህ....... ዘና ብለህ፥ ተጫወት እንጂ......

«እንዳይከፋኝና እንድዝናና ትፈልጊያለሽ.....?

«እንዴታ ምነው?» የማወቅ ፍላጐትና ርኅራኄ ባለበት ድምፅ።

የጨረቃ የብርሃን ውሽምፍር በየቅጠሉ ውስጥ ይዝቀዝቃል። በእልፎሽ አግድሞሽ የተሰበጣጠረ የብርሃን ጥላ ሙካሽ በመጥለፍ - ወርዶፋ ዋሽንቱን ይጫወታል - የዛፎቹ የእንቅስቃሴ ድምፅ የልዩ ዓይነት ፍነጠዝያ ደስታ እየመሰለ ይሄዳል - የሚያጣድፍ ደስታ - የልዩ ዓይነት የልብ ወጀብ - ባዘንና በጭንቅ ጊዜ የሚነሣ ድንገታዊ ነውጽ -

«እንግዲያው መጀመሪያ እንዲህ እንደምታይኝ አትይኝ። ከደብረ ሲና ከተመለስሽ ጀምሮ ሌላ ነው የሆንሽብኝ። - ይገርምሻል አሰያየትሽማ የባሰውን ዝም ነው የሚያሰኘኝ» የባሰ አጉርጣ ታየዋለች «እንደሱ አትይኝ ስልሽ ፍሬ ነገርም ሳንጫወት ተመልሼ እንድሄድልሽ ነው መሰለኝ የምትፈልጊው.......

«ምነው ይዘህልኝ የመጣኸውን የኮሶ ራቴን ሳትሰጠኝ? ሮማንኮ ነግራኛለች.....

ጨረቃዋ እያደር ትንቀሳቀሳለች፤ በያቅራቢያውና በየሩቁ እጅብ ብለው ከሚታዩት የባሕር ዛፍ ጉራንጉሮች ቦግ ቦግ ያሉ ኪሳ ኪሶች ፈጥራ አጉርጠው የሚያዴቡ አስደንጋጭ የጐልያዶች ዓይኖችን በማስመሰል። ቅርንጫፎቹና ቅጠሎቹ ቢሆኑ ሲንቀሳቀሱ መታየታቸው ይቀራል። ራሳቸውን ወደ ሞቃቱ ኅዋ አስግገው የወርዶፋን ዋሽንት በጸጥታ እንደሚያዳምጡ ዓይነት። - ከየደብዛዛውና ርቆ ከሚታየው ጥልቀት ውስጥ ከዋክብት ይንተገተጋሉ። ከየጉድባው ደረት ከየሸለቆው ከየቤቱ ፉካዎች ጭሱና ጭጋጉ፥ ይርመሰመሳል። - ምሽቱ ቀለል ያለ አየሩ በሙቀትና በቅዝቃዜ የተበረዘ ጣዕመ መለኪያው ውደቱና ደስሳው የሆነ በለዘብታ አፍንጫን ሰንጠር ዓይንና ጉንጭን ዳበስ ጐንተል የሚያደርግ.....ዙሪያ አካባቢው ጸጥታ የነገሠበት ታምቆ የተያዘ የሕይወት እፎይታ የሚብሰከሰክበት ነው - በዋሽንት አሸንዳ የሚፈስ......

«ሦስት አራት ጊዜ፥ መገናኘታችን ነው ይኸው ከተመለስሁ.....ግን እንደ ዱሮው አይደለም ሁኔታህ.....እምልህ ገሸሽ አድርጐልሃል.....ሳቅህ ቀልድህ - ስድብህ እንኳ

ቀርቷል» የማወቅ ፍላጐት አስተያየቷን አስቀርታ በርኅራኄና በወዳጅነት ዓይን፥ እየተመለከተች።

«ምን አለ፥ አልሸው እንግዲህ - ማርጀታችን አይደለም?......... ወዴት መሄዳችን ይመስልሻል..... የልጅነት ጠባያችን እንዲሁ ሳይታወቀን ይጠፋል......

«ደሞ ይኸ አትይኝ ብሎ ነገርህ ከመቼ ወዲህ ያመጣኸው ነው.....

«አይ እሱ እንኳ እንዲያው..... የውስጤን የሚያይብኝ እየመሰለኝ ነው......

«ምንቸገረህ ታዲያ አንተ ቢያየው? ምን እስከዚህ የምታፍርበት ነገር አለብህ?» ሳቅ እንደ ማለት ብላ «.....አዳል ለመግደል ራሳ መውረድህን እንደሁ ሰምቻለሁ.....

«አትቀልጂ እባክሽ......

«እምልህ፥ እዚህ ራሳ ሚሉት አገር ስዎቹም ሆኑ እንስሶቹ የከተማ ሰውን ከሩቅ ነው አሉ የሚለዩት ይሸታቸዋል፥ ይሉኛል፤ አፍንጫቸው ከሩቅ ነው የሚያነሣ..... እውነት ነው.....

«እውነት ነዎይ?! እንስሶቹማ አገርግረው ነው ገደል የሚገቡት - ገና ከሩቅ ነው ነፋሱ የሚወስድላቸው......

«ሰዎቹስ እንዴት ነው ሁኔታቸው.... እምልህ የከተማ ሰው ሲቀርባቸው......?

«አገጫቸው ወደላይ ያነሡና አፍንጫቸውን በጣቶቻቸው ጥርቅም አርገው ይይዙታል፤ ሽታው እንዳይገባ..... አንዳንዴማ፥ በግልጽ ትከረፊያለሽ ነው የሚሉሽ በተለይ፤ ከነሱ ጋር ያለሽ ወዳጅነት የቆየ ከሆነ እንደሁ......»

«እናንተስ ምን ትሏቸዋላችሁ.....?

«አይ እኛ ምንም አንላቸው ለምደናቸዋል»

«እሺ እኔንስ አንተ ምን ትለኛለህ?»

«ምን እልሻለሁ?» ድንገት ግራ ይገባዋል።

«እኔ እከተማ ብዙ ተቀምጬ ነው የመጣሁት...... አንተ ደግሞ ከባላገር ብዙ አልተንቀሳቀስክም...... እንዲያውም እንደሰማሁት ከሆነ እነዚያኑ አዳሎቹን አዳሎቹን ለመሸተት ቅቤ እየተቀባህ ቅቤ የተነከረ ሸርጥ እያሸረጥህ ዓዋዲ ለዓዋዲ ትዞር ነበር ብለውኛል.....ለሰባ ፍለጋ.....

«ምነው? እነሱን እነሱን አልከሹ ልበል? ማለቴ.......» ፊቱ ድንገት ቅጭም ይላል።

«የታባቱ አግኝቼ የነሱን ጠረን ዐውቄው?» በፊቱ ላይ ያለፈውን ለውጥ አላጤነችውም።

«ሰው መቼምኮ የራሱን ሽታ አያውቀውም......» ጠበንጃውን ከትከሻው ላይ አውርዶ ለደፉን እቀኝ ጫማው አናት ላይ ያደርግና በቀኝ እጁ በማዟዟር መሬት መሬት እያየ፥ ትንሽ ይቆያል።...... ጺወን ሁኔታውን ስታይ፤

«ጠበንጃህ በጣም ታምራለች...... ማን ይሏታል ስሟን? ተኩሰህባት ታውቃለህ?» በማለት ቶሎ ርእሱን ትለውጣለች። - እሱ ግን አይመልስላትም «......ከሩቅ እንኳን የዚያን ያህል ሲጮህ ጆሯችሁን አለማደንቆሩ ይገርመኛል......» ቀና ብሎ እንኳን ሊያያት የፈለገ አይመስልም።

«ያለፈው ሐሙስ ነበር ልብሴን ያሰፋሁት ደብረ ሲና ወጥቼ......» ዓይኑን ከመሬት ሳይነቅል በኃይል ይተነፍስና መናገር ይጀምራል።

የወርዶፋ ዋሽንት ይሸልላል..... ይድረቀረቃል..... የጉምስናን የግዴለሽነትን፥ የድፍረንት ሥራሥር እየነካካ - የሕይወትን የጥንካሬን ጅማት እየደባበሰ.....በማስገምገም..... በመዝለል..... በመጋፋት...... በመንቆርቆር...... ርስ በርስ በመንተራራስ ከሚኾጕለጕለው የድምፅ ጭፍራ ጋር.....

«አንድ ጥይት ብታስተኩሰኝ እንዴት በወደድሁህ!» ትላለች ጺወኔ ሳታስበው አፏ ይገባና።

«ላስተኩስሽ?» ይላታል ጕርፉም በቅጽበት ፊቱ ፈክቶ ቀና በማለት......በመቀጠልም «እመየቴ ታዲያ ሰው አያድርጉኝ ምን አባቴ ይበጀኛል ኋላ፤ እንዴት ብዬ፣ አይናቸውን......

«አትወደኝም ማለት ነው፤ ላንድ ጥይት ምክንያት ከፈለግህ» ታቋርጠዋለች ጺወኒኤ የፊቱ ወደ ደግ ማብራት ይገፋፋትና።

«አልወድሽም» አልወድሽም..... እኔ.....! ገድሌ ይሙት እልሻለሁ! እንኳን ላንድ ጥይት......» ጠበንጃውን ያቀባብልና አፈ ሙዙን ወደ ሰማይ አድርጎ ባጥሩ ላይ ተንጠራርቶ ይይዝላታል «በይ ምላጯን ወደ ታች ጫን በያት!» እያለ።

«የትኛዋ፥ ነች ምላጯ?» ሴባ ጣቷን እምላጯ ላይ ያደርግላታል፤ ለመጫን ትፈራለች።

«ጫን በያት ወደ ታች...... እንደሱ፤ አይዞሽ አትፍሪ» ትንሽ ሰውነቱ ይዝናናል «ግዴለሽም ተጫኛት.....» ሞት ሽረቷን ትጫናታለች..... ቋ ብሎ ይከሽፋል።

ደሟ ፊቷ ላይ ድንገት ጥቁር ይላል «ባዶውን ነው ለካ.....!»

ቶሎ ብሎ አስፈንጥሮ በመከሸፉ ምክንያት ያቀርብላታል። -

«የለም በቃኝ እንዲያውም ስፈራ ስቸር ነበር..... እማየም አውሬ ነው የምትሆነው.....

«ግዴለሽም ይችን ሞክሪ..... ምነው የያዝሁት ጥይት ሁሉ ፋፍሪካ መሰለሽ እንዴ.....?

«ለሱ ሳይሆን፥ እኔ ብቻ በቃኝ.....

ቁልቁል ወደሚያሶመሱመው ጭለማ መለስ ብሎ ራሱ ይተኩሰዋል። ጥይቲቱ ብልጭ ብላ አስገምግማ ትጠፋለች። የተከተሏት የጺወን ዓይኖችም አብረው እንደበረሩ አይመለሱም ርቀቱ፣ ትክታቸውን አልቀነሰውም። -

የወርዶፋን ዋሽንት ይንሴረሰራል በረጅሙ እያፏጨ ትንፍስ ትንፍስ እያለ - እየራቀ - እየጠለቀ እየወደቀ - እየተነሣ - እየለሰለሰ....... ሹክሹክታና ጭውውት እየመሰለ......እንደ መንፈስ አርነት እንደ ፍቅር ጥልቀት፣ የቅርብ ሩቅ እየሆነ......እንደተዋሐደ የኑሮ ሹክሹክታ ጆሮን እየደላሰሰ - እየራቀ..... እየራቀ...... እየራቀ......

ጕርፉ ባይኑ ብቻ ሳይሆን፥ በሐሳቡ በልቦናው በመላ ሰውነቱ ይከተላታል ጺወኔን «.....እንዴት ቆንጆ ሆናለች፤ እውብኝ እስቲ የፊቷን ጸዳል እነዚህን ዓይኖች እንደ ከዋክብት የሚንተገተጉ እንደ ጥልቅ ጉድጓድ ውሃ የሚጐትቱ የነፍሷ ብርሃን የሚታይባቸው...... እውብኝ እስቲ......» ይላል በመንፈሱ ባድናቆት ተውጦ። - ጺወኔ ድንገት መለስ ትልና ታይበታለች።

«ይኸው አንተም አስተያየትህ ተለውጧል......

«......ከፈገግታዋ መልከቷን ማንበብ የሚቻል...... እንዲህ ያሉ ጥርሶች...... እንዲህ ያለ ጭንቅላት ምንኛ፥ አቀማመጥ በተደላደለ ትከሻዋ ላይ..... ዘምበል ዘምበል ታረገዋለች ደግሞ - እንደ አበባ ራስ - ሽታውን በየመዓዛኑ እንደሚናኝ - ሽቶ እንደሚተነፍስ......

«ናና አቶ..... ምነው፣ ምን ሆነሃል? ተመልከት እንዴት እንደምታየኝ» ትለዋለች ጺወኔ፤ ጥይቲቱ የሰነጠቀችውን መሥመር እንዲለቁ ያልፈለገች ይመስል ዓይኖቿን ቶሎ መለስ በማድረግ። -

«.....መውደድ የሚሉት ነገር...... የእግዚአብሔር ትንግርት..... ወንድና ሴትን ሲሠራ..... ምን ይሏል እስቲ..... ልቤ ድውድውድው...... መርገብገብ ትርትር ማለት..... ምን ይሏል..... ምን ይሏል.....» ጺወኔ እንደ ገና አየት ታደርገውና መለስ ትላለች።

«አይ እንደዚህ አትየኝ፤ እፈራለሁ። - ምነው እኔም እንዳንተኮ ዝም ያሰኘኛል..... ያንጀቴን ለማወቅ ነው፥ መሰለኝ የምታየኝ......

«ያንጀትንሽ?» ያስተጋባል የተናገረችውን ድንገት የነቃ ዓይነት። -

«ምነው? እኔም እንዳንተኮ ብዙ ውጥን አለኝ - የተጀመረ - ያልተጨረሰ - ብዙ ምኞች አለኝ..... ብዙ ለማድረግ የምፈልገው ነገር...... አዲስ አበባ ለመሄድ..... ፈረንጅ አገር ለመሄድ..... ሙዚቃ ለመማር..... ምን ብቻ ልንገርህ.....

«ጺወኔ! ጺወኔ! እናትሽ ይጠሩሻል» ትላለች ሮማን ተሹለክልካ መጥታ - ጥይት ሲጮህ አልሰማችሁም..... እመየቴ ተቆጥተዋል፤ ጭሰኞቹ ብለው ብለው ደግሞ በጥይት ይጫወቱ ጀመር...... ቆይ ግዴለም ይላሉ። ጺወኔ ጐርፉን አየት ታደርገውና ደጎናደርም ሳትል ወደናቷ እልፍኝ ትመለሳለች «......እንጆሪውን ሰጠሃት? ትጠይቀዋለች ሮማን ጐርፉን እሱም ለመሄድ ዘወር ሲል..... ምንም ሳይናገር በብሳና ቅጠል የተጠቀለለ ነገር ከኪሱ አውጥቶ ይሰጣትና መንገዱን ይቀጥላል..... ሮማን ቅጠሉን በመገላለጥ «......አይ! ዱሮ ፈራርጧል..... ተበላሽቷል..... ተበላሽቷል...... ተበላሽቷል..... ፈራርጧል........» እያለች ከዚህና ከዚያ አንዳንድ እያነሣች ወደ አፏ በመውሰድ ተመለሳለች።

# ፫

# አደፍርስ

«ደሞ ወዴት መሸልሽ........» እንግዲህ አንቺ የወርዶፋ ጐጆ የሙጥኝ ካልሽ በጊዜ ላትገቢ? - - ምነው ሰው ያስባል ብትዪ ትንሽ - - በዚህ አያያዝሽ መግቻሽን እግዜር ያብጀው - - ይገርማልኮ ባካችሁ - - ቀን ቀን ይሁን በጄ፥ ደሞ የማታው እስኪ የምኖሽ

ይባላል..... አልበዛም....?» ይገሥጿታል ከውጪ ተጠርታ እንደገባች ጺወኔን ወይዘሮ አስጋሽ። -

«አዎ እሱ ጐጆ አነሣለሁ ስል ነው ጊዜው እንዲያው ሳይታወቅ የኳተነው.....

«አዎ እሱ ጐጆ ስትሆኚ ሁልጊዜ ጊዜው አይታወቅሽም..... ከኔ ጋር ቢሆን ኖሮ ግን ዱሮ አሥራ ሁለቱን ምክንያት በፈጠርሽ!..... ለመሆኑ የተነገ ወዲያ ሳምንት ዳኞቹን የምንጋብዝበት ቀን መሆኑን ዐውቀሽዋል.....?

«አዎ ዐውቄዋለሁ.....

«ታዲያስ ምን ምን ነበር የተነጋገርነው? ዱሮ ረሳሽው መሰለኝ ያንች ነገር.....

«እንዴት ረሳዋለሁ ደጋግመሽ ነውኮ የነገርሽኝ እማዬ አልረሳሁትም ......

«አዎ ‹ላንበሳ አይመትሩም.... ቢሆንም ካሳብሽ ባይጠፋ ጥሩ ነው። አዎ ያዲስ አበባ ሰው ሠልጠን ሠልጠን ሲሉ ይወዳል..... የኔ ያሰጋሽ አንድ ልጄ ባላገር እድንትባል አልሻም.... ዋይ ነዶ ዛሬ ሹርባሽን ተፈተሽው ቢሆን ኖሮ..... ነገ ደብረ ሲና ተማሪ ቤት ሆነሽ ድረስ ደጋግሞ ቢበጠር እዚያ ዘጴ ታበጅለት ነበር.....ብቻ ግዴለም አሁንም ቢሆን..... ‹ባለፈ ክረምት ቤት አይሠራም፤ ከተጋሽበት ይደርሳል። ነገ ጧት ማለድ ብለሽ ተነሥተሽ....

«አብዬ ወልዱ ይመጣል ይቀራል?»

«እንግዲህ መቼም ጴጥሮስ ለሁሉም ነግሬያለሁ ብሏል። ደግሞም ዳኞቹን በይበልጥ የሚያውቃቸው ወልዱ ስለሆነ እሱ ካልመጣ እነሱም ቀሩ ማለት ነው.የለም በደስታ ነው ብሏል ጴጥሮስ ዳኞቹ ግብዣውን የተቀበሉት፤ ስለዚህ ወልዱም አይቀር...... ይልቅ ስለ በላይ አልጠየቅሁትም....

«አይ አጐቴ ከመጣስ በላይ አይቀርም..... እኝህ አቶ ጥሶ ሴት ልጅ አለቻቸው አሉ እሷም ትመጣ ይሆን.....?

«ሳትመታ አትቀርም። ሌላም የእኅታቸው ልጅ የሆነ የውምበርሴት ተማሪ ተከትሏቸዋል ብለውኛል፤ ምናልባት እሱም ይመጣ ይሆን..... ብቻ ለሁሉም መጣፎችሽን የፈረንጁንም ያበሻውንም ትንሽ ትንሽ ብትመለከቻቸው አይከፋም.....» ቀደም ብሎ አጠገባቸው ከተቀመጠ አድን ድብኝት ውስጥ አባሯ የተሸከሙ መጽሐፎችና ደብተሮች እያውጣጡና «እፍ እፍ» እያሉ እያራገፉ ያቀብሏታል።

«አሁን እስከ ዛሬ ደብቀሽብኝ ቆይተሽ በአምስት ስድስት ቀን ውስጥ ምን እይዛለሁ ብለሽ ነው የምትሰጭኝ......? እንዲያው ነው አማዬ.....!

«የለም እንዲያው አይደለም። የኔ ልጅ ልባም ነሽ ሁለት ሦስት ቀን ቁጭ ብለሽበት ካደርሽ አያቅትሽም..... በተለይ የምፈልገው ፈረንጅ አፍ እንድታናግሪያቸው ነው..... እና ደሞ የ ‹ሳኒስ› ደፍተርሽንም እንድታሳያቸው። አዎ ሁሉንም ነገር ዐውቀን የተውነው መሆኑን እንዲረዱት ያስፈልጋል......

«የቋንቋ ችግር አልያዛቸውም እነሱ የኔ ማወቅ አለማወቅ....

«ግዴለሽም ልጄ የሚበጀውን ስነግርሽ ስሚኝ....... ከተማ ሰው ለሆነ ሠልጠን ሠልጠን ማለቱ አይከፋም - ባነጋገርሽ ባለባበስሽ በቋንቋሽ እንኳን ሳይቀር ሁሉም ዘበናይ መሆን አለበት። - እያለን እንደሌለን አያወቅም እንደማናውቅ መስለን መታያታችን ለማን ይድላው ብለን ነው.....? ልጄ እንዲያውቁት ያሻል...... እንዲያውቁት ያሻል......? ልጄ እንዲያቁት ያሻል.....እንዲያውቁት ያሻል...... አስጋሽ ማን እንደ ሆነች..... ጺወኔ ግን እንደሆነች...... አሰጋሽ የዋዛ ሴት ወይዘሮ ያለመሆኗን - እንዴታ! - እንዲያቁት ያሻል......

# ፬

## አደፍርስ

ጺወኔ የወይዘሮ አሰጋሽ ዝራው አንድ ልጃቸው ነች። በተፈጥሮዋ ደስተኛ ጤነኛና ያልተዘባነነ አስተዳደግ የነበራት የቀላልና ተራ መሳይ፥ ያኗኗር ዘዴ ኋላዋ የማትል ናት። ቃሏ ሐሳቧ ድርጊቷ ሁሉ ተዝናንተው የሚመነጩ ናቸው።......ብሩህ ነፍስ ቀስ ያለና ተደራርቦ የሚወጣ የወጣትነት ቃጭል ድምፅ ዝግ ያለ የማይለዋወጥ ጠባይ አላት። በተለይ የማትስማማበት ነገር ሲኖር ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ ትናገራለች። አምላኳን የምታፈቅርና የምትፈራ ሰውን እንዳታስከፋ የምጣጣር ትሕትና አንጀተ ሩሩ ነች። ድንገት የማያያት ሰው የተደላደለ ገራም ብርሃን በፊቷ ላይ ረብቦ ይመለከታል። በሊጋና በለምለሙቻ የማወቅ ፍላጐት ልቧ የሚፍለቀለቅ በከንፈሮቿ ላይ የተለዩ አዳዲስ ነገሮችን አይቶ የማድነቅ ዓይነት ፈገግታ የሚዟዟርባት ናት። ዓይኖቿ በመለኮታዊ ፍቅር እንጂ በዘማዊ እሳት፥ የማይንተገተጉ - አሁን አራዝመን በመመልከት የሌለን እንምሰል የሰጠምን እንምሰል አሁን፥ ትንሽ ድክምክም ያለች የተጨነቀች ድምፅ እንድታሰማ አድርገን በማጉረጥረጥ ሰዎችን ለርዳታ እናስከንፍ - አሁን የሚያዩንን ሁሉ

አትክነን በመመልከት እንዲርበተበቱ እናድርግ የማይሉ - ልዩ ዓይነት ግምት የሚታይባቸው ናቸው።

ማሰብ ስትጀምር ራሷን ወደ ግራ መታ የማድረግ ልማድ አላት። የተናገረችም እንዲሁ ምን ጊዜም ቢሆን ዋጋ ያለውም መስሎ፥ ባይገመት ግላዊ አስተያየቷን ነው። ነገር ግን አታበዛም። የረቀቀ የጠለቀ ተረትና ምሳሌ መጥቀስ ግጥም መዝረፍ ንግግር ማሳመር አታውቅበትም ስለ ፍቅርም ሆነ ስለ ሕይወት ስለ ሙዚቃም ሆነ ሥነ ጽሑፍ አንባ ያገኘችውን ወይም የሰማችውን አስተያየት የራሷ አስመስላ ማቅረብና ያለች ይበሉኝ ድንገተኛ የተጣደፈ ያልታሰበና ያጐረጠ አስተያየት መሰንዘር አትወድም። ከዚህም የተነሣ በየድግሱ ቤት ተጠርታ በሄደች ቁጥር ተደስታ አትመለስም። ስንቶቹ የዕድሜ እኩዮቿ ስንቶቹ ጐበዛዝት ተጨዋቾችና ቦረቦሬዎች ቀልድ ጨዋታ የማታውቅና ኩሩ እየመሰለቻቸው እሷ አጠገብ ሲደርሱ ጠባያቸውን ይለውጣሉ.... ጨዋታውን ያቆማሉ.... ምን እንደሚሉና እንዴት እንደሚሉ ይጠፋባቸዋል ይደናገራቸዋል። የሚጠጓት የሚያነጋግሯት አድናቂዎች አልነበሯትም። እሷም ያልታሰበ ድንገተኛ አጉል ነገር ወይም ስሜት የሚያናውጥ ሁኔታ ቢገጥማትም እንኳ፥ መቻል ልማዷ ነበር።ግፋ ቢል ሽፋሏ ይርገበገብ እንደሆነ ነው እንጂ ፊት የማትቆር ወይም ግምባር የመኮስተር ሁኔታ አይታይባታም።

ጐርፉ ቢሆን ግን አብሮ አደጓ ነው። አብሯት ፊደል፥ ቆጥሯል ዳዊት ደግሟል አርማኒያም እተቋቋመው መንግሥት ትምህርት ቤት አብሮ ገብቶ እስከ ስድስተኛ ክፍል ተምሯል። በኋላ ግን እሱ በፈቃዱት ምህርቱን ሲያቋርጥ እሷ ሰባተኛ ክፍል ወነበረበት ከተማ ወደ ደብረ ሲና ወጥታ አጐቷ አቶ ወልዱ፥ ዘንድ እየተቀመተች ትምህርቷን እስከ ስምንተኛ ክፍል ቀጠለች።

ደብረ ሲና በቆየችበት፥ ሁለት ዓመቶች ውስጥ ብዙ ጥበቦችና ቀሠመች። ልዩ ልዩ ጥልፍ መጥለፍ ሙዳይና አገልግሎች መስፋት ሐርሞኒካና ክራር መጫወት ችላ ነበር። በተለይማ በክራር ቅኝት ያሚያህላት አልነበረም። እንቅልፍ ሳያታልላት ሌሊት እየተነሣች መጫወት ትወድ ነበር።..... አዲስ ዘፈን በሰማች ጊዜ በቃሏ ስታንጐራጉረው ታመሽና ሌሊት ሲሆን ትጫወተዋለች። ቀን ቀን ሲሆን ግን እምብዛም ስትጫወት አትሰማም «.....ቀን ቀን ሲሆን በጅ አይለኝም» የሚሉ አማርኛ ነበራት።

አጐቷ አቶ ወልዱ በደብረ ሲና የታወቁ ነጋዴና የፈረንጅም ትምህርት ትንሽ የጠቃቀሱ ስለ ነበሩ የጺወኔን የሙዚቃ ወዳድነት እንደ አዲስ ነገር አላዩትም። ከእኅታቸው ከወይዘሮ አሰጋሽ ጋር እንኳን በተገናኙ ቁጥር ያወሩት የነበረው በቀለም ትምህርት ስለነበራት ጉብዝና ነበር እንጂ ስለ ክራሩ አልነበረም። አንድ ቀን ነው

እንዳጋጣሚ ሆን አባ አዲሴ የናቷ የነፍስ አባት አጐቷ ቤት አድረው ሌሊት ስትጫወት ሰምተዋት ኖሮ ነገሩ ሁሉ አጓጉል ትርጉም የወሰደው። በማግስቱ ጧት እሷ መሆኗን ሲሰሙ በጣም አዝነውና ግራ ገብቷቸው የመጽሐፍ ስሟን እየጠሩ ብዙ ተደገሙ በኋላ «ጻእ መንፈስ ርኩስ ጻእ መንፈስ ርኩስ!» እያሉ በውሃ በመቸቸር እማጥመቅ ድረስ የደረሱት። ከዚያ በኋላ ነው እንግዲህ ክራር መጫወት አለማቆሟን ሲረዱ ዘማዊ የሆነ ሌጌዎን የሚባል ሴጣን ተቆራኝቷታል በማለት ለናቷ ነግረው የመንግሥቱን ትምህርት አቋርጣ ወደ ትውልድ መንደሯ ወደ አርማኒያ እንድትመለስ የተደረገው። ሆኖም ግን ዱሮም ካርማኒያ ከመንቀሳቀሷ በፊት አዳዲስ የሥልጣኔ ቅርሶችን የመያዝ ችሎታዋ ፈጣን ስለ ነበረ ጉርፉን ብዙ ጊዜ ንግግሩን በማረም አለባበሱን በማኪያኪያስ የተሻለውን መንገድ እንዲከተል ትረዳው ነበር። ስለዚህ ደብረ ሲና ከርማማ በተመለሰች ርቀታቸው እየሰፋ ሄዶ ነበር።

# ፫

## አደፍርስ

ወይዘሮ አሰጋሽ ዝራው የነፍጠኛ ልጅ ናቸው። በአባታቸው መንዝ ገበታ በር ከአጋፋሪ ወልዱ የልጅ ልጅ በእናታቸው ደብብ እጎት ከሚባሉ የጺጋ ዘር ይወለዳሉ። አርማኒያ ከምትባለው ትንሽ ከተማ አቅራቢያ እያሳረሱ ይኖራሉ። ባገር ቤት እንደተለመደው የባላባት ልጅ ስለሆኑ አጥር ግቢያቸው የተሠራው የዶቃቂት ሚካኤል ከተተከለበት ጉባ አነስ ባለው ላይ ነው ‹ከሊቀ መልአኩ ራሴን ያወዳደርሁ እንዳይመስል ነዋ› ይላሉ አንዳንዴ ስለዚህ ወሬ የተነሣ እንደሆነ ሲያወሩ።

በጣም ሰፊና ዙሪያውን በቅንጭብ በጮጮ በዋንዛ፥ በአባሎ ዛፎችና በከትከታ ሽምጥ የታጠረ ነው። ግቢያቸው የሽምጡ ቁመት በሰው ቁመት አይደረስም። በውስጡም ከአምስት በላይ የሚሆኑ ቤቶች፥ አሉበት ጐጆ ከሚመሳሰሉት ጉተራዎች በስተቀር። -

እልፍኙ ተደራራቢ ቤተ ንጉሥ ነው፤ ዋናው እልፍኝ፣ ስምንት በስምንት ዙሪያውን የሚገኘው ተቀጥላው አራት በአራት። በወፋፍራም የወይራ የቆራስማ ያደርና የመዛዛኝ እንጨቶች፥ ተገርግሮ - በጥድ በዋንዛ፥ በቀጨሞ እንጨት ቋሚነትና አግዳሚነት በጓሳ ገመድ ተማግሯል። ክዳኑ በዋንዛ በግራር በዝግባ ፍልጦች ተሸጋጋሪነት ተገጣጥሟል። - እዝግባው ምሰሶ አናት ቅርጻ ቅርጽ ያለበት ዋልታ

ተሰክቶበታል። ከዋልታው በላይ ዙሪያውን ጣራውን ለሚሸጋገሩት መቃዎች ጥብቅት ለመስጠት ሲባል አለፍ አለፍ ብለው ከምሰሶው ተገናኙ የወይራና የጠዬ እንጨቶች ተዘርግተዋል። የተማገሩት በሙሉ በጠፍር ነው። ክዳኑም ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ የኖረ ቢሆን ንቅስ ያለና፥ ተከርክሞ በደምብ የተደመደመ መሆኑ ያስታውቃል። አናቱ ላይ ጉልላት ተጐልሎበታል።

ወደ እልፍኝ የሚያስገባው ዋናው በር አንድ ነው ውስጥ ውስጡን ግን ብዙ፥ በሮች አሉት - ወደ ማድ ቤት ወደ እቃ ቤት ፈትል ቤት የሚያስገቡ።

እዋናው እልፍኝ አንድ የጠፍር አልጋ አለ። ካልጋው በስተጀርባ እግርግዳው ላይ የሚቹ ባላቸው የሻለቃ ይነሡ መሣሪያዎች - ጦር ጋሻ፥ ለበን ጠመንጃ ድግ በስልቻ ዝናር አልፎ አልፎ በቆዳ የተለበተ ከዘራ ተሰቅለዋል። በሰተ ቀኝ የግርግዳውን ጥግ ይዞ ባለቤቲቱ ራሳቸው ማታ ማታ ጉርሻ ያስለመዷቸው የፍየልና የበግ ሙከቶች መታሰሪያ ነው። ከጠፍሩ አልጋ ትንሽ ራቅ ብሎ በፊት ለፊቱ ምድጃ አለ፥ ዙሪያውን በጭቃ ተለስኖ ሙያሌና ቁንጫ ለመከላከል ያልክ በእበት የተለቀለቀ። በአቅራቢያው ብዙ መደቦች ተመድበዋል በላያቸው ነጫጭ አቡጀዴዎች ጣል ጣል ተደርጎባቸዋል። የመደቦቹ አፍንጫ ላይ የሽክና ማስቀመጫ የሚሆኑ ጉድጓዶች ተሰርተዋል። በስተ ግራ ከጠፍር አልጋው ትንሽ ራቅ ብሎ እንደገና አሁንም የግድግዳው ጥግ ይግ ይዘው ጥጃዎች ታስረዋል። በቅርብ ጊዜ ውስጥ የተወለዱ ናቸው። እነሱን በማየት ስንት እንደሚያልቡ ለማወቅ ይቻላል። ባገር ቤት ስንት መስመር አለው አልተለመደም ስንት ያህል ባል? ስንት ይጠምዳል? ስንት ገበሬ ስንት ታጋዥ አለው ነው የሚባለው። ስለዚህ ጥጆቹ ከእልፍኝ ውስጥ የመታሰር እድል አላቸው። ባለቤቱም እልፍኝ በገባ ቁጥር ጥጆቹን እምቧ እምቧ ሲሉ ሲሰማ ጠረነችሁ አይራቀኝ በማለት ደስታውን ይገልጣልን፣ ይጠጋቸዋል ያሻሻቸዋል ሳራቸውን ጨርሰሁ እንደሁ ይጨምርላቸዋል መኸገር ይዟቸው እንደሆን ይነቅልላቸዋል። ሰውና እንሰሳ እንደዚህ በህብረት ባንድ ቤት ውስጥ ይኖራሉ።

አካባቢው ቤተ ንጉሥ ውስጥ ውስጡን ተከፍሏል። በዋናው እልፍኝ በር ገብቶ በስተ ቀኝ የሚታየው በር ክፍል የባለቤቷ የደጋን የቅል አንገት የንዝርት እቃ የፈትል የቅቤ ቅል የጨው ቅል የልቁጥ ድልህ ማሰሮዎች የሌማት የሰዷቃ ማስቀመጫ ነው። በስተ መካከል ሲል የሚታየው በር ክፍል የፈትል ዱባዎች የተደራ ድር አገልግሎች መሶበ ወርቆችና ሰፌዶች የልዩ ልዩ ቅመማ ቅመም ቅላቅሎች የጥራ ጥሬ፥ የልብስ የጠላ ጋኖች ማከማቻ ነው። በስተግራ የሚታየው በር ክፍል ደግሞ ለጊዜው

የማይሰራባቸው የሻለቃ የግብርና እቃዎች - ሞፈር ቀንበር ድግር እርፍ መርገጥ ወገል ማነቆ ጅራፍ ቅትርት ማረሻ የሚቀመጡበት ነው።

ከእልፍኙ ለጥቆ የሚታየው ቤት ሰቀላው ነው። ከዳኑ እንደልፍኝ ከዳን ኮራ ያለ ሳይሆን ረዘም ብሎ የደራ ነው። ስራው ቢሆን እንደ ሌሎቹ ቤቶች ከተላላፊ እንጨት ከመቃና ከሰንበሌጥ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ጋገራንና እንኩሮን የመሰለ እውስጡ ስለሚሰራ እሳት እንዲከላከል ተብሎ ግድግዳው የግንብ ነው። ተሳክተው ከተያዙ ድንጋዮች ተገንብቶ በመረሬ ጭቃ ተገርፎ ተተኩሷል። ሁለት በሮችና አልፎም አልፎም ፎካዎች አሉት። መዝጊያዎቹ እንደ እልፍኙ መዝጊያ ሰፋፊ ከሆነ ከዋንዛ ጥርብ ተቀናጅተው በሦስት በሦስት አግዳሚ ፍልጦች የተወተሩ ናቸው። አልተጋጠሙበትም ቦታ አንዳንድ የመቃ ሳጋዎች አሏቸው። ጣራውን ደግፈው የያዙ አምስት ምሰሶዎች አልፎ አልፎ ቆመዋል። እያንዳንዳቸው ሦስት አራት ባላዎች አሏቸው፣ በባላ ባላዎቹም ላይ የሳጠራ ወንበሮችና ገበታዎች ተሰቅለዋል።

የግንቡን ዙሪያ ጥግ ጥጉን ሰፋፊ መደቦች ተመድበውበታል። ባንድ መአዘን ምድጃ ይገኛል። ከምድጃው በላይ እጣሪያው አጠገብ ለዘር የሚሆኑ ባር ማሽላ፣ ማሽላ፣ ከነፍንዳቸውና ከነአገዳቸው ተሰቅለዋል። የገብስ ብቅል ዳቦዎች ጭስ እንዲጠግቡ ተብሎ ግድግዳውን እየተንተራሱ ተንጠልጥለዋል። አብዛኞቹ ከተጐነፉበት ቅጠል ከወጡ የሰነበቱ አይመስሉም። በምድጃው ትይዩ በሌላውም በዓዘን ትልልቅ የጥራጥሬ ድብኝቶች ተደርድረዋል። እየግንቡ አናት ላይ ደግሞ የበታች የበሬ እቃዎች ተሰልፈዋል።

ከዋናው በር ሲገቡ በስተቀኝ የጋማ ከብት ማሰሪያ ነው ሁለት ፈረሶችና አንድ በቅሎ ቆመዋል። በበሩ በስተ ግራ በቅርብ ጊዜ የተኮላሹ የፍየልና የበግ ሙክቶች ታስረዋል። ገና የያሽከሩን ጉርሻ እንጂ የእመቤቲቱን አለመዱም። ሰውነታቸውም መጥበቅ አልጀመረም። በቤቱ ዙሪያ ደግሞ በሁለት በሁለት ባላዎች መካከል የተቀመጡ አስር የሚሆኑ የንብ ቀፎዎች ተሰቅልዋል። እየስራቸውም የሚተናኮላቸው ጉንዳህን መከላከያ የሚሆን አልፎ አልፎ አመድ ፈሷል።

ከእልፍኙ በሰቀላው ሌላ እንደ ጐጆና ሁለት አነስ አነስ ያሉ ሰቀላዎች አሉ። ሰቀላዎቹ ከዳን ይኑራቸው እንጂ ግርግዳቸው ፍርግርግ ብቻ ነው። አንደኛው ለወላድ በጐችና ፍየሎች ከሆነ ግልገሎቻቸው ማጐሪያ ነው። ተኩላውና ቀበሮው ኃይለኛ ስለሆነ እያነገታቸው እንዳይሄድ እረኞቹም ጭምር የሚተኙት እዚሁ ነው። ሻል ያለውን ጥጋት መርጠው አራት እንጨቶች በአራት መዓዘን ይተከላሉ። ባለባላዎች ናቸው። አለፍ አለፍ እያሉም በምሣር ፈልፈል ፈልፈል ከተደረጉ በኋላ መለሎ መለሎ

እንጨቶች በቁመት ይዘረጉባቸዋል። በላያቸውም ድርቆሽ ሣር ይጐዘጐዝባቸዋል በሣሩ ላይ ቢገኝ ቁርበት መሳይ ባይገኝ አጐዛ ጣል ይደረጋል። ስሙ ቆጥ ይባላል - አልጋ መሆኑ ነው። ከሽማግሌዎች ገበሬዎችና ከሴት አገልጋዮች በስተቀር የሚተኙት በእንደዚህ ዓይነት ነው። ሁለተኛው ሰቀላ በማይታከት ጉልበታቸው የሁለት ጥንድ በሮች ማሠሪያ ነው። ለብቻቸው ጨው ይልሳሉ የማታ ራት ይታጨድላቸዋል። ለየብቻቸው ጋጥ አላቸው። እርዳኝ የኔ ነህ ስምቡልጥ ይባላሉ። እዚሁ ሰቀላ ውስጥ በሌላው በኩል ደግሞ አራት ወደል አህዮችና አንድ በቅርቡ የወለደች በድምሩ ስድስት አህዮች ታሥረዋል። ከውድማ ወደየጐተራውና ከዚያም ወደ ገበያ አንዳንዴም ዝክር ለማዝከር ሲያስቡ የውሃ ወፍጮ ወደያለበት እህል ለማስፈጨት ይጫንባቸዋል።

ጐጆይቱ ይገበሬዎቹ አለቃ ባለዋሽንቱ የወርዶፋ ናት። አነስ ትበል እንጂ፥ እንደ ዋናው ቤተ ንጉሥ መሰል ሆና ነው። የተሠራችው - ግማሽ በግማሽ በነጭ በሐና በመረሬ ተቀብታለች። ጀርባዋን ለበረቱ ሰጥታ በሯን በምሥራቅ ትይዩ አድርጋ ስለተሠራች የጧት ፀሐይ አይለያትም - ጣፋጭ አየርም ታገኛለች። በሩ ወደ በረቱ እንደሆነው እንደዋናው እልፍኝ በበረቱ ፍግ፥ ይልቅ ይችን ጐጆ ታዘወትራለች።

በተረፈ ዙሪያ አጥር ግቢውን የሸምበቆ ሪቅና ጐተራ ተረጥርጠውበታል። ንቅስ ብለው የተጓሱ ደረባቸውን ተሸክመው ከሩቁ ሲያይዋቸው እንዲያው ጐጆዎች ነው የሚመስሉት፣ ነጭ ጤፍ ጥቁር ማሽላ ባቄላ አተር ሽምብራ ምስር ደንጐሎ የሚኖሩባቸው እንደ ዘንጋዳና ጨረቂት ዓይነቶቹ መከተቻቸው ከሌላ ዘንድ ነው ከጉድጓድ ውስጥ ካጥር ውጭ ስፋቱ ሦስት ክንድ ርዝማኔው ስምንት በሚሆን ጉድጓድ - ተሸክመው - ይህን ከዙሪያው አካባቢያቸው ስለሚያመሳስላቸው በተለይ እማሳ ውስጥ የሆነ እንደሆነ የተጐደጐዱት የቤት ሰዎች ካልሆኑ በስተቀር ውጭዎች ሊያገኟቸው አይችሉም፤ አይሰረቁም። አንዳንዴ አድብተው ቦታውን ተከታትለው የሚደርሱበት ሌቦች ቢኖሩም ጉድጓዱን ከፍተው ሊያወጡ ሲታገሉ እዚያው ተንጨፍርረው ነው የሚገኙት። ጉርጓድ ከፍተው የታመቀው አየር እስኪወጣ ሰዓት ስለሚያስፈልገው ያገሬው ሰዎች እሰርቃለሁ ብሎ ሌባ ቢመጣ መጋኛ ያደርቀዋል፣ እያሉ በድፍረት ይናገራሉ። አንዳንዴ ደግሞ ሽፍቶች ሰው እየገደሉ ጉድጓዱን የእህል ሳይሆን የሬሳ ማጠራቀሚያ ያደርጉታል። ምናልባትም ካንድ ሠፈር ሰው እየጠፋ ካስቸገረ በሠፈሩ የሚገኙትን ጉድጓዶች አስከፍቶ መመርመር አስፈላጊ ይሆናል። ይህ እንደሆን መጠባበቅ የባለርስቱ ተግባር ነው።

የወይዘሮ አሰጋሽ አጥር ግቢ በስተ መካከል ከሚገኘው ለቀንድ ከብቶች ማጐሪያ ከሚጠቀሙበት በረት ጋር በእንዲህ የሚሠራበት ሲሆን በስተውጪ ወደ ጀርባው በኩል ሲል ደግሞ ያርባማሽላ እሸት ተዘናፍሎ የሚታይበት ነው።

# ፮

# አደፍርስ

ዳኞቹ እነ አቶ ጥሶ ከዚያ በፊት በነበረው ክረምት ያልተሰየሙ አዳዲስ ሰዎች ከመሆናቸው በስተቀር የተለመደ የያመቱን ግዳጅ ለመፈጸም ነበር የመጡት። ይግባኝ ባይ ነገረተኛ አዲስ አበባ ድረስ እየወጣ እንዳይንገላታ ታስቦ፥ በያመቱ በክረምት ወራት ዳኞች እያውራጃው እየተላኩለት ለብዙ ዓመታት ሲጐተቱ የነበሩ ጉዳዮችን እንዲቆርጡ በታቀደው መሠረት ወይዘሮ አሰጋሽም የሚመጡትን ዳኞች ሁሉ በመጋበዝ የተለመደ ተግባራቸውን ነበር የሚፈጽሙት። ወንድማቸው አቶ ወልዱ፥ ደብረ ሲና አስቀድመው ተዋውቀው ጓዝ ላለው የሚከራይ ጥሩ ቤት በመጠቀም ጓዝ ለሌለው ከራሳቸው ቤት አንድ ወይም ሁለት ክፍል ለቀው በነፃ በማስተናገድ የታወቁ ስለ ነበሩ ወይዘሮ፥ አሰጋሽ ዳኞቹን ግብዣ ለመጥራት አዳግቷቸውም አያውቅ።

አቶ ጥሶ ወደ ደብረ ሲና የመጡት ከነጓዛቸው ነበር። - ፍሬዋን ሴት ልጃቸውን - ወይዘሮ አካላት፥ ታላቅ እኅታቸውን ካደፍርስ ከልጃቸው ካጣሁ፥ ወሮታ ከገረዳቸውና ከሠዓሊ ጓደኛው ከክብረት ጋር አስከትለዋል። የሕግ ሚስታቸው የፍሬዋ እናት ከሞቱባቸው በኋላ ሌላ ሴት ሳያገቡ ከልጃቸው ጋር በብቸኝነት ይኖራሉ። ቁመተ አጭር ጥግትግት ያለ ፊት ሽካራ ናቸው። በረጅሙ ወደ ላይ የተጨፈቀ ጥቁር ጸጉርና በፈሰሰ ስሜት ዓይነት ከከባድ ሽፍሽፍታም አጐበር ሥር የሚፈልቁ ጥቋቁር ዓይኖች አሏቸው። በድምፃቸውም ሆነ በፊታቸው እንቅስቃሴ በሰውነታቸው ውስጥ የሚላወሰውን የስሜት ወይም ያስተያየት ለውጥ ለመተንበይ አይቻልም። ማንኛውም ሁኔታቸው የተመሳሰለና የማይለዋወጥ ባሕርይ ይታይበታል። - ፍሬዋን ልጃቸውን አቀማጥለው እንደ ያዟት ያስታውቃል።

ፍሬዋ ቅብጥብጥ ያለች ያሥራ ሰባት ዓመት ወጣት ናት። እወምበሯ ላይ መቁነጥነጥ ትናንሽ ትከሻዎቿን እንደመቂናጥ ላይና ታች ማንሣት መድፋት እስኪ እንሳቅ ሳቅ መሳቅ ዓይኖቿን አንዳንዴ በማጨንቆር አንዳንዴ በኀይል በማጉረጥ - ቀዝቀዝ ባለ በሚዳስስ አስተያየት እየመራች ሰውን ማደናገር ትወዳለች። እቀኝ ዓይኗ

ላይ ጠብ የማይል ሁለዚያዊ እንባ ተቋጥሮ ስለሚታይባት ያዩዋት ሁሉ የሚፍለቀለቅ የመንፈስ ግንፈላ ምልክት ይመስላቸዋል። አቋቋሟ መለል ብሎ የወጣ ቢሆንም ወገቧን ሁሌ በቆዳ ክርንት አድርጋ ስለምታስረው እስክትጠግብ በልታም አታውቅ አትመስል። - የፈረንጅ ሙዚቃ የሚኮረኩራት ‹አልጠላሽም ከቶ› የሚያስቃት ‹እችክ እችክ› የሚያዛት - ብርሃን የሳት እራት እንደሚስብ ያገኘችውን ወጣት ሁሉ የመሳብ ችሎታ ያላት ነች። እዚህ በራሷ አነጋገር ‹ጭጋግና ደመና ዝናብና ጭቃ እማይጠፉበት አገር› ስትመጣ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነው። እምብዛም አልወደደችውም። በተለይ ደግሞ የሚያበሳጫት አማላጅ ሁኝን እያለ ደጅ የሚጠናው ሰው፥ ብዛት ነበር። ግማሹ እንጨት ተሸክሞ በስልቻ ጤፍ ጭኖ ግማሹ ቅቤ ግማሹ ሙዝ ባገልግል ይዞ ግማሹ ሙክት ነድቶ ከሰል ጭኖ አርፈውበት ወደነበረው ቤት የሚጐርፈው ሰው ትንሽ አልነበረም። እሷ ግን፥ በመተያያ ስም የሚመጣ ማንኛውም ነገር እንዳትቀበል ከአባቷ ቋሚ ትእዛዝ ተሰጥቷት ስለ ነበረ ‹ፖሊስ ሳላጠራ ብትሄዱ ይሻላል› እያለች በማስፈራራት ታባርራቸው ነበር። በዚህ ነገር ልባቸው አይጠናም ምንም እንኳ ሲቀበሉ ያያቸው ሰው ባይኖርም የተቻላቸውን ያህል ረድተውኛል ..... እንደ ወንድምየው ጠናካራነት በጎትዮዋ ርዳታ ባይሆን ኖሮ አምስት ዓመት እከናነብ ነበር የሚለው አመስጋኛቸው ብዙ ነበር።

ወይዘሮ አካላት በዘመናቸው ብዙ ጀግናና መኳንንት ያስረገዱ ናቸው። አምስት ጊዜ አግብተዋል። ከአምስቱም የተለያዩ ባሎቻቸው አንዳንድ ልጅ ወልደዋል። አምስቱም ባሎቻቸው በሕይወት የሉም ሞተዋል። ነገር ግን የተቻላቸው ሀብታሞች ስለ ነበሩ ልጆቻቸው በሀብቱ ይንቀባረሩበታል። ‹ባል መምረጥ እንደ ወይዘሮ አካላት ነው› የማይላቸው ሰው አልነበረም። ስለ ፍቅር ሲነሳ ብዙ ማውራት አልፈልጉም። ስለ ባል ሲነሣ ግን አሁንም ቢሆን ራሱን የቻለ ባል ካገኙሁ ባይ ናቸው እድሜያቸው ከኀምሳ በላይ ነው። ለባልነት የሚፈልጉት ሰው ግን ከስድሳ ዓመት በላይ መሆን አለበት ባይ ናቸው። ‹የምን አጣብቂኝ ለባሽ ጐረምሳ የምን ቤተ ክርስቲያን የማይስም ጾም የማይጾም የእንጨት ሽበት - ምራቁን የዋጠ - ራሱን የቻለ፥ ሰው - ላደባባይ የሚሆነኝ ነው የምፈልገው› ይላሉ በገሃድ ሲያወሩ። ማዕረግ ያለው ወይስ የሌለው ባል እንደሆነ የሚፈልጉት ሲጠየቁ፥ መልሳቸው - ‹ማዕረግ ሀብት ነው ማዕረግ፥ የሚፈልጉት ነው› ነው። አማራ ጉራጌ፥ ወላሞ ጋላ፥ ትግሬ፥ አዳል ቢሆን ግዴላቸውም ..... ‹በአርአያ ሥላሴ ነው የተፈጠርነው፤ ሁሉም እኩል ነው፤ ሁሉም አንድ ነው፤ ዋናው ነገር መግባባት ብቻ ነውይላሉ እንደ ፈሊጥ አርገውት፥ - ስለዚህ የማይወዷቸው አንዳንድ ሴቶች ‹ባል አይመርጤ› የሚል ቅጽል አውጥተውላቸዋል። - ያም ሆነ ይህ ብቻቸውን ካሥር ዓመት በላይ ሊሆናቸው ነው፤ የባል ነገር አልተሳካላቸውም። -

እንዲያውም አንዳንዴ በግድ ላግባ ባይ እምቢ ሲባል ‹ባል ገፊ› ነች ..... ባሎቿን ሁሉ ገፍታለች እያለ ስለሚያስወራባቸው..... ‹እስከምንጊዜም ባል አያሻ› የሚለውን ፈሊጥ ማዘውተር ጀምረዋል እያደር -

አምስቱም ባሎቻቸው የሚታይዋቸው እንደ ሕልም ነው። የከሊትን አባት ወድጄው ነበር ለከሌ አባ ታብጀለት ነበር፥ ከማለት በስተቀር ስለሁኔታው ስላቋቋሙ ስለጠባዩ፥ ሲጠየቁ ምንም የሚመልሱት ነገር አልነበራቸውም - ‹ረስቸዋለሁ አሄሄ ከየቴ!› ከማለት በስተቀር። - ሁሉም ባሎቻቸው ጋር የነበራቸው ፍቅር ጊዜያዊ ነበር፤ ለትዝታ ያህል እንኳ ያልቀራቸው። ከወይዘሮ አከላት ይልቅ አቶ ጥሶ ይሻሉ ነበር ስለ እኅታቸው ባሎች በማስታወስ። ሆኖም ታዲያ ወይዘሮ አከላት ዛሬም እንኳቢሆን ድንገት ደስ የሚላቸው ነገር አግኝተው በስሜት የተፍለቀለቁ እንደሆነ ለዚያው አብረው ለቆዩበት ጊዜ ባሎቻቸውን ያስደስቱ እንደነበሩ ለመረዳት ይቻላል።

ልጆቻቸው በሳቸው ቁጥጥር ሥር በነበሩበት ጊዜ፥ ከየባሎቻቸው ቀላድ፥ የሚቀመጡት ጭሰኞችና ደጅ፥ ጠኝዎች ብዙ ስለነበሩ አጀቡ አዲስ አበባ ሚካኤል ያለውን መኖሪያ ቤታቸውን ግብ እንደሞላው ነበር። ወጣ ባሉ ቁጥር መሬት የሚለሸለሸው ሰው ብዛት እግራቸውን ለመሳም የሚጣደፈው ወጣትና ኮረዳ፥ ብዛት እፊታቸው የሚያረግደው የሚርበተበተው ብዙ ነበር። እያደር ግን ልጆቻቸው ለአቅመ አዳምና ሔዋን እየደረሱ ራሳቸውን ሲችሉ የያባታቸውን ሀብት እየተካፈሉ በመሄዳቸው ያ ሁሉ መከበርና ማርበድበድ ቀረባቸው። ስለዚህ አንዳንዴ የዱሮው ትዝ ሲላቸው በወንድማቸው በአቶ ጥሶ፥ ሥር እንዲከበሩ አብረዋቸው ይሄዳሉ። አማልዱኝም የሚሉ ሰዎች ቢሆኑ ከበብ ከበብ ማድረጋቸውን ስለሚወዱትና የዱሮው የተመለሰ ስለሚመስላቸው የነገረተኞቹን ጉዳይ በማዳመጥና ምክር፥ በመስጠት አንዳንዴም ምሳም ጠላም በመጋበዝ ከባለጉዳዮች ጋር ሲወዳጁ ይታያሉ።

አደርስ ልጃቸው፥ ቢሆን ብዙ ከሳቸው የሚገጥም ምግባር አይታይበትም። - ቢሆንም ግን፥ እንደ እናቱ ሰው ከበብ ከበብ ሲያደርገው የሚናገረውን ሲያደንቅለት ይወዳል። - ጠይም ነው ፊተ ሰልካካ። - ቀጭን ቁመተ ለግላጋ። - ሀያ አራተኛ ዓመቱን ይዟል፥ ከተወለደ።

በአብዛኛው አፋዊ ድርጊቱ ግዴለሽ መሳይ ነው። - ጸጉሩመላ የለው ሲያሰኘው ባጭሩ ያስቆርጠዋል - ሲያሰኘው ያስጐፍረዋል - ሲያሰኘው ደሞ ጨርሶ ተላጭቶ ኮፍያ መሳይ እልጩ ላይ ጣል አርጐ ብቅ ይላል። - አለባበሱ መላ የለው አንዳንዴ ሸሚዝና ቁምጣ አንዳንዴ ካናቴራና ጃኬትና ቦላሌ አንዳንዴ ሱፍ ኮትና ካኪ ሱሪ አንዳንዴ ደግሞ አጊጦ የወጣ ለት ኮቱ አንድ ዓይነት ሱሪው ሌላ ዓይነት የሆነ ሱፍ

ልብስ - መላ የሌለው። - አረማመዱ መላ የሌለው ወይ ጐንበስ ጐንበስ፥ ወይ ሱክሱክታ ወይ ለማያጣድፈው መጣደፍ.... አደፍርስ ከተማ አደግ ነው፤ ከአዲስ አበባ ወጥቶ የማያውቅ። - ዘንድሮም እንኳ ቢሆን ላንድ፥ ዓመት ዩንቨርስቲ አገልግሎት ምድቡ ደብረ ሲና ስለ ነበረ ቀድሞ፥ በመሄድ ከዘመድ ጋር ሆኖ አገሩን ለመለማመድ ሲል ነበር አብሯቸው የመጣው። -

«ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት፥ መፈራት የለባቸውም» የሚሉ የአነጋገር ፈሊጥ አለው። ጊዜያዊ ሁኔታ ያስመለከተውን ከማድረግ አይቦዝንም። ስለ ውጤቱ እምብዛም ሳያስብ.... በዚያ ላይ የመታየት የመታወቅ ፍላጐቱ ሰው ወደተሰበሰበበት ቦታ ስለሚገፋፋው ባነጋገርና ባሳብ አቀራረብ ዘዴው ለሁል ጊዜ የተዘጋጀ ነው። - እንደ ልቡ ይናገራል። - አንዳንዴ በሐሳብ አለመግባባት የተነሣ፥ ካድማጮቹ ጋር የሚጋጭበትም ጊዜ አለ። - በተለይ ስለ ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ ጥሩነት ወይም መጥፎነት ክርክር የተነሣ እንደሁ ለምሳሌ። - ደሙ እየፈላ ሰውነቱ እየተለዋወጠ ነው የሚናገረው። ስለ ጥሩነቱና ስላስፈላጊነቱ። - እንዲያም ሆኖ ታዲያ ተቃዋሚዎቹ ራስ ጸጉር ናቸው። - በየጊዜው የሚደጋገመው የተማሪዎች ሰላማዊ ሠልፍ ከጥቅሙ ጉዳቱ የተሰማቸው -

# ፯

## አደፍርስ

ደብረ ሲና ከሰነበቱ በኋላ አደፍርስ አጐቱ ወደሚያስችሉበት ፍርድ ቤት እየሄደ ከየነገረተኞቹ ጋር መወያየት ይጀምራል። - ነገረተኞቹም የዋናው ዳኛ የእኅት ልጅ መሆኑን እየሰሙ ቀስ በቀስ ይጠጉታል። - ከበብ ከበብ ያደርጉታል። ጉዳያቸውንም ያማክሩታል። እስካመጣው ድረስ የዩንቨርስቲ ትምህርቱን። - ከወር በላይ የያቤት ባውን የተመሳሰለ የተወሳሰበና የማይበጠስ የነገር ውጣ ውረድ ያዳምጣል። - እየሰለቸውና እያናደደውም ይሄዳል፥ እያንዳንዱ ሰው ንትርክ። - ለሁሉም የሚበጅ ምክር ለመስጠት ያቅዳል። - አንድ ቀን ቀደም ብሎ ፍርድ ቤት ይሻገርና እነገረተኞቹ መካከል ገብቶ በጠቅላላውና፥ በመሠረቱ የተሳሳቱትን ማድረግም የሚገባቸውን ለወደፊቱ እያብራራ ይጀምራል -

«.....የምትሉት ሁሉ ይገባኛል.... ነገር ግን እንዲህ ያለው ችግራችን ሊወገድ የሚችለው አንድ ሙግት ሁለት ሙግት በመርታት አይደለም። ዛሬ አንተ ሚስትህን

ረትተሃት ወይም እሷ ረትታህ ብትገባ ዋጋ የለውም፤ ሌሎች ደግሞ እንደ እናንተ ተፋትተው ይመጣሉ፤ የፍርድ ቤቱን ግቢ ይሞሉታል - ስለዚህ በመሠረቱ አንድን ነገር ከምንጩ መመርመር ይኖርብናል - መጀመሪያ ውሃን ከምንጩ ነገርን ከሥሩ እንደሚባለው -

«ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ የሚባለው» ያርሙታል -

«..... አዎን፥ እንደሱ እንደሚባለው..... እስኪ ለመነሻ ያህል የቤተሰብን አቋም ያፋለሱትን አንዳንድ መሠረታዊኢ ጥያቄዎች እንጠይቅ - አንደኛ..... በከተማና በገጠር ሽርሙጦች ለምን በዙ......?

«ቀላል ኑሮ ስላገኙ ነዋ?» ይለዋል ነገረተኛ አደፍርስ ነገሩን ሳይጨርስ

«.....አይደለም! አይደለም! መልሱ እሱ አይደለም..... መልሱን በኋላ እንሰጣለን - እንዴትስ ለመቀነስ ይቻላል? ሁለተኛው ጥያቄ.....

«ወደያገራቸው በመመለስ..... ሥራ ቤት በማቋቋም» ይለዋል አንድ ሌላ ነገረተኛ

.....ለመልሱ አትጣደፉ መልሱን እኔ እሰጣችኋለሁ አትቸኩሉ - የሽማግሌና የአሮጊት ፊት ለምን እየበዛ ይሄዳል? ሦስተኛ ጥያቄ.....

«ሳይጣጣሙ እየቀሩ!» በዝግታ ነገረተኛ -

«የወንዱም ወይም የሴቷ የዝሙት ፍላጐት ባለመብረዱ» በዝግታ ሌላ ነገረተኛ -

«ሴቱም ወንዱ ወጣት እየፈለጉ» በዝግታ ሌላ ነገረተኛ -

«.....የወጣቶቹስ የጋብቻን ፍራቻ በምን ምክንያት ሊፈጠር ቻለ? አራተኛ ጥያቄ.....

«ልቡ አላቅሙ እየተመኘ.....» አንዱ ነገረተኛ በለኆሳስ -

«የቤተ ሰብን ኀላፊነት የሚችል ልብ ስለሌለው!» ሌላው -

«የምንተኛ ሺ ሐሞቱ የፈሰሰ ትውልድ ስለሆነ» ሌላው -

......እንዴትስ ለማሻሻል ይቻላል! አምስተኛ ጥያቄ.....

«ላንድዬ በመጠለይ....

«የሃይማኖት ትምህርት በማስተማር....

«ሽማግሌዎቹ መልካም አርአያ በማሳየት......» ይመልሳሉ ነገረተኞች ለየራሳቸው -

.....አብዛኛው ሰው ለምን ውቃቢ የራቀው ሆነ? ስድስተኛ ጥያቄ -

«ተንኮለኛና ራሱን ወዳድ ስለሆነ.....» በአርምሞ ይመልሳሉ ነገረተኞች

.....እንዴትስ ራሱን ዐውቆ የተሻለ ኑሮ ለመኖር ይችላሉ? መጨረሻ ጥያቄ -

«ምን ይላል?» ይጠይቃል አንዱ ነገረኛ ጕላ ባለ አንደበት -

«ደሞ ራሱን የማያቅ አለ ሊል ነው» ይለጥቃል ሌላው -

«አቅሙን ዐውቆ በመኖር» ይመልሳል ሌላው -

......እንግዲህ እስኪ አንድ ባንድ ለመተንተን እንሞክር.....ለመተንተን እንድንችል፥ ከልቡስ ጥላ እንጀራለን.....

«ከጉድፍ ሴጣን! ምን ማለቱ ነው?» በመገረም ይጮሃል አንዱ -

.......ልቡሰ፥ ጥላ የምለው ከአእምሮ ክፍሎች በአነስተኛው ውስጥ የሚገኝ ልዩ ልዩ ነገሮች ማየትና..... ማውጠንጠን ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ የሚጠራቀም..... መያዣ መጨበጫ የሌለው የሚመስል ምስቅልቅል ሁኔታ ነው። - ከቤተ ሰቦቻችን ይወረሳል። ከልዩ ልዩ መጻሕፍት ይዘራል.....

«መጣፍማ ብንማር መቼ እንዲህ የማንም መጫወቻ እንሆን ነበር?» በለኆሳስ ይጀምራል አንዱ ነገረተኛ -

.....ከልዩ ልዩ ተረቶች፥ ሃይማኖት ነክ ከሆኑ ድርጊቶችና አዋልድ መጻሕፍት ይቃረማል.....

«ዱሮም ሃይማኖትና መጣፍ አጥፊና ጠፊ ናቸው» ይለጥቃል ሌላው -

«......ከየዕለታዊ ተግባራችን ከሚጠቅመንም ሆነ ከማይጠቅመን ከመልካሙም ሆነ ከመጥፎው ለዓይናችን ከሚያስደስተንም ሆነ ከሚያስጠላን ሁሉ ወደ አእምሯችን እየገባ ይጠራቀማል.....

«አንድ ዓይንህ ብታስትህ አውጥተህ ጣላት አዶለም መጣፉስ የሚለው» ያውጠነጥናል አንዱ ነገረኛ -

«ባምሮው ያስበም እንደ ሠራ ያህል ነው.....» ይለጥቃል ሌላው። -

.....ብዙ ጊዜ እንዴት እንደ ተጠራቀመ ለማወቅ ያዳግተናል.....

«ምንሳ! ሰው ብሎ ፍጡር.....

......መጠራቀሙን ግን፥ ሌሊት በሕልማችን ቀን በሥራ ፈትነታችን መከታነት እየመጣ ሲያስቸግረን ለመረዳት እንችላለን.....

«ርግጥ ሥራ መፍታትስ ሤጣን ያስከትላል.....

«ቀድሞ ማደሮው መቼ አሳርፎ ቢሳካም ባይሳካም ቆላ፥ ደጋ መሮጥ ነዉ.....

.....አእምሯችን ጮርቃ በነበረበት ጊዜ ቤተ ሰቦቻችን ያደነቁትን በማድነቅ ያከበሩትን በማክበር ያመሰገኑትን በማመስገን ይዘራል....

«መቼም ዘር መዝራት ለፍሬ ነውና እንዲያፈራ ማረምና መጠበቅ ያስፈልጋል.....

.....የጠሉትን በመጥላት የነቀፉትን በመንቀፍ ያንጓለሉትን በማንጓለል ያለመልማል። በነሱ እምነት የኛ እምነት በነሱ፥ ትዕግሥት የኛ ትዕግሥት በነሱ ቸርነት የኛ ቸርነት ያብባል። አንዳንድ የሚያስፈልጉ ነገሮች አብረው ቢያድጉም እንኳ እንደ ቤተ ሰቦቻችን መታረም የኛም እየታረሙ ይሄዳሉ.....

«እዚህ ላይ በጊዜ መዝራትንና በጊዜ ማረምንም ቢጨምሩ አይከፉ....ምክንያቱም አለጊዜው.....አሁን ለምሳሌ የኔ ባለቤት የከሰሰችኝ.....

.....ቆይ ቆይ፥ አላስጨረስከኝምኮ? እና የኛም ይታረማል ፍሬነት ይደርሳል። በቤተ ሰብ ዓይን ጀግና ሠራተኛ ቆንጆ ባለ ሞያ፥ የተማረች የምትባል ሚስት በልጅም ዓይን እንደዚኢሁ የተመሳሰለ ሚዛን ይዛ ታድጋለች። የልጅ አእምሮ፥ በቤተ ሰቡ አእምሮ ትይዩና መሰልነት ይበለጽጋል.....

«የዛሬ ልጅ መቼ በጄ ብሎ በናት አባቱ እግር ይተካና.....» ይላሉ ከእድሜያቸው ገፋ ያሉ አዛውንት።

......በተጨማሪ፥ ሽማግሌዎችና መጻሕፍት ዐዋቆች ከሚናገሯቸው ተረቶችና ልዩ ልዩ ታሪኮች የሶምሶንና የደሊና ታሪክ፥ የቅዱስ ጊዮርጊስ የብሩታዊትና የዘንዶው አዋልድ......

«ብሩታዊትን ከዘንዶ አፍ ያወጣው አምላክ ያውቃል» ይላል በግረ ሙቅ የታሠረው እሥረኛ።

......ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ ሁሉ በአእምሮው ውስጥ ይቀረጹበታል.......

«ርግጥ ነው ልብ ላረገው.....» ይላሉ አንድ ጠና ያሉ ሴትዮ

......ቀስ በቀስም በአእምሮው ውስጥ እንደሚመላለሰው ጀግና ለመሆን በአእምሮው ውስጥ ዝናዋን እንደሚያስተጋባው ሴት ዓይነት ለማግኘት ይፈልጋል። ይህ እንግዲህ የሚሆነው ጊዜውና ሁኔታው ያልተለዋወጠ እንደሆን ነው..... በታሪክ ከተያያዘ ዘመን ከእናት ካባት ቀዬ ሳይወጡ የቆዩ እንደሆነ ነው.....

«የናት ያባትን ቀዬ የሚያህል የለም! የስንቱ ዘመዶቻችን አጥንታቸው የተከሰከሰበት ደማቸው የፈሰሰበት.....ለዚሁ ብዬ ነው እኔም ሽንጤን ገትሬ በየፍርድ ቤቱ የምዞረው የዘር መቁጠሪያዬን ያባቴን እርስት አላስወስድም በማለት......እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ያድርጋቸውና ያንተ አጐት ካዩት ዘንዳ ብርረታም ብረታ ተደስቼ ነው አገሬ የምገባው - እየፎከርሁ! እየሸለልሁ! ዳኛ አይቻለሁ እሳቸው ዘንድ የሚደርስ የለም! ያ የሚያስገመግም ድምፃቸው ፍርድ ለመስጠት ሲምቦለቦል፥ እግዚአብሔር እንጂ ሰው የተናገረ አይመስልም። ረጂም ዕድሜ ይስጣቸው!

«ስማ ስማ አደፍርስ - አላየኸኝም መሰለኝ ሳዳምጥህ ነበርኮ.....

......በላይ! አላየሁህም፤ ምን እባክህ በሙሉ በምናገረው ተውጬ ዓይኔ ከሰው ሰው ይለፍ እንጂ አረጋግጦ አይመለከትም። - እህሳ፥ ምን ይመስልሃል፤ ይኸ የምተነትንላቸው ያኗኗር ዘዴ? ችግሩን ከሥሩ የመታሁት አይመስልህም? ብዙዎቹ የተከታተሉት ይመስለኛል፤ በተለይ ባስተያየታቸውና ባለመንቀሳቀሳቸው ስመለከተው። - አንዳንዶቹ ግን ይገርምሃል - ጭራሽ የምለውን ፈጽሞ አይሰሙኝም፤ ደንቆሮ ናቸው ወይም አይገባቸውም - እኔ ስለ ግብርና ሳወራ እነሱ የሚያወሩት ስለብሩታይት ነው.....

«ምን አለፋህ ብቻ ላቦትህን ነው የጨረስከው። - እነሱ አፍ አፍክን የሚያዩት፥ ለምትናገረው ነገር ጓጉተው ሳይሆን ከሙቼ የሚናገረውን ጨርሶ ከሙቼ ብሶታችንን አጫውተነው አማልዶን ብለው ሲጠባበቁ ነው። ከተናገርከው እንኳን ለነሱ ለኔም ብዙ፥ ያልገባኝ ነገር አለ...... እምልህ፥ ባንተ አስተያየት ይኸ ልቡሰ ጥላ የምትለው ነገር ከኖሩበት ቀዬ ካልለቀቁ በስተቀር መጻሕፍት በማንበብ ሌሎች አገሮችን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ሐሳብ ለሐሳብ በመለዋወጥ እያደገና አስተያየትን እየለወጠው አይሄድም ነው የምትለው......? አይመስለኝም፤ በኔ አስተያየት በእንደዚህ ዓይነት መንገድ የሚያድገው ልቡሰ ጥላ አለቅጥ ይመጥቅና በዚህ ዓለም ተመሳሳይ ስለማይኖረው ሰውዬውን ወይም ሴትዮይቱን አቻ አሳጥቶ በብስጭት ያኖራቸዋል ነው የምለው.......

በነገራችን ላይ ጋሼ ክብረት ይፈልግሃል፤ አንተንና እኔን ሊሥለን ይፈልጋል፥ ከፍሬዋ ጋር.... ይፈልጋል

«ጥሩ ነው እንሂድ» ዙሪያውን ወደ ነገረተኞቹ አየት በማድረግ «.....በሉ እንግዲህ እግዚአብሔር ይቅናችሁ፤ ሐሳቤን ባልጨርስላችሁም ዋና ዋናውን ጐረፍ ጐረፍ አድርጌላችኋለሁ..... ደህና ሁኑ.....

«ትንሽ ጉዳይ ነበረኝ ጌታዬ፥ የሚያቻኩል፤ እዚህ ከኛ ጋር ያጠፉትን ጊዜ ሩቡን እንኳ አልወስድብዎትም.....ቁም ነገር ነው ብዬ ነው ጌታዬ የማስቸግርዎት.....» ይለዋል አንዱ ነገረተኛ ከተል ይልና

«አዬ፥ አሁን ጊዜ የለኝም፤ ባይሆን ነገም እዚሁ ትገኝ እንደሁ፥ ነገ ይሻላል.....

«ነገማ ቀጠሮዬ ነው ጌታዬ! ቀጠሮው ካለፈ ምን ይበጀኛል። እባክዎ ስለ እግዚአብሔር ብለው ያነጋግሩኝ..... ባለጋራዬ ሀብታም ሰው ነው፥ ደግሞ ምክንያቱን አላውቅም ይኸው ካገር ቤት ከመጣ አምስት ቀን አልፎታል፤ ርስዎ አጐት ዙሪያ ያኮበኩባል.....

«እኔ ትምህርቴ ችግርን ከሥሩ ስለ መቋቋምና መፍትሔ ስለ ማግኘት ነው፥ የኔ ወንድም...... ደግሞስ ስታስበው ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት! ለየትኛው ነገር ብለህ ትቸገራለህ?...... አዎ..... መቸገር አያሻም..... ስለዚህ ስለ ግል ጉዳይህ ብዙ አታስብ አትደንግጥለት.... እውነት ካለህ እውነቱ ያወጣሃል....

«እውነቱ! እውነቱ! እውነቱ የቱ ነው ጌታዬ? እወንቱን የሚያገኘው የቀደመ ነው.....እውነቱን የሚያገኘው ጊዜ የሰጠው ሀብት ያለው፥ አባባሉን የሚያውቅበት ነው ጌታዬ.....

«ታዲያ ጠበቃ ግዛ! እኔ እንደሆንሁ ምናልባት እንደምታውቀው ተማሪ ነኝ.....አልሆንህ፤ ወይ በገንዘብ አልረዳህ.....

«መቼስ ምን አደርጋለሁ መስሎ ካልታየዎት ካልመሰለዎት አፌን ባላጠፋ ይሻላል.....» ድንገት ዘወር ይልና በኀይል እየተራመደ ወደ ፍርድ ቤቱ ይመለሳል። - አደፍርስና በላይ ለጥቂት ጊዜ ሳይነጋገሩ መንገዳቸውን ይቀጥላሉ። -

«ቅድም የጠየቅሁህንኮ አልመለስክልኝም እንዴት ነው መጻሕፍት ስታነብና ብዙ የኑሮ ልምምድ ያላቸውን (ግብር የገቡ) ሰዎች ስትሰማ ስለብዙ ነገሮች ስታውቅ ልቡሰ ጥላህ አይለዋወጥሞይ? ለመጀመሪያ ጊዜ ባበላገር ሳለህ፥ በባላገር የነበረችህን ልብስተ ጥላ የምትመስል ልጅ ብታገባ እከተማ መጥተህ ልቡሰ ጥላህ ሲያድግ ባሮጌዋ ልብስተ

ጥላ አምሳል ያገባሃት አታሰላህሞይ? አትፈታትሞይ? ወይም እሷ በበኩሏ አትፈታህም አትጠላህሞይ......?

«በመሠረቱ መቼም እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች አስቤባቸዋለሁ። ልቡሰ ጥላ ሊያድግ ይችላል። መጀመሪያ እንደተነጋገርነው ከቤተ ሰብ ጋር አብሮ በመኖር ያድጋል። ከዚያም ሌላ፥ ተረትና ታሪኮች አዘውትሮ በመስማት መጻሕፍትን አዘውትሮ በማንበብ አዘውትሮ በማሰላሰል፥ ሊያድግ ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ተዋሕደው በሰውነቱ ካልሰረጹበት የሚያመጡበት ለውጥ አይታወቀውም.....

«በሰውነቱ መዋሐድ አለመዋሐዳቸውን እንዴት ሊያውቅ ይችላል......?

.....የልቡሰ ጥላውን ውጋጋን የሚያሳዩ ሁኔታዎች ሲገጥሙት ስሜት ሳይሰጡት በመቅረታቸው ነዋ!...... ለምሳሌ ኅሊናን የሚያነቁ ሁኔታዎችን ባህላዊ ሙዚቃን ቀረርቶና ፉከራን የመሳሰሉትን ሲሰማ ልቡሰ ጥላ ጀግናው ትዝ ካላለው የፍቅር እንጉርጉሮ ሲሰማ ልብስተ ጥላ ፍቅሩ ትዝ ካላላችው ልዩ ልዩ ሥዕሎች ላይ የነሱን ሕይወት ሲንቀሳቀስ ካልያዘው..... በውኑ እያዳጉ በህልሙ ካልመጡበት በርግጥ ተዋሕደውኛል ሊል አይችልም። በርግጥ ተዋሕደውት እንደ ሆነ ግን በየዕለቱ ለሚገጥመው ለዙሪያ አካባቢው የሚኖረው ፍቅር እየተቀነሰ ለልቡሰ ጥላው ያለው ግን እያደገ እየበለጸገ ይሄዳል። እንዲያውም አንዳንዴ ከሰዎች ተገልሎ መኖርን ይመርጣል፤ ልቡሰ ጥላው በሚያስመለክተው ልዩ ልዩ ሁኔታና ቅርጻ ቅርጽ እየተደሰተ። - ከአእምሮው የሚመነጩት እነዚህ ልዩ ልዩ ነገሮች ለልቡ ደስታ ይሰጡታል። - ዓይኑ ይበራል። የደሙ ገንዳ የስሜቱ መስኖ ወደ ልቡሰ ጥላው ይከተራል። ለሰብአዊ ፍጡር ያለው ስሜቱ በውስጡ ተውጦ ይቀራል። ልቡሰ ጥላውም በዓይን ታይቶ ልኩ ዓይነቱ ቦታ አያያዙ ወሰኑ የማይታወቅ - ሽንጥ ዳሌ ክብር ግርማ ሞገስ፥ ኅይል ገናናነት በሚል ጌጣጌጥ ይክበሰበሳል። ጥቅሙና ወሰኑ የማይገመት ይሆናል። በሰዎች ላይ ሲፈልገው ያጣዋል። ራሱ ላይ ምስቅልቅል ትርኢት ይሆንበታል። በሕልም ሩጫ እያኳተነ በማስጐምዠት ወላንሳ አስቀምጦ ከማትገኝ ሚስት አጋብቶ ከሌለ ፍቅር አፋቅሮ የማይደረስበት ክብርና ኅይል ሰጥቶ ከሚኖርበት ዓለም ውጭ የሚኖር ሰንኳላ ፍጡር ያደርገዋል። እንደዚህ ያለው ሰው ዕድሜ ልኩን ሳያገባ ይኖራል። - ከሌላው በኩል ደግሞ፥ ሌላው ዓይነት ሰው በልቡሰ ጥላው የተጠራቀመውን ምስቅልቅል ትርኢት በግዙፋዊ ሁኔታ ለመያዝ ይፈልጋል። በሩቅም መንገድ ቢሆን ልቡሰ ጥላውን የሚመስል ሰብአዊ ፍጡር ሰብአዊ ሁኔታ ለማግኘት ይሞክራል። ለኑሮ አስፈላጊ ነው ተብሎ የታመነበትን የጋብቻ ድንጋጌ በግዳጅ ሳይሆን በሙሉ ፈቃድና እምነት ይቀበላል። ከጊዜ ብዛትም አምኖበት የተቀበለው አፍአዊው

እውነታ ውስጣዊውን ምስል ያስለቅቀዋል፤ ማለት፣ ልቡሰ ጥላው የነበረው በግዙፋዊ ነገር፥ ለምሳሌ በሚስት ይለወጣል - በግዙፋዊነት የነበረው ደግሞ የማይደረስበት መስሎ በነበረው በልቡሰ ጥላው ይተካል፤ አንዱን ከሌላው መለየት ያዳግታል። ውጫዊው ውስጣዊው ውጫዊ ሆኑ ማለት ነው። ለዚህ ነው በነገራችን ላይ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ባልና ሚስት ሲሆኑ፥ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኑ ብላ የምትለፈው። እውስጡ (ልብስተ ጥላው) የነበረች እውጭ (ሚስቱ ሆና) ብትወጣም...... እውጭ የነበረችው እውስጡ ገብታለች ማለት ነው፤ አንድ አካል አንድ አምሳል.....

«እውነቱን ለመናገር የተናገርከው ሁሉ ደስ ይላል፤ ግን መቼም ትንሽ ለኔ ረቀቅ ብሎብኛል..... አዎ ርግጥ ነው ተምሪያለሁ - በመማር ላይ ነኝ፤ እምልህ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ደርሻለሁ..... ሆኖም ያልከው ሁሉ አልገባኝም..... እና አሁን ይልቅ ጋሼ ክብረት እኛ ግቢ ውስጥ ሳይጠብቀን ስለማይቀር እንግባና ሥዕሉን እንነሣ.....

## ፰

## አደፍርስ

እነበላይ ቤት ግቢ ደርሰው በሩን ከፍተው ሲገቡ አንድ ትልቅ ወሠራ አውራ ዶሮ ካጥር ላይ ወደ መሬት ዘሎ ይኮኩላል። ወዲያውም በረት ውስጥ ትለቅም እነበረች ሴት ዶሮ ዙሪያ ማንኮራፋት ይጀምራል..... ከቀኝም ከግራም እንኮራፍቶ ለሽ ለሽ ማለቷን ሲያይ አንገቷን ዘሎ ይነክስና ለልም ታህል ጊዜ ላዋ ላይ ኮርፈፍ ብሎ ይወርድላታል። - ቡናኝ የበተነባት ይመስል እንደወረደላት እሷም በተራዋ ላባዎቿን አንኮራፍታ ታራግፍና ለቀማዋን ትጀምራለች። - አውራው በመገረም ዓይነት እየኮኮለ የሚለቃቀም ነገር ለማግኘት እየጠቋቆመ ይሄዳል። - አንድ ፍሬ እንደ ያዘ ወደ ግራ ወደ ቀኝ መልከት መልከት ይላል - ሌላ ሴት ዶሮ ባቅራቢያው ያያል.....ይጋብዛታል በመስቆሩ እያነሣ እየጣለ.....ስትፈራ ስትቸር ስትጠጋው ፍሬውን ይለቅላትና ትንሽ ራቅ ብሎ ደግሞ ሌላ ፍሬ ይፈልጋል.......ያገኛል.....እንደ ገና ይጠራታል..... አንዴ ሁለቴ ያንኮራፋል.....ይኮኩላል.......ይንደረደራል......ዶሮይቱም ቡናኟን ታራግፋለች።

አቶ ክብረት እበረንዳ፥ በወምበር ላይ ተቀምጦ ፀሐውን ይመልከካል። ዓይኑን የዶሮቹን ሁኔታ የሚመለከት ይመስላል፥ «እንዴት ያለ ‹ኩርብ› ይመስልሃል ያ አውራ ዶሮ የሠራው......» ይጀምራል ክብረት ግምባሩን ኮስተር ራሱን ነቅነቅ አድርጐ

እነበላይን እንዳያቸው ቶሎ ብድግ በማለት «......እንዴት ያለ ‹ኩርብ› ይመስላችኋል ያ አውራ ዶሮ የሠራው.....ካረፈ ወዲያ ደግሞ ያሳየው ንቅናቄ ‹ሙቭማው› የተከተለው መሥመር ደሞ ‹ሊኙ› እንዴት ያለ የማያደናገር ቀጥታ ነው - ወደ ዋናው ትርኢት ወደ መልዕክቱ የሚመራ! በክንፎቹ ውዝዋዜ ጊዜ ደግሞ ያሳየው የቀለም ትርግርግታ ‹አርሞኒው› እንዴት ይመስላችኋል.....ከተገኑ ጋር አዋሐዱ ‹ኮንትራስቱ› አስትራረፉ ‹ፔርስፔክቲቩ› እንዴት ይመስላችኋል..... ካለመኖር ወደ መኖር ከጨለማ ወደ ብርሃን እንደሚመጣ ዓይነት ከኋላው አጥር ወደ ፊቱ ሜታ.....ሕይወት ነፃነትት ዘለዓለማዊነት ወሰን የለሽነት.....

«ወንድን ሲፈጥረው እጁን ታጥቦ ነው እግዚአብሔር......» ይጀምራል በላይ

«ሴትን በፈጠረ ጊዜ እጁን ያቆሸሸው ነገር ባይኖር ይሆናል እሱስ..... እምልህ......» ያቋርጠዋል አደፍርስ ንግግሩን

«ቅድምኮ ስለ ባልና ሚስት የተፈላሰፍከው ብዙ ሳይቆይ እዚሁ ፉርሽ ሆነ - ተመልከተሃል ያ አውራ ምን እንዳደረገ፤ መጀመሪያ ዛጐልማዋን ዶሮ ነበር የወደደው..... ወዲያው ግን ፍቅሩ አልቆለት ወደ ገብስማዋ ሄደ - ባጭሩ ብቻ እንደ ንብ ማለት ነው፤ ካንዱ አበባ ወደ ሌላው.....

......አልስማማም በላይ! አልስማማም! ሰውና ዶሮ አንድ አይይደሉም......ሰው ውጫዊ ብቻ አይደለም፤ ውስጣዊም ጭምር ነው.....ሰብአዊ ሰውነቱን ከልቡሰ ጥላው ማስማማት ይኖርበታል። - ለመሆኑ ማነው ልቡሰ ጥላውን የማያፈቅር? ልቡሰ ጥላውሰ ያስመለከተውን ለመፈጸም የማይጥር? ሰው በተፈጥሮው ራሱን ወዳድ ስለሆነ በዓይነ ኅሊናው እውነት መስሎ የሚታየውን ነገር ሁሉ ከተፈጥሮ ጓደኛው ጋር ሲገናኝ ሐሰት መሆኑን እንኳን ቢገነዘበውም ልቡሰ ጥላው ለዘራበት አስተያየቱ ያለው እምነት የማያቋርጥና የማይበዛ ነው። በዚህም ምክንያት ልቡሰ ጥላው ያመለከተው ሁሉ በዓይኑ ከሚያየው ተመሳሳይ ነገር ሁሉ በልጦ ያገኘዋል.....

አቶ ክብረት መሣያ ሸራውንና ቡርሽ ቀለሞቹን አውጥቶ የመጀመሪያውን ንድፍ የንታትባል። -

«እንዴት ነው ጋሼ ክብረት ሳንዘገጃጅ ማንሣት ጀመርህ.....

«ሳንዘገጃጅ?! ትቀልዳለህ በላይ.....ከዚህ በላይ ዝግጅት የለም። - ቀጥሉ ክርክራችሁን....ይታወቅ የዘመኑ ወጣት በናንተ ውስጣዊኢ ግመት......በስሜት ተምቦልበሉ! የምነት አገቸሬነታችሁ በፊታችሁ ይነበብ.....

......እዚህ ላይ አንድ ልናስታውሰው የሚገባን መሰላል የሚሆን አስተአይየት አለ፤ ማለት ምንም ዓይነት ጥረት መፍጨርጨርና ድካም፥ ልቡሰ ጥላችን ያመለከተንን በሙሉ ልንደርስበት፣ አለመቻላችንን ነው። ልቡሰ ጥላችንን መሰል ማንኛውም ድርጊት በምድር ላይ በከፊል እንጂ ተሟልቶ ልናገኘው አንችልም። ነገር ግን ተመሳሳይ መስሎ የምናገኘውን አትኩረን ብንመረምረው ምድራዊ ኑሮ እንደሚፈቅድልን መጠን በቂያችን ሳይሆን አይቀርም። ለማስረጃ ያህል፥ ባሁኑ ጊዜ ውጤቱ አጥጋቢ መስሎ ያልተገኘውን የጋብቻን ሁኔታ እንመልከት። ብዙ ጊዜ እንደሚነፍሰው ተጽፎም እንዳነበብኩት ሚስት ከየት እናምጣ? በተለይማ የተማረች ሴት ሚስት አትሆንም፤ እሠራለሁ ትሠራለህ ተምሪያለሁ ተምረሃል፥ ሀብት አለህ ሀብት አለኝ እያለች ጋብቻን መልክ ታሳጣዋለች..... ወንዱም እንዲሁ ካሥሯ ጋር ዳንኪራ ሲረግጥ ትዳርን አያስበውም በሚል አኳኋን የተውተፈተፈ - እውነትን በሙሉ ያልጨበጠ ውሸትም በሙሉ ያልነገሠበት ያምባ ገነን ንግግር እሰማለሁ። እንደኔ አስተያየት ግን የተማረችም ሆነች ያልተማረች እንደደረጃቸው የሞቀ የደመቀ፥ ትዳር ለመቀለስ ይችላሉ። ወንድም የምትሆነውን ካገኘ ቅድም አንተ እንዳልከው ሳይሆን ማለቴ አበባ እንደምትቀስም ንብ አሥሯን መቅመሱ ይቀርና በአንድ ሴት ይወሰናል። ደምወዙን በውጪ ጨርሶ ሚስቱና ልጆቹ በችጋር ሲያልቁ ዝም ብሎ ይመለከታል እንደሚለው እንደሌሎችም ሳይሆን ለትዳሩ ለሚስቱና ለልጆቹም አሳቢ ይሆናል። አንድ ጊዜም በተክሊልም ሆነ በማዘጋጃ ቤት ድንጋጌ መሠረት ካገባ ጸንቶ ሊኖር ይችላል ነው የምልህ......ያንተን የንብና ከአበባ አበባ አስተያየት አልቀበልም.....

«እንዴት ነው ጋሼ ክብረት ይኸ የምታነሣው ሥዕል ጨርሶ የኛን አይመስልም.....» ይለዋል በላይ ቀረብ ራቅ ቀጥ ሸንደል በማለት በሙሣያ ሸራው ላይ የተምቦራጨቀውን የልዩ ልዩ የቀለም አንድነት ትግል በመመልከት።

«እኔ ለመሳል የምፈልገው እውነታን አይደለም፤ እንደ ካሜራ መገልበጥ አይደለም ዓላማዬ። በየፎቶግራፍ አንሺው ሱቅ መስተዋት ውስጥ እንደምታይዋቸው ሕይወት፥ ሲንቀሳቀስ እንደማይታይባቸው በልዩ ልዩ አቋቋም የተነሡ የበድን ሥዕሎች የሚመሳሰሉ.....በውነት እላችኋለሁ እነዚያ ፎቶ ግራፎች የሙት (የሬሳ) ወይም በሕይወቱ ያለ ሰው የተነሣቸው ፎቶ ግራፎች ለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ምልክት አይታይባቸውም......

«እውነትህን ነው ጋሼ ክብረት አንተ የምታነሣው ሥዕል በላይን ወይም አደፍርስን መሆን የለበትም። በአፍአዊ ሰውነታቸው እንዲታይ፥ ልዩ ጥበብ ያለው ተመልካች ያስፈለገውን ውስጣዊነታቸውን ወይም በሌላ አነጋገር እነሱነታቸውን ነው።

- ‹እኔ ማነኝ?› ብሏል አንድ ዐዋቂ? አንተ ማንሣት ያለብህ፥ ወጣትን ሳይሆን ወጣትነትን - በላይን ሳይሆን በላይን ስታይ የሚሰማህን መሆን አለበት..... ውስጣዊው ነገራችን የሕይወታችን የኑሯችን ቁልፍ ነው። ለምሳሌ የሰው ልጅ ውስጣዊ የሆነችውን ልብሰተ ጥላዊ ሚስቱን ቢያገኝ በምድር ላይ ከሚያያቸው ቆነጃጅት አብልጦ እንደሚወዳት የታወቀ ነው። ካለማግኘቱ የተነሣ ግን የሚገጥሙት ሴቶች ሁሉ በመጥላት ያገባትን ሚስቱን በመፍታት ስለ ቁንጅና ያለው አስተያየቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለዋወጠ - ጥቁር ሲያይ ጥቁር ቀይ ሲያይ፥ በየዕለቱ እናያለን። እያንዳንዱ ሰው የቆንጆ አመራረጡ የተለያየ ነው፤ ያንዱ ኩስኩስት ላንዱ ድምቢጥ - ያንዱ ረቂቅ ላንዱ ኮፍጣና - ያንዱ ኮምበር አፍ ላንዱ አበባ ፍንድ ከንፈር - ያንዱ ዱፍንዱፍ ላንዱ መከዳ..... ያንዱ ድሁር ላንዱ ምጥን..... ያንዱ ቀጨሞ እግር ለሌላው ቀላቅሌ..... ያንዱ ወርሃ ለሌላው ቁም ነገረኛ ናቸው፤ ማለቴ እንግዲህ የያንዳንዱ ሰው ልቡሰ ጥላው የተለያየ ነው። - በዚህም ምክንያት ሁሉም የየራሱ ምርጫ አለው እንጂ ያንዱ ቆንጆ ለሌላው ቆንጆ አትሆንም.....

«......እሱን እንኳን ርሳው እባክህ......» ይለዋል በላይ። -

.......እንዴት አድርጌ፥ እውነት አይረሳምኮ፥ በላይ.....! ርግጥ ነው አንተ የታሰበህ ገብቶኛል። አንዳንድ ሰዎች የይሌላን ቆንጆ በመመልከት የራሳቸውን ልብሰተ ጥላ ትመስላቸውና በጣም ይታለላሉ፤ ለፍተው ጥረው ግረው ሊያገኟት ይጣጣራሉ። ያገኙት እንደ ሆነ ግን፥ ያ እንደዚያ ያስፈቸላቸው ውበት በወር ውስጥ ግፋ ቢል በዓመት ያስጠላቸውና ፍቅራቸው ይቋረጣል። ዓያንቸው አይቶ ያሯሯጣቸው ጆሯቸው ሰምቶ ያናወዛቸው ዘላቂነት ያለው ሳይሆን ከልቡሰ ጥላቸው ጋር የማይስማማ ጊዜያዊ ሥዕል አጥበርብሮትና አንቀሳቅሶት መሆኑን ይገነዘባሉ። በእንደዚህ ዓይነት ይሁን ይሁን የምትገባው ሚስት ከባሏ ልቡሰ ጥላ ጋር ካለመስማማቷ የተነሣ የባሏ ጠባይ ሲለዋወጥባትና በመጨረሻም ስለቸቷት ጥላው ስትሄድ ይታያል።

«......ለምሳሌ እኔ አሁን የምሥለው እናንተ በየምታምኑበት ነገር ስትከራከሩ ሳያችሁ ስለ እናንተ፥ የተሰማኝን ያን ልብ እንደሚይዝ ፍቅር ድንገት ያዝ አድርጎ እንደሚለቅ ዓይነት የሆነውን የማይደጋገመውን ደራሽ ስሜት ነው እንጂ እናንተ ሁልጊዜ እያያችሁ የተለማመዳችሁትን የዘወትር እውነታችሁን አይደለም.....ውስጣዊውን ስብእናችሁን ነው ልደርስበት እምሻው......

......ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት! እርግጥ ነው፥ የእውነተኛ ሠዐሊ ተግባሩ ውስጣዊውን ንቅናቄ አፍልቆ ማሳየት ነው መሆን ያለበት - ለምሳሌ የባሏ ውስጣዊ

ስሜት ልቡሰ ጥላው ሲተአኝና ሲደክም ጊዜያዊ የባሏ ፍቅር አይለያት ይሆናል። ያጭውታታል ያስቃታል ያስደስታታል። ነገር ግን ባልታሰበ ግዚኤ የባሏ ልቡሰ ጥላ ሲነሣና አቅም ሲያገኝ እንደ ጭጐጐት ሳይወድ ተሰግስጋበት የምትኮሰኩሰው ነው የሚመስለው...... ባይኑም ለማየት እንኳ ቢጸየፋት አይገርምም። እንደዚህ ያለ ሁኔታ የደረሰባት ሴት ጥላው ካልሄደች በስተቀር የባሏ ልቡሰ ጥላ በተለዋወጠ ቁጥር ጥላው ካልሄደች በስተቀር፥ የባሏ ልቡሰ ጥላ በተለዋወጠ ቁጥር እየተሸማቀቀች ምን ጊዜም ሙሉ እምነት ሳይኖራት ዓይኗ ርቆ እየተመለከተ ልቧን ግን እንጀራ እያሸነፈው ስትበደል ትኖራለች። ካልፈታችውና መሰሏን ካላገኘች በስተቀር ከባል የሚገኘውን ደስታ ልታገኝ አትችልም። ባሏንም ቢሆን ጭራሹንም ሌሎችን ሴቶችና ራሱንም ጭምር እስከመጥላት ሊያደርሰው ይችላል። በርግጥ በርግጥ ሠዐሊ የሆነ ሰው የልቧን ፍመትና ያይኗን አይደረሴነት መሆን ይገባዋል መሣል ያለበት.....ለእንጀራ የተገዛው ሰውነቷ ጭራሽ ዋጋ የለውም......

«.......አንድ ሕፃን ልጅ የእግሩን አውራ ጣት ጐርሶ አልጋው ላይ ተኝቷል ፊቱ ፈገግ ፈገግ እያለ......ሦስት ቡችሎች አፋቸውን አጠጋግተው እመኪና መንገድ ማህል ተጥለዋል......አንዱን ባለ መኪና ይለያታል፤ ወደ ፊት - ወደ ኋላ - ወደ ፊት ወደ - ወደ ኋላ - ውጭ ነፍስ ውጪ ነፍስ ትተናነቃለች....... ጨርሶ አልጨፈለቃትም ባለ መኪናው። እሺ! እንግዲህ እኔ እነዚህን ልዩ ልዩ ነገሮች ባየሁ ጊዜ ምን ነበር ስሜቴ! እነዚያን ስሜቶች ነው በሠዐሊነት ጥበቤ አፍኜ ይዤ መለየት የሚኖርብኝ......እነዚያን ግላዊ የሆኑ የሕይወት ፈገግታና - የሕይወት ውጊቶች......እነዚያን አይደገሜዎች.....

........አንድ ሰው ድንገት የተሰማውን ስሜት ፍላጐትን ተስፋ - ወይም እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎችን ንቅናቄዎች በመንፈሱ የመያዝ ችሎታ አለው። ነገር ግን በገቢር ለማዋል በሥነ ጽሑፍም ሆነ በሙዚቃ በሥዕል - ወይም በጠቅላላው በአኗኗር መንገድ ይዞ ለመገኘት አስቸጋሪ ነገሮች ናቸው። - ልዩ ተሰጥኦ ያስፈልጋቸዋል። - ከተሰጥኦ ውጪ ማለት ተሰጥኦ የሌለ እንደሆነ ግን የማያቋርጥ የመንፈስ ቆራጥነትና ከግቡ የሚያደርስ የየዕለት ትግል ይጠይቃሉ.......ለምሳሌ አንድ ሰው ሚስት ለማግባት ሲፈልግ መጀመሪያ ልብስተ ጥላ ሚስቱ ምን ዓይነት እንደሆነች በዓይነ ኅሊናው መንገዘብ አለበት። መቼም ልብስተ ጥላ ሚስቱ በተፈጥሮ ያደገች የሰውነቱ ክፍል ስለሆነች በጣም ሳያፈቅራት አይቀርም። ስለዚህ ዓይነተኛ እርምጃው ሊሆን የሚገባው ልብስተ ጥላ ሚስቱ ከኅሊናው ወጥታ የኑሮ ጓደኛ እንድትሆን ማድረግ ነው። ይህንንም ሲያደርግ ልብስተ ጥላዊ ሚስቱ ያላትን አቀራረጽ ያላትን ጠባይ ሌሎችንም ስለ ድምፅዋ ስላነጋገሯ፥ ሊያገኝ የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር እሱ እሷን ሲያገኝም ሊያደርግላት የሚፈልገውንና የሚችለውን ሁሉ በነጭና ጥቁር ማሥፈር አለበት.......

«.......እውነትህን ነው.......» በቡርሹ የሚሥለውን ሥዕል ነካ ነካ እያደረገ «.......እውነትህን ነው፤ በተለይ በሥዕል ሥራ ስለ ብርሃን አጣጣል - ስለ ፀሐይ - ስለ ዳመና - ስለ ጭፍና - ስለ ምሽት - ስለ ጭለማ - በጠቅላላው ነጭና ጥቁርን - የፀሐይን ብርሃን እንዴት እንደምትጠቀምበት ማወቅ ትልቅ ጥበብ ነው.......

.........በዚህ በነጭና ጥቁር ስለሚያሠፍረው ነገር ደግሞ ዝግጅት ያስፈልገዋል። ጧት ጧት ወደ ሥራው ሲሄድ በወረቀት ላይ ያሠፈረውን የልብስተ ጥላዊ ሚስቱን ፎቶግራፍ እያነበበ ቢያጋጥመው ለመፈለግ ይሞክር......» በላይ ወገቡን በእጁ ይዞ ግምባሩን ኮስተር አፉን ኩርትም አድርጐ የእውነተኛ ኮፍጣና ፊት እንዳለው ዓይነት ሆኖ እንዲነሣ ይጥራል። ጭውውቱን የተከተለው አይመስልም...... ካለፍ አገደም ክብረት ባላይን አየት ያደርገዋል።

.......እንግዲህ አንድ ቀን ውቃቢው የደነገጠለት አንዲት ልጅ ያግኝ እንበል......ምናልባት በጽሑፍ ካሠፈራቸው አስፈላጊዎች ውስጥ ከሀያ እስከ ሠላሳ በመቶውን የሚኖራት.......ከዚያ በኋላ ሳይተዋወቃት በፊት በሩቅ ሆኖ ይከታተላት - በርግጥ ያያቸው ነገሮች መኖራቸውን ሲገነዘብ በቀጥታ መንገድ ተዋውቆ (የስሜቱን ፈጽሞ የእንጀራ ገመዱን በጥሶ፥ የሰው በታች ለማድረግ ሳይሆን) ልብስተ ጥላ ሚስቱን ቢያገኝ ሊያደርግላት ያሰበው የነበረውን የሚያስደስትበን መንገድ በዚች ልጅ ላይ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚፈጥር ለማወቅ እየቆጠበ ይሞክረው። ይህን በሚያደርግበት ጊዜ በጻፈው መግለጫ መሠረት ከልጅቷ ከሚፈልጋቸው ነገሮች ውስጥ ሊያውቅ የሚፈልጋቸውን፥ በቅርብ እንጂ በሩቅ ሊታወቁ የማይችሉን ያጥና.......

«እሷስ አልጠና ያለች እንደሁ፤ ስታይህ የምትሸሸ የምትቆጣ የሆነች እንደሁ። - ጨርሶ ያልወደደችህስ እንዲሁ። - ወይም ደግሞ የተዋወቅህበትን ምክንያት እስኪታውቅ ድረስ ብታነጋገርህ እንኳ ልታነጋግራት በተጠጋህ ቁጥር ልብህ በኃይል እየተመታ ግምባርህን እያበላህ ንፍጥህ ያለትሮው እየመጣ ልትናገረው ያሰብከው ነገር እየጠፋብህ፥ እየዘባረቅህ፥ ጭራሽ ያይደለኸው ስውነትህ እየታዬ ያስቸገረህስ እንደሁ - ምን ትሆናለህ ወንድሜ - ምን መፍቻ ምን ማገጃ - ምን ዘዴ ታገኝለታለህ? ለእንዲህ ያለው ሊቆጣጠሩት የማይቻል ነገር......» ይለዋል በላይ ድንገት አደፍርስን።

........ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት! እዚህ ላይ ወንድነትህን መርሳት የለብህም፤ ቆስካማነትህን ማሳየት የለብህም - ብታጉማማ ብትበሳጭ ዋጋ የለውም። - እና ብቻ እንዳጋጣሚ ሆኖ የምትፈልገው ነገር ከጎምሳ ሲያልፍና በተፋጠነ ሁኔታ እያደር ሲያድግ......ያንን ጽፎት የነበረውን ማንበቡን ያቋርጥና እሷ ዘንድ ቶሎ ቶሎ እየሄደ ሊያነጋግራትና ሊያጫውታት ይሞክር.....

«እምቢ አልጫወትም ያለችውስ እንደሁ ነውኮ የሚልህ - አልተዋወቅም፥ አላነጋገርም ያለችውስ እንደሁ ነው የሚልህ በላይ!» ሠዓሊው ድንገት ቀና ብሎ ይናገራል።

......እዚህ ደረጃ ሲደርስ.....» ጨርሶ ያልሰማ መስሎ አርቆ እየተመለከተ «.......በወረቀት ላይ የሠፈረው የልብስተ ጥላው መግለጫ ተደጋግሞ ከመነበቡ የተነሣ - ምንም እንኳ ልብስተ ጥላው ከሆነችው ሚስቱ ውስጥ በዛ ያለ ሊገለጥ የማይችልም ነገር ቢኖር፥ እወረቀቱ ላይ ባለው ብቻ ተወስናለችና እንዲሁም እወረቀቱ ላይ የሠፈረው በተገኘችው ልጅ ቀስ በቀስ እየተለዋወጠ ሄዷልና ቢጋቡ በባልና በሚስትነት ጸንተው መኖራቸው አያጠራጥርም - ውጫዊው በውስጣዊው ውስጣዊው በውጫዊው ተለወጡ ማለት ከአዳም፥ ከግራ ጐኑ ተፈነቀለች - ማለት ባልና ሚስት አንድ አካል አንድ አምሳል ናቸው - ማለት ባጭሩ ትርጉማቸው ይኸው ነው.......

«እኔ የቸገረኝ ሌላ እሱ የሚያወራው ሌላ! እባክህ ጋሼ ከብረት ጨርሰህ እንደሆን እንሂድ.......!

«ምንም ያህል አልቀረኝ......የብርሃኑን አበታተን ላስተካክለው ብዬ ነው.......

.......እንግዲህ እውነተኛ ሚስቱ ልትሆን የምትችለውን ደጋግሞ ከማነጋገሩ የተነሣ ስለ እሷ ብዙ ነገሮች ሲያውቅ የሚፈልጋቸውም ነገሮች ከመቶው - ከሃምሳ በላይ ሲሆኑና እድገታቸውም የሚያኮራ ሲሆን እሱ መጀመሪያ ላይ በሠራበት ፎርም መሠረት እሷም በተራዋ የምትፈለውን ሰው መግለጫ እንድትሰጠው ያድርግ.......

«እሱን የሚመስል ሳይሆን የቀረስ እንደሁ? - በተራዛሚ መንገድ እንኳን ቢሆን ሳይቀራረብ የቀረስ እንደሁ - ከዚያ ሁሉ ጥረት በኋላ......

.......እዚህ ላይ የሚገርመው ብዙ ጊዜ ስላነጋገራቸውና ውቃቢዋም በከፊል ሳይፈቅደው ስለማይቀር የምትጽፈው መግለጫ እሱን የሚመለከት መሆኑ ነው......

«ይቺ በጭራች መሠረት የሌላት ያንተ የብቻ መላ ምትህ ናት - በበኩሌ አልቀበልህም» ይለዋል ሠዓሊው።

.......ባይሆንም እንኳኮ እሷ ከሱ ላይ ከምትፈልገው ሀያ ከመቶ ከተገኘበት ለብቻው መጠየቁ አይከፋም - ምናልባት ለልብስተ ጥላ ሚስቱ ሊያደርገው ይመኘው ከነበረው ውስጥ አንድ አሥረኛውን እንኳ አላደረገላት ይሆናል። ስለዚህ ወደ ፊት ወደ ፊት የሚበልጠውን የሚያስደታትን ነገር ባደረገላትማ ጊዜ ልጅቱ ለሱ የሚኖራት አስተያየት እያደገ እንደሚሄድ አያጠራጥርም......

......እነዚህ ባልና ሚስቶች አይፋቱም ለመጀመሪያው ጊዜ ሚስቱ ለባሏ የልብስተ ጥላው መስታዋት ናት፤ እንዲሁም ባሏ ለሚስቱ የልቡሰ ጥላዋ መስታአዋት ነው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ያገባት ሚስቱ በአእምሮ ውስጥ ልብስተ ጥላውን የነበረች በተጨማሪም እውነተኛና በዓይኑ የሚያያት በእጁ የሚዳስሳት ስትሆን፥ እሱም በሚስቱ አእምሮ ውስጥ ልቡሰ ጥላዋን ሆኖ የኖረ፥ በተጨማሪም እውነተኛና በዓይኗ የምታየው በእጅዋ የምትዳስሰው የምትመካበት ባሏ ይሆናል......

«እኔኮ የምለው እንዲህ ያለው የተወገዘገ የኑሮ እተረጓጎም ከወዴት ተፈጠረብህ......?» ይጠይቀዋል ሠዓሊው

.......ከየት የተፈጠረብኝ ይመስልሃል - ከዩንቨርስቲ ነዋ! ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት! - ለምን ይመስልሃል ዩኒቨርሲቲ የገባሁት የተጻፈን ለማስተጋባት አይምሰልህ......የፕሮብሌሞችን መነሻ ከሥራቸው እያጠናሁ መልስ ለማግኘት ነው። - እውነት ካለችበት ፈልፍዬ ለማውጣት......ብቻ እንግዲህ እኔ ባገኘሁት እውነት መሠረት ወንድም ሆነ ሴት ልቡሰ ጥላቸውን መሰል ካላገኙ፥ ወንድ - ነጠላ ትከሻ ቀትረ ቀላል አጉራ ዘላይ ይሆናል፤ ሴትም - ቅዥቃዣ ቀበጥ፥ ተለዋዋጭና የእንግዳ ቁርበት ትሆናለች። - ማለት የወንዱ ልብስተ ጥላ በሰብአዊ ሴት የሴቷ ልቡሰ ጥላ በሰብአዊ ወንድ ካልተለወጠ ሴትና ወንድ አንድ አካል አንድ አምሳል ይሆናሉ ብዬ አላምንም ነው የምልህ። - ሌላውን ተወው፤ የዱሮ አባቶቻችን እንኳ ቢሆኑ እንደዛሬዎቹ ወጣቶች አይተንትኑት እንጂ የጋብቻቸው ሥርዓት ይኸንኑ እኔ የተናገርኩትን መንገድ የተከተለ ነበር - ሽማግሌዎችም ሆኑ ልጆቻቸው ከበረታቸው ውጪ የማያውቁ ከነሱ የተሻሉ አርአያነታቸውን የሚከተሉት ሰዎች ያላጋጠሟቸው ሐሳባቸው ከአያት ከቅድመ አያት በወረት ልቡሰ ጥላቸውና በልዩ ልዩ ተረቶችና ምሳሌዎች ብቻ የተወሰነ ነበር። ከዚህም የተነሣ በሚወልዷቸው ልጆች የሚቀረጸው ልቡሰ ጥላ ያንኑ ያባቶቻቸውን መሰል ስለ ነበረ ባባቶች ልብስተ ጥላ መሠረት ትመረጥ የነበረችው ሚስት የልጆዮውም ልብስተ ጥላ መሰል ስለ ነበረች ልጆቹ ቤተሰቦቻቸው የመረቱላቸውን ያገቡ ነበር። ሲያስተሣሥራቸውም ይኖር የነበረው ከአባቶች የወረሱት የሚወዱት የሚያፈቅሩት ልቡሰ፥ ጥላ ባባቶቻቸው እንደገና የተመረጠ ስለ ነበረና ልጆቹም በሙሉ እምነት በአእምሯቸው ውስጥ ምስቅልቅል ሁኔታ የነበረውን ልቡሰ ጥላቸውን በተጨበጠ መንገድ ያገኙት ስለሚመስላቸውና አእምሯቸው የፈለገውን በአእምሯቸው ያደገውን ከአእምሯቸው ወጥቶ የኑሮ ጓደኛቸው ሆኖ ስለሚያገኙት ነበር። ብዙ ሳይመራመሩ በቀላሉ ሄዋን ከአዳም ከግራ ጐኑ እንደወጣችና እስከ ዕለተ ሞቱ እንዳልተለየችው በመንገዘብ ባልና ሚስት አንድ አካል አንድ አምሳል ናቸው ምን ጊዜም መለያየት የለባቸውም በማለት አምነውበት ኖረዋል። - በአእምሮ የተፀነሰች

ልብስተ ጥላ ናትና ከሰውነት ጋር አብራ ያደገች ስለሆነች፥ ሥጋ ለበስ ሆና በጐን ከሰውነት ክፍል የማትሆንበት ምክንያት የለም......

«ይኸ ሥዕል አይገባኝም ጋሼ ክብረት፤ እዚህ ላይ የሣልከው እኛን ባየህ ጊዜ የተሰማህን ስሜት አይደለም - እዚህ ላይ በቀጭኑ የተሰነጠበ የፊት ግማሽ እዚህ ላይ ደሞ በቀጭኑ የተሰነጠበ የፊት ግማሽ - አፍ - ጆሮ - ለየብቻቸው እዚህጋ ደግሞ ዓይን - ደግሞ እዚህጋ አለቦታው እግር........በተረፈ ሜዳ ሙሉ በያይነቱ ቀለም.......ይኸ እንኳ የቀለም ቦግታ እንስራ የተሸከመች ሴት ይመስላል - ፍሬዋ እንደሁ አልመጣችም ማን አየህና ተሰምቶህ ነው የሣልከው.......?» ይለዋል በላይ - ዓይኑን ባለማመን አንዴ ሁለቴ አሸት አሸት ብልጭ ድርግም አድርጐ ከተመለከተ በኋላ። -

«ይኸኮ የእናንተ ሥዕል እናንተን አይቼ በተሰማኝ ስሜት ላይ አይደለም የተመሠረተው - እዚህ ላይ ለማሳየት የሞከርኩት አደፍርስን ወይም በላይን አይደለም - እናንተ በምትኖሩበት በአሁኑ ጊዜ ያለውን ቁደረኛ ጐበዝነትን ነው። የዘመናችሁን ቃንቄነት - የዘመናችሁን ወጣትነት - እንደምታየው ይኸን ሳደርግ የተለየ የወጣትነት መልክ ወይም የተለየ በስም የታወቀ ወጣት ፊት ወይም ካስፈለገኝ በስተቀር ሙሉ ሰው የሚታይበት ሰውነት መሣል የለብኝም። የዘመኑን ቁደረኛ ወጣትነት የሚገልጹ፥ ማለት ሊገልጹ ይችላሉ የምላቸው ጥቂት ምልክቶችን ከጠቆምሁ በቂ ነው ማለት ነው። የቀለሙ መወራቸት ደግሞ ዓላማው የዘመኑን ድምፀታና ቀልብ ፍላጐት አዝማሚያና ጠቅላላ አየር ለማሳየት ያህል ነው......

«እንደዚህ መሆኑን ባውቅ ኖሮ ጋሼ ክብረት ጭራሽ ጊዜዬን አላጠፋም ነበር። እኔ የፈለግሁት አፍንጫዬም እንዳለ ዓይኔም እንዳለ ጆሮዬም እንዳለ እጄም እንዳለ ሆዴም እግሬም እንዳለ እንደተፈጠርሁ እንድትሥለኝ ነበር እንጂ ለዚህ ኖሯል? ዱሮ ፈረንሣይ አገር ከመሄዴ በፊት የሣልኩት ነው ብለህ ያሳየኸኝ እንዴት ይሻል ነበር። መልክ ለሌላቸው እንኳ መልክ ነበር የምትሰጣቸው - የመላእክት ዘር እንጂ የሰው ዘር አይመስሉም ነበር፤ እንዲያም ሆኖ ታዲያ ለመለየት አላዳገቱም........አሄሄ! ትምህርት ሲበዛ ጥሩ አይደለም......

«ወንድሜ አፍንጫ እንዳለ ዓይን እንዳለ ወይም ደግሞ ሌላው ዘዴ ሰው የመልአክ ዘር መስሎ የሚሣልበት ዘመን አልፏል። ዛሬ ሕዝቡ ተራቋል፤ ጸጉር ሰንጥቋል። - ልቡን የሚያረካው አእምሮውን የሚመግበው የሚያሳስበው ነገር ይፈልጋል። - አንተ ጠቅልለህ ከምታጐርሰው ይልቅ በገዛ፥ እጁ መርጦ አስተካክሎ አመቻችቶ ቢመገብ ይመርጣል፤ የሚደክምበት ነገር የበለጠ ይጣፍጠዋል......

«.......ሕዝብ ተራቋል ትለኛለህ ደግሞ እኔ ከሕዝቡ ውስጥ መሆኔን እየረሳህ......! ርቅቀት እንደዚህ ከሆነ እኔ አልተራቀቅሁም - መራቀቅም አልፈልግም - ይኸን ዓይነቱ ርቅቀት ግልበት ነው ለኔ የሚመስለኝ.......

«ለመሆኑ ግን ከፍሬዋ ጋር እንዲያ ስለሲያንሱ ጆግራፊው ሥነ ጥበቡ ኪነ ጥበቡ ስለ ስንቱ ነገር ስትከራከሩ ምንም ያህል አልለወጠችህም.......» ይለዋል ክብረት በላይን። - በዚህን ጊዜ በላይ ዘወር ቢል አደፍርስን ያጣዋል።

«.....ምን ዓይነት ጥላ ቢስ ፍጥረት! ምን ጊዜ ከፊቴ ተሰወረ!» መለስ ብሎ ፈጥኖ ሊያደርሰው በሚያስችል ሩጫና ርምጃ ይፈተለካል።

........ሰበብህ አመለጠህ ፍሬዋን ማያ ዘዴህ!» ይላል ክብረት ለራሱ እንደሚናገር ዓይነት የሚሥለውን ሥዕል ፊቱን ሠየፍ ሠየፍ እያደረገ በቀኝና በግራ እየተመለከተ።

# ፱

## አደፍርስ

ሰበቡ ያመልጠዋል ክብረት እንደተናገረው። አደፍርስ የሄደበትን አቅጣጫ ተከትሎ አልነበረም ጥድፊያው። - ፍሬዋን ቢሆን እቤቷ ስለ ነበረች ያገኛታል። - ከነገር ነገር የተነሣም እሷ የምትወደውና እሱም በደንብ የሚያውቅ ዓይነት የመሰለው ርእስ ይገጥመውና በረጅሙ ይይዘዋል ጨዋታውን...... «ያን ጊዜ ገና ከባላገር ደብረ ሲና አልመጣነም......ግፋ ቢል አሥር ዓመት ቢሆነኝ ነው። ድግስ ተጠርተን ካባቴ ጋር ሄድሁና አባቴ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ እኔ ካላደርሁ ሞቼ እገኛለሁ ብዬ ስላስቸገርሁ እዚያው እድግሱ ቤት ቀረሁ። - ማታ ራት ቀርቦ ስንበላ እኔ ስለ ቤቴ፥ ስለ አባቴ ስለ ማሳድጋት ውሻ እያሰላሰልሁ አንድ ከወጥ ውስጥ የወጣ የዝልዝል ሥጋ ጉራጅ አፌ አድርጌ አልታኘክ ብሎኝ በመተናነቅ ላይ ሳለሁ ተናደድሁና ብውጠው በሥራሥር ነገር ከጥርሴ ጋር ተያይዞ ኖር እንቅ አደረገኝ። ወዲያ ብል ወዲህ የተያያዘበትን ልፋጭ ላገኘው አልቻልኩም። ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ ሆነ። በጣቴ ብኮረኩር ጉሮሮዬን ያዝ ለቀቅ እያደረግሁ ብተናነቅ ፋይዳ አልሠራም። እንባዬ ርግፍ ርግፍ ይል ጀመር። አብሮኝ ይበላ የነበረው የባለቤቱ ልጅ አየኝ። የምሞት የመሰለው ዓይነት ደንግጦ አባቱን ጠራ። ወዲያውኑ መጡ። ጣታቸውን ወደ አፌ አልጨመሩም ማጅራቴን በጃቸው ሰደፍ መቱት - ከጥርሴ የተያያዘው ተመንጭቆ በጉሮሮዬ ወደ ታች ተሽቀነጠረ። ዓይኔ ተገለጠ። ባለቤቱ ሳቅ አሉ።......ለወትሮው ወደ ውጭ ቱር ይል

ነበር፥ ዛሬ እንዴት ወደ ታች ወረደ ብለው ገረማቸው - ‹መዘዘኛ ላም የሰው ልጅ አስከትላ ነበር› አሉ በመቀጠልም። - ላሚቱ ገደል ስለገባች ነበር የታረደችው.......» እያለ። -

ፍሬዋም «እስካሁንኮ ስለ አየሃቸው ሠይጣኖች ምንም አልነገርከኝም፤ እኔ የምፈልገው ስለ እነሱ ለመስማት ነው፤ ሌላውን በሌላ ጊዜ እንጫወተዋለን.....» በማለት የተነሣበትን እንዳይስት እያስታወሰችው። -

.......እሺ እሺ - ወደ ሠይጣኖቹ መምጣቴ ነው። - ለካ ታዲያ ይኸውልሽ ዋናው ነገር፥ ይኸ በሥጋ መታነቅ የተለመደ ነገር ኖሯል። ሰውን ሥጋ ካነቀው ጊዜ ሞቱ ደርሶ ነው ይላሉ አባቶቻችን አሉ ባለቤቱ። ተመልከችው እንግዲህ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ምናልባት ታንቀው የሞቱ ምናልባትም እንደ እኔ የዳኑ ከዚያ በፊት አይጠፉም ማለት ነው። ገረመኝ። መብላቴንም አቆምሁ። ለማባበል ያህል እንደገና ከሳቸው ወጥ አስወጥተው በርቦ መሳይ ለብቻዬ ሰጡኝ። እኔ ግን ከድንጋጤዬ የተነሣ ብዙ ሊበላልኝ አልቻልም ‹ኧረ አንተስ ዘበናይ ነህ› አሉኝ። ብርቅ ሆኖብኝ እንደ ልጅ ጐረስ ጐረስ የማደርግ መስሏቸዋል። እኔ ለራሴ ካባቴ ጐን ቂጥጥ እያልኩ አብሬ መመገቤን አላወቁም። - ቅይጥ እንኳን በልቼ አላውቅም - ይገርምሻል። - ታዲያ ብርቅ የሆነብኝ መሏቸዋል ከሳቸው ወጥ ማጥቀስ። መልስ አልሰጠሁም። የኔ ትራፊ ለሳቸው ልጅ ተሰጠው። ድጎና አድርጌ አቀላጠፋት። እንደዚያ ያለ ዕድል አጋጥሞት የሚያውቅ አልመሰለም እንዳበላሉ። ወደ መኝታዬ ልሄድ ስል የባለቤቱ ሚስት፥ የደረሰብኝ አደጋ በጣም ሰግጥጧቸው ኖሮ፥ እጄን ያዝ አድርገው ፊት ፊቴን በማየት - ወዳጄ እንኳን እግዜር የናትህ ውቃቢ ያዳነህ ብለው እንትፍትፍትፍ አሉብኝ.......

«በላይ እኔ ስለ እሳቸው እንትፍትፍ ደንታ የለኝም፤ ስለ ሠይጣኖቹ ትነግረኝ እንደሁ ንገረኝ፤ አለዚያ ተወው......» አጣሁ ወሮታ የናደፍርስ የኖረች የቤት አሽከር ተከታትላቸው ኖሮ የምትሠራበትን የጭስ ቤት ግድግዳ ተገን አድርጋ የሚሉትን ታዳምጣለች።

.......ልነግርሽኮ ነው......! በመቀጠልም ታዲያ የሳቸው ዛር ፈረስ ከተነሣ መቼ ከብቱንም ሰዉንም ካልጨረሰ ይቆማል? አሉ። ለካ ባለቤትዮው ዛር ኖሮባቸዋል። ላሚንም ገደል የጨመራት ዛራቸው ኖሯል። ጊዜ ጊዜ አለው እንጂ ዛራቸው ሁል ጊዜ ቢቆጣ ሁላችንንም ይጨርሰን ነበር። - ዛሬ ደግሞ ምን ጐደለኝ ምን አምጡ ይሆን የሚለው? እንደ ልማዳቸው ከሚያጨርሱን በፊት ያንኑ ስም አይጠሬን ጐትተው ምክንያቱን አይጠይቁም? አሉ። -

«ስም አይጠሬ ደሞ ምንድነው?» ትለዋለች ፍሬዋ በተቆጣ አንደበት።

........ስም አይጠሬ የምሥጢር ስም ነው ሠይጣን ለማለት፤ እና ይኸውልሽ ነገሩ ሁሉ ገረመኝ። ስም አይጠሬም ማን እንደ ሆነ ለማወቅ ፈለግሁ። ግን ወዲያ ወዲህም ብል ማንም አልነገረኝም......

«ለምን ሴትዮዋን አልጠየቅሃቸውም.......?

«አይነግሩኝም ነበር......

«በምን ዐወቅህ ሳትጠይቃቸው በፊት» አጣሁ ወሮታ የሚነጋገሩበት ነገር ስለ ምን እንደ ሆነ ሊገባት አልቻለም፤ ስለ ፍቅር ወይም ስለ ጋብቻ ሳይሆን አይቀርም በማለት ግን ልቧ ገንግኗል።

.......አይነግሩኝም ነበር ብቻ ምን አለፋሽ..... እና ይኸውልሽ ዝም ብዬ ወደ መኝታዬ ሄድሁ። - ሌሊት አንድ ሁለት እመም እንቅልፍ እንዳሳለፍሁ አሽከሮች ሲያጉተመትሙ ሰማሁ። ስም አይጠሬ! ስም አይጠሬ! ጌቶች ስም አይጠሬን ይጠራሉ ሲሉ። ለማየት ዳጉቻለሁና ተነሣሁ። ነገር ግን ከኋላዬ አንድ ጠንካራ እጅ ወደ ነበርኩበት ጕትቶ በደረቴ ደፋኝ። ደነገጥሁ። ስም አይጠሬ መሰለኝ። መለስ ብዬ እንዳላየውም ፈራሁት.....

«መለስ ብለህ ማየት ነበረብህ......

.......የለም ፈራሁ፤ ያረፈብኝ እጅ ከላዬ አልተነሣም፤ እያደር ከበደኝ፤ ጩህጩህ አለኝ - ጮኩኝ!

«ጮህህ......?!!!

......አዎ ጮኩኝ፤ ያረፈብኝ እጅም ከላዬ ተነሣ.....

«አዬ ወንድ አትባልም......!» አጣሁ ወሮታ ድንግጥ ብላ፥ ዓይኗ ያጕርጥና አፏን ትይዛለች።

........መለስ ብል ከኋላዬ ምንም ነገር የለም። - አንድ ሁለት እረኖች ራቅ ብለው ቆመዋል። እኔ ግን የሆንኩትን ለመናገር አልቻልኩም......

«ዋጋ አልነበረውም ‹ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ› ሳይሄድ በፊት መልስ ብለህ ማየት ነበረብህ......

......ከዚያ ብቻ ይኸውልሽ ከእረኝኖቹ አንዱ ጠጋ አለኝ.....

«ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት ይላል አደፍርስ..... በቃኝ እንግዲህ እባክህ......! ስለ ሠይጣኑ ጨርሰህ የለም? ጨርሰሃልኮ ሳታየው ቀርተሃል.....

.......ምነው ብታስጨርሽኝ! ገና መጀመሬ ነው የምን መጨረስ.......! እና ታዲያ ይኽ እረኛ የጮኩበትን ምክንያት ጠየቀኝ። መልስ ግን አላገኘም። ቅዠት ቃዥተህ ይሆናል አለኝ። በመቀጠልም ጌቶች ሥራ ይዘዋልና ማንም ወደ በረት እንዳይወጣ ብሎ ተናገረ። እኔ ግን ስም አይጠሬን ለማየት የነበረኝ ጉጉት፥ እንዲያውም እጁን ካሳረፈብኝ ወዲህ እየገነነ ሄዶ ስለ ነበረ ሽንቴንም ለመሽናት ልወጣ አልችልሞይ ብዬ ጠየቅሁት........

«መጠየቅ አልነበረብህም፤ እሱን ተደብቀህ ልታይ የምትችልበትን መንገድ ነበር መፈለግ የነበረብህ......

......ምን መሆንሽ ነው - ልጅ ነኝ - ይኸን መርሳት የለብሽም.......የሆነው ሆኖ እሱም መልስ አልሰጠኝም። ዝም ብሎ ወደ ጓዳ ገባ። ከዚያም ቆሬ መሳይ መክፈያ ይዞ መጥቶ እዚህ ላይ ክፈለው አለኝ......

«ከፈልከው!»

.......ለመውጣት አልቻልኩም ማለት ነው...... እረኛው ኮቴውን ሳያሰማ እንደ ሰላቢ ተመልሶ ወጣ። ሁለቱ እረኞችና እኔ ቀረን። ስለ ስም አይጠሬ እነሱን መጠየቅ ግድ ሆነብኝ፤ ጠየቅኋቸው። - እነሱም በሹክሹክታ አባ ድብልብሌ የሚባል ቁጣው ከባድ ልግስናው ትልቅ የሆነ የቀያችን ንጉሥ ነው አሉኝ። ገረመኝ.......

«እኔ ገና አልገረመኝም.....

........እውነትሽን ነው፤ የሰጡኝ መግለጫ አላጠገበኝም። - ርግጥ ስለ አባ ድልብልቤ ከዚያ በፊት ሰምቻለሁ፤ ነገር ግን አላየሁትም...... እንደሰማሁት ከሆነ አባ ብልብሌ - አጥር የማያግደው፥ መዝጊያ የማይመስለው ሲያሰኘው ከጣራ የሚወርድ፥ ሲያሰኘው ከመሬት የሚወጣ ቢበላ የማይጠግብ ዙሪያ ሆድ፥ በተለይ የልጆችና የከብቶች ጠላት ነው። - እናቴ እንዳወራችልኝ ማንም ሰው ያየው እንደሌለና ማንም ደግሞ ወዳጅ እንደማያደርገው ነበር። ግን አሁን እረኞቹ እንደሚያወሩት ከሆነ ጌቶች እየጠሩ ያነጋግሩታል። - ለማየት እችላለሆይ ብዬ ጠየቅኋቸው......

«ለምን ራስህ መንገድ ፈልገህ አታየውም? ለምን ትጠይቃቸዋለህ......?

........ካየኸውማ፥ ዓይንህን ያሳውርሃል - ሰውነትህን ያሳብጥሃል አሉኝ። ወዲያውም ይህን ስንነጋገር ከሁሉም በዕድሜ ከፍ ያለው እረኛ ከመኝታው ተነሥቶ

እያዛጋ መጣ። ሁለቱን እረኞች እየቦታቸው ተመልሰው ሄደው እንዲተኙ አዘዛቸው። እሱ ግን ከኔ ጋር ቀረ። - የሚሉህን አትስማቸው፤ እንዲያው ነው የሚያስፈራሩህ አለኝ። ለኔ የነበረውንም መልካም አስተያየት በመመልከት እሱንም ስለ ስም አይጠሬ ጠየቅሁት - በሹክሹክታም እንዲህ እያለ ሊነግረኝ ጀመረ.....

«ስማ ስማ በላይ፥ እኔ የምፈልገው ያየኸውን እንድትነግረኝ ነው፤ የመስማት የመስማት ከሆነ ካንተ የበለጠ ስምቻለሁ - በመድረክ ላይ ምታት ሲፈስ አይቻለሁ - ስለ አስማትም ብዙ አንብቢያለሁ። ያየኸውን ንገረኝ፤ አለዚያ በከንቱ ጊዜዬን አታስመሽብኝ......

......ስም አይጠሬ ብዙ ዓይነት ነው..... ሲል ጀመረ፥ የባሕር ውስጥ ስም አይጠሬ አለ። የአየር ስም አይጠሬ አለ። የጉድፍ ስም አይተሬ አለ። ሁሉም ለየብቻ ሥራ ሥራ አላቸው። በኅይለኝነት የሚበልጠው ግን የአየሩ ስም አይጠሬ ነው አለኝ። - ቀጠለም - የጌቶች አባት መምሬ (ማነው..... ስማቸውን እረሳሁት) የሰማውንም የባሕሩንም ስም አይጠሬ ይጐትቱ ነበር። በዚህ፥ ላይ ድምብር ገፌ ስላቢ ነበሩ ይባላል። ነፍሳቸውን ይማረውና ሲቀበሩ መቃብራቸው መቅን ገባ ይሉናል። እስከዛሬ ድረስ መቃብራቸው ይጮሃል......

«ለምንድነው የሚጮኸው?» ትጠይቀዋለች ፍሬዋ፤ የመጮሁ ነገር በጣም የገረማት በሚያስመስል አመለካከት እየተመለከተች።

.......እኔም ጠይቄው ነበር የዚህኑ ዓይነት ጥያቄ እረኛውን እና ባለማወቄ እየተገረመ እንደሚከተለው ነገረኝ...... ብቻ ለሰው እንዳትነግሪ መሬት እስከ ዛሬ ድረስ ሬሳቸውን አልተቀበለችውም። በየጊዜው ልትተፋው ትሞክራለች። እንደተቀበሩማ ሰዓት ሦስት ጊዜ እየተፋቻቸው ታቦት ወጥቶ መሬት ተገዝታ ነው የተቀበለቻቸው። ከዚያም ጀምሮ ቁልቁል መቀመቅ ይኸው እስከዛሬ ይወርዳሉ፤ እና መቃብራቸው የሚጮኸው ቁልቁል ወደ አንጦረጦስ ስለሚወርድ ነው አለኝ......

«ብቻ ምን አለፋህ፥ ከረኛው ጋር ስትጨቃጨቅ ሰውዬው እውጪ የሚሠሩትን ነገር አላየኸውም ማለት ነው......ዋናውን ነገር.......ብታየው ኖሮ ይኸ ሁሉ ዝባዝንኬ.....

.......ላመጣልሽኮ ነው......እና ታዲያ በመከያው......ምን ነካቸውና ሞቱ? ታመው ነወይ ብዬ ጠየቅሁት። እሱም......

«እኔ ልንገርህ፥ ስለ ሰውዬው አባት ስትጨርስ ደግሞ ስለ ሰውዬው እንደምትጀምር ይገባኛል......እና ይኸን እንደጨረስህ ወደ ፍሬ ነገሩ ካልሄድህ...... ምናለፋህ ብቻ መቆራረጣችን ነው...... ምንድነው ተምረሃል...... መንግሥት ተማሪ ቤት

ገብተህ - እንደምን ከረሙ ቤተ ሰቡስ ልጆቹስ፥ ከብቶቹስ የወለደችውስ ላም እርሻውስ ጥጃውስ..... የሚል ዓይነት አነጋገር መናገር......» ትለዋለች ንዴቷ በምፅዋ ጉልህነትና ንዝረት የታየው። -

.......አሄሄ...... ገና ልጅ ነህ አለኝ እሱም፣ በመቀጠል። እሳቸው ሞቱ አይባልም፤ ስም አይጠሬ ጠራቸው ነው። - አንድ ወራት ሰብላቸውን ተምችና አንበጣ ተጫውቶበት ነበር። ከዚያም የተነሣ ከመዐቱ እንዲያወጣቸው ስም አይጠሬን ለመጠየቅ ፈለጉ። ነፍሳቸውን ይማረውና ባለቤታቸውን ለስም፥ አይጠሬ የሚያስፈለገውን ምስ ሁሉ እንዲቋጥሩላቸው ካደረጉ በኋላ፥ የወንዙ ስም አይጠሬ ለመቆጣቱ በሕልም ተገልጾላቸው ነበርና እወንዝ ወረዱ። በነገርህ ላይ ያባትዮው ሁዳድ የነበረው መኖሪያቸው እዚያ ማዶ ነበር። አባትዮው ከሞቱ በኋላ ነው፥ እኚህ ልጃቸው ሸሽተው እዚህ የሠሩት - ከዚያ ይኸውልህ እወንዝ ወርደው ስም አይጠሬን ከጠሩት በኋላ የሚፈልጉትን ሁሉ አግኝተው ወደ ቦታው እንዲመለስ ምሱን ሊሰጡት ስልቻቸውን ቢፈቱ በጣም ተፈላጊ የነበረው ሪሚጦ ተረስቶ አገኙት....... መቼስ አይጣል ነው እንጂ ምን ይሏል..... ይናደድልህና አረባይቶ አረባይቶ...... ለቋቸው ኖሮ......

«ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት የሚሉ አነጋገር..... አደባይቶ አደባይቶ ለቋቸው ኖሮ...... እሺ....... !» ፍሬዋ መቀመጡ ይደከማትና ተነሥታ ያጣሁ ወሮታን ጭስ ቤት ተደግፋ ትቆማለች። - አጣሁ ወሮታ እንዳትታይ ሸሽት ትላለች። - በላይ ፍሬዋ የምትሄድ መስሎት ቀና ብሎ ያያትና አለመሄዷን ሲያጋግጥ ታሪኩን ይቀጥላል....... አርቆ እየተመለከተ።

.......በቃሬዛ እቤት ያመጧቸዋል። ምን ይሆናል..... የቀበጡ ለት ሞት አይገኝም........ ጠላትህ ይታሠርና በጠፍር እንደ ታሠሩ ካልጋ ሳይወርዱ ሰውነታቸው ሁሉ አባ ሰንጋ እንደ ያዘው አባብጦ በመጨረሻ ተገላገሉ እልሃለሁ...... እሳቸው ከሞቱ በኋላ የቀንድ ከብቱንም በጉንም ፍየሉንም እየተከታተለ ስም አይጠሬ ፈጀው። ባለቤታቸውንም እግራቸውን እስከ ሙሃሊታቸው አሳብጦ እየበላ እየቆረጠማቸው አቅኑኝ ደግፉኝ እግሬን ጨብጡልኝ እያሉ ለሰፈር አስቸግረውና አሰልችተው መሞት አይቀርምና.......

«ተገላገሉ! አለህ.......

......ሞቱ አለኝ። በዚያን ጊዜ እኚህ የኛ ጌቶች እዚህ አልነበሩም። አባትዮው በንጉሥ ዘንድ የታወቁ አቅኚ ስለ ነበሩ ቤተ መንግሥት ወስዶ ያሳድጋቸው ነበር። ገና

ዕድሜያቸው አምስት ዓመት ሲሆነው ጀምሮ። አባትና እናታቸው ካለቁ በኋላ ነው እዚያው አድገው ተሾመው ተሽልመው በመንግሥ ሁዳድ ላይ አዛዥ ሆነው የመጡት። ከደህና ተወለድ ወይም ከደኅና ተጠጋ እንዲሉ ዱሮም፥ ባባታቸው የተደላደሉ ጌታ ነበሩ ንጉሡም ጨመሩላቸው.... አሰለቸሁህ መሰለኝ በንግግሬ አለኝ........

«...... የለም የለም - ትንሽ ደግሞ ስለሚስትዮዋ አስተዳደግ ንገረኝ አልከው......

...... እኔም እኮ ልለው ነው፤ ምን ማለትሽ ነው? ብዙ ነው ያወጋነው....... ትኩር ብዬ ተመለከትሁት.....

«ዓይኑን ቶሎ ስብር አረገ.....

......ትኩር ብሎ ተመለከተኝ፥ እሱም - ከዚያ ነው ድንገት አሁን ጌቶች የሚጠሩትን ስም አይጠሬ ብናይ ምን አለበት ያልኩት - አንገቱን ሰበር አድርጐ ትንሽ አሰበ። ጠብቀኝ ብሎ ወጣ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ተመለሰ። በቡልኮው ውስጥ ሁለት ቀምበጦች ይዟል። አዲስ የተቀጠፉ ነበሩ። አንዱን ለኔ ሰጠኝ፤ አንዱን ራሱ ያዘ። ተከተለኝ አለኝ። ተከተልኩት። በደረታችን እየዳህን አንድ እህሉ ተሟጦ ደረባው እመሬት እተቀመጠ ሪቅ ቦታ ደረስን። ባለቤቱ እፍግ መቆለያው ዲብ ላይ ቆመው መጽሐፍ ያነባሉ። እሳቸውም ባንዱ እጃቸው ቀምበጥ ይዘዋል። ብቻቸውን ናቸው - እግረኛው ልጅ እጄን ነካ አደረገኝና ቀምበጡን ጥርቅም አድርገህ ያዝ ይነጥቁሃል እለኝ። በመቀጠልም ምናልባት የሚያስቅ ወይም አስጸያፊና መጥፎ መጥፎ ሥራ ሲሠሩ ስታይ እንዳትስቅ፤ እይሳቅህ እንደሁ በጥፊ ያጠናብሩሃል አለኝ። ቀምበጡን ጥርቅም አድርጌ ይዤ አነሳቸውን እመለከት ጀመር። ባጠገባቸው ሁለት ጠያይሞችና አንድ ጥቁር ሰው አለፉ። ባለቤቱ እጃቸውን እየዘረጉ ስም በመጥራት አኳኋን በኃይል ያነቡ ጀመር። ሦስቱ ሰዎች እያንዳንዳቸው የያዙትን እቃ እፍጉ ቁልል ላይ አስቀመጡት። ወዲያውም እግራቸውን እያነሡ አንዳንዴም አጉል የወገብ ንቅናቄ እያሳዩ ባፋቸው ይመስለኛል እያንዛረጡ ይጨፍሩ ይሯሯጡ ጀመር። ሦስቱም ሰዎች ቀምበጥ በጃቸው ከመያዛቸውና ሐፍረታቸው ላይ ቅጠል ዓይነት ነገር ከማሠራቸው በስተቀር ራቁታቸውን ናቸው። ከመካከላቸው አንዲቷ ሴት ትመስላለች። በጥርስና በጥርሷ መካከል ፊቷን የሚሸፍን ትልቅ ሙዳ ሥጋ ነክሳ መካከል ነክሶ ይዟል። ሦስተኛው ግን ዋና ሥራው ልዩ ልዩ አጓጉል የሰውነት ንቅናቄ ማሳየትና ፊቱን በልዩ ልዩ ዓይነት የመኮመታተር ሁኔታ መለዋወጥ ብቻ ነበር። ወዲያው ይኸው ሦስተኛው ሰውዬ በኃይል ጮኸ። ከዙሪያውም አፈር እየዘገነ ከነድንጋዩና ጠጠሩ ከነፍጉ፥ ወደ

እኛ በኩል ቤቱ ላይ ይበትን ጀመር። እንደጨረሰም ሦስቱም አብረው ወደመጡበት ተመለሱ። - ባለቤቱ ቢሆን ንባባቸውን አላቋረጡም፤ የጥድፊያ ነበር እንዲያውም አነባበባቸው። - ብዙ ቆይተውም ታላቅ ድምፅ እንሰማ ጀመር፤ ትርጉሙ የማይገባ የሚያጓራ የተናገረም የሚመስል ከወዴት እንደሚመጣ ለማወቅ የማይቻል - የሰውዬው ንባብ እንኳ አይሰማም ነበር - ሳይታሰብ፥ ባለቤትዮው መጽሐፉን እንደያዙ ወደቁ። አሽከራቸው ራቅ ብሎ ይጠብቃቸው ኖሮ አነሣና ደግፎ ወደ ቤት አገባቸው። - አብሮኝ የወጣውም እረኛ ዛሬ አልተሳካላቸውም መሰለኝ፥ ሳያውን እየመኘታችን እንመለስ ብሎኝ እንዳመጣጣችን እየዳህን እየመኘታችን ደረስን። - ስለ ሦስቱ ሰዎች ጠየቅሁት፤ ምናልባት የሠይጣኑ አሽከሮች ይሆናሉ አለኝ..... በመቀጠልም፥ እኔም የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው፤ አንተን አይቼ ነው ተደፋፍሬ ላይ የመጣሁት፤ እስከ ዛሬ አይቼ አላውቅም አለኝ...... ከዚያ በኋላ ትንሽ ቢያሽልበን ብለን ወደመየመኘታችን ሄድን........

ፍሬዋ የማድቤቱን ግድግዳ ከለላ በማድረግ ሹልክ ብላ ኮቴዋ ሳይሰማ ወደ ቤቷ በር ታመራለች።

.......መንጋት አይቀርምና ነጋ። ወደ ባለቤቱ እልፍኝ ሄድሁ። - ባለቤቱ እንደተኙ ናቸው። ያቃስታሉ። ከጭሰኛቸው አንድ በዕድሜ ጠና ያሉ አዛውንት አጠገባቸው ተቀምጠዋል። ለሳቸው ረጅም ወሬ ጀምረዋል.....

አጣሁ ወሮታ ተደብቃ ታዳምጥበት ከነበረው ከማድ ቤቱ ውስጥ ቀስ ብላ ትወጣለች። ፍሬዋ ቆማበት እነበረው ቦታ ቆማ ሳትንቀሳቀስ ትሰማለች፤ ፊቷን ጨምደድ ለቀቅ ፈገግ ኮስተር ቆጣ በማድረግ..... የሚናገረው ነገር የገባት አይመስልም፤ አልተያያዘላትም።

«.......ቀያችን አባቴን አላግባብ ካጉሳቆላቸው ወዲህ፥ እኔ ሁለተኛ ከርኩሳን መናፍስት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳላደርግ ምዬ ይኸው እስከ ዛሬ ተቀምጬ ነበር ይላሉ ባለቤቱ....... ትላንትና ማታ ግን ጤና አልነበረኝም። ሌሊቱንም ቅዠት አጠቃኝ። ስለዚህ ያረገውን ያርገኝ ብዬ ማላዬን ጥሼ ካንድ ካኃይለኛ ቅዠት በኋላ ሰውነቴ ሁሉ በላብ እንደተጠመቀ መጽሐፉን ከተሰቀለበት አውርጄ በቂውን ምስ ሳላዘጋጅ ወጣሁኝ። የባሕሩና የአየሩ ቢሆን ኖሮ እስከዚህ አልዳፈርም ነበር። ነገር ግን የጉድፍ ልቡሰ ሥጋ እንደዚያ የሚጻረረኝ አልመሰለኝም ስለዚህ ዶሮ መልሶ ሲጮህ ሰውነቴን ሳላደርቅና ታጥቤ ሰውነቴን ሳላነጻ ወጣሁኝ። እንደሚወደው እንደሚወደውም ጨዋታውም ሳይቀርበት አቀረብኩለት። እሱ ግን እንደ ነፋስ ባጠገቤ እያለፈ መልስ ከለከለኝ። እንዲያውም በመጨረሻ ግራ ጉኔን ጠቅ አደረገኝ፤ ሰውነቴንም ላብ አጠመቀኝ። እንደ ልቤም ተዝናንቼ ለመቆም አልቻልኩም.....በስንት

ፈተና እንዳልተለመነኝ ስገነዘብ መመለሻውን አንብቤ ስጨርስ አዞረኝና ወደቅሁ። ከዚያ በኋላ ልጆች አንሥተው አገቡኝ መሰለኝ እኔ ግን ነፍሴን አላውቀውም ነበር ሲሉ ያበቃሉ...... እና ይኸውልሽ ሳይሳካልኝ፣.......» እያለ ፊቱን ዘወር ሲያደርግ አጠገቡ ቆማ የነበረችው ሴት ቶሎ ራመድ ሽተት ብላ ወደ ማድ ቤት ስትገባ ያያታል። - ሰውነቷ ይወፍርበታል። - ልብሷ አልባሌ አረማመዷ የፍራት ትከሻዋ ሰፊ ጀርባዋ ጉባጣ ይሆንበታል። ተለዋወጠችበት ፍሬዋ። - ሁኔታው አልገባህ አለው። ያ በልጅነቱ በደረቱ የደፋው ያልታወቀ ነገር ታሰበው። ባይኑ ላይ አጥበርባሪ ነገር የመረገበት መሰለው። - መላው ጠፍቶበት ቀና ቢል የጣርማበር ተራራ ጭጋጉን ተሸክሞ ለምቦጩን ለንጨጩ የተሞለጨ፥ አርባ ስምንት ጥርሱን ገልጦ ያለማቋረጥ የሚስቅበት ልቡሰ ሥጋ መሰለው «........ሞትና ሕይ - ወ - ት - ድንቀኍ.......» - ከንፈሮቹ ለመላወስ ሲሞክሩ ዓይኖቹ መናወዝ ይጀምራሉ - ከቦታ ቦታ፤ ጢሻዎች አዲስ የታረሱ ጉባዎች ሸለቆዎችና ጉድባዎች እርጭ ያሉ የባሕር ዛፍ ጫካዎች - ኮርች - አመራሮ - ምሥሮች - ችፍርግ - ኩርንችት - የምድር እምቧይ - ገበር እምቧይ - የቆላ እምቧይ - እምቧይ - እምቧይ - የምድር እምቧይ - አፈርማ መንደሮች - ቁራዎች - ዋኔዎች - ርግቦች - ጭልፊዎች.......የነፍሬዋን አጥር ግቢ ወጥቶ ወደ ራሱ አጥር ግቢ ያመራል።

# ፲

# አደፍርስ

ማታ ቤተ ሰቡ ሁሉ ወደ የመኝታው ሄዶ፥ አጣሁ ወሮታ የእመቤቷን የወይዘሮ አካላትን እግር አጥባ የሚቆረጥማቸውን ስታሻሽላቸው -

......የለም የለም ማንም እንዲህ ያለ ነገር አላወራም፤ ስለ ጋብቻስ? ስለ ጋብቻ ማንም አላነሳም። በላይ ለራሱ ህጣን...... ገና ህጣኖች ለራሳቸው.......ሆሆይ ምን ቢቆርጣቸው......ምን ቢቆርጠኝ እዋሻለሁ....... የመድኃኒ ዓለም ቤተስኪያን በር ዘጋለሁ ቢፈልጉ......በሥዕለ ስእለቱ እምላለሁ........ ለማን ይድላው ብዬ...... የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው ስሰማ...... አዎ ግን ሰምቻለሁ...... በጣም የተለየ ነገር ነው ግን የሰማሁት...... ይኸ ክብረት የሚባል ሰው ደሞ...... ጌቶች ለምን እንዳስከተሉት አይገባኝም.......የሚኻየልን የገብሬልን እሺ! የሴትና የወንድ ሥዕል መሣል - የዛሬ ትምርት ተበላሽቷል ግዴለዎትም....... ደግሞ እንድታገባው መጠየቁ......

«ምን? ምን? ክብረት......» እግራቸውን ምንጭቅ አድርገው ይሰበስቡታል «......ምን ጠይቋታል ነው ያልሽው.......»

«የለም ይኸም እልም ያለ ውሸት ነው፤ የሚኻየልንና የገብሬልን ሥዕል ብቻ ነው የሚያስተምራት....... ምን ቢያገደው...... ምን የመሰለ አልጋ ላይ ሞቀ ቤት የሚያንፈላስስ ጌታ......ሆሆይ እመቤታችንን ነው የምትመስለው........ ሥዕሉን ሲያሳያት እንኳ ፊቱን አዙሮ ነው። ምን ቢያገደው ያሥር ድሃ ልጅ...... እነዚህ ደሞ የስፈሩ አሽከሮችና ገረዶች እንዴት ያሉ ወሬኞች...... ደሞ እንዴት ያምርባቸዋል እያሉ ማውራታቸው...... የማይቋጥሩ...... ያቺ ታየች - ለተፈሪ - ተፈሪ - ለወለቱ - ወለቱ - ለታደሰ - ታደሰ ደሞ እዚህ ድረስ መጥቶ ለኔ - የዋዛ ሰው መስየዋለሁ በሱ ቤት - ከማንም ሰው - ከማንም ባላገር ጋር የምዋዛ - ቢያሳው ላይ እንደ ሽናንበት አያውቅም....... የወሬ ነገር፥ ክብረት ቢያገባት ምንኛ በተስማሙ ማለት ደሞ - የሚኻየልን ሥዕል እንኳ የማያስተምር......

«ምን ዓይነት ወሬኛ ሰፈር ገባን እባካችሁ...... ደሞ አንቺስ ከምኔው ዐወቅሻቸው......

«በጣም እንጂ...... እመቤቶቻቸው ወጣ ሲሉ ቡና እያፈሉ የሚጠጡ - ቅቤ የሚጠጡ - ጠላ የሚጠጡ.... ይኸ ታደሰ ደሞ ጌታውን እንኳ ተከትሎ ሲሄድ የሚያንቀላፋ ነው የሚመስለው....... ፍሬዋ ቀድሞ ሁሉ ወንድ ወንድ አይመስላትም.......ወንድ አታባልም ነው የምትለው....... ሽንትህን በመክፈያ የምትከፍል....... ደሞ የማግባት ደሞ የሠርግ ጣጣ..... ሆሆይ! ምን ቢያገድ! ከሠርግ ይልቅ አርባ ወይም ሰማኒያ መደገስ ይሻላል......የኔ ብጤ የሚበሉበት - የእግዜር አገልጋይ የሚበሉበት......

«ብቻ ለወደፊቱ ስለዚህ ለማንም እንዳትለፈልፊ.......

«ልፍለፋ! ምን ቢቆርጠኝ......ትዝም አይለኝ.......ደሞ መለፍለፍ! ምን አልለና የሚለፈልፉት.......ገና ይኸው ስለ በላይም መጀመሪያ ጊዜ ማየቴ ነው። እግዚአብሔር ይቅሠፈኝ......ስሙን እርስዎ ሲያነሡት እንዴት ገርሞኛል.......አስደነገጠኝ እንዳንዳች! አንቀጠቀጠኝ እንዴት ይሆናል ብዬ! ደሞ የምን ሠርግ - ርሶ የመጡት አየር ሊናፈሱ......ማንም አላለመውም - እኔ ራሴ ሁለዜ ወጥ ቤት፥ ከማን ተነጋግሬ.......እነዚያንም አሽከሮች ካየኋቸው ከወር አልፎኛል........ስማቸው እንኳ ተረስቶኛል........ደግሞስ ማን አለ እዚህ የሚያነጋገሩት.......ታደሰ ብሎ ሰው.......የሚያንቀላፋ.......በውነት ነው፤ ጆሮዬን ይድፈነው፤ አልሰማሁም። - ግድግዳው መቼ አሰምቶ.......

«ጥሩ ነው፥ ጥሩ ነው፥ በቃ አሁን.....

«......እንዴት ያልሆነ ነገር ሆነ ይባላል......? እኔ ለራሴ ጊዜም የለኝ እቴ! ለእንዲህ አይለው ነገር......ለራሴ ከጧት እስከ ማታ በሥራ ተወጥሬ! ቢሆንስ ደሞ...... ሲያቅፋት ባይስ.......ሆሆይ ምን ቢያገደኝ - ሚኻየል ምስክሬ ነው - የሚኻየልን ሥዕል እንኳ የሚያስተምር......

## ፲፩

## አደፍርስ

አቶ ጥሶ ደብረ ሲና ከወረዱ ጀምሮ እንደ ልማድ አድርገውት ራት ከበሉ፥ በኋላ ጠለላ ወጥተው ቁጭ ይላሉ። በዚህን ጊዜ ነው ካደፍርስና ከጺወኔ ከሌሎችም ሰዎች ጋር ስለ ልዩ ልዩ ነገሮች የሚያወጉት......

«ስለ ባህል ትንሽ ትንሽ ባስረዳኸኝ መሠረት፥ የገባኝ፥ መስሎኝ ለበላይ ላስረዳው ብሞክር ዛሬ፥ ድንግርግር አለኝ። ልማድ፥ ወግ፥ ቅርስ፥ በጠቅላላው ባህል ይባላሉ ብለኸኛል.....

«አዎ በየሻለሁ!» ይላሉ አቶ ጥሶ ለልጃቸው ለፍሬዋ።

«ልማድ ስንል፥ ጥሩ ልማድና መጥፎ ልማድ እንዳለ ነግረኸኛል። የስምንትና የዘጠኝ ዓመት ልጃገረዶች ለባል መስጠት - ራስ ምታት፥ ውጋት ሲይዘን በጋለ ብረት መተኮስ - መታመምን በተጨነቅን ጊዜ እዛር ፈረስ፥ መጽሐፍ ገላጭ ሞራና ስኒ ተመልካች ጠጠር ጣይ ጨሌ መች ዘንድ መሄድና ዕወቅልን ማለት - በየበዓላቱ በመስቀል ወሰራ ዶሮና ዳለቻ በግ በጥር ዛጐልማ በዚያ ላይ ለጠቋር እያሉ፥ ከለድማ ፍየል አራት አሻል በግ ዋላ በግ፥ ጣዝማ ካላረዱ በሽታና መዐት ይመጣል ብሎ ማመን.......

.......እኔ እይነገርኩሽን ነው መልሰሽ ለኔው የምትደግሚው? ያልገባሽ እንዳለ ይልቅ ብንነጋገርበት አይሻልም......?

«.......እኮ እኔ ያልገባኝ...... ጥሩ ልማድ ጥሩ ወግ፥ ጥሩ ቅርስ የምንላቸው የቶቹ ናቸው......?

.......ከልማድም ከወግም፥ ከቅርስም፣ ብዙ ልዩ ልዩ ዓይነቶች አሉ......» ብለው ይጀምራሉ አቶ ጥሶ «......ለምሳሌ ብዙ ዘመን ሲሠራበት የኖረ፥ የሰው ንብረትን የማክበር ልማድ አለን። የራሳችንንም አናስነካ የሰውም አንፈልግም። - ይኸን አክብሮታችንን የሚያስከብር፥ መብታችንን የሚጠብቅ የሥልጣንና የበላይነት ልማድ

አለን። - ምን ማለት ነው እንግዲህ ሥልጣንን የማክበርና በላይነትን የመታዘዝ ልማድ አለን ማለት ነው። - በቤተ ሰብ ውስጥ አንድነት ጸንቶ የሚኖረው በአባት ሥልጣንና በላይነት ነው ለምሳሌ። ያባት ሥልጣን ከተሻረ ያባት በላይነት ተወዳዳሪና ተቀናቃኝ ከገጠመው አንድ የነበረው ቤተ ሰብ ይበታተናል ማለት ነው....... ከዚህም ሌላ ቤተ ክህነት የሃይማኖት ሥልጣን መንግሥት ለሰላማዊ ኑሮ ዋስትና የሚበጅ የሹማምንት ሥልጣንና የበላይነት አላቸው።

«......እዚህ ላይ የመንግሥትንና የቤተ ክህነትን ሥልጣን መለየት አልገባኝም.....

........ከዚህ ቀደም ደጋግሜ እንደነገርኩሽ ኢትዮጵያ የምታምነው በሰማያዊና በምድራዊ በመንፈሳዊና በሥጋዊ ኃይል በጐለበተ እንደ ሰሎሞን ባለ መሪ ነው። ለዚህ ነው አርማችንም «ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ› የሚለው። - ስለዚህ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የቤተ ክህነታችን ሥልጣን በግብጻውያን ተይዞ ስለነበረ በውነትም የመንግሥቱና የቤተ ክህነቱ ሥልጣን እሁለት የተከፈሉ መስለው ነበር። ዛሬ ግን ሁለቱ ሥልጣናት አንድ ሆነዋል። የኢትዮጵያ መሪ ለመጀመሪያ ጊዜ፥ ቤተ ክህነትን በውጭ ሥልጣን ሥር ከመዋል አድኖ በራሷ ሥልጣን ሥር እንድትኖር አድርጓታል። - ኢትዮጵያዊ ሥልጣን ይመራታል ማለት ነው እንግዲህ። እንዲያ ከሆነ ዘንድ ደሞ፥ ማንኛውም ነዋሪ ነው የምንለው የሀገር መታወቂያ ሳይንሱም ሆነ ሀይማኖቱ፥ ፍልስፍናውም ሆነ ኪነቱ ከልማዱ ከወጉና ከቅሪቶቹ ጋር በመዋሐድ በመሪው ስብእና አድሮ...... ከዚያም እያንጸባረቀ መታየት ይኖርበታል ማለት ነው። - ይገባሻል......?

«አዎ አዎ ይገባኛል......

........ንጉሥ ከፕሬዚደንት ከጠቅላይ ሚኒስትር ይለያል ብዬ ያስረዳሁሽ ትዝ ይልሻል.......?

«ትዝ ይለኛል......

.......አዎ እንግዲህ ንጉሥ የነዚህ ሁሉ ጥሩ ነገሮች ማንጸባረቂያ ከሆነ የቤተ ክህነቱም ጥሩ ነገሮች ማንጸባረቂያ ነው ማለት ነው። እና በዚህ መሠረት የቤተ ክህነት ነዋሪ ሥልጣን በንጉሡም ስለሚገለጽ ከምድራዊ ሥልጣኑ ጋር ተዋሕዶ አንድ ሆኗል ማለት ነው.....

«ሥልጣኑስ በግብጻውያኑ እጅ ቢሆን ሁለት ሥልጣኖች ይኖሩ ነበር ማለት ነው......?

.......እንዴታ! አታውቂም እንዴ ከታሪክ ጣናትሽ......በነ አጼ ዮሐንስ በነ አጼ ቴዎድሮስ አጼ ምኒልክ ጊዜ ሁሉ ሳይቀር - ስንት ፍጅት ነበረበት ወዳጄ.......

«.......እሺ ስለ ጥሩዎቹ ልማዶቻችን ነበር የምትገልጽልኝ - ሌሎች ደሞ ጥሩ የምትላቸው እንዴት ያሉት ናቸው?

....... ተሰብስቦ የመወያየት የመመካከር ልማድ አለን። - በሸንጎ በእድር እንደምታይው። በኅብረት የመሥራት ልማድ አለን። በወንፈል በጊሶ በደቦ እንደምታይው..... አብሮ የመብላት የመጠጣት የመዝፈን የመጫወት ልማድ አለን - በማኅበር - በሠርግ በየበዓላቱ ሲደረግ እንደምታይው። - የሰው ስብእናው ትልቅነት የሚገለጽባቸው ልዩ ልዩ ልማዶች አሉን፥ - ገና በልጅነታችን ክርስትና ስንነሣ የሐዋርያቱን ስም እንሰጣለን። - ስንሠረግ በተክሊል በሥጋወ ደሙ እናገባለን። - ስንሞት እንደ ውሻ ሬሳ መወርወር ሳይሆን - ሲሆን ጉዞ ፍታት ሳይሆንም እንደዬ ተፈተን የመጨረሻ ክብርን እናገኛለን......

«ጥሩ......ለጊዜው ስለ ልማድ ይበቃኛል......ወግ ከምንላቸው ደግሞ ጥቂት ብትጠቅስልኝ.....

........ኦ! ብዙ ብዙ ወግ አለን - ስለ..... ስለ ሰላምታ አሰጣጥ......ስለ አበላል - ስለ አቀማመጥ የሴትና የወንዱ ተለይቶ - ለምሳሌ ሴት ልጅ እግሮቿን ከፍታ መቀመጥ የለባትም - ስለ አለባበስ ከነጠላ እንኳን አቅም - ወንድ በቀኙ - ሴት በግራዋ ነው የምታጣፋው - ስላረማመድ.....

«.......እሺ፥ ስለ ቅርስስ.......?

.......በልብስ በኩል - ባለ ወርቅ ጥብጣብ ካባ - ላንቃ - ጐፈር - ለምድ - እጀጠባብ። ልዩ ልዩ የበቅሎ እቃዎች በያይነቱ። - የግብርና እቃ በያይነቱ። - የሙዚቃ እቃ በያይነቱ፤ ዋሸንት እምቢልታ፥ ክራር በገና። - የቤት አሠራር - ቤተ ንጉሥ ሠቀላ። - የምስሉ ዓይነት - የሐውልቱ ዓይነት......ምናለፋሽ ብቻ ከያይነቱ ቅርስ አለን.....

«እኔ እምልህ አባዬ.....እነዚህ የዘረዘርካቸው ሁሉ - በርግጥ ከሌሎች ሠልጥነናል ከሚሉት አገሮች እኩል እንን ሊያስብሉን ይችላሉ?

......ካልሽስ የምንበልጣቸውም አይጠፉ......ብቻ ቢሆንም - አዎ - መሠረታችን የጸና ስለሆነ እኩል ነንም ብንል የሚያሳፍረን አይደለም። ሕንጻው ታንጾ እስኪያልቅ ብዙ ጊዜ ይፈጅ ይሆናል። ለታነጸ በኋላ ግን - እንደ ግሪኮች እንደሮማውያን ሕንጻዎች መፈራረስ እንደማያስፈራው እተማመናለሁ......

«በተለይ ስሜት በሚገለጽባቸው ነገሮች ወደ ኋላ የቀረን አይመስልህም......?

.......በመሳቅ በማልቀስ፥ በማዛጋት - በማስነጠስ - በቡጢ በዱላ - በዘፈን በጭፈራ ነው መቼም ስሜት የሚገለጸው - እኛ ኢትዮጵያውያን በነዚህ ነገሮች ወደ ኋላ ቀርተናል ብትይኝ አይገባኝም......

«አባዬ ግን በውነት በውነት - ካንጀትህ ነው የምታምነው......በኢትዮጵያ ትልቅነት......

......እንዴታ! አንዲም እንድታምኚ ያሻል እንጂ - ያልገባሽን እየጠየቅሽ መረዳት.....ስድብን በጣሊያንኛ - ፍቅርን ማላን በፈረንሳይኛ - ቴክኖሎጅን በእንግሊዝኛ ካልተናገርን - ትልቅ ላንባል ይሆን እንዴ እባክሽ.......? ፍሬዋ - አይሆንም ኋላ ቀስ እያልሽ ተራመጂ........

«እኔኮ የሚገርመኝ - ሀገርንና መንግሥትህን እስከዚህ የምትወደው ምን ኖሮህ ነው......? ሀገሬን ለምትልበት መሬት - መንግሥቴን ለምትልበት እስከዚህ - ትልቅ ሹመት የለህ - በጣም ነው የሚገርመኝ......

......ፍሬዋ! እየበሰልሽ ስትሄጂ ታውቂዋለሽ......አየሽ፥ እኔ አባትሽ - አንቺ አሁን የጠየቅሽውን ሁሉ አላጣሁትም - አዎ እንድታውቂው ያሻል - እኔ አባትሽ - አገሬን እወዳለሁ የምልበት ብዙ ርስት አለኝ......

«አባዬ.......!

.......ካንዱ ቦታ ወደ ሌላው አፍንጫዬን አየር ላይ ሰቅዬ እግሬ ሳይፈራ ሙሉ ለሙሉ የተራመድሁበት ሁሉ ርስቴ ነው። ሹመትም ስላልሽው የያዝሁትን ለጤና ያድርግልኝ የሚል አንጀት ባይኖረኝ ኖሮ አቅሜ የሚፈቅደውን ሹመት መንግሥቴ አያሳጣኝም......

«.......ብቻ አባዬ አለህ ነገር አንተ.......!

........አዳምጭ ፍሬዋ! ሀገርና መንግሥት ርስትና ሹመት ብቻ አይደለም - ርስትና ሹመትስ የትም ቢሔዱ ማንም ቢገዛ አይታጣም። ሀገርና መንግሥት አለኝ የሚያሰኙ፥ ልማድ ወግ፥ ቅርስ - ሌሎችም የጠቀስናቸው ባህሎች በሰው ላይ አድረው ውሕደታቸው ደም ግባትና ትከሻ ክብደት ሲያመጣ ነው - አለዚያ ሀገር ቢስ ወይም ውቃቢ ቢስ ነሽ እንጂ ባለ ሀገር ባለ መንግሥት አይደለሽም....

## ፲፪

# አደፍርስ

ከስድሳ ከሰባ ሰሰማንያ ዓመት በላይ ነው ስናውቀው የማይል የለም ወርካውን...... ዙሪያውም በአምስት ሰው እቅፍ አይደረስም። ሥር ሥሩን ሥጋጃ የሚመስል ሣር ስለማያጣ አጠገቡ በነበረው ጐዳና የተጓዙ ሁሉ ሳያርፍበት አያልፍም። በየቅርንጫፎቹ ላይ ብዙ የስለት ፈትሎች ጨሌዎች እይሻሽ ቁርጥራጮች ተንጠልጥለውበታል። በዋናው ግንድ ዙሪያ ሰው እንዳይደርስበት ሆኖ ሰፊ ጃኖ ታሥሮበታል። ቅቤም የተቀባ ቦታ አልፎ አልፎ አለበት። በየጊዜው የተሾሙት የያውራጃው ገዥዎች ሦስት ጊዜ ያህል ሊያስቆርጡት እየመጡ ቆራጮቹን ስለተተናኮለባቸው አልሆነላቸውም እየተባለ ይወራል አንዱን ገድሎታል - አንዱን አዙሮ ደፍቶታል - አንዱን እንዳውሬ አስጮሆ ከሥፍራው አባሮታል ይባላል። ያም ሆነ ይህ ወርካው የሚታየው በታላቅ አክብሮትና ፍራት ነው። - በሥሩ ክረምት ሲሆን ብቻ ግንፍል ግንፍል የምትል ወንዝ ትወርዳለች -

ከወርካው በላይ፥ ወደ ደሴ እሚወስደው መኪና መንገድ አቅራቢያ ሲል የማርያም ቤተ ክርስቲያን ከበታቹ ደግሞ፥ ወደ አረጋዊ ደብር መግንጠያው ላይ የድንጋይ ቁልል ይታያል - የድንጋዩን ቁልል አድባር ይሉታል። ክርስቲያኑም እስላሙም ዛር ፈረሱም ጠንቋዩም ሃይማኖት የለሹም በዚያ ጐዳና የሚያልፉ ከሆነ ከሩቅ ሥፍራ እጃቸው የገባውን ነገር እንጨትም ሆነ ድንጋይ ይዘው መጥተው እላዩ ላይ መጨመር ይኖርባቸዋል። ያልታሰበ አደጋ እንዳይመጣ ይከላከላል የሚል እምነት አላቸው።

ከወርካውና ከድንጋዩ ቁልል ባሻገር ኮረብታ ላይ የአቡነ አረጋዊ ደብር ነው። በጥድ በወይራ፥ በሾላ በጋሜና በብሳና ዛፎች ተከቦ ችፍግ ብሎ ይታያል። መግቢያው አጠገብ እሚታየው ዛፍ ላይ ረጅም የተጠረበና ጥፍጣፋ ድንጋይ ተንጠልጥሏል - የቤተ ክርስቲያኑ ደወል ነው። በሩቁ ሲያውት የተሰቀለ ሰው ይመስላል።

ቀኑ እሁድ በአራት ሰዓት ገደማ ከቤተ ክርስቲያን መልስ ተናጋሪው የደብረ ቢዘኑ አባ ዮሐንስ ከአዲስ አበባ የተላኩ የአረጋዊ ደብር አለቃ ቦታው የወርካው ሥር የሚናገሩት ንግግር ዓላማ የከተማው ሕዝብ ገንዘብ አዋጥቶ ተጨማሪ የትምህርት ቤት ክንፍ እንዲሠራ ለማበረታታ ነበር።

.......በሰላም ጊዜ ተባባሪ በዘመቻ ጊዜ ጀብዶኛ በጦርነት ጊዜ መንፈስ ቆራጥ የሚያደርግ የወንድነት ሐሞትን የሚያፈላ ያርበኝነት ወኒን የሚያገነፍል የድፍረት

ግመት ያማያሞኘው አንድነት ነው.......» ይላሉ አባ ዮሐንስ ካዘጋጁት ንግግር ጭከ ብለው ለሕዝቡ ሲያነቡ «.......ጐበዝን የሚያሞካሽ የሚያጋንን የሚያስፋፋ እከሌ - እንደ ጥይት ተወርዋሪ እንደ አንበሳ ግርማዊ እንደ ነብር ግልፍተኛ የሆነ፥ ጐበዝ፥ ቁጡ ኃይለኛ የማይደፈር ወንድ ነው የሚያሰኘው......ለሴት አሞት ለወንድ ድፍረት የሚሰጠው አንድነት ነው......» ያነባሉ አባ ዮሐንስ።

ፍሬዋ ከቤተ ሰቦቿ ጋር መጥታ ስለ ነበር ግራ እግሯን እድንጋይ ላይ አሳርፋ ቀኝ እግሯን እሚወርደው ውሃ ውስጥ ነክራ እወንዙ ዳር በመቀመጥ በላይ የላከላትን ግላዊ የፍቅር ደብዳቤ በለኆሳስ ታነባለች

«እስከ ዛሬ ድረስ በተስፋ የቆየህ

ሁነው ልቤ ባሕር መስከረም ይጥባልህ።

እንዳች ያለ ቆንጆ ትንፋሽ የሚያሳጣ

አበድሁ ከነፍሁ ነው ነፍሴ ልትወጣ.....

«.......የሥልጣኔ ኩርንችት የኑሮ አሽከላ የመወያየት እንቅፋት የፍቅር ሻህላ እየሆኑ በጥራዝ ነጠቅነት በተመረዘው ወጣት መካከል እንቁራሪት በሆዱ እንደቋጠረ እባብ ተቋጥረው የሚታዩትን አንዳንድ አጉራ ዘላይ አጥንተ ብልዝ ሰዎች የሚሻለውን መንገድ አሲዞ ከግብ የሚያደርሳቸው አንድነት ነው......

«ዓይንሽ የሚመስለው የብር ጉልላት

ጸጉርሽ የሚመስለው የሃር ጉንጉናት፥

ጥርስሽ የሚመስለው የበረዶ እምብርት፣

ሽንጥሽ የሚመስለው የነብር ጅራት........

«........ሳቅን በደስታ ጭብጨባን በማጒልመሻ ለቅሶን በሐዘን፥ መጒሳቆልን በድህንት ያለጊዜ ማርጀትን በብስጭት ተርጉሞ ከሰው እኩል የሚያራምድ አንድነት ነው......

«ትናንትና ማታ ብዬ ካልጋ ደገፍ፥

የፍቅርሽ ወለምታ ሰበረኝ ወደ እንቅልፍ።

እረ እንዴት ያለው ነው ፍቅር የሚሉት

ሲያወራኝ ቆይቶ ጠፋ በድንገት።

አንገት የምትሆኚ ወዝሽ እጅ ያልነካው፥

ፍቅርሽ በሽታ ነው ልቤን ደነዘዘው።

ስጭኝ መሀረብሽን ለፍቅሬ ትዝታ

ባስታወስኩሽ ቁጥር እንድድን እንዳፍታ......

«.......አንድነት ከሌለ ግን፥ ሳቁ - በጥቃብ በማናለብኝነት፥ በማሽሟጠጥ በማፌዝ፥ በማናካት ይተረጐማል። ጭብጨባው - ቀረ! ቀረ! ተበላሽ! ተበላሽ! አስቀየመ! አጀብ አጀብ፥ ጉድ ጉድ! በሚል ስሚት ተገዝቶ የመደሰቻው ምልክት መቀለጃ ይሆንና አንድ ሰው እንዲያስጨበጭብለት ያሰበው የወጠነው አስጨበጭቦበት ይፈጸማል። ለቅሶው - በስካር፥ በማጭበርበር በማደናገር በጥጋብ፥ ተተርጉሞ እንዲያውም ገፍቶ እይብስና ‹ዞ ልትተናኮል ስትፈልግ እያለቀሰች ትጠጋለች› እንደሚባለው በተንኮል መሠረትነት ይለወጣል። መጐሳቆል ከአያት በቅድመ አያት ዘመን በተሠራ የዘር ግፍ ባገኙ በበለጸጉ ጊዜ በተፈጸሙ እኮያት በልብ ከዬ በተፈጥሮ ጠማማነት የኀጢአት ዋጋ በመሆን ተለውጦ ሲያራርቅ ሲያመናጭቅ ይኖራል። ያለ ጊዜ ማርጀትም - ያለ አቅም መንጠራራት የራስን ልክ አለማወቅ ጋት ሲያሳዩ ስንዝር ስንዝር ሲያሳዩ ክንድ መመኘት የተነሡበትን ረስቶ ለማይደርሱበት መንጠራራት ይሆንና የሰው ልጅ ዕድሜው ለማይፈቅድለት ሥራ ስለ ባከነ - በስሜት አርጅቶ በሐሳብ ረግረግ ተውጦ፥ ሕልማዊ መንግሥትን በመግዛት ከሰውነት መዝገብ ስለተፋቀ - የመጨረሻ ጉደሎ ፍጥረት የሚያሰኝ የሰው በታችነት ስም ይሰጠዋል......

«ብትታዪ ባይሽ የማላፍርብሺ፥

መላእክት በሰይፋቸው አጥረው የያዙሺ

ወተት ከሰማይ ላይ የሚመግቡሺ፥

ለፍቅርሽ ወለምታ ጠበል ያፈለቅሺ

ነይልኝ በሞቴ ልፈውስልሺ.....» ታነባለች ፍሬዋ በለጥሳስ፤ ምንም ዓይነት ለውጥ ፊቷ ላይ ሳታሳይ።

«........አንድነት ነፃነት ነው፤ ነፃነት አንድነት ነው። አንድነት አገር አገር አንድነት ነው። አንድነት መንግሥት ነው፤ መንግሥት አንድነት ነው። ሥልጣኔ አንድነት አንድነት ሥልጣኔ ነው። ሕይወት አንድነት ነው፤ አንድነት ሕይወት ነው። ኀይል

አንድነት አንድነት ኃይል ነው። እንኪያስ የሀገር ማተቧ ከተበጠሰ የሕዝብ እምነቱ ከጐደለ ሀገሪቱም ሕዝቡም አወዳደቃቸው አያምርም ማለት ነው......

«ሳልበላ እንድጠግብ አንቺን አንቺን ሳዩ፥

ነይልኝ የኔ አካል ባይን እንተያዩ።

ብርሃን አንቺ ነሽ የውስጥ አከላት፥

ላዩ የጀምበር ነው ጥንት የመራሁት።

አንድ ቀን ለሁለት እንገንባ ፍጠኚ፥

ቀን ሠርተን ለማታ ብርሃኔ ሁኚ......

«.......አንድነት ነፃነት ነፃነት አንድነት ነው። - አለዚያማ፥ ነፃነት ነፃነት ቢሉት ለአፍ ሞልቶ አንጀት አይደግፍ - ለዓይን ደምቆ ለሰውነት ፍሥሐን አይስጥ - ለጀሮ፥ የራቀ የጠለቀ የጣመ፥ የጣፈጠ ቢመስል ልባችንን አኩርቶ እንዳሻን አያከበሰብስ - ምን ተስፋ ምን አለኝታነት ሊኖረው ይችላል? የለም! ነፃነት አንድነት ነው፤ የግል የጋራ እንደ ፀሐይ እንደ ውሃ እንደ ዓየር - ጌታና ድሃን የማይመርጥ የሚያፍነሸንሽ የሚያንቦላካ - ሌት ተቀን ቀን ከማታ እንዳሰኘ የሚያረካ የሚመግብ - ባጉል ነገር ያልተበረዘ፥ በእስከ - ያልተወሰነ ነው። ነፃነት፥ ሕያው ዘለዓለማዊ ነው፤ ሆኖም በሰማይ ላም አለኝ ብቻ የሰውን ልጅ ደስታ ለመደለል አይሻም.......ታዲያ እንግዲህ እንዴት ይሆናል? እንዴት ምድራዊውን ከሰማያዊው ለማስተባበር ይቻላል......? ሊሆን የሚችለው.......

«ሂድ ሂድ ትይኛለሽ ብሄድ አላፈጥን

ታስፈራሪኛለሽ አልሰማ በድን

ፍቅርሽ ደራሽ ሆነ የድንገት ውጥን፥

ፍቅር የድንገት ነው እንዳለ ሰሎሞን

ነይልኝ የኔ ሆድ እንመሥርት ፍቅርን....... ቀጥላለች ፍሬዋ ንባቧን -

«.......ለማስተባበር የሚቻለው ማግኘትም ማጣትም መደሰትም ማዘን አንድነት ሲሆን ነው። ነፃነትና አንድነት መንትዮች ናቸው። የአንደኛው አንድነትና አድራጐት ከሌላው የተለየም ቢሆን እንደ ነፍስና ሥጋ አብረው የሚሠሩ መሆናቸውን ዐውቀን እንድንሠራባቸው ያስፈልጋል። እንዲህ ካልሆነ ግን ነፃነት ምናልባት ያልታወቀ ትርጉም ይኖረዋል ማለት ነው። ምናልባት ይህ ትርጉም ማለት ያልታወቀው ትርጉሙ፥ ለጥቂት

ሰዎች እንጂ ለብዙዎች አልተገለጸ ይሆናል። ምናልባት ለብዙዎች ሲገልጽ በሽታ ይሆን ይሆናል። ምናልባት እንደ ማር በጥቂቱ እንጂ ሲበዛ ይመር ይሆናል። ምናልባት ይህ ልዩ ትርጉሙ እየታወቀን አያናግር አያሠራ አያበረታታ ደቄውን ተክሎብን ይሆናል - ምናልባት ማን ያውቃል.......» ያስተጋባል ያባ ድምፅ ከጋራ ጋራ።

«ብሄድስ ምን ልድን እንዲያው እኔ ብቻ

የጣትሽን ጌጥ ሳልይዝ ለፍቅሬ መተቻ።

እራብሽኝ እራብሽኝ ጠማሽኝም ከቶ፥

ባይን እንኳ እንገናኝ ሌላው እንኳ ቀርቶ......» የጺወኔም ንባብ ባይኖቿ ብቻ።

«......አገር አንድነት አንድነት አገር ነው። አለዚያማ አገር አገር አይሆንም፤ ውሃው ይመራል - እህሉ ያንገፈግፋል - ዓየሩ የጐመዝዛል - መሬቱ እንደ ረሞጫ ያቃጥላል - የሣር የቅጠርሉ ሽታ ይመርዛል - ሽጥ፥ ሽለቆው ይከብዳል ያስጠላል - ተራራ ሽንተረሩ ያንሽራትታል ያዳልጣል - ኑዋሪውም እንደ አይጥና ድመት እንደ ተኩላና ፍየል ተፋጦ ዕድሜውን በሙሉ ድንግጥ ድንግጥ ፍርግግ ፍርግግ ንቅል ንቅል ትክል ሲል ነጠላ ትከሻ ሆኖ የተጠራበትን ምድራዊ ኑሮ በሕልም እሩጫና በገደል ማሚቶ ዘዬ ይጨርሳል......ይህ እንዳይሆን ታዲያ እንዴት ይከላከሏል? እንደምንስ ራስን ይደልሏል......? አገራችን የጋራችን እንደ መሆኗ መጠን - አያት ቅድም አያት ቅም አያት......

«እቴ በወለዱሽ በናት ባባትሺ፥

ነይልኝ እኔ ቤት አንዳፍታ ልይሺ።

«......ጣርማበር ላይ ሆኖ ይታያል.....» በማለት እየዘፋፈነ በጐዳናው ይመጣል። የወርካውን ሥር ሰው ተሰብስቦበት ሲያይ ዘፈኑን ያቋርጥና «ትውውሼ!» በሚለው ቋንቋ ይቀጥላል - ቀርቃባቸውን እያስተካከለ - መንገድ የለቀቁትን አህዮች ጆሮ ጆሯቸውን እያጠኹ በመመለስ። -

«.......እንዲህ ካልሆነ ግን ከሰው የባሰ አውሬ የለምና እራሱን ስንኳን ለመግደል የማይመለሰው ፍጡር...... ሌላው ቀርቶ ጌታ የሱስ ክርስቶስ እንኳ እንደ ገና ተወልዶ ቢመጣ - ዓላማውን የሚያሰናክልበት ሆኖ ካገኘው - ይሁዶች ካሠቃዩት የበለጠ አይሠሩ ሥራ እንደሚሠራው አይጠረጠርም.....

«......አንቺ በእንጉርጉሮ እኔ በፉጨት፥

አልማዜ እንገናኝ ጀውሃ ጅረት» ሲል ይሰማል ነጋዴው ከሩቁ።

«ታዲያንን! ይህን የሰውን አውሬነት እንደምን ለማስወገድ ይቻላል......? አንድነት ኅይል ኅይል አንድነት መሆኑን በማስገንዘብ ነዋ! እያንዳንዳችን ራሳችንን በዚህ ጐዳና በመምራት አፍንጫ ላይ ብናገኘው.....» በማለት ንባባቸውን ይጨርሱና በኃይል ተንፍሰው ወደ መቆሚያቸው አለፍ እላለሁ ሲሉ «.....ኧረግኝ ዋ የኔ ነገር......ዋናውን ነገር ረስቸው......እንግዲህ ሁላችሁም ለዚህ አንድነታችንን ለሚያጠነክረው ያማራው የጋላው ያዳሉ የእስላሙ ልጅ ለሚማርበት ትምህርት ቤት የያቅማችሁን እርዳታ አድርጉ......በመሬት የሰጣችሁት በሰማይ ይቆያችኋል...... እኔ በበኩሌ ይኸውና ሦስት ብር ረድቻለሁ......» ገንዘብ ለመቀበል ወደ ተዘጋጁት ወደ አቶ ወልዱ ይቀርቡና ሦስት ብሩን ይሰጣሉ «......በነገራችን ላይ የምሥጢር ቤታችን ቆርቆሮ ስላረጀና መቅቀየር ስላለበት የእግዚአብሔር ወዳጆች የሆናችሁ ሁሉ የእርዳታ እጃችሁን እንድትዘረጉልን አሳስባችኋለሁ........ዞሮ ዞሮ በሙሉ ሲበላሽ ጉዳቱ የእናንተ መሆኑን በማሰብ ነው.......

«ካራማራን ዞረሽ ጅጅጋን ያየሽው

እንደልብሽ ኩራት የታል ያገኘሽው...... እያለ ይመጣል ሌላው ነጋዴ አህዮቹን አስቀድሞ -

«በቃሪያ በበርበሬ አትሠራም ዶሮ፥

እንዴት ነው ጅጅጋ ካራማራን ዞሮ......

ይቀጥላል ነጋዴው - ወርካውን አልፎ ከሄደ በኋላ!

ፍሬዋ በተጻፈላት ደብዳቤ ውሀ እየቀዳች ትጫወትበታለች......ሁለት እጅዋ ላይ መበሳሰክ ሲጀምር - ጭራሹኑ ውሃው ላይ መበሳሰክ ሲጀምር - ጭራሹኑ ውሃው ላይ ትለቀዋለች፤ ሳግ - ሳግ - ሳግ - ስጐ ሲያበቃው ቁልቁል - ይመነጠቃል።

«ጣርማበር ላይ ሆኖ ይታያል አጋምበር፥

ልቤን አናወጥሽው አረግሽው ፍር ፍር......» ያስተጋባል ነጋዴው ጣርማበር።

## ፲፫

## አደፍርስ

«ደፍሳ መቼም ዓይነት ዓይነት አለው - ለአጉልም ለበጐም ይሆናል። ለበጐ ምግባር ዓይነተኛ ምልክት ሲሆን ኅብረተሰባዊና ፖለቲካዊ ይዞታ ይኖረዋል። ቤተ ሰባዊ አፍዳሽ፥ የጋብቻን ትልቅነት የመውለድን የማሳደግን፥ አስተምሮም ጠቃሚ ዜጋ ለሀገር የማበርከትን ያህል ደስታ ያለመኖሩን ያወራል። ጋብቻን የማይፈልጉን ያገቡትንም የሚያኪያኪሱትን ሽንጡን ገትሮ ይከራከራል - የሞቀ የደመቀ ንብረት እንዴት እንደሚገኝ ልጆች በታረመ ሁኔታ እንዴት እንደሚያድጉ እንደሚያበለጽጉ የተጠየቀ እንደሆነ - ስሜት በተሞላበት አንደበት ይናገራል.....

«እራሱስ የሚናገረውን የሚሰብከውን ይኖረዋል......?» ይጠይቃቸዋል አደፍርስ አጐቱን አቶ ጥሶን - እጠለላ ቊጭ ብለው የምሽት አየራቸውን ሲቀበሉ -

«አላስጨረስከኝምኮ! አስጨርሰኝ - የሃይማኖት አፋዳሽ ደግሞ አለ......

«እንደ ጧቱ እንደ አባ ዮሐንስ ዓይነት.......!» ያቋርጣቸዋል እንደ ገና አደፍርስ።

.....አስጨርሰኝ! የሃይማኖት አፋዳሽ.....ስለ ሃይማኖት አስፈላጊነት ስለ እምነት ጥናት ስለማይመረመረው የእግዚአብሔር ሥልጣን ስለ መንግሥተ ሰማያት ስለ ገሃነመ እሳት፣.......ስለ ቤተ ክርስቲያን ትልቅነትና መሠረትነት - ስለነዚህና እነዚህን ስለመሳሰሉ ሌሎች ሁኔታዎች በሰፊው ያትትልሃል - ባገኘውኸው ቁጥር ስለሌላ ነገር ጭራሹንም ማውራት አይሻም......

«እኔኮ የሚገርመኝ.....

.......ቆይ ቆይ አስጨርሰኝ.......! እንግዲህ በዚህ ዓይነት መንገድ - የሀገር ፍቅር አፋዳሽ፥ የገንዘብን ፍቅር አፋዳሽ፥ የኅብረተሰብ አፋዳሽ፥ የሥልጣኔ የጥንታዊን ቅርስ አፋዳሽ፥ ትምህርትን አፋዳሽ - ድንቁርናንም አፋዳሽ አይጠፋም። ይሁን እንጂ ከሌላው ከተራ ዓይነት የሚያፋድሰውን ነገር ለይቶ ሳያውቅ ከመቅረቱ የተነሣ ባገኘኸው ቁጥር ማፋደሻውን ከሚለዋውጠው አጉል ወይም አምባልጋ አፋዳሽ ተለይተው የሚታወቁበት መምሪያ አላቸው። - መታወቂያ አላቸው። - ዐዋቂ አፋዳሾች ናቸው.......

«........ዐዋቂም ሆኑ አላዋቂ መቼም ያው አፋዳሾች ናቸው። የሚፈልፉትን በሥራ የማይገልጹ ቢላሾች - የሀገር ሸክሞች - አምባ ገነኖች - አጉሎች......

.......አልተግባባንም አደፍስ፤ መጀመሪያ አስጨርሸኝ። ዐዋቂ አፋዳሾች ናቸው በይሃለሁ። ምን ማለት ነው እንግዲህ ይኸ - ራሳቸው ማፋደሳቸውን ዐውቀው ነው ማለት ነው የሚያፋድሱት። ራሳቸው ራሳቸውን ጭምር መሸንገላቸው ይታወቃቸዋል፤

ሌሎችም ሰዎች እንደሚያውቁባችው ያውቃሉ። ስለዚህ ማፋደሳቸውን የማያቋርጡት ዘበናዊ የሚያሰኝ የኑሮ ግዳጅ ሆኖባቸው ነው.......

«የኑሮ ግዳጅ! የኑሮ ግዳጅ......? አብዬ ጥሶ......

.......አስጨርሰኝ አደፍርስ.....! ለነሱ ደፍሳ፥ የመልካም አነጋገር የመልካም አቋቋም የመልካም፥ አኗኗር በጣም የሠለጠነ የዘበናይ ኅብረተ ሰብ ምልክታቸውና ማስፈራሪያችው ነው። ሰላምታ አሰጣጣቸው ምግብ አመጋገባቸ ስለባበሳቸው አካሄዳቸው ሁሉ ነገራቸው፥ የታቀደና የተመረተ ነው። የነሱ ጐሳ የሆነንውና ያልሆነውን የሚለዩትም በዚህ መለኪያቸው ነው። ስለዚህ ደጉ እንገር ብቻ ይህ ግብዝነታቸው ዘበናይ ነን ብለው በሚያስቡት በነሱው አካባቢ ብቻ ተወስኖ መቅረቱ ነው። እንዲያስ ባይሆን ኖሮ ሌላው ኅብረተ ሰብ ባልተለጐመ ዘመናዊ ፍላት ተቀቀለ ማለት ነበር። በሀብትም ሆነ በደረጃ ከፍ ያሉ ሰዎች ብቻ ስጦታ በመሆኑ ግን ሲያያዝ የመጣው ያብዛኛው ሕዝብ ባህል ተጠበቀ። ላብዛኛው ሰው ልቅ ቢሆን ኖሮ ግን ለመለወጥ ወይም ለመወሰን የሚጥር ኅብረተ ሰብ ስለሚነሣ የተለየ ክብር አጐናጻፊነቱ ተደምስሶ - ሕጋዊ መሆኑ ቀርቶ ባህላዊ አብሮ የመኖር ሥርዓት መሆኑ ቀርቶ ልማዳዊ ይሆን ነበር ማለት ነው። ከፍተኛ ደረጃ ላይ ባሉ ሰዎች በገዥዎች ሲወሰን ግን ባህላዊ ብቻ ሳይሆን ሕጋዊ ልማዳዊ ብቻ ሳይሆን አብሮ የመኖር ሥርዓት ወይም ድንጋጌ ስለሚሆን ከሥራቸው የሚኖሩትን ያርበደብድ ያንሸቀሽቅላቸዋል ነው የምልህ......

«.......እኮ አሁን የምትለው ፍደሳ በጥቂት ሰዎች ብቻ ሲወስን ጥቅሙ ሊኖረው ይችላል። አፍዳሾቹ ዐውቀው ስለሚሠሩበት ከሚያመጣው ጉዳት ይጠነቀቃሉ አይደለም የምትለኝ?

«......አዎ፥ በመጠኑ እንዲያ ነው.......

«ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት......! ታዲያ እሺ፥ ዐውቀውትም በራሳቸው ላይ የሚያመጣውን ጉዳት መከላከል አቅቷቸው ያየህስ እንደሁ? ከጊዜ ብዛት አምነው ያልጀመሩትን ራሱን የሐሰቱን ፕሮፓጋንዳ ሆነው ያገኘሃቸውስ እንደሁ? የሚናገሩትና እናምንበታለ የሚሉት ከሚሠሩት ሥራ ጋር ሲያስተያዩት እንደ ሰማይና ምድር ርቆ ያየኸውስ እንደሁ......?

«እዚህ ላይ መልሱ አጭር ነው፤ አንደኛ አፋዳሽ ለአፋዳሽ ስለሚግባባ የሚነገረው ማንኛውም ፍደሳ ጊዜያዊ እንደ ሆነ ይተዋወቃል - መሳቂያና ጊዜ ማሳለፊያ እንጂ ለአእምሮው ምግብ እንዳልሆነ ያውቃል - እንደ አንገት በላይ ሳቅ ማለት ነው። - ሁለተኛ ከጊዜ ብዛት የሚናገሩት ሐሳብ ምስልም ቢሆኑ የሚናገሩትና የሚሠሩትም

ቢለያይ የሚኖሩበት ኅብረተ ሰብና አካባቢ የተለየ ስለሆነ የውጭ ግለ ሰብእ መጥቶ ንግግራቸውን ከአድራጐታቸው ጋር አስተያይቶ ሊታዘባቸውም ሆነ ሊፈርድባቸው እድል አይገጥመውም - እርስ በርሳቸው ቢሆን ቅድም እንዳልኩት ይተዋወቃሉ - እትዝብት አይደራረሱም......

«እሺ - እኔ ግለ ሰቡ አንተ እንዳልከው ሳይሆን ሰውዬው የተናገረውን ካዳመጥሁ በኋላ በሥራ ላይ እንዴት እንደሚያውለው ለማየት ተከታትዬ የምደርስበት ዘዴ ያገኘሁስ እንደሁ?

«.......አይጠቅምህም - ቀጣፊ ለፍላፊ እበላ ባይ...... አፍበርባሪ የሚል ሕዝብ ነው ዙሪያህን ያጠረህ አንተን። የሱን ሁኔታ የምትቀዳበት አካባቢ የለህም - ኑሮህን የምትደብቅበት ግቢ የለህም። ድንቁርናህን የምትሸፍንበት ሀብት የልህም - ምን አለፋህ ብቻ ተከታትለህም ብትደርስበት - አንደኛ ባገኘኸው ውጤት የሚያምን - ሁለተኛ እንደ ሰውዬው ለመሆን ብትሞክር - ሁኔታህን የሚቀበል ኅብረተ ሰብእ አይደለም የከበበህ ነው የምልህ - ለፍላፊ - እበላ ባይ የሚሉትን ቅጽሎች ነው የምታተርፈው ነው የምልህ.......

«......የለም የለም ጋሼ ጥሶ - የሀገሩ ሰው እውነተኛ ሁኔታ መታወቅ አለበት.......

«......ባጉል ዝላይ እንዲታወቅ ለማድረግና ለውጥ ለማምጣት አይቻልም አደፍርስ......ስለ ሀገሩ ሁኔታ አጥልቆ ሳያውቅ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ወይም በቢሮ ውስጥ ብቻ ይሥራ በመሰለ መላ ምት ተነሣሥቶ ይኸ ይኸ መሆን አለበት ማለት በቂ አይደለም። እርግጥ እንዳልከው፥ የሀገሩ ሰው እውነተኛ መንፈስ መታውቅ አለበት፤ ግን የኔ መታወቅ አለበት ከአንተ መታወቅ የሚለይ ይመስለኛል - የኔ መታወቅ አለበት - የሰው አስተሳሰብ - የኔ ኅሊና የማይቀበለው አጉል ዓይነት እንኳ ቢሆን፥ እሱኑ ጠንቅቆ ዐውቆ ማንኛውም መሻሻልም ሆነ ለውጥ በሱ ላይ መመሥረት አለበት ባይ ነው። ያ ምናልባት ለኔ አጉል መስሎ የሚታየኝ የሕዝብ መንፈስ ዓላማውን ዐውቆ አጥብቆ የሚከተል መሆኑን መርሳት የለብኝም። - በሃይማኖትህ - በንብረትህ - በመሬትህ መጣብህ ብለው - ጋሻውን አንግቦ ጦሩን ነቅንቆ ይነሣል - ግብ አለው። የምትጠጣውን ውሃ የሚመርዝ የምትዘራውን እህል የሚያጠፋ - ደክመህ እቤትህ ስትመጣ የማያስተኛ ሥልጣኔ መጣብህ ብለው - ዓይኑ ደም ጐርሶ ጠመንጃውን አንግቦ ይነሣል - ግብ አለው። ስለዚህ ማንኛውም ለውጥ በነዚህ የመንፈስ አለኝታነት ነው መገልገል ያለበት - አለዚያ የማይበጅን የማይጠቅምን - ውሸት መስሎ የሚገመት ማንኛውንም ነገር ለመቋቋም የሚደረገው ትግል አጉል ይሆናል.......

«.......እኮ በዚህ አስተያየት ኢትዮጵያዊ ፊታችንን ሌላው ዓለም ይወቀው፤ ራሱን የቻለ እንጂ ግልባጭ አለመሆኑን ይረዳው ማለት - ዓላማ የሌለው ነው ማለት ነው......? በሀገር ፍቅር በሃይማኖት፥ ጽኑነት በንብረት አክባሪነት ኩርትም ብሎ በወንድነት በጀግንነት በቆራጥነት በልበ ሰፊነት በእንግዳ ተቀባይነት የዳጐሰው ፊታችን - የአንዱን የእንስሳ ዘር ፊት ከሌላው ተመሳሳይ እንስሳ መለየት እንደማይቻለው እንደ ውሻ ሙርሙር አይቆጠር - ኢትዮጵያዊ መልካችን ይገለጥ - ይመርመር ማለት ዓላማ አይደለም ማለት ነው?

«.......እስካሁን በለፈለፍኩት የገባህ ይኸ ከሆነ ጥፋተኛው እኔ ነኝ። በተራዘሚም መንገድ እንኳ ቢሆን ኢትዮጵያዊ መልካችን ተለይቶ አይታወቅ የሚል አነጋገር በአንደበቴ የገባ አይመስለኝም። ይልቁንም መገለጥ አለበት ብዬ ብቻ ሳይሆን የማምነው የሚያይ ታገኝ ምን ጊዜም እንደ ተገለጠ ነው ብዬ ነው። ንጉሥ ንጉሠ ነገሥት የሚለው የኢትዮጵያ መሪዎች የማዕረግ ስም በሌላው ዓለም በብዛት ከሚሠራበት - ፕሬዝደንት ጠቅላይ ሚኒስትር ከሚለው የማዕርግ ስም ይልቅ የበለጠ ግዳጅን ይጠይቃል። መሠረታችንን አጽንቶ አንድነታችንን አጠንክሮ የነበረውንና የሚኖረውን ፊታችንን አስተካክሎና አዋሕዶ የሚገልጽ መልክ መያዝ አለበት። አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም አንድ ፕሬዝደንት የመንግሥቱ የአስተዳደሩ መሪ ነው። - አንድ ንጉሠ ነገሥት ግን ከእንደዚህ ዓይነቱ ጊዜያዊ መረዳዳት በላይ ነው - ሀገሩና የሀገሩ ሰው ላለው ወይም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሊኖረው ለሚመኘው ኑዋሪና ዘላቂ ለሆነ ባህል - ቅርስ ወግና ልማድ - አስተሳሰብና ስብእና ሁሉ ማንጸባረቂያ ኢትዮጵያዊ ነው። የፕሬዚንደንቱ ወይም የጠቅላይ ሚኒስትሩ የግል ልማድ የግል አስተሳሰብ የልግ አኗኗር ዘዴ ሊኖር ይችላል......ካስተዳደር ሥራቸው ውጭ የሚያሳዩት ማንኛውም ነገር በግላዊ መንገድ ካሆነ በቀር እኔን አይመለከተኝም - የንጉሠ ነገሥቱ የሆነ እንደ ሆነ ግን የራሴም ጭምር ነው። ማንኛውም ዘላቂ ነገር ማንጸባረቂያዬ ስለሆኑ - የሚናገሩትም ሆነ የሚሠሩት ግላዊውም ሆነ ሕዝባዊው ሥራቸው ሁሉ ኢትዮጵያዊነቴ የሚታይበት መሆናለበት። ስለዚህ ስለ ንጉሠ ነገሥቴ አጉል ነገር ለመስማት አልፈልግም። ምናልባት አንዳንድ ለመቀለድ ለማሾፍ፥ ወይም ንጉሠ ነገሥቴን ለማረም ለማኪያኪያስ - ለመንቀፍ የሚነሣ ቢኖርም ወደ ኋላዬ የማልል ጠላቱ ነኝ........

«........ሞትና ሕይወት! እሱን አላጣሁትም፤ ብቻ እኔ የምለው! ‹ቅዳሴ ቢጐድልበት ቀረርቶ ሞላበት› እንዳንባል ንጉሠ ነገሥታችን እንዲያንጸባርቁ ከፈለግን ትንሽ ትንሽ እንድቅማችን ብርሃን እንሁናቸው ነው - እኛ የብርሃን ከያለበት ሲንተገተግ ነው የሳቸው ጸዳል የሚያበራ ነው የምለው.......

« ‹አድላዊ ዳኛ አምጣ ይላል የዶሮ ሻኛ› እንዳትባሉ እንጂ ብርሃን መስጠታቸውም ሆነ ለመስጠት መፈለጋቸው አያጣላንም። - እንዲያውም ሀብታችን እስከፈቀደልን ያህል - ሰውነታችሁን ማንቂያ የሚሆኑ የትምህርት ቤቶች የተከፈቱላችሁ፥ የብርሃንነታቸው አስፈላጊነት ስለታወቀ ነው......

እቤት ውስጥ ወይዘሮ አካላት በገናቸውን መቃኘት ጀምረዋል......አንዳንዴ የሚተክዙ አንዳንዴ የሚያለቅሱ አንዳንዴ የሚለምኑ ድምፆች ይስረገረጋሉ። ግርማዊ ሞገሳዊ መንፈሳዊ ድምፆች ይዘንባሉ......ሰሚዎችን ከወገባቸው ቀና አድርገው አንገታቸውን እንዲያነሡ የሚኮረኩሩ - የልብን ግመት እየቀሰቀሱ የዝናን የመታወቅን ሕልም የሚደባብሱ ይመስላል። እንደ ታፈነ እንደ ታመቀ - ከሩቁ እንደሚስማ ያጀብ ድምፅ እንደ ታዛዥ አድናቂ ዜጋዎች እልልታና ውካታ፥ አውራውን ተከትሎ እንደሚያስገመግም የንብ ሠራዊት.......ያምማል.......ያምማል......የወይዘሮ አከላት በገና.......የሰውን ልጅ ድካና የምግቡን አይደረሴነት የሚያወሳ በመምሰል.......ያምማል......የምማል........ያምማል......ተስፋ እንደ ቆረጠ ልብ አውታር የኅሊና ነውጽ እንደ ተሰማው አፍቃሪ ረዘም ባለ - የተሰነጠበ በሚመስል እንደ ሾህ በሚወጋ እሮይታ በመፈጸም.......

አቶ ጥሶ በኃይል ተንጠራርተው ከመቀመጫቸው በመነሣት ከበረንዳው ወደ ቤቱ ውስጥ ይገባሉ። - አደፍርስም ወዲያው ይከተላቸዋል - ትንሽ ቆይቶ - የሕፃናትን ጫጫታ የልጆችን ጩኸት የሕይወትን ያልታፈነ ድምፅ የሚመስል - ስርግርግታ ከቤት ውስጥ መፍለቅ ይጀምራል......እየደረደረ - እየለዘበ......እያንቋረረ - እየበራ - እየጠፋ.......የአደፍርስ አኮርዲዎን።

በጣርማበር ተራራ ላይ ጥቁር ዳመናዎች ትርምስምስ መሥመር እየሠሩ ይላወሳሉ። ሥሩ ሥሩን - ጫካና ተረተሮቹን እታች ረባዳው ከተማው ድረስ ስስ ወተትማ ጭጋግ አፍኗቸዋል። ኃይለኛ ደረቅ ነፋስ ሳይቋርጥ ይነፍሳል - ቃጠሎ ቃጠሎ በሚል ሽታ - አፍንጫን አብሶ እያለፈ.......

## ፲

## አደፍርስ

ወይዘሮ አሰጋሽ የተቻላቸው እመቤት ናቸው። የሚቹ ባለቤታቸው የሻለቃ ይነሡ ሀብት ብቻ ቀላል አልነበረም፤ ይብ እልጥ አሥር ጋሻ የሚሆን ባገልግሎት የተገኘ የማደሪያ መሬት - ያባታቸው የነበረ ለብቻው ጠጅ የሚያጠጣ ርስተ ጉልት.......በተለይ

በገባሮቻቸው ላይ ግብር የመጨመርም ሆነ የመማር ሙብት ስለ ነበራቸው በውስጡ የሚተዳደሩትን ሁሉ አንሸቅሽቀው የሚገዙበት - (አንድ ጋሻ ብቻ - አንድ ጉንዶ ማር ማስከፈል ሢሶ ማሳረስ ሦስት ዳውላ እህል ማስገበር አምስት ቁና እህል ወፍጮ ማስፈጨት ጐተራ ማስጠበቅ እንጨት ለማገዶ ማስቀረብ ቀላል ነገር አልነበረም) - አንድ ሻምበልና የበታች ሹማምንት የሚያስተዳድር የመንግሥት ሁዳድ.......በጠቅላላው የባሌን ነፍስ ይማር ብለው ሳይጸልዩ የማያልፉበት ሰፊ ይዞታ ነበራቸው።

በራሳቸው በኩል ደግሞ ከነአለቅነቱ ከአባታቸው የወረሱት ርስት ነበራቸው። - ባለቤታቸው በሕይወት በነበሩ ጊዜ በተለይ ባለቅነታቸው ብቻ ቀጥታ ከየምንዝሮቻቸው ከሚይዙት የማርና ዶሮ ግብር ሌላ ይጠይቁት የነበረው ግዳጅ ሀብታም የሚባል ሰው እንኳ የሚቀናበት ነበር - አረም ማሳረም እርሻ ማሳረስ ውቂያ ማስወቃት.......ውሃ እስከማስቀዳት እንጨት እስከማስለቀም ከብት እስከማሳገድ ድረስ። - በተለይማ በእርሻና በዘር ወራት ምንዝሮች ሲባሉ የማያዛቸው ሹም አልነበረም፤ አለቃው ሻለቃው መልከኛው......ሁሉ የኔ ሥራ ይሠራ ባይ ነበር። ስለዚህም የየምንዝሮቹ ሥራ ዞላ እየቀረ ችግር ቤታቸውን ይፈታዋል - ልጆቻቸውን ለረኝነት ሚስቶቻቸውን ለፈጫይና ለፈታይ ራሳቸውን ለግብርና ላጃቢነትና ለተከታይነት ያሳድራሉ። - በመጨረሻም ውቃቢ ርቋቸው የራስን መቻል ኑሮ አንገፍግፏቸው፥ ቤታቸውን ዘግተው ቤተሰባቸውን እስከ መበተን ይደርሳሉ ወይም ጠቅልለው ለሻለቃው አለቃአው ለአለቃው ለመልከኛው ያድራል። -

ባሁኑ ጊዜ ማንኛውም ቁጥጥር ጴጥሮስ በሚባል በቅርብ ረዳታቸው አማካይነት በወይዘሮ አሰጋሽ ሥር የሚካሄድ ስለሆነ አብዛኛው ግዳጅ እየቀረ ሄዷል። እርግጥ አሁንም እቤት ካሉት እረኞች ውስጥ ሁለቱ በግብር የተያዙ ናቸው አባቶቻቸው ግብሩን እስኪከፍሉ ድረስ ሊያገለግሉ የመጡ። - ሆኖም ልጆቹን የተቀበሉት ተለምነው ለነፍሴ ብለው ነበር እንጂ አስገድደው አልነበረ። - ስለዚህ የዱሮ አስተዳደር ይዞታቸው አብዛኛው ቀርቷል። ምናልባት ያልቀረ ነገር ቢኖር ‹እኔን መንገድ ላይ ስታውኝ አትጋፉኝ ሽረር ብላችሁ መንገድ ልቀቁልኝ› የሚለው አስተሳሰባቸው ይሆን ይሆናል።

ዛሬ ከአዲስ አበባ የወረዱትን የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች የሚጋብዙበት ቀን ስለ ሆነ - ዝግጅቱ ከሌሊት ጀምሮ በመጣደፍ ላይ ነው። ጴጥሮስ የሀብታቸው ሁሉ የበላይ ተቆጣጣሪ ሠርግና ምላሹ ሆኗል። ከቁመናው ሰፋ ብሎ የወጣ ሹል ግምባር ጥርጣሬ የተሞሉ ትንንሽ ዓይኖች ልል ጉንጮች ያሉት ኩርፋ ፊት እምሳይ ቢሆንም አጋጊጦ

ከወዲያ ወዲህ ተፍ ተፍ ሲል ሲያውት በቤቱ ያለው እሱው ብቻ ነው የሚመስለው። ሸር ጉድን ከመጠን በላይ ይወዳል፤ በተለይ እንደዚህ የዛሬው ዳኞች በሚጋበዙበት ጊዜ ዙሪያውን ሲያንጃብብና ጠብ ርግፍ ሲል መታየት ልማዱ ነው። ደረጃውን የማሳየት ፍላጐት ይጠናበታል። ራሱን ቢያከብሩት ባያከብሩትም እምብዛም ደንታ ያለው ስለማይመስል እሱም ሁኔታው ካላስገደደው በቀር ሌላን ሰው የማክበር ልማድ አይታይበትም። ውርደት የፈለጉትን ማጣት እንጂ ፍላጐትን ለማግኘት ሲባል የሚደርሰው ርግጫና ግልምጫ አይደለም ባይ ነው። - በመክሊታዊነት ላይ የተመሠረተው እምነቱ ዘለቄታ ያለው የመኖር ፈትሕ ሆኖ አግኝቶታል። -

ወይዘሮ አዘጋሽ፥ እንደ ሌሎቹ ሠራተኞች ሁሉ ማልደው ተነሥተው ነበርና አሁን እወርዶፋ ጐጆ በር አጠገብ እግርምቡድ ላይ አረፍ ብለዋል። - በትከሻቸው ላይ አንገት ልብስ ጣል አድርገው። በጃቸው መታረሪያ ዓይነት የቀጨሞ እንጨት ይዘዋል። - ከአሥር ወይም ከአሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜ በላይ የማይሆነው ወንድ ልጅ የጸጉራቸውን አናት ቀስ እያለ የንድፍላቸዋል - በደጋን ብን ብሎ ወደ ላይ እንዲጨፈቅ። አንዲት ኮረዳ ጫማዎቻቸውን አጥባ ጨርሳ ጥፍራቸውን ታስተካክላለች። ሥጋቸው ቆንጠር በማድረግ ታሳምማቸዋለች መሰለኝ፥ ራሷን ቋ ይሰጧታል እንደዘበት - መታረሪያው።

እንግዶቹን የሚቀበሉበት ዋና እልፍኛቸው በሚገባ ተዘጋጅቷል። በየማዕዘኑ ሦስት መሶበ ወርቆች ቄጭ ቄጭ ብለዋል - እስከየግርጌ እስከየግርጊያቸው የሚጀቡን ጃኖ ለብሰው። አጠር ያለ የሳጠራ ገበታ መካከል ገደማ ተዘርግቷል፤ ባንድ ፊት ባለመቀመጫና ንቅሳታም ሸክናዎች ባንድ ፊት ብርጭቆዎች ተደርድረውበታል። በአንድ ሰታቴና በሁለት አነስ አነስ ያሉ ድስቶች የሚቁላላው ሽንኩርት ድልህና ቅቤ - በምሶሶው ዙሪያ የተሰቀልው ጮማ የሆነ ትኩስ የሙከት ሥጋ - በመካከለኛ ጋን የተሰየመው የሚሰነፍጥ አዲስ የተቀዳ የማሽላ ጠላ ውሃው ያልረገፈ ትኩስ ታጮ የተጐዘጐዘው ሣር - ዝናብ ካጨቀየው በረት ውስጥ እየተግፈጠፈጠ የሚነሣው ያዛባና የከብት ሽታ - አንድነት ሆነው ልብን ናድ ናድ የሚያደርግ ዓይነት ዓየር ሰጥተውታል ለእልፍኙ - ነፍስን ወደ ላይ ጐትቶ እጐሮሮ ውስጥ የሚወትፍ ውደት......

«......እንግዲህ የማስተናገዱን ነገር ባንተ ትቸዋለሁ» ያልሉ ወይዘሮ አሰጋሽ ለጴጥሮስ ታጥበው ተበጥረው ተኩለው አጊጠው ከጨረሱ በኋላ - የእልፍኙን ውስጥ ዝግጅት አንድ ባንድ እየተመለካከቱ «........ስለ ክትፎውና ስለ ቁርጥ ሥጋው ስላልጫው፥ ስለ ቀይ ወጡና ስለ ፍትፍቱ እኔም ቄሱ ነኝ አላስቸግርህም...... ስለዚህ ‹ስላሮቶ› ለጋ ጥብስ ብስል ጥብስ ስለምትለው የፈረንጅ ቅርንጥህ ነው ትንሽ ግራ ገባ

ያለኝ....... ደሞ ምንድነው ያ ሌላ ነገርህ ‹ዎሞሌ› ነው ምንድነው የምትለው? ስለ ዕንቁላል.......አዎ እሱ እሱን ባንተ ላይ ጥየዋለሁ.......ጣጣ ነገር በፈረንጅ ስም ካልተጠራ በቀር ሥልጥንና አይደለም የሚሉ ፈሊጥ። - አንድ አዲስ ነገር አናይበት ተሠርቶ ሲቀርብ.......እስኪ ላንተም ይታይህ......አሁን ጤፍ እንጀራን በፈረንጅ አፍ ብትጠራው ባበሻ አፍ.......እርቦኝ ከፈለግሁት ዘንዳ ልተወው ማለት? ጤፍ ያው ጤፍ ነው ውላጂ - በማንም አፍ ከተናገርከው መልኩንም ሆነ ጣሙን አይለውጥም - ራብ ብቻ ሁሉንም አጣፋጭ - ሌላው ዘበት ነው...... እና ታዲያ ሁሉንም ነገር ልቤ እያወቀው ነው እንደ ብጤህ ያልኩት......

«እኔ መቼም በምን በኩል ነኝ የምይረዳቸው ቢዩ ሳስብ መጀመሪያ በጀርዩ ወሬ የምሰማቸው የነበርኩ ልዩ ልዩ የምግብ ስም ትዝ አለኝ...... እኛ ባላገሮች እንዳይመስል...... የዛሬ ሊቃውንት ጨረቃ ደርሰው ሕይወት መኖሩ አለመኖሩ መርምረው እንደ የምኖራት መሬት እንዲጠቀሙላት ብዙ ጣር ችግር ያሳልፋሉ......በፈረንጅን አፍ መናገር ክብር አለው፤ ግን ጨረቃ ላይ መውጣት አይሆኑም......ዳኝኖች ካቀረቡላቸው ሆዳቸው ሳይሞሉ አይተውም፤ ዐውቃለሁ። ሆኖም ለመለየቱ ስል በፈረንጅ አፍ እንድናገር ጎሊናዩ ይገደደኛል......

«ጥሩ ነው፥ ጥሩ ነው በፈረንጅ አፍ ታናገራቸዋለህ.....

«እመየቴ ክፉ ያደርግ አለ እንዳይሉኝ.....

«ምን ቆርጦኝ....... ክፉ አሳቢን ክፋቱ ይጣለው..... ብቻ ያፍክን ብዛት ጠላሁቲ - ክፉ ያደርጋልስ አልልም..... ባይሆን እፊት እፊቴ ሲሆን ባበሻ አፍ ብትናገር ደስ ይለኛል.....

«እኔ ትግሪኛ ትግረ፥ እችላሎህ፤ እርሶ አይችሉም..... አማርኛ ለኔ ያስቸግራል....... የርሶ እናት ትግሬ ናቸው...... እርሶ ለምን ትግሪኛ አይችሉም?

«የጠራች መንዜ ናት የኔ እናት.....

«ወንድሜ እናቴ ትግሬ ናት ብሎኛል!

«የሱ እናት ርግጥ ትግሬ ነበሩ....... በናቱ ወጥቶ ነው ባሕር ማዶ ለባሕር ማዶ ሲንከራተት የኖረው...... ባባታችን ነው ከወልዱ ጋር የምገናኘው.....

«እኔ....... እኔ አላወኩም ነበርኩ......!

«እና ታዲያ እንዳልኩህ ማስተናገዱን ባንተ ትቸዋለሁ..... የከተማ ሰው ዐመሉ አይታወቅምና በዘዴ በዘዴ አድርገህ እንድታናግድልኝ...... አዎ ይኸው ነው......ጺወኔንና ሮማንን ጥራልኝ...... እንግዲህ መምጫቸው ደርሷል፤ አፋፍ ወጥተህ ብትጠብቃቸው......

«ለመውጣት ቢዬ አስቤ ነው ለመሄድ ያሎህ.....

«አዎ ጥሩ አስበሃል......» ወደ ምድጃው ጠጋ ብለው ማማሰያቸውን ደኅና አድርገው ካጠቡ በኋላ አልጫውንና ቀይ ወጡን እያጠቀሱ ወዳፋቸው በመውሰድ ሲቀማምሱ እነ ጺወኔ ይገባሉ። እንደገቡም «...... ሮማኔ እንግዲህ እንደነገርኩሽ የክት ልብስሽን ለብሰሽ በሚገባ ታደገድጊና እበርጩማዬ ኋላ ትቆሚያለሽ...... ያንን ያይንሽን መቃዠትና አሥረይዬ ምራቅሽን መዋጥሽን ኋላ አደራ...... ጺወኔ መቼም ነግሬሻለሁ...... ባይነት ባይነቱ - እንጀራ ሲያልቅ እንጀራ...... ፍትፍት ሲያልቅ ፍትፍት...... እፊት እፊታችን..... እፊት እፊታችን..... ማቅረብ ያንቺ ፈንታ ነው። - እቃ ማጋጨትና እግር ማማታት - እሰው ላይ ማንጠባጠብ - በሰው ትከሻ ላይ ማምጣት - ቢያናግሩሽም አፍሽን ሳትሸፍኚ መናገር..... አደራሽን እንዳላይ - ጥንቅቅና ኩስትር እንድትይልኝ..... ምናልባት ያጐረሱሽ እንደሆነ አፍሽን በትንሹ ከፍተሽ - የሚበልጠውን በጅሽ ደገፍ አድርገሽ መቀበል አለብሽ - አዎ! እንደ ሥራ ቤቶች ባፍሽ ሙሉ እንዳትቀበይ......» እያሉ የመጨረሻ ምክራቸውን ያቀርባሉ። -

ከቤት በታች ወደ ወይዘሮ አሰጋሽ ቤት ወደሚያወጣውና ወደ ማፉድ እሚያወርደው መንታ ጐዳና መገናኛ ጥቂት ሰዎች ያመራል። በቃሬዛ በሽተኛ ተሸክመው፤ አንድ ጥቁር እብግ እየጐተቱ። ጊዜው አንድስቅጤና ተልከስካሽ መንገዱን ይዞታል ተብሎ የሚታመንበት ከባድ ተሲያት ላይ ነው። እነ አቶ ጥሶ በሻገሩ እሚገኙ ጉባ ላይ ብቅ ይሉና ወደ መንታው መንገድ ያሽቆለቁላሉ። ባለ ቃሬዛዎቹ ጥቁሩን በግ፥ በታመመው ሰውዬ ዙሪያ ሦስት ጊዜ ያዞሩና በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ያርዱታል - መንታው መንገድ መገናኛ ላይ እንደ ደረሱ። በደሙም፥ የመስቀል ምልክት፥ እበሽተኛው ግምባር ላይ ያደርጉና በጥድፊያ ቦታውን ለቀው ወደ መጡበት ይመለሳሉ።

በጉ ይንፈራፈራል፤ አቶ ጥሶ እቦታው ይደርሳሉ። ‹ዕድላችን ነው!› ይሉና ከኪሳቸው ሴንጢ አውጥተው የበጉን ጆሮ ይቀነጥቡታል - በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም - አሽከራቸውንም ዕድላቸውን እሚሄዱበት ቤት እንዲያመጣ አዝዘው መንገዳቸውን ያቃናሉ። ባላቦረንትቾች ወደ ጭዳው መለስ አላሉም፤ ቦታውን እንደ

ለቀቁ ሤጣኑ መጋበዙን ይጀምራል። - በሚጋበዝበት ጊዜ ደግሞ ጋባዦቹ መለስ ብለው ካዩት ሕመምተኛውን የለቀቀው በሽታ መልሶ እንደሚይዘው ያውቃሉ።

አቶ ጥሶ ወደ ወይዘሮ አሰጋሽ ቤት የሚያወጣውን አቀበት ሲያያዙት ጴጥሮስ ይደርስና እንዳገሩ ደንብ፥ አደግድጐና እጅ ነሥቶ ይቀበላቸዋል።

## ፲፫

# አደፍርስ

የአቶ ጥሶ አሽከር እንደታዘዘው በጓን ይገፍና በቅጥ በቅጡ ካደረገ በኋላ ሥጋውን በቆዳው ጠቅልሎ መንገድ ይገባል። የወይዘሮ አሰጋሽ አሽከር የሆነ መንታው መንገድ አቅራቢያ ጥጆች ያግጥ ስለ ነበረ በቀዬው አይቶት የማያውቀው ሰው ያደርገው የነበረውን ሁሉ ተደብቆ ተመልክቶ ነበርና መጨረሻውን ለማየት ብሎ ቀስ እያለ ኋላ ኋላው ይከተለዋል። ወደ እመቤቱም ግቢ ማምራቱን ሲያይ ያቆራርጥና ቀድሞ ደርሶ አቶ ጴጥሮስን ከተፋፋመ ግብግቦ ከደራ ጨዋታ ላይ አስጠርቶ፥ የጥቁር እንግዳውን መምጣት ይነግረዋል። -

«.......ኢትዮጵያ ምን ጊዜም ቢሆን ጠባቂ አላጣችም..... ጥንት በሕገ ልቡና ቀጥሎ በሕገ ኦሪት ኋላም በሕገ ወንጌል ባዲሱ ዘመንም በሕገ መንግሥት የተጠበቀች ነች........» ይላሉ አባ አዲሴ የወይዘሮ አሰጋሽ ነፍስ አባት...... ከአደፍርስ ጋር ክርክር ገጥመው አይተውት አይቀጥሉት ነገር ሆኖባቸዋል። እንደ መንቀፍ እንደማጐዘልም፥ እንደማኪያኪያስም ይሻቸዋል ያደፍርስን ንግግር። - አደፍርስ በበኩሉ በሞቀና ስሜት በተሞላበት አንደበት ይናገራል...... ሐሳቡ ሁሉ ብዙን ጊዜ ያሰበበትና አውጥቶ ያወረደው ያሰላሰለው ይመስላል...... የስሜቱ ክፍል እየተቦጨቀ እንደሚወጣ ዓይነት......

«ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት! እኔ የምለውኮ ጠባቂ አጥታ ነበር አይደለም። - በዚህ በሀያኛው መቶ ዓመት ላደረግነው ግሥጋሤ ቅድምና የለውም፤ የድሀውም የሀብታሙም ልጆች፥ እብኩልነት ደረጃ ዕውቀትን ሹመትን መታወቅ ያገኙበት ዘመን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አልነበረም - የመጀመሪያ ጊዜው ነው ነው የምልዎት...... ኢትዮጵያ እጆቿን ሰብስባም ሆነ ዘርግታ ያልተቀመጠችበት - በርግጥ በሚታይ በሚጨበጥ በሚገባ መንገድ መሥራት የጀመረችበት ጊዜ ነው የምልዎት...... ኢትዮጵያ እንደ ግመል ሽንት ወደ ኋላ መሄዷ ቀርቷል - ወደ ፊት በመገሥገሥ ላይ ነች ነው የምልዎት...... እንዴት ብዬ ልንገርዎት ይሆን?» ይመልሳል አደፍርስ።

ጺወኔ ብዙ ጊዜ አሳላፊነቷን እየዘነጋች አፍ አፉን ትመለከተዋለች። አንዳንዱ ይገባታል፤ አብዛኛው አይገባትም። - ገባትም አልገባትም ግን ከሰውነቱ የሚፈልቀው በቃላት ሊገለጽ የሚተናነቀው የአደፍርስ ስሜቱ እየገነፈለ ወጥቶ እንደ ዳመና ግላጭ ድርቅርቅታ ደሟን ሲንደው ይሰማታል። በአደፍርስ በኩል ቢሆን ግን መኖርና አለመኖሯንም ያጤነው አይመስል፤ ተስቶት እንኳ ወደ እሷ እየተመለከተ አላወራም - እንጀራ እንኳን እየቀረሰች እፊት እፊቱ ስታደርግላት። - ያለወትሮዋ ነደድ ነደድ ሊያደርጋት ጀምሯል ጺወኔንም ‹ከከመ ጤፍም አልቆጠረኝ..... ገረድ መስዬው ይሆናል...... ቢሆንስ እንዴት አንዴ እንኳ ተሳስቶት አያየኝም......› የሚሉ የሐሳብ ነጸብራቆች ይፈልቁ ይጠብቁታል።

« ‹ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር› የሚለውን ቅዱስ ቃል ለማጒዘል ነው መሰለኝ አነጋገርህ....... ያልያዝኩልህ አይምሰልህ....... እንኳን ይችንና የዝንብ ጠንጋራም እናውቃለን...... ኢ. ሄ. ሄ. ሄ - የትና የት! ሰማሆይ ‹ኢኮነ ሠናየ ነሢአ ኅብስተ ውሉድ ወውሂብ ለለባት......› የልጆቹን ኅብስት ለውሾቹ...... ኢትዮጵያ ታዲያ ምን ተጠቀመች....... የማንንም እከሌን የማይባል ልጅ ሰብስበው አይደለም እንዴ ንጉሡ መከራቸውን የሚያውት......?

«ሞትና ሕይወት......! ይስሙኝ አባ የእልህ ሳይሆን እየተደማመጥን እናውጋ...... እግዚአብሔር ማንኛውንም ሰው በምሳሉ ነው የፈጠረው። - ጥበብን ለማግኘት የእከሌ ልጅ ተብሎ መታወቅ የሚያስፈልገው ነገር አይደለም፤ ጤነኛ ሰውነትና የሚያስብ ጭንቅላት ነው የሚያስመርጠው። - ምነው! ‹ከናንተ ማህል ከፍ ከፍ ለማለት የሚሻ ቢኖር ራሱን ዝቅ ዝቅ ያድርግ› ...... ‹እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ማህል መሪና አስተማሪ ለመፍጠር ይችላል› ተብሎ የተጻፈውን ቅዱሳዊ አነጋገር ወዴት ያንጓልሉታል...... የለም አባ - የነገርን አንድ ፊቱን ብቻ አይመልከቱ። ቢያስጠላዎትም እንኳን ሌላውንም በኩል መመልከቱ አይከፋም.....

«...... ምነው ታዲያ ቢሆንስ - ከሰውምኮ ሰው አለው፤ ‹ከእንጨት መርጦ ለታቦት ከሰው መርጦ ለሹመት› ሲባል አልሰማህም የኔ ልጅ...... አሁን ለምሳሌ - አሽከሮቼን ገና ለገና በዝጌር አምሳል ተፈጥረዋል ብዬ ከኔ ጋር እኩል ናቸው ልል ነው? የለም የኔ ልጅ ዙሪያንም አካባቢን እያዩ ነው ጭዋታ......» ወይዘሮ አሰጋሽ ጣልቃ ይገባሉ።

«እረ ከወዴት! ሁሉ ሰውማ እኩል ከሆነ የሱስ ክርስቶስ ራሱ መቼ - «ሀቡ ዘነጋሢ ለነጋሢ› ይል ነበር?» ይቀጥላሉ አባ።

«ሞትና ሕይወት! የሱስማኮ የቁሣሩ ምስል ያለበትን ለቁሣሩ ብሎ የተናገረው ሕዝቡ ለመንግሥቱ ይከፍለው የነበረውን ግብር እንዳያገባ ይሰብካል ብለው እንዳይወነጅሉት ነበር እንጂ - ቄሣር ያልሆነ ሰው በገንዘቡ እንዳይጠቀምበት ለማለት አልነበረም» ይመልሳል አደፍርስ።

«ትውልድ ዕሉት ወዘማ! የዛሬ ዘመን ልጆች ምናችሁም አያምረኝ...... ‹ነስሐ በእንተ ዘገብሮ ለስብእ› ተብሎ የተነገረው አምላካዊ ቃል በእንደ እናንተ ያለው ላይ ነው.......

«ታዲያ እኛ የዱሮዎቹ ከዛሬዎቹ እንበልጣለን ማለትዎ ነው እንዴ አባ?» ይጠይቃሉ አቶ ወልዱ። - አቶ ጥሶና አቶ ክብረት ዝም ብለው ያዳምጣሉ። - ለሁለቱም ተከራካሪዎች የሚጠቅም ማቃኛ አስተያየት ሊኖራቸው ሲችል ለጊዜው ምንም ዓይነት ሐሳብ ሊያቀርቡ የፈለጉ አይመስሉም። - ሁለቱም ተከራካሪዎች ሊሰሙና ሊያሰሙ እንጂ ሊማሩና ሊያስተምሩ የፈለጉ ዓይነት በቅን መንፈስ የተነሣሡ ለመሆናችው የሚገልጽ የሐሳብ መለዋወጥ ይዘው የቀረቡ መስሎ አልታየም።

«ባንበልጥም አናንስም......» ይመልሳሉ አባ።

«እርግጠኛ ነኝ ከዱሮዎችም ሰዎች ዐዋቂና ደንቆሮዎች ከዛሬዎቹም እንዲሁ አይጠፉባቸውም......» ይቀጥላሉ አቶ ወልዱ።

«እሱማ ‹እምፍሬሆሙ ታአምርዎሙ› - በፍሪያቸው ታውቋችሁ ተብሎ የለም - እርግጥ ነው፥ ከሁሉም ብስልና ጥሬ አይጠፋም.......

«ታዲያ - ‹አብን ዘመነንዋ ነደቅት ወይእቲ ኮነት ውስተ ርእሰ ማእዘንት› ንም ይጥቀሱ እንጂ ለምን የዘመኑን ልጆች ዘማዊነት ብቻ ያጕድሉታል.......?

«ጊዜው ነውኮ! ጊዜው ስምንተኛው ሺህ ባይሆን ኖሮ ‹ይከውኑከሙ ለዕቅፍት› ተብሎ ይንገርባቸው ነበር? የለም ግዴለዎም ጊዜው ነው......

«አሄ.......በጊዜውም ማመካኘት አይበጅም...... የተነገረውንም ቅዱስ ቃል - ቃል በቃል መውሰድ ቤተክሲያንን ከልጆቿ ይነጥላታል እንጂ አያቀራርባትም......ሰሙኞይ.....?! ለመሆኑ ‹ይቀልል ይኀልፍ ገመል እንተ ስቊረተ መርፍእ እምባዕል በዊአ መንግሥተ እግዚአብሔር› ን ቀጥታ ከተረጐምነው የትኛው የነጋሢ የትኛው የመስፍንና የትልቅ ሰው ልጅ ነው መንግሥተ ሰማያት የሚገባው? ሀብታም የሆነን ሁሉ ለሲዖል ዳረግነው ማለት አይደለም?» ይቀጥላሉ አቶ ወልዱ።

«አዎ በዚህ ጥቅስ መሠረት እከሌን የማይባሉ ልጆች ብለው የጠቀሷቸው ናቸው ማለት ነው መንግሥተ ሰማያትን የሚወርሷት.......» ጣልቃ ይገባል አደፍርስ፥ አባ አባን እየተመለከተ።

ካጥር ውጪ ከፍ ያለ ጭቅጭቅ ተፈጥሯል። ያቶ ጥሶን አሽከር እስከተሸከመው የበግ ሥጋ ይዘውታል። በእመቤታቸው ላይ ጭዳ ሊጥልባቸው የመጣ መስሏቸው በጡጫና በጥፊም አቅምሰውታል። በኋላ ነው እነ ሮማን ፍሬዋን ከሚያስተናግዱበት ከወርዶፋ ጐጆ ወጥተው መጥተው ጉዳዩ የተገለጸው። - ፍሬዋ ሁኔታውን በሙሉ ታስረዳቸዋለች።

«......ቢሆንም የቦረንትቻ ሥጋ እመቤቴ ግቢ አይገባም፤ እነሱን የለቀቃቸው በሽታ እኛንም ከብቶቹንም ነው የሚጨርሰን» ይላል ወርዶፋ አለቅጥ በተጨነቀ አነጋገር።

«እንዲያ ከሆነ እንግዲያው እኔ እዚህ የምቆበት ምክንያት የለም፣ ደብረ ሲናዬ እመለሳለሁ...... እንዲያውስ ምን የምቆይበት ምክንያት አለ......» ቁርጥ ባለ ቃል ተናግራ መለስ ልትል ስትል - ወይዘሮ አሰጋሽን ሮማን ትጠራቸውና

«ምንድነው ነገሩ? የምን የቦረንትቻ ሥጋ ነው ደሞ እኔ ግቢ የሚገባው? በክርስቲያን ደንብ የተባረከው መቼ ጠፋና...... ቢያስፈልግ ሌላ ሙክት እናርዳለን......» እያሉ ፈገግ ኮስተር በማለት እየተናገሩ ይመጣሉ።

«እኔ የእርስዎን ሙክት አልፈልግም...... ፈቃድዎ ቢሆን ለብቻዬ ቢት ይፍቀዱልኝና የቦረንትቻውን ሥጋ በመብላት ብቻ ሲይዘኝ እስኪ ሊያው ይችላል!» በማለት ትቋቋማቸለች ፍሬዋም።

«ብኖር አይደለም ለማየት የምችለው? - የለም የኔ ልጅ...... ሁሉ ነገር ሞልቶ ተርፎ፥ የሰው ጃኒ እግቢዬ አስገብቼ መከራዬን አላይም.....

«እንግዲያው ይፍቀዱልኝና ወደ ደብረ ሲናዬ ልመለስ..... ምን ያደርጋል አጉል ሐሳብ ከምሆንብዎ ይሻላል......

«እኔ ምን አግብቶኝ ወዳጄ? ደሞ የመፍቀዱ ጋጋታ! ምን ቢገደኝ! አባትሽን ጠይቂና እንዳፈተተሽ ልትሆኚ ትችያለች......

አባ አዲሴ አቶ ጥሶ፥ አቶ ወልዱና በላይ የጭቅጭቁን መካረና ይሰሙና ይወጣሉ። -

«....... ልጅዎን አንድ ይበሉን..... የቦረንትቻ ሥጋ እዚህ ግቢ ካስገባሁ ብላ ደብረ ሲና እወጣለሁ እያለች ታስፈራራለች› ይላሉ ወይዘሮ አሰጋሽ ውዴታና ልመና በተመላበት ዓይናቸው የፍሬዋን ዓይን ዓይኗን እየተመለከቱ።

«ምናለ ታዲያ ትውጣ! ለመቆየት ብትፈልግ ያገሬውን የቀየውን ደንብ ተከትላ ትቆይ! አለበለዚያ ድግሞ እምቢ ካለች መሄዱ የራሷ ፈንታ ነው.....» ይመልሳሉ አቶ ጥሶ ዝግ ባለ አንደበት።

«እንዴት ብለው አንድ ልጅዎን መረን ይለቃሉ? በዚህ ባጉል ነገር የተለከፈች እንደሁ ጠጠቱ የማነው?» ይጠይቃሉ ወይዘሮ አሰጋሽ - እናታዊ በሆነ የፊት አየርና አነጋገር። -

« ‹አምፍሬሆሙ ታእምርዎሙ› የዛሬ ዘመን ልጆች የናት፥ ያባታቸውን ትእዛዝ አይፈጥሙ - ራሳቸው የሚያደርጉትን አያውቁ ነገራቸው ደረቅ ዕድሜያቸው አጭር......» አባን ሁኔታው ያናደዳቸው ይመስላል።

«ፍሬዋ የምትሄድ ከሆነች እንግዲያው እኔም አብሪያት እሄዳለሁ። እኔም እንደ እሷ የቦረንትቻው በግ ሥጋ እዚህ ቤት የማይገባበት ምክንያት አይታየኝም......» ሳይታሰብ ድንገት ቀደም ይልና በላይ የፍሬዋን ሐሳብ ይደግፋል።

«አንተ ደሞ ምን ትባል ይሆን አሳራችን...... ያየሁት አይቅረኝ ነው? አንተንስ ማሸነፍ አያቅተኝም..... አባትህን፥ ወልዱን እንኳን እሥሬ አግብቼዋለሁ...... እንኳን አንተን....

«እንግዲያው ፍሬዋ ከሄደች እኔም በመሄዴ ቆርጫለሁ ይወቁት......

«ወልዱ ምን ዝም ብለህ ታየኛለህ እኔን! ይኸን ሁሉ ገብ ልጅህን አንድ አትለኝም......?

«አይ መቼስ እንግዲህ ካንቺ ሙከት የቦረንትቻ በግ ከበለጠበት ምን ማድረግ ይቻላል? እንደምታውቂው የዛሬ ልጆች የራሳቸው አስተሳሰብ አላቸው፤ እኛ ባልናቸው አይሄዱም...... እና ምን ላርግ ትይኛለሽ......?

በላይ በላይን እያዩ «.......ሁለተኛ ብቻ አክስቴ ብለህ ቁልቁል ሰበር ሰካ እንዳትሊ ዛሬስ፥ መቼም ሠለጠንሁ ብለህ አምልጠሃል - ባንተ ቤት......! አንቺ የኔ ልጅ.....ፍሬዋ ብትሆኝ....... ልቤ ወዶሻል፤ ዓይንሽን እንኳ ሙሉ ለሙሉ አይቼ ሳልጠግበው አንድ ሁለት ሳንነጋገር ልሂድ በማለትሽ ባዝንብሽ አይከፋም - እውነቴን ነው እምልሽ እንዲህ ባንደዜ ሰውን አይቼ እንኳን ወድጄ አላውቅም..... ጥሎሽ ሆነሽብኛል። - ብቻ ምን

ያደርጋል ቦረንትቻውን እንድታስገቢ ልፈቅድልሽ አልችልም...... እኔ እንኳን ልቤ ቢፈቅድ ይኸ የምታይው አሽከሬ ሁሉ ነው ጥሎኝ እብስ የሚለው......በስንት ዓይነት ቋንቋ የሚናገረው ጴጥሮስ እንኳ ቢሆን......ለነፍሱ የማይፈሪ ሰው የለም እንደምታውቂው.......» ፍሬዋ ወይዘሮ አሰጋሽ ሳያስቡት ድንገት ወዳጠገባቸው ሮጥ ሮጥ በማለት በሁለት እጆቿ አንገታቸውን አቅፋ አፋቸው ገደማ ሳም ታደርጋቸውና በቀረበችበት ዓይነት መለስ ብላ ወደ ነበረችበት ታመራለች።

«እንዲህ ያለች ልጅ?! ቍንጥርጥር ያለች...... ከኔ ጋር ውላ ብታደርግ ልቤን በሙሉ በወሰደችው...... ጣጣ ነው እባካችሁ......እባካችሁ........ውዴታ የሚሉት ነገር የማይቆጣጠሩት.....

« ‹ቅንዑ ለእንተ ተዐቢ ጸጋ› ብሎ የለም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ። - ሃይማኖትን ተረክን ልማድን ወግን፥ በጠቅላላው ባህልን የመሰለ ክብረ ሰብእና ሲነካ የሚወደውን ነገር የማይሠዋ የለም ‹ኢመሀኮ ለወልድከ እምኔየ› አንድ ልጅህን እንኳን ከኔ አልደበቅኸውም - ለመሥዋዕት አቅርበኸዋል ተብሎ ለብርሃም የተነገረው ዛሬም ለእናንተ ቢነገር አይገምርም...... እግዚአብሔር በመለኮትነቱ ንጉሥ በመንግሥቱ ጐልማሳ በሚስቱ ቢደርሱበት እንዳይወድ - በለምለም መሬቱ በነፃነት ሀብቱ በጸናው መንግሥት በተደላደለው ንብረቱ በሚያምንበት ወግና ልማዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢደርሱበት አይወድም...... እና እግዚአብሔር አስመልክቶሽ ያደረግሽው ሁሉ በሚገባ ነው.... እነሱንም እመንገድ የሚገቡትን እሱ የልብን ዐዋቂው አምላክ አቅፎ ደግፎ በደኅና እቤታቸው ያግባልን...... አቡነ ዘበሰማያት..... አንችንም ‹እግዚአብሔር ልዑል ይባርክኪ ወያርኢ ገጾ ላዕሌኪ› ቡርክት ሁኚ..... የጳጳሳቱ የቀሳውስቱ የመነኮሳቱ የነገሥታቱ የመኳንንቱ በጠቅላላው የቅድስት ሀገራችን ሕዝብ ጸሎት፥ ከስምተኛው ሺ መቅሠፍት ይጠብቀን..... ቡሩክ ሁኑ.......

ሁሉም ተያይዘው ወደ ግብዣው ይገባሉ። ወይዘሮ አሰጋሽ ትንሽ ቆይተው ብቅ ቢሉ፥ የፍሬዋንና የበላይን መሄድ አሽከር ይነግራቸዋል - ቀና ሲሉ የባሻገራቸውን አቀበት ተያይዘውት ይመለከታሉ። - እነ ፍሬዋ ቢሆን መለስ ያላችሁ እንደሁ የጨው ዐምድ ትሆናላችሁ ያሏቸው ይመስል - አፋፍ ላይ እንኳ ሲደርሱ መለስ አላሉም...... አደፍርስ ከወይዘሮ አሰጋሽ ለጥቆ ብቅ ይላሉ...... እቤት በታች ሸለቆ ውስጥ አንድ ገበሬ ያቅራራል.......

«ግራ ነፍሶ ቀኝ እስቲመልሰው፥

የተናገሩህን እሺ በል አንተ ሰው......

«ድንቁርናና ዕውቀት! እምቢ በል አንተ ሰው! አይልም፥ ላፉ እንኳ ቢሆን!?» ያስተጋበል አደፍርስ ሸለላውን።

ጺወኔ ብቅ ትላለች። -

«እንዲህ ያለች ልጅ!» ይሉና ተመልሰው ይገባሉ ወይዘሮ አሰጋሽ - ፍሬዋን በዚያ ጠምዛዛ አቀበት ለዓያንቸው እስክትጠፋ ድረስ ሲከተሏት ይቆዩና......

«ታውቂያለሽ?» ይላል፤ ጺወኔ ከቤት ስትወጣ እንጂ ወደ አጠገቡ መጥታ መቆም አለመቆሟን ሳያይ የሚናገረው አደፍርስ «.....ከቃላት ሁሉ ደስ የሚሉኝን...... እምቢ! አሻፈረኝ እምቢ አሻፈረኝ! እነዚህ ናቸው ከቃላት ሁሉ ነፍስ ያላቸው የሚመስለኝ...... ሙዚቃ እንደሰማሁ ዓይነት ደሜን የሚያፍለቀልቁት..... በሙዚቃ መደርደር..... በድምፅ መታወጅ ያለባቸው የሚመስለኝ.....

እቤት በታች ደሞ እሥምሪቱ ሆኖ ሲዘፍን ይሰማል ወርዶፋ.....

«አዲስ አበባ ሜ በይ

አሥመራ ቡኢ መሌ

አባ ፌቴ ጃለ - ዱ

ነጀላ እንዱኢን መሌ......

## ፲፮

## አደፍርስ

«በዛሬው ዘመን ሳይጋቡ መፋታት በተማሩት ሰዎች ውስጥ ተጋብቶ መፋታት ባልተማሩት ውስጥ ይበዛል። በኔ አስተያየት ሳይጋቡ መፋታት በተማሩት ሰዎች ውስጥ የሚበዛበት ምክንያት ልቡሰ ጥላቸው ተመሳሳይ ስለማይገኝለትና አስቀድሜ እንዳጫወትሁሽ...... በመጀመሪያ በወረቀት ማስፈር የሚገባቸውን የልቡሰ ጥላቸውን መግለጫ ስለሚዘነጉ ነው...... በትሆናለች በምስቅልቅል ልቡሰ ጥላ እየተመሩ እውነተኛ ልቡሰ ጥላቸው የሥነዘረውን እየተዉ በዓይን ዐዋጅ ስለሚመሩ....... እንዳጫወትሁሽ እንግዲህ ይኸንን ሁኔታ ለማስወገድ መጻፉ ይጠቅማቸዋል ማለት ነው......» እያለ ያመጣዋል አደፍርስ ጥላ እንደ በረደ ካጥር ውጭ ሲዝናና ጺወኔን ባርማሽላ እሸት ስትቆርጥ ያያትና ጠጋ ብሎ ቆረጣውን እየረዳት ሲያወራት..... ጺወኔ የሚናገረው ነገር

ሁሉ ጨርሶ ባይገባትም በስሜት እየገነፈለ ስለ ነበረ አነጋገሩ ባድናቆትና ባክብሮት ዓይን እየተመለከተች ነበር የምታዳምጠው......

«...... ከተጋቡ በኋላ የሚፋቱት ከየቦታው እየመጡ ከተማውን የሚያጣብቡት ወንዶችና ሴቶች ምክንያት ግን ምን ይመስልሻል?...... ባባትና እናቶቻቸው ልቡሰ ጥላ ትይዩ ተመሥርቶ የነበረው ልቡሰ ጥላቸው ድንገር እከተማ በመምጣት ስለሚያድግባቸው ነው። ተመልከችው ለምሳሌ - ስንት ዘመዶቻቸው አሉ እከተማው ደርሰው እየተመለሱ ብዙ ነገር የሚያጫውቷቸው...... ስንት ጓደኞቻቸው አሉ እከተማ ደርሰው እየተመለሱ ብዙ ነገር የሚያጫውቷቸው...... እነሱም በበኩላቸው እየከተማው እየሄዱ ማየትና መስማታቸው አይቀርም እንግዲህ...... ሌላው ቢቀር የሰሙትን ለማረጋገጥ...... እንግዲህ ምን ይሆን ይመስልሻል ልቡሰ ጥላቸው በዚህን ጊዜ......? ያለመጠን ያለመጠን ያድጋል...... ድንገተኛው ልቡሰ ጥላቸው የዱሮውን ልቡሰ ጥላቸውን ይደመስሰዋል። እያደገ የሄደው ልቡሰ ጥላ በጥንታዊ ልቡሰ ጥላ ከተመሠረተው የኑሮ ጓድ ጋር ሊኖር አይችልም። በርግጥ ሁኔታውን ለማሻሻል ከተፈለገ የልቡሰ ጥላው እድገት እንዲቋረጥ ማድረግ ያሻል ማለት ነው። በዘመናዊ ትምህርት ሳይበለጽጉ ልቡሰ ጥላን ብቻ ማዳበር በሽታ ማትረፍ ነው። ስለ ከተማው ያዩትንም ሆነ የሰሙትን ሁኔታ፥ ጠንቁን ሳይተክል በፊት ብዥ ብዥ እንዳለ ማስቀረት ያስፈልጋል። ጥንታዊ ልቡሰ ጥላቸውን ባለበት እንዲላወስ እንጂ እንዲድህና ቆሞ እንዲሄድ በማይረዳው በዚህ በያዝነው መሸጋገሪያ ዘመን እስከዚህ የከተማው ሁኔታ እንዲያጓጓ አያሻም። ከቅሬነትና ካጉራ ዘላይነት ኑሮ በስተቀር ምን ሊገኝ ነው እከተማ በመምጣት? የያዝሁት ያዝሁትና የይድረስ ይድረስ ኑሮስ የቱን ያህል ደስታ ሊሰጣአቸው አይችልም። የከተማዎቹም ሆነ የባላገሮቹ እንደ ልቡሰ ጥላቸው መኖር አለባቸው። እንዳጫወትሁሽ የከተማዎቹ ሰዎች እንደየልቡሰ ጥላቸው ሲያገቡ ከየባላገሩ የሄዱት ቅሬዎች ጐብኚ ያጡና ወደ የመጡበት ጐሬ ይመለሳሉ። ለመውጣት እየጐሬው አፍን ጫማ ላይ የደረሱት ጓደኞቻቸው የነሱን መመለስ ሲያዩ እየጐሪያቸው ይቀራሉ። የያዙትን እንዳይነጠቁ እንጂ ያልያዙትን ለመያዝ አይፈልጉም..... እንዴ! ምን ማለትሽ ነው? አሁንማኮ የባላገሩ ዳንዴ ሁሉ ያለሚስት ቀረ? መልከ ቀናና ልጅነት ያላት ሁሉ ወደ ከተማ መጉረፍ..... በልዩ ልዩ ዓይነት ያባለ ዘር በሽታ መለከፍ...... መክኖ መቅረት........ የሕዝባችን ቁጥር መቀነስ....... እንዴ ምን ማለትሽ ነው.....

እቤት ውስጥ አቶ ጥሶ፥ ወይዘሮ አሰጋሽና አቶ ወልዱ ወሬ ይዘዋል። የቦረንትቻው ሥጋ ነገር ከጨዋታ ጨዋታ በመውለድ ልዩ ልዩ መልክ እያወጣ ሄዷል -

«.......የፈጥመኝ ንጉሥ ያፈራርደን ካለ አለቀ...... የጨው ዐምድ ነው የሚሆነው ያገሬው ሰው ሁሉ.......» በረጅሙ ይዘዋል ወጉን ወይዘሮ አሰጋሽ «...... አሁን በቀደም ታምር ነውኮ የሆነው...... ጆሮ የማይሰማው ነገር የለ......! እርስዎማ መቼም...... ወምበር የሆነ ሰው...... ስንቱን ነገር ሰምተውታል......በኛ አገር ግን ጉድ ተባለ...... ጉድ ማለቂያ የለው። እዚህኮ፥ ተጉለት ውስጥ ነው። - ሴትዮዋ ልጅዋን ትልከዋለች ድውር አሲዛ እሸማኔ ቤት። ሕፃን ልጅ የስድስት ይሁን የሰባት ዓመት። ምን ይመጣ ብላ አስባ! ወደ ሌላ ጉዳይዋ ሄዳ ኖሯል። እግዜር ያስባችሁ እንግዲህ - እቤቷ ስትመለስ፥ ብትጠብቅ አይመጣ ብትጠብቅ አይመጣ...... ምነው ዘገዬ ይኸ ልጅ ትልና ወጣ ማለት...... እንዲህ አለ አይደለም...... መንገዱንም ሰፈሩንም ቃኘት ቃኘት ከየት ቢመጣ...... በቀዬውም ታጣዋለች። ትሮጣለች ወደ ሸማኔው ‹......ልጄን ድውር አሲዤ ልኬው ነበር› ትለዋለች። - ‹ዓዎ ልከሽው ነበር፤ ድውሩን ሰጥቶኝ ወዲያው ተመልሷል - እዚህ እንዲጠብቅሽ ከፈለግሽ ለምን አልነገርሽኝም?› ይላታል። ከዚያ መቼስ ምኑን ትያዘው - የናት ሆድ የናት ሆድ ነው፥ ወደ ዱርም ወደ ወንዝም ወደየዘመዱም ብትል ከዬት! ምን ይዋጣት! ምን ትሁነው? ብትጠብቀው አይመጣ..... ብትጠብቀው አይመጣ - ዋለ - አደረ - ሰነበተ - ቁቁ ሆነ...... ‹የተቸገረ መቼም እርጉዝ ያገባል› አይደለም...... ትሄዳለች...... ወደፈጥመኝ። ‹ልጄን ተነጠቅሁ! ልጄን ተነጠቅሁ! ቀማኛ ወሰደብኝ.......መልስልኝ ልጄን፥ መልስልኝ ልጄን!› በማለት እጫማው ላይ ወድቃ እየተንፈራፈረች ትነግረዋለች። ባለውቃቢውም ‹ተነሽ! ተነሽ! ይልና ይጠይቃታል ሁኔታውን...... አትነሣም እሷ ግን። - እንዳለች ሆና እሸማኔ ቤት ልኬው ነው ሳይመለስ የቀረው ትለዋለች ‹......ተነሽ ተነሽ!!› ይላታላ። እንደ ገና። አትነሣም አሁንም። - ‹ተነሽ ነው የምለው!› ሲላት ነው በሦስተኛው ጊዜ ብድግ የምትለው። ከዚያ ነው እንግዲህ ቀጥታ ሂጂ የሚላት ወደ ሸማኔው ቤት......ጉድ ስሙልኝ እንግዲህ ‹......ወደ ሸማኔው ቤት ሂጂማ እግሩን እያወዛውዝበት ጉድጓድ ውስጥ ት....ክ ብለሽ፥ ትክ ብለሽ ተመልከተሽ ነይ› ይላታል። እንደታዘዘችው ትሄድና የሸማኔውን ጉድጓድ ትክ ብላ አይታ ትመለሳለች። - ‹ምን አየሽ?› ይላታል ይሰየምና። - እንደ ዱሮው አይደለም፤ ዱሮ የተደመደመ ነበር፤ አሁን ግን አፈሩ ተቆፍሮ ገና አልረጋም› ትለዋለች። ከመቀመጫው ብድግ ይላል ባለውቃቢው.......ጐርደድ፥ ጐርደድ ‹.......ሂድና ሸማኔውን ጥራው› ብሎ መጮህ ነዋ! አንዱን አሽከሩን ትክ ብሎ እየተመለከተ። ተላላኪው እንደ ታዘዘው ይሄዳል። ሸማኔው ግን..... ‹እኔ ባለውቃቢ ምኔ ነው አሽከሩ መስየዋለሁ እንዴ? አልመጣም› ብሎ ይመልሳል። - ሁለተኛ ጊዜ ይልክበታል። ሸማኔው ለበን ጠበንጃውን ያወጣና ጥይቱን አጉርሶ በመልከተኛው አይቶ ያመልጥና ይመለሳል። ሦስተኛ ጊዜ ‹ሄደህ አሁንም የፈጥመኝ ንጉሥ ና ይልሃል› በለው ብሎ ያዘዋል

አሽከሩን። - ‹ይገድለኛል እንዴት ብዬ ተመልሼ እሄዳለሁ? ምን ብዬ እሄዳለሁ?› ብሎ ይጨነቃል አሽከሩ። ‹እሱ ከገደለህማ እኔ ገደልሁህ ማለት ነው ሂድ!› ብሎ ያዘዋል......... ይሄዳል። - ሽማኔው ለበኑን ያወጣና አነጣጥሮ መተኮስ ነዋ፤ ቃታውን ሳብ ሲያደርግ ‹ቋ!› ይልና ዝም...... ሦስተኛ ጊዜ አጉርሶ ሳብ ሲያደር ‹ቋ!› ይልና ዝም.......መለስ ነዋ አሽከር በዚህን ጊዜ። - የፈጥመኝ ንጉሥ የሽማኔውን ሆድ ወዲያውኑ ሌሊቱን ንፍትፍት አድርጎት ማደር......ወዲያ ቢል ወዲህ ውጪ ነፍስ ግቢ ነፍስ መጨእንቅ መጠበብ ሆነ.......እምን ይግባ? ጐረቤቶች ይሰበሰቡና ጉዱን መቼም አልወቁም.........ምነው ብትማልደው ምናልበት ምን ክብርህን ይቀንሰዋል ይሉና በግድ ይገፉፉታል። ጉድ አልሰሜ የጐረቤት ነገር...... ሽማኔም የተያዘ የተጨነቀ ምን ይሁነው - ሌላ ዘዴ ስላጣ በቃሬዛ ውሰዱኝ ይልና እፈጥመኝ ዘንድ መምጣት ነዋ! እደጅ ያሳርፉታል፤ እቤት እንኳን ሳያስገቡ....... ያን በግሩ ለመምጣት የኮራ ሰውዬ። የፈጥመኝ ንጉሥ ይሰየማል....... ይፈርድበታላ! ገድለህ እመሥሪያ ጉድጓድህ ውስጥ የቀበከውን ልጅ ስታስወጣ ትድናለህ ብዬ......! ሁለት ተመልካች ይጨምርና በቃሬዛው እንዳለ ይመልሰዋል.......! ጉድጓዱ ሲቆፈር በዝተት ተሸፍኖ ብቅ ይላል ሬሳው። - ሽማኔውም ወዲያው በሽታው ይተወውና ይነሣል። - ምን አለ ከዚያማ....... ሬሳንና ገዳይን አያይዞ ለብረ ብርሃን ችሎት ላካቸው.......መንግሥት እንደ ፍጥርጥሩ እንዲያርደጋቸው..........

«ለመሆኑ ለምን ገደልሁት አለ?» አቶ ወልዱ ይጠይቃሉ።

«እረግ እረግ ዋናውን ነገር ረስቸዋለሁ ለካ......ደሙም በጠርሙስ ሆኖ ተከቶ ተገኘ እቤቱ......

«የምኑ ደም?

«የልጁ ደም......

«ምን ሊያደርግለት ቀዳው ደሞ የልጁን ደም......?

«.......የእንተ ነገር - አንዱ ዐባይ ጠንቋይ ባልባለቀ ልጅ ደም፥ ዕፅ እሰጥህ ትጨምርና - እጅህን ደረትህን ጀርባህን ሙላህን ከተነቀስህ ሀብታም ትሆናለህ ብሎት ነዋ! ሊከበር ሀብታም ሊኮን......! ዛሬ ሰዉ ሁሉ የያዘው ይኸንኑ አይደለም እንዴ........? እነዚህ በየቦታው አዳዲስ የእህል ወፍጮ የሚተክሉ ሁሉ ትንንሽ ልጆች እየፈለጉ ሲሆን እዚያው እተተከለበት ቦታ ድረስ ወስዶ በማረድ ካልሆነም ደግሞ እሌላ ቦታ ታርዶ በጠርሙስ በመጣው ደም ባቡሩን ካልረጩ መቼ ገበያ ያገኛሉ?....... የስንቱ ልጅ ነው ይመስላችኋል? እንደዋለ የሚቀረው...... የዚህ በጠርሙስ የሚመጣውማ ደም ሺሺ! ብር ነው አሉ ዋጋው......

«በምን ያውቀዋል የሰው ደም መሆኑን? የበግ የፍየል ደም ሊሆን ይችላል ለምሳሌ!» ይናገራሉ አቶ ጥሶ ሲያዳምጡ ይቆዩና -

«የለም ሁለት ጆሮቹን ቀንጥቦ ይዞ መሄድ አለበት ይላሉ ለምልክት!»

«የሚገርም ነገር - የከፋታቸው ከፋት ደሞ ሁለቱንም። - እውነታቸውን ነው፤ በባላገር ገንዘብ አለመገኘት የጠቦት በግ ደሙን በጠርሙስ እያደረገ፥ ካንድ ጆሮ ጋር የሚያቀርበው ሰው ይበዛ ነበር። - ምን ከፋው ባንድ ጆሮ ሽ! ብር ካገኘ......? ለመሆኑ ከነነፍሱስ የሚመጣው ስንት ያወጣ ይሆን?» ይጠይቃሉ አቶ ወልዱ።

«እሱ ሁለት ይደፍን እንደሁ - ነገሬም ብዬ አላጤንኩት፤ ብቻ መቼስ በየቦታው ንግድ አድርገው ይዘውታል ይሉኛል......

አቶ ጥሶ ኩስትርትር ያለና የተጨነቀ የመሰለ ግንባራቸውን በጃቸው እያሻሹ ወደ ውጭ ይወጣሉ።

«አሁን ታዲያ ይኸን ያንተን ድርቆሽ በስንት ብር ልሸጥልህ? ስድሳ ብር በጣም ውድ ዋጋ የሆነ መሰለኝ.... እምልህ» ይጠይቃሉ ወይዘሮ አሰጋሽ ወንድማቸውን አቶ ወልዱን።

«...... ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት......! ባላገሩ ነው የኢትዮጵያ ተስፋ..... ከባላገሩ ከሚወልዱት ልጆች ነው ላገራችን ዶክተሮች መሐንዲሶች እናገኛለን ብለን ተስፋ ያለን.......

«......የእናንተ ነገር - አንዱ ዐባይ ጠንቋይ ባልባለቀ ልጅ ደም ዕፅ እሰጥሀ ትጨምርና - እጅህን ደረትህን ጆርባህን ሙላህን ከተነቀስህ ሀብታም ትሆናለህ ብሎት ነዋ! ሊከበር ሀብታም ሊኮን.....! ዛሬ ሰዉ ሁሉ የያዘው ይኸንኑ አይደለም እንዴ......? እነዚህ በየቦታው አዳዲስ የእህል ወፍጮ የሚተክሉ ሁሉ ትንንሽ ልጆች እየፈለጉ ሲሆን እዚያው እተተከለበት ቦታ ድረስ ወስዶ በማረድ ካልሆነም ደግሞ እሌላ ቦታ ታርዶ በጠርሙስ በመጣው ደም ባቡሩን ካልረጩ መቼ ገበያ ያገኛሉ?...... የስንቱ ልጅ ነው ይመስላችኋል? እንደዋለ የሚቀረው......የዚህ በጠርሙስ የሚመጣውማ ደም ሺሺ! ብር ነው አሉ ዋጋው.......

«በምን ያውቀዋል የሰው ደም መሆኑን? የበግ፥ የፍየል ደም ሊሆን ይችላል ለምሳሌ!» ይናገራሉ አቶ ጥሶ ሲያዳምጡ ይቆዩና -

«የለም ሁለት ጆሮቹን ቀንጥቦ ይዞ መሄድ አለበት ይላሉ ለምልክት!»

«የሚገርም ነገር - የከፋታቸው ከፋት ደሞ ሁለቱንም። - እውነታቸውን ነው፤ በባላገር ገንዘብ አለመገኘት የጠቦት በግ ደሙን በጠርሙስ እያደረገ ካንድ ጆሮ ጋር የሚያቀርበው ሰው ይበዛ ነበር። - ምን ከፋው ባንድ ጆሮ ሽ! ብር ካገኘ......? ለመሆኑ ከነነፍሱስ የሚመጣው ስንት ያወጣ ይሆን?» ይጠይቃሉ አቶ ወልዱ።

«እሱ ሁለት ይደፍን እንደሁ - ነገሬም ብዩ አላጤንኩት፤ ብቻ መቼስ በየቦታው ንግድ አድርገው ይዘውታል ይሉኛል....

አቶ ጥሶ ኩስትርትር ያለና የተጨነቀ የመሰለ ግንባራቸውን በጃቸው እያሻሹ ወደ ውጭ ይወጣሉ።

«አሁን ታዲያ ይኸን ያንተን ድርቆሽ በስንት ብር ልሸጥልህ? ስድሳ ብር በጣም ውድ ዋጋ የሆነ መሰለኝ......እምልህ» ይጠይቃሉ ወይዘሮ አሰጋሽ ወንድማቸውን አቶ ወልዱን።

«.......ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት......! ባላገሩ ነው የኢትዮጵያ ተስፋ...... ከባላገሩ ከሚወለዱት ልጆች ነው ላገራችን ዶክተሮች መሐንዲሶች እናገኛለን ብለን ተስፋ ያለን.....

ታዲያ....... እባላገር የሚቀሩት አሮጊቶች ብቻ ከሆኑ የመውለድ ጊዜያቸው ከተላለፈ አሮጊቶች ጋር ብቻ ከቀሩ......ይኸ ተስፋችን እንዴት ይሳካ ይመስልሻል......? የለም! የለም - ኮረዳ ኮረዳዎቹ ከየመንደራቸው የማይወጡበት የወጡትም ወደየመንደራቸው የሚመለሱበት መንገድ መገኘት አለበት። እስቲ ለምሳሌ ተመልከችው - ይኸን ባገር ቤት ያለውን ሃይማኖታዊነት ርኅራኄ ገርነት ሰው አፍቃሪነት እንግዳ ተቀባይነት ዘመናዊ ትምህርት የቀላቀልሽበት እንደሆን እንዴት ይመስልሻል ውጤቱ? አይናፍቅሽሞይ? አያስቀናሽሞይ? ምንኛ የሚያጓጓ ይመስልሻል! እስኪማ በረጅሙ አስቢው......» ብዙ ጊዜ ከንፈሮቿን ሳትከድን ቆይታ ኖሮ ጥያቄ ሲያቀርብላት ነቅነቅ ስታደርጋቸው እንደባይተዋር ገላ ሲገናኙ በመስማታቸው ፈዝዛ መቆየቷ ይታወቅትና መልስ በመመለስ ፈንታ አፏን ኩርትም አድርጋ ይዛ እሱን እሱኑ ታየዋለች።

«......የዋሁ፥ ሰላማዊው አገሩን ወዳዱ ንጉሠ ነገሥቱን አፍቃሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንኛ በተበራከተ! ምንኛ በተራመደ! ምን ይመስልሻል ታዲያ አንቺስ ስታስቢው? እንዴት ይመስልሻል.......የወደፊቱን ባሳብ መነጥር.......

«ጥልያኒኛም እችላለሁ!» ጴጥሮስና ሮማን እየተነጋገሩ በዚያው በሸቱ ውስጥ ሲያልፉ ይሰማል።

«አስተምረኝ እስቲ ጥልያኒኛ...... ካምራ አፍ ያስቸግራል?» ትጠይቀዋለች ሮማን።

«አ፥ ቤ፥ ቼ፥ ዴ...... አዎ አዎ፥ አስቸጋር ነው - ዶሞ..... እኔ ላንች አስተማር ሆኜ ልያገልግል እመየቴ አይወዱም......እመኩር ነበር ግን......

«ታዲያ ለምን አታስተምረኝም.....?

«ከፎሎክ ዶሞ በቀላል ምይንገድ ከሳቸው ልያመልጥ እችላለሁ......

«የትውልድ አገርህ አይናፍቅህም፥ ብዙ ዓመትህ ነው መቼም እዚህ ከመጣህ.....

«አዎ! ካሥመራ ከመጣሁት ብዙ ጊዜ ቆይቷል፤ ክንፍ ቢኖረኝ እንደ ሚካኤል አድርጌ ሰውነቴ ያወጣት ነበር.....

## ፲፯

## አደፍርስ

በማግስቱ ከብት ማጐሪያ ሰዓት ገደማ ጺወኔ አጥሩን መርኮዝ ብላ ቆማ ማዶ ማዶውን ትመለከታለች - ሸለቆውን ጉባውን ድንጋዩንና ጫካውን...... አልፎ አልፎ ቆቅና ጅግራዎች ድንገት፥ ዣበብ ሸተት ብለው እየመጡ እየጐጅዋቸው አጠገብ ዶፍ ዶፍ በማለት ሲያርፉበት ይታያል። ደርሶ ተወርውረው የተተከሉ ይመስል የጺወኔ ዓይኖች ግን የሕይወትን እንቅስቃሴ ሲከታተሉ አይታዩም፤ ባንድ ነገር ላይ ረግተዋል - ሌላውን ትርኢት ሁሉ አንድ ላይ አምጥቶ የከሠተ በሚመስል። -

ከኋላዋ ሁለት እጆች ቀስ እያሉ እያሰሉ ይጠጉና ዓይኖቿን በጣቶቻቸው ሸፍን ያደርጉታል። ጭንቅላቷን ሹልክ አድርጋ በማስለቀቅ ፈንታ እሷም በበኩሏ በጉንጭና በጉንጮቿ አቅጣጫ ጣቶቿን በጣቶቿ ያዝ እንደማድረግ ትልና፡ -

«ዐውቄሻለሁ እባክሽ፤ ሮማን ነሽ.....» ትላለች፤ የሸፈኗት ጣቶች ቢሆን አይነሡም «ፍቅርተ ነሽ» ትላለች ትቀጥልና። አሁንም አይነሡም። ለሦስተኛ ጊዜ እንደምታስብ ዓይነት ትንሽ ቆየት ትልና ያለጥርጥር ያወቀች በሚያስበስላት አንደበት...... «ማሚቴ ነሽ!» ትለለች። ጣቶቹ ቢሆን ንቅንቅም አይሉም። - እንደምንም ታግላ «አንዴ ምነው ልቀቂኝ። የምን ጣብቂያ ነው» ብላ ዓይኖቿን ትገልጣለች።

«ሴቶች ብቻ ናቸው እንዴ ካንቺ ጋር የሚቃለዱት?» ይጠይቃታል አደፍርስ ጣቶቹን እንዳስለቀቀችው ቀስ ባለ አንደበት።

«አዎ ሴቶች ብቻ ናቸው..... ከጐርፉ ወዲህ ከወንድ ጋር ተዋዝቼም አላቅ......

«ጐርፉ - ጐርፉ!» ያስተጋባል አደፍርስ ስሙን።

«የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ነበር፤ ዛሬ እንዲህ ነገር ዓለሙን ሊተወው.....

«.....ድንቁርናና ዕውቀት! እና ታዲያ እኔ ታዲያ እኔ አዲስ ነገር ሆኜ ብሻለኋ?!

«ምን ጠርጥሬ ደሞ፥ እጅህ እንኳ የወንድ አልመሰለኝም......

«ሻከር፥ ጐልደፍደፍ ብሎ ጨቦድ የሚያደርግ ዓይነት አይደለም፤ እውነትሽ ነው......

«እሱ ሳይሆን፥ እጅህንስ ለነገሩ ያህል ያዝ አርጌው አልነበር......?

«አዎ ጣቶቼን ያዝ አድርገሻቸው ነበር.....

«ምን ጠርጥሬ ደሞ አንተን......ወደርሻ ወርደሃል አልተባለም ነበር እንዴ? ምን ዐይነት ሰላቢ ነህ ለመሆኑ......» ሳቅ ሳቅ በሚል ፊት እየተመለከተችው «ጭራሽ ኮቴህን አልሰማሁትም.....

«ተመለስኋ ታዲያ! እዚያው ያመሻል ብለሽ ነበር.......?

«እምልህ ያን አኮርዲዎ ተሸክመህ የመጣኸው ላትጫወትበት ነው እንዴ? ምን አሸካከመህ ለዚህ ለዚህ......

«ሙዚቃ የሌለበት ገጠር መስሎኝ ነበር ያመጣሁት......

«ታዲያ አሁንስ የት ሰማህ ሙዚቃ......?

«......ሞትና ሕይወት! የት ሰማህ ሙዚቃ? ሙዚቃ የት ሰማህ? ትቀልጃለሽ ልበል....... እስከዚህ አካባቢያችን ከሚያምመው የድምፅ ዑደት የበለጠ ምን ሙዚቃ አለ? ልንገርሽ እንግዲያው እውነቱን የተሰማኝን። - ከዱር እንደገባሁ አጥሩ አጠገብ ቆመሽ ባየሁሽ ጊዜ አንቺ መስለሽኝ ነበር በልዩ ጥበብሽ ዙሪያውን የምትቃኚው ጉር ጉራንጉሩን ሸጥ ሸለቆውን የምታዘፍኚው ከወጣት ጉሮሮ እንደሚፈስ ዜማ እንደ ጐልማሳ ጩኸትና ድንፋታ እንደ ቤተክስያን ማሕሌት እንደሚዥጐደጎድ የማዕበል አመጣትና እንደሚያስገረግር እንደሚያስረገርግ የድል ድምፅ እንደ መከራ - ጭንቅ - ብስጭት - ምን ልሁነው ዋይታ ነፋስ እንዳጠኸየው የዝናብ ዳመና ስግምግምታ - ዙሪያውን ሲምሸከሸክ ሲደረደር ሲድረቀረቅ - አንዲ መስለሽኝ ነበር የምትቃኚው። - ዓይኖችሽን በጣቶቼ ሰሸፍናቸውስ የነበረው ጽጥታ....... የልብ ምታችን እንኳ የቆመ

መምሰሉ ላንዳፍታ...... ምናለፋሽ ብቻ የመላው ቀዬ ንዝረቱ ውህደቱ ዝማሬው እፎይታው...... ከዚህ የበለጠ ሙዚቃ ይኖር ይመስል......ከዚህ የበለጠ ሙዚቃ ይሰማ ይመስል.......?! ሙዚቃ የት ሰማህ ትይኛለሽ?!

«ቢሆንም እኔ መስማት የምፈልገው አኮርዲዮን ነው...... ይኸ ያገሬ ጭልቅልቅታ በየለቱ የሚያደነቁረኝ ስለሆነ ሙዚቃነቱ አይሰማኝም......

«እውነትሽን ነው፤ በየለቱ የሚደጋገም ነገር ዋጋ ያለው መሆኑ አይታወቅም። - ከድግግሞሽ የተነሣ ዓይን ጆሮና ሌሎችም የስሜት አውታሮች እንኳን በጠቅላላው ይበድናሉ...... ተባራቸውን ይረሱታል.......

«እኮ ታዲያ አኮርዲዮን ተጫወታ......?

ከወፍራሙ ወደ ቀጭኑ ከቀጭኑ ወደ ወፍራሙ ጣቶቹን ሸርተት ሸርተት ያደርግና ትዝታን መጭወት ይጀምራል - አኮርዲዮውን ከተሰቀለበት ከወይዘሮ አሰጋሽ እልፍኝ ያመጣና...... ቀስ ቀስ እያለ የሚስብ በሚመስል የድምፅ ፍልቅልቅታ - ትንፋሽ እንደሚቆርጥ የድንጋጤ ህቅታ - ቀስፎ ይዞ መላ ሰውነትን እንደሚሰገጥጥ ድንገተኛ ርግፍገፍ - እንደ ሻህላ እንደ ምስጥ ውስጥ ውስጡን ነከሰ ነከስ ቆንጠር ቆንጠር እያደረገ አመም ደስ የሚል ስሜትን በመስጠት አታሎ አታሎ እንደሚጐለስስ ብርክርክታ። - እየተሰነጠረ፥ ይማታ - ይላጋ - ይርመሰመስ ይጀመራል - ካኮርዲዮው እየተመጠነ የሚፈሰው የድምፅ ርቺት። -

ሮማን ትመጣለች - የየገበሬዎቹ ልጆች ይመጣሉ - ገረዶቹ ሁሉ እነ ማሚቴ ፍቅርተ ሳይቀሩ ሁሉም ይሰበሰባሉ፤ ይከቡታል - ያውታል - ያውታል - የሚነካውም የሚጐርሰውም ይመስላል ዓይናቸው...... በማየት ወይም በማጥናት ዓይነት አመለካከት ሳይሆን - የቧምቧ ውሃ እንዴት ነው አሁን ለቀቅ አድርጎ ድንገት ሲዘጉት የውሃው ጉራጅ ከቧምቧው እንዳልመጣ ዓይነት ድምፅ ሰጥቶ ነጥሮ የሚበተነው - ልክ እንደዚያ...... ያውታል - ያውታል - ያውታል.....

«ሮማን! ሮማን!» ወይዘሮ አሰጋሽ ይጣራሉ፤ መልስ አያገኙም። -

«ጺወኔ! ጺወኔ!» ይጣራሉ ደግመው ወይዘሮ አሰጋሽ። - አሁንም መልስ አያገኙም።

«ፍቅርተ - ሮማን - እሜቴ!...... እንዴ! ምን ዘጋችሁ ይባላል?!» እያሉ ከእልፍኛቸው በቁጣ መንፈስ ወጥተው ወደ በረቱ ይመጣሉ። - ወደ ተሰበሰቡበትም ቦታ ጠጋ ይላሉ። እንደ ተጠጉ ለጊዜው ሙዚቃው የሳቸውንም ልብ ነካ ያረገው ዓይነት

ቁጣቸው በረድ ይልና ሌላ ብርሃን ፊታቸው ላይ ሲረበብ ከጺወኔ ጋር ድንገት ዓይን ለዓይን ግጥም ይላሉ። ራሳቸውን የረሱና የዘነጉ ይመስል ቶሎ ሰብሰብ ኩስተር ብለውም «......የምን መደናቆር ነው እባካችሁ? ድምፄ ጣራ በጥርቆ እስኪወጣ ድረስ ስጣራ ደሞ አለመስማቴ? ማነው እንደዚህ መረን እንድትወጡ የፈቀደላችሁ...... ሮማን ብል ማሚቴ ማን ሰምቶኝ..... ያሙስ ገበያ ይመስል ስትጮሁበት ግቢዬን.....

አኮርዲዎው ጨዋታውን ይቀጥላል። - ገረዶቹ ቅር እያላቸው ተነሥተው ወደ ሥራቸው ይመለሳሉ። ጺወኔ ብቻ አትንቀሳቀስም። - ወይዘሮ አሰጋሽ በንዴት መንፈስ እየተናገሩ መለስ ሲሉ፥ የነፍስ አባታቸውን አባ አዲሴን ደስ ባለው መንገድ የሙዚቃውን ንዝረት ተከትለው አንገትና ትከሻቸውን ከእንቅስቃሴው አስማምተው ይመለከታሉ። እዚያው አቅራቢያ አቶ ወልዱ ፊታቸውን ፈካ አድርገው ደስ ባለውና በተዝናና ፍልቅልቅታ ቆመዋል።

«ንሺ እቴ! ሁሉንም ትተነው ነው.....!! አንቺን ነውኮ እይምለው ነይ፥ ተነሽ!» ጐንተል ያደርጓታል ጺወኔን በግራቸው፤ ሊሄዱ ከዞሩ ወዲያ ተመልሰው። ጺወኔ ድንግጥ ትልና ብድግ ትላለች..... ያኮርዲዎው ድምፆች ይሰባበራሉ «ከራርሽን አውጭና ነይ አሰሚያቸው ለአቶ ጥሶ። - ሰው ማስረሳቱን ዐውቀን ነበር ዱሮም ዘፈን የከለከልነው..... የኔ ልጅ እንኳን ሰዉንና ነብርና አንበሳውን ነው የምታብረከርኪው ከተጫወትሽ...... ደሞ እንደ ደንቆሮ አፍሽን ከፍተሽ እዚህ መቀመጥሽ..... ድንቄም ሙዚቃ ተጫውታለች የከተማ ጨኸት!...... ወርዶፋ ወርዶፋ!» ይጣራሉ ወደ ሰቀላው ቤት መለስ ይሉና። - የወርዶፋ ከሥራ መግቢያ ጊዜ አለ እምድረሱን ዘንግተውታል። ጴጥሮስ ብቅ ይላል «......የጺወኔን ክራር እባክህ አውርድላት»..... ቀና ብለው አላዩትም። የልጃቸውን እጅ ያዝ አድርገው ወደ እልፍኛቸው ይመለሳሉ።

ጴጥሮስ አንድ አገር አቧራና ትቢያ የተሸከመ ስልቻ ያወጣና ለማራገፍ ይሞክራል፥ እውጪ። አብሯው ልብሱ ላይ እየተራገፈ ሲያበሳጨው ይታያል። የስልቻውም ማሠሪያ ያስቸግረውና ታግሎ ታግሎ ሲፈታለት አንድ እንጨቱ የተጣመመ የሚመስል ክራር ብቅ ይላል - ሮማን ትመጣና ትቀበለዋለች። በራፊ ጨርርቅ መሳይም እየጠራረገች ይዛ ወደ እልፍኙ ትገባለች።

« ‹የዮሴፍን ሞት ለዮሴፍ አረዱት› ይላሉ አባ፤ ነገርን ወዲያ ወዲህ ሆኖ ሲያገኙት.... አባባል.....! ጥሩ አባባል.......! ያሰጋሽ ልጅ ለከተማ ሙዚቃ አፏን ከፈተች!! ጆሮ የማይሰማው ነገር፤ የለ። - ዐውቆ መናቅ ያስደፍራል ቢሉኝ አፌን ዳባ ዳባ አለው.....» እውጪ የጀመራቸው ሁኔታ አልለቀቃቸውም ወይዘሮ አሰጋሽን።

«ቅዱስ ያሬድኮ ጨርሶታል የሙዚቃን ነገር፤ ከግዕዝ፥ ከዕዝል፥ ከአራራይ በላይ የሙዚቃ ውህደት ይኖራል ማለት ዘበት ነው። - በግዕዝ ጀምሮና አነሣሥቶ በዕዝል ደርቦና ጨምሮ በአራራይ አሳዝኖ ልብን መስጦና አስደስቶ አራርቆ አሳምሮ ያቀረበ ከሱ ሌላ የለም......!» ይላሉ አባ አዲሴ፥ ቀስ ብለው፤ የውጪ ሁኔታቸውን ወይዘሮ አሰጋሽ እንዳጤኑባቸው በመንገንዘብ ፍራት የተጫነው በሚመስል አንደበት። -

«የርሶ ደሞ የያሬድና ሌጊዎን ታሪክ ተነግሮ አያልቅም..... አንድ ሰውሞ ሙዚቃን የሚያስወድድ ሌጊዎን የሚባል የዝሙት ጋኔል ነው ይሉ ነበር። አንድ ሰውሞን ደሞ፥ የእግዚአብሔር ሰው የነበረው የበቃው፥ የነቃው ቅዱስ ያሬድ ነው ሙዚቃን ያፈለቀው ሲሉኝ ነበር...... ቅድም በከተማ ሙዚቃ እስክስ ሲሉ ምንም አልቀረውትም። - አዬ አባቴ! አንዳንዴ ነገርዎ ሆነ ሥራዎ ቆማጣ ያስሮጣል.....

«ዐውውቆ ካልተውት ከሰው ጥፋት መቼ ይጠፋል ብለሽ ‹ሰሚዐ ትስምዑ ወኢትሌብው› ተብሎ የለም? በቅዱስ መጽሐፍ መስማት ትሰማላችሁ ነገር ግን አይገባችሁም..... ተብሏል። - እንኳን እኔ ምስኪኑ የጌታ ባሪያና እነዚያም የበቁት የተሰወሩት ከስሕተት አልራቁም። - ዋናው ነገር ብቻ አድኅነነ ከማቱ ነው......

«ቢሆንም ቢሆንም ፈረስ ከጥሬ ያጣላሉ አንዳንዴ...... ተፈትሮ የሚሉት ነገር ወድደውን አይደለም ዐውቃለ፥ ጺወኔ ታዲያኮ ቃኘት ቃኘት አድርጊው እንጂ - አንችን

ያኮርዲዎው ጨዋታ አላቋረጠም። እንዲያውም የድምፅ ርዳታ ተጨምሮለታል ልማድም ያለው ባይመስል መዝፈን ጀምሯል አደፍርስ -

« ‹አሸወይና ነሾይ

ትመጫለሾይ!

ነይ በመስኮቱ

ኮቱ!

ነይ በመስኮቱ

ኮቱ!

ነይ በመስኮቱ

ኮቱ፥

ነይ በመስኮቱ!› » ይጥላል ያነሣል ታኮርዲዎውን ማናገሪያ። የሚዘፍንም ያሚያሾፍም ይመስላል እንዲያያዙ።

እንደሚድልቀፈቀፍ ወራጅ ውሃ ሲንዶቀዶቅ የሚደነቅፈውን ነገር እንደሌለ የጉለንታ ውሃ ሲምሸከሸክ ምላሱ እየታጠፈ እንደሚናገር ያረህ ላይ ፏፏቴ ሲንቸከቸክ ይሰማል የጺወኔ ክራር «......እኔ ቀን ቀን ሲሆን በጅ አይሉኝም! ለማለት ያህል የጣቶቿን እንቅስቃሴ ያዝ ባረገች ቁጥር እያረፈ....... «.......ቀን ቀን በጅ አይለኝ!» ለማለት እንቅስቃሴዋን ያዝ ስታደርግ..... እያረፈ....... እያረፈ.......

ወይዘሮ አሰጋሽ ሲቆጡ እየስርቻው ገብተው የነበሩትና እንደ ገና ተመልሰው ያዳምጡት የነበሩት አሽከሮች የክራሩን ጨዋታ መጀመር እንደ ሰሙ -

«ሁሉንም ነገር ንቀው ትተውት ነው እመዬቴ» እያሉ በመናቅ አየር - ግምባራቸውን ኮስተር አፍንጫቸውን ቅብንን እያደረጉ አንድ ባንድ እየተነሡ አደፍርስን ብቻውን ትተውት ወደ ክራሩ ያመራሉ። -

ወይዘሮ አሰጋሽ ይጣራሉ

«ሮማን......!

እሜቴ!» ቶሎ ብላ ዘላ ትገባለች።

«አንችን ማለቴ አይደለም!» ይመልሱላታል - «ፍቅርተ......!

«እሜቴ!» ከመ ቅጽበት ትባላለች።

«አልጠራንሽም.......!» አያይዘውም «ማሚቴ.......!

«እሜቴ!» ብድግ ብለው ወደ በራፉ አምርተው ነበርና ከጥድፊያው የተነሣ እያላቸው ወጥታባቸው ነበር።

እውጪ ብቅ ይላሉ፤ የልባቸው የሞላ በሚመስል ንቅናቄ። አደፍርስን አኮርዲዎ መጫወቱን አቁሞ ከአንድ የፍየል ወጠጤ ጋር ውጊያ ገጥሞ ያዩታል። ፍየሉ ያቅሙን ያህል ሁለት እግሮቹን ወደ እላይ እያነሣ አንገቱን እያሰገገ መጥቶ ከአደፍርስ መጫሚያ ጋር ይላተማል። ይመርግበታል ፍየሉ አንገቱን ባነሣ ቁጥር እግሩን እያነሣ ይመርግበታል «ሁሉንም ነገር ዐውቀን ንቀት ትተነው ነው!» ይላሉ ወይዘሮ አሰጋሽ አንጀታቸው በራሰ ሁኔታና አነጋገር ዙሪያውን ባይናቸው ማተር ማተር ካረጉ በኋላ «.......ንቀን ትተነው ነው......!

በማግስቱ ሰኞ ጧት ወደ ደብረ ሲና ይመለሳሉ አቶ ጥሶ።

## ፲፰

## አደፍርስ

«.......አኮሪዶዎ በጣም ደስ ይላል» ትለዋለች ሮማን ቀስ እያለች መጥታ ትጠጋና። አደፍርስ እንደ መሳቅ ዓይነት የፊቱን ሥሮች ነቅነቅ ያደርግና ዝም ይላል «.......እንደዚህ እንደርሶ የሚዘፍን ባገራችን የለም..... ድምፅዎ ደሞ በጣም ደስ ይላል። - አኮሪዶ የሚሉት ነገር፤ በጣም ነው ደስ የሚለው......

«የወለደሽ አባትሽ ነው አቶ ወርዶፋ.......» ይጠይቃታል አደፍርስ ንግግሯን ያዳምጣትና።

«አዎ የወለደኝ አባቴ ነው፤ ግን እኔን አይመስልም..... ይመስላል......?

«ገጥ ስትይ ከወደዚህ ከወደ ጉንጪሽ አጥንት በኩል ትመስያለሽ» ይመልስላታል አደፍርስ። - ሮማን ፊት ይፍታታና ደስታ ይሞላታባል። አባትሽን ትመስያለሽ ላላት ሁሉ የልቧን ያንጀቷን ማውራት ልማዷ ነው።

«ጋሼ ወርዶፋ ጥሩ ሰው ነው። ዋሽንት ደሞ ሲጫወት እባቡ ሁሉ ከየድንጋዩ ውስጥ እየወጣ ያዳምጠዋል ይላሉ። እርሶን ወዶዎታል ጋሼ ወርዶፋ.......አኮሪዲዎውንም ወዶታል......» እያለች ትጀመራለች። -

«እናትሽ የታገር ናቸው.....?» ይጠይቃታል አደፍርስ ነገሯን ያቋርጥና።

«ሞታለች እናቴ......! አንዳንዴ ደስ ያለው ቀን እናትሽን ትመስያለሽ ይልና እቅፍ ያደርገኛል ጋሼ ወርዶፋ...... ሶዶ ነው የተወለደችው፤ አባቷ አማራ እናቷ የስልጢ ጉራጌ ናቸው ይባላል። ቆንጆ ነበረች ይላሉ ደሞ..... እንደ እናቴ ቆንጆ ነኝ፥ አዶለሁ......?

«አዎ ቆንጆ ነሽ - የጠይም ቆንጆ.....» ይመልስላታል አደፍርስ።

«......ባልጠቁር ኖሮ ይሻል ነበር.....

«ጠይም ዓሣ መሳይ ሲባል አልሰማሽም......?

«ገና ዛሬ ነው ሰው ቆንጆ ነሽ ሲለኝ የሰማሁት..... ጐርፉ እንኳ ልቡ እየወደደኝ ቅልጥልጥ ነው የሚለኝ..... ቆንጆ አይለኝም...... ሹርባ ልሥራ? ሹርባ ስትሠሪ ደስ ትያለሽ ይለኛል ጋሼ ወርዶፋ.....

«ባትሠሪም እንደዚሁ እንዳለሽ ደስ ትያለሽ......

«ከጺወኔ ጋር ሲላፋ ሲጫወት ከኔ ጋር አይላፋም...... የጐርፉ ነገር አንዳንዴስ ይነደኛል! አንችን አይሰድብሽም ትለኛለች ጺወኔ እንኳን...... እሷን ይሰድባታል ሲናደድ! እኔን ግን አይሰበኝም.....

«ምነው ቅልጥልጥስ.....?

«አይ ቅልጥልጥ የቤቱ ሰው ያወጣልኝ ነው...... የሱ አዶለም - ቅልጥልጥ ደሞ ያንጀት ስድብ አዶለም። የቀልድ ስድብ ነው...... ሰው ሲናደድ የሚሳደበው አዶለም። - አሁን እርሶ ቅልጥልጥ! ቢሉኝ ያስቀኛል፤ አያናድደኝም።

«እግርሽ ተረከዝሽ ደሞ ቆንጆዎች ናቸው.....

«መልክሽ ዓይንና ጥርስሽ ነው የሚሉኝ..... እግሬ ደስ ይላል? የቤቱን ሰው ሁሉ ያስቸግሩት እኔን ምንም አያረጉኝ ሙያሌዎች - ጺወኔን እንኳን ይይዛታል። እኔን ግን ጨርሶ አይዙኝም፤ አመድ ውስጥ እንኳን ብወትፈው እግሬን...... እጅ ጣታቸው ላይ ሁሉ ነው የሚወጡት እሌሎቹ ሰዎች ላይ.....

«......እንግዲህ የምታገቢበት ቀን ደረሰ አይደለም እንዴ.....? እርግጠኛ ነኝ ቀሚስሽን አሠርተሻል..... አገልግልና ሌማት ሰፍተሻል......

በትሬንታ ተሳፍሬ ነው የምጠፋው.....

«ለማግባት አትፈልጊም - ለምን ትጠፊያለሽ.....? እንዴት ነው - የሚያገባሽን ሰው አትወጂውም......?

«እንኳን ልወደው ዓይኑንም አይቼው አላውቅ.....

«ሞትና ሕይወት.......! ታዲያ በትሬንታ ወዴት ትሄጃለሽ......?

«የትም - የትም - እዚህ እባላገር ማደሮ ከመያዝ - የትም ብሞት ይሻለኛል......

«እስከዚህ የባላገር ማደሮ አንገፍግፎሻል ማለት ነው......?

«አሥመራ ነው የምሄደው በትሬንታ.....

«አሥመራ.......?

«አዎ አሥመራ......

«ቀረብ የሚለው ይልቅ አይሻልሽም.......? አዲስ አበባ......

«ድራሽ አባቴ እንዲገኝ አልፈልግም......እርቄ...... እ......ር......ቄ ለመጥፋት ነው የምፈልገው?

«አባትሽ አያዝንብሽም ድንገት ስትጠፊ......

«አያዝንብኝም...... እሱም መሄጃ አጦት ነው እዚህ የተቀመጠው...... የባላገር ማደሮ አንገፍግፎታል.......

«አዲስ አበባ ቢሆን እኔም ባቅሜ ልረዳሽ እሞክር ነበር፤ እምልሽ - እፈረንጅ ቤት እንድትሠሪ - ልጅ አሳዳጊነት ወይም ሣህን አጣቢነት እንድትቀጠሪ......

«የፈረንጅ አፍ አልችልም......አዲሳባ መሄድ ምን ከፍቶኝ። - ብቻ ጥሊያንኛ አልችም...... አይ እርሶማ ቢረዱኝ! ሥራ ቢዶሉኝ ያሉኝን....... ያሉኝን......ያዘዙኝን ነው የምሠራው....... ያሉኝን! ለምን እሳት ውስጥ አልገባም......

ጺወኔ ብቅ ትላለች በወርዶፋ ጐጆ አጠገብ ሽምጥ ላይ «ያሉኝን ያሉኝን ያዘዙኝን ሁሉ እሠራለሁ.......» ስትል ትሰማለች ፍሬዋን።

«.......እሱ ነው ትልቁ ነገር.......» ይመልስላታል አደፍርስ ማዶ ማዶውን እየተመለከተ። - ጺወኔ እንቅታ ታዳምጣለች።

«ይኸን ሥራ እሺ......! ይኸን ሥሪ እሺ......! ካልኩኝ ምነው ዘበናይ ሥራስ ቢሆን ለምን ያቅተኛል.....?

«ትልቁ ነገር እሺታ ነው......ትልቁ ነገር......

«እንዲያው ያሉኝን አልኩዎት......ያሉኝን......

«ግዴለም እንግዲያው...... እንረዳዳለን.......» አደፍርስ ከነበረበት ካጥር ውጭው አፋፍ ላይ ብድግ ይልና ወደ ውሃው መቅጃ ኲሬ ያመራል። ጺወኔ ወደ ወርዶፋ ጐጆ ትመለሳለች። - ሮማን ቢሆን ብዙ ትቆያለች እንደ ተቀመጠች -

........ነጭ ቀሚስ እለብሳለሁ...... በዚያ ላይ ካባ እደርባለሁ...... ሚዜዎቹ እኔ ልዘል እያሉ ይጣላሉ...... ከዚያ ምንድነው ነገሩ..... የለም የለም...... ቆይ...... መጀመሪያ እኔን ለማየት ይፈልጋል...... እንዲያው ላይኑ ያህል....... እደበቅበታለሁ እኔ ደሞ...... ውሃ መቅጃ እንኳን አልሄድም..... ከዚያ ምንድነው ነገሩ..... ለጓደኛዬ ጉቦ ይሰጥና...... ጫማዋን ይስምና...... አንድ ምክኛት ፈጥራ እንድትጠራኝ ያደርጋል...... ሞኝት ተላሊት ምንድነው ነገሩ...... አገር ጤና ነው ብያለሁ በኔ ቤት..... ፈሰስ ፈሰስ ስል...... አንድ ሪቅ ሥር ተደብቆ አየዋለሁ.......ሪቅ! ሪቅ!.........አዲሳባ ሪቅ የለም! የብረት በርሚል ነው

ብለዋል የእህል ማስቀመጫቸው...... ያላየሁት መስሎት ታዲያ አንገቱን ብ.... ቅ ሲያረግ ከበርሜሉ ሥር..... ምንድነው ነገሩ..... እንደ መጮህ ብዬ እንደነግጥና ወደ ቤት እበራለሁ..... ምኑ ቅጡ...... አኮርፋታለሁ ከዚያ በኋላ ጺወኔንም አላነጋግራትም...... አኮርፋታለሁ.......! አባ አዲሴ አማላጅ ሆነው ይመጣሉ፤ ይለምኑኛል...... በቅዱስ ሚካሌ ይገቨሻለሁ...... ሊቀ መልአኩን ይገፔ ነው ላስቸግርሽ የመጣሁት.... በሊቀ መልአኩ...... ይሉኛል...... ዳሩ ጺወኔስ አባ አዲሴስ የት ይመጣሉ አዲሳባ.......? የለም ሌላ በጣም ትልቅ ቄስ ነው የሚሆኑት..... ጥምጥማቸው ብቻ እንደ ሐምሌ ዳመና ሰማይ የደረሰ መስቀላቸው የወርቅ ካባቸው እንደ ወርቅ የሚያበራ...... ይቅርታ አድርጌላታለሁ እላቸዋለሁ....... የኔ ልጅ! ብለው በካባቸው እቅፍ ያደርጉኛል...... የወርቅ መስቀሉን ያሳልሙኛል..... ምንድነው ነገሩ......

«.......እንረዳዳለን......? እንረዳዳለን......?» ትደጋግማለች የሰማችውን ቃል ጺወኔ «......ያሉኝን! ያሉኝን.......! ያሉኝን......» አጠገቧ የሚነገሩ ዓይነት ይሰሟታል። - ሮማንን ትወዳታለች። - አደፍርስን ግን ትወደው አትወደው ገና አላወቀችውም። ቢሆንም የሰማቻቸው ቃሎች አገንግነዋታል። በሮማንም ጌታዋ ከሚሆን አንቱ ከምትለው ሰው ጋር እንደዚያ ተዝናንታ በመጫወቷ ትንሽ ተናዳለች። ሊከፋባትም ጀማምሯል ልቧ። - የሥራ ከመፍታት ሥራ የሙዳይ ልጅ ይዛ ትጠቃቁማለች። - አልፎ አልፎ ወስፌና እጅዋን እየጠቆማት በስጨትጨት ስትል ይታያል። -

«.......ዳሱ በሰፊው ይጣላል..... ገበታው ይዘረጋል...... ጠላው በጋን በጋን እየሆነ - መቀነት እየታሠረ ይደረደራል። - እንጀራው - ነጩ ጤፍ ባንድ ፊት ጥቁሩ ጤፍ ባንድ ፊት ቅይጡ ባንድ ፊት ይቆለላል..... ጮማው ሥጋ በየባላባልቾው ላይ ተሰቅሏል። - ቢላዋው ተስሎ ተስሎ ተደርድሯል......» ትቀጥላለች ሮማን «......ምንድነው ነገሩ...... የኔ ዘመድ የሆነ ሰው ያዝለኛል...... ካሥር በላይ ሰው የበራ ጧፍ ይይዛል። - መዐት ሴቶች እየዘፈርኑ እያጨበጨቡ ይከተሉኛል...... ምንድነው ነገሩ..... ከዚያ በኋላ..... ከዚያ በኋላ..... እቤተ ዘመዶቼ አጠገብ እበርጩማ ላይ አውርዶ ቁጭ ያደርገኛል..... ከዚያ በኋላ ሽማግሌ ሽማግሌዎቹ እጃቸውን ራሴ ላይ እያደረጉ ይመርቁኛል..... ይመርቁኛል.... በየተራ። - ምንድነው ነገሩ - ከዚያ በኋላ፥ ወደ ዳሱ ይወዱኛል። - እዚያ...... እዚያ ደሞ..... የሚገባኝ ሰውዬ እመየቴ ይቀመጡበት እየመሰለ አበባ ምንጣፍ ላይ ተቀምጧል..... መከዳም የመየቴን ዓይነት እጐኑ ተደርጐለታል...... አፍንጫውንና አፉን በቀጭን ኩታው ሸፍኖ በኮራና ባማረ ሁኔታ ቁጭ ብሎ ይጠብቃል። ከዚያም እበርጩማ ላይ እነገር አባት ሽማግሌዎች አጠገብ ከባሌም ሳልርቅ ቁጭ እላለሁ። - ምንድነው ነገር..... ታገባታለሀይ ብለው ይጠይቁታል....... አዎን አገባታለሁ ብሎ ይመልሳል። - ከዚያ በኋላ እንደ ተሸፈንሁ እጁን ያሾልክና ትንሽ ጣቱን ከትንሽ ጣቴ

ሊያያይዝ ይሞክራል....... እሺ አልልም እኔ ግን..... በኋላ በመከራ ጣቶቻችንን እናቋልፋለን...... ከዚያ ምንድነው የጥሎሹ ነገር - ይወርዳል - አልበው - ወለባው - ድሪው...... አምባሩ....... ጉትቻው.....

«.......እርግጠኛ ነኝ አብሬ ልሂድ አይደለም የምትለው ምን ቢቆርጣት.......? ከጠፋን ከጠፋን ደሞ አብረን እንጠፋለን ብያታለሁ......» ትላለች ብቻዋን ጺወኔ ሙዳይዋን እየጠቋቆመች።

........ አሥር ፈረሰኛ ይከተለናል...... ከኔ ጋር አንዱ ፈረስ ላይ እኋላው አንድ ሚዜ፥ ይቀመጣል...... ምኑ ቅጡ ከዚያማ በኋላ...... እባሌ ቤት ደሞ ድግሱ ይቀልጣል...... አዬ ጣጣዬ..... መምሸት አይቀርም መቼም......ጉዴ ይፈላል.......ጉዴ ይፈላል - አነባዋለሁ...... አለቅሰዋለሁ..... መምሸት አይቀር.... መምሸት አይቀር.....

አደፍርስ ከኩሬው ገደማ ቀስ እያለ ይመጣል..... የሮማንን በሐሳብ መውዋጥ ያይና..... እያሰላ ከኋላዋ ቀርቦ በጣቱ ወጋ ያደርጋታል....... ‹ዋይ!› ብላ አገሩን አናግታው ብድግ ትላለች። ጺወኔ ከወርዶፋ ጐጆ ትወጣለች ድንግጥ ብላ። ክብረት ማሚቴና ወይዘሮ አሰጋሽ እየተንጋጉ ይወጣሉ።

«.......የተመስጦ እንጉርጉሮ.......! የፍቅር መለከት......! ጐሕ ቅደትና ልቀት......ቅኔያዊ ንጋት...... ይህ ነው ደንበኛ የፍጥረት ድምፅ...... የሕይወት...... የኑሮ....... አለሁ የማለት ቋንቋ..... ይህ ነው ራስ ከራስ ግንኙነት....... ይህ ነው እውነተኛው ድምፅ.......» እያለ ይወራጫል አደፍርስ። - ሮማን የድንጋጤ ዓይኖቿ እንዳጕረጡ....... የኋሊት የኋሊት እያለች እሽምጡ ጥጋት ስትደርስ መለስ ብላ ወደ ግቢ ትሮጣለች። የነ ወይዘሮ አሰጋሽንም ሆነ የነክብረትን ከውስጥ በኩል አጥሩ አጠገብ መቆም አልተመለከተችም። -

«ራሱን አመም ያደርገዋል?» ብለው ይጠይቃሉ ወይዘሮ አሰጋሽ ክብረትን «........እንደ ድንገተኛኮ ብናደርግለት......?

«አደፍርስ....... አደፍርስ!» እያለ የሚሆነውን ሁኔታ ሰው እንደሚመለከተው በሚነግር አንደበት ይጠራዋል። -

«........ሰምተህልኛል ያን ድምፅ! ስምተህልኛል.....! ሰምተህልኛል.......! ሰወንትህን ሰንጥሮ የሚገባ ነገር ነበርኮ......እውነተኛ የሕይወት ድምፅ...... አማርኛ እንግሊዝኛ! ቋንቋ ይባልልኛል ደርሶ.......ይገርምሃልኮ ጋሼ ክብረት........ ድንገትኮ ነው...... ፈዘዝ

ማለቷን አየሁና.......ድንገትኮ ነው ከኋላዋ....... ዳጐጥ ያደረግኋት.......? ምን ዓይነት ሙዚቃ እንዲያ ሊሆን ይችላል......? እንዴት ያለ ኀይልስ እንዲያ ዓይነት ኃይል ይሆናል.......? ምን ዓይነትስ ፍጥነት.......! እንደ ጥይት........እንደ ጥይት ነውኮ የተተኮሰችው ከመሬት.......»

«.......ግዴለህም ትንሽ ድንገተኛ ምንም አይለው......» እያሉ ካጥር ውጪ ይወጣሉ ወይዘሮ አሰጋሽ። -

«......ይገርምሃልኮ......! ይገርምሃል...... ይገርምሃል.......ይገርምሃል......

«........ከምኑም ከምኑም፥ ይከላከላል......» ቀጥለዋል ወይዘሮ አሰጋሽ ብቻቸውን «.......ከተልከስካሹም..... ካይነ ጥላውም...... ከድንገተኛውም......» ቅጠሉን እየቀጣጠፉ «......ማድረጉ አይከፋም......ባይበዛም በትንሹ ቁር እናደርግለታለን ባፍንጫው.....ከሚታኘከውም ከሥራ ከሥራ ሥሩ አኘክ አኘክ እንዲያደርግበት......

## ፲፱

## አደፍርስ

ሞቅ ሲል ነው ጧት፥ ጺወኔ እወርዶፋ ጐጆ አጠገብ ተቀምጣ ያንኑ ሙዳይዋን ስትሰፋ፥ አደፍርስን ውልብ ብሎ ሲያልፍ ታየዋለች -

«የት ነው እንደዚህ ማልደህ የምትሄደው?» ትጠይቀዋለች።

«ኦ አልነገርኩሽም፥ ትንሽ ‹ኤክሰርሳይስ› አስፈልጐኝ ነው፤ እምልሽ ሰውነቴን ማዝናናት» ይመልስላታል አደፍርስ።

«ታዲያ ፍሎቤሩ ምን ያደርግልሃል......?

«ትምህርት ያላሻሻለው ያውሬነት ተፈጥሮዬ የቱን ያህል እውስጤ እንደቀረ ልለካበት......

«ትምህርት ያላሻሻለው ያውሬነት ተፈጥሮ አላውቅም......

«በተፈጥሮ አንችም እኔም አውሬዎች ነን፤ አንችም እኔም ደም ለማፍሰስ ወይም ደም ሲፈስ ለማየት እንፈልጋለን.....

«እኔ አንደኛ አውሬ አይደለሁም - ሁለተኛም ደም ለማፍሰስም ሆነ ሲፈስ ለማየት አልሻም - የዶሮ እንኳ ቢሆን.....

«በአርአያ ሥላሴ የተፈጠርሽ ነሽ አንቺ!

«አንተም ነህ.....

«ሞትና ሕይወት ብሎ ነገር....! ስሚ - የዱሮ አባቶቻችን አደን የሚያድኑት ወንድነታቸውን ለማሳየት ወይም ምግብ ለማግኘት ነበር። - አንድ አጐት ነበሩኝ እስከ ገሙ ጐፋ ድረስ ዝሆን ለማደን ብቻ ሄጄ ነበር እያሉ የሚያጫውቱኝ......

«አንተስ ለምንድነው የምታድነው? ምግብ ፍለጋ አይመስለኝም......ደግሞም እንኳን የአቶ ጥሶ የእኅት ልጅና የሌላም ልጅ ቢሆን ወንድነትቱን ለማሳየት አደን መሄድ ያለበት አይመስለኝም...... በዚያ ላይ የተማርህ......

«ለደስታ ነው ጺወኔ ለደስታ! እኔ አደን የምሄደው። - ራሴን ለማወቅ ውስጣዊ ሰውነቴን ለመመርመር ልቡሰ ጥላዬን ለማግኘት ያውሬነት ቅሪቴ ወደ አናት እንዲወጣ...... እንዲሠፍ.....

«አይገባኝም......

«ሊገባ አይችልም ሰው ስለነገረሽ ብቻ......

«አንተ ሰው ነህ?!» ትለዋለች ጺወኔ ለሱ ያላትን አክብሮትና ወዴታ በሚገልጽ አንደበት።

«........ራስሽ መርምረሽ ልትደርሽበት ያሻል፤ ይሆናል አይሆንም ያዋጣል፤ አያዋጣም ብለሽ......ራስሽ ተኩሰሽ ራስሽ አድነሽ......

«በል ብቻ ጊዜህን አልውሰድብህ......!

«......አንድ ሊገለጽ የማይችል ልዩ ዓይነት ደስታ ነው የሚሰጠው - ጅግራ ቆቅ ሶረኔ ወይም ሰስ ሚዳቋ፥ ድኩላ፥ ተኩሰሽ ስትመቺ..... ይኸ ነው የማይባል ደስታ ነው የሚሰጥሽ ኩርምት ሲሉ ማየት - ብድግ ታደርጊያቸውና ደሙን በጣትሽ ነካ አድርገሽ፥ ያነጣጠርሽበትን ብልት ያልሳትሽ መሆኑን ስታውቂው - ይኸ ነው የማይባል ድስታ ነው የሚሰማች - ደምሽን ናድ ናድ የሚያደርግ ዓይንሽን የሚያበራ.....

«አይገባኝም፥ በእንስሳት ሥቃይ እኔ አልደሰትም...... አንተም ብትሆን ላፍህ አልከው እንጂ እነሱ ሲሰቃዩ አንተ የምትደሰት አይመስለኝም......ይኸው እንግዲህ ከሳምንት በላይ እንዳወቅሁህ ከሆነ የዚህን ዓይነት አንጀት ያለህ አይመስለኝም......

«ምን ይመስልሻል ምክንያቱ እንደዚህ ይኸን ሁሉ የሚያስፈልፈኝ? ግዴለሽነቴ ይመስልሻል። - ከተማም ብዙ ሰዎች ሳልገባቸው እየቀረሁ ራሱን ወዳድ የሚል ስም ሰጥተውኛል። - እግዚአብሔር ያሳይሽ እንግዲህ - ለምሳሌ ‹ፓርቲ› ወይም ሌላ ዓይነት ግብዣ ትጠሪያለሽ፥ ስንት ጐበዛዝት ተሰብስበዋል ማለት ነው........ እሺ ሁሉም ካንቺ ጋር ለመደነስ ይፈልጋሉ። - አንዱ ደግሞ በተለይ ከሁሉም የበለጠ ካንቺ ጋር ለመደነስ ይፈልጋል...... ለምሳሌ ያህል ነው፥ ልንገርሽ - እንዳንቺ ዓይነት ደስ የሚል እንገር ከተማ ብዙ አይገኝም - ለምሳሌ! እሺ! አንድ እንደ እኔ ዓይነት ራሱን ወዳድ በተለይ ለብቻው ሊይዝሽ ይፈልጋል - ምን ታደርጊያለሽ? ቢያንስ ቢያንስ ከሁሉም ጋር አንዳንዴ መደነስ ይኖርብሻል፤ እንዲቀየሙሽ አያስፈልግም። - ካንዱ ጋር ብቻ ተጣብቀሽ የቀረሽ እንደሁ ይጠምዱሻል ሌሎቹ.....

«ምን ቸገረኝ ታዲያ ልቡሰ ጥላችን ተገጠመ.....

«እሱ እውነትሽን ነው፤ ግን ራሱን ወዳድ እንደሚያስብለኝ አይጠረጠርም......በቀደምለት ለምሳሌ የትምህርት ቤት መሥሪያ ገንዘብ ለመሰብሰብ አባ ዮሐንስ ንግግር አድርገው ነበር። - የተናገሩት ንግግር አብዛኛው ፍሬ ቢስ ስለመሰለኝ ተከራከርኳቸው......መጀመሪያ ለብቻቸው በኋላ ምስክር ፊት። - እርግጠኛ ነውኝ አሸንፊያቸዋለሁ በክርክሩ...... ‹የዛሬ ልጆች እውኝ እውኝ ደብቁኝ ደብቁኝ ለማለት ነው ኋላ!› ከማለት በስተቀር አንድም የመለሱት አጥጋቢ መለስ አልነበረም። - እና ታዲያ ላባም ለሌሎችም ምናልባት ራሴን ወዳድ መስያቸው ይሆናል.......ግን እውነት እውነት ነው የምልሽ ራሴን ወዳድ አይደለሁም። ያሳዝነኛል በጣም ላንችም እንዲያ መስዬ ታይቼሽ እንደሆን! ስለ እኔ ምን እንድምታስቢ እግዜር ይወቅ፤ አላውቅም - ምናልባት ማን ያውቃል? ሳላውቅ አስቀይሜሽ ይሆናል......እና ቢሆንም አንቺ አስቀይሜሽ እንደሁ እውነቱን እንደምትነግሪኝ እተማመናሁ......ራሴን ወዳድ እመስልሻለሁ......?

«እኔ ስለ እሱ ብዙ ነገር አላውቅም፤ ግን ስላስተማርከኝ ትምህርትና ስለ ሰጠኸኝ ነገሮች አመሰግንሃለሁ......

«አ! ስለ ብዕሩና ስለ መጽሐፉ ማለትሽ ነው? ይገባኛል። ተስፋ አለኝ እንዳላስለቸሁሽ....... እርግጠኛ ነኝ ክፉ ሰው እንደማልመስልሽ። ቀልድ ጨዋታ የማላዘወትር የተሰማኝን ሐሳብ ያስቀይማል አያስቀይምም ብዬ ሳላስብ ቀጥታ መግለጽ የምወድ......

«.......ብዙ ሐሳብ ያለህ ልብህ አንድ ቦታ ያላረፈ ተዟዟሪ ዓይነት ሰው ነው የምትመስለኝ እኔ እንደማስብህ.....

«እንዳስመለከተሽ አስቢ....... ራሱን ወዳድም እንኳ በይኝ፤ ብቻ.....» ትንሽ ኮስተር ብሎ «ብቻ አደራሽን.......የጊዜው ሰው አትበይኝ..... ያለም ሰው አትበይኝ......የለም! የጊዜው ሰው ያለም ሰው አትበይኝ..... ያ ጐርፉ የምትይው ልጅ ራሱን አይወድም.......?

«እኔ እንጃ እንግዲህ እኔ ብሆን እወደዋለሁ። ጨዋታው ደስ ይለኛል፤ ያስቀኛል...... አንዳንዴ ባነጋገሩ ለልቤ ልብ ይሆነኛል። ደሞ ስለሚያስደስተኝና ስለሚያስቀኝ ብቻ አይምሰልህ የምወደው። አወሬ የሚሆንበት ጊዜ አለ ደግሞ...... ሲያሳዝነኝና ሲያበሳጨኝ ደስ የሚለው ጊዜ - ሆኖም ታዲያ ከሌሎች አብልጦ እንደሚወደኝ ያለ ጥርጥር ስለማምን እኔም እወደዋለሁ - አልከፋበትም......

«ሞትና ሕይወት! ታፈቅሪዋለሽ ማለት ነው እንዳነጋገርሽ። ልቡሰ ጥላችሁ ተስማምቷል ማለት ነው..... የልቡሰ ጥላ መገናኘት.......» ይላታል ትክ ብሎ እየተመለከተ።

«አዎ ምነው - ከሌሎች የበለጠ ስለሚወደኝ እኔም እወደዋለሁ...... ይችን ሮማንን ይወዳታል ለምሳሌ..... አበበች የምትባል የትምህርት ቤት ጓደኛዬም አለች፤ እሷንም ይወዳታል ግን እኔን ከነሱ ሁሉ የበለጠ ይወደኛል...... እኔን የሚወደኝን ያህል አይወዳቸውም......

«......ትቀልጃለሽ፤ ጺወኔ! በምን ታውቂያለሽ? ይኸኮ እንዲህ የሚያናግርሽ ልቡሰ ጥላው ስለተሟላልሽ ነው.......

«ገብቶኛል..... ለምሳሌ ልንገርህ! በቀደም እዚያ አልሞተ አጥር ሥር ከአንድ ሰዓት የበለጠ ነው ቆመን የተጫወትነው..... እያሳቀኝ፤ የልቡን ያንጀቱን እያጨወተኝ - ስለ አዳል መግደል...... ስለ ጥይት መተኮስ..... ስለ አዳል በሮች፥ ስለጠረናቸው....... ከነሱ ጋር ቢሆን እንዲያ አስችሎት አይቆይም...... በጣም ነው የሚወደኝ፤ እንደ እኅቱ ነው አያያዙ ሁሉ እኔን..... አንዳንዴ ይከፋዋል..... አንዳንዴ በሐሳብ አንስማማም...... አንዳንዴ የሚነግረኝ ነገር አይገባኝም፤ እሱም እኔ ባይገባው...... አንዳንዴ የሚጠይቀኝን ነገር አላደርግም...... አንዳንዴ እንዲያውም ዓይኑን ላየው አልፈልግም...... ግን እንዲያም ሆኖ እወደዋለሁ፤ እሱም እንደሚወደኝ ዐውቃለሁ። አዎ፥ እውነቴን ነው የምልህ አሁን ለምሳሌ እነሮማንን ቢሆን ጨርሶ አይከፋባቸውም፤ አይጨነቅላቸውም...... ብዙ ሰዓት ቆሞ የልቡን አያወራቸውም......

«ብቻ ባጭሩ ትወጅዋለሽ ማለት ነው.....» በዝምታ ዓይን ትመልስለታለች። - ፍሎቤሩን ያነግትና ወደ አደኑ ያመራል.......

# ፳

## አደፍርስ

ከማሳ ማሳ ሲዟዟር ብዙ ጊዜ ይቆያል። ቆቆችም አግኝቶ እየተኮሰባቸው ይስታል። ወደ ስምንት ሰዓት ገደማ እወይዘሮ አሰጋሽ ቤት በታች ይመለስና ሲተኳኩስ ይሰማል። ጺወኔ የተቀቀለ ባርማሽላ ትይዝለትና ወደ ቦታው ትሄዳለች። እንደ ደረሰች ደጋግሞ ሲተኩስ ታየዋለች። ሌሎች የገበሬ ሚስቶች ራቅ ራቅ ካሉ ጐጆዎች ወጥተው ወደ አደፍርስ እየተመለከቱ ይናገራል -

«እንዴት ያለች ሲካካ ዶሮ አለችኝ፤ ሰሙኔ ከሁለት ፍራንክ እሸጥልዎታለሁ..... ጥይትዎን ከሚያባክኑ......» ትላለች አንዷ። -

«እዚህ እኛ ማሳ ውስጥኮ ብቻ ሦስት ጥይት መተኮሳቸው ነው» ትቀጥላለች ሌላዋ ኮረዳ መሳይ። -

«ሰሙኔም ቢሆን እሸጥልዎታለሁ፤ ለመጠማጥ ከምገብር......» ታግባባለች የመጀመሪያዋ። -

«እኔም ያን ኩብኩባ ዶሮዬን እሸጥላቸዋለሁ ከፈለጉ ስሙኒ ካራት ፍራንክ ይግዙኝ..... ምነው ካንቺ በልታ በልታ እንዳውራ ከምትኮኩል መሲና የኔ፥ ኩብኩባ ይሻላቸዋል.......» ኮረዳዋ ትደግማለች።

«እኔ ቆቅ ነው የምፈልገው፤ የእናንተን ዶሮ አልፈልግም!» ይላቸዋል ጮክ ብሎ ንዴት በያዘው ድምፅ ዓይነት።

«ቆቆቹ ሁሉኮ እየተነሡ ሲበሩ ሳላየናቸው - ከሚደክሙ ብለን ነው......

«ለመጠጥማ ገብሯቸው እነሱን.....

«ምናልባት ለምሳ ይሹ እንደሁ ግዴለም ይሁን አምስት ዕንቁላል እጨምርልዎታለሁ.......

«ሞትና ሕይወት! ቆቅ ነው የምፈልገው አልኩኝኮ......!

«ነገም እዚህ ከዋሉ በወጥመድ ይገፔ እሸጥልዎታለሁ......» ይለዋል አንድ እረኛ ድንገት ከየት እንደ መጣ ሳይታይ አጠገቡ ደርሶ ቆሞ።

«እኔ ኰበኩባ የቆቆቹን ያህል ባይገራ ገንዘብዎን እመልሳለሁ፤ በኔ ይሁንብዎ - ምነው! በንዴት ለምን ጥይትዎን ይጨርሳሉ በዛሬ ጥይት ውድነት.....?

«ለምሳ ሳትገባ ቀረህ..... ባርማሽላ ይዝልህ መጥቻለሁ!» ትለዋለች ጺወኔ፤ ራቅ ብላ አጠገቡ እንደ ደረሰች

«ኩብካብ - ባርማሽላ - ዶሮ!!» በባሻገሩ ተረተር ሥር እሚያየው ቋጥኝ ላይ እያነጣጠረ የተረፉትን ሁለት ጥይቶች ይተኩስና - በኀይል እየተራመደ ወደ ቋጥኙ ያመራል። - ጺወኔ ልትደርስበት አልቻለችም፤ ብዙ ወደ ኋላ ትቀራለች።

«አሁንስ ቀናቸው መሰለኝ» ስትል ትሰማለች ከገበሬ ሚስቶቹ አንዷ - ምንጥቅ ብሎ የተነሣ አረማመዱን ተመልክታ። -

«ዕድለኛ ልጅ የሻለቃው ልጅ ገድ ይሆናላ!» ትላለች ሌላዋ።

«......ከደኀና ተወለድ ወይም ከደኀና ተጠጋ አዶለም......?

«ጦሎተኛ ማንም ከዘራቸው እንደሷ የለም.....

አደፍርስ ሰውነቱን ስለ ወበቀው ጃኬቱን አውልቆ እትከሻው ላይ ወርወር በማድረግ ዝግ ብሎ ወደ ቤቱ ሲያመራ ያዩታል ባሻገራቸው። - አለመጠን አልቦት - ፊቱን አንገቱም እየተንቸፈቸፈ -

«አልተሳሳትሽም - ያውና በብረቱ ነው መሰለኝ ትከሻው ላይ ምንም አንጠልጥሎ ይታያል.....

«አልኩሽኮ.......!

«አዎ አልተሳሳትሽም......!

ጺወኔ ያቅሟን ያህል እየተራመደች እነሱ ደጅ እሚታየው ተረተር ላይ ስትደርስ ትንፋሿን ለመዋጥ ያህል አረፍ ትላለች - ከቀኟ ከግራዋ ከፊለ ፊቷ ሙሉ ይፋት ይታያል - የጥሙጋ ጋሎች የዘላን አዳሎች የወላስማዎች መዘዋወሪያ የነበረው ይፋት...... እነ ሳብር አዲን እነ ማሕፉድ ኣይሸመቁ እነ ዐምደ ጽዮንን እነ ዘርአ ያዕቆብን ያሰለቹበት ይፋት...... በአንድ ዘመን መንዝና ይፋት ይባል የነበረው ዛሬ ደግሞ ተለውጦ ይፋትና ጥሙጋ ተብሎ የተሰየመው - አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰባ ገባሮች አንድ ሺህ ዘጠኝ

መቶ ኀምሳ ግንደ በሎች ስምንት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሰሞነተኝኖች አምስት መቶ አሥር ሲሶ አራሾች የሚኖሩበት ይፋት። - አቅራቢያዋ ሸለቆ ውስጥ ደግሞ እንደ ምልክት የትልቅ መሣሪያ ድምፅ ያስገመግምና ተራራውን ሸጥ ሸለቆውን ትሶ ለመውጣት የሚታገል የሚመስል የሽለላ ድርቅርቅታ ይሰማል ሲያስተጋባ - ከጋራ ጋራ!

«ወንድሙን ሲገድሉት ወንድሙን ካልከፋ

አቅርቡለት ልብሱን ደሙ እንዲከረፋው።

የናቴ አገር ያባቴ አገር ዱሬ፥

እገባብሻለሁ የትም ዞሬ ዞሬ!

እያለ ሲያናግረው......

# ፳፩

# አደፍርስ

ዝናቡ አቋርጦ የመብረቁ ዳመና አልፎ ከንፈሩን የገመጠ የሚመስል ነፋስ ውደቱን መነስነስ ጀምሯል። እንደ ስጋጃ የተነጠፈው ሣር በደማቅ አረንጓዴና በወርቅማ ቀለም አደግድጓል። - በተሸከመው ውሃ ምክንያት እርስ በርሱ የተያያዘው የዛፍ ቅጠል በሕይወት ይርመሰመሳል - እንዳይታይ ዓይንን እያጥበረበረ። ኃይለኛ የሆነ የአዝእርትና ዕፀዋት ሽታ ከየቦታው ይምቦለቦላል። - በማይመረመር ጥበቡ ተብትቦ..... እንቅ - ጭንቅ - እምቅ - ጥብብ - ስብርብር - ክርሽምሽም አድርጐ እከሌን በማይባል የልብ ፍላጐት የሚያናውጥ ጸጥታ ባካባቢው ነግሥዋል። - ጺወኔ እንደ ልማዷ እግቢያቸው ሽምጥ ሥር ከውስጥ በኩል ቆማለች። - ዓይኖቿ ለብዙ ጊዜ አርቀው ሲመለከቱ ይቆዩና ቀስ በቀስ እየቀረቡ ይመጣሉ፥ በደጅዋ ተረተር ላይ እየዳኑ በየቆሙት ዛፎች - በየግንዳቸው - በያይነታቸው ላይ (አዝጋሮ፥ አደር ባሎች መዛዝኝ....... እመዛዝኙ ባላባልቾዎች መካከል - እበታቹ እሚታየው ሸለቆ ውስጥ እየተመለከተ) ጀርባውን ሰጥቶ እተቀመጠው አደፍርስ ላይ አርፈው - ወደ ራሷ እስኪመለሱ ድረስ። - ምንጥቅ ብላ ወጥታ አጠገቡ ትቆማለች።

«ተቀይመኸኛል መቼም፤ ልቤ ነግሮኛል» ትለዋለች ቀስ ብላ......

«ድንቁርናና ዕውቀት! ለምንድነው የምቀየምሽ....... አልተቀየምሁሽም» ይመልስላታል አደፍርስ ባይጠያየቋ የተደነቀ በሚመስል ድምፅ።

«የለም ተቀይመኸኛል - አደኑ ቦታ ስለመጣሁብህ.....!

«አልተቀየምሁሽም አልኩሽ እንግዲህ.....

«እሺ እውነት ካልተቀየከኝ እንደ ዱሮው ፈታ በልና እንጫወት - እምልህ ወይም አኮርዲዎውን አሰማኝ.....

«አላሰኘኝም......

«እኔን አሰኝቶኛል......

«አንገቱን ወዝወዝ ወዝወዝ እያደረገ «አላሰኘኝም ማለት አማርኛ......

«እሺ እሺ ይቅርብኝ...... እንግዲያው እኔ እንድጫወትልህ ትፈልጋለህ.......?

«ምንድነው የምትጫወችልኝ.......?

«ክራር......

«እናትሽ የተቆጡሽስ እንደሆነ.......?

«እሱ የኔ ጉዳይ ነው አንተ ምንቸገረህ - ብቻ ትፈልጋለህ አትፈልግም.......?

«የለም እናትሽ ይቆጡሻል......

«ግዴለህምኮ አልኩህ......

«ደግሞ በቀደም ተጫውተሽ እንዳበቃሽ፥ ልምምድ ሳትደርጊ መቆየትሽን ነግረሽኛል.....

«ምነው ከትናንት ወዲያ ጧት የተጫወትሁ ጊዜ ያሻሻልኩ አልመሰለህም.......?

«ከትናንት ወዲያ ጧት? አሻሽለሽ ይሆናል - ብቻ እኔ እስከዚህ ትዝ አይለኝም.....

«ደስ ብሎኝ ከተጫወትሁ እንግዲያውስ ብዙ ልዩነት አያመጣም........

«ብዙ ልዩነት ያመጣ እንደሁ ብቻ አፍሬም አላበቃ......

«ትናንትና ተኩሰህ፤ ስትስት ሳይህ እንዳፈርከው........?» ሳትስበው ያመልጣትና ትደነግጣለች «......ወደኸው ነበርኮ ታዲያ ጨዋታዬን.......» ትቀጥላለች ወዲያውም እርሱን የለወጠች ይመስላትና።

«ድንቁርናና ዕውቀት.......! ትዝ የማይለኝን እንዴት እወዳለሁ......» ይመልሳል አደፍርስ ቅሬታው በድምፁ እየታወቀ።

«እምልህ የትናንት ወዲያ ጧቱን......

«ትዝም....... ትዝም......

«ከፈለግህ እንደ ገና ዛሬ ልጫወትልህ እችላለሁ - እምልህ - ከፈለግህ.....

«ትዝታው ውሎ ያላደረ ነገር...... አላደክምሽም......!

«አይመስለኝም ለኔ ድካም የሰጋህ...... አላምንህም......

«ሞትና ሕይወት! በጣም ትገርሚያለሽ......! ነገርሽን ሁሉ ሳየው ድካምሽ ሁሉ እልም ስልም ድክም ጭርስ የሚያደርግ፥ ወፎች የሚያረግፍ የሚያነሆልል ጣዕመ ዜማሽን እንደ ገና አስሰሚኝ እንድልሽ ዓይነት የፈለግሽ ነው የሚመስለው....... በጣም በጣም ግሩም ትጫወቻለሽ እንድልሽ ዓይነት....... ወይም..... ወይም..... ወይም...... ብቻ......

«ቢሆንም ምናልባት ብጫወትልህ ግዴለም ይህናል...... እምልህ ጊዜ ለማሳለፍ ያህል.....

«ግድአለኝ እንጂ እንዴት ግድ የለኝም። - አንች የመንደር አሪሆ ወይም አዝማሪ አይደለሽም...... እመየቴ እናትሽም ይኸንኑ ዐውቀው ነው እንዳትጫወች የሚከለክሉሽ......

«በርግጥ አንተ እንድጫወት የማትፈልግበትን ምክንያት ልንገርህ?

«ምን ትነግሪኛለሽ እኔ የነገርኩሽ.....

«አንተ እውነቱን አልነገርከኝም.....

«አታደርጊውም! ደግሞ.....

«ደግሞም እኔ እስከዚህ ችሎታዬን አልጠራጠረውም...... የሰማኝም ሁሉ ሳይደሰት ቀርቶ አያውቅም......

«የራሱ ጉዳይ.....

«ከሰሚዎቼ ውስጥ አንተም ስለነበርህ ልትደስት ይገባ፥ ነበር.......» ፈገግ ይልና - ወዲያው ገታ ያረጋል እራሱን። -

«ነግሬሻለሁኮ እንደ ሌሎቹ ሰዎች መቀላመዱን አጥቼው አይደለም....... በጣም ስለሚያሰላኝ ብቻ ነው......

«.......እና ታዲያ ከትናንት ወዲያ፥ ምንም ሳትል ሄደህ ቢሆን ኖሮ...... በፊትህ ላይ ምንም ነገር ልውውጥ ባላይ ኖሮ እርግጠኛ ነኝ እታመም ነበር......

«ፊቴ ላይ! ፊቴ ላይ! አብደሻል........!

«አዎ ፊትህ ላይ አይቻለሁ........!

«በእግዚአብሔር እንስማው፤ ምን ይሆን ያየሽው!» በማያምንና በሚያንጓልል ዓይነት ድምፅ።

«አይቻለሁ አይቻለሁ.......!

«ያየሽውኮ ምንድነው ነው የምልሽ.......?

«እንባ! እንባ ነው ያየሁት...... ምንም እንኳ ለመደበቅ ብትታገል.......እናንተ ወንዶች ግን ትገርማላችሁ..... የልባችሁን ቋንቋ ለመደበቅ መድከማችሁ..... ምን እንደሚያሳፍራችሁ እንጃ! - ይልቅ አንዳንዴ ያለቅጥ ዐውቅን ብላችሁ ስለ ሃይማኖት ስለ ቤተ ክርስቲያን ስለ ንጉሥ ስለምትለፈልፉት እፈሩ......ወንዶች ስትባሉ የሚያስቅ ኩራት አለባችሁ......

«ሀ - ሀ - ሀ - ሀ - ድንቁርናና ዕውቀት ይልሻል ይኸ ነው......! እውነት ለመናገር እፍሬዋ ዓይን ላይ በሆነ ባልገረመኝ! እኔ ዓይን ላይ እንባ.......? ተሳስተሻል ጺወኔ...... በጣም ተሳስተሻል.......!

«አጉል - አጉል - አጉል ኩሩ ነህ...... ቢታወቅህ...... ያላየሁትን አየሁ አልልም እኔ......

«ያየሁትን ነገር ባላይ እታመም ነበር ብለሻለኮ አንችማ? ጨርሰሽዋል.......!

«አዎ ብያለሁ......

«ያየሽ መስለሽ ስለዚህ......ራስሽን በራስሽ ደለልሽው......ለምን ይመስልሻል......?

«ያየሁትን አላየሽም ብለህ ከካድህ...... ምን አደካከመኝ መልስ ለመስጠት! መድከም አያሻም......

«ድንቁርናና ዕውቀት ብሎ ነገር..... ኩሩ ስለሆንሽ ነው...... ራስሽን የደለልሽው! እኔ እመልስልሻለሁ...... ኩሩ ስለሆንሽ......!

«ይሆን ይሆናል...... ሁሉም በየበኩሉ ኩሩ ነው...... ኩራት ራት ተብሎ የለም...... ኩራት ራት....... ምናልባት አንተ ኩራት የለህ ይሆናል......ማለቴ...... ምናልባት አንተን እኔን የተሰማኝ አልተሰማህ......» ሳትጨርሰው ትቆማለች -

«ምን አልሽ......?» ይጠይቃታል አደፍርስ ደከም፥ ኮስተር ባለ ድምፅ። -

«ምንም አላልኩ - እምልህ፥ ሁለተኛ አይለምደኝም ቀልድ - ካንተ ጋር...... ምሳሌ ነው ጠላቴ..... መቀለዴኮ ደሞ ያልሁት በሆነ...... ምን ቆርጦኝ......» ትለዋለች፤ ድምፅዋ እየተርገበገበ -

እስከዚህ ድረስ እሷን የሚያስጨንቅበት ምክንያት ስለልነበረው ሁኔታዋ አንጀቱን ይነካዋል። ልቧን መልሶ አንጀቷን ለማረጋጋት ይፈልጋል። - ምንም ነገር ለማለት ግን ያቅተዋል።

«.......ምሳሌ ነው ጠላቴ...... ጕርፉም ደጋግሞ ነገሮኛ...... እሱ እዚህ ቢኖር ኖሮ ምንኛ በተስማማ.......» ትቀጥላለች ጺወኔ - ዘወር ብላ ዓይኖቹን ባይኖቿ ይዛ በማቆም፤ እርስ በርሳቸው የሚመጣጠጡ ይመስል...... የሷ ፊት ደም እየሠገረ የሱ ፊት ደም ዓይኑን ሊያፈርጠው ዓይነት እያሰመሰመ.....

«አንችን እያየ በምትናገሪው የማይስማማ የለም.....» እስኪያሰኘው..... ያመቀውን ስሜት፥ እያተነነ - እያጐመ - እያወረዛ እስኪያሶጣው። - ጺወኔን ድንገት ግራ ይገባታል። -

«እኔን እያየ የማስማማ የለም?» ደሟ እንደ ገና ፊቷ ላይ ይመለሳል «.......ደስ ይልሃል ላንተ የምለው ነገር...... ደስ ይልሃል......? ደስ እልሃለሁ እኔ......?» አደፍርስ እንደ ገና የሚመልሰው ያጣና ግራ ይገባዋል «......ሁልጊዜም እንዳሁንህ ብትናገር......» ዓይኑን መሸሽ ታመጣለች ስትናገር..... የምትናገረውም እየተበጣጠሰባት ይሂድና ትቆማለች።

«አብዛኛውን ጊዜ አንጀታዊ ንግግር መናገር አስቸጋሪ ነው......» ይጀምራል አደፍርስ ይቆይ ይቆይና መቀጠል ግን ያቅተዋል። እንደ ገና ምንም ሳይነጋገሩ ብዙ ጊዜ ይቆያሉ፤ አንዳቸው ያንዳቸውን መኖር የዘነጉት ይመስል - ድንገት ነው..... ያን እንዲያ የተቸነነ ጸጥታ ጥሳ......

«እሺ አሁን ታዲያ ምን ላድርግልህ?» ብላ የምትጠይቀው ግምባሯን ሰብሰብ፥ ዘቅዘቅ - ዓይኖቿን ቦግ - ፊቷን ፈገግ እያደረገች «......እምልህ እንዳይሰለችህ,

«መሰልቸት? ሞትና ሕይወት! ማን አለሽ ሰለቸኝ?» ከሌላ ዓለም ውስጥ የሚፈልቅ በሚመስል ድምፅ የሚመልስላት አደፍርስም «......ካንቺ ጋር ሆኖ ስልቸታ...... ታሾፊብኛለሽ መሰለኝ......?

«ቢሆንም ቢሆንም.......» በቀልደኛ ዓይነት ዓይኖች ታጠምደዋለች እንደ ገና

«እሺ - እንግዲያው እንዳልሽ...... መች ያጣላናል፤ አያጣላንም ይኸ......እኔ ደሞ...... በተራዬ......

«አኮርዲዎ ትጫወትልኛለህ.......!» ሕይወት ትፍለቀለቅ ትምቦለቦላለች ካይኖቿ..... የሥራ አካላቷ ይፍማል..... በደስታ ይበረቀቃል። - ከወገቧ ቅንጥስ ያለች በመምሰል ተነሥታ ትመዠረጋለች፤ ከራሩን ለማምጣት። - በዓይኖኡ እየተከተላት አደፍርስ..... ሮጥ - ሮጥ - ሮጥ - ሮጥ - ...... እዋናው አጥር በር - አፍ ትደርሳለች። - ጨርሳ ልትገባ ሁለት እግሮቿ..... መጨረሻ - ውዝ - ውዝ - ውዝ - ውዝ ይላሉ። - በዚያን ቅጽበት አደፍርስ አይሰሙ ስሜት ይሰማዋል...... ስግጥጥ የሚያደርግ..... ጭንቅላቷን ደረቷን ወገቧን ውጦ እግሮቿን ብቻ አልዋጥ ብለው አስቸገረው ከአፉ ውጪ ሲወዛወዙ.....

«ነገርኩህ እንግዲህ እከንፈሬ ላይ ሳቅ አልፈልግም..... እይምን መገለጢጥነት ነው እቴ!» ይላሉ ወይዘሮ አሰጋሽ - የእጅና የእጅ ማስደገፊያ ያለው - ባላቸው በጣሊያን ጊዜ እዘረፉት ወንበር ላይ እግቢው ውስጥ ወርዶፉ ጉጀ አጠገብ ቁጭ ብለው «.......አዎ አያስፈልግም..... ሳቅና..... ምንድነው ስሙ..... ቤት ያጠፋል......

«......ባይስቁስ..... ትንሽ ከንፈርዎን ለቀቅ ባደርገው - እምልዎት ኩርትም ብሎ ባይጋጠም ምናለበት?» ያባብላቸዋል ክብረት መሣያ ሽራውን በቡርሽ እየደባበሰ «ምነው እስከዚህ ሥራዬን የማላውቅ አይምሰልዎት - የሚካኤልን ቤተክሲያን ነው የማስመስልዎት.....

«ምን ቢያገድ! እኔ ከጌታዬ ከፈጣሪዬ አልወዳደርም። - ቢሆንም አሰጋሽ አሰጋሽ ነች፤ የማንም ደንጐሌጥ እኞ አይደለችም፤ የራሷ የሆነ ክብር አላት - አዎ እሱን አትርሳ ማለቴ ነው.....

«የቀሚስዎ ቀለም ምን ዓይነት እንዲሆን ይፈልጋሉ.......?

«ምን ዓይነት ነው የለበስኩት?» ይሉታል ኮስተር ይሉና - ወዲያውም ከመቀመጫቸው ፍንጥር ብለው ወደ ክብረት በመሄድና የሚነዳድፈውን በመመለካከት «ይኸ ደግሞ የምን ጉጀ ነው ከኋላዬ የሚታየው? እናንተ የከተማ

ሰዎችኮ የነገር አካሄዳችሁ አይታወቅም...... እየፈጩ ጥሬ ነገር - የምን ጐጆ ነው? ይኸን ነውኮ የምልህ.....» በጣታቸው እያመለከቱ -

«የወርዶፋ......!

«እጡ.... ብ - እጡብ! ባንተ ቤት አሰጋሽን ከጐጆ ጋር ስትነሣት የማይገባት ይመስልሃል? ተሳስተሃል - በጣም ተሳስተሃል......» ራመድ ራመድ ብለው ወደ እልፍኛቸው ይሄዱና ሮማንን የከት ልብሷን - እግር አሻሻቸውን ልጅ አዲስ የተሰፋለትን እጀ ጠባብ አስለብሰው ይመለሳሉ «አንቺ በይ ጃንጥላውን አጥሊኝና ከኋላዬ ቁሚ..... አንተ ደሞ እግር እግሬን እያየህ እዚህጋ ተቀመጥ.....» በእግራቸው የእግራቸውን አጠገብ ያመለከቱና ቀና ብለው «......በል እንግዲህ አሁን ልታነሣን ትችላለህ......ዐወቅሽ ዐውቅሽ ቢሏት መጣፍ አጠበች...... ሁሉንም ዐውቀን ትተነው ነው፤ ንቀነው ነው..... እና..... አይምሰልህ......

## ፳፪

# አደፍርስ

ሮማን እኩሬው አጠገብ ቁጭ ብላ እግሮቿን ትታጠባለች፤ ተረከዞቿን እድንጋይ ላይ እየፈገፈገች ባቶቿን ሁሉ ሳይቀር ትፈትጋቸዋለች። - እስኪሟልጩ። - በተለይ ከፊቷ ቅልጥልጥ እየጠረገች አበስ አበስ ባደረገቻቸውማ ጊዜ እንደ ቅቤ ቅል ማብረቅረቅ ይጀምራሉ። እንደ ጨረሰች እንስራዋን ሞልታ ትሽከምና ወደ ቤቷ ትመለሳለች።

ሁለተኛ ጊዜ ወደ መቅጃ ስትወርድ በአባቷ ጐጆ አጠገብ ታልፋለች፤ የበረቱን መካከል እግር የለመደ መሄጃ በመተው። - አደፍርስና ጺወኔ በግርምቡድ ተቀምጠዋል እጐጆዋ አጠገብ። - የሰዓት በኋላውን በራድ አየር እየጠጡ.....

«.......ግሩም የሆነች ነገር ይቺ ሮማን የምትሏት ልጅ......» ይናገራል አደፍርስ እንደ ዘበት በአጠገባቸው ማለፏ ምክንያት ይሆነውና። ጺወኔ አትመልስለትም «...... ብትማር ኖሮ እንዴት ያለች የቤት እመቤት በወጣት» ይቀጥላል አደፍርስ። - አሁንም አትመልስለትም «.......የሚገርመውኮ ምኗ መሰለሽ......? የልቧ ትልቅነት..... እና ደሞ ወሰን የማይከልለው የሚመስለው አስተያየቷ...... ሩቅ - ሩቅ - ሩቅኮ ነው አመለካከቷ......» ዘወር ብላ አየት ታደርገውና ወዲያው መለስ ትላለች «......እንዲህ እንዲህ ዓይነቷ አሁን፥ እዚህ እባላገር በሞያሌ በትኋን በበረሮ በቁንጫና፥ ቅማል ተጨብጣ ስትቀር አያሳዝንም?» ይቀጥላል አደፍርስ «.......በውነት ነው የምልሽ በጣም ያሳዝናል....

«አቶ ክብረት የሚካኤልን ታቦት አስመስያቼዋለሁ እናትሽን ይሉኛል......በፎተግራፏ ላይ። - እማማ ግን እጅግም አልወደደችላቸው......» ትናገራለች ጺወኔ ታዳምጥ ታዳምጥና።

«......ሮማ ነች ታቦት ማለት..... ድምፅዋን አልሰማሽውም? እንደ ቤተክሲያን መርዋ እጠምቧ ብሎ የሕይወትን እውነታ በለፈፈ ጊዜ...... በዚያ ላይ ደሞ ልበ ገርነቷ.....

«......ያይኖቼን ስንጥቦች የቁልቁሊት አድርጓቸዋል...... ፊቴን ያለመልኩ መልክ ሰጥቶታል..... አጥቁሮታል......... ጣቶቼን አጉል እርዝማኔ ሰጥቷቸዋል...... ጥፍሮቼንም እንደ ባለጌ ጥፍር አሰረዝሞ የጻረ ሞት ጥፍር አስመስሎብኛል...... ውቃቢዬን ደስ የማይለው ብዙ ነገር ጨምሮበታል ነው የምትለው.....

«......የጅና የግሯ ነገርኮ ልዩ ነው....... እምልሽ የሚገርም ነገር......ድሃን እግዜር ይጠብቀዋል ማለት......እጄንና እግሬን ሙያሌ አያውቀኝም አለች ስታጫውተኝ.....

«ወዲያ ወደ ድብኝት ውስጥ አስቀምጭው ብያታለሁ..... ምን ዕዳ አለባት እስከዚያ ውቃቢዋ ካልወደደው.......?

«.......ውቃቢ የወደደው ነገር፤ እውነትሽን ነው - ያስደንግጥ አለው...... ስለ ልቡሰ ጥላ እንዳጫወትኩሽ ማለት ነው - አጥልቆ ከተመለከቱት...... የልቡሰ ጥላ ግንኙነት......ልቡሰ ጥላ ሲገጥም......» እየተናገረ ብድግ ይልና ወደ ኩሬው አቅጣጫ ይሄዳል። -

# ፳፫

# አደፍርስ

እኩሬው አጠገብ ሲደርስ ሮማንን እጉዳባው ውስጥ ገብታ ስትቀዳ ያያታል። - ለስለስ ባለ ድምፅ ስሟን ይጠራዋል። ድንግጥ ትልና የምትቀዳበት ሸክና ከጅዋ ያመልጣታል። - አንድ አህያ ወደ ኩሬው አፋፍ ላይ ስታመራ ያይና ደእብቅ ይላል አደፍርስ። - ሮማን ኮቴ ትሰማለች። - ምንም ዓይነት ፍጥረት ግን አይታይም። - የምትቀዳበት ሸክና እንዳመለጣት ብቅ ጥልቅ እያለ ተንሳፍፎ ርቆ ሄዶ ነበርና በቁራጭ እንጨት ቀስ እያለች እየገፋች ወዳጠገቧ ልትመልሰው ትሞክራለች። - ይደግምና ቀስ ብሎ ስሟን ይጠራዋል አደፍርስ - ድንግጥ ትልና አሁንም ቀና ትላለች። ምንም ዓይነት ፍጥረት ግን አይታይም። ሸክናው ወደ ነበረበት ይመለሳል። - እንጨቱ እየገፋት እንደ ገና ወዳጠገቧ ልታመጣው ትሞክራለች። ሦስተኛ ጊዜ ይጠራዋል ስሟን አደፍርስ። - ድንግጥ ብላ ቀና ትላለች። - አህያይቱ እጉድባው ጠርዝ እሚታየው ድንጋይ ላይ ብቅ ብላ ቆማለች። የቀኝ እግሯን ሰኮና አስቀድማ...... ሮማን የባሰውን ተደናግጣ እንስራዋን ተሸክማ ልትወጣ ስትል

«በጣም በጣም ድንጉጥ ነሽ!» እያለ ብቅ ይላል አደፍርስ፥ ከወደ ተደበቀበት። -

«እርስዎ ነዎት ለካ? እኔ ደሞ አህያዋ አፍ አወጣች ብዬ ፈርቼ መሸሼ ነበር..... እንዴት አስደነገጡኝ.......» ትናገራለች ሮማን ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ «......ምን አስቤዎት እዚህ..... ከጂወኔ ጋርኮ ያየሁዎት መስሎኝ......!

«በቀደም ከኋላሽ አስልቼ ስለዳኰጥሁሽ አኩርፈሻል መቼም......?

«ኩርፊያ......! የምን ኩርፊያ......! ኩርፊያ አላውቅም እኔ። - ይልቅ ያኮረፈች ጺወኔ ነች..... እኩል ቤት ረገጥሽ የሚሉ ፊሊጥ አምጥታለች......

«አንቺ አታኮርፊም.......?

«አላኮርፍም......

«ምንም ቢያደርጉሽ.......?

«ምንም ቢያደርጉኝ...... ቆይ ይኸን እንስራዬን ገልብጬ ስመለስ እንጫወታለን......» እመንገዷ ገብታ ሽቅብ ታቀናለች።

«........አሁን ለምሳሌ እጅዋን ያዝ ባደርገው......ጡቷን ጨበጥ...... ትከሻዋን አቀፍ እንደማድረግ...... ሄሄ....... ውሽቷን ነው፤ ትከፋለች። ደርሶ መከፋት ሊበቃት...... ስትሮጥ ነው ሄዳ የምትናገረው ለቤተ ሰቡ ሁሉ። - በተለይ ደሞ ለጺወኔ.......! ምን ትል እንዲህ እንዲህ አረገኝ ስትላት? እሷን እንኳን ገና እስከዚህ አልተጠጋኋትም...... ከዚያ ላይ ደሞ የወርዶፋ ልጅ...... በሷ ቤት እሷ ያሰጋሽ ልጅ ስለሆነች የምትበልጥብኝ መስሏታል........

አሁን ለምሳሌ የትኛዋን ትመርጣለህ ብባል ለሚስትነት...... አላገባም እንጂ እኔ....... እውነት ነው የትኛዋን እመርጣለሁ......? ሮማን ድንጉጥ ነገር እኔ እወዳለሁ። - ሙዚቃስ? ሙዚቃ ደሞ በጣም እወዳለሁ። - ጺወኔ የሙዚቃ ሰው ነች። - ግንኮ ሮማን ድምፄን ሳይቀር ወዳዋለች። አዎ አዎ፥ ግን! ድንቁርናአዋ ነው ድምፄን ያስወደዳት....... ጐርናና አይደል በርዳዳ የኔ ድምፅ...... ወይ ደሞ እንደ ሌሎቹ ቃጭል አይደል መረዋ? - አይመስለኝም፤ የመውደዷን ያህል ነው የተናገረችው......» አህያዋ እጉድባው ትገባና ጠጥታ ተመለሳለች....... ጠጠር እያነሣ ወደ ኩሬው ውስጥ መወርወር ይጀምራል - እያረፈ - እያረፈ........ዝም ብሎ ይወረውራል - ጠብታ ትንሽ ክብ - ትልቅ - ትልልቅ - ትልልቅ - ትልልቅ - ትልልልልቅ ክቦች እየፈጠረ ይጠፋል። - ሮማን ትመለሳለች። ራቅ ብሎ ኋላዋ ተከትሏታል ጴጥሮስ።

«.......እምልሽ...... እምልሽ.....» ይጀምራል አደፍርስ........ አህያዋ ብቅ አለችበት ድንጋይ ላይ ቁጭ ትልና ሮማን፥ እግሮቿን ወደ ታች ዘርግታ ውዝ ውዝ እያደረገች እሱን እሱን ስትመለከተው «እምልሽ....... እውነት እውነት...... አታኮርፊም......?

«.......አላኮርፍም!» ትመልስለታለች፤ አንገቷን ቀና ፊቷን ፈገግ እንደ ማድረግ ታፍታታና - በሌላ ሰው ላይ ታይቶ የማይታወቅ ልዩ ስጦታ ያገኘባት ይመስላታል።

«አሁን ለምሳሌ፥ ጠጋ ብዬ እጅሽን ያዝ ባደርገው.....

«ምንቸገረኝ! ያዙት - ይኸውልዎ.......! ያዙት....... እውነቴን ነው.......» እያለች እሱ ወደ ተቀመጠበት ወደ ባሻገሯ ጠርዝ ላይ ትመጣለች። - አደፍርስ እግር እግሯን ይመለከታል -

«.......እሺ....... ጡትሽንስ ብነካው!» ይላታል በተቻኮለ አነጋገር። -

«ምን ቸገረኝ ታዲያ...... ይንኩት......! አላፍርምኮ.......! የሚያፍር ባሪያ ብቻ ነው ይላሉ እመየቴ.......! ይኸውልዎ ይንኩት...... ትለዋለች አንገት ልብሷን ገለጥ ታደርግና። - ሲፈራ ሲቸር ቁስ የሚነካ ይመስል ይነካዋል «አይዞዎ ይንኩት...... አያምምኮ እስከዚህ...... ይንኩት......

ጴጥሮስ ሰውነቱ ሁሉ ይለዋወጣል። - ከመ ቅጽበት እየሮጠ ይወጣና አቀበቱን ለጺወኔ የንገራታል። - ከተልም ይላትና ወደ ጉድባው እሚወስደውን መንገድ ስትገባ ከኋላው ሹልክ ብሎ ወደ ወርዶፋ ሥምሪት ይሮጣል። - ለሱ ደሞ ለመንገር። -

«.......እግሮቼ ቆንጆ አልሆኑም?» ትጠይቀዋለች ሮማን በተራዋ፤ ባንድ እጅዋ አንድ እግሯን አሸት አሸት እያደረገችና ተረከዟን ሽቅብ እየገለጠች። -

«........እምልሽ..... ለምሳሌ - ይኸ እየውሃው ዳር ያለው ሜጣን ያገኘሽስ እንደሁ......

«አያገኘኝም........!

«ጡትሽን ንክስ ነው የማደርገው.......

«ጡት? ጡት አይነካም እሱ.......! ልጃገረድ ይተናኮላል ነው የሚባለው እንጂ ጡት አይነካም። - አሁንኮ ግመሬ ዝንጀሮም ቢሆን ይተናኮላል። - ወንድና ሴት ወንድና ሴት እየሆንን ሥምሪት የምውለው.......

«........ወንድና ሴት ስትሆኑ አየንካችሁም........?

«ወንዱ ከሴቷ አጠገብ ካልተለየ አይነካም....... ግን በተለይ ሲመሽ መጠንቀቅ ያሻል ይባላል። - ወይ ወገቡን ለመዛወር፥ ወይ ለሽንቱ ወረድ ያለ ጊዜ ወንዱ ያነዬ ነው እማማው ላይ ወጥቶ የሚደፍራት...... እሁን በቅርቡ አንዷን እንዲህ አበላሽቷታል ተብሎ ይወራ ነበር...... አዎ፥ እንጨት ሰበራም ብቻችንን አንሄድም.......!

«ጡቶቿን ነካ ነካ ማድረግ ይጀምራል እንደ ገና አደፍርስ። - ሮማን እግሮቿን እጥፍ ዘርጋ ታደርጋለች። - ጺወኔ ሁኔታቸውን አየት ታደርግና ምንም ያህል ሳትቆይ ወደ ቤቷ ትመለሳለች። -

«ሰውስ አልፎ አልፎ - እምልሽ እረኞች ገበሬዎች፥...... ሲያንቋቸው አይሞከሩም......?

«አሄሄ....... አይደፍሩም....... ማን በጅ ቢላቸው.......እንሚማታለኒ...... ማን በጅ ቢላቸው.......» ብድግ ብላ ወደ ጉድባው ውስጥ ትገባለች። - ገምቦዋን ትሞላለች ተሸከማ መንገድ ትገባለች «ስመለስ ደሞ እንጫወታለን» ትለውና። -

ጴጥሮስ ለወርዶፋ ይነግርና ቀድሞት ሲሮጥ ይመለሳል፥ ወደ ጉድባው። - ሮማንን ወደ ቤት ስትመለስ ያያታል....... ቆሞ ይላል ላንዳፍታ። - ድንጋይ ያነሣና ወርውሮ ሮማን የተሸከመችውን እንስራ ያደቀዋል። - ውሃው ሰውነቷን ያጠልቀዋል። - እንደ ተደናገጠች ወደ ቤቷም እንደመሄድ ከጀል ታደርግና ግራ ቀኟን አየት አየት አድርጋ ወደ ጉድባው ትመለሳለች። - አደፍርስ ከመቀመችው አልተንቀሳቀሰም። - ሮማንን ሲያያት በርግጥ ይደነግጥና እቅፍ እንደ ማድረግ እጆቹን ዘርጋ አደርጋለሁ ሲል...... ያልታሰበ ውርጅብኝ....... ከጁ ከግሩ - ባንዳፍታ ያጣድፉታል «........ሞትና ሕይወት...... ሞትና ሕይወት...... ሞትና ሕይወት........» እያለ ይዘረዘራል። -

«........ሲያንቃት! ሲያንቃትኮ ነው......! አመልጣለሁ ብላ ስትተናነቅ.......! እስራው የተሰበረው........» እያለ ይጎደራል ወርዶፋም። -

«.......ነገሩ አጉል ይሆናል። - ጥንቃቄ ያስፈልጋል....... ስድ መልቀቅ አይሆኑም...... ብያለሁ በፊት......» ይናገራል ጴጥሮስ በበኩሉ። -

ሮማን ድንገት፥ አጠገቡ መጥታ እንደዚያ ሆና ስትቆም የነበረው ጸጥታ....... ወዲያ ከመቅጽበት የተነሣው ውካታ - ሾፉ - ቀልድና ለገቻ...... ከከበቡት መካከል አንደኛው ቀረብ ይልና እጅ የሚነሣው መስሎ ጉንበስ በማለት ከመሬት ሲደባልቀው የነበረው ሁኔታ....... ወዲያው ሩምታው....... ቻቻታው መሬት እንደዘረጉት። - አረግ መሳይ! አረግ መሳይ! አረግ መሳይ! - አዎ! እሠረው! እሠረው! - በጅራፉ ለምን አታሥረውም? በጅራፉ እሠረው.......! ጥድፊያቸው ትርምሳቸውና ጨኸታቸው በሙሉ..... እሠረው.......! ጥድፊያቸው ትርምሳቸውና ጨኸታቸው በሙሉ....... ራሱን ያስዘነጋዋል ላንዳፍታ አደፍርስን። - አቧራና ትቢያ እየቃመ ታሥሮ ሞትና ሕይወትን ባፉ እንዳንጠለጠለ ይወስዳል ወደ ወይዘሮ አሰጋሽ ዘንድ። -

እየተንቻቹ ሲመጡ ሲሰሙ ብቅ ይላሉ፥ ወይዘሮ አሰጋሽ እደጅ «........የትኛውን ነዶ ሲሰርቅ ነው የያዛችሁት ይኸን ደሞ......ቀልባጣ ውላጅ....... አሰጋሽ ዋዛ መስላዋለች» እያሉ። - ወዲያው እሥረኛው እፊታቸው ይገፈተርና ይቆማል። - እሥረኛይቱ እፊታቸው ትገፈተርና እሥራቸው ትደፋለች «.......ምንድነው ነገሩ!» ይጮሃሉ ወይዘሮ አሰጋሽ........ ዙሪያቸውን ገለምጥ ያደርጉና «.......ወሂዱልኝ ካጠገቤ......!» ሠራተኛው ሁሉ ወደ የሥራቸው ይገባል። ጆሮዋን እያልመዘመዙ ያዝ በማድረግ አንገቷን አስግገው ያስነሥዋትና ወደ እልፍኛቸው ሲያዳፏት «.......አንተ ወርዶፋ...... ወርዶፋ!» እያሉ በመዝናናት አየር መለስ ይሉና በመጥራት «........አሁን ውረድና ምናሳባለን ጥራልኝ.......! እንትፍ ያልኳት ምራቄ ሳትደርስ እንድትደርሽ ተብለሻል በላት! ይኸው.......» እንትፍ ይሉና «......እንትፍ ያልኳት ሳትደርቅ!» ወደ እልፍኛቸው ይገባሉ። ምናሳባለ ባገሩ እይታወቀች የልጃገረድ ክብር ያለ ወይም የሌለ መሆኑን መርምራ የምትናገር ጥሩ መድኅኒተኛ ነች። -

«........በያ እንግዲህ እንስማው!» ይላሉ ወይዘሮ አሰጋሽ። - እትራሳቸው የተሰቀለውን ቁርዝ አውርደው ሁለት ሦስት ጊዜ ካሳረፉባት በኋላ - እንስማው እንጂ......! እንስማው....... እንስማው......!» ይደጋግሚታል፤ የምትበስል የምትበስልበትን ቦታ እየመራረጡ «.......እንስማው.......! እንስማው.......!

## ፳፬

# አደፍርስ

«........አንተ መቼም ብልግና ትሠራለህ ብዬ አይደለም!» ይናገራሉ አቶ ወልዱ በበኩላቸው አደፍርስ ሰውነቱን ከተጣጠበ በኋላ ካጥር ውጪ ወጥተው ሲሄዱ «.......ቢሆንም ግን...... ቢሆንም....... ያገሬውን ጠባይ ማወቅ ነበረብህ!........ አዎ ከዚህ በተሻለ መንገድ መያዝ ነበረብህ እነሱን...... ሠርጓ በመደገስ ላይ ካለ ልጃገረድ ጋር ጨዋታም ቢሆን እንኳ ቢቀርብህ መልካም ነበር.......

«አውሬ! አውሬዎች ናቸው እነሱ አቶ ወልዱ........ ሰዎች አይደሉም.......» ይናገራሉ አደፍርስ ያመቀውን አየር በማስወጣት «አውሬ ያውቃሉ.......? ከነሱ የባሰ አውሬ የለም......

«.......ዐውቀሃቸው ቢሆን ኖሮኮ እስከዚህ ባልተናደድህ...... ተፈጥሯቸው ነው አደፍርስ። - በነሱ ቤት አሁን ትክክለኛ ተግባራቸውን ማሳየታቸው ነው። መሰላችሁ

እንጂ ምንም ያደረግሁት ነገር የለም ብትላቸው....... ሌላው ቀርቶ አባ አዲሴ እንኳን እንዲህ ቢነግሯቸው አይሰሙም...... አይቀበሉም። - ምናሳባለ ብቻ ነች አሁን ዳኛዋ.......

«........እኔ ደሞ እንዴት በሐሳብ ልረዳው ሞከርሁ ይመስልዎታል ወርዶፋን....... እንዲሻሻል! አምልኮ ባዕዱን እንዲተው ልጁንም እንዲያስተምር - ስንት ነገር ይመስልዎታል ያጫወትሁት....... ሥራ እንኳን አስገባሃለሁ ብዬው ነበር...... በዚህ በዋሸንት ጨዋታው.......

«.......ይግባህ አደፍርስ...... እነሱ ያንተ ሐሳብ ምናቸውም አይደል። - የሚጠጡት የሚበሉት የሚጨብቱት...... ይኸ ይኸ ነው እውነታቸው ለነሱ! አንተ የሰጠሃቸውን ተስፋ እንደ ሰማይ ላም አለኝ ነው የሚቆጥሩት........ ቢሆንም ባይሆን ግድ የላቸውም........

«ግድ የላቸውም.......?

«አዎ፥ ግድም የላቸው......

# ፳፫

# አደፍርስ

«ፓሪ በነበርኩ ጊዜ ፍሊጶስ እንለው ነበር፤ እንደዚህ እንዳንተ ዓይነት አስተሳሰብና የነገር አካሄድ የነበረውን...... ታሪክ መቼም ተምረሃልና ሳታውቀው አትቀርም ፍሊጶስን.....

«ፍሊጶስ! ፍሊጶስ......! ትዝም አይለኝ.......» ለማስታወስ ይሞክራል አደፍርስ።

«እንግዲያውስ እኔ እነግርሃለሁ........» ብለው ይጀምራሉ አቶ ወልዱ «.........ፍሊጶስ የማሪትሬዛ ልጅ የኦስትሪያ ንጉሥ ነበር...... ማርትሬዛን ታውቃታለህ መቼም - ይኸ ብሯ እኛ አገር ድረስ ዘምቶ ሥር የሰደደው.......?

«አዎ ስለ እሷ ሰምቻለሁ.......!

«ይኸውልህ እንግዲያው የማሪትሬዛ ልጅ ነው። - እንደዚህ እንደናንተ እንደ ዝመእኑ ልጆች ነፃነት ዕሪና (እኩልነት) ወንድማማችነት በሚሉት የሰው ልጆች ምናብ ያምን ነበር። - እናቱ ማሪቴሪዛ በዘጠና ዘጠኝ ዓመቷ ነው ይባላል የሞተችው። - እንግዲህ አስበው....... ዘጠና ዘጠኝ ዓመታት ስትኖር ስንት ዓይነት ያገዛዝ ያመራር የሥልጠና መጨበጫ ክንዶች እንደነበሯት። - የምትሰጠው ሹመት ከልጅ ልጅ

የሚተላለፍ ነበር። - አባቱ መስፍን የነበረ - ልጁም መስፍን - አባቱ ድሃ የነበረ - ልጁም ድሃ ነበር። ሕዝቡም ተደስቶ ነበር የሚኖረው፤ የበታች ለበላዩ ታዞ የበላይም የበታቹን አንቀጥቅጦ። - ፍሊጶስ እንግዲህ በዕሪና መንፈስ ተነሣሣልህና የበታችና የበላይን ርብራብ አጥፍቶ አንድ ሊያደርግ አቀደ። - ልክ እናቱ እንደ ሞተች መሳፍንቱንና መኳንንቱን እቤተ መንግሥቱ ጋበዘ። - ከብግግሡም በኋላ ወደ የመጡበት እንዳይመለሱ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ዘጋባቸውና ርስትና ሀብታቸውን ለየበታቾቻቸው ከፋፈለው። - የናቴ ቅልቦች ነበር ይባላል የሚላቸው ሲጠራቸው። - ምን ሆነ ይመስልሃል ታዲያ ‹ኤሌጋሊቴ› - ‹ፍራቴርንቴ› - ‹ሊቤርቴ› - የሚባል ምናብ! - በየክፍያውም ትክክለኝነት ስላልነበረ ትንሽና ትልቅ ተፈጠረ። - ፍሊጶስ የፈጠራቸው ትልቆች ማሪትሬዛ ከፈጠረቻቸው ትልቆች ባሱ። ሕዝቡን ገፈፉት አሰቃዩት - መሳንፍቻችንንና መኳንንታችንን ልቀቅልን ብሎ አቤት ሊል ወደ ቤተ መንግሥቱ መጣ። - ፍሊጲሶን ሊገባው አልቻለም። - ከዕሪና ይልቅ የተበላልጦ ኑሮን የመረጡበትን ምክንያት ጠየቃቸው። - ዘረ ድሆች ስለሆንን ድህነቱን ችግሩን መራቡን መጠማቱን መገረፍ መታሠሩን ለምደነዋል - አይሰማንም። - የሚሰማቸውን ጌቶቻችንን ግን ባልለመዱት ሁኔታ ተይዘው ሲሠቃዩ ማየት ስለማንሻ በዚህ ምክንያት ነው ብለው መለሱለት...... ‹ኤጋሊቴ› ብሎ ነገር! ምን አለ ይመስልሃል ታዲያ ፍሊጶስ.......? ባለመማራችሁ ነው፤ ቀስ እያለ ይገባችኋል - አስተማሪም ትምህርት ቤትም አንፈልግም የምንፈልገው ጌቶቻችንን ነው ብለው መለሱለታ....... ጋዳ ማን ሰምቶ። ፍሊጶ በዕሪና ምናብ ተታሏልና ሳይቀበላቸው ቀረ። - ምን ሆነ ይመስልሃል ታዲያ? - አንድ ቀን ሌሊት እነዚሁ ባላገሮች ይመጡና ባላባቶቹ የታሠሩበትን ቤተ መንግሥት መውረር ነዋ!! ወረሩት! እርግጥ ዘበኞቹም ይነቁባቸዋል፤ ብዙዎች ባላገሮች ያልቃሉ - ግን....... አሁን ትክክለኛ ቁጥሩን ረሳሁት ብቻ........ ሦስት ይሁን አራት መሳፍንት ያመልጣሉ......... በዚህ ሁሉ ትርምስ መካከል - ቀላል ነው እንደምታየው - ወገበ ቀላል ሆኖ ከተገኙ - እና በእነዚህ ባመለጡት መሳፍንት እየተመሩ ፍሊጶስ መጠዝጠዝ ጀመሩታ አገሬው! አልቻላቸውም፤ የቀሩትን መሳፍንትና መኳንንት ሁሉ እንዲፈታ አስገደዱት....... የሚገርም ታሪክ ነውኮ? እንዴት ሳትማረው እንደቀረህ አላውቅም.......

«ሳልማረው እንኳ ቀርቼ አይደለም...... ብቻ በጊዜው አላጤንኩትም......

«.......እና ይኸውልህ ፍሊጶስም ካገር አገር ሲያሳድዱት ይመስለኛል በግዞት ሞተ እልሃለሁ..... ለመሐይምን ሕዝብ ደግ የማሰብና የመሥራት ዋጋው........

«በእርስዎ አስተያየት ታዲያ የኢትዮጵያም ሕዝብ ከዕሪና ይልቅ የተበላልጦ ኑሮን ነው የሚመርጠው ነው የሚሉት.....?

«የተበላልጦን ኑሮ ብቻ አይደለም። - ከነፃነትም ደልዳልነትን የበለጠ ይመርጣል ባይ ነኝ...... ያላሳብ ያለ ሥጋት እንዳሰኘው - እንቅልፍም ቢሆን ሥራም ቢሆን የፈለገውን እያደረገ የሚኖርበትን የጸና ደልዳልነት ነው የሚመርጠው - ‹ሊቤርቴ› ምንድነው...... ‹ሴኩሪቲ› ይሻለዋል እውንም......! ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት የሚለው ቃል ደልዳልነትን የሚነካ የሚያቃውስ ከሆነ ትርጉም የለውም። - በሚስትህ በንብረትህ በሃይማኖትህ የሚሉት ወንድማማችነት የፈረንሳዎች የነፃነት ምልክቶች እንደ ነበሩ ዓይነት። - ምናልባት ደልዳልነቱን ካልነካችሁበት - ወንድማማችነቱም እንግዳ በማስተናገድ ባህሉ ውስጥ ያለ የነበረ ስለሆነ እንደ አዲስ ግንጥል ጊዜ ስለማይቆጥረው ይቀበለው ይሆናል። - ዕሪናውንም - ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስልተፈጠረ በፈጣሪው ፊት እኩል ነውና የእኩልነቱን ሁኔታ ሃይማኖቱን አስታኮ ካስተማሩት እንደ አዲስ ግንጥል ጌጥ ስለማይቆጥረው ይቀበለው ይሆናል። - ነፃነቱንም የራስህ የምትለው ነገር እንዲከበርልህ - ሌላ ሰው የራሴ የሚለውን ነገር ማክበር ይኖርብሃል ማለት ነው፤ የራስክን ርስት ይዘህ የሌላ ሰው ርስት ደግሞ ከሻህ የራስክን ንብረት አስፋፍተህ የሌላን ሰው ንብረት ከደፈርክ የነፃነት ጠላት መሆንህ ነው...... ብለው ካስረዱት እንደ ግንጥል ጌጥ ስለማይቆጥረው ይቀበለው ይሆናል። - ስለዚህ እናንተ የዘመኑ ልጆች በተለይ ስለ ነፃነት ሳወሩ ያልታየ ያልነበረ ካስመሰላችሁት ያላዩት አገር አይናፍቅምና እንኳን ሐሳባችሁን ሊቀበሏችሁ እናንተንም እንደ እብድ ቆጥረው ከኅብረተ ሰቡ ውጭ ሊያደርጓችሁ ቢፈልጉ አይገርምም። - ወሰን የሌለው ነፃነት ያለ መሆኑን በሥራ ሊታይ የማይችል የምናብ ነፃነት የሕልም ሩጫ ዓይነት ነገር መሆኑን እናንተም ጭምር እንድታውቁት ያሻል......

«እኮ እርስዎኮ አሁን የሚሉት ባጭሩ - ሮም ስትሄዱ እንደ ሮማውያን ሁኑ። - በእግር መሄዳችሁን ትተው በእጅ ሲድሁ ብታገኟቸው እናንተም በእጃችሁ ዳሁ። - ቁንጣን እስኪይዛችሁ በልታችሁ በመንገድ ስትንሸረሸሩ...... ያጋጣሚ ነገር አንድ ምስኪን ረኃብ ይዞት ሲፈራገጥ እንደ እናንተው በዚያው በኩል የምታልፍ አንዲት ሴት ጉርሻ እንጀራ ስትሰጠው ብታዩና..... ቢጐርሰው ከመሞት እንዲድን ብታውቁም - ከጁ መንጭቃችሁ ራሳችሁ ጉረሱትና ብትፈልጉ መልሳችሁ አስወጡት...... አይደለም?...... ሌላው ሐሳብዎ ደግሞ በባህላችን ውስጥ መሰል ካልተገኘለት በስተቀር አዲስ የሥልጣኔ አካሄድ አስፈላጊ አይደለም። - ቢያስፈልግም ሕዝቡ ስለማይቀበለው መግባት የለበትም...... በግድ መግባት አለበት ብትሉም እንደ ፍሊጾ መውደቂያ ታጣላችሁ አይደለም........?

«አነጋገርህ ሁሉ የጐድን የጐድን ሆነ እንጂ በልብህ ዋና ዋናውን ነገር ሳትይዘው የቀረህ አይመስለኝም....... እና አንድ ነገር ደግሞ እንድታውቀው የምፈልገው እኔም በዘመኔ የፈርንሳይ ተማሪ እየተባልሁ እንዳጉል ፍጥረት ስታይ የኖርሁ መሆኔን ነው። ጨርሶ የውጭ አገር ትምህርት ከሌላቸው አንዳንድ ሰዎች ይልቅ እኔ ፍላጐታችሁና ዐላማችሁ የሚገጥማችሁም መሰናክል በይበልጥ ሳይሰማኝና ሳይታየኝ አይቀርም..... እና የልቤን ለልቤ እንዳጫወትሁ ያህል ነው ያጫወትሁህ.......

«እሱ ይገባኛል፤ መጽሐፍ ካስተማረውም ኑሮ (ግብረ ግበት) ያስተማረው መብለጡን ዐውቃለሁ። - የመጽሐፍ ትምህርት ከደም ጋር ተቀላቅሎ ነፍስን ስሎ በመግባት ወደ አንድ ዓይነት እምነትነት እስኪለወጥ ብዙ ጊዜ ይፈጃል........ በአእምሮ ውስጥ መጠራቀሙ ብቻ ዋጋ ሊሰጥ አይገባውም። - የሆነው ሆኖ ሊገባኝ ያልተቻለው ለምን እንደ ሆነ አላውቅም የእምነትዎ ጽናት ነው........

«ሰማኖይ አደፍርስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለደልዳልነት ኑሮ የሚያስፈልገው ሁሉ አለው፤ ዘመናዊው ነገር አለው፤ ዘመናዊው ነገር እንኳ ሳይቀር። - ተመልከት - ሌላው ዓለም እንደ ፈረንሳይ መንግሥት ዓይነቱ ለምሳሌ በብዙ ደም መፋሰስ ያገኘው ቤተ መማከርት እንኳ ሳይቀር.......

«እንግዲያው ልንገርዎት ካመጡት አይቀር....... የኢትዮጵያ ቤተ መማከርት...... ደም ስላልፈሰሰለት ነው ሕዝቡ በየጊዜው በሚያደርገው የእንደራሴዎች ምርጫ ግዴለሽነቱን የሚያሳየው ቢመርጥ ባይመርጥ ቤተ መማከርቱ ቢኖር ባይኖር.........ግዴለውም። - ንጉሥ ነገሥቱ ብቻ ይኑሩለት። - ሌላው ሁሉ ትርፉቻ ነው። - ነገር ግን በውነት፥ ምን የምልዎት ደሙን አፍሶለት ቢሆን ኖሮ የመምረጥ መብቱን ተጠንቅቆ ነበር የሚጠቀምበት። - ስለሚመርጣቸውም ሰዎች ብቁ ድካምና የግል ጥናት ያደርግ ነበር። - መቼ እንዲህ እንዲያው እንደ ግብር ይውጣ ነገር......

«ይኸኮ ነው አደፍርስ! የመሐይምን ሕዝብ መሪ መሆን ችግሩ....... ባንዱ መልኩ ሲጠቅም በሌላው መልኩ ይጐዳል። - መሐይምን ሕዝብ ከንጉሡ የሚፈልገውንም ሆነ ለንጉሡ የሚያደርገውን አያውቅም። - ነጭ ኑግ ጥቁር ወተት መግበኝ ይላል። ሌላው ቀርቶ ከስንፍናው፥ የተነሣ ቢርበውና ቢጠማው ኑሮውን ማሸነፍ ቢያቅተው ወይም ደሞ የፀሐይ ግለት ቢያስቸግረውና ድካም ቢጫነው ወይም ደሞ ዝናብ አልዘንብ ብሎ ድርቀት ቢያጠቃው በንጉሡ ነው የሚያመካኘው። - በንጉሡ ነው የሚያዝነው። - እውነቱን ነው የምልህ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ነው የሚያመዝነው። - ሰማሆይ! እግዚአብሔርም ቢሆንኮ ርዱኝ ረዳችኋለሁ ነው ያለው። - ራሳችሁን ርዱ ማለቱ ነው የኔን ርዳታ ከፈለጋችሁ። - ላለው ይጨመርለታል - ከሌለው ያለው

ይወሰድበታል ያለውም ይኸንኑ የሚደግፍ ነው...... ያለው የበለጠ እንዲኖረው ስለሚሠራ...... የሌለው...... ስለሚሰንፍ ስለማይሠራ። - እግዚአብሔር የብርቱካን ገነት ከሰጠን በኋላ እየቀጠፍህ ለያንዳንዳችን ባፋችን ጭመቅልን ብንለው ምንኛ ይከፋው! በዚያ ስፋቱና፥ ምጥቀቱ እንኳ ሊያረገው አይሻም። - መቼም እንግዲህ የምህል....... እስከ ዛሬ አላረገውም። - ንጉሥማ ታዲያ በሰብአዊ ሰውነቱ፥ ሰማሆይ? እንዴት ይቻለዋል? ለያንዳንዳችን አፍ ብርቱካን ለመጭመቅ..... አይቻለውም.....

«አንድ ጨዋታ ይዘን ነበር አባቴ! ከመጡ እንዲያውም ይረዱኛል..... ጥሩ የጻድቃን ቀጠሮ ሆኗል......

ትንሽ ያመነታታሉ «......ልጄን እንዴት አደርሽ ሳልላት? ምነው ድምፅዋን አልሰማውም? እቤት የለች ይሆን......?

«ጐተራ ነች መሰለኝ...... ግዴለም በኋላ ያገኟታል እሷን..... ስለ ዘመኑ ወጣቶችና ስለ እኛ ስለ ዱሮዎቹ ሰዎች ነበር ጨዋታ የያዝነው.....

«ምን የዛሬ ልጆች ዕቡዮች...... ዕልውና ናፋቂ ሁሉ......

«የለም እንዲያ አልነበረም ጨዋታችን...... እኔ እምለው የኛ ሕዝብ...... የኢትዮጵያ ሕዝብ...... የሚያምነው ከኀያል ይልቅ በታምር ነው..... ነው..... የምለው.....

«እንዴታ! ምን ጥርጥር አለው፤ የኀያል ሥራ አዳምና ሄዋንን ከመንግሥተ ሰማያት ያወጣቸው ነው..... በሙሉ ልባችሁ በሙሉ ነፍሳችሁ እመኑኝ አለ እንጂ ተመራመሩኝ አላለም ጌታ ሕጉን ሲሰጠን። - በመመራመር ፈትሕ እንደ ማይኖር ዐውቆት ነው የኢትዮያም ሕዝብ በታምር የሚያምን ነው...... አሁን ታምረ ማርያምን ያነበበ ሰው..... ታምረ ሚካኤልን ታምረ......

«......እኔ እምለው ታዲያ......» አባን ያቋርጧቸዋል አቶ ወልዱ «.......ገና በታምር የሚያምንን ሕዝብ በግድ በኀሊያ እመን ብሎ ማስገደድ አያስፈልግም ነው.....

«ለምን ‹ገና› ይላሉ እርስዎ ደግሞ፤ ገና አይባልም...... መጀመሪያውም የእግዚአብሔር ታምር ነው..... ‹እነወቱ አልፋ ወኦ› ብሏል ጌታ ራሱ በመለኮትነቱ......

«......ሁለተኛ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በ ‹አታውሪቴ› እንጂ በ ‹ቮሎንቴ› መተዳደር ገና አይቻልም ነው የምለው.......

«ልጄን እንዴት አደርሽ ብላት ይሻላል መሰለሽ..... ባማርኛችን አልተግባባንም......» ይሉና ብድግ እንደ ማለት ሲሉ......

«የለም የለም..... ያልኩትኮ! ሕዝቡ ገና በሥልጣን ጉልበት ‹በመባሕት› እንጂ ራሱን በራሱ ገዝቶ በፈቃዱ መተዳደር አይችልም ነው.......

«ይኸም ጥርጥር የለውም..... አሁን የዚች የኔ ልጅ ጭሰኞችና ባገሮች........ ይኸውና ራሳቸውን ማስተዳደር እያቃታቸው አይደለም ከየሚስት ከየልጆቻቸው እየገቡ የሚያድሩላት..... ይኸውና እንዳያችሁት ወንዶቹን ለገበሬነት - ሴቶቹን ለፈጫይ ለፈታይነት ላረም ለጉልጓሎ - ልጆቻቸውን ለረኝነት ለተከታይነት ለተላላኪነት እያዋለች ታስተዳድራቸዋለች...... ማንም ሳይጠይቃቸው ንብረታቸውን እያፈረሱ ርስታቸውን ለባላባቷ እየመለሱ ነው መጥተው የገቡላት...... ምንም ጥርጥር የለውም...... መባሕቱን በሚችለው ሰው ሥራ መተዳደርን የመሰለ ሐሳብ የሌለበት ኑሮ የለም...... በራስ ፈቃድ መኖር የሚሉት ነገር! እህሉ ሲሉት ልብሱ ልብሱ ሲሉት ጨው ጨዉ ሲሉት ግብሩ...... ምኑ ቅጡ...... በየቦታው ነው የሚያፈተልከው የኑሮ ትብትብ...... መባሕቱን በሚችለው ሰው ጥላ ሥር መኖር ምንኛ ሐሳብ መጣል ነው.......

«.......ይኸውልህ እንግዲህ እንደምታየው...... ሕዝቡ በግፈራ እንጂ በምናብ የመኖርን ደስታ ገና አልደረሰበትም...... «ሬቭ› - ህ......! ‹ሬቭ›! ገና በሕዝቡ መንፈስ የለም...... ‹ራሳዚዬይ› ብቻ!»

«አይፈረድበትም ደግሞም! መጀመሪያ የመቀመጫዬን ተብሏል! ሰው ማን ይመስላል ቢሉት የሚበላውን.....

«ድንቁርናና ዕውቀት......! በእርስዎ አስተያየት እንግዲህ የማይዋጥ ነገር ሲሳይ አይደለም ማለት ነው.....?» ይላቸዋል አደፍርስ አባን ወደ እሳቸው ድንገት ዘወር ብሎ ንግግራቸውን ያቋርጥና።

«የለም የሚዋጥ ነገር ብቻ ነው ሲሳይ አላሉም አባ፤ እንዲያውም..... አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖረው ለምናቡም ጭምር ነው....... ደግ ሠርቼ፥ እግዚአብሔር የሚያዘውን ሁሉ ፈጽሚ መንግሥተ ሰማያት ገብቼ እኖራለሁ በማለት..... አይደለም እንዴ አባቴ......?» ጣልቃ ይገባሉ አቶ ወልዱ - ነገሩ እንዳይካረር በማሰብ።

«ዲያብሎስኮ የመላእክት አለቃ ነበር.......!» ይጀምራሉ አባ አዲሴ ትንሽ ከፋ ባለው ሰው አንደበት «......ዛሬስ ቢሆን ምን ይሳነዋል...... ሲያሰኘው እንደ ብርሃን መልአክ ያበራል - ክቡር ቅዱስ ለመሆን የበቁትን እንኳን ለማሳሳት እስኪያበቃው ድረስ። መጠን የሌለውንም ዓለምና ተስፋ በማሳየት እንደ ፈጣሪው ለመሆን ይቃጣዋል...... ይኸ ሁሉ የኔ ነው ከኔ ጋር ከሆናችሁ የእናንተም ጭምር ነው በማለት..... በሕልም በራእይ ይገለጻል...... በልቡሰ ሥጋነት ይገለጻል......

«ልቡሰ ጥላን ማወቅን የመሰለ ነገር......» ሊጀምር ሲል -

«ቆይ እንደዜ አስጨርሳቸው.......» ይሉና ያቆሙታል አቶ ወልዱ።

«.......በትንቢት...... ታምር እንኳ በማሳየት ጭምር......» ይቀጥላሉ አባ «......በልዩ ልዩ ቅባት እያማረ ያናግራቸው የሚቀርቡትን...... የበሽታ መዐት በማውረድ ኅሊናቸውን በማናወጥ ነፍሳችውን በማሠቃየት፥ ሕይወታቸውን ዓላማ በማሳጣት እንዲያከብሩት እንዲፈሩት እያደረገ..... ራሱ ስለተረገመ ሌሎችም ከሱ ጋር አብረው እንዲረገሙ ይሻል...... እሱ የሱስ ክርስቶስ ከእንዲህ ያለው አሽከርነት ያውጣህ......አቡነ ዘበሰማያት......» ይሉና ደግመው ሲጨርሱ በመነሣት «ልጄን እንዴት አደርሽ ልበላት.......» ብለው ወደ ጐተራው ቦታ ያመራሉ።

## ፳፯

# አደፍርስ

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ይመለሳሉ አባ፥ ከጐተራው ቦታ - ወይዘሮ አሰጋሽ ጋር። - የናደፍርስ ተዋሥኦት ባለመቋረጡ የተገረሙ በመምሰል - አቶ ወልዱን አየት ያደርጓቸውና ወደ እልፍኙ ያመራሉ። -

«ይኸውልህ እንዲህ እንዲህ ያለውን በመድምም የሚያምን ሕዝብ ነው በአእምሮ ልትመራው የምትሻው...... በ ‹ሚስቴር› የሚኖርን ሕዝብ ባንደዜ በ ‹ሬንዞ› ለማግባባት መሞከር..... የሚሆን አይመስለኝም አደፍርስ - የሚሆን አይመስለኝም.....» ይቀጥላሉ ተዋሥኦታቸውን አቶ ወልዱ። -

«......እኔ የምልዎት ደግሞ የሚሆን ስለማይመስል ጭራሹኑ አይሆንም ብለን ወስነን እጃችንን አጣምረን ቁጭ ማለት የለብንም ነው። - እኔ የምለው ሕዝቡ ቢወድም ባይወድም በግድም ቢሆን የተሻለውን ኑሮ እንዲያውቅ መማር አለእብት ነው...... በየቦታው ተማሪ ቤት መክፈት....... የግንብና የሳንቃ ቤቶች ሳይሆን ብዙ የጭቃ ቤቶች መሥራት...... ዘመናዊም ሆነ ጥንታዊ ትምህርት የተማሩን መምህራን መቅጠር ቢያንስ ቢያንስ፥ ሕዝቡን ማንበብና መጻፍ እንዲችል ማድረግ። - ከዚያ በኋላ የተሻለውን የኑሮ አስተሳሰብ የሚያሳዩ መጻሕፍትን አሳትሞ መበተን......! ማን ያውቃል በዚያን ጊዜ የሕዝቡ አስተሳሰብ የቱን ያህል እንደሚለወጥ......

«......ልጆቼን ለረኝነት እጠቀምባቸዋለሁ፣ ለትምህርት አልሰጥም ያለስ እንደሁ ሕዝቡ.......! በአንድ ሽልንግ አንድ መጽሐፍ ከመግዛት አራት ብርሌ ጠጅ

እጠባበታለሁ ያለስ እንደሁ ሕዝቡ..... የጡት ማስጣያ ቋንቋዬ ትግርኛ ነው..... ጋልኛ ነው.... ጉራጊኛ ነው....... ወላሞኛ ነው..... ሶማሊኛ ነው...... ባማርኛ የተጻፉ መጻሕፍትን አልፈልግም ያለስ እንደሆነ ደግሞ ጥቂቱ ሕዝብ.......?

«እኔ ይኸ ሁሉ መሰናከል ሊሆን አይችልም ባይ ነኝ...... በጡት ማስጣያ ቋንቋቸው የሚያመካኙ ቢኖሩ በማስገደድ ሳይሆን ጡት ማስጣያ ባልሆነው ቋንቋ የሚያጓጓ ሥራ ሠርቶ ሱካር ጉንዳንን እንደሚስብ ዓይነት እንዲስባቸው ማድረግ ያሻል። - አለዚያ ብሔራዊ ቋንቋ ብሎ ስም በመስጠት ብቻ አንድ ቋንቋ ሊወደድም ሆነ ሊያድግ አይችልም። - የእንግሊዝን የፈረንሳይን የጣሊያንን የመስኮብን ቋንቋዎች ያስወደዷቸውና ያሳደጓቸው እንደ ሼክስፒር ሞልየር ሚልተን ቶልስቶይ! ዓይነት ደራስያን ናቸው። - በአገራችንም - ከዱሮዎቹ እነ ብላቴን ጌታ ኅሩይ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ነጋድራስ አፈወርቅ አለቃ፥ ታዬ ለአማርኛ ቋንቋ እድገት የተቻላቸውን ደክመዋል - በዘመናችንም የተቻላቸውን ያህል የሚጥሩ ብዙዎች ናቸው...... ሆኖም ታዲያ ጥረታችን እስከዚህ የሚያጓጓ አይደለም....... እና - እኔ የምለው እንዲያጓጓ መሆን አለበት ነው.......

«ጡት ማስጣያ ቋንቋችንን ትተን በሌላ ቋንቋ መሠልጠኑ የጐሣ ባህላችንን ያጠፋብናል ያሉህስ እንደሁ......? ምን ትመልሳለህ......?

«ቀላል ይመስለኛል የዚህም መልሱ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም እንኳ ብዙ ልዩ ልዩ ቋንቋቆች ቢኖሩ እምብዛም የዘርና የባህል ልዩነት የለም። - ለምሳሌ አማርኛና ትግሪኛ ተናጋሪዎችን ብንወስድና የሚያምኑባቸውን የሚመሩባቸውን ልዩ ልዩ ነገሮች ብንመረምር አንድ ሆነው እናገኛቸዋለን። - የጋብቻቸውን አስተሣሠር የሃይማኖታቸውን አስተሳሰብ የቀን በቀን ኑሯቸውን አካሄድ ብቻ መመልከቱ በቂ ነው። - እንግዲህ የነዚህ የሁለት ጐሣዎች ዘርና ባህል ከሌሎች ጐሣዎች ዘርና ባህል - ምናልባት ልዩነት ሊኖረው ቢችልም - በጣም ትንሽ ነው...... ስለዚህ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ልዩ ልዩ ባህል ያላቸውን ሕዝቦች አያመለክቱም። - ስለማያመለክቱም ባህላቸው የተነካ ሊመስላቸው አይገባም......

«አይደለም ችግር ሊፈጥር ይችላል፤ ለምሳሌ በትምህርት በሰሎች ተጠንቶ እንደ ተደረሰበት.......

«በትምህርት በሰሎች.......? ምን ማለትህ ነው......?

«አ! የትምህርት በሰሎች - በልዩ የትምህርት ክፍል ሙያቸው የታወቁ...... ‹ኤክስፐርት› ማለቴ ነው......

« ‹ኤክስፔር!!»...... ገባኝ....... እሺ......

«እና...... በሰሎቹ እንደሚሉት አንድ ሕፃን ልጅ አምስት ዓመቱ ድረስ በጡት ማስጣያ ቋንቋው መማር አለበት ነው..... አለ እንፉዝ! ሞኛሞኝ - በሽተኛ ይሆናል ነው ምክንያታቸው፡፡ - ሁለተኛ ደግሞ በተለይ በአሁኑ ጊዜ ብሔራዊውን ቋንቋ የሚናገረው ሕዝብ ቁጥር ስድሳ ከመቶ እብላይ ስለማይሆን......

«ምን ማለትህ ነው ስድሳ፥ ከመቶ......? ጋልኛና አማርኛ ከሚናገር የትኛው ሊበልጥ ነው.......?

«አማርኛ ተናጋሪው ይበልጣል፤ ምክንያቱም አማርኛን የሚናገሩት ጡት ማስጣያ ቋንቋቸው አማርኛ ያልሆነ ሁሉ ስለሆነ ነው...... ጋልኛ ትግሪኛ ጉራጊኛ ወላሞኛ ሶማሊኛ የጡት ማስጣያ ቋንቋቸው የሆነ ብዙ ሰዎች ይናገሩታል፡፡ - ባይናገሩትም ይሰሙታል፡፡ - ሌሎቹ ቋንቋዎች ግን የዚህን ዓይነት ዕድል አላጋጠማቸውም፡፡ - ምናልባት በየጠቅላይ ግዛቱ የሚገኙ ጋልኛ የሚናገሩ ያማራ ነፍጠኞች ይኖራሉ፤ ግን ብዙ አይመስሉኝም፡፡ - በተጨማሪም አማርኛ - የአምስት መቶ ኀምሳ ዓመታት በላይ የጽሑፍ ቅርስ ያለውንና አስተዳደር ቋንቋ በመሆኑ ምናልባት ሳይረዳው አልቀረም፡፡ - ስለዚህ ነው ስድሳ ከመቶ ሳይሆን አይቀርም ያልኩት......

«......ብቻ ጠቅላይ ግዛቱን ስመለከተው..... ወለጋ ገሙ ጐፋ.... ከፋ.......

«......ገባኝ ገባኝ የሚሉት - እዚህ ላይ አንድ ነገር ላስታውስዎት የምፈልገው አለኝ - ኢትዮጵያ ውስጥ ያገር ስፋትና የሕዝብ ቁጥር አይመጣጠንም - ለምሳሌ የጠቀሷቸውን አገሮች ብንወስድ ወለጋ - 1 – 357 – 087 ሚሊዮን...... ገሙጐፋ - 914 – 924...... ቆይ ቆይ እረ ማስታወሻ አለኝ እንዲያውም....... ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩንቨርስቲ የጆግራፊ ክፍል በሺ፱፻፷፩ ዓ.ም ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ባደረገው ጥናት መሥረት..... አዎ..... ይኸው!» የማታወሻ ደብተሩን ያወጣና ያነባል......

1ኛ ክፍል

ወለጋ፥ - 1 – 357 – 087

ሲዳሞ - 1 – 123 – 492 (ከምባታ፥ ወላሞና ሲዳሞኛ የሚናገሩት ተቀንሰው)

ሸዋ - 1 571 – 872 (አማርኛ ትግሪኛ ጉራጊኛና ሌሎችም ቋንቋዎች የሚናገሩት ተቀንሰው

ገሙጐፋ - 918 – 924

ኢሉባቦር - 845 – 682

አሩሲ - 877 – 872

ባሌ - 821 – 000

ሐረር - 165 – 327 ( አማርኛ - አደሪኛ - ሶማሌኛ፥ የሚናገሩት ተቀንሰው)

ከፋ፥ - 654 – 020 (ከፍቾ ጊሚራ፥ ቦሻ፥ ሞቻ፥ ሸናሻ ሞአ የሚናገሩት ተቀንሰው)

ወሎ፥ - 94 – 000 (አማርኛና ትግሪኛ የሚናገሩት ተቀንሰው)

በድምሩ - 8 – 429 – 276

2ኛ ክፍል

ጐጃም - 1 – 806 – 787

በጌምድር - 1 – 345 – 535

ሸዋ - 3 – 313 – 946 (ጋልኛ ጉራጊኛ ትግሪኛና ሌሎች አንዳንድ ቋንቋዎች የሚናገሩትን ቀንሶ)

ወሎ - 3 – 027 – 115 (ጋልኛና ትግሪኛ ተናጋሪዎች ተቀንሰው)\

ሐረር - 1 – 365 – 378 (ጋልኛ ሶማሌኛ አደሪኛ አዳልኛ ተናጋሪዎች ተቀንሰው)

ድምር - 10 – 858 – 761

3ኛ ክፍል - ትግሪኛ - ጉራጊኛ - ሶማሌኛና - ልዩ ልዩ የከፋና የሲዳሞ ቋንቋዎች የሚናገሩት

ትግሬ - 1 – 821 – 892

ኤርትራ - 2 – 131 – 000

ሐረር - 1 – 043 – 576

ሸዋ - 438 – 808

ከፋ - 704 – 462

ሲዳሞ - 1 – 658 – 444

ድምር - 7 – 798 – 182

ምን ማለት ነው እንግዲህ ይኸ.......? በሁለተኛ ክፍል የተዘረዘሩት ጠቅላይ ግዛቶች ሕዝብ ቁጥር ባንደኛው ክፍል ከተዘረዘሩት ይበልጣሉ ማለት ነው። - በመጀመሪያው ክፍል የተዘረዘሩት በሙሉ ጋልኛ ተናጋሪዎች ናቸው ብንል እንኳን ከሁለተኛው ክፍል ጋር ሲወዳደሩ ያነሱ ናቸው ማለት ነው። - በሙሉ ግን ጋልኛ ተናጋሪዎች አይደሉም፤ የወለጋን የሸዋን የሐረርን፥ እንደ ተግባቢና እንደ አንድ ቋንቋ ብንቆጥራቸው እንኳ። - ከስምንት ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ውስጥ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚናገሩ በትንሹ ከግማሽ በላይ ሳይሆን አይቀሩም። - አልፎ አልፎ ከሚገኙት አማርኛን እንደ ጡት ማስጣያ ቋንቋቸው ከሚናገሩት ውጪ ማለት ነው...... በዚያ ላይ ደሞ፥ አማርኛን እንደ ተወለዱበት አካባቢ ቋንቋ ወይም እንደ ሁለተኛ ቋንቋቸው አድርገው የሚናገሩት ሦስተኛዎቹ ክፍል አሉ። - ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ሺ አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ትንሽ ቁጥር አይደለም። - ጋልኛ ተናጋሪዎቹን ሊያህል ምንም ያህል የማይቀረው ማለት ነው። - እና እንግዲህ ያማርኛ ብሔራዊ ቋንቋነት የሚያጠራጥር መስሎ አይታይም፥ በዚህ አስተያየት......

«እሺ አሁን ወደ ጀመርከው ተመለስና ቀጥል - የቋንቋ ልዩነት ስለሚያስከትለው ችግር ነበር የምትዘረዝረው...... ይችን ደሞ የሕዝብ ቁጥር ዝርዝርህን ብትሰጠኝ ብገለብጣት...... ጥሩ ነገር ነች፤ የየጠቅላይ ግዛቱን ሕዝብ ቁጥር ለማወቅ...... ለመሆኑ......» ማስታወሻውን ተቀብለው በማስታወሻቸው ላይ እየገለበጡ «ለመሆኑ - የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ስንት ደርሷል ይባላል......?

«አ......! በጣሊያን ጊዜ - አምስት ሚሊዮን ብቻ ነበር ተብሎ የተመዘገበው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር...... ዛሬ...... ሰላም ዘመናዊ መኀኒትና ሕክምና - ከሀያ ሰባት ሚሊዮን ሰማኒያ ስድስት ሺህ በላይ አድርሶታል። - እሱን ዝርዝሩን ቢደምሩትኮ ሊያገኙት ይችላሉ.....

«ጥሩ ነው ጥሩ ነው - ቀጥል ቅድም ስለጀመርነው......

«አዎ እና...... ታዲያ፥ አማርኛን የሚሰማውም ሆነ የሚናገረው ከሚናገረውና ከሚሰማው ጋር ከስድሳ ከመቶ ስለማይበልጥ - ሌላው ቀሪው አርባ ከመቶው ማለት ነው የተንጓለለ ስለሚመስለው የኢትዮጵያዊነት ስሜቱ መነካቱ አይቀርም፤ እምለው - በሬዲዮ የሚነገረውን በጋዜጣ የሚጻፈውን በብሔራዊ መሠረተ ትምህርት የሚሰጠውን ለማግኘት ስለማይችል.......

«ታዲያ ምን መፍትሔ የሚኖረው ይመስልሃል......?

«በውነቱ ከሆነ እንደዚህ እንደ ኢትዮጵያ ከአርባ በላይ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እሚነገርበት አገር በየቋንቋው የተጻፉ መጻሕፍትና በየቋንቋው የሠለጠኑ መምህራን ስለሌሉና እንዲኖሩም ለማድረግ ለጊዜው ኢኮኖሚያችን ስለማይፈቅድ ምናልባት በተለይ ለብሔራዊ መሠረተ ትምህርትና በዝቅተኛ ደረጃ ለሚማሩ ሕፃናት እንደ ተናጋሪዎቹ ብዛት ታይቶ - ማለት አማርኛንም እንደ አንድ ትምህርት እያስተማሩ - ሁለት ወይም ሦስት ቋንቋዎች ለመምረጥ ይቻል ይሆናል.......

«ልጆቹን ለረኝነት ብሬን ለብርሌ አውላቸዋለሁ ለሚለውስ ምን ዘዴ ታገኝለታለህ.......?

«ስለ እረኝነቱ፥ በየቦታው አንዳንድ የከብት ማቆሚያ መስኖጌ እየቀየሱ፥ ከብቶቹ ያለ እረኛ የሚሠማሩበትን ዘዴ ማሻትና - ከዚያም በላይ ማንኛውም ሰው ልጁን ቢያንስ ቢያንስ ስድስተኛ ክፍል ድረስ እንዲያስተምር የሚያስገድድ ደንብ ማውጣት...... ስለ ብርሌው ቢሆን አሁን ባለንበት ዘመን ማስተው የሚቻል አይመስለኝም - ምናልባት ከብርሌው ይበልጥ መጽሐፉ መጣፈጡን የምናሳይበት ዘዴ ካላገኘን......

«እሱንማ ቅድም ተናጋግረንበታል - የሚያጓጓ የሚጣፍጥ መጽሐፍ በመጻፍ ሕዝቡን ለመማረክ ይቻላል ብለሃል...... ሐሳብህ ይሠራ አይሠራ እንደሆን የሚያሳየን እንግዲህ መቆየት ነው.....

«ፃእ መንፈስ ርኩስ! ፃእ መንፈስ ርኩስ!» እያሉ ጠበል እየረጩ ይመጣሉ አባ አዲሴ...... ሊቸችሩት ሲዘጋጁ ሲያይ ምንጥቅ ብሎ ያመልጣቸዋል አደፍርስ «ጻላኤ ሠናያት እኔ ፊት አይቆምም» ይሉና ላደፍርስ ባመቻቹት አቶ ወልዱን ይቸችሯቸዋል -

........ከት ያለ ደስ የሚል የጺወኔ ቃጭል ድምፅ ሲስበረበር ይሰማል ካባ አዲሴ ኋላ ኋላ «.......ሌጊዎንን አባረሩት - ሌጌዎንን አባረሩት!» እያለ ሲንቀሳቀስ -

አደፍርስ አልሰማትም -

# ፳፯

# አደፍርስ

ጐርፉን እቤታቸው ድረስ አስጠርተውታል፥ ወይዘሮ አሰጋሽ። - ጴጥሮስ እንደ ነገራቸው በየሳምንቱ ወይም በያሥራምስት ቀኑ ውሃ መቅጃ ድረስ መጥቶ እየጠበቀ ሮማንን እንደሚያነጋግራት ሰምተዋል። - ከቤተ ሰባቸው አንዷ በሚወዱት የአብሮ አደጋቸው ልጅ አልባሌ ቦታ መጠበቋ አንገብግቧቸዋል። - የወይዘሮ አሰጋሽ ቤተሰብ! በዚያ ላይ ደግሞ ቃል ያሠረች፤ ጐድፋ የተገኘች እንደሁ ደግሞ ምን ይውጣቸዋል? - አሰጋሽን የሚያህል ስም......! ሲመጣ ምን ምን እንደሚሉት ያወጡ ያወርዳሉ...... የነፍስ አባታቸውን እንኳ ጠበል እንደ ረጩ ቆይተው እንዲያሜውቷቸው ሳይፈልጉ። -

«........ነገር ከሰነበተ ቅራሪ ከሆመጠጠ አጉል ነው - ነገር ከሰነበተ ይከራል፤ ቅራሪ ከሆመጠጠ ያቅራል...... አዎ፥ ይኸ ጥሩ አጀማመር ነው...... እሺ ከዚያ ቀጥዬ ደግሞ ያሳደግሁት ልጄ ስለመሆኑ - የዋንጫ ቡሽ የውሃ ጉሽ የለውም፤ ዘርህ የጠራ፥ ማን በቡሽ ይከድናል? አንተስ....... ቆይ ቆይ......! ትልቅ ቡሽ ያሠራ ነዋ ያለኝስ እንደሁ...... ውሃስ ይደፈርስ የለም እንዴ እሱማ ጉሸስ ባይኖረው....... የእባብ ለማዳ ያህያ ፍሪዳ - ሴትና ወንድ ጭር አለበት ቦታ አጉል ነገር ያስከትላ....... አሄሄ ይኸም አጉል ነው....... እሱ እንዲያውም ነገር ጠምዛዥ ነው፤ እባብ ብለሽ ሰደብሽኝ ነው የሚለኝ...... ሮማንንስ አህያ አሉሽ ቢላት...... አይ እሷ እንኳን ልማዷ ነው፤ ቢሆንም እሱ ስለሰማው ይከፋት ይሆናል...... ቃል ያሠረች ልጃገረድ ትንሽ ትንሽ ክብር አይጠላባትም........ የለም አይበጅም...... አንተ ለራስህ የምታጓጓ - በዕውር ጐዳና ብርቅ ነው አንድ ዓይና!...... ልቧ ይታለልና...... በዕውር ጐዳና?!....... ይኸማ አሰጋሽም እውነ ነች ማለት ነው...... አሰጋሽ እንኳን ባልላት ሀብት የሱን ዓይነት አላስገኘችም ማለት ይመስለው ይሆናል...... አሄሄ! የማይደረገውን...... ራሴን በራሴ ልሰድብ? ተደርጐም አያውቅ...... ሲያይ የሞተውን ሲሰማ ቅበረው እንዳይሆን ብዬ ነው ያስጠራሁህ - አዎ ይኸ፥ እንኳን ጥሩ መጀመሪያ ይሆናል...... ግን የት ቦታ አዩኝ ያለኝስ እንደሁ ጴጥሮስ ዋሽቶስ እንደሁ? አይ ጴጥሮስ አይዋሽም...... ባይሆን ከዚያም ከዚያም ትንሽ ትንሽ እህል ያጠፋፋ እንጂ ውሸት አያውቅም...... ጉቦ ምናልባት ከየጭሰኞቼ ይቀበል ይሆናል...... ቆይ ቆይ! ቃልህ ሳይዘጋ እግርህ ሳይዘረጋ ለምን የምትሆንህን ፈልገህ አታገባም ብለውስ? አዎ፥ እናቱ ነኝ ምክሬን ባካፍለው መከፋት የለበትም...... እንደማትከፋ...... ለኑሮ ፈውስ የምትሆን....... የማይፈወስ ድውይ የማይመለስ ጊጉይ እንደማትሆን ስለማውቅ...... እእእ......! አጉል አባባል - እንዴታ! አብሮ አደጉ ነች..... አብረው ሲዘሉ..... ቢዘል

እማጆት ቢወጋ ምንቸት - እእእ.......! ያስከፋዋል ይኸም...... አዳል ዘመቻ የወረደ....... ስንቴ ነው በሬና ላም እየዘረፈ...... ላም እሳት ወለደች ልጅዋ ነበርና ላሰች - ልጄ ነህ አንተም ያጠፋኸውም ነገር ቢኖር መቻል አለብኝ.... መቻል አለብኝ...... መቻል አለብኝ......?! የለም መቻል የለብኝም...... ውሃ መቅጃ እየጠበቁ ማነጋገር ትልቅ ድፍረት ነው..... ትልቅ ድፍረት...... ደሞ የምን ጐን ጐን መሄድ...... ቀጥታ ነው የምነግረው........ ያላዋቂ ነገር.....ያላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል....... አዎ ቢከፋውም ይከፋው........ የሚያውቅም ይለቀልቃል ያለኝስ፥ እንደሁ..... የለም እንዲህ አይደፍረኝም...... ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጐረቤቱ አይበላም..... የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም........ እና ታዲያ....... ታዲያ....... አንተ እርምጃህ ትንሽ ተፋጥኗል....... ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል........

## ፳፰

## አደፍርስ

ጐርፉ ከዚህ በፊት፥ ጺወኔን አጥር ሥር ባነጋገራት ጊዜ ለብሶት የነበረውን ልብስ ለብሶ ግቢውን ይገባል። - እወይዘሮ አሰጋሽ እልፍኝ በር ሲደርስ ጠበንጃውን እውጪ ቆሞ ለሚጠብቅ ልጅ ይሰጥና ያደገድጋል። - ልጁ ጠበንጃውን ይዞ ገብቶ መምጣቱን ይነግርለታል። - ወይዘሮ አሰጋሽ፥ እጅታሙ ወንበራቸው ላይ ተቀምጠዋል። - ጐርፉ ፈቃድ እንደ ተሰጠው ይዘልቅና እወይዘሮ አሰጋሽ ጫማ ላይ ዘፍ ብሎ ይስማል.......

«እንደምነህ ወዳጄ..... እንደምነህ...... እንደምነህ....... እንደምነህ!» እያሉ አገጩን፥ ቶሎ በጃቸው ቀበል በልው በመሳም ፈንታ በሚያግደረድር መንገድ ወደ ታች እንደ ዘረጉት ብዙ ጊዜ ይቆያሉ «......እንደምነህ ታዲያ!» ይቀጥላሉ አሁንም ቀና ድርገው ከሳሙት በኋላ «......አባትህ ቀኛዝማችስ እንደምነው......?

«ደኅና! ደኅና!» እያለ እጅ ይነሣል ጐርፉም......

«እናትህስ........!

«እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነች......

«ልጆቹስ...... ከብቶቹስ......

«ይከበር ይመስገን ለፈጣሪ.....

«አንተስ እንደምን ይዞሃል.......?

«ክብሩ ይስፋ ክብሩ ይስፋ! እስካሁን ይጠብቀኛል መቼም......

«እርሻው ጉልጓሎው የክረምት ነገር......

«ይዘነዋል መቼም..... እንደ ነገሩ......

«እንዲያው አንድ ታቦት እየተሳለምን መጠፋፋት.......

«ማደሮው መቼ ይለቃል ብለው.....

«ቢሆንስ! ቢሆንስ! ከብቶቻችን አንድ ሥሪት እየዋሉ...... አንተስ በጄ! ካብትህስ ቢሆን.......

«እሱም አልተመቻቸው.......

«ያለፈው የሰኔ ሚካኤልኮ ሦስት ወሬ መሆኑ ነው አንተም አባትህንም ካየኋችሁ.......

«ይሆን ይሆናል.......

«ግርም ድንቅ ነው የሚለኝ የዘመኑ መጠያየቅ......

«ልጆቹንኮ ባገኘኋቸው ቁጥር እጅ ንሡልኝ ማለቴ አልቀረም......

«ሆይ ታሪክ! ሆይ ታሪክ - የዛሬ ልጆች በመልክት እጅ መንሣት...... የማታመጡት ፈሊጥ የለ..... እደጄ ድረስ መጥተህ እየተመለስህ ደግሞ እጅ ንሡልኝ...... እንዲያው ዘመድ መጠየቄን ትቼዋለሁ አትልም......

«ዋ እረ ሳይሞላልኝ እየቀረ! እንዲህ አርጐም የለ! እደጄ ድረስ እየመጣህ እኔን እናትህን እጅ መንሣቱ ላይ አልሞላልህም......» ጐርፉ ድንግጥ ይላል፤ ከጺወኔ ጋር ባጥር ላይ የተነጋገረ ለት መምጣቱን የሰሙ ይመስለውና «.......አረፍ በል እንጂ ታዲያ፤ የኔ ነገር ዝም አልኩህኮ....... እዚያ እበርጩማው ላይ ቁጭ በል......

ቁጭ ብሎ ምራቁን እንደዋጠ «እርስዎስ ይኸን እግርዎን የሚቆጣጥምዎትን....... ምን ማስታገሻ አገኙለት........?

«ምን አገኘሁለታለሁ አለ ሊቀ መልአኩ....... በሱው እመት ሳሻሸው ነው እሚታገሥልኝ.......

«ዐዋቂው እንደ ብርካቴው በሽታ አለ መጥፋቱ.......

«........ያዋቂውን ነገር አለማንሣቱ ይሻላል እባክህ...... በወገቤ ዙሪያውን ታጥቄው በትከሻዬ የጥፈቱ ዓይነቱ...... ምኑ ቅጡ..... ስመ አምላኩ ትምርተ ቦአቱ አስማተ ሰለሞን ጨብጨቤው ግርማ ሞገሱ በቁመቴ ልክ ብራና የተጣፈው ጥፈት ዓይነት...... ምን ብቻ ልንገርህ....... አልለ የተባለ መዳኒት አልቀረኝም.......

«ማስታገሻውን እሱ ካላዘዘው ይሆናል.......

«አላዘዘውም...... አላዘዘውም....... ባያዘው ነው..... ሊቀ መልአኩ ተቀይሞኛል...... አምና ታስታውስ እንደሆነ የንግሡ ለት ሦት ዱለቻ ጥዬ አዘከርኩት...... የሦስት ቤተክሲያን ቄስና ደብተራ ጋብዤ። - ስንቱን ለምድርና ለሰማይ የከበደ ሰው ነው የኔ ጠላና ጠጅ ያብረጅረጀው....... ታስታውስ እንደሁ ዳሱ እንኳን የፈረሰው በሦስተኛው ቀን ነው...... እኔ የት ላይ እንደበደልኩት አይገባኝም። - አሁን በበቅሎዬ ስሄድ ከየትም ማዘን ይሁን ገጥ ይለኝ የለም? አሽከር ሳያፈልገኝ ዱብ ብዬ ነው የምሳለመው...... አባ አዲሴም የኔ ልጅ ጥፋት የለብሽም ነው የሚሉት፤ የወደደውን መፈታተን ልማዱ ነው ይሉኛል...... ታዲያ እኔ የሚገርመኝ ፈትኖኝ ፈትኖኝ የሱ መሆኔን ሲያውቅ አለመተው..... እንዲያውም ቁርጥማቱማ የሚብስበት እሁድ እሁድና ለሱው ጠበል ጠዲቅ ባደረግሁ ቁጥር ነው...... በሌሊት እየተነሣሁ ባስቀደስኩና ከጧት እስከ ማታ አደግድጌ በየጊዜው ጠበል ጠዲቁን ባዘከርሁ..... ምን ይውጣት ብሎ ነው እስቲ! በያመት ባሉ - ስንዴ ሲሉኝ ስንዴ ጋድ እንጨት ሲሉኝ ጋድ እንጨት ጧፍ ሲሉኝ ጧፍ ዕጣን ሲሉኝ ዕጣን ግምጃ ሲሉኝ ግምጃ...... አይ እሱም አሁንስ የሚፈልገውን አጥቶታል......

«ሳይቸግረው ወዳጁን ይፈታተናል!» ይላል ጐርፉ ያዳምጥ ያዳምጥና።

«አባ አዲሴም ይኸንኑ ነው ያሉት......!» ይመልሳሉ ወይዘሮ አሰጋሽ፤ የልብ ኩራታቸውን አውጥቶ በሚያሳይ አነጋገር።

«አብዬ ወልዱ መጥተዋል ልበል፤ በሩቁ ያየኋቸው መሰለኝ» ይጠይቃቸዋል ጐርፉ ድንገት ርእሱን በመለወጥ።

«መምጣትህ ካልቀረ ታዲያ እዚህ ድረስ ምን ነበረበት ገባ በለህ እንዴት ናችሁ ብትለን?» አንዷን ቃል ብቻ ያጤኑለት ይመስል ይጠይቁታል መልሰው።

«ኧረ መጥቼም አላውቅ...... እንዴት ሰላምታ ሳልሰጥዎት እሄዳለሁ?» ይላል ጐርፉ እንደገና ድንገት ድንግጥ ይልና።

«ተው ተው! የኔ ልጅ እንኳን ውሸት አታውቅም ነበር......

«የትናንት ወዲያውን ካልሆነ በስተቀር...... እምለው ሚካኤል ስለት ነበረብኝ....... እና ታዲያ፥ ታቹን በጉድባ ሳልፍ ሮማን አይታኝ ነበር......

«አዎ እሱን ማለቴ ነው........» ይላሉ ወይዘሮ፥ አሸጋሽ፥ አነጋገራቸውን ጠበቅ አድርገው «የጉድባውን! ታዲያ ምን ነበረበት ከቤተስኪያን መልስ እንኳን ጐራ ብለህ ብትጠይቀን.......?

«ማስቸገር እንዳይሆንብኝ......

«እንግድነትህ እንዳያስቸግረን....... ማለትህ ነው...... ታዲያ ከሮማን ጋር..... ቆም አላልከም ኖሯል እንዴ.......?

«አዎ ብቻ ቆም ብዬ ነበር......

«ስታልፍ አይደለም ያየችህ.......?! ታዲያ፥ እምልህ ወርዶፋ እንዲህ ያለ ነገር አይወድም፤ ብትሆን ቀጥቶ ነው ያሳደጋት...... እንዲህ ያለውን መገናኘት ይወደው ይመስልሃል.........?

«ውይ ምነው እመዬት! ለምን አይወደውም?? ባነጋግራት ምን አለበት..... አብረው አፈር ፈጭተን አድገን..... ሰው እኅቱን ሳያነጋግር እንዴት ያልፋል?? እርግጠኛ ነኝ፤ አብዬ ወርዶፋም ቢያይ እሱም ወጥቶ ነው የሚያነጋግረኝ......

«እሱን ማለቴ አይደለም...... ብቻ ቢሆንም ወንድና ሴት ብቻቸውን መቅጃ ሲታዩ አጉል ትርጉም ያመጣል...... ዛሬ፥ እንኳን ኢጋኽ አግኝቶ ሌጊዎን ብቻውንም አልተቻለ...... የስንቱ ልጆች ከሌጊዎን እያረገዙ........

«ሌጊዎን? ሌጊዎን?.......?

«አዎ የዝሙት ጋኔል አለ፤ ሌጊዎን የሚባል። - ስንቱን የጨዋ ልጅ አበላሽቷል ይመስልሃል...... እንዲሁ እየወንዙ ዳር እየውሃ መቅጃው እየተፃረራቸው........

«እኔ እንዲህ ያለውን ነገር ከየቴ ዐውቄ..... ሌጊዎን ብሎ ጋኔል......

«አዎ አታውቅም - አባ አዲሴ ያውጉህ ስለ እሱ...... እንደ እመቤታችን የማምናትን ጺወኔን እንኳን እንድጠራጠር ነው ያደረጉኝ....... አሁን ደግሞ ሰሞኑን ጨዋታቸው አኮሪዶ ብቻ ሆኗል...... ይኸው ሌጊዎን ባኮሪዶ ተጭኖ እቤትዎ ገብቷል ይሉኛል......

«አኮሪዶ ደግሞ ምንድነው.......?

«አንድ እዚህ እኔ ቤት የሰነበተ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ እኅት ልጅ አለ..... እሱ የሚያጮኸው ነገር ነው.......

«የሚያጮኸው.........?

«አዎ እሱማ ዘፈን ዘፈንሁ ብሎ ልቡ ወልቋል...... ውምበርሴት የሚባለው ተማሪ ቤት የሚያመጣው ነገር የለ......?

«የውምበርሴት ተማሪ ነው.......?

«ይሉኛላ.........!

«እነሱ ሰዎች በከተማውም ወሪያቸው አላማረ..... አሁን በቅርቡ አንዱ አባት የውምበርሴት ተማሪ ልጁን ገደለ ማለትን ትናንት ኅሙስ ገበያ ሰማሁ......

«ምን አጠፋህ ብሎ......

«ለንጉሥ አንታዘዝም የሚሉ አማርኛ አምጥተዋል ነው የሚባለው.......

«ለንጉሥ አንታዘዝም! ለንጉሥ አንታዘዝም....... አይጥ ወልዳ ወልዳ ጅራቷ ሲደርስ ሲጥ...... ለማን ሊታዘዙ ነው ኋላ! የማንንም የድሃ ልጅ ሰብስበውኮ ነው እንዲያው መከራቸውን የሚያዩት እኚህ ንጉሥ..... ዘረ ድሃ ያው ዐመለ ድሃ ነው....... ቢሾሙት ቢሸልሙት..... አሁን አህያን ቢያስጌጧት የትኛውን ግርማ ሞገስ ልታገኝ......?? ይበጅ አርጓል....... ሞትም ሲያንሰው ነው......

«ከራርን እንኳን የመሰለ ጨዋታን ሲያስከለክሉ እንዴት አኮሪዶ ፈቀዱ.......

«ምናባቴ ላርግ በለህ..... አጐቱ ወደ ደብረ ሲና ሲመለሱ ካንድ ምስል ከሚያነሣ ጓደኛው ጋር እዚህ ከተቀመጡ ይኸው አሥራምስት ቀናቸው ትናንት ቅዳሜ አለፈ.......

«ምን እንሁን ባዮች ናቸው?»

«አንዱ አደን አድናለሁ ባይ ነው፤ ሌላአው ደግሞ ያገሩን ምስል አነሣለሁ ይላል.....

«አይ እውንም ነገሩ አያምርም...... አባ እንዳሉት......

«የሚካኤልን ምስል አንሣልኝ ብለው ደግሞ ምን አደረገ ይመስልሃል.......?

«በየት አባቴ......

«ኧረ እሱንስ አለመስማቱ ይሻል......? ቢያወሩትም አያምር......

«ግዴለዎትም እነዚህ ያውምበርሴት ተማሪዎች ጠግበዋል......

«ኧረ ይኸስ ጨርሷል ነው የሚባለው ትምርቱን - እኔ መላውም አይገባኚ...... ምን አረገ ይመስልሃል ታዲያ...... አንድ የኔ ጭሰኛ አለ፤ እዚህ እበታቼ እተረተሩ ላይ የሚኖር......

«አዎ ዐውቀዋለሁ.......

«ካወቅኸው ምን ልንገርህ...... መቶ ካሥር ያህል ዕድሜ አለኝ ባይ ነው.....

«ሰምቻለሁ.....

«ዘንጉን ለድንገቱ ነቀል ያደረገ እንደሆነ ነፋስ ነው የሚያግተረትረው......

«በነፋስ ግፊት ነው የሚሄደው፤ ዘንጉን ቶሎ መትከሉ ያቆመዋሊ። - አንዳንዴ ይዞት እንዳይሄድ እፈራለሁ......

«ይኸውልህ ታዲያ እሱጋ እየወረደ የሱን ምስል ያነሣል ብለው ልጆች ነገሩኝ........ እኔ ደግሞ ምን ጠርጥሬ.....

«አጥንቱ የተንቋቋ ሽማግሌ...... ምን ይሠራልኝ ብሎ.....

«ጉዱ ሊመጣልህ አይደለም? የሚካኤልን ምስል ሠራሁ አለልህና አመጣ......! በቀኝ እጁ የመዘዘው ጐራዴ ይንተገተጋል። - በግራ እጁ ሚዛኑን ከፍ አድርጐ ይዞ የፈጣሪን ፍርድ በሚገባ ያሳያል። - በወርቅ የተንቆጠቆጠ ክንፉ ላይን ያስፈራል -

የብርሃንነቱ ድልቅልቅታ መቼስ ይኸ ነው አይባልም.... ዲያብሎስን እሆዱ ላይ ስለቆመበት ምላሱን አስጐልጉሎታል - ያይኑ ደም መልበስ የግሩ ሁናቴ የጭራው አቆላለፍ...... ውጭ ነፍስ ግቢ ነፍስ ሆኗል..... ትይጐሽ ልጄ! እንዲህ ነው! እንዲህ ነው! እሱ ሚካኤል ከግራ ቀኝሽ ጥላ ከለላ ይሁንሽ...... የሠራውንም እጁን ይባርከው በማለት ወደ ቀኝ ወደ ግራ እያደረጉ ራቅ ቀረብ እያሉ ሲያውት ቆዩና ድንገት ፊታቸው ቅጭም ሲል ታየኝ...... ምነው ምን ሆኑ አልኳቸው እኔም..... ምን ጥፋት ተገኘበት?...... የሊቀ መልአኩን ፊት ጠይም የዲያብሎስን ፊት ቀይ አድርጐት...... አዬ አዬ ሠርቶ መና እያሉ ብስጭትጭት አሉ። - ማየቱን መቼም እኔም አይቼዋለሁ...... ታዲያ የዲያብሎስ ፊት የሚሠቃይ ፊት መሰለኝ ቅላቱ አልታየኝም ለጊዜው....... ፊቱን ካላስለወጥሽ ይኸንን ይገፔ አልሄድም፥ አይሉልህም ታዲያ አባ.......!

«እሳቸውም እንዲያው ለሁሉ ነገር ጥንቁቅነት ያበዛሉ....

«እንደ ፈረደብኝ አስጠራሁና የሊቀ፥ መልአኩን ቀላ የዲያብሎስን ጠቆር እንዲያደርገው ጠየቅሁት፥ ሣሊውን...... ሞቼ እገኛለሁ አይልልህም ታዲያ እሱ!

«ምን? አልለውጥም ነው?

«እንዲያሳ!

«ምነው አለ!

«ጉድና ጭራ ወደ ኋላ - ሽማግሌው ፊቱ ጠይም ነው አይለኝም እንዴ? የቱ? ምንም አላልኩ ብቻ፥ የቱ ሽማግሌ አልኩት....... የእርስዎ ጭሰኛ - እተረተሩ ላይ.......

«የመዐት ያለህ!

«ከመዐት ያውጣህ ወንድሜ......! ትኩር ብዬ አየሁልሃ...... የሣለውን ምስል...... ቁርጥ ያያ አጅቤን መልክ....... ሚዛኑ ላይ ያሉት ነፍሳት ደግሞ ቁርጥ የሮማንንና የጺወኔን ፊት ዓይነት ያላቸው...... ዓይኔም እንደሆነ አላውቅ በኋላም የዲያብሎስም ፊት የኔን ፊት መሰል አለኝ....... ያንቺ ምስል ነው ብሎ ከሣለው መቼም አይብስም.....

«ምን መዐት ወርዶብዎታል ወንድሜ!

«በል እንካ ወዲያ እምትወስድበት ውሰድ፤ ባይኔ ሁለተኛ እንዳላየው ብዬ ከእልፍኝ አስወጣሁት እልሃለሁ....... እውነት ነው የምልህ ያን ለት ነበር እሱን ከነጓደኛው ከቤቴ ማባረር የነበረብኝ......

«አባስ ምን አሉ......? እምቢ አለ ሲሏቸው......

«ግዴለም ይመልሰው - ፊቱን ባገር ቤት ሣሊ እናስለውጠዋለን ብለው ነበር...... እኒነ ግን እንደ ስድቻ መታኝ..... ያያ አጅቤን ፊት መሳለሙ...... ለሳቸው አልነገርኳቸውም...... ብነግራቸው እብጃቸው ስለነኩት እንኳ ስንት ቀን ሱባኤ እንደሚገቡ እግዜር ይወቅ......

«ምን አረገው ለመህኑ ምስሉን......

«እዚህ ወደ አዳሉ ውስጥ የተተከለ ሚካኤል አለ፤ ለሱ ሰጠው ይሉኛል.....

«ወይ አያ አጅቤ..... ዕድሜ ልኩን የቁም ስቅሉን ሲያይ ሊኖር ነዋ!

«እሱ ብቻ ሊቀ መልአኩ ይቅር ይበላቸው የሚሳለሙትን ሰዎች......

«አይ እነሱማ ሚካኤልን በነፍስ አላዩት በምን ይወቁት? የለም እነሱ አይፈረድባቸውም......

«አያ አጅቤንስ መቼ አይውቁታል እሱንማ ካልህ...... እውነትህን ነው - እኛም አጅቤን ባናቀው ኖሮ እንሳለውም ነበር...... እግዚአብሔር በቸርነቱ ይቅር እንደሚለን አይጠረጠርም......

«ታዲያ እርስዎም ሱባዔ ለመግባት አስበዋል......?

«የለም እኔስ ዘዴ አድርጌበታለሁ........ አንድ መቃብር ቤት የሚኖሩ የበቁ ባሕታዊ....... ከስሜን ነው አሉ የመጡት...... እዚህ አረጋዊ ደብር አሉ ብለውኝ በጴጥሮስ በኩል የሚያስፈልገውን ገንዘብና እርዳታ አድርጌ እሳቸው፣ የሚያስፈልገውን ሁሉ አደርጋለሁ በለው ቃል ገብተውልኛል..... ባስተርጓሚ ነው አሉ የሚናገሩት...... በሽተኛ ሁሉ ይፈውሳሉ ይላሉ.......

«ስለ እነዚህስ የከተማ ሰዎች ምን የበጀ ነገር አገኙላቸው.......?

«አይ እስከ ተነገ ወዲያ ድረስ እጠብቃቸውና ካልሄዱ፥ ሮብ ወይም ኀሙስ ጧት ዘመድ እጠይቃለሁ ብዬ ከነ ልጇ ጥያቸው ነው እብስ የምለው....... ቀደም ብለው ከቤቴ እንዲሄዱልኝ በጠሎትህ አትርሳኝ...... ሮማንንም እንኳ ወደ ኋላዬ አልተው፣...... ደግሞ እስቲ የወልዱስ አይብስ....... እሱ ነው ያባለጋቸው በየርስቱ ይዞ እየዞረ....... እዚህ ቦታ ጥሩ አደን እዚህ ቦታ ደስ የሚል ፏፏቴ አለ እያለ...... እርግጠኛ ነኝ፥ እነሱ እዚህ አይቆዩም ነበር......

«ምነው ንግዱን ትተውታል እንዴ አብዬ ወልዱ.....

«ምን እሱኮ፥ ዱሮም ቢሆን ሥራውን አይሠራም፤ አሽከሮች ናቸው የሚነግዱት..... የሱ ሥራ ካለፍ አገደም መቆጣጠር ነው.......

«መጣፈ ቄደር ያስነከሯቸው እርስዎ መሆንዎን አባቴ ይነግሩኛል። - ዓይንህን አላይም አለዚያ ብለው። - ብዙ ጊዜ ቆይታችኋል ይመስለኛል፤ ለእንዴት ዋላችሁ አደራችሁ እንኳን ሳትዳረሱ...... የሃይማኖት ነገር እሺ አይልዎትም......

«......ካንድ ዘጠኝ ዓመት በላይ.......! የምን ኮተሊክ የምን መጫሚያ ሰኪ፥ የምን ጨርቅ አሣሪ..... ታስታውስ እንደሁ....... የኔ ነገር ደግሞ...... ያኔ አንተ አልተፈጠርክም ቀድሞ...... ከየቴ ብለህ....... እንዴትኮ ይመስልሃል ከነአርኮ በፊት አርኮን መስሎ የመጣው - ዥንጉርጉር ጨርቅ ነገር አንገቱ ላይ አሥሯል...... እንዳገር የሚያብለጨልጭ ቁልፍ የተሸከመ ከቦርታ ደርቧል...... ዛሬ ቦለሌ የምትሉትን ሱሪ

ለብሷል...... ብቻ ምን አለፋህ...... አይሆኑ ሁኔታ ሆኖ ነበር የመጣው...... ታዲያ አሰጋሽ መቼ ዋዛ! ዓይንህን እንዳለየው። - መጣፈ ቄደር ሳትነከር የናት ያባትህን ቀዬ አትረግጣትም አልኩታ! ሊቀ መልአኩን እንኳ እንዳይስም ከመሳለሚያው ውጪ እንዲቆም እያስደረግሁ.......

«እንዲህ ፍቅራችሁ ለሁሉ ሊያስቀና! የማን እኅትና ወንድም ነው በዛሬው ጊዜ ባባት እናቱ ርስት ያልተጋጨ...... ማንስ ነው መሬቱን ሳይካፈል ያፈራውን ብቻ እኩል እየበላ የሚኖር......

«ታዲያኮ አሁንም ቢሆን እንጣላለን። - ያ የባሕር ማዶ ሤጣኑ መቼ ለቀቀው መሰለህ! የፈረንጅ አገር ስም ሲጠራ በፈረንጅ አማርኛ ሲናገር እሰማዋለሁ....... አሁን ከነዚህ ልጆች ጋር የሚሆነውን ነገር...... አፍ ለአፍ ገጥሞ ሲቦተልክ የሚውለውን ብትሰማ ግርም ነው የሚልህ...... ዱሮ ከሚያውቃቸው ፈረንጆች ጋር ያለ ይመስለዋል መሰለኝ...... የኔ ያሰጋሽ ግቢ መሆኑን ይረሳዋል...... መጣፈ ቄደር?! አዎ መጣፈ ቄደርስ አስነከሬው ነበር...... በነገራችን ላይ እዚህ ጀውሃ ትልቅ ጠበል ፈልቋል ይላሉ ለቁርጥማትም ጠሩ ነው ይሉኛል...... ፍልውሃ ነገር ከመሬት እየፈለቀ......

«እንዲህ አይደለም....... ለኔማ ምን ልንገርዎ እንደ ቤቴ ያህል ሆኗል። - እያቅራቢያው የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ዐውቃቸዋለሁ....... በየጊዘው ነው የምሄደው...... ሥራ ሥርን ነውኮ የሚያፍታታው እንዲህ አይምሰልዎት...... ሁለት ቀን ቢጠመቁ የያዘዎ አባዜ ነው ከትከሻዎ ላይ ለቆዎት ብድግ ሲል የሚሰማዎት......

«አባዜስ አልያዘኝም፤ እንዲያው ይኸው የእግሬን ቁርጥማት አንድ ቢልልኝ ብዬ ነበር......! ታዲያ እንግዲያው አሁን አንተ ልጄ እያለህ ምንድነው ሽጉዱ...... ዓርብ ባስራዘጠኝ ገብርኤል ቅዳሜ እንጰታ ማርያም....... እርግጠኛ ነኝ የዘረ ክርስቲያን ልጅ - ሁለቱንም ታቦቶች እንደምታከብር......

«አይ እኔ እንኳን......

«እንግዲያው ለዚህ ነው ይኸውልህ ያስፈልገሁህ...... የወደዱትን ቢያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ...... ከነዚህም የውምበርሴት ሰዎች ታድነኛለህ...... ለመቼ ልትሆነኝ ነው.......

«መቼስ ሌላ ሰው ከታጣ...... እሱ እንኳን የሚያሳስት አልነበረም ቦታው.....

«ምነው እንዳንተ ያለ ሸንቃጣ ወታደር እጐኔ ማስከተሌስ - ምን ያውጣ.......?

«እሺ እንግዲያው መቼስ? ማለድ ብዬ እመጣለሁ ዓርብ ጧት......

«የለም ማለዳ አይደለም። - ሐሙስ መጥተህ እዚሁ ታድርና አብረን ሆነን፥ የሚያስፈልገውን እናዘገጃጅና ዓርብ ጧት ለማኝ ሳያራ ተነሥተን መንገድ እንገባለን......

«መልካም እንግዲያው....... ሐሙስ ወደ ማታ ገደማ እመጣለሁ.......

«ይኸው ነው እንግዲህ ለእናትህና ለአባትህ ሰላምታዬን አድርስልኝ...... ደኅና ናችሆይ...... ብርቱ ናችሆይ...... እንዴት ከርማችኋል...... ብርቱ ከርማችኋሎይ...... በጐ ናችሆይ በጐ ናችሆይ......

## ፳፱

# አደፍርስ

አደፍርስ የአባ አዲሴን ጠበል ሸሽቶ እንደ ወጣ ቀጭኔ የእግር ስላች ተከትሎ በመዝናናት ዓይነት መንገድ ያዘግማል፤ ከዚያ በፊት ያለፈበት ስላች መሆኑንም ያለማጤን። - እጉድባው ከደረሰ በኋላ ነው የሚያውቀው...... የተደበደበውን የሚያስታውሰው....... ይቆማል - ዙሪያ አካባቢውን በጥንቃቄ ይመለከታል - ችፍግ ብሎ የሚታየውን የኵሬውን ዙሪያ በማጥናት፤ ምንም ሕይወት አይንቀሳቀስበትም። - ራሱን ውሃውን ያጠናዋል ይቀጥልና ቀረብ ብሎ - ያይጥ ዓሣዎች ይምሽከሽካሉ ውስጥ ውስጡን - እንቁራሪቶች አልፎ አልፎ ብቅ ጥልቅ ይላሉ፤ ያንገታቸውን ሥር በውሃ ቀብተው - ከምን ወይም ከወዴት እንደሆነ ባልታወቀ እምሽ..... ክ! እያለ እያረፈ በሚሰማ ያቅራቢያ ድምፅ እየታጀቡ። - በግምት የአሥራ አራት ዓመት ዕድሜ የሚኖራት አንዲት ልጅ እንስራዋን እጀርባዋ ላይ እያመናሸች ብቅ ትላለች በዚያው ባንዱ ስላች። - ዝቅ ብላም ወደ ጉድባው ትገባለች። - የጭቃ ብጥብጥ የሚመስለውን ውሃ ደምቦቅ ደምቦቅ ስታደርገው ይመለከታል በአንኮላ - የአደፍርስ። ከቀኟ በኩል ትልቅ ትክል ጥቁር ድንጋይ ይታያል። ከግራዋ በኩል ደግሞ ኵሬውና የባሻገሩ ጢሻ አለ። - ካለፍ አገደም ፊቷን ትኮሰትርበታለች በጢሻው። - ቀድታ ልታበቃ አቅራቢያ ነው እምሽክ እምሽክ ድንገት የምትከሰተው - በቋጥኙ አናት ላይ ብቅ የምትለው - አህያዋ ኖራለች። - ቀናም ብላ አልተመለከተቻት ውሃ ቀጅዋ - ምንዝካዋ፥ ከአካባብቢው ከሚመነጨው ድምፅ ጋር ተዋሕዶ የራሱ የሆነ መልለያ የሌለው ይመስል....... የተለመደ ጩኸት...... መላልሶ መላልሶ የሄዱትን መንገድ ይመስል...... ዕለት በዕለት የማትለየው የብዙ ዘመን ጓደኛዋ ይመስል - ምንም ነገር የሰማች አልመሰለችም። - እንስራዋን ሞልታ በሆዷ ጭምር ገፍታ በማንሣት እቋጥኙ ላይ ታስቀምጥና - ቀስ ቀስ እያለች - እንስራው ዙሪያ እታበተውና በደረቷ ዙሪያ

በሚያልፈው ገመድ ውስጥ ትከሻዋን በማንሸራተት ጀርባዋ በእንስራው ትይዩ ሲሆን ተሸክማ ጉድባውን ትወጣለች - ጢሻውን ገርምማ...... ጸጉሯ ስለተሸረበ ፊቷ ጢም ብሎ የሞላ ይመስላል። - ከወገቧ በታች አጭር ሽርጥ ታጥቃለች። - ከወገቧ በላይ ግን ሳትለብስ የለበሰች ትመስላለች። - የልብስ አስፈላጊነት! ለባሹ ካልተሰማው በስተቀር ተመልካች የማያየው ይመስል! እንስራዋን እጀርባዋ ላይ ሽር ሽር እያደረገች ወደ ቤቷ ታቀናለች። -

አደፍርስ ቁጭ ይላል እኩሬው አጠገብ - ኩሬ ኩሬውን እየተመለከተ...... ጠጠር እያነሣ ወደ ኩሬው ውስጥ መወርወር ይጀምራል...... ያይጥ ዓሣዎች ይሠርጋሉ..... እንቁራሪቶችም አልፎ አልፎ እንኳን ድምፃቸው መሰማቱ ይቀራል..... ሠፈሩ ሁሉ እርጭ ይላል። - አህያዋ እንኳን ዝም ብላ እሱን እሱኑ ታየዋለች። - ጠጠር እያነሣ ይወረውራል አደፍርስ፥...... ጠብታ፥ ትንሽ ክብ - ትልቅ ክብ - ትልልቅ - ትልልቅ - ትልልልልቅ - ትልልልልልቅ - ክቦች እየፈጠረ ይጠፋል። - ድንገት አያምሩ አምሮት ያምረዋል። - አይፈልጉ ፍላጐት ይፈልገዋል። - ወረድ ብሎ በርከክ ብሎ በጆቹ ዘገን ዘገን እያረገ ከዚያ ኩሬ መጠጣት! እንደ ሰዎቹም ብድግ ማለቱ አልቀረም...... ያመነታል..... ያስባል -

........አሜባ የያዘኝ እንደሁ...... ትል ያፈራ እንደሁ ጨጓራዬ ጉሮሮዬ ዐልቅት የተጣበቀስ እንደሁ...... አንዴ - ሐኪም ቤት፥ ካንዲት ልጅ ጉሮሮ ውስጥ በመጐጥ ነገር መኸርጠው ሲያወጡት አይቻለሁ...... እንዴት ነው የሰገጠጠኝ...... አፈሩስ እጉበቴ ውስጥ ቀርቶ ያኮረተ እንደሁ...... ሌላው ቢቀር ተቅማጥ ሊያስከትል ይችላል......

ውሃ ቀጅዋ እንደገና ትመለሳለች። - የጢሻውን አጠገብ አሁንም ገላምጣው ትሄዳለች - ቀድታ ስታበቃ። - አደፍርስን ግን ከቁም ነገርም የቆጠረች አልመሰለች። - አደፍርስ ተመልሶ ይቀመጣል......

......እንዲህ ያለች ነገር..... ያጐጠጐጤዋ አቀማመጥ ደሞ...... በችንካር የቆመ ይመስል..... ነቅነቅ እንኳ አይልም..... አይበርዳትም ልበል..... ምንኛ ጥብቅ ያለ ሰውነት ቢኖራት ነው...... አሁን ጠጋብ ብላት ትጮሃለች....... ምን ይባላል በኋላ ወይዘሮ አሰጋሽ ቢሰሙ...... ወይ አባቷ እዚሁ አቅራቢያ ያርስ ይሆናል...... ወይምኮ እኔ እዚህ መኖሬን ዐውቀው ይሆናል እየደጋገሙ የሚል ኳት...... ለማሳት ያህል.......! ሞኝ ሕዝብ...... እንዝህላል ይመስላል ደርሶ፥ ተንኮሉን እብሸሸቱ ይዞ......» ይወረውራል አሁንም ጠጠሩን..... ጠብታ ትንሽ ክብ ትልቅ ክብ፥ ትልልቅ ትልልልልቅ - ትልልልልልቅ ክቦች እየሠራ ይጠፋል። - አሁንም ትመጣለች ውሃ ቀጂዋ! ቀድታ ታበቃለች። - ወደ ጢሻውም መልከት ብላ መገርመም ብቻ ሳይሆን ከደረቷ

ትንጠራራና በኅይል ቱፍ ብላበት መንገዷን ትቀጥላለች...... ከጢሻው ሥር ክብረት ብቅ ይላል...... አንድ አነሰ ያለች የሥዕል መንደፊያ ደብተርና እርሳስ በእጁ እንደያዘ......

«ተፍታብን ሄደችኮ በል! ተፋችብንኮ! ተፋችብን.......!» አደፍርስ ምንም አይመልስም «ተፍታብን ሄደችኮ......» ይቀጥላል አሁንም። -

«ፋደት ፋደት ሽተናት ይሆናል......!» ይመልስለታል አደፍርስ፤ በልቡ ያወጣ ያወርድ የነበረውን ነገር ፈጽሞ ቢሆን ኖሮ አይቶ ይታዘበው እንደ ነበረ ሲረዳው......

«ይገርምሃል! ዛሬ ሳይቀናኝ የቀረ አይመስለኝም! በዚህ በንድፌ የተመሠረተ መልክ ለማስፈር ከቻልሁ ኢትዮጵያዊ ውበትን ያዝኳት ለማለት እችላለሁ........

«ኢትዮጵያዊን ውበት! ትቀልዳለህ! ኢትዮጵያዊ ውበት የሚባል ነገር የለም..... ውበት ውበት ነው..... ውበትን ቦታ አይወስነውም....... ቀለም አይከልለውም...... ጊዜ አያስረጀውም.....

«እሱን እንኳን ተወው! ማጠቃለሉን....... ኢትዮጵያዊ መልክ ካለ ኢትዮጳይዊም ውበት አለ። - ምናልባት አንተን ያጠራጠረህ በቅርጽ፥ ሠሪ በሠዓሊም ሆነ በጸሐፊ እስከ ዛሬ ድረስ ተይዞ ባለማየትህ ይሆናል - ገና ስልልተጨበጠ። - እርግጥ ነው - እምልህ....... ኢትዮጵያዊ የሆነ፥ ግርማ ሞገስ ያጐላው ዘላለማዊ ውበት የሰፈነው እሰውነቱ ቅርጽ ላይ አይደለም። - አቋቋምም ላይ አይደለም። - ዝለት እሚያሳይ ቀስ አለ አረማመድና ጥንካሬና ኅይልን እሚያሳይ ንቅናቄም ላይ አይደለም - ውብ የሰውነት ትክል የሚታየው። - ለምሳሌ አንዲት ኢትዮጵያዊትን ቆንጆ የምንላት እንደ ሐውልት የተቀረጸች ሰው በመሆኗ አይደለም። ከሚያበቱ ዓይኖቿ የነዳፊነት ፍላጐት እንደ ብርሃን ወራውርት ሲንነፋ ያየን እንደሆነም አይደለም። - ከንፈሮቿ ፈዘዝ ባለ የየዋኅን ሕፃናት ፈገግታ በሚመስል የመሳብ ዘዬ ተገልጠው ያየን እንደሆነም አይደለም..... ሌላው ቀርቶ ገርጣ ያለ ቆዳ፥ ደከም ያለ አስተአይየት የደም መሽከርከርን የሚያሳዩ ጉንጮች እንኳ ቢሆኑ፥ የኛ አገር የውብ መልክ ምልክቶች አይደሉም፤ የኢትዮጵያን ውበት አያሳዩም.........

«እንግዲህ እንዲያ ከሆነ የኢትዮጵያዊት ውበት የማይያዝ የማይጨበጥ በአእምሮ ውስጥ ብቻ ያለ የሚመስል ነው ማለት ነው..... እንዲያ ከሆነ ደሞ....... ራሳችንን መደለላችን ካልሆነ በቀር ውበት የለንም ማለት ነው.......

«አላስጨረስከኝምኮ........!

«እኔስ አስጨርሼሃለሁ....... ብቻ ካስፈለገህ ቀጥል.......

«እሺ እንግዲያውስ ስማ...... የኢትዮጵያዊት መልክ፥ እሚንቀሳቀስ ሕይወት ላይ ያሰፈፈ ነው፤ ነፍስ ስታልፍ ስታገድም የሚታይበት። - በድንጋይም ላይ ሆነ፥ በመሣያ ሽራ ወይንም በወረቀት ላይ ጠቁሞ ለመያዝም ያስቸገረው በዚሁ ምክንያት ነው። - ቆራጥነትና ልበ ሙሉነት ሲፍለቀለቁ ኀሊና ያልተቀበላቸው ረቂቃን ሲዛዛቱ መስሎ ለመኖር የሚደረጉ ቸልተኛነት፥ ቻይነትና ኀይለ ስሜት ሲዋጉ የተደበቁ ደስታዎችና ብሶቶች - ጠቅላላ የሐሳብ ነጸብራቆች - እምቅ ጭምቅ ከሚለው ልብ እያውገነገኑ ሲወጡ የሚታይበት መነሳንስት ነው። - በየፎቶው ቤት እንደተሰቀለው ዓይነት፥ ሕይወት የለሽ ባዶ ዓይኖች ያጕጡበት፥ ሐሳብና ስሜት የማይሠርጉበት መልክ፥ ውበት ነኝ ካለ፥ ኢትዮጵያ ሰብእና ጠፉ ማለት ነው......

«በቃላት መቼም...... እውነቱን ልንገርህ ምንም አልያዝኩልህም...... ምናልባት በመሣሪያ ሽራህ ይሳካልህ እንደሁ እናያለን...... ይልቅ ወደ ቁም ነገሩ እንመለስና - ያቺ ልጅ ስንት ጊዜ እንደተመላለሰች አይተሃል......?

«አዎ አይቻለሁ!» ይለዋል ከፉ ባለው አንደበት። -

«ሦስት ጊዜ መጣችኮ፥ እኔ እንኳን እያየኋት......

«እኔ ደሞ ብቻዬን ከዚያ በፊት ብዙ ጊዜ አይቻታለሁ...... ምን ይሁን ታዲያ!

«እምልህ አሁን ያን ሁሉ ውሃ ምን ልታደርግበት ነው? የሌላ......

«ጠላ ልትሞለበት.....

«ቀልዱን ተወውና የሌላ፥ ነገር አይመስልህም? - ምናልባት አንተን ወይም እኔን ለማጥመድ......

«አንተ ደሞ አይቸግሩ ችግር ይቸግረሃል ሁል ጊዜ.......

«ሙት እውነቴን ነውኮ........!

«ለመሆኑ...... ለመሆኑ...... ምንህ ነው የሚጠመደው...... እምልህ ምንድነህ አንተ? ራስክን ከፍ አድርገህ ስለምታይ ብቻ አይምሰልህ.......

«ሞትና ሕይወት! እኔን ያበሰለኝ ጡጫ አንተንም አግኝቶህ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ባላልህ.....

# ፴

# አደፍርስ

ሰኞ ሌሊትና ማክሰኞ እስከ ሰዓት ድረስ ያለማቋረጥ ይዘንባል። ከሰዓት በኋላ ነው የመጀመሪያው ትንሽ ተግታ የተገኘው - እያለፈ መጀጀሩም ባያቋርጥ። ዳመናዎቹ አሁንም ለርክፍካፏቸው የሚዘጋጁ ይመስላሉ፤ ዝቅ ብለው ያሞለሙላሉ - ፀሐይን ሳይከልሉ። - አልፎ አልፎም ፈለቅልቅ ፈለቅለቅ ይላሉ፤ አብረቅራቂ ንስነሳቸውን ለመጠቀም - በሽውታ በስልታ ዓይነት ድምፅ ለማነብነብ እሥራቸው የተንጣለለውን ብጫ አረንጓዴ አፈርማና ግራጫ አገር በድንገተኛ ውርጃቸው ለማጥለቅለቅ። እስኪያም ቢሆን ትንተገተጋለች ታዲያ ፀሐይዋ - በዚህ ሁሉ የዳመና ጥርስምስምና ትርግርግ መካከል እያለፈች....... ሞቅታ ብሩኅ፥ በብርሃን የሚምቦለቦል ዓይነት ሕይወት ሰጥታው ለቀኑ። -

በነፋሱ ሲመናሽና ሲመሳቀል የቆየው ሳር አሁን እርጥበቱን ይመገምጋል፤ አይንቀሳቀስም። - ቅጠላ ቅጠሎች እስከ ሥራሥሮቻቸው ድረስ እርሰው በለዛዛዊ ግንዶቻቸው ላይ ይምሸከሸካሉ። - ወፎች ከየቦታው ይጠራራሉ...... ግሪሳው - ጨረባው - ወማዩ - ነጐዴው - ዱዱቴው። - እየተጋፋ ጉርምርታና ሽውሽውታ እየደከመና እየራቀ የሚሄደው የዝናብ ጉርምርምታና ድርቅርቅታ ከያካባቢው ከሚፈልቀው ከሙሉና ከስንጥብ ጉሮሮ ይወጣ ከሚመስለው የሕይወት ሲርሲርታ - ኩርኩርታ - ችርችርታ ጋር ተዋሕዶ ሲሰሙት የስሜት፥ ታንቲራ ይቀሰቅሳል። - መጫሚያ ሲጨብጡ የነበሩት መንገዶች አሁን ይጨሳሉ...... ተግ እያለ ከሚቸችረው ዶፍ የተነሣ ችቃቸው በየቦታው አደጥድጦ.....

ጺወኔ፥ የባዘነች እምትመስል አንዷት ጥጃ ኋላ ኋላ እያለች የአደፍርስን እግር ተከትላ በውጣችበት ጊዜ አገር በሙሉ ደስስ........ እያለ በየሠራ አካላት ውስጥ በሚሠርግ ውደት ተሞልቶ ነበር። ሰማዩም እንኳን በከፊል ጠርቷል ለማለት ይቻላል። - ውጡና ተንሸርሸሩ በሚል ዓይነት ገልጾታ.........! ሣሩና ችፍርጉ እግሮቿን እየደባበሷት በትኩስነት የሚቡለቀለቁት ጤዛ አዘል ቅጠላቅጠሎች ዙሪያዋን እየተንሻሹ የጥላና የብርሃን ውዝግቦች እላዋ ላይ እየወጡ እየጠለቁ - እየተውረገረጉ ነበር ጺወኔም አረማመዷ...... በነፋሱ ምሥጢር እየተገፋፋችና በወጣትነት ሕይወቷ እየተፍለቀለቀች...... ብዙ ወዲያ ወዲህ ካለች በኋላ ሳታስበው ነው ድንገት ከወደ ጢሻ ውስጥ ዱብ ሲል የምታየው - አደፍርስን......

«አንተ......!» ትለዋለች ከወደኋላው - ድንግጥ ብሎ ዘወር ይላል። «አገኘሁህ ይኸውልህ፤ አገኘሁህ - ባንተ ቤት ተደብቀህ መምጣትህ ነበር......

«ድን.....ቁ...... ርና! ለመሆኑ እዚህ ምን አመጣሽ? እንዴት አገኘሽኝ......!» ይላታል ድምፁ ድንጋጤውን እንዳያሳይ ለመደበቅ በመታገል «እምልሽኮ...... ብቻሽን እንዴት ትመጫለሽ ነው?!» ይላታል ይቀጥልና ግራ በገባው ሁኔታ።

«አሁን አትጠይቀኝም! ምን ያስፈልጋል አሁን ጥያቄ......? ምን ያረጋል - አሰልቺ ነገር...... አንተ የሄድህበትን ቦታ ለማግኘት ፈለግሁ፤ መጣሁ...... አለቀ......!» ጠጋ ትልና ኮቱን ያዝ አድርጋ «ምነው ተቆጣህ እንዴ......?» ወበቷን በሚያጋንን በብሩህና ደስ ባለው ዓይን ትመለከተዋለች፤ ሕፃናዊ እምነትን በሚተነፍስ አስተያየት «.......እንደ ጠረጠርሁት እዚህ ሳገኝህ ምንኛ ደስ አለኝ ይመስልሃል? ምንኛ......!» ሳቅ በማለት እሱን እየተመለከተች «ምናልባት በጣም ርቀህ ሳትሄድ አትቀርም ብዬ ነበር..... ትናንትና የአባን ጠበል እንመለጥህ ነገር አሳቀኝና...... ወዲያው ሳቁ ወደ ሐዘን ተለውጦ ቀኑን ሙሉ ደስ ሳይለኝ መሸ..... ምን እንደ ነካኝ አላውቅም..... ስለዚህ አንተንም እንኳን ላይህ አልፈለግሁም ነበር..... ምን በወጣህ ትቸገር እኔ መላዬን ባጣሁ......» መልከት ትለዋለች ቀና ብላ «......ደስ አላለህም.......? ምነው ፊትህን ጨፍግጐሃል ዛሬ......! አትናገርም? ደስ አላለህም? እኔስ፥ እንደዚህ እንዳውሬ አሽትቼ ሳገኝህ ነገሩ ገርሞህ ያስደትህ ነበር የመሰለኝ...... አንተ ግን እንቅልፍ የገረዘዘህ መስለሃል....... ይንቁ ይንቁ ጌታዬ! ጂወኔ ከርስዎ ጋር ናት......» ትንሽ ጐንተል ታደርገዋለች «ደኅና አይደለህም? ምን ሆነሃል........?

«ደህና ነኝ እኔስ፤ ብቻ ትንሽ ቅር ያለኝ እንደዚህ እርቀሽ ብቻሽን መምጣትሽ ነው.....

«ይኸ የኔ ጉዳይ ነው..... ምነው ከሮማን ጋር ብመጣ ይሻል ኖሯል.....?

«አዎ፥ ይሻል ነበር.....

«ባውቅ ኖር ይዣት እመጣ ነበር......» እሮጥ ትልና ወደ ፊት - አንድ የወይራ ቀምበጥ በመቅጠፍ «እኔ ደግሞ ሮማንን - ለምን እንደሆነ አላውቅም...... ላይንህም እንኳ ማየት የምትፈልጋት አልመሰለኝ....... ከኔ ጋር ደግሞ ብቻችንን ሆነን ስንጫወት ደስ ይለኛል ብለኸኝ ነበር፤ ረሳኸው......?

«አዎ ብየሻለሁ፤ ግን እዚያው እግቢው ውስጥ ማለቴ ነበር......

«ምነው፥ እዚህ ቢሆን ምናለበት? ትፈራለህ.......? ማንን ትፈራለህ.......?

«አዎን እፈራለሁ፤ ራሴን እፈራለሁ.........» ስብርብር ሳቋን ታመጣለች ጺወኔ...... ወደ ሆዷ ወደ ሆዷ የምትውጠው እያስመሰለች። - ትንፍስ ትንፍስ እያለች -

«ራስክን ትፈራለህ......? ራስክን ትፈራለህ.......? ነገርህ ሁሉ ያስቀኛል....... በጣም ያስቀኛል......» ትለዋለች። -

«እንዲያው ለመሆኑ ምን ሰበብ አግኝተሽ መጣሽ ይባላል? እመየቴ ቢሰሙ...... ሌላ ያገሬው ሰው ቢያየን.....

«ይኸ እባክህ ሊቸገሩበት አያሻም..... ይልቅ ስለ ሌላ ነገር እናውራ - ምን ኖሯል ልነግርህ ያሰብሁት..... ረሳሁት.....

«ምናልባት እዚህ እንዴት እንደ መጣሽ እንደሆን......?» በመጠባበቅ ዓይን እየተመለከታት -

«አይ ኤዲያ..... ለምን ችክ ትላለህ - እስከዚ እኔን ሕፃን ማድረግህ ነው እንዴ? አንድ ነገር መደጋገም አይሰለችህም...... ምን ልል ነበር የፈለግሁት...... ግዴለም አሁን አስታውሰዋለሁ..... ውዬ......! ደስ ይላል እዚህ! ተመልከት እዛፉ ሥር የተለሸለሸውን ክርክም ያለውን ሣር..... ተመልከት ደሞ፥ እውጪ የተጋደመውን የዚያን የዋንዛ ሥር...... ለምን ሥር...... ለምን ወደ ጫካው ውስጥ አንገባም......? ደስ ሲል እንዲህ አይምሰልህ.....

«ጫካ! አብደሻል? ጤዛው ሁሉ ገና መቼ ረገፈ! እርግጠኛ ነኝ፤ በጣም ነው የሚያረጥበው ውስጡ..... ቅጠላ ቅጠሉን በነካሽ ቁጥር ጤዛው ሰውነትሽን እያራሰው..... እኔ ደሞ ኮት ወይም ቡልኮ አልለበስኩም እንደምታይው.....

«እኔም አለበስኩም፤ ምን ያስፈልጋል? በጣምኮ ነው ደስ የሚለው...... እንሂድ እባክህ......» እንደ መሮጥ እያለች ትጐትተዋለች። - እያጉረመረመ ይከተላትና ወደ ጫካው ያመራሉ። -

«ለመሆኑ ከግቢው ሲያጡሽ ምን ይሉ ይመስልሻል?» እንድገና ይጠይቃታል። -

«ልንገርህ......?» ስልት ትጀምራለች ጫካው መካከል፣ ሲደርሱ «አሁን ልነግርህ እችላለሁ፤ ወደ ኋላ ሮጠህ አትመለስም - እርግጠኛ ነኝ እሜዳ ቢሆን ኖሮ እስከዚህም አትመጣ ነበር......

«ለምን.......?

«ዓርብ ጧት፥ ጀውሃ ትሄዳለህ ከኛ ጋር.......?

«አዎ ለምን አልሄድም ከፈለጋችሁ........!

«በጧት ተነሣ ታዲያ! ዓርብና ቅዳሜን እዚያው ውለን እሁድ ወደ ደብረ ሲና ትወጣለህ......» ምንም መልስ አይመልስላትም፤ ዝም ብሎ በሩቁ ይመለከታል «አይ እንግዲያው እኔም እዚህ እንዴት እንደ መጣሁ አልነግርህም......

«አርብ ጧት አብሪያችሁ ጀውሃ ድረስ እሄድና ከዚያ ያንለቱኑ ወደ ደብረ ሲና እወጣለሁ.....

«ይገርምሃል! እዚህ የመጣሁት ለምን መሰለህ.......? አንድ ነገር ልነግርህ ፈልጌ.....

«ምን.......? ምንድነው ልትነግሪኝ የፈለግሽው........?

«ማለት...... አንተ ከኛ ጋር ጀውሃ ሄደህ መክረም ያለብህ መሆኑን...... ቸኩዬ ነበር ልነግርህ.....

«ምን ማለትሽ ነው? አሁን እስከዚህ ድረስ ስድ እለቀቃለሁ ነው የምትይኝ..... እምልሽ...... እንዲያው ወዴት ሄደችም አትባይ? - አረም አታርሚ ከብት አታስወጪ - ወይ ማምሻ እንጨት አትለቅሚ......

«ለምን አላርምም - ለምን አላስወጣም - ለምን አልለቅምም......

«አያሠሩሽማ በቃ! ልሥራም ብትይ አያሠሩሽም! እና አንድ ምክንያት ፈጥረሽ ይሆናል ከቤት የወጣሽው......

«ከቤት የወጣሁት......? ህእ...... ወጣኋ! በቃ፥ ወጣሁ.......! እምልህ - ምን ያረጋል ብለህ ነው አሁን ስለዚህ ማውራት.....?» በጅዋ ሙሉ ቅጠል አፍሳ ወደ ሰማይ ትበትናለች......ወዪ.......! እንዴት ደስ ይላል? ሠፈሩ ሁሉ...... ደስ አይልም.......? ደስ ነው ያለኝ እኔስ...... ነገም እዚህ እንምጣ እባክህ.......

«ሞትና ሕይወት! መጀመሪያ ዛሬ እዚህ እንዴት ልትመጪ እንደቻለሽ ንገሪኝ...... ስለ ነገው......

«......አያስቸግርም እንመጣለን!» ትሞላለታለች ጺወኔ፡፡ -

«ቀልድም ታውቂበታለሽ ለካ......!

«የኔ ነገር እየረሳሁትኮ ነው ቀልድ አለመውደድህን......? እሺ አልቀልድም..... አንተ ብቻ አትቆጣ..... አሁን ልሂድና ለጥጃው ሣር ልቦጭቅለት መሰለኝ፤ ቶሎ እመለሳለሁ.....

«ለጥጃው? የምን ጥጃ......?

«ምነው ቅድም አልነገርኩህም......?

«የት ነው የነገርሽኝ......?

«ውዬ አልነገርኩህ? እንዴት ብዬ! ረስቼው ይሆናል። - አንዱእን እቤት የታሠረች ጥጃ ለቅቄ በሷ ሰበብ ነው ልፈልጋት ብዬ የወጣሁት......

«ታዲያስ.......?

«በቃ! ምን ታዲያስ አለ......? ያ - ያ - ያኣ...... ያ!» በሩቁ ታሳየዋለች «ማ ሚሉት ቤተክሲያን ይሆን......!?

«የቱ?»

«ያ! ያ! በግራችን በኩል ያለው........?

«ሚካኤል ይሆናላ! ሌላ ማን ይሆናል? አገሩን ሁሉ ያለበሰው መቼም እሱው ነው...... እሺ እምልሽ ጥጃዋን ለቀቅሽና......

«........እንዲህ መሰለህ እንዴ? እምቧ እምቧ እያለች አስቸግራ...... ለምለም ሣር በጄ ቦጨቅ ቦጨቅ አድርጌ እፊቷ ሳደርግላት ነው ዝም ያለችው......

«ስለ ሣር ቡጨቃ አልነበረም የምናወራው....... እሺ ከዚያ ምን አደረግሽ.....

«ምን አደርጋለሁ፤ ምንም አላደረግሁ......

«ጥጃዋ ታዲያ የታለች.......?

«ታሥራለች ከመንገድ ወጣ ብላ......» በሩቁ ፊለፊታቸው ያለው ተራራ በመመልከት.....

«እንደ ታሠረች አግኝቶስ አውሬ የበላት እንደሁ......?

«ያ እተራራው ደረት ላይ ያለው መንገድ እንዴት የተጠመዛዘዘ ነው......! እስኪ አንድ ቀን ወደ አጠገቡ እንሂድ...... ወደ አዲሳባ መሄጃችሁ በዚያ በኩል ነው........?

«አዎን በዚያ በኩል ነው.....

«በየት በየት አርጐ ነው የሚያስሄደው? አታሳየኝም.......?

«ጥጃዋንስ አውሬ የበላት እንደሁ........?

«አይበላትም፤ እኛ ቀዬ ደግሞ አውሬ የለም...... ይኸኔ እሷ ለራሷ ደጎና ሣሯን ትበላለች...... እኔም ይኸው ደጎና ካንተ ጋር እጫወታለሁ.....

«ምን ማለትሽ ነው ጺወኔ? አትቀልጂ! እኔ በምሬ ስጠይቅሽ.....

«ምን ቀልድ አለ፤ እውነቴን ነው.... ሆን ብዬ ጥጃዋን ለቀቅኋትና ከታሠረችበት ተከትያት መጣሁ......

«አሽከሮች ተልከው ያገኟትስ እንደሁ ጥጃዋን? አንቺ ወዴት ሄድሽ ይባላል.......?

«አጥታት እሌላ ቦታ ትፈልጋለች ይባላል.........

«ማን አሠራት ይባላል ታዲያ......

«ታሥራ ተገኘች አይደለም የሚባው፥ ተጠላልፋ፥ ተገኘች ነው......

«የሰው እሥርና ዐውቆ ተጠላልፎ የታሠረ መለየት አውኳቸው......

«ከዚህ በፊት ጥጃ ተጠላልፎ እንጂ የትም ታሥሮ ስላልተገኘ የታሠረ አይመስላቸውም......

«አትቀልጅ እባክሽ..... ታሥራ አገኘናት ያሉ እንደሆነ ምን ይበጅሻል? እስከ ዛሬ ያላሉ እንደሁ ዛሬ ላይሉ ነው......?

«ምንድነው እንዲህ ያለ ነገር.......? ሰማይ ቢከነበልብንስ - ዛፉ ቢጐርሰንስ...... ተራራው እግር አውጥቶ ቢሄድስ...... ጥጃዋን አውሬ ቢበላትስ...... ምንድነው እንዲህ ያለ ነገር?» እንደ ገና ቅጠል አፍሳ ወደ ሰማይ ተበትናለች «ምን ይሁን ታዲያ......?!

«ካንቺ ቀድመው ያገኟት ይሆናል አሽከሮቹ፤ እንደ ታሠረች......! የለም ይቅርታሽንና እኔ ደስ አላለኝም ነገሩ....... እንመለስ..... አይሆንም......

«ምን መሆንህ ነው.......? ምንም ምንም ሳትነግረኝ..... ጃንሆይ ስለ ሰጧችሁ ቤተ መንግሥት...... ስለዩንቨርስቲው...... ስላስተማሪዎቹ...... ስለትምህርቱ...... ምነው ቀስ ብለን አጫውትሻለሁ በለኸኝ......

«ስለ እሱ እዚያው እግቢም ቢሆን እናወራለን..... አሁን ቢሆን መመለስ አለብን...... እመየቴስ ምን ይሉ ቢሰሙ...... በሳቸው ገንጋኝነት......

«እሺ እንግዲያው እንዳልህ መቼስ.....» የተመልሶ መንገዳቸውን እንደተያያዙት እሷ ቀስ እያለች ለመሄድ ስትፈልግ እሱ ያጣድፋታል «ለምን ታጣድፈኛለህ! ቆይ.......! ባይሆን እንኳን ቀስ እያልን እንሂድ...... የምን ጥድፊያ ነው.......» ልታስቀስሰው ትሞክራለች። -

ብን ያለ የሚያነበንብ ካፊያ ማካፋት ይጀምራል «.......ይኸውልሽ መመለሳችን በጅቷል...... አጉል ቦታ ሊይዘን ነበር ዝናቡ.......» በሩቁ እየተመለከተች ቀስ እያለች ትራመዳለች...... ምንም መልስ አትመለስለትም «ይኸ የክረምት ዝናብ አባራ ሲሉት አካፋ ነው.......» ምንም መልስ አያገኝም አሁንም..... ጺወኔ ከመገዱ ወጣ ወደምትል ሥርጥ ታመራለች...... አደፍርስ ይከተላታል...... ጥጃዋ የተቦጨቀላትን ጨሌ በላልታ በጉልበቶቿ ጋድም ብላለች....... መንዝከ - መንዝከ - መንዝከ ቆም - መንዝከ - መንዝከ - መንዝከ ቆም እያደረገች አፏን.......ቀናም ብላ አላየቻቸው -

«አሁን ልትነግረኝ ትችላለህ እንግዲህ ስለ ጃንሆይ ቤተ መንግሥት......» ትለዋለች ጺወኔ - ከጥጃዋ አጠገብ ተመቻችታ ትቀመጥና -

«አብደሻል እንዴ! እንደዚህ እያካፋ እንዴት እዚህ እንቆያለን....... ጉንፋን ብርድ በሽታ ትክትክ..... እምልሽ ስንት ዓይነት በሽታ - ያስከትላል.......» አንገቷ ላይ የነበረች ትንሽ አንገት ልብሷን ታውርድና - እጥጃዋ አጠገብ አመቻችታ አንጥፋ -

«ያውልህ ሱሪህን እንዳያረጥብብህ...... እጨርቁ ላይ ተቀመጥ!» ትለዋለች።

«ጺወኔ! እኔ እንዲህ ያለውን ነገር አልቀበልም......

«እንዳልኩህ ይኸውና አሽከሮቹ አልወሰዷትም ጥጃዋን፤ አሁን እንግዲህ ምን የሚያሰጋ ነገር አለ.......?

«ትቀልጃለሽ ጺወኔ.......!

«ቢወስዷት ኖሮ እውነትም ቶሎ ወደ ቤት እንመለስ ነበር.......

«ምነው ለራሳችንስ ጤንነት....... በሽታ ያመጣብናል ስልሽ አይገባሽም.....

«ልጅ ሆነህ አሳድገኝ! አሳድገኝ! አሳድገኝ! እያልልክ እዝናብ ውስጥ ተጫውተህ አታውቅም.......?

«ያ ሌላ ይኸ ሌላ!

«እንግዲያው ያው ነው፤ ዛሬም ቢሆን ልጆች ነን..... በሽታ አያመጣብንም.....

«አይ፥ እንግዲህ አንቺ እንደ ብጤትሽ! እኔ መሄዴ ነው..... እዚህ ኪኒን እንኳን እማይገኝበት አገር...... ‹ፍሉ› ይዞኝ ለመማቀቅ አልፈልግም.....

«ጨከነህ ጥለኸኝ አትሄድም!

«ሞትና ሕይወት ብሎ ነገር.......! የጭካኔ ነገር አይደለም ይኸ.......» ዘወር ብሎ መንገድ ይገባል።

«ጨከነህ......?

«ነገርኩሽ እንግዲህ.....

«ጨከነህ...... ጨከነህ.....?» እምቧ ማለት ትጀምራለች ጥጃዋ፥ ከባሻገሯ የከብት ድምፅ ስትሰማ.....

## ፴፩

# አደፍርስ

ለሐሙስ አጥቢያ ሌሊትም እንዲሁ ዘጥሮ አደረ ዝናቡን - ዲደን ቅልቅል ሆኖ እየመጣ ሲያብረገርገው። - ረፋድ ገደማ ነው ወደ ንፍንፍ የተለወጠው። - ያም ሆኖ ታዲያ እስከ ሰዓት በኋላ ተግ አላለም። ጺወኔ ብርድ ብርድ እያላት እጅግም ጤና የላት። - ረቡ ለት ስለ አደፍርስ የተሰማት ግብት ግራ አጋብቷታል። - አንዳንዴ ለትስብኤ ያላት ሐቅረት ቀኖቱን በሠራ አከላቷ ነስንሶ ይሰማታል። - አንዳንዴ የርቄት ዓለም አንዳንዴ፥ የበከ ዓለም ይታያታ፤ የሕይወቷ ሑረት ቀኖቱን በሠራ አካላቷ ነስንሶ ይሰማታል። - አንዳንዴ የርቄት ዓለም፥ አንዳንዴ የበከ ዓለም ይታያታል፤ የሕይወቷ ሑረት በማይመረመር ምያኔ ተውጦ የሚቀር ይመስል...... በመታወቅ ምያኔ - በሀብታምነት ምያኔ - በሙዚቀኛነት ምያኔ - በጋብቻ ምያኔ - በዩንቨርስቲ ትምህርት በፈረንጅ አገር ትምህርት በዐዋቂነት ምያኔ። - አንዳንዴ ደግሞ ሰው የማይሰማው ሕሠም ያለባት ይመስል የፍራት ፍራት ባርባርታ ይተራመስባታል። - ጐርፉ በቀጠሮው መሠረት ሲደርስ ከአደፍርስ ጋር እበረት ይገናኙና አብረው ወደ ወይዘሮ አሰጋሽ እልፍኝ ይሄዳሉ። - ወይዘሮ አሰጋሽ እማሳ የደምበሾ ጉድጓ አስከፍተው ማሽላ

ያስወጡ ስለ ነበረ አያገኟቸውም። - ጺወኔ ግን ቤት ውስጥ ስለ ነበረች ገባ ሲሉስ ታያቸው ቶሎ ራሷን ትገዛና ብድግ ትላለች።

«ውዱ፥ መጣህ እንዴ፥ ጐርፉ......? እንኳን የመጣህ!» ትልና «እማዬ እጉድጓድ ቦታ ነች...... ቁጭ በሏ ታዲያ......» አቡዳዎቹን እመደቡ ላይ ታስተካክልላቸዋለች።

«ብዙ ጊዜ፥ ላነጋግረው ፈልጌ፥ አሁን ደኅና አጋጣሚ አገኘሁ መሰለኝ......» ይላል አደፍርስ ፈገግ ብሎ።

«ኧረ፥ ልታነግጋግረው ፈልገህ ነበር? ለምን አልነገርከኝም ታዲያ.....» ፊቷ ላይ የነበረው ጭጋግ ላንዳፍታ ይነሣል።

«አንቺ መቼም ሰውን ያለ አንድ ምክንያት ስለማትወጂ......

«ትወድሃለች በልና በል አኩራዋ እንግዲህ? እንዲያውም እንዲያ ነሽ እንኳንስ ዘንቦብሽ......

«መውደዷን ማወቅህ ያኮራሃል?» ይጠይቀዋል ጐርፉን ወደ እሱ መለስ ብሎ።

«ህእ!!» ይልና ዝም ይላል ጐርፉ። -

«ስቀልድ ነው። - ጐርፉ ባይሆን የድንገት ክፉት አለበት እንጂ ኩራት አያውቅም....... ደሞ እንደምወደው ያውቃል......ታውቅ የለም እንዴ ጐርፉ.......?

«ህእ!!» ይልና ዝም ይላል አሁንም

«መዋደድን የመሰለ ነገር የለም.......» ይላል አደፍርስ፤ ከማንም መልስ የማይፈልግ በሚመስል ድምፅ።

«ዛቢያና ምሣርስ ይዋደድ የለም? የመዋደድ ነገር...... ምን አሉ አሉት......?» ድንገት ያመጣዋል ጐርፉ።

«እውነት ነው፤ ብዙ ዓይነት መዋደድ አለ...... አሁን ለምሳሌ፥ ለጊዜው የሚሆን የፍወት መዋደድ አለ - እንግዳ ቁርበቶች አጉራ ዘላዮች ዘንድ እንደሚገኘው ዓይነት። - በተፈጥሮ ባካባቢ፥ ባይነት፥ በፍላጐት የተገናኘ በመመሳሰል ላይ የተመሠረተ መዋደድ አለ - ድመት ድመትን ውሻ ውሻን እንደሚወድ ዓይነት። - ከልማድ የተነሣ አብሮ፥ ከመኖር ብዙ ጊዜ እየደጋገሙ ከመገናኘት የተነሣ የሚፈጠር መዋደድ አለ፤ ለምሳሌ - ድመትና ውሻ እንደሚኖሩት ዓይነት። - ከትንሽነት ወደ

ትልቅነት ተከባክቦ ለሚያሳድጉት ነገር የሚኖር ልዩ ዓይነት መዋደድ አለ - የተከለውን ዛፍ ቢቆርጡበት፥ ያሳደገውን ውሻ ቢሙቱበት የሚወድ ማን አለ.......?

«ታዲያ የኛ መዋደድ የትኛው ዓይነት ይመስልዎታል?» ይጠይቃል ጐርፉ አደፍርስን ቀስ ብሎ።

«እኔ ምን ዐውቃለሁ - የምታውቁት ራሳችሁ....... ልቡሰ ጥላችሁ ተገናኝቶ እንደሁ......

«እሺ እኔ ለምሳሌ አንተንም እወድሃለሁ፤ እና.......» ትለዋለች ጺወኔ አደፍርስን መሬት መሬት እየተመለከተች «........የቱን ዓይነት መዋደድ ነው የኛ.......

«እንደ ድመትና ውሻው ዓይነት እንደሆን?» ይመልሳል ጐርፉ አሁንም ቀስ ብሎ። -

«ሊሆን ይችላል፤ እውነትህን ነው። - ለትንሽም ጊዜ ቢሆን እየደጋገሙ ከመገናኘት የተነሣ የሚፈጠር...... የማይሆንበት ምክንያት አይታየኝም - ሊሆን ይችላል......

«አይመስለኝም!!» ትላለለች ጺወኔ። - ድንገት አደፍርስና ጐርፉ ሲገቡ ወደነበረችበት ምያኔ በመመለስ...... ለትንሽ ጊዜ ሁሉም ዝም ይላሉ። -

«ታዲያ እስኪ ትንሽ ስለ አገር ቤት ጨዋታ አምጣ!» ይለዋል አደፍርስ ጐርፉን። - ጐርፉ መልስ አይመልስም...... «ስለ ፈለግኸው ነገር፤ ስለ ባህሉ ስለ ኑሮው ስለ ጨዋታው.......!» አይመልስም አሁንም ጐርፉ «እምልህ፥ ሌላው ቢቀር ብዙ በቃል ሲተላለፍ የኖረ ጨዋታ አለ....... እንደ ተረት ዓይነት - ለምሳሌ.....

«ካወቁት እንግዲህ እርስዎ ያውጉና.....

«መኖሩን ዐውቃለሁ፤ እንዲህ ነው ብዬ ማውራት ባልችልም.....

«ታዲያ እንዴት ዐውቁት.......?

«እኔ አላጫውታችሁ አንድ ተረት...... እንኳ ብቻ ምን ዓይነት ነው ልበል...... አያስቅም...... አያሳዝንም...... እንዲህ እንግዲህ አለ አይደለም.....

«ጥሩ ጥሩ እንስማው.......! እስከዚያ ድረስ ደሞ......» ይልና ፈገግ ብሎ መለስ ወደ ጐርፉ።

«ማነህ ባለ ሳምንት ማለትዎ ነው? ይገባኛል.......! እስኪ እንግዲህ የጺወኔን እንስማና......

«ያስጠምድህ ባሥራ ስምንት አይደለም አጃቢው?» ይጠይቃል አደፍርስ አሁንም ወደ ጐርፉ ዘወር ብሎ......

«አቶ ጅብ ሦስት ልጆች ነበሩበት ይባላል። - በተወልዱበት ቦታ ስም ነበር የሚጠራቸው - አምቡልጋ አባ ጆቢጥ አዲላላ እያለ። - እንደ ልባቸው ነበር የሚኖሩት.......» እያለች ትጀምራለችን ጺወኔ «- አንድ ቀን አቶ ጅብ ከበኩር ልጁ ከአምቡልጋ ጋር አብሮ ሲዝናና ያመሸና ሲመለስ ሁለቱ ልጆቹ አንደ ውለው ኖሮ ምንም ሳይሳካላቸው ደከመው መመለሳቸውን ይነግሩታል። - አባት ነውና መቼም - ይነደዋል በጣም ይነደዋል - በልጆቹ ሥራ አለመሳካት። - ኑ እንውጣ ተመልሰን ይልና ይዟቸው ይሄዳሉ። - ሰው ወደ ሚኖርበት ሠፈር ሄደው ያገኙትን እያገኙ ያስሳሉ ለብዙ ጊዜ! አጣን ብለው ተስፋ ሊቆርጡ አቅራቢያ ነው ዕንግዲህ ያልታሰበ ዕድል የሚገጥማቸው፤ አንድ የፈረጠጠች አህያ የሚያገኙት። ይደሰታሉ፤ ይፈነድቃሉ...... መቼስ ያልታሰበ ነገር የሚሰጠው ደስታ ምኑ ይጠየቃል ከዚያም አምቡልጋ ፊታውራሪ አባት ተገን ሆነው እየተከታተሉ ወደ ምንጭ አጠገብ ይነዷታል.... እያረፈ እያማገ፥ ቀስ እያለ ነው የሚባለው ይባላል ዥብ...... እንዳህያ ዙሪያ ሆድ ነው ይባላል...... እዚህ አዲሳባ እሚሉትማ አገር ከሰው እኩል ነው አሉ የሚጋፋው....... እና ታዲያ ምናለ፥ ከዚያማ እምንጩ አጠገብ እንደ ደረሱ አቶ አባት ቀስ ብሎ ያደባና ሆድቃዋን ዘርግፎ ሊጥላት ይሞክራል። - እሷ ግን ኀይለኛ አህያ ጅማቷን እየጐተተች - ሆድ ዕቃዋን ቦትርፎ ኀይለኛ አህያ ጅማቷን እየጐተተች - ሆድ ዕቃዋን ቦትርፎ እስኪያወጣው ድረስ አትወድቅለትም...... የራበው ዥብ ግን ምን ርኅራኄ አለው? ዓይኗ እያየ...... ፍርግጥ ፍርግጥ ስትል...... ነፍሷ ሳይወጣ...... ዓይኗ እያየ ይበላታል ቀስ እያለ። - ራቡ ጋብ ሲልለት አህያዋም ስትሞት የኋላ ኋላ ነው አምቡልጋን ፊታውራሪውን እንኳን የሚጋብዘው። - መጋበዝ ግን ይጋብዘዋል..... እና ሁለቱ ብቻ ዝም ብለው ይኘደኻዳሉ። - አባ ጆቢጥና አዲላላ ተጋበዙ ይሉናል በማለት ቢጠባበቁ ከአቶ አባት ትንፍሽ ይጠፋል፤ ይናደዳሉ። - እንግዲያው ለምናልባቱ ቢሆን ተገን ይዘው ይጠባበቃሉ። የኋላ ኋላ አዲላላ አላስችል ይለውና ከአባ ጆቢጥ ተለይቶ ስጡኝ ብሎ አፍ አውጥቶ ስለሚጠይቅ አንድ ጆሮ ይወረውሩታል....... አባ ጆቢጥን ግን ከልክለውት ዓይኑን እያቁለጨለጨ ሲመለከት ቆይቶ ሁናቲያቸው አላምር ይለውና መሸሻ ወደሚያመችበት ሥፍራ ጥቂት እንሳነከሰ አምቡልጋ አባቱን እንዲህ ይለዋል......

«የጨረቃ ንጋት

የቦረቦር ልማት! ስለማይታወቅ እንሂድ!» አባት ግን የተመለከተው ሆዱን ብቻ ነበርና......

«የጨረቃ ንጋት

ያህያ ስባት

ዝም በልህ ብቻ አንከት!» ብሎ ንግግሩን እንደ ቀላል ይወስድበታል። ወዲያው ይህን ተባብለው እርም ታህል ጊዜ ሳይቆዩ የአህያይቱ ባለቤት ድሞትፈሩን አንግቶ ከተፍ ይልባቸዋል። ሆዱ ከሞላ መቼ ሆዱ የጐደለ በኀይል ይሮጣልና አባ ጆቢጥ እግሬ አውጪኝ ሲል፥ አባት መጣራት ይጀምራል......

«ልጄ አባ ጆቢጥ፥

ልጄ አባ አባ ጆቢጥ.......!

«ብቻህን እንደ በላህ ብቻህን ሩጥ!» ይደርሰዋል መልሱ። -

«ልጄ አዲላላ

ልጄ አዲላላ......!» እንደገና ይጣራል።

«ምን አቅምሰኸኛል ካንድ ጆሮ ሌላ.......!» ይደርሰዋል መልሱ። - በመጨረሻም የተማመነበት ልጅ ሲሸሽ በማየቱ

«ልጄ አምቡልጋ......!

ልጄ አምቡልጋ.......!» እያለ ቢጣራ

«ምነው እንሂድ ብየህ ሳይነጋ.......!» ብሎት እብስ ማለት ነዋ። - ምን ልበላችሁ እንግዲህ ከዚያ ወደዚያማ....... አቶ አባት....... ማንከሱም ባይቀር ለማምለጥ........ ብቻውን እንደ በላ ብቻውን ቀራ!!

«አሀ......! ይልና እጅዋን ዘሎ ይይዘዋል አደፍርስ፣ ወዲያውም ቶሎ ይለቃትና «ይቅርታ!» ይላታል ድንግጥ ብሎ።

«እንደዚህ እንዴት ተሰማህ.....?» ትለዋለች ጺወኔ ቀስ ብላ - ዓይኖቿ እንደ ማጉረጥ ይሉና

«አ...... አ! እንዴት ተሰማኝ.......?» ይጀምራል አደፍርስ ሰብሰብ ብሎ «ምንም አልተሰማኝ! ምን ተሰማኝ? ይቅርታ፥ እጅሽን ስለ ያዝኩሽ እንደሁ...... ይቅርታ.......! አንዳንዴ እንዲሁ....... እንዲህ ያረገኛል.....

## ፴፪

## አደፍርስ

«እሺ፣ የኔን ተረት ደግሞ ለመስማት ይፈልጋሉ?» ይጠይቀዋል ጐርፉ፥ በአደፍርስ ሁኔታ ይገፋፋና። -

«ያስጠምድህ ባሥራስምንት አይደለም........? ያስጠምድህ ባሥራስምንት.......! ሙሴው አይደለም እንዲህ የሚለው.......? ሙሴ፥ የማኅበሩ አላፊ......» ያከታትላል አደፍርስ ያሳብ ድግግሙን......

«መቼስ ቅድም እርስዎም...... ቅድም ጠቅሰውታል..... ደጋግሞ ከተያዩ መለማመድ አይቀርም.....» ይጀምራል ጐርፉ «እና በጥንት ዘመን...... አንድ አንበሳና አሥራ ሦስት ናቸው አሥራራት ጅቦች ወደ አደን ሄዱ ይባላል..... እንግዲህ አብሮነታቸው ቅድም ስለ ድመትና ውሻ እንዳስረዱን ዓይነት ነው ማለት ነው..... እና ሲያድኑ ሲያድኑ ሲያድኑ ይውሉና አሥራታቸውም፥ አሥራራት ፍሪዳ አገኙ ይባላል...... ያጋጣሚ ነገር...... ካጋጠመ.. ብዙም ይገኛል መቼም፤ ከዚህ የበለጠ ማለቴ ነው.... እኔ እንኳን ወደ አዳሉ አገር ወርጄ ብዙ ጊዜ ብዙ ብዙ ከብቶች..... ምን ያረጋል ብቻ፥ ለነገሩ ያህል ማለቴ ነው...... አሥራራቱም አሥራራት ፍሪዳ አገኙ። - ጓደኝነት አብሮ የለፉበትን አብሮ ለመብላት ነውና በስምምነት አድርገው ያችኑ አንዳንዳቸውን ተካፈሉ። - በዚህን መካከል..... መቼም ፈሪ አይጸድቅምና...... ከነዚያ ሁሉ ጅቦች አንደአኝው ብድግ ብሎ - እንዴት እንዲህ ይሆናል! አቶ አንበሳ እንዴት አንድ ፍሪካ ይበቃቸዋል? አይበቃቸውም ብሎ ለፈፋ......! ማነው ይበቃቸዋል ባዩ ያኔ?! ያን ያቶ አንበሳን እንደ እሳት የሚንተገተግ ዓይን...... ያን ስንቱን ስንቱን ሊያደባይ የሚችል ያንበሳ ክርን እየተመለከተ። - አሥራሦስቱን ፍሪዳዎች ላቶ አንበሳ፥ አንዲቱን ለአሥራሦስታቸው ተካፈሉና እየምላዳቸው ተመለሷ። - ግን የወሬን ነገር ምን አለ አሉት...... የእንጀራ አባታቸው የሆነ ሌላ ጅብ ሌላ ቦታ ውሎ ኖሮ ሲመለስ ያገኛቸዋል። - የዋሉበትንም ይጠይቃቸዋል። - አሥራሦስታችንና አንድ አንበሳ ሆነን አደን ሄደን ዋልን....... ላሥራራታችን አሥራራት ፍሪዳ አገኘን....... ይኸው ግን እንደምታየው አሥራሦስቱን ላቶ አንበሳ ለቀን አንዷን ብቻ ነድተን መምጣታችን ነው

ይሉታል....... አቶ የእንጀራ አባት ይናደዳል....... ይበሳጫል...... እንዴት እንዴት ያለ ለጆሮ የሚቀፍ ነገር ብሎ ይንጐራደዳል....... ላንድ አሥራሦስት ላሥራሦስት አንድ እንዴት ያለ መካፈል ነው በማለት ይጦፋል...... ምኑ ቅጡ!! ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም አይደለም የሚባለው...... አንዷን መልሰን አሥራሦስቱን እናመጣለን አላቸው! አሥራሦስተቱ ጅቦች የሰጡትን እሱ አንዱ ጅብ ሊያስመልስ......! ልብ ካለ ምናለ መቼም.......! ወደ አቶ አንበሳ ቤት እየፎከረ ሄዳ! እየፎከረ! እየተድረቀረቀ.......! መድረስ አይቀርም መቼም ደረሰ! አቶ አንበሳም ቤት....... እውነትም ታዲያ እጅ ነሥቶ እንደ ቀረበ ያቶ አንበሳን ፊት ቢመለከተው....... እንኳንስ አንዲቱን ተቀብሎ አሥራሦስቱን ሊመልስ አንዷም ስለጐደለችበት ለካስ በሆዱ ተጠጥቶ ኖሮ........ እሳት ለብሶ እሳት ጐርሶ..... ጐምለል ምለል እያለ....... ከወዲያ ወዲህ ሲጐደራ ጠበቀዋ......! ጠበቀው። እህ! የመጣንበትን ጉዳይ ንገረና! አይለውም - ባሽሙር ዓይነት አነጋገር..... አቶ ወንድ ታዲያ ምን አለ ይመስልሻል......?» ወደ ጺወኔ ዘወር ብሎ «.......ዋ ጌታዬ ያችን ያሥራሦስት ድርሻ ትሁን ብለው የመረቁልንን ፍሪዳ - አሥራራተኛ አድርገው እንዲቀበሉኝ ነው በልጆቼ ስም ሆኜ የምማጠነዎት ሆና........! ምን ከዚያማ ጐምላላው አንበሳ! ከብህ ቀንሶ ከሞኘ ጨርሶ የሚኖር ብልጥ....... እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብሎ መቀበል ነዋ! ተቀበለው ሳቅ ሳቅ እያለ........ ተቀበለው......! ተቀበለው.....

«.......እኔ እምልህ እንዲህ ጨዋታ ስታውቅ...... እህ! እህ! እያልህ አጉል አጉል አስተያየት ነበር ያደረብኝ.......» ይለዋል አደፍርስ ጐርፉን በርግጥ በደስታና ባድናቆት በሚያበሩ ዓይኖቹ እየተመለከተው

«........እኔ እልምህን እንዲህ ጨዋታ ስታውቅ..... ህእ! ህእ! እያልህ አጉል አጉል አስተያየት ነበር ያደረብኝ......» ይለዋል አደፍርስ ጐርፉን በርግጥ በደስታና ባድናቆት በሚያበሩ ዓይኖቹ እየተመለከተው «........እምህል እስኪ ደግሞ....... ስለሌላ ነገር..... ባገር ቤት ስለሚገኙት አዝርእት....... እንስሳት........ እምልህ...... የምታውቀውን ያህል......

«አይ...... ምን ያህል ብለው...... ስለ እንስሳት ብዙ አላውቅም....... አዎ አሉ የማውቃቸው...... እምልዎ...... እርሻው...... እየጠረጋው...... እየደኑ የጋጠሙኝ...... ለምሳሌ ጠቃሚ የምንላቸው እንስሳት፥ አሉ አጥፊ የምንላቸው እንስሳት አሉ፤ መርዘኛ የምንላቸው እንስሳት አሉ፤ ዋጋ የለሾች የምንላቸው እንስሳት አሉ፤ በጣም በጣም አሰልችዎች የምንላቸውም እንስሳት አሉ። - ዶሮ፥ ቆቅ ጅግራ፥ ሶረኔ በግ ዓይነቶቹ ጠቃሚዎች ናቸው። ቀበሮ፥ ተኩላ ወማይ ነጐዴ ጐሴ፥ ግልገል አንሣ አጥፊ የምንላቸው ናቸው። - እባብ ዘንዶ፥ ጊንጥ መርዘኛ ከምንላቸው ውስጥ ናቸው። - እንደ እንቁራሪት ገበሎ ቢራቢሮ እንሽላሊት ዋጋ የለሾች ናቸው። - ቅማል ቁንጫ

ትኋን በረሮ አይጥ ዝምብ፥ አይጠ መጐጥ የመሳሰሉት ደሞ አሰልችዎች ከምንላቸው ውስጥ ናቸው። - ብቻ ምን አለፋዎ ዱሮ ተማሪ ቤት አሉ የሚሉንና እኔ ያገኘኋቸው የተለያዩ ናቸው......

«አ! ተማሪ ቤት ገብተህ ኖሯል......?

«አዎ ገብቼ ነበር...... ከጺወኔ ጋር ነበር አብረን የገባነው.....

«እንዴት ዓይነቶች ነበሩ ተማሪ ቤት ሆናችሁ አሉ የሚሏችሁ........?

«ምኑ ቅጡ፥ ብዙ ነበሩ...... መጀመሪያ በመሬት ላይ ያሉትን ፍጥረቶች በሦስት ይከፍሏቸዋል - ሰው እንስሳት አዝርእት ብለው...... ምኑ ቅጡ ብቻ..... ባንድ አፋቸው ሰውን አንዴ እንስሳ ነው አንዴ ነፍስ ያለው ፍጡር ነው ይሉናል..... እንስሳቱን ደሞ አከርካሬ ያላቸውንና አከርካሬ የሌላቸውን ይለያሉ.......

«ታዲያ የተማሪ ቤቱ አከፋፈል የሚሻል አይመስልህም........?

«የሚሻል? ለምኑ ነው የሚሻለው ጌታዬ? አንዱ እንስሳ አከርካሬ ያለው ሌላው አከርካሬ የሌለው መሆኑን ዐወቅሁትና የት ላይ ነው ጥቅሙ...... ከብዙ ለማምረት ነው የሚጥቅመኝ? ወይስ ደምጎ አስተካክዬ ለመተኮስ.......?

«ለመሆኑ አሁን የተማረ ሰው ስታይ...... ምነው ተምሬ ቢሆን ኖሮ አትልም ማለት ነው? ለምሳሌ እኔን ስታይ......?

«መቼም ያንጀት አይደለም ጨዋታ.......? አልልም! ምነው ተምሬ ቢሆን አልልም......! እኔ የተማረ ሰው አያስቀናኝም...... ያሳነኛል እንዲያውም.....

«ድንቁርናና ዕውቀት! ያሳዝነኛ...... ያሳዝነኛል?! የሚታዘንለት የትኛው ሆነና.......?

«አልያዙልኝም መሰለኝ አማርኛዬን...... እንዴት ማለት መቼም ደግ ነው ለጨዋታ.......

«እሺ እንዴት ነው የማሳዝንህ.........?

«እርስዎን አላልኩም ጌታዬ! የተማረ ሰው ቢሉኝ ነው......» ይልና ሊናገር የጀመረውን ቁርጥ አድርጐ ይቆማል። -

«እኮ ታዲያ የተማረ ሰው የሚያሳዝነው እንዴት ነው......?

«አይ ምን ያረጋል...... የባላገር ነገር...... ወይ ሳላውቅ አስቀይምዎት ይሆናል...... የከተማ ሰውና የኛ የነገር አካሄድ አይገናኝ......

«ግዴለም...... ግዴለም...... ምንም የሚያቀያይም ነገር የለ እዚህ......

«እና ታዲያ ለምን እንደሚያሳዝኑኝ ሊያውቁ ነው የሚፈልጉት.......?

«አዎ ለምን ያሳዝኑሃል.......?

«አሁን እርስዎ ከዚህ እራሳ በባዶ እግርዎ ይወርዳሉ......? መቼምም አያድርስብዎትና በዚህ በልስልስ እጅዎ ዶማ ጨብጠው ሞፈር ቀንበር አቀናጅተው አርሰው ሊኖሩ ይችላሉ? እምልዎ ንጉሡ የእናንተ ሥራ በቃኝ፤ አያስፈልገኝም...... እንደገበሬው እንደ ነጋዴው እንደ ወታደሩ እየሠራችሁ ኑሮ - የቢሮ ሥራ አልጠቀመኝም..... ሂዱ ውጡ ከተራው ሰው ተደባለቁ ቢሉዎ ምን ይውጥዎታል? ሌላው ቀርቶ በረሮውንና ትኋኑን ብቻ የትኛው ሰውነትዎ ነው የሚችለው? እሾሁን እንቅፋቱን ሙያሌውን የትኛው እግርዎ እንው የሚቋቋመው.......? አንዴ.......! እኔስ ካንጀቴ ነው ያሳዝኑኛል ያልኩት......

«አይ እንዲያ ከሆነ ቀላል ነው፤ ለጉዞም በቅሎ..... መንገድ ካለም መኪና...... ካስፈለገም አይሮፕላን አለ። - ለእርሻውም የእርሻ መኪና እናመጣበታለን....... ተውሳኮቹንም በ ‹ዲዲቲ› ድራሻቸውን እናጠፋዋለን። - ለሙያሌውና ለምናምንኑም መጫሚያ እናደርጋለን...... ይኸን ይኸን ቀላሉን ነገር.......?

«ጌታዬ መቼም ይኸ ይኸ....... ለኛ የዳመና ሕልም ነው፤ እኛ አገር ሌላው ቀርቶ በቅሎም የሚኖረው የደላው ነው...... የርሻ መኪና...... የርሻ መኪና ላሉት በውነቱ ይኸን ሜዳ የማይታይበት፥ አባጣ ጐርባጣ የኛን አገር መሬት የሚያርስ መኪና ካለ ጥሩ ነው፤ ግን ሳስበው በድንቁርና ልቦናዬም ቢሆን የሚኖር አይመስለኝም..... ስለ ‹ዲዲቲ› ው እኛም ባቅማችን እየገዛን መሞከራችን አልቀረም፤ እየጠጡ ቁጭ ሆነዩ......

«ምን? ምን እየጠጡ ነው ቁጩ......?

«አዎ ጌታዬ...... የኛን አገር ተውሳኮች የፈረንጅ መዳኒት አይደፍራቸውም..... ‹ዲዲቲ› ውን ይለምዱትና ውጠው ውጠው ሲፈረክሱ ጠንቃቸው ለኛው ነው የተረፈው። - ከርፋታቸው ከጉድጓድ አይጥ የሚያስወጣ እየሆነ፤ አይስማማቸውም። - እኛም ታዲያ ምን እናርግ መቼስ አልወደድነውም። - ከሁል አሁን የኛ የቆላ አይጦች....... እንዲህ መርዝ የሆነ ነገር በምግብ ስናቀርብላቸው ግፋ ቢል አንዷ ቀምሳ ብትሞት ነው..... ሌሎቹ ንክች - ሲያልፍም አይነካቸው። - ገና በሽታው ነው.... ከሩቁ

የሚሸሹት። - ምን አለፉዎ ብቻ እንኳን ተውሳኮቹን እኛንም አይደፍረን የፈረንጅ መዳኒት....

«አይመስለኝም! አሰጣጡን ሳታውቁበት እየቀራችሁ ይሆናል.....

«ምነው የሚያቁበትስ መቼ ሆነላቸው? በቀደም አንድ የኛ መንደር ልጅ ታመመችና ሮቢ ወስድናት! ላኪሙ ሦስት ቀና ነው እንቅልፍ ባይኗ ሳይዞር አልነው...... የእንቅልፍ ኪኒን ብሎ ሁለትም እንደሁ አዘዘላት - ዋጠችና ዓይኖቿን ቁልጭ ቁልጭ ሆነ......! በጣም ገረመውና እንደ ገና አንድ እንዲጨመርላት አዘዘ..... በጣም ኃይለኛ ኪኒን ነው እያለ! ዋጠችና ምንም......! እንደ ገና ጨመረላት...... ንክች! አይ ከዚህ በላይ አደገኛ ነው አለና ተዋታ እንደብጤቷ.......!

«እርግጥ ነው የምትለው መቼም እውነት አያጣም...... እናንተ የባላገር ሰዎች ብዙ የሰውነት ጥንካሬ አላችሁ...... መድኂት በቀላሉ አይደፍራችሁም......

«ለራስ ምታቱ ኪኒን ለጭረቱ ፋሻ፥ ለሆድ እመሙ ስንት ዓይነት ቅርንጥ..... መጥኔውን መጥኔውን ይስጣችሁ ብቻ እናንተ የተማራችሁ ሰዎች...... እናንተ ያላሳዘናችሁ ማን ያሳዝን? ተምሬ ቢሆን ኖሮ አትልሞይ የተማረ ስታይ አሉኝ? ይገርማል! ሌላው ቀርቶ በተኩ ቀርቶ በተኩስ እንኳ ቢሆን የተማሩትን አይተናቸዋል...... ተኳሽ ቆለኛ! አንድ ጥይት በከንቱ ጠብ የማትልበት..... የምን ትምርት ደሞ....... አሁን ሰሞኑን፥ እዚህ መንደር አንድ ሰው መጥቶ ዝም ብሎ ጥይቱን ያዘራል ሲሉ ሰማሁ በቀደም ሚካኤል ወጥቼ! እግዜር ያሳይዎ እንግዲህ....... ቆቅ ለመግደል ነው አሉ ያ ሁሉ ጥይት ማባከን......

«አደፍርስ ሰውነቱ ቅጭም ይላል። - ጺወኔ እነሱን እያየች ታዳምጥ ነበርና ስለ ተኩስ ማውራት ሲጀምሩ ቀስ ብላ ብድግ ትልና ወደ ውጪ ትወጣለች።

«ታዲያ አምተማ እኔ እንተኩስ እንዴ......?!» ይጠይቀዋል አደፍርስ ጐርፉን - የጺወኔን ሹልክ ብሎ መውጣት ያጤንና -

«ምን ከፋኝ ጥይት ካለዎት..... እኛ አገር ጥይት ውድ ነው......

«ጥሩ ነው እንግዲያው፤ ጠመንጃም ጥይትም አለኝ........! ፍሎቤሩን ከተሰቀለበት ከወደ ጓዳ ያመጣና ከግቢው ውጪ ይወጣሉ። - አንድ የቅል ዒላማ ባሻገራቸው ይተክሉና ሁለት ሁለት ጥይት ይዘው ይተኩሳሉ - መጀመሪያ የተኮሰው ጐርፉ ነበርና፥ በሁለቱም ጥይት ይስታል...... አደፍርስ ለጥቆ ሲተኩስ በሁለተኛዋ ጥይት ትንሽ ጨረፍ ያደርጋታል - ቅሏን.......

«ታዲያ ተኩስ አንችልም እንዴ......?!

«ይቺ የርስዎ ብረት ለትከሻ ትቀላለች...... አሻንጉሊት ዓይነት ነገር......» ግምባሩን አንገቱን ያልበዋል «...... እኔ መቼም ስለ ተኩስ ጉዳይ....... አይ፥ ምን ዋጋ አለው ብቻ..... አገር ይበል.......

«ባንተ ብረት እንወዳደራ! በዚህኛው ካላመንህ......? እኔ ግድም የለኝም......

«በኔ ብረት እንወዳደር.......? ጥሩ ነው፥ እስማማለሁ...... አንድ ጥይት ለርስዎ እሰጥዎታለሁ፤ አንድ ጥይት ራሴ እተኩሳለሁ......» ብረትና ዝናሩን ያስመጣና ዝናሩን ጠጋ አድርጎ «በሉ ያውልዎ አንድ ጥይት ይምዘዙ» ይለዋል። - አደፍርስ ሲመዝ ቀለህ ብቻ ይሆናል...... ጉርፉ እርፍ ይላል፤ ባዶ ቀለህ ለዝናር መሙሊያ ማስገባቱን በመርሳቱ «.....ለዝናር መሙሊያ የተደረገ ነው..... ግዴለም...... ይምዘዙ፥ ሌላ ያገኛሉ!» ይለዋል። - አደፍርስ  ይመዛል። - አሁንም ግን የመዘዘው ባዶ ቀለህ ይሆናል « - ወየ ጉድ! የሱ መገኘት! የርስዎ ደግሞ እየደጋገሙ እሱኑ መምዘዝ.......!» ሦስተኛ ጊዜ ሲመዝ ደንበኛ ጥይት ያወጣል - ይተኩሳል፤ ነገር ግን ይስታል። - ጉርፉ በተራው መዞ ሲተኩስ ይመታል። -

«እኩል በኩል ሆንን ማለት ነው!» ይለዋል አደፍርስ «እንደ ገና ለመተኮስ ትፈልጋለህ....?

«የለም ጌታዬ በዚህ ባጉል ነገር ጥይት አላባክንም......

«በኔ ጥይት እንወዳደር እንግዲያው.....

«የርስዎ ብረትኮ እሺ ብላ አትገባም አልኩዎ..... እንጃ ብቻ ከወደ አናቷ ገደማ ጠመም ያለች መሰለኝ..... ተሳስቼ ሊሆን ይችላል......

«ደግ እንግዲያው ካልመሰለህ ይቅር...... ብቻ ቢሆንም የተማረ ሰው እስከዚህ እጅ እግሩ የታሠረ አይምሰልህ......

## ፴፫

## አደፍርስ

እልፍኙ ገብተው አረፍ አረፍ እንዳሉ «እኔኮ እምልዎ...... በኮፍ ጫማም ተሄደ፥ በግምብ ቤትም በፎቅም ተኖረ..... ጻዳ ጻዳ ልብስም ተለበሰ...... የተማረ ሰው ምን የፈጠረው ነገር አለ እስከዚህ......?» ይጀምራል ጉርፍ ቀስ ይልና «...... እኛም

መቼም ያዳል ጫማም ቢሆን እናደርጋለን...... ልብስም እንለብሳለን....... እንዳገራችን፥ አንገታችንንም እምናስገባበት እንደ ነገሩም የተውተፈተፈ ጐጆ ቢሆን አለን። - ጤንነት ኖሮን ሥርተን ከገባን ልጆች፥ ወልደን አድገውልን በእርሻውም በእረኝነቱም ሲያግዙን ካየን..... ከዚህ የበለጠ ምኞት ከዚህ የበለጠ ደስታ ምን ይኑረን.......?

«ያላዩት አገር አይናፍቅም ሆኖ ነው ነገሩ........

«እንዴ! ያላዩት አገር ለምን ይናፍቅ.......?

«ስማ አጭር ምሳሌ....... አሁን አንተ የኔን ልብስ ለመልበስ አትፈልግም.......?

«ውይ በስማብ ወልዴ! እርስዎም ስለለበሱት ገርሞኛል፤ ሙቀቱን መቻልዎ! እውነቱን ልንገርዎ እኔ ከሆነልኝ ከቁምጣዬ በቀር ራቁቴን መሆን ነው የምፈልገው......

«ለምን ከቁምጣህ በቀር........?

«አይ እሱማ መቼም፥ አፍረቴን መከለል አለብኝ........!

«ለመሆኑ ልብስ ለጌጥ ይሆናል ሲሉ ሰምተህም አታውቅ?

«እሰማለሁ፤ ግን አይታየኝም! ሴት ልጅ፥ ይሁን ታጊጥ፥ መቼስ ምን ይደረጋል...... የወንድን ጌጠኛ መሆን ግን አላውቅም። - የወንድ ጌጡ ሥርቶ ማብላቱ ብቻ ነው....

«አሳረፍከኝ አሳረፍከኝ! እንግዲህ እትራሴ እሰቅልና ቀና ባልኩ ቁጥር እሳለመዋለሁ.......» እያሉ ይገባሉ ወይዘሮ አሰጋሽ። - ከአቶ ወልዱና ከአቶ ክብረት ጋር ሆነው መመለሳቸው ነው፤ የጉርጓዱን ማሽላ ደኅናውን ከደምበሸው ካስለዩ በኋላ። - ክብረት ከሁኔታው አንድ ንጥረ ሐሳብ ስላገኘ ‹ደንበሾው› በሚል ርእስ ሥዕል ለመሣል አንዳንድ ንድፍ አውጥቷል። - እዚያው ሆኖ ግን ስለዚሁ ሐሳብ ሲያስላስል የሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ወለል ብሎ ከሚታይበት አቅጣጫው ስላገኘው በእርሳስ ብቻ ጥሩ አድርጐ ነድፎ ለወይዘሮ አሰጋሽ ይሰጣቸዋል። - ይኸን ስጦታ እየተመለከቱ ነው እንግዲህ የገቡት - ልባቸውም ቢጠራጠር፥ አንተ የሣልከውን ሥዕል አልሻም ሊሉት አልፈለጉም። - ሲገቡ ጉርፉና አደፍርስ ብድግ ብድግ ይላሉ «.......መቼ መጣህ ጉርፉ» ይሉና «ና ሳመኝ እንጂ ታዲያ......!» እጃቸውን ዘርጋ ያደርጋሉ....... ጉርፉ ለጥ ብሎ መጫሚያቸውን ይስማል «.......ምነው ወደኛ ብትመጣ ኖሮ! እኔ ደሞኮ እንዲያው ከልቤ አልለየሁህም..... ያቺ ደሞ የኔ ጂወኔ የት ሄዳለች...... መጣ እንኳን ብላ እስኪ ብትነግረኝ..... ለሌላ ነገር ቢሆን መቼም ይሄኔ ትሮጥ ነበር......

«ከሳቸው ካቶ አደፍርስ ጋር ጨዋታ ይዤ ነው..... ከጄል አርጐኝ ነበር ለመምጣት እንኳን......

«ስለዚህ ስለ መሳም ነገር - እንዴት አንድ ማሻሻያ ሳይገኝለት ቀረ......?» ይላል አደፍርስ እንደ ቆመ። - ወይዘሮ አሰጋሽ የተለመደውን ‹በአበው በጻድቃን ተቀመጥ›ን እንኳን አላሉትትም፤ እሱም ያጤነው አይመስልም።

«ስለ የቱ ወዳጄ.......?» ይሉታል ወይዘሮ አሰጋሽ፤ ምን ነገር ሊያመጣ ነው ብሎ በፈራ አንደበት።

«ይኸ እግር መሳም ጉንጭ መሳም ድንጋይ መሳም መስቀል መሳም........ ወረቀት መሳም..... እጅ መሳም......

«ምን ወጣው ታዲያ.......? ባህላችን ነው መቼም። ልማድን ልተውህ ቢሉት ይተዋል...... እኔ አሁን አንድ ነገር ልንገርህ፥ እቤት ውስጥ ስላለው ሥራት...... ይቺ የኔ አገልጋይ አለች እግሬን የምታጥበኝ፥....... ታዲያ...... ማታ ማታ እግሬን አጥባ ስታበቃ አንደኛውን ካልሳመች ጭራሽ..... ጭራሽ ነው የምልህኮ.......! ጭራሽ የታጠብኩ አይመስለኝም....... እሷስ የታባቷ ልትገባ...... ሌላ ደሞ ልንገርህ - አሁን ይኸ የኔ ልጅ ጐርፉ አለ...... ለሁለት ወይም ለሦት ቀን እንኳን ሳላየው ቀርቼ የመጣ እንደሆን ከልሳመኝ፥ ትልቅ ትልቅ ነገር የቀረብኝ ነው የሚመስለኝ..... ድንጋይ ስላልከው ግን...... ድንጋይ....... አልስምም.... ሌላም ሰው ሲስም አላየሁም..... ይኸን መሳለሚያውን ማለትህ ይሆን........? አድባሩን.....

«ምነው የቤተክሲያኑን ደፍ - የቤተክሲያኑን ግድግዳ - የቤተክሲያኑን ደረጃ.....

«ተው ተው ተው ተው! ጥሩ አይደለም ወዳጄ! ጥሩ አይደለም....... ስለ ቤተስኪያን መሳም አጉል አትናገር..... ምን እናገር ትላለህ......? እዝጌርን ራሱን አግኝተን አንስመው? ምን እናርግ ትላለህ.......? ግን ግን ድንጋይ አይደለም የምንስመው..... እኔ እንዲአይው አሁን እስከትናገረው ድረስ የምስመው ድንጋይ መስሎ ታይቶኝም አያውቅ....... በጭራሽ.......! ምን አጉል ነገር የሰማኸኝ ወንድሜ! አጉል ነገር......

«ምን መስሎ ኖሯል የሚታይዎት.........?

«የሚታየኝኝ! የሚታየኝ.......! የዝጊያብሔር ቤት ምኑ ይመረመራል? ምን ሊታየኝ ይችላል.......?

«እምልዎት ያም ያም ያም፥ ሲስመው በሽታ ሊይዝዎት ይችላል....... ስንት ዓይነት ነገር ይመስልዎታል በዚህ መንገድ ሊተላለፍ የሚችለው......

«ተላልፎም አያውቅ! የዝጊያብሔርን ቤት በሽታ አይደፍረውም...... አጉል ነገር አሰማኸኝ ግን...... እሱው ይሁነኝ...... እንጃልኝ እንግዲህ እንደ በፊቴ መሆኔን..... አጉል ነገር ያንተ ንግግር....... ቤተስኪያን በሄድሁ ቁጥር ነው ትዝ የሚለኝ...... ማስረሻ ዘዴ ቢገኝለት ለነፍስ አባቴ አጫውታቸዋለሁ...... ሆድ ግን መቼ በጇ ይላል...... አንዴ አጉል ነገር ከያዘ በኋላ....... ባይቀበለውም ማስታወሱ አይቀርም......

«የሰው እግርማ የስንቱ ዓይነት ‹ሚክሮብ› መጠራቀሚያ ነው...... በውነቱ ከሆነ ሌላው ቢቀር እርስዎ በሚያዙበት ቦታ ሁሉ እንዲህ ያለውን ነገር ማስቀረት አለብዎ..... ቢያንስ ቢያንስ በቅርብ የሚያስተዳድሯቸው ሰዎች እንዳያደርጉት.....

«መቼ በጇ ይላሉ ሰው፥ እግሬን እንዳይስም ብከለክለው..... ምን አድርጊያት ነው ብሎ ነው ያማላጁን መዐት የሚያዥጐደጉደው...... ደግሞም ማንንም እግሬን እንዲስም የምፈልግ አይምሰልህ...... አዎ...... እመርጥበታለሁ! በጣም የቅርቤ የምለውን ነው የምፈቅድለት......

«እኮ ቢያስቀሩት......

«ነገርኩህኮ! ይቅር ብሎ በመናገር ብቻ የሚቀር አይደለም ነው የምልህ...... እንደ እህል እንደ ውሃ አስፈላጊ ነው። - ያለ እሱ ለመኖር አይችልም ሕዝቡ...... እውን ጐርፉ፥ አሁን አንተ ጫማዬን አትሳም ብልህ.....

«አይ፥ እርስዎም አይሉኝ.....

«ይኸውልህ እንግዲህ፥ እስከዚህ ድረስ ነው.....

«አሁን አንተ ጫማ መሳም እፈልጋለሁ ማለትህ ነው.......?

«ለምን አልፈልግም? ማን አስገደደኝ ታዲያ.......?

«አትስመኝሞይ አሉህ! ከዚህ የበለጠ.....

«አይዶለም አይዶለም..... ከትናንት ወዲያ እዚሁ ስለነበርሁ......

«አዎ ከትናንት ወዲያ መጥቶ ነበር...... ምናልባት እንደኔ ጊዜው አልረዘመበት ይሆናል.....

«ይልቅ አሁን ስለ ነገው ጉዞሽ ብንነጋገር...... ይኸ አጉል ትርኪ ምርኪ ለማናኛችሁም አይበጅ...... እኔ እምለው አንቺ ከሄድሽ እኛስ ባለቤት አሌለበት ቤት ምን እንሠራለን...... እኔም እሁድ ስብሰባ አለብኝ..... ስለዚህ ስለ ትምህርት ቤት ማሠሪያ መዋጮ...... እና ብዙ ጉዳይ ብተኩስም፥ ያለወትሮዬ ሰነበትሁ......» ጣልቃ ይገባሉ አቶ ወልዱ። -

«አይ እኔማ ከነጺወኔ ጋር ለመሄድ ተስፋ ሰጥቻለሁ.......» ይላል አደፍርስ ይለጥቅና

«ተስፋ! ተስፋ! ተስፋ ሰጥቻለሁ? ከነጺወኔ.......!» ይገረማሉ ወይዘሮ አሰጋሽ «.....እነ ጺወኔ ደሞ እነማናቸው? የኔን ልጅ ማለትህ እንዳይሆን.......

«ኋላ ስንት ጺወኔ አለና.....

«ታዲያ እሷ ከኛ ጋር የምትሄድ መስሎኝ ነበር...... እየፈጩ ጥሬ የሚሉት ነገር ሆነ እንዴ.......? የተስፋው ጋጋታ.......?!

«ምናለ እኔስ አብሬ ብሄድ......

«አይደለም፤ ነገሩን የደረስክበት አይመስለኝም...... እኛ ለዓለም ለደስታ አይደለም የምንሄደው ጠበል ለመጠመቅ ነው....... ዘመድ አዝማድ የምንለው ባቅራቢያ አይኖርም....... ለአንድ ሁለት ቀን ብንቸገርም በማለት.....

«አይ መቼምኮ እሳቸው አብረዋት ሊሄዱ ከፈለጉ በርከት ብለን ማረፊያ እንዳናጣ እኔ ልቀር እችላለሁ.......» ይላል ጐርፉ።

«ዕውር ያለ በትሩ የት መንገድ ይወጣል...... ያንተ መቅረት ዘበት ነው...... ደግሞስ እስከዚህ መቼ አደከምህ ነበር..... እንዲህ በቀላሉ የምትተካ መሆንህን ባውቅ......

«......እና ታዲያ እኛም ዕቃችንን በቅጥ በቅጥ አድርገን በጧት ብንነሣ......» ጣልቃ ይገባሉ አሁንም አቶ ወልዱ። -

«ለመሆኑ የኛን መሄድ ወሬ ከእንዴት ያለች ወፍ ሰማኸው.......? ባለተስፋዋ ማለቴ ማነች.......?

«ከየት እሰማዋለሁ እናንተው ስትነጋገሩ......

«እኔ ነኝ የነገርሁት...... ማረፊያ የማይኖር አልመሰለኝም ነበር......» ትመለሳለች ጺወኔ ቶሎ ብላ። -

«የኔው ነሽ ለካ? እኔስ ምን መንገድ አገኝ ብዬ......

«.....እንግዲያው እኔም መሄድ አልፈልግም ማረፊያው ችግር የሚፈጥር ከሆነ..... ጤነኛ ነኝ ደግሞ በዚያ ላይ.......ፍል ውሃ ምን ይሠራልኛል?» ትቀጥላለች ጺወኔ። -

«.......ነገ ጧት ወደ ደብረ ሲና! ሌላ ጭቅጭቅ የለም እንግዲህ!» በቆረጠ ቃል ይናገርል አደፍርስ። -

«ልጅ ነሽ አንቺ! ስለ ጤንነትሽ የምታውቂው ነገር የለም......» ይገሥጿታል አሰጋሽ ጺወኔን። -

«እዚህ አገር ፍልውሃ ኖሯል ለካ? ከሆነ ከሆነ በውነቱ ማየቱ አይከፋም ነበር...... ብቻ ከሰው ጋር ሆነን ከደብረ ሲና መጥተን ልናየው እንችላለን...... ከመሄዳችን በፊት.......» ይናገራል ክብረት። -

«ቀስ በለን ልንመጣ እንችላለን...... ከኔ ጋር.......» አቶ ወልዱ ቃል ይገባሉ።

«ጥሩ ነው እንደ ብጤታችሁ....... አሁን ስለ ጉዟችን.......» ይሉና ወደ ጉርፉ ዘወር ይላሉ፥ ወይዘሮ አሰጋሽ - አደፍርስ ከእልፍኝ ይወጣል...... አቶ ወልዱ ይለጥቃሉ....... ክብረት ይከተላል..... ጺወኔም ብድግ ስትል «ምነው አርፎ አላስቀምጥ አለሽ? የያዘሽ አባዜ......! ይኸ አኮሪዶ ነው መሰለኝ እንዲህ ያናግር የነዛብሽ.......» ቶሎ ብላ ተመልሳ ቁጭ ትላለች «እሺ ልጄ፥ ምን ምን ብንይዝ የሚሻል ይመስልሃል ታዲያ......? እንደ አገልግልም...... እንደ ድርቆሽም......

## ፴፬

## አደፍርስ

«እንዴት እንዴት፥ በቀላል ነገር የምትተካ መሰለሆይ ይሉታል ጉርፉን ያህል ሳልሆን ቀርቼ ማለት......? የሳቸውን እግር ሳልስም ቀረሁና.....

«የለም የለም አንተን ማለቷ አይደለም...... ቦታውን እንደ እሱ የሚያውቀው የለም ሌላ ሰው የሚሆን ቢሆን እሱን አልፈልግም አላስቸግርም ነበር ማለቷ ነው...... ለካ ነገሯ የጐድን አነጋገር አይሆንላትም የጐሪጥ ነው አቀራረቧ ሁሉ...... ያስከፋል

አያስከፋም ሳትል...... ለጊዜው መስሎ የታያትን......» ያግባባሉ አደፍርስን አቶ ወልዱ ከእልፍኝ ወጥተው ወደ መኝታቸው ወደ ወርዶፋ ጐጆ እንደ ተመለሱ «የለም በእንዲህ ያለ ጉዳይ ልቡብ መሆን ይኖርብሃል......

«ቢሆንም ቢሆንም...... ያባባል ስሕተት ዓይነት ዓይነት አለው..... እርግጥ ነው መቼም አልክድም...... ጕርፉ ደኅና ልጅ መሆኑን......

«እንዲህ ያለ ጠዋይ አስተያየት.......

«ጠዋይ ጠዋይ! ምን ማለትዎ ይሆን ደግሞ እርስዎ......?

«የተወለጋገደ የተጣመመ አስተያየት ማለቴ ነው፤ ጥሩ አይደለም...... የኋላ ኋላ የሚጐዳህ ራስክን ነው። - እንኳን አለመልኩ መልክ ሰጥተውት የዛሬን ነገር እንዲያውም አልተቻለ፣..... አሁን በየፍርድ ቤቱ የምሰማው ጠዋይ ክርክር......ጠበቃው የሚያመጣው ጥውየት - ዳኛው የሚያሰማው ጥውየት፥ የሕጉ መጽሐፍ የሚዘረዝረው ጥውየት..... ሰምሚን ስለቸው ነው..... እንዲያው ሄደት ብለህ አንድ ቀን ቀን ብታዳምጥ......

«ሰው መቼም ካነጋገሩ ከሁኔታው እንደ ገባው አይደለም የነገርን መሄጃ የሚያገኘው.......?

«እኮ! እሱ ላይ ተሳስተሃል ነው የምለው......

«አዬ እንዲያውም እርስዎም ትንሽ ተጫኑኝ...... ምን ያረጋል መቀጠሉ......

«አንድ ነገር ተመልክተሀልኛል ለመሆኑ.......?

«ምን.......?

«ስለዚህ......ስለ እናንተ ስለ ዘመኑ ልጆች...... አሁን እኛም በዘመናችን..... ችኮ መንቻኮች የመጨረሻ ምርዱዳን ተብለናል....... በተለይ አንድ ክርክር የያዝን እንደሁ...... እንዲያው ምን ቢሆን መረታታችንን እንኳን ልባችን ቢያውቀው፥ እንዴት ብለን በገሃድ አጉራህ ጠናኝ ልንል....... ግትሮች ነበርን...... ታዲያ ቢሆንም አሁን ሳየው እናንተ የባሳችሁ መስለኝ......

« ‹ኦብስቲኔት› ማለትዎ ነው.......?

«አዎ ‹ኦፒስቲኔ› ናችሁ...... ከልክ በላይ......!

«......የትምህርታችን ይዞታ እንደሁ እንዲያ ያረገን? አይታወቅምኮ......

«......ሊሆን ይችላል...... የዛሬ ትምርት ፍደሳና መድልው ይበዛበታል..... ‹ኢፓክሪት!› ‹ኢፓክሪት› ብቻ ነው በየቦታው የሚታየው......

«ሆኖም ታዲያ የዘመናዊ ሰው ምልክት አይመስልዎትም......?

«አዎ፥ አዎ፥ የሚንነት ምልክት ነው! የ ‹ፊኔስ› ምልክት ፈረንሳዎች እንደሚሉት......

«አንድ ነገር ብጠይቅዎ...... ይቅርታ አድርገውልኝ.......

«ጠይቀኝ ጠይቀኝ ምን አለ? እምልህ የምመልሰው ከሆነ.....

«እንደዚህ እንደ እርስዎ ያለ ሰው፥ ብዙ ዓለም ያዩ! የተማረ! ምን ይሠራ እዚህ እገጠር......?

«ብዙ ዓለም! ብዙ ዓለም...... አዎ ብዙ ዓለም አይቻለሁ፤ የፓሪው ወልዱ ነበር የቁልምጫ ስሜ..... አለባበሴ አደናነሴ ልዩ ነበር..... ሁሉ ነገር ያምራል በጊዜው....... ስንቱን ስንቱን ሠራንበት...... አንዴ አስታውሳለሁ፥ በ፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረት ገደማ ባልጋ ወራሽነታቸው ጊዜ፥ ጃንሆይ መኳንንታቸውን አስከትለው ፈረንሳይ አገር መጥተው ነበር......

«ታዲያ እንዴት ዘመድ ሳያበጁ ቀሩ? እምልዎ? በዚያን ዘመን የኢትዮጵያዊ ፊት ፈረንሳይ አገር ማየት ብርቅ መሆን አለበት......

«ብርቅ? በጣም እንጂ! ብርቅ ነበር። - እኛው ነበርን ሽርጉድ ያልንበት...... አስተርጓሚዎቹ ከራባት አሣሪዎቹ...... ምኑ ቅጡ.......

«ታዲያ ኢትዮጵያ ሲመለሱ እንዴት ወገን አልሆኑዎትም፥ እነዚያ ያስተናግዷቸው መኳንንት.........?

«ወገን? ወገን! ህ! ወገን ራስ ብቻ። - ሰማሆይ....... እንዲህ ሆንሁልህ በዚያኑ ጊዜ...... አንዱን ትልቅ ሰው አምኜ....... አገሬ ወስጄ ላሹምህ ላሽልምህ አሉኝ..... እምቢ አልኳቸው። - ብዙ ብዙ ስብከት አመጡ...... ስለ ሀገር ስለ ወገን ስለ ስንቱ.......? ልቤን አሸፈቱት....... ጃንሆይን እጅ ልንሣ ቀረብንና...... ያገሬ ልጆች የሆናችሁ ወደ እናት አገራችሁ ለመግባት የምትፈልጉ ልውሰዳችሁ....... እኔ ረዳታችሁ እሆናለሁ አሉን። - ለጊዜው ማንም የፈለገ አልነበረም....... እኔም ሳመነታታ ብዙ ቆየሁ። - በመከያው የኝሁ ጌቶቹን ተከትለው የመጡት ሰው...... ስማቸውን መጥራት አልሻም..... የሳቸው ስብከት አሸነፈኝ። - ፓሪ መቼም ተደስቻለሁ፤ ይከበር ይመስገን ለፈጣሪ ዓለምን አይቻለሁ......

በየዳንሱ ቤት አባክነው የነበረው ገንዘብ.......! ተቀማጭ የሚሉትን ነገር ማን አስቦት....... እና ይኸውልህ ወዳገሬ ለመመለስ ስቀርጥ እከሌን የሚሉትም ገንዘብ አልነበረኝ...... እኝሁ እጃንሆይ አሽከር ላይ ነው ሽክም ሆኜ እዚህ የደረስሁት...... ምን አለ ከዚያማ...... እንደመጣሁ ነጋድራስ ብለው ሾሙኝ። - አገር ቤት ሄደህ ዘመዶችህን ትጠይቃለህ ብለውኝ ነበርና፥ ዘመዶቼን ልጠይቅ ይፍቀዱልኝ አልኳቸው....... ፈቀዱልኝ። - በቅሎም እንዲታዘዝልኝ ጠየቅሁ...... አዘዙልኝ በቅሎውንም። - እንገሩ እንግዲህ በቅሎ መረጣው ላይ ነው...... የገንዘብንም ጥቅም ያወቅሁት ያን ጊዜ ነው። - በቅሎ ጋጥ ገባሁና በቅሎ ስመርጥ..... ያቺን ልውሰድ አልኩት ባልደራሱን...... ከትብሎ ሳቀብኝ...... ድሃ በሕልሙ ቅቤ ባይጠጣ ደርቆ ይሞት ነበር አለኝ....... ተናደድሁ! ጦፍሁ! የመረጥኋት በቅሎ የጌቶች ኖራለች...... አንድ መጋዣ ነገር ሰጠኝ...... የበቅሎ ዕቃውንም ስንቱን ብጥስጣሽ ከያለበት አጠራቅሞ....... ምናለ መቼስ እምቢ አይሉት ነገር..... ብቻ ምን አለፋህ፥ በዚያው ንዴት ባመቱም እንደሁ ወደ ተረዳሁ፤ እንደ በፊቱ አልታለልሁኝም....... ስድስት ጊዜ ነው በካናል ሱዌዝ ላይ የተመላለስኩት......

«ታዲያ ለምን የመንግሥት ሥራ ሳይዙ ቀሩ? እምልዎት፥ በመጨረሻ ጊዜ ላይመለሱ ቆርጠው አገርዎ ሲገቡ.....

«አልፈለግሁም....... ለሌላ ሰው ባሪያ ከመሆን ለራሴ ባሪያ መሆንን መረጥሁ...... ለራሱ ባሪያ መሆን ያልቻለ ለሌላ ሰው ባሪያ ይሆናል ነው የኑሮዬ ፍልስፍና...... ስለዚህ ለራሴ እንዳሽከርም እንደ ጌታም ሆኜ እኖራለሁ....... ይከበር ይመስገን ሀብት አለኝ። - ግን ቢሆንም ከረዳቶቼ ጋር ቁፋሮም እንደሁ አብሬ ቆፍሬ..... ሽክምም እንደሁ አብሬ ተሸክሜ ነው የምኖረው.....

«ከዚህ እገጠር ታዲያ ምን ይሠራሉ? አዲስ አበባ መጥተው ንግድዎን አሻሽለው ለምን አይኖሩም.......? «አዲስ አበባ ለኔ ብርቄ አይደለም....... ያዲስ አበባን ዓይነቱ ከተማ ሰልችቶኛል...... ከዚያም በላይ፥ ሠራተኛ ሆኖ መገኘት ነው እንጂ የትም ሆነ የት ልዩነት አያመጣም....... እዚህም ንግዴን ላስፋፋ እችላለሁ ከፈለግሁ...... የሰው ጠባይ ስለሆነ ነው እንዲያው አዲሳባ አዲሳባ የሚለው ሕዝቡ...... ሱካር እንዳየ ጉንዳን አንድ ላይ ለመታጀብ..... እኔ እንዲህ ያለው ኑሮ ሰልችቶኛል.......! እህል በቀርባባ - ዕንቁላል በወታቦ የሚገዛበትን አገር..... ህ! ገጠር......?! ሰፊ..... ሰፊ..... ሜዳ ተራራና ሸንተረር የሚታይበት ንጹሕ አየር የሚተነፈስበት አገር ነው የማይሰለቸኝ እኔ! እና..... የማይሰለቸኝንም አግኝቻለሁ ነው የምልህ........» ለትንሽ ጊዜ ሁለቱም ዝም ይላሉ። -

«...... ነገ እንግዲህ ማለድ ብለን መነሣት አለብን?» ይጠይቃቸዋል አደፍርስ።

«ምን አስቸኮለን? ሞቅ ሲል እንወጣለን የሚያስቸኩልም ነገር የለ......» ዝም ይላሉ እንደ ገና ሁለቱም ለትንሽ ጊዜ «.......አስለፈለፍከኝኮ አንተ ልጅ..... ወዴታዬን ዐወቅህና......» ቆም እንደ ማለት ይሉና «እስኪ ልሰናበታት አሰጋሽን፤ በሌሊት ሃያጅ ነች መሰለኝ......» ወጣ ካሉ በኋላ «አንተም ብትሰናበታት አይከፋም.......» ወደ እኅታቸው እልፍኝ ያመራሉ። -

## ፴፫

# አደፍርስ

እሁድ ለት፥ ከቤተክርስቲያን መልስ ወደ ወርካው ጥላ ሲያመሩ «ስሚኝ ፍሬዋ ጋሼ፥ ጥሶ የሚያመጣው፥ የባህል ተጠየቅ ሁሉ ሳይገባኝ ቀርቶ አይምሰልሽ በየጊዜው ስንከራከር የምትሰሚው......» ይተውታል አደፍርስ። -

«እንዲሁ ስትከራከር ነው የሚመሽልህ በየጊዜው........ እኔ እምለውኮ....... ከገባህ ታዲያ ለምን አይገባህም? ለምን መልሰህ መልሰህ ያንኑ አንዱን ነገር ታመጣዋለህ.......?

«አንዱን ነገር? ምን ማለትሽ ነው አንዱን ነገር! እኔ የማመጣውን አንድ ነገር ብቻ አይደለም ብዙ ነገር ነው.....

«እምልህ..... ስለ ባህላችን ስለ ሕጋችንም ሆነ ስለሌላው...... አሁን ለምሳሌ - ኢትዮጵያ ነበሩ አሉ፥ ይመጣሉም ብላ ስለምታምንባቸው መሪዎችና ጀግኖች ጻድቃንና ሰማዕታት...... ከኔም ይሁን ካባዬ ጋር ስንት ስንት ጊዜ ነው የተከራከርነው......

«ነበሩ ስለሚባሉት መቼም አሁንም ቢሆን የማውቀው ነገር የለኝም...... ይመጣሉ ስለሚባሉትም በሰማይ ላም አለኝ.....

«እንዴት በሰማይ ላም አለኝ ይሆናል? ደግሞስ ስለ ነበሩት እንዴት አታውቅም? ባይሆን እያወቅህ አላምንም ወይም አልቀበልም በል እንጂ ጨርሰህ አላውቅም የምትለውን ነገር አልሰማም...... እንኳን አንተ ብዙ የተማርከው እኔም ዐውቃለሁ እላለሁ......

«እኮ፥ ከመሪዎች ውስጥ እንደ ዘረ ያዕቆብ እንደ ዐምደ ጽዮን ያሉትን..... ጀግኖች እንደ ልዑል ራስ መኮንን ራስ፥ ጐበና ደጃች ባልቻ ራስ አሉላ...... ከጻድቃን እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንደ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ...... ከሰማዕታት እንደ ቴዎድሮስ እንደ ዮሐንስ ዓይነቶቹን ማለትሽ ይሆናል ምናልባት........?

«ምን እኔ ብቻ አንተም ማለትህ ይሁን እንጂ! በተዘረዘሩት በማንኛዎቹም መስኮችኮ ቢሆን በሌላው ክፍለ ዓለም በጊዜያቸው ከነበሩት ባለ ታሪኮች የሚያንሱ አይደሉም.....

አባ ዮሐንስ አቶ፥ ትሶ አቶ ወልዱ ወይዘሮ አከላትና በላይ ሆነው እየተጨዋወቱ ወደ ወርካው ሥር ይመጣሉ። - ዛሬ ለትምህርት ቤት ማሥሪያ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማዋጣት ባቀዱት መሠረት የሁለተኛው ትልቅ ስብሰባቸው ቀን መሆኑ ነው። ፍሬዋና አደፍርስ ቀደም ብለው ሥፍራ በመያዝ ክርክራቸውን እንደ ቀጠሉ ይደርሳሉ። -

«.......ለምሳሌ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ጻድቅ ሊያሰኛቸው የቻለው ምንድነው? ደብረ ሊባኖስን አቅንተው ገዳም ስላደረጉ? እምልሽ፥ ምን ሠርተዋል እስከዚህ? በእሳት ተቃጠሉ? በአናብስት ተቆራረጡ? ታሠሩ ተገረፉ ተሰቀሉ? ምን ሠርተዋል እስከዚህ ሊያሳውቃቸው እይቻለ......?» እያለ በረጅሙ ይዘታል አደፍርስ። -

«የወጣቶች ነገር......... ደግሞ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ምን አደረጉ ይሆን የምትሉት........?» እያሉ ይጠጋሉ አባ ዮሐንስ። -

«ምን አደረጉ እንላለን.......? ምንም አላደረጉ ነው የምለው እኔ በበኩሌ......» ይመልሳለ አደፍርስ።

«እውነትህን ነው፤ ሃይማኖትን የሚያበላሽ አገርን ወገንን የሚበድል ምንም ያደረጉት ነገር የለም......

«ጻድቅስ የሚያሰኝ..... ታቦት የሚያስቀርጽ ምን ነገር ሠርተዋል........?

«እንዴት ነው፤ ጻድቅነታቸውን ትጠራጠራለህ ልበል ይሆን.......?

«አዎን እጠራጠራለሁ......

«የጸላኤ ሠናያት መጠጋት.......! ጸላኤ ሠናያት ቢቀርብህ ነው ወዳጄ! ተክለ ሃይማኖት የጻድቅ ጻድቅ ናቸው። - እንዴታ! ጥርጥር ሊገባህ አይገባም። መቶሎሚን የመሰለ የወላሞ አረመኔ ንጉሥ ወደ በጐ ምግባር መልሰው አስተምረውና አጥምቀው ክርስቲያን ያደረጉ....... ሰባት ዓመታት ሙሉ በአንድ እግራቸው ቆመው ስለ ሀገር ስለ ሕዝብ ሲጸልዩ የቆሙበት እግር እስከ መቆረጥ የደረሰ....... ስድስት ክንፎች እስከማብቀል ድረስ ክብር የተሰጣቸው........ ጻድቅ ናቸው እንጂ የኔ ልጅ! ከሳቸው የበለጠ ጻድቅ ከየት ሊመጣ.......?

«እኔኮ የምለው ስለ ክርስቶስ ሲሉ የተሠቃዩት ሥቃይ የለም ነው......

«ሥቃይ.......? በቆዳ እየተጠቀለሉ እገደል ከመወርወር እባሕር ውስጥ ከመጣል የበለጠ መሠቃየት አለ እንዳትለኝ......

«ተክለ ሃይማኖት እገደል ተወርውረዋል....... እባሕር ተጥለዋል ነው የሚሉኝ......

«እንዴታ! ከተጣሉበትም ሁሉ ምንም ሳይሆኑ ወጥተዋል...... ኋላ መቶሎሚን በየትኛው ጦር ሠራዊታቸው አሸነፉት........?

«ስድስት ክንፎችም አውጥተው ነበር ነው የሚሉኝ ከቅድስናቸው የተነሣ........?

«እንዴታ! እተቆረጠው እግራቸው ላይ እቁርጭምጭሚታቸው ገደማ፥ የበቀለላቸው ክፍን ሳይቆጠር.....\

«እስከሱ ስምንት መሆኑ ነው እንግዲህ......

«አሉ ገድላቸው ስምንት አይልም...... ስድስት ነው! እየምስላቸው ላይ ግን በግልጽ ልታየው ትችላለህ...... በርግጥ እግራቸው ክፍን አጐጥጉጦ ይታያል.....

«ጋሼ ጥሶስ ምነው ዝም አልህ........ ምንድነው ያንተ አስተያየት.......?

«እንዲህ ዓይነቱን ነገርኮ ከዚህ ቀደም የተወያየንበት መስሎኛል። ምናልባት እንጃ ከፍሬዋ ጋር ይሆን.......

«በጠቅላላው ተነጋግረናል ከኔም ጋር.....

«ስለ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ....... አልተነጋገርንም ካንተ ጋር........?

«በተለይ ስለሳቸው አልተነጋገርንም፤ ግብጻዊ መሆናቸውን ግን ዐውቃለሁ.......

«ግብጻዊስ ግብጻዊ ናቸው...... ብቻ ቢሆንም በመላ ኢትዮጵያ የታወቁ ጻድቅ ናቸው........

«አቦ የሚሏቸው አይደሉም.......?

«አቦ አቦም፥ አቡነ ገብረ ሕይወትም አቡየ ጻድቁም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ይሏቸዋል.......

«ያገራችን ጻድቃን መቼ እነሱንና ነው ታዲያ....... ካሉ ማለቴ ነው....... በሰው አገር...... ጻድቃን....... የምናምነው........?

«ካሉ አትበል ወዳጄ፤ ሞልተዋል.......! እነ አቡነ ዜናዊ ማርቆስ እነ አቡነ መልከ ጼዴቅ እነ ወለተ ጴጥሮስ እነ ዘርዓ ብሩክ እነ ተክለ አልፋ እነ ሐራ ድንግል እነ ሙብዓ ጽዮን እነ አቡነ ፊልጶስ፥ እነ አቡነ ተክለ ሐዋርያት........ እነ አቡነ ሳሙኤል ዘዋሊ እነ ቅድስት እማሙዝ....... እነ አቡነ ዘርአ አብርሃም፥ እነ አቡነ አቢየ እግዚእ......

«እሺ እሺ ሰማሁ፤ ብዙ ናቸው ማለት ነው.....

«በጣም እንጂ ብዙ ናቸው..... ፈጣሪ ይክበር ይመስገን......

«ሸዋዎች መሆን አለባቸው መቼም እነዚህ ሁሉ ቅዱሳን......

«ሸዋዎች.......? ሸዋ፥ ግብጽ ቁስጥንጥንያ ሮም፥ አይልም ቅድስና...... እንደ እንጉዳይ ነው የእግዚአብሔር ጸጋ በወረደበት ቦታ ሁሉ የሚበቅሉት.....

«የምለው ኢትዮጵያውያኑ ጻድቃን.....

«እነሱም ቢሆኑ ከጐጃም ከተጉለት ከቤጌምድር ከደብረ ቢዘን ከትግሬ ከድፍን ኢትዮጵያ ናቸው.......

«ለምሳሌ ከወሎ፥ ከአሩሲ ከባሌ፥ የሉባቸውም......

«አይ ከድፍን ኢትዮጵያ ናቸውኮ ብየሃለሁ...... ከድፍን ኢትዮጵያ! ከአንድ ቦታ መርጋት የለባቸውም፥ ጻድቃን ሲባሉ። - ለምሳሌ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ድፍን ኢትዮጵያን በመዘዋወር ወንጌልን አስተምረዋል......

«እዚህ ላይ መቼም አባ ዮሐንስ ቅዱሳን ሲሉ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችን ብቻ አይመስለኝም....... ማለቴ እስላሞችም ቢሆኑ በአንድ ፈጣሪ የሚያመልኩ ስለሆኑ - የእግዚአብሔርን ጥሪ የተከተሉ ቅዱሳን አሏቸው......» ጣልቃ ይገባሉ አቶ ጥሶ።

«አቦ የሚሏቸው አይደሉም.......?

«አዎ አቦም አቡነ ገብረ ሕይወትም አቡየ ጻድቁም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ይሏቸዋል......

«ያገራችን ጻድቃን መቼ እነሱንና ነው ታዲያ...... ካሉ ማለቴ ነው...... በሰው አገር..... ጻድቃን...... የምናምነው.......?

«ካሉ አትበል ወዳጅጄ፤ ሞልተዋል......! እነ አቡነ ዜና ማርቆስ፥ እነ አቡነ መልከ ጼዴቅ እነ ወለተ ጴጥሮስ እነ ዘርዓ ብሩክ፥ እነ ተክለ አልፋ እነ ሐራ ድንግል እነ መብዓ ጽዮን እነ አቡነ ፊልጶስ እነ አቡነ ተክለ ሐዋርያት...... እነ አቡነ ሳሙኤል ዘዋሊ፥ እነ ቅድስት እማሙዝ...... እነ አቡነ ዘርአ አብርሃም፥ እነ አቡነ አቢየ እግዚእ......

«እሽ እሺ ሰማሁ፤ ብዙ ናቸው ማለት ነው.....

«በጣም እንጂ ብዙ ናቸው....... ፈጣሪ ይክበር ይመስገን......

«ሸዋዎች መሆን አለባቸው መቼም እነዚህ ሁሉ ቅዱሳን......

«ሸዋዎች......? ሸዋ፥ ግብጽ ቁስጥንጥንያ ሮም አይልም ቅድስና...... እንደ እንጉዳይ ነው የእግዚአብሔር ጸጋ በወረደበት ቦታ ሁሉ የሚበቅሉት......

«የምለው ኢትዮጵያውያኑ ጻድቃን.....

«እነሱም ቢሆኑ ከጐጃም ከተጉለት ከበጌምድር ከደብረ ቢዘን ከትግሬ ከድፍን ኢትዮጵያ ናቸው......

«ለምሳሌ ከወሎ ከአሩሲ ከባሌ የሉባቸውም.......

«አይ፥ ከድፍን ኢትዮጵያ ናቸውኮ ብየሃለሁ...... ከድፍን ኢትዮጵያ! ከአንድ ቦታ መርጋት የለባቸውም፥ ጻድቃን ሲባሉ። - ለምሳሌ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ድፍን ኢትዮጵያን በመዘዋወር ወንጌልን አስተምረዋል......

«እዚህ ላይ መቼም አባ ዮሐንስ ቅዱሳን ሲሉ የክርስትና ሃይምኖት ተከታዮችን ብቻ አይመስለኝም...... ማለቴ እስላሞችም ቢሆኑ በአንድ ፈጣሪ የሚያመልኩ ስለሆኑ - የእግዚአብሔርን ጥሪ የተከተሉ ቅዱሳን አሏቸው......» ጣልቃ ይገባሉ አቶ ጥሶ።

«እንዴታ! ሞልተዋቸዋል..... እንደ ሼህ ከድር ዓይነቱ ለምሳሌ ከወሎ......» ያብራራሉ አባ ዮሐንስ።

«.......ቀይ ገደልስ ማነው ስማቸው - ጌታው ሼክ ሁሴን..... ባሌ ደግሞ ሌላ ሼክ ሁሴን..... አሩሲ ደግሞ እንዲሁ ሌላ ሼክ ኑረ ሁሴን..... ሞልተዋቸዋል.........» ይቀጥላሉ አቶ ጥሶ። -

«ስለዚህ ብቻ፥ በጠቅላላው ሞልተውናል ማለት ነው ጻድቃን በኢትዮጵያ.......» ያመቻቻል አደፍርስ

«እንዴታ እንዴታ ሞልተውናል......» እያሉ ይስፋፋሉ አባ ዮሐንስ።

«.......ለምንድነው ታዲያ አቡነ አረጋዊ አባ ሊባኖስ አባ ገሪማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቅዱስ እስጢፋኖስ የምንለው? ግብጻውያኑ ሶርያውያኑ ምን ያደርጉናል? ለምን የራሶቻችን ብቻ አይበቁንም.......?

«ቅዱሳኑና ሰማዕታቱን አደባለቅሃቸው..... ብቻ ቢሆንም...... ጻድቃንና ሰማዕታት ለመሆን ጊዜና ቦታ አይወስነውም ያልኩህ ይመስለኛል......» ይመልሳሉ አባ። -

«ስለ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጀምረን ነበር ቅድም.......» ረጋ ባለ አንደበት ያስረዳሉ አቶ ጥሶ «ግብጻዊ ናቸው ብለናል። - በኢትዮጵያ የታወቁ ጻድቅ ናቸው ብለናል። - ገድላቸው እንደሚያትተው ሲወለዱ አንሥተው የናታቸውን ጡት አልቀመሱም ይባላል። - ለመወለድም እንኳ የበቁት የአባታቸው ርስሐት ከቀጤማ ላይ ፈሶ ኖሮ እናቲቱ እንደ መተከዝ ብለው ቄጠማውን ቆርጠው ስለመጠጡት ፅንስ ሆኖ ነው ይባላል......

«ጋሼ ጥሶ፥ አንዳንዴ ብረር ብረር ነው የሚያሰኘኝ ንግግርህ..... ደሞ ደሞ..... እንዴት...... በአፍ የገባ ነገር ወደ ማሕፀን ገብቶ ተፀንሶ ሰው ሆኖ ተወለደ በልህ ታወራልኛለህ.......?

«የሱስን ማርያም የወለደችው በድንግልና አይደለም......?

«ቢሆንም የሷ ይሻላል..... የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእምነት ጉዳይ ነው.....

«እንግዲያው የአምቦ ፅንሰት የእምነት ጉዳይ ነው.....

«ደግሞ ሲወለዱ ጀምሮ የእናታቸውን ጡት አልቀመሱም......» ይቀጥላል አደፍርስ። -

«ምነው ለምን ያስገርምሃል ይኸ? ስንቶቹ ናቸው የዛሬዎቹ እንኳ ልጆች በፍየል ወተት በላም ወተትና በዱቄት ወተት የሚያድጉት..... ምናልባት በፍየል ወተት አድገው ይሆናል.....» ትቋቋመዋለች ፍሬዋ ታዳምጥ ታዳምጥና።

«.......ዝቋላ የተባለውንም የሠይጣን ቦታ ለራሳቸው ለማድረግ በራሳቸው ተደፍተው ብዙ ዘመን ጸልየዋል። - ከርጎራኄያቸው ብዛት የተነሣ አንድ የተጠማ አሞራ ቢመጣ ዓይናቸውን ሰጥተውታል። - በጃቸው ይይዟት የነበረች ጭራ ግን አንድ

ዝንብ መግደሏን በመመስከሯ ለሞታቸው ምክንያት ሆኖባቸዋለች። -አናብስትን አናብርትን መባርቅትን ለማዘዝ በቅተዋል.....

‹አቡየ ጻድቁ

አቡየ ጻድቁ

ገደል እንዳከርማ የሚሰንጥቁ

በዘንጋቸው ወግተው ጠበል፥ የሚያፈልቁ› ሲባልላቸው ይኖራል ይኸው እስከ ዛሬም......

«ድንቁርናና ዕውቀት ብሎ ነገር! የሚገርመኝኮ የተቃራኒው ብዛት..... ጠበል ሊያፈልቁ ሲችሉ ዓይናቸውን ለአሞራው መስጠር...... በአንድ ዝምብ ሞት ምክንያት እሳቸው እንዲሞቱ መፈረድ..... ጭራው ደሞ ከፈረስ ላይ የተቆረጠ መሆን አለበት መቼም.....

«ሳይቆረጥም  እንዳንዱ ተነቅሎ የተበጀ ሊሆን ይችላል.....» ትናገራለች ፍሬዋ። -

«ከብቃታቸው የተነሣ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውም ሊሆን ይችላል.......» ይመከታሉ አባ።

«ብቻ ያም ሆነ ይህ...... ባንተ አስተያየት አደፍርስ...... ከየትም ይምጡ...... ዕድለኛ ሆነህ ብቻ ይምጡልህ፤ ጎያላን አውሬዎችን አዘው ከሥልጣናቸው ሥር የሚያውሉ...... መብረቅን ያህል ቁጣ ተቆጣጥረው ለጠላት መመከቻ የሚያደርጉ..... ለሕይወት ከመሳሳታቸው የተነሣ የዝንብን ሕይወት እንኳ ቢሆን ለማሳለፍ የማይሹ...... ከርኅራኄያቸው ከደግነታቸው የተነሣ ለተፈጥሮ ጓደኛቸው ብቻ ሳይሆን ለአሞራ እንኳን ዓይናቸውን የሚሰጡ..... እንዲህ ያሉ ጻድቅ ቢኖሩህ አትወድም.......?

«እንዲኖሩኝ መፈለጌና የሌሉኝ መሆን የተለያዩ ነገሮች ናቸው......

«አንድ ጊዜ ደግሞ ከሞቱ በኋላ ስእለት የቀረበላቸውን አውራ ዶሮ፥ አንድ ዐቃቢ እርድ አድርጐ በልቶባቸው ኖሮ....... ቄሶችና ዲያቆኖች ተሰብስበው ዶሮውን የሰረቀውን ሰው ለማግኘት ተጨንቀው ሳለ...... በተአምር አርዶ እበላው ዐቃቤ ሆድ ውስጥ እንዳለ፥ ኩኩሉ ብሏል ይባላል...... አውራ ዶሮው ታርዶ ተሰልቆ ሆድ ውስጥ የገባው አውራ ዶሮ...... እና ታዲያ ምድር ምንኛ በተሻሻለች የሰው ልጅ ምንኛ በተቀራረበ እንደ አቡየ ጻድቁ እውነትን ፈልፍለው የሚያወጡ ጻድቃን ቢፈጠሩ.....

«አልተፈጠሩማ አልተፈጠሩም........

«ያልተፈጠሩ አይምሰልህ...... አደፍርስ፤ ተፈጥረዋል....... ወደፊትም ይፈጠራሉ። - ዋናው ነገር ብቻ በእምነታችን ጸንቶ መገኘቱ ነው። - ጻድቃን የትክክለኛ ኑሮ አርማዎቻችን ናቸው፤ የእውነተኝነት የርኅሩኅነት የመንፈሳዊ ኃይል የሰው ልጅ ትልቅነት...... የብዙው የብዙው ስብእናችን......

«.......የክርስቶስ ሠምራ አሁን ዋናው ልመናዋ ሰዎችን የሚያስተውን ሠይጣንን አስምራ ሁሉንም ሰው ለማጽደቅ ነበር። - እና ታዲያ እግዜር...... ዲያብሎስ እሺ አይልሽም እንጂ እሺ ካለሽ ምንቸገረኝ ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶላት፥ ከሲዖል አፋፍ ላይ ወጥታ ጠርታዋለች ዲያብሎስ ዲያብሎስ እያለች በማቆላመጥ። - እሱ ግን ያልለመደውን ፍቅራዊ አጠራሯን ሰምቶ በዓይኑ ለማየት ቀና ቢል መጥፎ ተግባሩ በሰውነቱ ሥራ ተገልጾ በቅንድቡ ስቦ ሲዖል ጭምሯታል። - ይቅር ባዩ አምላክ ግን ይህን ሁሉ ያይ ነበርና፥ እባክህ ያቺ የዋህ ሴት ሲዖል ገብታለችና ሄደህ አውጣት ብሎ ሚካኤልን አዞላት ወዲያው ወጥታለች። - ለብዙም ነፍሳት እሷን ተከተለው ወጥተው ድነዋል። - አቡነ ዘርአ ብሩክም ሱስንዮስን ለማውገዝ በሄዱ ጊዜ መጻሕፍታቸውንና ኩስኩስታቸውን በዐባይ ላይ አደራ ጥለው ቢሂዱ ምንም ሳይሆን ሲመለሱ አግኝተውታል። - ከጽድቃቸውም ስፋት የተነሣ፣ ሰማይና ምድርን ደግፈው የያዙትን የብሔሞትንና የሌዋታንን ጥርሶች ቆጥረው ወጥተዋል። - ቅድስት እማሙዝ የምትባለዋ ደግሞ...... ከቅድስናዋ ስፋት የተነሳ አምላክን ለምና ከሰንሰል የተሠራው ቤተ ክርስቲያኗ እስከ ምጽአት ድረስ እንዳይፈርስ ቃል ኪዳን ገብቶላት እስከ ዛሬ ድረስ እንዳጋደለ ይኖራል.......

« ‹ሊኒንግ ታወር ኦፍ ፒዛ!› ም አለን በሉኝ!» ጣልቃ ይገባል አደፍርስ።

«ሊንንቶርፒዛ አልወጣኝም........!» ይቀጥላሉ አባ

«እንግዲህ ሕዝቡ ተሰብስቧል...... የመጣንበትን ጉዳይ ብንጀምር» ይናገራሉ አቶ ጥሶ። -

«.......የማሙዝ ቤተክሲያን እስከ ዛሬ እንዳጋደለ አለ ነው ያልኩህ...... እስከ ዛሬ......» እያሉ ሕዝቡ መካከል ይገባሉ አባ። -

# ፴፪

# አደፍርስ

ፍሬዋ እንደ ልማዷ አንድ እግሯን እውሃው ውስጥ ነክራ ሌላውን ከውሃው ውጪ አዛንታ በማሳረፍ እወንዙ ዳር ተቀምጣለች። - የሚንሻሻ የሚቦልቅ የሚንዶቀዶቀው የውሃው ግርግርታ አፍዟታል። - የፀሐይ ግለት ማቃጠሉንና ማዳከሙን ጀምሯል - አልፎ አልፎ በሚነፍሰው ቀዝቃዛ አየር ከመበረዙና ከመቀዝቀዙ በስተቀር። - በቀዘቀዘ ቁጥር ከወራጁ ውሃ ጋር አብራ የፈሰሰች የመሰለችው ሕየት ስትመለስ ይሰማል። - በላይ እፍሬዋ አጠገብ ተቀምጧል ሁለንተናው በአፍአዊ እንቅስቃሴ ተውጦ። - የሚወርደውን ውሃ ድምፅ አይሰማም። - ያባን ዲስኩር አያዳምጥም። - ሁለንተናው በጆቹ ምሥጢር ተወስኖ ከዘልማድ ሥራቸው በላይ የተጠየቁ ተዝናንተው ያሉትን መሳይ አጣማጆቻቸውን የፍሬዋን እጆች ሠርዶ እንደ መንቀል እያሉ እንካ ለማድረግ የሚያዴቡ የሚመስሉ ጣቶቹን እያንቀሳቀሰ። - አባ ዲስኩራቸውን ያምበለብሉታል......

«.......ዱር እየመነጠሩ አውሬ እያባረሩ የሚኖሩበት የድካም የፍርሃት፥ ዘመን አለፈ። - ከቆላ ወርዶ በረኸኛ ከደጋ፥ ወጥቶ ደገኛ በመባል ብቻ የሰው ልክ የሚታወቅበት ዘመን አለፈ። - ትምህርት በሚሉት መልከተኛ ተጭንኖ አገራችን ገባ፥ ሥልጣኔ። - ‹መንፈስ ይትናገር በላዕሌክሙ› መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ አድሮ ይናገርላ የተባለበት ዘመን መጣ..... የረዘመውን የሚያሳጥር ያጠረውን የሚያስረዝም ምትሐት ትምህርት የሚሉት ነገር ተስፋፋ በሀገራችን..... ሻካራውን ለስላሳ ጉጣጡን መዘዞ ወልጋዳውን ሰተቶ፥ ጠማማውን መለሎ የሚያደርገው ትምህርት። - ልማትና ስፋት ውበትና ጽዳት፥ ክብረትና ሀብት የያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዓላማና ግብ ሆኑ.....

አህዮቹን አስቀድሞ ብቅ ይላል ደገኛው ነጋዴ ከወደ ቆላው እየዘፋፈነ

«ካራማራን ዞረሽ ጅግጅጋን ያየሽው

እንደልብሽ ኩራት የታለ ያገኘሽው......» ከኋላ ከየህ መጣህ የማይባል የሚያጣድፍ አውሎ ነፋስ እየገገረ እየተጥለመለመና በሰፊው ክብ እየሠራ ይመጣና የነጋዴውን ደበሎ በራሱ ላይ ከልብሶ፥ የተሰበሰበውን ወንድና ሴቱን ሸማ አመሳቅሎ አጋልጦና አመናጭቆ ወንዙን እሻገራለሁ ሲል ፍሬዋን እበላይ ችኖች ላይ ይደፋታል። - በላይንም እፍሬዋ ራስ ላይ...... እንደ ኀይለኛ የንብ ሠራዊት ሠፈሩን ሁሉ ያብረገርግና ያልፋል። - ሩምታው ጓጓታው ሽውሽውታው ሁሉ በቅጽበት ይዋጣል ባካባቢው። -

«አሥራ ሁለተኛን ክፍል እንዳለፍሁ......» ይላል በላይ ቀስ ይልና..... የተነከረውን እግሯን አምቦራጭቃ ራሷን ቀና ታደርጋለች ፍሬዋ ከጭኑ ላይ......ትክ ብላም ትመለከተዋለች «አሥራ ሁለተኛን ክፍል ስንጨርስ.......» ይላል በላይ ይደግምና። -

ነፋስ ያስወረዛቸውን ዓይኖቿን እየጠራረገችን «.....ኮሌጅ ትገባለህ...... ዲግሪ ታገኛለህ......» ትጨርስትለታለች ፍሬዋ «ወይ ደግሞ እንደኔ የወደቅህ እንደሁ...... አሥራ ሁለተኛን......» ትቀጥላለች ንግግሯን። -

«አብረን ሥራ እንይዛለን.......» ብሎ ይጨርሳል፥ ያምጥ ያምጥና ጀምሮት የነበረውን ሐሳብ። - ፀሐይዋ ትንተገተጋለች፤ በርብርማ ዓይነት ቀለም በአናቱ ላይ በሚያልፉት ዳመናዎች ላይ ብርማ ጨስ መልክን በመዘርጋት። - ያየሩ ትኩስነት ዓይኖቹን በትንሹ ያረጥባቸዋል..... ሰውነቱን በዝግታ እየደሳሰሰ ወደ ሳምባው ሲፈስ። -

«.......አልፎ አልፎ ጉልበት እያወጣ፥ ሥሩን እያዛመተና እያለመለመ መሬት ለመሬት ተስቦ ሜዳውን እንደሚይዘው የሰኔ ሰርዶ በየጠቅላይ ግዛቱ በያውራጃው በየወረዳው በየቀበሌው ሥሩን ሰደደ ዘመናዊ ትምህርት። - የመስፋፋቱ ዐዋጅ ከመሰማቱ ያፈራሩ ማግር ዜና እግር በእግር ተከተለ። - ምን ልበ ሰፊነት ምን ተጋድሎ ምን መሥዋዕትነት ብናሳየው ምን ስጦታ ምን እጅ መንሻ ምን ገጸ በረከት ብናቀርብለት በዛበት ሊባል ይችላል......?» ቀጥለዋለል አባ። -

የተሰበሰበው ሕዝብ በየተራ እየተነሣ የያቅሙን ገንዘብ ያዋጣል።

-

«ጣርማበር ላይ ሆኖ ይታያል ሞላሌ፥

አንችው ነሽ ወዳጄ ቻይዋ እንዳመሌ» እያለ ነጋዴው፥ የሚዘፍነውን ያስተጋባል ጋራው ጉራንጉሩ። -

## ፴፲

# አደፍርስ

አቶ ወልዱ፥ አደፍርስና አቶ ጥሶ ክርክራቸውን ቀጥለዋል ከስብሰባው መልስ

«ንብና የወባ ትንኝ ሁለቱ የተለያዩ ነፍሳት አበባን ይቀሥማሉ። - ንብ ከአበባ ባገኘችው ንጥር ማርን ትሠራለች። - ለራሷ በቅታ ለሰው ትተርፋለች። - የወባ ትንኝ ደግሞ ከዚያም ካበባ በተገኘው ንጥር መርዟን ትሠራለች። - በመርዟም የወባ በሽታን ታስተላልፋለች። - እንግዲህ አንደኛው ለደግ ሌላው ለክፉ ስላዋሉት ያበባ ንጥር አያስፈልግም ለማለት አንችልም.......

«ባጭሩ ሥልጣኔ እንደ ተቀባዩ ነው የሚሉት አቶ ወልዱ.....» ያጠቃልላ አደፍርስ ያቶ ጥሶን ሐሳብ የሚቋቋምበት ነቁት ያገኘ ይመስለውና። -

«ቢሆንም ቢሆንም.......» ይለጥቃሉ አቶ ጥሶ «እኛ አገር የሚታየው ያሠለጣጠን ሁኔታ በይበልጥ የወባ ትንኞቹን መንገድ የተከተለ ነው የሚመስለኝ...... እንዴ የለም አይሆንም! ያለንን ሳናውቅ የሌለንን ለማግኘት የምናደርገው ጥረት ሁሉ ከንቱ ነው...... እየተግባባን እንጂ....... አሁን ለምሳሌ ምዕራባዊ ሥልጣኔ ሀገራችን መግባት ከጀመረ ጊዜ አንሥቶ እስኪ ያፈራውን ፍሬ እንመልከት.......

«በጣም ጥሩ! በጣም ጥሩ! እንመልከት.......» ጣልቃ ይገባል አደፍርስ። -

«እኛ አገር የገባው ምዕራባዊ ሥልጣኔ እንዴት ዓይነቱ ነው......? መጀመሪያ እንዴት ያለ እንደ ሆነ ማወቅ የሚኖርብን ይመስለኛል......

«ጥሩ ነው ዕንወቅ፥ እንዴት ያለው ነው.....? አሁንም ጣልቃ ይገባል አደፍርስ። -

«......እኛ አገር የገባው ምዕራባዊ ሥልጣኔ በቀጥታ ወይም በዝውርውር መንገድም ይሁን - ሀብት ወይም ማዕረግ የሚያስገኝ...... ድህነት አጨራምቶት የኖረን ሁሉ የመንግሥት ወይም የግል ድርጅት የቢሮ ሥራ የሚሉት ደረጃን የሚያሻሽል ነገር ስለ ተገኘ ፈተናን ሰጥቶና አሳልፎ እተባለው ቦታ የሚያደርስ...... ወደ ምዕራባውያን ማኅበራዊ ኑሮና ኅብረተ ሰብ የሚያስገቡ በሮችን የሚከፍት...... አብዛኛውን ጊዜ በገቢር ላይ የማይውል የቀለም ትምህርትን እንዲያስተጋቡ እያደረገ በቅዠት ላይ የተመሠረተ ያኗኗርን ዘዴ የሚያሳይ..... ልዩ መቀመጫው፥ እግዚአብሔር ቢረዳንም እንደሁ ባይረዳን አላውቅ ልዩ መቀመጫው ከተማ የሆነ - ከመሃል ከተማው ውጪ አፍሎ ወደ የገጠሩ ያልገባ..... ምዕራባዊ ሥልጣኔ በመባል ብቻ ተወዳጅ ወይም አስፈሪ የሆነ ነገር ነው.....

«ከማህል ከተማ አልፎ ወደ የገጠሩ አለመግባቱ እንኳ ያስደስታል እንጂ አያሳዝንም...... አገሬው ስንዴውን ከምርቁና ከገላባው ለይቶ ዳቦና ኅብስት እንደሚጋግር ሁሉ ከውጪ ከሚገባውም አዳዲስ ነገር ክፉና በጐ እንዳለው ተረድቶ

የሚመርጥበት ትምህርገና ያስፈልገዋል....... ዘጠና በመቶ የሚሆነው በመድፈንፈን ላይ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ገና ገና ዘመናዊ የሆነ የራስ ቁርና የደረት ጥሩር ያስፈልገዋል......

«እውነትዎን ነው አቶ ወልዱ...... ጥንታዊቷን ኢትዮጵያን ከወራሪ ጠላት ያዳኗት ተራሮቿና ሸንተረሮቿ፥ ሃይማኖቷና ቆራጥነቷ የነበሩትን ያህል ከዘመናዊዎቹ የስብእና ወራሪዎች ሊያድኗት የሚታገሉት ደሞ በዱሮው መንፈስ የጠነከሩት አስተሳሰቧና ድንቁርናዋ ናቸው.......» ያምናሉ አቶ ጥሶ። -

«አሁንስ ረቀቃችሁብኝ - ጸጉር ስንጠቃ እንለዋለን፥ በዘመናዊ አማርኛችን እንደዚህ ዓይነቱን......» ይናገራል አደፍርስ «ለመሆኑ በእናንተ አስተያየት ኢትዮጵያን የሚጠብቃት ድንቁርናዋ ነው ማለት ነው.......?

«የየዳንሱን ንቅናቄና ውዝዋዜ፥ የየሙዚቃውን ንዝረትና ስግምግምታ የየሲኒማውን ቤት ብልጭልጭታና አይሠሩ ሥራ የየሥነ ጽሑፉን ውስጥ አጉል ሁኔታና ፕሮፓጋንዳ በእቅዱ መሠረት ገብቶን አንጥረን አንጠርጥረን ተርድተነው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ኢትዮጵያዊ ሰወንታችን ጥንጣን እንደ በላው እንጨት ተበልቶ አልቆ ነበር...... ምዕራባውያን ሥልጣኔ የሚሸከምበት ጭንቅላት ትከሻና ደረት ባላገኘም ነበር......» ይቀጥላሉ አቶ ወልዱ።

«የኛ ሰውነት የሚተማመኑበትን ጥይት የሚያከሽፍ ነው የሆነው ለምዕራባውያን......» ያክላሉ አቶ ጥሶ።

«ስለዚህ ብቻ ሁለታችሁም አጉሉ እንጂ ጥሩው መልኩ የታያችሁ አትመስሉም እንዳነጋገራችሁ........

«አጉል መልኩ ብቻ ሳይሆን የሚያዳዳ የሚመስለውም በኩሉ ስለ ተገለጸልን ነው የምንነጋገረው...... እያዘንን እየተደሰትንም......

«......እውነትዎንኮ ነው አሁን አቶ ጥሶ..... እንዴት ይመስልዎታል እኔ አሁን የማዝነው..... ምዕራባዊ ሥልጣኔ ሲባል ሊመኙትና ሊፈልጉት የሚገባ ዕድገት ነው..... ነገር ግን..... እንዲህ እንደምናየው...... የፈረንጆችን እንቶ ፈንቶ ታሪክና ገናናነት ለማስተባቃት እንጂ የራሳችን የምንላቸውን ጠቃሚ ነገሮች ለመረዳትና ለማወቅ ያላስቻለን ሆኖ ሳየው...... ዐወቅን፥ ሠለጠንን የሚሉት ሰዎች በቅርቡ ከሚሠሩት ጥቅጥቅ ይልቅ፥ በረጅሙ የሚወጥኑትን ሽክሽክ ስመለከተው...... መልካም ምግባርንና ጠባይን እያስረሳ መሄዱን ሳየው...... በተግባር እድ በኪነ ጥበባት በጠቅላልው በሙያ

ትምህርቶች ምንም ያህል ያላፈናፈነን መሆኑን ሳሰላስለው...... በጣም ነው የማዝነው አቶ ጥሶ፥ በጣም......

«የሚደሰቱትስ - የሕዝቡ ጤና በመጠበቁ ትምህርት ቤቶች በመከፈታቸው ኢኰኖሚያችን ማደግ ስለ ጀመረ የሕዝቡም የኑሮ ደረጃ ከፍ ከፍ እያለ በመሄዱ ከፍትሕ ነገሥት በላይ የሆነ ደንበኛ ሕገ መንግሥት በመገኘቱ አስተዳደር በመሻሻሉ የምድር የአየር የባሕር ኀይሎቻችን በመደርጀታቸው....... ይሆን ይሆን ምናልባት.......?» ሐሳቡን ያቀርባል አደፍርስ የጐድን በሄደ ሁኔታ። -

«አደፍርስ......!» ይላሉ አቶ ጥሶ «የሥልጣኔን አስፈላጊነትም ሆነ መሠልጠን ያስገኘውን ነገር ሳናውቅ የምናገር አይምሰልህ....... መከላከያና መፈወሻ መድኀኒት ማግኘት የወሩን መንገድ በአንድ ሁለት ሰዓት መድረስ ጠላትን ፊት ለፊት ሳይተያዩ ድል መንሣት በሕግ ፊት እኩል የመሆንን ሥልጣን ማግኘት በበቅሎና በፈረስ ዘጥ ዘጥ ከማለት በመኪናና በአይሮፕላን መፍሰስ...... ሌሎችም..... ሌሎችም ብዙዎቹ ቀላል ነገሮች አይደሉም። - ነገር ግን እኛ የምንለው ዘመናዊውን ሥልጣኔ ለመቀበል ከብረት ምሰሶ የጠና ሰውነት እንዲኖረን ያሻል ነው፤ አንዴ........! ምነው ለማኝ እንኳ አቅማዳውን ሳያዘጋጅ ልመና አይወጣም...... ስለዚህ ዘመናዊውን ሥልጣኔ ለመቀበል መጀመሪያ መቀበያ ስብእናችንን እናጠናክር ነው የምለው...... ባህላችንን - ልማዳችንን ወጋችንን፥ ቅርሳችንን እንመርምር...... መርምረን ያገኘነውን ይዘን ያላገኘውን እንፈልግ - አለዚያ ነፍስ እድነ ተለየችው ሥጋ ሆነን ብንቀርብ በመዘውር የሚሄድ ስብእና ነው የምናተርፈው ነው የምንለው.....

«በመዘውር የሚሄድ ስብእና አሉ.......?! ይገርምዎታል ስለዚህ ነገር - እፈረንሳይ አገር በነበርኩበትም ሆነ ባሁኑ ጊዜ ብዙ በመዘውር የሚሄዱ ሰዎች ዐውቃለሁ። አንዳንዶቹ ከሀገራቸው በልጅነታቸው ወጥተው በሰው አገር የኖሩ፥ የሀገራቸውንም ሆነ የሰውን ሀገር ስብእና ያልሆኑ ግንጥል ነገሮች ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ በአንድ አሳዳጊ ሳይረጉ ይቆዩና የረጋ መንፈስ የሌላቸው የናት ያባት የዘመድን፥ ፍቅር ያልጠገቡ ቅዥቅዥ ያሉ ነገሮች ናቸው......

«ጨዋታዎን አላቋርጠዎና አንድ በጣም ሀብታም የሆኑ፥ ወዳጄ ልጅ አለ አዲስ አበባ......» ጣልቃ ይገባሉ አቶ ጥሶ «ታዲያ የመጀመሪያይቱ አሳዳጊው ብዙ ያገራችንን ቋንቋ የምትችል ሴት ነበረች አሉ - ከዚያ ደሞ ኢጣልያዊት አሳዳጊ ተለወጠችለት ይሉኛል - ከዚያ ደግሞ ፈረንሳዊት - ከዚያ ደግሞ እንግሊዛዊት....... በመጨረሻ ጀርመን አገር ላኩት ይሉኛል...... አሁን ተምሮ ተምሮ ሲመለስ ጭንቅላቱ ትልቅ ማሰሮ አህሎ አንገቱ ሰልስሎ ከወደ ኋላው ደሞ ሾላካ ሆኖ...... ምን አለፋዎ ብቻ

ሳይጠየቅ መናገር የጀመረ እንደሁ እጁን ማወዛወዝና አለ ምክንያት ምላሱን መጐልጐ ሆኖ ሥራው ተቀምጧል እልዎታለሁ...... አሁን ቢቸግራቸው የጅ ሥራ ያስተምሩታል ይሉኛል ዘመዶቹ.....

«ያንዳንድ ሰዎች ስሕተት መቼም ሁሉንም መርገሚያ ሊሆን አይገባውም...... ከሆነም ግን እንዴት ያሉ ይመስልዎታል እርስዎ አቶ ወልዱ በእኛ ምዕራባውያን ሥልጣኔ ተቀበሉ በምንባለው ወጣቶች ላይ የሚነገሩት አጉል ነገሮች......

«......አንዳንዶቹን እጠቅስልሃለሁ..... ለማስታወስ ያህል...... ለምሳሌ - ወላጆችን የመድፈር ሃይማኖትን የማፍረስ ሥልጣንን የመናቅ ሁናቴዎች ይታይባቸዋል ይሏችኋል..... ከቤተ ሰቦቻቸው ራቁ አጉል የገለልተኝነት መንፈስና ኑሮ ፈጠሩ ይሏችኋል..... ብዙ ጊዜ በማይቆዩ ከልዩ ልዩ ምዕራብና ምሥራቅ ሀገሮች በተጠራቀሙ መምህራን ስለሚመሩ ውጤታቸው የማያጓጓ ሆነ፤ እንደ እስስት ይለዋወጣሉ፤ ቋሚ ሐሳብ የላቸውም ጐደሎ ስብእና ነው መደምደሚያቸው ይሏችኋል...... አንዳንድ መምህራን ብዙ ጊዜ የማገልገል ዕድልም ቢሰጣቸው የቀለም፥ ትምህርት እንጂ የሕይወት መርሕ የሚሆን አዲስ ትውልድ የሚፈጥር ትምህርት ስላልሰጧቸው የሚያስተማምኑ ዜጋዎች አልወጣቸውም ይሏችኋል...... የተማሩት ትምህርት በጠቅላላው የዱሮውን ትውልድ ጠቃሚ ነገሮች ከማይጠቅሙት የማይለይ በማይጠቅሙት የሚጠቅሙ ለመተካት ያልቻለ ነው ይሏችኋል......

«እሺ፥ እርስዎስ ምን ይሉናል.......?

«አይ የኔ አይከፋም..... እኔ በመቻቻል ተፈጥሮ የማምን ሰው ነኝ.....

«እኮ ምን ይሉናል.......?

«እስከዚህ የእናንተ ሁኔታ አሳሳቢ አይመስለኝም፥ እኔ ስመለከተው። - ምዕራባዊ ሥልጣኔ ያላችሁ በሌላቸው ስትዋጡ እዱሮው ቦታችሁ ትመለሳላችሁ። - ከትምህርት ቤት ያገኛችሁትም አንዳንድ እምነት ቢኖር በሥራ ላይ ስትሠማሩ እንደማይጠቅማችሁ ስትረዱት ትተውታላችሁ ብዬ ነው የማስበው..... የኛ የኛ እንኳን ጓደኞች ስንቶቹ ነበሩ ‹ነፃነት እኩልነት ወንድማማችነት› እያሉ የሚፎከሩ። - ሀብት ሹመት፥ ትልቅነት፥ ሲያገኙ ደሞ መዝሙራቸውን ለውጠው ሰምተናቸዋ..... እና የእናንተ ሁኔታ እስከዚህ የሚያሰጋ አይመስለኝም....... እንዲያውም በትምህርት ቤታችሁ እንደ ፈለጋአችሁ በመዝሙርም በጽሑፍም በሥዕልም በልፍለፋም የፈለጋችሁትን እየተናገራችሁ ቢወጣላችሁ ነው የሚሻል የሚመስለኝ.....

«ቅድም እንዳሉት ግን እናንተ በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የሚሰማችሁ ፍላት፥ ለዘጠና በመቶው ኢትዮጵያ ሕዝብ ሙቀት ይሰጣል ተብሎ መውጣት የለበትም...... ቀስ በቀስ እስካጤነው ድረስ የሚበጀው ድንቁርናው ነው.....

« ‹ወጣቱ ፈላስማ› እሚል ዩንቨርስቲ ቅጥር ግቢ እተነበበ ግጥም ውስጥ እንዳለው ዓይነት ነው ማለት ሐሳብዎ.......?» ይጠይቃል አደፍርስ። -

« ‹ወጣቱ ፈላስማ› የሚል? ትዝም አይለኝ....... ብቻ ዩንቨርስቲ ውስጥ የሚነበቡት ግጥሞች ቅድም እንዳልኩህ ፍላት የሚስማቸው ስለሆኑ፥ እምብዛም ለኔ ለውጪው ጆሮ አይጥሙኝም.......

«ሳይሰሙት!....... ይስሙት እንጂ....

‹ድሃ ድህነቱን ከምትረግረው

ያንጀት በሽታውን ከምታሰማው

ለምን በተማርከው አትደግፈውም

ቅዠት ሆነህበት ከሚያጣ ሰላም.....

ቂጣን መተናነቅ ዶዮ መዛቅን

አሹቅን መከርተፍ ቆሎ መቃምን

በሽታ ነው እያልክ በሽታ አትስጠው

ስትነግረው ነውና ሆዱን የሚያመው.....» እያለ የተደረደረ ነውኮ! በፍላት የተጻፈ ይመስልዎታል ታዲያ.......?

«ይኸ ምንም አይል፤ ብቻ ቢሆንም ግጥማችሁ እግቢያችሁ ቢቀር የሚሻል ይመስለኛል.......

«እሺ! ከትምህርት ቤት ባገኙት አስተያየት የጠና እምነት የሚኖራቸው ኢትዮጵያውያንስ የተገኙ እንደሆነ? አሻፈረኝ በዘጠና በመቶው ውስጥ አልዋጥም የሚሉ የተነሡስ እንደሆኑ? ምን ማገጃ የሚገኝለት ይመስልዎታል አቶ ወልዱ......

«......ራሳቸውን እንዳይጐዱ፥ ራሳቸውን ካላቀኑ ማቅኛ ዘዴዎች ይበጁላቸዋል አያስቸግርም.....

«ጋሼ ጥሶ፥ ባንተ አስተያየት አስተማሪዎች ለመንግሥቱም ሆነ ለሕዝቡ ያለባቸው ግዴት እንዴት ያለ ይመስልሃል.......?

«አስተማሪዎች መንግሥት የቀጠራቸው ናቸው። ራሳቸው በግል የሚያምኑበትን ሳይሆን መንግሥቱ የሚያምንበትን ማስተማር ነው ግዴታቸው። - ሥልጣኔ፥ መሻሻልም ቢሆን የነበረንም መጠበቂያ ስለሆነ አንዳች ለውጥ ሲያስፈልግ መምጣት ያለበት ከተማሩትም በኩል ቢሆን በርግጥ ተፈላጊነኡ ሲታወቅና፥ መንግሥቱም ሲቀበለው ነው እንጂ በቀለም ትምህርት ወይም በፍልስፍና በመራቀቅ የማኖር ዓለም ፈጥሮ ይጠቅመናል ከማለት አይደለም..... ኢትዮጵያም እስከ ዛሬ የተከለችው ይኸንኑ መንገድ ይመስለኛል......

«........ማናቸውም ከንውንና ጥዩቅ፥ ከታየ፥ ከተገለጸ ከታወቀ በኋላ ነበር ከመባል አይቀርም። - ስለዚህ ለሁሉም ነገር - ያለፈውን ከአለለው ከጊዜው ጥዩቅ ጋር አስተያይቶ ሙሉነቱና ጐደሎነቱን ለማመዛዘን እንኳ ቢሆን - ነበርን ማወቁ የሚበጅ ይመስላል.......» እያሉ ብድግ ይላሉ አቶ ወልዱ ከመቀመጫቸው። -

«.......ስማ አደፍርስ......» ይለጥቃሉ አቶ ጥስሎ እየተንሡ «በቴክኒክ በኢንዱስትሪ፥ በጠቅላላው በሀገር ልማት በኩል ለመራመድ፥ ሥልጣኔ ያመጣውን ጥበብ - በማስተዋል በማመዛዘንና፥ በማስላት ዓይነት መንገድ - ለመቀበል ዝግጁ ነን። - ጐን ለጐን መተያየት ማከባበሩን ወደ ኋላ መቅረት ግን አነስተኛ ግምት ማስሰጠቱን አላጣነውም........ ነገር ግን ባነጋገራችን ባካሄዳችን ባለባበሳችን በአፍአዊ ድርጊታችን ሌላን በመምሰል ብቻ ተወስኖ እንዲቀር አንሻም እኩልነታችን የኒውክለር መሣሪያ በመሥራትና ወደ ጨረቃ የሚያስኬድ እርምጃን በማፋጠን እንኳ ቢሆን። - እምብዛም ሊያጓጓን አይገባም እንዲህ ያለው ከንውን........ እንደ እጦትም ተቆጥሮ የበታችነት ስሜት ሊፈጠር አይገባውም። - በኩልነት ደረጃ እኛ ያለንባቸውንም ወደ ማሳወቅ - ኢትዮጵያዊ ጥዩቆቻችን ከምዕራባውያን ጥዩቆች ይለዩ እንጂ ያነሱ ያለመሆናቸውን ወደማሳመን ደረጃ እንዲመራን መታገል ይኖርብና - ሥልጣኔ። - የኛ የኢትዮጵያውያን ጉጉት የላቀ የመጠቀ፥ መሆን ይገባዋል - ውስጣዊውን ስብእና ወልውሎ በሚያሳይ በመፈሳዊ ጥበብ በልጽጐና በመንፈሳዊ ኀይል ጐብቶን ለመገኘት መጣጣር። - በውነት እልሃለሁ አደፍርስ አጣንም ቆረቆዝን የበታችም ሆንን ብለን ማዘን የሚገባን ይህ በውስጣችን ሲምቦለበል የኖረው መንፈሳዊ የሰብአት ሕይወት ፈሳሽ ያለ መኖር መሰናከል ይገጥመውና የደረቀ የተመጠጠለት ነው.....

# ፴፷

## አደፍርስ

ወይዘሮ አሰጋሽ ሮቢት ከወረዱበት ቀን ጀምረው ደጋመው ተጠምቀዋል በፍል ውሃው። - የሚጨመድዷቸው ሥራ ሥሮች በመጠኑ ተፍታተዋል። - ቁርጥማታቸውም ጨርሶ ባይተዋቸው እንኳ ፋታ ሰጥቷቸዋል። ሰንበት ብለው ደጋግመው ቢጠመቁ እየተሻላቸው እንደሚሄድ ተማምነውበታል። - የፀሐዩ ግለት ያካባቢው ውብቃ ያየሩ ርበቃና ክብደት ቢሆን ግን የሚያስነብታቸው አይመስልም። - በነጋ በጠባ ቁጥር - ዛሬስ ብረሪ ብረሪ ነው ያለኝ እንዳሉት አሉ። ከጠበል መልስ ስለ ነበረ ጊዜው ትራስ መሳይ ተደግፈው እመደብ ላይ ጋደም ብለዋል..... ሁለት እግሮቻቸውን እቆሬ ውስጥ ነክረው። - ሮማን ቀስ እያለች አሸት አሸት ታደርግላቸዋለች ቆጣቆጣ በልው የሚታዩትን ሥራሥሮቻቸውን - ዘቅዘቅ ያለ በመሰላት ቁጥር፥ ከጠበሉ ዕቃ ወደ ቆሬው እያፈለቀች ፍል ውሃውን። - እምድጃው ላይ የባርማሽላ እሸት ይፍለቀለቃል በማሰሮ - ቲስ ቲስ በማድረግ እሳቱን እያነቀረ። -

«ምንድነው ይኸ እሸታችሁ አሁንም አልበሰለም? » ይጠይቃሉ ወይዘሮ አሰጋሽ።

«ትንሽ ቀርቶታል» ትመልሳለች አገልጋያቸው - አንድ ራስ ታወጣና ሁለት ሦስት ፍሬዎች ፈንቀል ፈንቀል አድርጋ በመቅመስ። -

«ባይሆን ያመነ ያመነውን አውጪው እሥር እሥሩ ያለው ሳይገባው አይቀርም......

# ፴፱

## አደፍርስ

ጐርፉና ጺወኔ ወደ ጅረት ወርደዋል። - ባካባቢው የሚገኘውን የሸንኮራ አገዳ የሙዝ የትርንጐ የብርቱካን የሎሚ የትምባሆ ተክል እየዟዟሩ የመለከታሉ።

የሮቢ ፀሐይ ያለ ወትሮው ያንገበግባል እራስን ፈጥርቆ እየገባ። - በየመዓዘኑ ሲንተገተግ ርግብግብግብግብ ሲል ሲያውት አየሩ ላይ ረግቶ ሲያበቃ የተቆረሰ በመውረድ ላይ ያለ ነው የሚመስለው - እየተግረገረገ። ዙሪያ መሬቱም እንዲሁ

በረሞጫ በሱፉጭና በባልጩት ይርገበገባል። - እግርን በመሞልቀቅ እየሰነጠረ ገብቶ ርግብግቢት ድረስ ሲያጠኸይ ነው የሚሰማው። - በረገጡት ቁጥር።

ጐርፉና ጺወኔን ቢሆን እምብዛም የተሰማቸው አይመስልም። - ጐርፉ ትናንሽ ድንጋዮች በማንሣት እየወረወረ ይዝናናል። ጺወኔ አንዲት ሎሚ ከነቀምበጧ ለመቅጠፍ ትተናነቃለች፤ እማትቆረጥበት ላይ ጠምዝዛ አልሰበር ብላት። - ጐርፉ ውርወራውን አቁሞ ራመድ ራመድ ብሎ ይጠጋትና እሷ፥ ለመቅጠፍ ከምትተናነቀው የተሻለውን ሎሚ ቀጥፎ ይሰጣታል። - ምንም ያህል አይነጋገሩም። - ቀስ እያሉ ወደ ፍል ውሃው ቦታ ያመራሉ።

«ያስከፋሁሽ ነገር እንዳለኮ ብትነግሪኝ....... አጥፍቼ ይሆናል....... ከሰው መች ጥፋት ይጠፋል አልሽው?» ሲፈራ ሲቸር መናገር ይጀምራል ጐርፉ -

ድንገት ፊቷ ቦግ ይልና «ማስከፋት?! ማንን ማነው የሚያስከፋው........?» ትጠይቀዋለች ጺወኔ። -

«ኋላ ምን ይሏል? ይኸው ሮቢ ከመጣን ጀምሮ እንደ ማንተዋወቅ ዓይነት ነው የሆነው...... ስም ትይኛለሽ! ለወትሮው ዝምታ አትወጂ...... እኔ ነበርሁ ባይሆን ዱዳው......

«ያንተ ነገር!» እጁን ያዝ ታደርገዋለች፤ እንደ ዘበት።

«ምናልባት ያደፍርስ አለመምጣት ቅር አሰኝቶሽ እንደሁ...... መቼስ ሚካኤል ምስክሬ ነው፤ እኔ ቀርቼ እሱ ቢመጣ ፈቃዴ ነበር....

ቶሎ እጁን ለቀቅ ታደርግና «ጨዋታ ያውቃል አደፍርስ....... ምን ቢጫወት ጨዋታ አያልቅበትም!» ትናገራለች አርቃ እየተመለከተች -

«አዎ፥ ጥሩ ልጅ ነው» ይመልሳል ጐርፉ። -

«ሁኔታው ሁሉ ደሞ እንደ ከተማ ሰው አይምሰልህ...... ይገርምሃል......» ትቀጥላለች።

«የከተማ ሰው ሁናቴ ምናባቴ ዐውቄ እኔ!»

«አዎ፥ እንደናቴ ልጅ አምኜው የትም ልሄድ እችላለሁ ከሱ ጋር......

«አይ ቁም ነገር የሚያጣ አይመስልም.......

«ይገርምሃልኮ፥ አሁን አንተ አለህ አይደለም...... አብሮ አደጌ በጣም ዐውቅህ ይመስለኛል መቼም......

«እንዴታ ምን ጥርጥር አለው፤ ታውቂያለሽ እንጂ በጣም......

«አዎ የማውቅህን አንተን እንኳን የሱን ያህል አላምንህም.....

«ምን ታረጊው! ጊዜው አላስተማመነም..... በዛሬው ጊዜ ከጐን ነው ጠላት የሚወጣ......

«እሱን ማለቴ ሳይሆን አሁን ለምሳሌ አንድ ቤት ውስጥ ብቻየን....... ማለቴ...... ሌላ ሰው ሳይኖር..... ካንተ ጋር ብቻ..... አንድ ቤት ውስጥ አላድርም......

«እኔም አላድር ካልሽስ.......!

«አንተ ደሞ ለምን አታድርም.......? እኔስ ሴት ስለሆንሁ አልደር አቅም ስለሌለኝ.......

«እኔም ደሞ ወንድ ስለሆንሁ......

«ውሽታም ነህ...... አሁን እውነት......

«አላድርም አልኩሽ.....

«እኔ ግን ካደፍርስ ጋር........ እምልህ......

«ብታድሪ ግዴለሽም.....

«ባድር ግዴለኝም......

«አይ፥ ለጥሩነቱ ጥሩ ልጅ ነው......

ለትንሽ ጊዜ ምንም ያህል አይነጋገሩም። የየራሳቸውን ሐሳብ የሚያውጠነጥኑ ይመስላሉ። - ከፊለፊታቸው ወደ ደሴ እሚወስደው ድልድይ ሥር......... ደስታ በተሞላበት ሁኔታ ይምቦጫረቃሉ፥ ያዳል ልጃገረዶች እውሃው ውስጥ ራቁታቸውን ቁጭ ቁጭ ብለው...... ካለፍ አገደም ውሃውን በጃቸው እየዘገኑ፥ ራሳቸው ላይ ፈሰስ ፈሰስ በማድረግ። - እንዲያ ርቀው ቅባት እንደ ጠገበ ቅቤ ቅል ሲያበራና ሲያብለጨለጭ ይታያል ሰውነታቸው......... ከውሃው ጥብርብር ጋር ፉክክር የያዘ ይመስል። -

ጐርፉ ጺወኔን ድንገት ቀረብ ይላትና «ጺወኔ!» ይላታል። - በጣም ያስጨነቀውን የስሜት እንፋሎት ለመተንፈስ የቸኮለ ይመስል። - ጺወኔ መለስ ትል ታየውና ትቀጥላለች ርምጃዋን «አቅሜ በሚፈቅድልኝ ዓይነት እጠብቅሻለሁ....... አቅሜ፥ በሚፈቅድልኝ.......! አቅሜ.......» ይቀጥላል። -

«ምነው እስከዚህ የተጠራጠርኩህ መሰለህ? ያደፍርስን ያህል አላምንህም ስላልኩህ!» ትላለች ጺወኔ ቆም ብላ መለስ በማለት። - በመቀጠልም እየሄደች «......የለም ውሸቴን ነው፤ አብሮ አደጌ፥ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ካንተ የበለጠ የማምነው ማን ሊኖር ብለህ......

«እንጋባ አንችና እኔ!» ቦግና ቅዝቅዝ ባለ አንደበት ይናገራል አደፍርስ - እንደ ድንገተኛ የሙብረቅ ተግታ። - ጺወኔ ዓይኗ ይጐርጥና ዘወር፥ - መልከት - መለስ ብላ ከቀድሞው በፈጠነ ርምጃ ትመነጠቃለች። -

«.......አዳል ሲባሉ ያው አዳል ናቸው፤ ተመልሰው ቅቢያቸውን ሊነክሩ ይኸ ሁሉ ብቅ ጥልቅ። - ደሞኮ አሽት አሽት አያደርጉትም - ምን አደከማቸው ግን....... እውነት እንው፤ ጠረናቸው እንደሁ አይለወጥ...... ደሞ ያ ጸጉራቸው! እንኳን ውሃ ጥይት የማይበሳው...... ዶቃቸውንስ መቼ ያወልቁታል። - ወምበርቲያቸውንም እንደ ታጠቁ ይሆናል ይኸነዜ....... የቅጭልጭላቸውስ ብዛት..... ምናባቱንስና..... አንድ ሦስት ወር እረግጣለሁ እዚህ መጥቼ...... ወታደርነትም ኑሮ ነው፤ አምስት አለቃ አሥር አለቃ...... ሹመትም አላጣ...... አናት በስቶ የሚገባው ደሞ የዛሬ ፀሐይ...... አረሞጫውስ እንዴት ያቃጥላል። - ይኸኔ እዚያ ማዶ እንዷያ ጥቁር ድንጊያ የመሰለችው ራቁቷን የተኛች አዳል ነች......» ብዞቱ ያናውዝ ያተራምሰዋል ጐርፉን ያለ ወትሮው። -

## ፴

## አደፍርስ

እፍል ውሃው ሲደርሱ አንድ ወንድና አንድ ሴት ሲጠመቁ ያገኛሉ። - አንድ ደግሞ ሌላ ሽማግሌ ሰውዬ ራቅ ብለው ልብሳቸውን ጭፍ ጭፍ ያደርጋሉ።

«የማዬን ልብስ አጥብልሻለሁ ስልት የሰማሁ መስሎኝ ነበር.......!» ትላለች ጺወኔ እንደ ዘበት «እኔም ልብሴ ውሃ ውሃ ቢሸተኝ አልጠላ......» መለስ ትልና ወዳረፉበት ጐጆ እሚወስደው መንገድ ትገባለች። - ጐርፉ ፍራት ፍራት ባለው እርምጃ ቀስ እያለ ኋላ ኋላዋ ይከተላታል።

«......እግሬ ምን መስሏል? ያዳል ጫማዬ ደሞ መንጋደዱ...... እጄስ ቢሆን ምን እጅነት አለው ሞያሌ ያዶለዶመው ይመስል...... ስታብኛለች ማለት ነው ያንለት፤ አፌን ከፍቼ ተረት ሳወራ ለዚያ ለከተማ ጮሌ...... እንደ ንክር ባላገር ገምታኛለች ማለት ነው...... ልብ እንደ ሌለው...... አሞቱ እንደ ፈሰሰ...... እንደ ዝምባም ባላገር...... እንደ ሞያሊያም..... እንደ ፈለጋም...... እንደ ፎከታም ባላገር..... ለሷ፥ ጒርፉ፥ የተጣመመ ያዳል ጫማ ያደረገ ነው...... ቁጭ ብሎ እንዳሮጊት ሴት ተረት የሚያወራ......በጠመንጃው...... በሞፈሩ......ባዳል ዘመቻው አልዋለበትም በሷ፥ ቤት....... ዋይ ነዶ....... ብቻ ቀረ ነገር....... አንግቻት ነበር ዛሬ አገሬ የምገባው - ደርሶ የማላቅበትን ልዝብ ንግግር...... የከተማ ሰው ይደልላት በልዝብ ንግግሩ...... እኔ ብሆን በጒልዳፋው ሥራዬ አሳያታለሁ.......» ይታገላል፥ ጒርፉ ከኅሊናው ጋር።

ጺወኔ ዝም ብላ ትገሠግሣለች። ድካሟ ገና አልታወቃትም - አረሞጫውና የባልጩት እንትግትግ ባናቷ ከሚገባው የጠራራ ፀሐይ ግለት ጋር እየተፋጨ ዓይኖቿን ማስዋኘት ጀምሯቸዋል ግን፤ ቀኟም ግራዋም ፊቷም ኋላዋም በውሃ የተጥለቀለቀ ሆኗል....... የምትራመድም...... የምትሮጥም...... የምትከንፍም...... የምትዋኝም - የተኛችም ይመስላታል። - እሴት ትደርሳለች። - ቁጭ ትላለች። ትድረስ አትድረስ ቁጭ ትበል አትበል ግን አልታወቃትም። ባናቷ ላይ ውሃ ያፈሱባትና ትንሽ ያርገፈግፏታል። -

ጒርፉ ፈቅ ብሎ ተቀምጦ ሁኔታዋን ይመለከት ነበርና ጺወኔ ራሷን ስትገዛና ዓይኖቿ በደንብ ሲገለጡ መጀሪያ የምታየው እሱኑ ነው፤ ዓይን ለዓይን ግጥም ይላሉ። - ፊቷ ቅጭም ይላል። - ዓይኖቿንም ጨፈን ጨፈን እንደ ማድረግ ብላ ትከድናቸዋለች። - ከሸክና ውሃ ቀድቶ ይይዝና ጠጋ ይላታል «አንዳንድ ጒደሎ ቀን...... ምን አሰኘንና ወጣን ይባል እንደ ዘበት...... የቀን ጒደሎ ማለት እንደ ዛሬው ያለው ነው......» ይጀምራል ቀስ ይልና «እኔስ ብሆን ከየት አመጣሁት ይባል ምላሱን...... ምናባቴ ያናግር እንደ ነዛብኝ አላውቅም ደሞኮ......! ይገርማልኮ እባካችሁ?! ከወዴት አመጣሁት ልበል እንግዲህ......

«እባክህን ተወኝ ይበቃሃል........» ትላለች ጺወኔ ቀስ ብላ።

«አልጠጣሁ..... አልሰከርሁ...... ከየቴ አመጣሁት ይባላል.......?»

«ምነው ብትተወው.......!

«እጡብጡብ የሚያሰኝ ነገር ነው...... ራስን የሚያጠራጥር........» ይቀጥላል ጒርፉ። - ጺወኔ እግሯ ሥር ወድቆ የነበረውን የሎሚ ቀምበጥ ታነሣና ብድግ ብላ

ወደ ውጪ ትወጣለች። - ጕርፉ ይከተላታል። - ቀስ ብሎ ለራሱ የሚናገር ዓይነት «እውነት ይመስል እስቲ......» በሰሚ ፍለጋ ጉልህነት «እውነት በሆነ ደሞኮ!» እያለ። - እጐጆዋ ዙሪያ የምትገኘውን ያጋም ሽምጥ ወጥተው ይኼዳሉ። -

## ፵፩

## አደፍርስ

«.......ደሞኮ እውነት በሆነ..... እውነት በሆነ!» ይደጋግማል የተናገረውን ኋላ ኋላዋ እየተከተለን ጕርፉ። -

«ካፍ ከወጣ አፋፍ፥ እውነት ሆነ አልሆነ......

«እርሺው አልኩሽ...... ለሚካኤል ብለሽ...... እርሸው.......!

«እውነት በሆነ ብሎ አነጋገር! ምነው አሁን ይልቅ ብትተውኝ.......

«እኔ ሳላውቅ ልቤ ተመኝቶ ይሆናል....... ሚካኤል ምስክሬ ነው........ ግን እውነት አይደለም......

በመገረም ዓይነት ራሷን ቀና ታደርግና «ውሸትነቱ እንዴት ነው?» ብላ ትጠይቀዋለች....... በዚያ ከዚህ ቀደም ባንዘረዘረው፥ የውስጡን በሚፈለፍል አሰያየቷ ታጠምድና። -

«አዎ እውነቴን ነው እርሸው.......! አትቆጪ...... የማይሳሳት የለም...... ራሴን ዘንጋ አድርጌ ነው...... በፀሐዩ ግለት ምክንያት ነፍሴን ረስቼ.......

«በፀሐዩ ግለት ምክንያት ነፍስህን ረስተህ!» ድንገት ቀለሟ ልውጥ ዓይኖቿ ድብዝዝ ይላሉ። -

«አልተቆጣሽም ታዲያ እንዲያው?! ረስተሽዋል ማለት ነው? ረስተሽዋል! አልረሳሽውም?» ይደጋግማል ጥያቄዎቹን ጕርፉ ጐንበስ እያለ የጐደለውን እየተመለከታት። -

«አሁንስ አበዛኸው! ምንድነው የምትለው? ምን ትፈልጋለህ ከኔ?» ቁጣነቱ በሚታወቅ የዝግታ ድምፅ ትጠይቀዋለች። - «......የምትለው ነገር ሁሉ ጨርሶ አይገባኝም....... ምኑን ነው የምረሳው? ርሺው ብሎ ነገር......!» እንደ መንጠራራት ብላ ስትራመድ ቀምበጡ ከእጅዋ ይወድቃል። - አታነሣውም «ደግሞስ እኔ ምንቸገረኝ......

ደስ ይበልህ...... ልብም አልለው....... እርሽው ብሎ ነገር!!» ጉንበስ ብላ ክትክታ ትቆርጥና ጥርሷን እንደምትፍቅ ዓይነት በጥርሶቿ ነከስ ነከስ አድርጋ መልሳ ትጠለዋለች። - የሎሚውንም ቀምበጥ የክትክታውንም ግንጣይ ከመሬት ያነሣል ጉርፉ። - እንደ ገና ድንገት የተቆጣችበት ምክንያቱም ባይገባው ያስቆጣበት ነገር በርግጥ ያለ ስለ መሰለው ተደናግጧል -

«...... ምን አባቴ ይብጀኝ...... ምን ብያት ይሆን ደሞ? ምን ተናግሪያት ይሆን ሳላውቅ......?» ሲያሰላስል በጎሊናው፥ ሎሚውንና ክትክታውን እጁ ላይ ያየዋል «በዚህ ይሆናል የተናደደችው፤ እሥር እሥሯ እየተከተልሁ የጣለችውን ሁሉ በማንሣቴ......

«ቤቴ መመለሴ ነው!» ትናገራለች ጺወኔ ድንገት ወደ ቤቷ ወደማይወስዳት መንገድ በመግባት። - ካንጀቷ እየዳመነ የሚነሣ ነገር ጉሮሮዋን ያፍናታል። - ለመቆጣጠርም የማትችለው እንባ ፈንቅሎ የሚመጣባት ይመስላታል። -

## ፵፪

## አደፍርስ

«.......መንገዱን ተሳስተሻል........ ይኸኛው መንገድ ይቀርብሻል...... እሱኛው ቅድም ወደነበርንበት ቦታ ነው የሚመልስሽ» ይላታል ጉርፉ እየተከታተለ። - ጺወኔ ቢሆን በሩጫና ርምጃ ቅልቅል ትጣደፋለች..... ፊት ፊቷን እያየች። - መለስ እንኳን አትልም። - ባጉልና በተጠመዛዘዘ መንገድ ሄደው አረፉበት ጉጀ አጠገብ ሲደርሱ ነው፥ ዘወር እንደ ማለት ብላ..........

«ቀጣፊ...... ውሸታም..... አታላይ.......» በማለት ግማሹ ተውጦ ግማሹ በሚነገር ድምፅ መናገር የምትጀምረው። -

«ያጠፋሁትንኮ ባውቀው........?

«ከየት አነሣኸው ደሞ እሱን ቀምበጥ......» ትለዋለች ትቀጥልና እጅ እጁን እየተመለከተች። -

«ቀምበጥ? ቀምበጥ.......?

«እሱን እጅህ ላይ የያዝከውን...... ውሸት ነው በል እሱንም.....

«ከየት አነሣሁት...... አንቺ ስትጥይው ነው ያነሣሁት...... ከመንገድ ላይ......

«ማን አንሣ አለህ? ውሸታም ከሆንህ....... ለምን አነሣኸው.......?

«ለምን አነሣሁት? ለምን አነሣሁት?! አነሣሁታ! ለምን አነሣዋለሁ....... ጣልሽው፤ አነሣሁት......ሳላስብ ነው ያነሣሁት.......

«እረግዲያ........ሳታስብ ነው ያነሣኸው......

«እንዴ?! ለምን ጣልሽው አንቺስ......

«ከጄ አመለጠኝ እኔማ......

«ሆን ብለሽ ነው የጣልሽው፥ ተናደሽ.......!

«ስለዚህ አንተ ተናድጄ፥ ስለጣሁት አነሣኸው.......

«አዎ አነሣሁት.......!

«መናደዴ ደስ ብሎህ አነሣኸው.......!

«የምን ብቀታ ነው እንግዲህ......! እሺ በመናደድሽ ደስ አለኝ፥ አነሣሁት..... ምንድነው ታዲያ..... አጥፍቼ እንደሁ......

«እኔ በመናደዴ ደስ አለህ........!

«በመናደድሽ ሳይሆን........ መቼስ ይኸው ሚካኤል ምስክሬ ነው....... ብቻ ቀምበጡን አነሣሁት...... እና ደሞ ሮጥሽብኝ...... ልሰጥሽ ነበር መልሼ........

«እኮ እኔ በመናደዴ.......

«በመናደድሽ አይደለም.......! እንዴት ብዬ ልንገርሽ...... እ...... እ...... አዎ ስላናደድሁሽ ነው ደስ ያለኝ......!

«ስላናደድኸኝ.......?!

«በርግጥ ስትቆጪ ስላየሁ......

«በርግጥ ስቆጣ.......

«ለወትሮው ሳናድድሽ ትስቂብኛለሽ.......!

«ቀድሞ ምን አልከኝና እናደዳለሁ.......

«ያልኩት እውነት አይደለም....... እውነት አይደለም እያልኩ ስለደጋገምኩብሽ.......!

«ታዲያ እኔ ምን ያናደደኛል........ አንተ ስለዋሸህ........ ደግሞስ እውነት ያይዶለው ምንድነው? እኔ እንደሁ ትዝም አይለኝ......

«ተናደድሽ.......!

«ስለዚህ ደስ አለህ.......

ፊቱ ላይ ብርሃን ያበራበታል «አዎን ደስ አለኝ........!

«ለምን ደስ ይልሃል.......?

«አልነግርም......!

«አትነግረኝም.......?!

«አልነግርም......!

አረፋበት ጐጆ ጥግ ገደማ ቁጭ ትላለች «እኔም አልፈልግም...... እንድትነግረኝ አልፈልግም....... አልፈልግም.....!

«ውሸትህን ነው.......!

«ውሸትህን ነው.......!

«ውሸቴን ነው......

«ውሸቴን ነው? ውሸቴን ነው?» ብድግ ትላለች ከተቀመጠችበት «ውሸቴን ነው.......?!

«የምን ውሸት ነው ደሞ! እውነታችሁም እውነት እውነት አይል እንኳን ውሸት ተናግራችሁ.......» ይላሉ ወይዘሮ አሰጋሽ ጐጆዋ ውስጥ ጋደም እንዳሉ «ጺወኔ...... ጺወኔ! አቅራቢያሽ እንዳለ ጕርፉን ጥሪልኝ እባክሽ....... ውሸት ብሎ ነገር....... ውሸቱን ሌላ ጊዜ ታረጊዋለሽ......

## ፶፫

## አደፍርስ

በማግሥቱ ማታ ጕርፉ የደረሰበት ይጠፋል። ጠመንጃና ዝናሩን ቢሆን አልወሰደም። ምናልባት አዳል ጠልፋው እንደ ሆነ በማለት በጣም ሰግተዋል፥ ወይዘሮ

አሰጋሽ። የሮቢትን ከተማ ጣቢያ አዛዥ የኀምሳ አለቃ ፖሊስ አረፉበት ቦታ ድረስ አስጠርተው ስጋታቸውን ይገልጻሉ

«ምን እንደነካው አላዋቅም - ከጺወኔ ጋር እጅረት ወርዶ ሲመለስ አስጠራሁትና ቀሚስና ኩታዬን ጭፍ ጭፍ አድርግልኝ ብዬው ይዞ ወጣ...... እኛ ደሞ ምን ይነካው ብለን...... እስከ ከብት መግቢያ ድረስ ጠበቅነው፤ ሳይመጣ ቀረ። - ቢቸግረኝ፥ ይኸን ያረፍኩበትን ሰውዬ አስቸገርኩና እጅረት ቢወርድ ያው እንደስሙት......

«ልብስዎ እንደ ተሰጣ ነው የተገኘው......

«አዎ መቼም ወጉ ደርሶታል......

«ምን ማለትዎ ነው፥ ወጉ ደርሶታል...... ቅር ያለወት ነገር እንዳለኮ ቢነግሩኝ......

«ምን ቅር ይለኛል? ምንም ቅር የሚለኝ ነገር የለ......

«ቅር ያለወትስ ነገር ያለ ይመስለኛል......

«አይ ባቦልዎ ምን ቅር የሚል ነገር አለኝ ብለው..... እንዲያው ብቻ አይፍረድ ነው፤ ምን ሲያቀብጠኝ እሱን እንደላኩሁ አላአውቅም...... ወይኮ ደሞ ልብሴንም በደንብ ባጠበው፤ እንዶዱ እንኳን ጨርሶ አለቀቀም.....

«ቶሎ ቶሎ ጐረፍ ጐረፍ አድርጎ ይሆናል ያወጣው.....

«ነከር ነከር አድርጎ ማለትዎ ነው ደሞ እርስዎ......? እንዲያው ምን ይሆናሊ አሳይዎት ነበር...... አሁን ሮማን ነች እንደ ገና መከራዋን አይታ የልብስ መልክ የሰጠችው....... ከብት ያኘከው ነበር አስመስሎ ያሰጣው......

«እንዲያው ምናልባት እስኪደርቅለት ቁጭ እንዳለ፥ ሳትታሰብ አደጋ ጥላበት ይሆን.......? በዚህ ወራት ደሞ አስግታለች፤ እንዲህ አልፎ አልፎ አደጋ እየጣለች......

«ምናባቴ ዐውቄ እንግዲህ....... ቢሆንስ ታዲያ እንዴት አንድ ምልክት ይጠፋል...... እንደ ልብስም....... እንደ ደምም...... የሆነው ይሁን ብቻ...... አንድ ነገር.....

«የልብሱን ይብሉኚ....... የደሙ እንኳ በምን ያስታውቃል፤ ያውሬውም የምኑም...... ይታያል አልፎ አልፎ በየመንገዱ.......

«ቢሆንስ እንዴት ትኩስና የሰነበተ ደም አያስታውቅም..... እግዚአብሔር ብቻ ከመዐቱ ያውጣኝ...... ምን ይለኝ ቀኛዝማችስ፤ አንድ ልጁን አምጥቼ እንደ ዋለ ሳስቀርበት...... ምን ይለኝ, ምን ይለኝ...... ምን ይለኝ.......!!

«እንዲህ በቀላሉ የሚጠቃ አይመስለኝም ልጁስ.....

«ያውቁታል ማለት ነው ጐርፉን......?» ትጠይቃለች ጺወኔ ንግግራቸውን ስትዳምጥ ትቆይና። -

«እንዴታ! በጣም ዐውቀዋለሁ። - አንድ ሁለት ጊዜ አብረን ወርደናል ወደ ቆላው...... አልፎ አልፎኮ መጎነታተሏ አልቀረም አዳል......

«ነጭ ለባሽ ነኝ ብሎኛል፤ አንድ ቀን እንዲሁ ስላዳል ጉስጐሳ ሲያጫውተኝ.....

«አወን ነጭ ለባሽ ከሆነ ቆይቷል። - እና ታዲያ የዋዛ ልጅ አይደለም፤ ጥንቁቅም ነው በጣም....... ራሱን አይጥልም.....

«አይ..... እባክዎን ያምሳ አለቃ! ዋናው ነገር ብቻ አለመቀደም ነው......

«እኮ! አይቀደምም ነውኮ የምለው...... እጀውሃ ጅረት ወርዶ የሚያንቀላፋ አይመስለኝም......

«ሰውኮ ተጠንቅቆ ሲወጣ ነው...... እንዲህም እንዲያም ለማለት የሚቻለው። - እሱ ለራሱ መሣሪያውን አልያዘ...... የኔን ቀሚስ ብቻ ነው ጠቅልሎ የወጣው.....

«ቢሆንም ሌላው ቢቀር ወምበርቲውን ከወገቡ የሚለይ አይመስለኝም.....

«አይ ወምበርቲውንስ ታጥቋል...... እሱን ከወገቡ ለይቶም አያውቅ.......» ትናገራለች ጺወኔ። -

«ለሁሉም እንግዲህ ዛሬ መቼም መሽቷል - ነገ ነጭ ለባሽም ከኛም ወታደሮች አደርግና ማለዳ ጀምሬ ፍለጋውን እቀጥላለሁ.....

«አይርሱኝ ያምሳ አለቃ! አይርሱኝ......! ከዚህ ማጃ ያውጣት በሉኝ.......!

«ግዴለዎትም፤ እስከዚህ የሚያሰጋ አይደለም ልጁ...... በዚያ ላይ ደሞ አገሬው ይወደዋል። - ጐርፉ ልብ ሽፍታ ጐስጓሹ ሁሉ ነው፥ መሣሪያውን ጎትቶ ከየሥርቻው የሚነሣው.....

«እግዚአብሔር ያውጣት በሉኝ ብቻ...... ዋናው ነገር እሱ ነው..... እሱ ሲለው ነው ሁሉም የሚሆነው....

«እግዚአብሔር መቼም ሥራችንን ያቃናው እንጂ፥ የተቻለንን እናደርጋለን.....

## ፵

# አደፍርስ

«.......ገና ለገና ሳታጤነው ቀርተህ ስላልተሰማህ፥ በዱሮውና በዛሬው ተጠየቅ ልጠይቅህ ሙግት መካከል ለውጥ የለም አትበለኝ.......» ተቋቁመዋል አቶ ጥሶ አደፍርስን፤ እንደ ወትሮው ከራት በኋላ ጠለላ ወጥተው ቁጭ በለው። -

«ካለ እንግዲያው ለኔ አልታየኝም። - ነገ የሚሰቀለው ገዳይ ለምሳሌ በኔ፥ አስተያየት...... በሽተኛ እንጂ ወንጀለኛ አይደለም...... እና...... ይኸ ለውጥ የምትለው ነገር......

«የትየለሌ! ለውጥስ ለውጥ ነው.......? የዛሬውና የዱሮው ተጠየቅ ልጠይቅህ! ደሞ ምንና ምን ወንድሜ.......! አንተ ልጅ ነህ፥ አልደረስህበትም እንጂ...... ለውጥስ አለ አደፍርስ...... አለ ለውጥስ....... እንዲህ ነበር...... እንዲህ ነበር የዱሮው ተጠየቅ ልጠይቅ.....

‹ጊደሬ ጠፍታ ተደጋ

እኔ መጥቼ በፍለጋ

ከደጅህ አገኘሁ ሙዳ ሥጋ

ያደርግሃል ባለ ዕዳ........› በማለት ያቀርባል ከሳሽ። -

‹ጊደር ብትጠፋ ተደጋ

አንተም ብትመጣ በፍለጋ

እደጅም ቢገኝ ሙዳ ሥጋ

ተቤቱ በታች ትልቅ መንገድ

ቀን ሠራዊት ሌት አራዊት የሚያሳልፍ፥

ተቤቴ በላይ ትልቅ ወርካ

አሞራና አውሬ የሚያሽካካ -

አሞራና አራዊት ሲጣለፉ

ሙዳ ሥጋ ቢተፋ

ከደጀም ቢገኝ ሙዳው ሥጋ

አያደርገኝም ባለ ዕዳ› ሲል ይመልስለታል ተከሳሽ.....

«ይኸ ታዲያ ግሩም አይደለም እንዴ! እንዴት ነው ደስ የሚለው.....

«ደስ የሚል ነገር ሁሉ እውነትን አያስገኝም አደፍርስ...... የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው እውነተኛ ፍትሕ ነው። - አለ ዚያ እርስቱ ንብረቱ ሃይማኖቱ ዋጋ የላቸውም....... እርስቱን አራሙቻ ቢገማሽርበት ንብረቱን ወዳጅ ጠላት ቢሠርግበት በሃይማኖቱ ገሀነመ እሳት......... ሲያል ቢገባ - ግዴለውም። - እውነትን አጣሁ ብሎ ካመነበት ጊዜ ጀምሮ እስኪሞላለት ነው እንጂ የሚጠብቀው ኑሮው ኑሮ አይደለም። - እውነትን ያገኘለት ግን እውነትን ያሳጣውን ሰው በመግደል እንኳ ቢሆን - ወዲያውኑ ሕይወቱን ቢያጣ ግዴለውም። - ትክክለኛ ፍትሕን እንደ ዘለዓለማዊ ሕይወት አጉል ፍርድን - እንደ ዕድሜ ልክ ገሀነመ እሳት ነው የሚቆረው......

«ታዲያ እውነትህን ያሳጣውን ሰው በመግደል እውነትን ያገኘ ይመስልሃል እንዴ ጋሼ ጥሶ.......?

«አንተ ምን ይመስልሃል.........?

«እኔ ሰውዬውን በመግደል ውሸትን ዘለዓለማዊነት የሰጠው ነው የሚመስለኝ......

«ውሸትን ዘለዓለማዊነት የሰጠው ነው የሚመስልህ......

«ሰውዬውን ገደለው እንጂ ውሸትን አልገደለው.....

«ምነው ሰውዬው ሲሞት አድራጐቱ ሁሉ አብሮ የሚሞት አይመስልህም.......?

«አድራጐቱ አይሞትም፤ እንዲያውም ዘለዓለማዊነት ነው የሚያገኘው.....

«ዘለዓለማአዊነት ስትል ምን ማለትህ ነው........?

«የማይሞት ማለቴ ነው......

«ሰውዬው በሕይወት መኖር አለበት ማለትህ ነው እውነትን ከውሸት ለመለየት.......?

«እውነትን ለማኖር ውሸትን ለመግደል ሰውዬው በሕይወት መገኘት አለበት........

«እውነት የምትለው በሰውዬው በአእምሮው ውስጥ ያለውን ነው ወይስ ባንጓለለው በኅሊናው ውስጥ ያለውን........?

«በሁለቱም ውስጥ ያለውን ነው........!

«እሺ፥ በሁለቱም ውስጥ ያለው ውሸት ነው ብለህ ያመንክበት የሆነስ እንደሁ........?

«ድንቁርና ከዕውቀት! እንዲያማ ከሆነ ሰውዬውን መግደልን አንድ ሕፃን ልጅን እንደ መግደል ያህል ነው የምንቆጥረው......

«ምን ማለትህ ይሆን........?

«ምንም የማያውቅ ደንቆሮ ነው ማለት ነው ሰውዬው...... ካለማወቁ የተነሣ ነው ማለት ነው እውነትን በውሸት የሚለውጠው...... በውነት በውነት ጋሼ ጥሶ እንዲህ ያለውን ሰው የሚገድል በኔ በኩል የመጨረሻ ትልቅ ወንጀለኛ የምለው ነው.......

«እሺ፥ እንዲህ ከሆነ እንግዲያው እውነትን ለማግኘት፥ አይቻልም ማለት ነው......?

«እንዴት አይቻልም ይቻላል እንጂ.......!

«ሰውዬው እውነትና ውሸትን ያልለየው በድንቁርናው ምክንያት ከሆነ እንዴት አድርገህ እውነትን እንዲያውቅ ልታደርገው ትችላለህ........?

«በማስተማር.......!

«አንተ እውነት ነው ብለህ የምታምንበትን ማለት ነው......?

«አዎ ለጊዜው ሁኔታው ባህሉ አካባቢው እውነት ነው ብሎ የሚገምተውን......

«ዘለዓለማዊ እወንት የለም ማለት ነው እንግዲህ እንደዚህ ከሆነ......

«ምናልባት በሳይንስ ጥበብ በኩል ሊኖር ይችላል.....

«በኅብረተ ሰብአዊ ኑሮ ውስጥ ግን ሊኖር አይችልም......?

«ላይኖር ይችል ይሆናል......

«እንግዲህ እውነት እውነት ውሸት ውሸት፥ የሚባሉት ነገሮች እንዳካባቢው ሁኔታ ይለዋወጣሉ ማለት ነው.....

«አዎ ይለዋወጣሉ.....

«እውነትም ሆነ ውሸት የሚኖሩት ርሁኔታው እባህሉ፥ አካባቢው ውስጥ ነው.....

«ይመስለኛል......

«ስለዚህ ሰውዬውን በመግደል ውሸትን ዘለዓለማዊነት አልሰጠኸውም ማለት ነው...... ሰውዬውን በመግደል ጊዜያው እንፋሎትህን አስወጣህ። የምትፈልገውን ዓይነት እውነት ግን ኅብረተ ሰቡን አስተምረህ ልታገኘው ትችላለህ ማለት ነው፤ ማለት ከሰውዬው ጋር አይሞትም......

«ጋሼ ጥሶ! ዛሬስ ክርክርህ የልከራከር ፍላጐት ይመስላል..... በዚህ አስተሳሰብህ፥ እውነትን አጣሁ የሚል ሰው፥ እውነት ያሳጣውን ሰው በመግደሉ ትስማማለህ ማለት ነው........?

«መስማማት አለመስማማቴ ሌላ ነገር ነው....... እውነትን ውሸት ያደረገብህን ሰው በመግደልህ ውሸትን ዘለዓለማዊነት ትሰጠዋለህ የሚለውን አስተሳሰብህን ግን አልተቀበልሁትም.....

«ብዙ ትክክልና እውነት ነው ብዬ ያመንኩበትን ነገር አናወጥህብኝ........

«ዓለምን የያዛት አብዛኛው የምታምንበት ነገር ከሰው የመነጨ በመሆኑ ታምናለህ? ማለቴ የምናምንበት አብዛኛው ነገር ራሳችን የፍጠርነው አይመስልህም.......?

«አብዛኛው? አዎ፥ ከሰው አእምሮ የመነጨ ነው.....

«እውነትና ውሸትም በኛው በሰዎች የተፈጠሩ ናቸው ማለት ነው......

«መሆን አለባቸው........! ማለቴ በጠቅላላው መላ ምት ከተስማማን.....

«እኛው የፈጠርናቸው በኛ ውስጥ ይኖራሉ......

«በሌላም ውስጥ እንዲኖሩ እንጥራለን......

«በኛው በሰዎች ውስጥ ማለት ነው.....

«አዎ በሰዎች ውስጥ.....

«እኛ ሰዎች ደግሞ ስንጠፋ ምናልባት የፈጠርነው ፈጠራ ሁሉ ይጠፋ ይሆናል...... ከኛ የተሻለ ፍጥረት ተነሥቶ ካልቀጠለበት......

«ምናልባት......

«ውሸት ወይ እውነት ብለህ የምታምንበት ነገር በውስጥህ አለ.....

«አዎን አለ......

«ቢያጤነውም ባያጤነውም - እውነትን በውሸት ለወጠ እምትለው ሰው ውስጥም አለ.....

«መኖር አለበት.....

«ያንዱ እምነትና እውነት በዚያ ባንዱ ላይ ተወስኖ ከቀረ ሰውዬው ሲሞት እምነትና እውነቱም አብሮ ይሞታል ማለት ነው.....

«አዎ እምነትና እውነት ተከታይ ይፈልጋል - ዕድሜ የሚሰጠው.....

«እውነት ብለህ ያሰብከውን በውሸት ቢለውጥብህም፥ ለጊዜው ባመንክበት ነገር የገባ ሰው ነበር.....

«አዎን ነበር.....

«እውነት ወይም ውሸትህ ሌላ አንድ ተከታይ አፍርቶ ነበር....

«እርግጥ ነው ይኸ መቼም.....

«አንተ ግን አንተ የመሰለህን እውነት ስላላወጣልህ ገደልከው........

«እኔኮ በመግደል አልተስማማሁም.....

«ገብቶኛል፥ ገብቶኛል ለነገሩ ያህል ማለቴ ነው.....

«እሺ ገደልኩት......

«ታዲያ ምን ይመስልሃል! ውሸትም ሆነ እውነት እንደ ገና ባንተው ብቻ ተወስኖ ቀረ ማለት ነው..... ዞረህ ዞረህ ደከመህ ደከመህ እጀመርከበት ተመለስህ ማለት ነው........ ቋቱ ጠብ አላለም......

«ስለዚህ ውሸትን ገደልከው.......

«እውነትንም ጭምር ገደልከው........ ማለት አንተ እውነት ብለህ ያመንክበትን - በጠባብ ደረት፥ ባጭር ቁመት - ባንተ በራስህ ዕድሜ ብቻ ወሰንከው........

«ስለዚህ.......

«ስለዚህ እውነትህ እምነት መሆኑ ቀረ...... ዘለዓለማዊነቱን አጣ......

«ሞትና ሕይወት!! ጋሼ ጥሶ የባሰ ሐሳቤን ሁሉ አዘበራረቅብህኝ........ ፊት የተነጋገርንበትን ሳሰላስል ሌላ ነገር ደግሞ አምጥተህ ደንቀርህበት በሐሳቤ......... በሌላ ጊዜ ብንነጋገርበት? ይልቅ እስቲ አሁን ሌላ የዱሮ ሙግት ብትነግረኝ....... እንደ ቅድሙ ዓይነት........

«የዱሮ የነገር አካሄድ...... መቼስ በጊዜው ሠርቷል.......... እኛ የነሱ እንደሚያስቀን ምናልባት በአፀደ ነፍስ ቆመው ያዳምጡን እንደሁ፥ የኛም ምንኛ ያስቃቸው.......

«እኮ ታዲያ አንድ ተጠየቅ - ልጠይቅህ........?

« ‹......እኔ ባርኮ......

መጣሁ እኮ

እንደ ውሃ ስፈስ

እንደ ጋጃ ስነፍስ፥

ሚስቴ ገባር

በቅሎዬ ሰጋ......» ይለዋል አንደኛው። -

አንተ ባርኮ

ብትመጣ እኮ፥

እንደ ውሃ ብትፈስ

አስቀድድሃለሁ ፈሰስ፤

እንደ ጋጃ ብትነፍስ

አሳጭድሃለሁ ለፈረስ፤

እንደ ጋጃ ብትነፍስ

አሳጭድሃለሁ ለፈረስ፤

ሚስትህ ብትገብር

ቤቷን ታሳድር -

በቅሎህ ብትሰግር

እመሸበት ታድር!› ይመልስለታል ደሞ ሌላው። - የዱሮው የዱሮ ስለሆነ አይናቅም...... የዛሬውም የዛሬ ስለሆነ አያስፈነድቅም አያከበስብስም...... ሁሉንም በየፈርጁ ተመልክቶ እንደሚበጅ ዓይነት አስተካክሎ መያዙ ይሻላል - አደፍርስ........

## ፶፫

## አደፍርስ

ሰኞና ሐሙስ የመንዝና ይፋት ገበያተኞች የሚያገናኙባቸው ቀኖች ናቸው። ካለፍ አገደም አንዳንድ ወንጀለኞችም ሲፈረድባቸው ግርፍም ሆነ ስቅላት የሚፈጸምባቸው በነዚሁ ቀኖች ነው።

ዛሬ ሐሙስ ነው። አንድ ቀን ቀደም ብሎ ቁመቱ ከሩቁ የሚታይ ረጅም መስቀያ እገበያው መካከል ገደማ ተዘጋጅቷል፤ በረጃጅም የባሕር ዛፍ ግንዲላና አግዳሚ። ማነቂያው ገመድ ከቡን አሳምሮ መካከል ላይ ተንጠልጥሏል። እሥሩ፥ አንድ መሰላል፥ ከፍ ብሎ እተሠራ ቆጥ ዓይነት ርብራብ ላይ ተደግፎ ቆሟል። ፖሊሶች አቶ ጥሶና ሌሎች ዳኞች፥ እነ አቶ ወልዱና ሌሎች በከተማው የታወቁ ታላላቅ ሰዎች እነ፥ አደፍርስና ፍሬዋ፥ ተማሪዎች ሁሉ ሳይቀሩ...... የመስቀያውን ዙሪያ ከበው ይጠባበቃሉ። - ከአንድ ቅጡ ከጠፋት በአንድ ቦታ አልረጋ ብላ እየለፈለፈችና እየሸለለች ካስቸገረች እብድ ሴትዮና እፊትና እኋላ እየመጣ ከሚጮህባት ባለቤቱን ያጣ ውሻ በስተቀር አብዛኞቹ ሰዎች በየሸቀጡ ተራ ሆነው የመጡበትን ገበያ

ይገበያያሉ። - ወሬውን ለማየት ቢሆን አልፎ አልፎ ሰብሰብ ሰብሰብ ያሉት ገበያተኞች ብዛት እስከዚህም አልነበረም። -

ሰባት ሰዓት ገዳማ ገዳዩ፥ በወሕኒ ቤት ዘበኞች ታጅቦ ይመጣል። በተለይ አንዱ ዘበኛ የገዳዩ እርምጃ ቀረት ባለ ቁጥር እየገፈተረ ስለ ነበረ አመጣጡ «ኃይለ ሥላሴ ይሙት በለቀቅ ኖሮ አንተን ደሞ ነበር የጥይት ራት የማደርግህ.......» እያለ ሲዝት ይሰማል ገዳዩ። - እመስቀያውማ አጠገብ ሲደርስ ያዝ እንደ ማድረግ ብሎ ወደ ሕዝቡ መካከል ሊገፈትረው ሲል ሳይታሰብ ገዳዩ በኃይል ቢመነጭቀው፥ ዘበኛው ተውተርትሮ ባፍ ጢሙ ተደፍቶ ነበር።

ሰባት ሰዓት ተኩል ሲሆን፥ ጉዳዩ የሠራው ወንጀል የተዘረበትና በስቅላት እንዲቀጣ የተፈረደበት የፍርድ ማስፈጸሚያ ግልባጭ ተነቦ ሲያልቅ፥ እብዲቱ ሴትዮ ሽለላዋ ጨርሶ አላቋርጥ ይላል

«አውልቀው ወንድሜ

አውልቀው ሱሪህን ምን ያደርግልሃል

ስንት አዕላፍ ሴት ውስጥ አንቀው ይገድሉሃል» እያለች ታድረቀርቀዋለች፤

«ያባቴ አገር -

ወንዜ ተራራዬ የሚሉት ምንድነው?

ንዴቱ፥ ብሶቱ፥ ጥቃቱ ካልገባው!» እያከታተለች በረጅሙ በማንቆርቆር። -

ገዳዩን፥ ባጉል፥ ዓይነት አኳኋን ጥብቅ አድርጐ የፊጥኝ አሥሮ እርብራቡ ላይ ያወጣዋል፤ ባፍ ጢሙ ሊደፋ የነበረው ዘበኛ። - ዘበኛና ገዳይም ርብራቡን እንደ ረገጡ ገዳይ ዘራፍ ብሎ በመጀመር እያንጠረጠረው ይፎክራል

«ዐዋዲ ገዳይ

ቆሬ ላይ ገዳይ

ራሳ ገዳይ...... ዘራፍ...... ዘራፍ...... ዘራፍ - ኮምጫጫው - ኮምጫጫው....... ዘራፍ...... ዘራፍ...... ዘራፍ......

እብዲቱ ትሽልላለች

«ወንድሙን ሲገድሉት -

ወንድሙን ሲገድሉት ወንድሙን ካልከፋው፥

አቅርቡለት ልብሱን

የወንድሙን ሱሪ ደሙ እንዲከረፋው.......

ገዳይ ፉከራውን ይቀጥላል፤ በሞቀ፥ በደመቀ በጋለና ልቡ ውጪ ወጥቶ ይምቦገቦግ በሚመስል ስግምግምታ......

«ዘራፍ...... ዘራፍ...... ዘራፍ..... ዘራፍ.....

ራሳ ገዳይ -

ማፉድ ላይ ገዳይ -

ጀውሃ ገዳይ....... ጀውሃ ገዳይ..... ዘራፍ....... ዘራፍ...... ዘራፍ...... እዚህ ላይ ገዳይ......!!» ዘበኛውን በርግጫ አሽቀንጥሮ እመሬት ይፈጠፍጠዋል «ደብረ ሲና ላይ...... እጉባዬ ላይ...... እጉባኤ ላይ...... ጠላቱን ገዳይ.......» ድምፁ ጭርስ ወደ ማለቱ ይቃረብና ጸጥ ይላል። - ድንገት እሳቱ ጠፍቶ አመዱ ብቻ ተከምሮ መክሰም የጀመሩ ሁለት ፍሞች እንደተዳፈኑበት ምድጃ። - ጭንቅላቱን እገመዱ ውስጥ ግራና ቀኝ አስታኮ ያገባና ርብራቡን ለቅቆ በገዛ እጁ ይንጠለጠላል። - እመሬት የተዘረረው ዘበኛ ንቅንቅ ሳይል ይቀራል...... እብዲቱ ትሸልላለች......

«አውልቀው ወንድሜ

አውልቀው ሱሪህን ምን ያደርግልሃል

ስንት አዕላፍ ሴት ውስጥ አንቀው ይገድሉሃል......

## ፵፯

## አደፍርስ

አቶ ጥሶ «የብዙ ሰው ጥፋት የአንድ ሰው ወንጀል ይሆናል ያልታደለ ሰው የሚቀጣበት......» እያሉ ከአቶ ወልዱና ከሥራ ጓደኞቻቸው ጋር እያወሩ ከገበያው ወጥተው ወደ ፍርድ ቤቱ አቅጣጫ ያመራሉ «.......ስለዚህ ስሕተት ሲደረግ ገና ለገና አያገባኝም ብሎ የሚያልፍ ሰው፥ ራሱ ዋና ስሕተተኛ ነው፤ ማለቴ በትንሽም ነገር እንኳን ቢሆን.....

«እኔኮ ደሞ በጣም የገረመኝ የሰው ግዴሌሽነት..... ባንድ እፍኝ ሽምብራ አንድ አንጓ አገዳ፥ ባንድ ጭብጥ ጥጥ ላንድ ፍል የምትሆን ቡና..... ዝም ብሎ ገበያ ገበያውን ብቻ....... ትንሽም ዘበኛውን ገፍትሮ ሲጥልና ሲገድለው አዲስ ነገር ሆኖበት ሰብሰብ አለ እንጂኮ ከመጤፍም አልቆጠረን.......» የሥራ ጓደኛቸው የተሰማቸውን ስሜት ይገልጻሉ......

«.......እንደዚህ ያለው ሁናቴ ለነሱ እንደሚተነፍሱት አየር ሆኗል፤ ጨርሶ አይሰማቸውም....... ወደ ተስፋ ማድረግም ሆነ ወደ ተስፋ መቁረጥ ወደ ደስታም ሆነ ወደ ሐዘን ወደ ማመንም ሆነ ወደ መካድ አይገፋፋቸውም። - ራሳቸውንም ሆነ ሀገራቸውን እዙሪያቸው በየእለቱ ከሚያጋጥማቸው ድርጊት ዝባዝንኬና ዝብዝብ ለይተው የመገንዘብ ችሎታ የላቸውም....... እኛን ነው የሚሰማን። - ሌላው ቀርቶ ለብዙ ጊዜ በመደጋገም ያየነው ድርጊት እንኳ ቢሆን እንደ አዲስ ነገር ሆኖ ሳያንብሰለስለንና የሴት ሰደድ ሳያስነሣብን የሚያልፈው...... እንደዚህ እንደ ዛሬው ዓይነት በየጊዜው የምናየው ግዳጃችንን የምንፈጽምበት ሁኔታ እንኳ ቢሆን...... የብዙ ጊዜ ቅሬታ አሳድሮብን ይቆያል......» ያብራራሉ አቶ ጥሶ።

«ታዲያ እንዲህ ከሆነማ መስቀሉስ መግረፉስ ምን ይበጃል? የመንግሥቱ ጥረትኮ ባንዱ ቅጣት ሌላው እንዲማር ነው እንጂ እንግዲያማ እንደ ኢትዮጵያ ላለ ሠላሳ ሚሊዎን እንኳን ላልሞላ ሕዝብ ያንድ ሰው እንኳን ሞት ቢሆን ሳይጐዳ ቀርቶ አይደለም.......» አቶ ወልዱ ሐሳባቸውን ያቀርባሉ።

«ዛሬ ለምሳሌ ሕዝቡ ከቅጣቱ ምን የተማረ ይመስልቆታል.......?» ይጠይቃሉ አቶ ጥሶ።

«ምን ይታወቃል?! ስሪን ይታጠቋል እንዲያ ነው......! እናት ወለድሁ ትበል....... ሥርግ እንጂ ሞት አይባልም...... ወንድ፥ ወንድን ያስንቃል...... እውነትም ኮምጫጫ፥ ጥርጥር የሌለው........ ሲሉ ነበር የምሰማው.........

«እኮ ታዲያ ይኸ አባባል ምን ፈር ይሰጥዎታል? ስለ ሕዝቡ አስተሳሰብ......» ይጠይቃሉ ደግመው።

«መቼም የስሜት ጉዳይ ስለሆነ የጠየቁኝ...... ወንዱም እንደ ገዳዩ ዓይነት ገዳይ ቢወጣው...... ሴቷም ወይ በጋብቻ ወይ በእናትነት እንዲህ ያለው ወንድ ወገን ለመሆን የፈለጉ ነው የመስለኝ......

«.......እኔም እንግዲያው እንዲያ ነው የመስለኝ...... ሌላው ቀርቶ ካንዳንድ ሰዎች ዓይን ሲረግፍ ያየሁት እንባ እንኳ፥ የደስታና የፍንደቃ ዓይነት ነበር....... ሳቅ

ጠርቶ ለመታየት ያለቀሰ እንጂ ሐዘን ብሶትን ለመወጣት ያነባ አይመስልም ነበር። - ኩራት የወንድነትና የልበ ሙሉነት ስሜት ነበር በየሰዉ ፊት ሲግም የሚታየው.....

«እኮ ታዲያ ፊት ወደ ጠየቅሁት ጥያቄ ተመለስንኮ! እንደዚህ ከሆነ የጥፋተኛው መሰቀልና መገረፍ ምን ጠቀመ?

«ምንም ጥቅም የለው ብሔራዊ በሆነ መንፈስ የተመለከቱት እንደሆነ.....

«እፈረንጆቱ አገር እንደሚያደርጉት ታዲያ መስቀልና መግረፍ ቢቀር ጥሩ ይመስልዎታል.......?

«የለም የፈረንጆችንም መንገድ መከተሉ ጥሩ አይመስለኝም...... እንኳን ሞትንና ግርፋትን በእሥራት ለውጠንለት የወንጀለኛው ብዛት፥ አሁንም እሥር ቤቶቻችንን አጥለቅልቆታል.....

«እኮ ታዲያ ሌላ ምን ፈትሕ ይገኛል.......?

«የብዙ ሰው ጥፋት የአንድ ሰው ወንጀል ከመሆኑ በፊት ነቅቶ ጥፋቱን ለማረም መሞከር........ ዋናው ፈትሕ ይኸ ነው የሚመስለኝ........ ለምሳሌ ባገራችን አንዱ አንዱን የሚገድልበት ዋና ዋና ምክንያት....... ወይ እርስቱን ወይ ሚስቱን ሲቀማ....... ከድንቁርና የተነሣ  አዳሎች ለሰለባ ሲሉ የሚፈጽሙት...... ባልታሰበ ድንገተኛ አምባጓሮ ምክንያት የሚደርስ....... ችግርና መጉላላት ያጠቃውና ከችግሩ ለመውጣት ሲል በሚያደገው ጥረት ወደ ሌብነት ወይም ወደ ቀማኛነት ስለሚያመራ እግረ መንገዱን ጥፋቱን እደብቃለሁ ሲል....... ወይም አንዳንዴ በዐባይ ጠንቋይ አነሣሽነት ስለሚሆን ወንጀሉ ከመሠራቱ በፊት ለመቆጣጠር አያዳግትም ባይ ነኝ......

«እሌላውም ሀገር ቢሆንኮ ምክንያቶቹ እነዚሁ ይመስሉኛል......

«የሌላው ዓለም ግድያ እነዚህንም የያዘ ቢሆን ሌላ ሌላ በተንኮልና በምናለብኝነት የተመሠረተ አገዳደልም ይጨምራል........ እንደ መዝናኛና እንደ መጫወቻ - በተፈጥሮው ሰውን እንደ እንስሳ እንጂ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ መሆኑን በመካድ ላይ የተመሠረተ...... በአእምሮ ንክነትና በበሽተኝነት የሚፈጸም....... በግድያ ፍላጐት ብቻ በመነሳሳት ያለምክንያት የሚፈጸም ብዙ ብዙ ዓይነት ግድያ አለ.....

«ታዲያ እንግዲህ የሚገድሉበት ምክንያት ስለተቀነሰኮ የሚቾች ብዛት ያንሳል ማለት አይደለም......

«እኔም አላልኩም፤ ብቻ ግን ለመቆጣጠር ይቻላል ነው የምለው። - በኔ አስተሳሰብ አንድ ሕዝብ ወደቀ የሚባለው ፈሪሃ እግዚአብሔርን ሲያጣ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እስላምም ሆነ ክርስቲያን ወይም ሃይማኖት የሌለው በጠቅላላው እግዚአብሔርን ፈሪ ነው። - ስለዚህ እኛ በዳኝነታችን ሌላአው በፖሊስነቱ ሌላው ደግሞ ባስተዳደር በአመራሩ ኅሊናው ትክክል ነው ብሎ ለሚያስመለክተው ፍትሕ ከሠራ ገዳዩም ሆነ ሌባው ይቀነሳል እላለሁ። - በድንቁርና ለሚመጣው መባላት ትምህርትን የመሰለ መቀራረቢያ ካለ...... ሚስቱንና ሀብቱን ለተቀማው እውነተኛ ፍትሕ ከተሰጠው - ለታረዘ ለተራበ፥ ሥርቶ የሚያገኝበት ዘዴ ከተገኘለት....... በድንገተኛ አምባጓሮ ለሚገድሉት ቅነሳ፥ መጠጥ ቤቶችን የመቆጣጠሪያ ደንብ ከወጣ....... በየሥፈሩ እየዞሩ በየባላገሩ ንብረት ውስጥ እየገቡ የሚያታልሉትን ዐባይ ጠንቋዮች እየተከታተለ በሕግ የሚያስቀጣ የመደር ሽማግሌዎች ሸንጐ ከተቋቋመ - አብዛኛው ችግሯን ይቀነሳል እላለሁ......

«ጨርሶ ግን ገዳይንም ሆነ ሌባን ለማጥፋት አይቻልም...... ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል ነው። - አጉል ልማድን የፍላጐት ሁሉ መሟላት ሊያስቀረው አይችልም.......

«ጊዜ ይፈጃል እንጂ ጨርሶ ለማጥፋትም ቢሆን አይቻልም። - ዋናው መንገድ ብቻ ቅድምም ደጋግሜ እንደ ተቀስሁት የብዙዎቻችን ጥፋት ያንድ ሰው ወንጀል እስኪሆን ቸል አለ ማለትና በሕዝቡ ዘንድ አለ ብለን እይምንኮራበት ፈሪሀ እግዚአብሔር እንዳይጠፋ ቤተ እግዚአብሔር የምንትጠነክርበትን መንገድ መሻቱ ነው። -

## ፵፪

# አደፍርስ

አደፍርርና ፍሬዋ እገበያው ውስጥ ሲዟዟሩ ይቆዩና አቶ ወልዱ ቤት ጐራ ብለው ጨዋታ ይዘዋል ስለተሰቀለው ገዳይ። - ጨዋታውን እንደ ያዙ ነው እንግዲህ ዓይኑን ሌላ ነገር የሚጠልፍበት...... ባለቤቲቱ ያጠለቁትን ጨሌ ያይና ያልጠረጠረው አጉል ነገር ያየባቸው በሚያመስል አንደበት -

«ጨሌ?! በጨሌ ያመልካሉ?» ብሎ ድንገት የሚጠይቃቸው አደፍርስ ወይዘሮ ማለፊያን። - እሳቸውም ያጠያየቁ አየር የገባቸው በሚመስል ሁኔታ ፊቱን እጁን፥ ጠቅላላ ሰውነቱን ዝግ ባለ የመንፈስ ብርሃን እየደሳሰሱ -

«አዎ ልጄ አመልኻለሁ....... ሰው እንደ ውቃቢው እንዳባዜው እንደ ብጤቱ አዶል?» ብለው የሚመልሱለት። -

«ቢሆንስ እንዴት፥ እርስዎን ያህል አዛውንት በላይን ያህል የተማረ ልጅ ያደረሱ...... ምን ይጐዳዎ ነበር፥ እንዲህ ያለውን ልማድ ቢተውት?» ይናገራል በድጋሚ አደፍርስ። -

«ያስለመዱትን ነገር ወዳጄ አልተው እያለ ነዉ ወደን ነው ይመስላህል?» ይቋቋማሉ ለውዴታቸው ወይዘሮ ማለፊያም።

«ይኸነዬ አንድ ዐባይ ጠንቋይ ይሆናል አንግቱ ያለወት......

«ትግሪዋን ማለት? አዶለም ወዳጄ ትግሪዋ ያባይ ጠንቋይ ሥራ አዶለችም፤ ትግሪዋ የዘር ማንዘራችን አለኘታ ነች...... ትግሪዋ ስደተኛ ነች...... ትግሪዋ ማር የሚቆረስበትን ወተት የሚቀዳበን አገር የምትመራ እመቤት ነች....... ባሌን ልጄን ከብቶቼን ትጠብቅልኛለች፤ እንኳን ባመት አንዴ በየጁኑም ባነግታት በወደድሁ.....

«ከዘር የመጣች ጨሌ ነች ማለት ነው........?

«ቅድም አያቴ ናቸው ከትግሬ ይዘዋት የመጡት....... እና ከዚያ ቅድም አያቴ ለአያቴ አያቴ ለኔ እናት የኔ እናት ደሞ ለኔ አስተላለፈችልኝ........ ዋ የኔ ልጅ ባየሃት...... አዛኝ ነች....... ሩሩ ነች ምን ከበደችኝና ልተዋት.......?

«ይኸ ሁሉ መቸም ከፍራት የተነሣ የሚመጣ ልማድ ነው......

«ፍራት? ተሳስተሃል ልጄ! የምን ፍራት! ሰው እናቱን ይፈራል? ፍራት ታይሆን ውዴታ እንው እኔ ያለኝ ለሷ። እወዳታለሁ....... ሁሉ ዘመዶቼ ቲያልቁ የቀረችኝ እሷ ብቻ ናት......

«እምልዎ አሁን በርግጥ ያምኑባታል ማለት ነው........?

«እምነት? አንተ የደላህ እቴ....... እንደኔ ያለ ደካማ እምነትን ከየት ያገኘዋል? መነኰሳቱና ኽሳውስቱም አላገኙት....... እንደኔ ያለ ደካማ! እምነትማ በኖረኝ ከዚህ ከሚያሰቃየኝ ኡርጥማትና የሰውነት ማቃጠል ድኜ ባልነበር? ተየት ተገኝቶ ውላጅጄ? እንደዜ ወላዋይ ልብ ተፈጥሮብን......

«ታዲያ ታላመኑባት.....

«እምነትና ጥናቱን እንዲሰጠኝ ያልተሳልኩት ታቦት የለም.....

«አንተስ እምነት አለህ......?» ድንገት ትጠይቀዋለች አደፍርስን ፍሬዋ፥ ታዳምጥ ታዳምጥና።

«የምን እምነት? መቼም በጨሌ እንደማላምን ታውቂያለሽ..... ቢፈልጉ አሁን አውጥቼ ገደል እጨምርላቸዋለሁ...... ምንም እንደማታደርገኝ ሊያው ይችላሉ.....

«ምን አፍ፥ ምን አቅም አላትና ምን ብላ ትጐዳሃለች.......?

«በጨሌስ አትመን እሺ! ብቻ በምንም ይሁን እምነት አለኝ ባይ ነህ መቼም......

«እንዴታ! መጠርጠሩስ - አለኝ እንጂ በደንብ፤ እምነት አለኝ......! መቀለዱ ይሆን ባንቺ ቤት......?

«እሷን ብትጥላት እኔን ገደልሽኝ ማለት ነው...... ያለ ጥርጥር እሞታለሁ.....

«እባክዎን የበላይ እናት፥ ዶቃ ስለ ተጣለ እንዴት እርስዎ ይሞታሉ.......?

«ዶአ! ዶአ! የለም ውላጇ አልተግባባንም፤ እሷ ለኔ ዶአ አዶለችም፤ የዘር ማንዘሬ ቅሪት ነች...... ቅርሴ ነች...... አለኝ ታዬ ነች......... አዘኔን ብሶቴን ተካፋዬ ነች......

«ትገርማለህ.......» ትጀምራለች ፍሬዋ ራሷን በማዘዋወር «ብትቀበለው ባትቀበለውም ልንገርህ፤ እምነት የሚሉት ነገር ጨርሶ የለህም አንተ። - ከዚያም እብላይ ደግሞ የሚያሳዝነው እምነት የሌለህ መሆንህን እንኳን አለማወቅህ...... እምነተቢስነትህን እምነት አለኝ ብሎ ብቻ በሙሉ በመናገር ለመሸፈን መሞከርህ.......!

«ለመሆኑ አንቺን ራስሽን ልጠይቅሽ...... ስንት አገር ያዩትን ያቶ ወልዱን ባለቤት በጨሌ ሲያመልኩ ማየትሽ አልገረመሽም.......?

«መግረም! ህ! የማይጠረጠር እምነት አለኝ ባይነትህ ነው እኔንስ የገረመኝ......

«እኮ በጨሌ ሲያመልኩ......

«በጨሌ ማምለክ በጨሌ አምምለክ እያልህ ደጋግመኸዋል...... በጨሌው በርግጥ ያመልኩ አያመልኩበት እንደሁ እንዳንተም ርግጠኛ ባልሆን ምናልባትም እንዳልከው አምልኮት እናውጣቸው እንጂ ሐሳቡ ከኔም መታ ካንቺ ልዩነት የለውም........

«ነገርኩህኮ በጨሌ ያመልካሉ የምትለውን አነጋገር ስላልተቀበልሁት ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ የማድረጉ ነገር አላሳሰበኝም......

«አሁን በቅርቡ አንቺው ራስሽ የቦረንትቻ ሥጋ ካልበላሁ ብለሽ የእንዴት ያሉ አዛውንት ግብዣ ረግጠሽ አልተመለስሽም.......?

«ያ ሌላ ይኸ ሌላ......! በነገራችን ላይ የሰው ግብዣ ረግጬ አልተመለስሁም፤ አስፈቅጄ ነው። - ካመጣኸው አይቀር ግን ልንገርህ ልዩነቱን......

«ያኛው መንገድ አምልኮት ይኸኛው ጨሌ አምልኮት ነው......

«ቀልድና ለገቻ ከሆነኮ ፍላጐታችን ክርክራችንን ብንተወው ይሻላል......

«እሺ እሺ ቀጥይ ! የምን ቀልድና ለገቻ? ክርክራችንስ ደርስ ያለው ነገር ላይ ለመድረስ ነው......

«ጥሩ አንተ እንዳየኸውና እንደ ሰማኸው...... በዚያን ጊዜ እኔ ባለቦረንትኞቹን አከፍቻለሁ........?

«አላዩሽም እንጂ፥ ክፊት ሳይሆን ደስታ ነበር የሚሰማቸው........ ሠይጣኑ ባንቺ አድሮ መሥዋዕታቸውን የተቀበላቸው መስሏቸው.........

«እመየቴን ወይዘሮ አሰጋሽንም ሆነ ቤተ ሰቦቻቸውንስ አስከፍቻለሁ? ስሜታቸውን እምነታአቸውን ነክቼባቸዋለሁ........?

«የበጉ ሥጋ ከገባ በሽታው ይጨርስናል ብለው የሚያምኑትን ሰዎች አይጨርሳችሁም ብለሽ አጉዝለሽባቸዋል፤ ባታስከፊአይቸውም የነካሽባቸው ነው የሚመለኝ እምነታቸውን......

«ራሴን ለመሥዋዕትነት አሳልፌ ልስጥ አልኩ እንጂ እምነታቸውን አልነካሁም.......

«እኔም ጨሌውን ልጣልላቸው...... ጨሌይቱ የምትችል ከሆነ እኔን ትመመኝ ትግደለኝም ብዬ ራሴን ለሳቸው ሰጠሁ እንጂ እምነታቸውን አልነካሁም......

«ያንተና የኔ አቀራረብ ግን ትልቅ ልዩነት አለው..... የኔ ፍቅርና ችግራቸው በገባው ልብና አንጀት ሲሆን.......

«የኔ በድፍረትና በግዴለሽነት መንገድ ነው.....

«አዎ ባይሆንም ነው የሚመስለው......

«ይልቅ እኔን አሁን የቸገረኝ ምን እንደ ሆነ ታውቃለህ የኔ ልጅ......» ይጀምራሉ ወይዘሮ ማለፊያ ያዳምጡ ያዳምጡና «ሴት ልጅ ያለመውለዴ!! አንጀቴ ነው የሚርመሰመሰው ባሰብሁት ቁጥር......

«ምን የመሰለ ወንድ ልጅ ወልደዋል፤ ሴት ልጅ ምን ያደርግልዋል.......? ማለቴ ወንድና ሴት መውለድ የሚመኙት ነገር ነው.......? ግን እስከዚህ ካልሆነ ዘንዳ ምን የሚያስጨንቅ ነገር አለ.......?

«አላገኘሽኝም ውላጄ........! ትግሪት የወንድ ልጅ አደራ አዶለችም....... ሴት ልጅ ብትኖረኝ ሴት ልጄ ካልሆነም እግዚአብሔር ልበ ሰፊዋን ሚስት ለልጄ ቢሰጥልኝ የልጄ ሚስት ነች የምትወርሳት.......

«እሷን ማንስ ወረሳት ማ እርስዎ ከሞቱ ወዲያ ምን አስጨነቀዎት..........?

«ያያት የቅድም አያቶቼ ቅሪት የትም እንድትወድቅ አልሻም የኔ ልጅ። - እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ አንጀቴ የሚረጋባት ልጅ ይስጠኝ......

«ከእንግዲህ እንዲወልዱ ማለት.........?

«ምነው የልጄስ ሚስት ልጄ አዶለችም? ምን ፋይዳ አለው በለህ ዘጠኝ ወር አርግዞ መውለድ........ ፋይዳ የለውም.....

«ለመሆኑ አንተ በጨሌ ያመልካሉ ብለህ እንዴት ደፍረህ ትናገራለህ......?» ትጠይቀዋለች ፍሬዋ አደፍርስን የወይዘሮ ማለፊያን ፍላጐት ካዳመጠች በኋላ። -

«ለምን አልናገርም.......?» ይጠይቃታል መልሶ በመገረም - አደፍርስ። -

«እንዴት ዐወቅህ.......?

«ንግግርሽ አንዳንዴ ቆማጣ ያስሮጣል። - እዚሁ ቁጭ ብለሽ እያወራሽና እየሰማሽ እንዴት ዐወቅህ ትይኛለሽ......?

«አይ የኔን ምስክርነት ከጠየቅህ እኔ የሰማሁት በእዚአብሔር ማመናቸውን ታቦቶችን መማለዳቸውን ጨሌዋንም ካያት ከቅድም አያታቸው የመጣች ስለ ሆነች የሚወዷትና የሚያከብሯት መሆኗን ነው.......

«ይኸ ያንቺ ነገር ማሳመር የሳቸውን እምነት አይለውጠውም። - ደግሞም ከፈለግሽ በጨሌዋ ማምለክ አለማምለካቸውን ለመረዳት መልሰሽ ልትጠትይቂያቸው ትችያለሽ......

«እሳቸው ያሉት የገባኝ ሰለመሰለኝ እኔ፥ አልጠይቃቸውም......

«እኔ ያልገባኝ እንግዲያው ደግሜ፥ ልጠይቃቸው...... በጨሌ ያምናሉ አያምኑም፥ የበላይ እናት........?

«ባፌ ሙሉ አምናለሁ አልልም፤ ድፍረት ይሆንብኛ...... ሰው ስንባል በጣም ደካሞች ነን - መጣምመጣም...... እድም እንዳልሁት..... የሱ የፈጣሪ ምርጦች እንኳ ካገኙት ዓለም ነው......

«ምነው ተንሸስ ቢሆን እምነትዎን በዶቃ ላይ መጣልዎ......?

«ከመስጠም ለመዳን የሚፍጨረጨር ሰው የሚጨብተውን ነገር ውበትና አስጠሊነት አይመለከትም፥ መዳኑን ብቻ ነው የሚያስበው...... አስረዜ ዶቃ ዶቃ አትበል........» ትመልስለታለች ፍሬዋ። -

«እና፥ በዚህ አነጋገርሽ በርግጥ በጨሌዋ ያምኑባታል ማለት ነው........ ሲታመሙ የምታድናቸው መከራ ሲመጣባቸው ከመከራ የምታወጣቸው በመሆኗ ያምናሉ ማለትሽ ነው......

«ጥሩ እንዲያም ከሆነ የገባ....... አንዳንድ ጥያቄዎች ልጠይቅህ........?

«የልፈለግሽውን.......... የፈለግሽውን.......

«የሥነ ጥበብ መጽሐፍ ስታነብ፥ በኅልያህ፥ ከተጻፈው በላይ አታስብ.......?

«ተማራማሪ ከሆንሁ አስባለሁ......

«ጥሩ፥ የሥነ ጽሑፍ መጽሐፍ ስታነብ ከተጻፈው በላይ አትመለከትም....... በሐሳብህ፥ እየጨማመርህ እየጨማመርህ ያልታየ ዓለም የምታይ አይምስልህም..........?

«መጽሐፉ የሚያስደስት ከሆነ ከተጻፈው የበለጠ ሊመጣ ይችላል በአእምሮ.......

«የታሪክ የሳይንስ መጻሕፍት ስታነብ ከተተረከለት ጀግና በላይ የሆነ ሰው፥ ከተፈጠረው የሳይንስ ውጤት የበለጠ ክንውን ሊኖር እንደሚችል በኅልያህ መጥቶብህ አያውቅም........?

«ይኸ ይኸ ሁሉ የምትይው እርግጥ ነው፤ ብቻ የዚህ ሁሉ ተጠየቅ አመጣጥ ለምን እንደ ሆነ አልገባኝም......

«የሚካኤልን የገርኤልን የጊዮርጊስን ምስል ስታይ ከምስሉ የበለጡ፥ በሰማያዊ ኀይል የጐለበቱ መላእክት....... እምልህ....... በራቀ በጠለቀ ዓይነት መንገድ አይታዩህም.......?

«ድንቁርናና ዕውቀት.......! አይ እዚህ ላይ አይታዩኝም........

«እሺ፥ ግዴለም አይታዩህ። - ማንኛውንም ሥዕል ስታይ ከሮርሙና ከቀለሙ ውበት ውጪ የሆነ ልዩ ዓይነት ውበት ያየህ አይመስልህም.......?

«ያየሁ ይመስለኛ፤ ግን ላላይ እችላለሁ.......

«ታቦት ስትሳለም ለታቦቱ ነው ስግደትህ ወይስ ለእግዚአብሔር........?

«ለእግዚአብሔር ነው......

«ለምን ታዲያ፥ ለታቦት እየሰገድህ ለእግዚአብሔር ነው ትላለህ? በኀልያህ ለሚታሰብህ እንጂ በሚታይ፥ በሚጨበጥ በሚዳሰስ ነገር በሚገለጠው አለማመንህ ከታወቀ ታዲያ፥ ለምን ሰውን እምነት ቢስ ታስመስላለህ.......?

«ብለሽ ብለሽ፥ ታቦትና ጨሌን አንድ ናቸው በይኝ......!

«አንድ ናቸው አልወጣልኝም - ብቻ እኔ የምለው አንተ፥ በኀይልያህ ከታቦቱ በላይ መጥቀህ ለእግዚአብሔር ያደርህ ከሆንህ እሳቸውም ከጨሌው በላይ መጥቀው ለእግዚአብሔር ያደሩ ሊሆኑ ይችላሉ ነው...... ሥነ ጽሑፍን ሥነ ጥበብን ታሪክን ሥዕልን ቅርጻ ቅርጽን ሳይንስን አምጥቆ ሰማያዊ ጥልቀት የሚሰጠውን ኀልያ...... ጨሌን አድባርን ታቦትን ማምለክን አምጥቆ ሰማያዊ ጥልቀት የማይሰጥበት ምክንያት የለም ነው የምልህ። - ባንድ ልብ ባንድ ኀሊና የተቀበሉት እምነት እግዚአብሔር መንግሥት ያደርሳል ነው የምልህ....... ከዚህ በተረፈ ማታ እንደ ልማድህ እንግዲህ ካባዬ ጋር ልትከራከር ትችላለህ እኔ ክርክር ቶሎ ይሰለቸኛል......

«ባላውቅሽ ኖሮ በዛሬው አነጋገርሽ ከሆነ፥ ጭራሽ የመሻሻል ፍላጐት ያለሽ አትመስይኝም ነበር......

«መሻሻልን?! መሻሻሉን እርሳው እባክህ! መሻሻል ትላለህ ደግሞ ያንተን አስተያየት....... ስማኝ ልንገርህ....... አሁን አንተ እንዳረከው ዓይነት ለሰው ስሜት ለሰው እምነት ዋጋ ሳይሰጡ የሚደረገው መሻሻል ባፍንጫዬ ይውጣ...... መሻሻል.......?! ልንገርህ አንድ ነገር! ለማንም ሰው ቢሆን መጀመሪያ የሚያስፈልገው ፍቅር መግባባትና መከባበር ነው። - ስንፋቀር አንድነታችን ሲጸና ነው መሻሻል ሊገኝ የሚችለው...... ያኔ፥

መሻሻል ያላንዳች ድካም ከውስጣችን ይመነጫል። - መሻሻል ትለኛለህ ደርሶ! መጀመሪያ አንተ ራስህ ሰው ሰው መስሎ ይታይህ....... ሰው ሰው መስሎ ሲታይህና እነሱም የታየህ መሆኑን ሲረዱልህ ነው የምትለውን የሚቀበሉህ...... አለበለዚያ ግን ጥሩው ነገርህ እንኳን ይጐዳ ስለሚመስላቸው ትርፍህ ድካም ነው....... የሚሰማህ አይገኝም..... መሻሻል ትለኛለህ ደሞ........?!

«መሻሻል እስከዚህ ደካማ ናት........? እንደዚህ በመደባበስ ካልተጠበቀች በስተቀር የማትገኝ.......?

«ብትገኝም አንተ የቀየስከውን መንገድ ተከትላ አይደለም። - ፈረንጆች ገሥጋስፐች ናቸው....... ፈረንጆች ይሮጣሉ....... ፈረንጆች ይበራሉ........ ፈረንጆች በጭንቅላታቸው ወድቀው አንገታቸው አልተሰበረም......

«ያውም እጨረቃ ላይ......!» ያደናቅፋታል አደፍርስ።

«ፈረንጆች ኀይለኞች ጠንካሮች ናቸው እያልን የነሱን መንገድ ለመከተል ብንፈልግ፥ የግሥጋሤውም የሩጫውም የበረራውም ትርፍ ተደናቅፎ መደፋት ነው። - ባንገት የማረፉን መልስ እርግጠኛ ነኝ ታውቀዋለህ። -

«እኔኮ እንደ ፈረንጆች ካልሆንን መሻሻልን አናገኝም አላልኩም......

«እንግዲያው እነሱን እንዳናስተጋባ ከተስማማን ራሳችንም እነሱን ሆነን ከመቅረት ድነናል ማለት ነው...... ሌላው ነገር አይቸግርም......

«ሌላው ነገር አይቸግርም? ምን ተናገርሽና ነው ሌላው ነገር አይቸግርም........?

«አገርህን ያገርህ ሰው እንደ ባይተዋር ሳይሆን...... እወጉ እልማዱ እቅርሱ ውስጥ ገብተህ ዕወቀው። - የፈረንጆች ሐሳብ ሳይሆን የራስህ ሐሳብ ይኑርህ....... ማንኛውንም ያገርህን ችግር በራስህ ዓይን እየው....... አስብበት አውጠንጥነው። ጥሩውን ገና ለገና ሰው በወደደው አትውደደው........ መጥፎውንም ሰው ባጥላላው አታንጓለው። - መታረም እሚገባው ነገርም ቢኖር እውስጡ ሆነህ ቀስ እያልህ ንቀለው እንጂ በንዴት አትጐድፍረው..... አብዬ ሁለዜ ቀስ ብለሽ አርሚ - የሚሉ አነጋገር አለው......

«ጋሼ ጥሶ ደንበኛ የገደል ማሚቶ ወልዷል። - ሆኖም ሲበዛ ጥሩ አይደለም - እምልሽ አንዳንዴ የራስሽም አስተያየት ቢኖርሽ አይከፋ......

«ያመንሁበትና ከሰውነቴ የተዋሓደው አስተያየት ሁሉ ምን ጊዜም እንደ ራሴ ነው...... አለዚያ የራስ የሚባለው ነገር ሁሉ ዋጋ የለውም - ትርጉም የለውም......

ወይዘሮ ማለፊያ ጆሯቸውን ጭምር በጀቦነው ራስ ማሠሪያ የታሠረውን ራሳቸውን - ምንም እንኳ ከእርጅና የተነሣ አልፎ አልፎ ቢንቀጠቀጥም - ደስ የሚላቸው የሚስማሙበት ነገር በሰሙ ቁጥር - በማወዛወዝ....... አክብሮት ርኅራኄና ያለ ጭቅጭቅ የመታዘዝ ልማድ በሚታይባቸው ደብዛዛ ዓይኖቻቸው ትክ ብለው እየተመለከቱ ሲያዳምጧቸው ከቆዩ በኋላ ብድግ ብለው መሬት ደርሶ የሚከበሰበውሰውን ቀሚሳቸውን ሰብሰብ ሰብሰብ በማድረግ መቀነታቸውን እያጠባበቁ ወደ ጓዳ ይገቡና ሁለት ኩባያ እርጐ ይዘው ይመጣሉ። - ከንፈሩን ጠረግ ጠረግ በማድረግ አንዱን ኩባያ ለፍሬዋ ይሰጧታል

«አጥቤ አጥኜ ነው ያስቀመጥሁት፤ ራሴ የምጠጣበት ኩባያ ነው» ይሏታል ፍሬዋን - ኩባያውን አየት አየት አስታደርግ ሲያዩ። - ሌላውን ኩባያ ላደፍርስ ሲሰጡት -

«የለም እኔ አሁን እርጐ አልጠጣም፤ ምሳዬን አያስበላኝም........» ይላቸዋል።

«ታዲያ ምሳ እየበላህ ጠጣዋ ምሳ ላምጣ.......!»

«የለም እቤት ይጠብቁኛል......

«እባክህ የኔ ልጅ...... ምንም አይልህ፤ ባይሆን ቀመስ አርገህ ተወው...... ቆራስማ አትወድ ይሆን......?

«የለም፥ ለሱ ብዬ ሳይሆን....... በሌላ ጊዜ ይሻላል......

«የምን በሌላ ጊዜ...... በሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ ይገኛል...... ምንም አይልህ ግዴለም.......

«ይቅርብኝ፤ ቢቀርብኝ ይሻላል...... እና እንዲያውም ልሂድ መሰለኝ...... ደኅና ዋሉልኝ.....

«ደኅና ዋልልኝ! ደኅና ምሳህ ለምን ላሰናክልህ........ እውነትህን ነው.......» ወደ ፍሬዋ ጠጋ ብለው እጅዋን ያዝ በማድረግ «የኔስ ልጅ፥ አልጣፈጠሽ ይሆን......? በርበሬ መሳይ ባረግሽ.......?

«ምንም አያስፈልገው እማዬ! እንዲሁ ብቻውን ሆኖ በጣም ነው የሚጣፍጠው......

«ወደድሽልኝ? እንኳን የወደድሽልኝ.......!» እንደገና ወደ ጓዳ ይገቡና የእርጐውን ማሰሮ ይዘው ይመለሳሉ «ላንድዬ ምን ይሳነዋል! አንድዬ ያውቃል! እንዲህ እንዳንቺ ልበ ሰፊዋን ቢስጠኝ ምን ይሳነዋል........? አንድዬ ያውቃል.......

## ፵፫

# አደፍርስ

ወይዘሮ አሰጋሽ፥ በበኩላቸው ጺወኔን ሮማንን አገልጋያቸውን ጭምር አስከትለው ወደ ጅረት በመውረድ ወፍ ሳይቀምሰው በፊት እንደ ልማዳቸው በፍል ውሃው ከተነከሩ እብኋላ የሰው እግር ዱካ ያመነ ያመነበትን ስላች እየመረጡ ፍለጋቸውን ይይዛሉ። እስከ ረፋዱ አጋማሽ ድረስ ሲፈልጉ ይቆያሉ። ምንም ዓይነት ምልክትም ሆነ ሌላ ተስፋ የሚሰጥ ነገር ግን አያገኙም። - ድካም እየተጫጫናቸው ሲሄድ ስጋታቸውም እየበረታ ይሄዳል። -

«በጣም የደከመሽ መሰለኝ፤ ሰውነትሽ ሁሉ ጥውልግልግ ነው ያለው እማዬ......» ትናገራለች ጺወኔ አየት ታደርጋቸውና «አንችና እንኮዬ ወደ ቤት ብትመለሱ ይሻላል.......

«የራሽን ሰውነት ባየሽው........ ትናንት ጭርስ እንዳልሽው ዓይነት የሆንሽ ነው የምትመስይው...... ባይታወቅሽም......

«ግዴለም እማዬ ለኔ አታስቢ። - ትናንት ጠራራው ፀሐይ ነው ራሴን ያዞረኝ። - አሁን ግን እንደምታይው ፀሐይዋ ገና አናት አልደረሰችም....... ለኔ አታስቢ ግዴለሽም......

«ባቦልሽ! መቆየት ከፈለግሽ ምን እላለሁ? ብሆን እንዳልሽው ብመለስ ይሻላል....... ሻል ያለኝ ቁርጥማቴ ነው ደሞ የሚነሣው...... ቢሆንም ታዲያ እየጥላው ዐረፍ እያላችሁ....... አዎ፥ እሪያውንም እንድስቅጤውንም እየተጠነቀቃችሁ ታዲያ...... ኋላ አይሆንም.......

ትንሽ ወዲያ ወዲህ እያሉ ፍለጋውን እንደ ቀጠሉ የፀሐዩ ግለት እየተሰማቸው ስለሄደ እጥላ ዐረፍ ይላሉ ጺወኔና ሮማን። - ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆዩ ግን አከላፋ ነገር ቁቁታ ይሰማሉ፥ ከወዳረፉበት መንደር። - ደንግጠው በመነሣት፥ በሩጫና ርምጃ ቅል ቅል ወደ ቤት እሚወስደው ስላች መንገድ ይጣደፋሉ። - በዚህን ጊዜ ነው እንግዲህ ከወደ ጢሻ ውስጥ ሁለት ጐረምሶች ብቅ ብቅ ይላሉ ጺወኔን አፈፍ ጅቡን

የሚያደርጓት። - ሮማን ቀድማ ነበርና አካሄዷ መለስ ስትል ጓደኛዋን - ዱሮ በቡልኮ ተጠቅላ እሰው ጀርባ ላይ ስትፈራገጥ ትመለከታለች። - ትጮሃለች....... እንደ ቁቁታም ይከጅላታል። - ጐረምሶቹ ሁለት ጥይት ወደ ሰማይ ይተኩሱና እግሬ አውጭኝ ይላሉ። - ሮማን የምትሆነውን የምታደርገውን እንዳጣችው እገላጣና አዳጋ ሥፍራ ላይ ትደርሳለች። - ውጭ ነፍስ ግቢ ነፍስ ድንገት ኀይል ትገዛለች። - ቁቁታውን በረጅሙ ትለቀዋለች። - አንድም ሰው ግን አልደረሰላትም። - ቀድሞ የጀመረው የመንደሩ ቁቁታ ነበር የሚያስተጋባ የመሰለው - ላገሬው። - እንዳበደ እየከነፈች ቤት ስትደርስ ነው ኋላ ሁኔታው የሚታወቀው። -

አስቀድሞ ወደ መንደሩ ገደማ ቁቁታውን የጀመሩት ግን ወይዘሮ አሰጋሽ ነበሩ። ከነጺወኔ ተለይተው እቤት እንደ ደረሱ የጐርፉን ጠመንጃና ዝናር እተሰቀለበት ቢመለከቱ ስላጡት። - እንዳጋጣሚ ፖሊሶችና ነጭ ለባሾች ፈጥነው ይደርሱላቸውና ቁቁታቸው እየደከመ እየደከመ ይሂዳል..... ቀስ በቀስ ያዘው ያዘው የሚል ነገር አገር ምድሩን ለሚሞላው ጨኸት እየለቀቀ። - የተኩስ መለዋወጥ ይጀምራል። ትንሽ ቆይቶ ይፋፋማል። - ቀዬው በሙሉ ይሸበራል ላንዳፍታ። - ወዲያው ግን የሚተኮሰው ጥይት ብዛት እየቀነሰ ድምፁም እየራቀ እየራቀ ይሄዳል። - ወደ ተሲያቱ ገደማ ጭራ ሜዳ በታች እሚገኘው ሸለቆ ውስጥ ይደርሱባቸዋል ወንጀለኞቹን። - እምጥ ይግቡ ስምጥ ግን ሊያገኟቸውም ሆነ ሊይዟቸው አልቻሉም። ጐርፉና ጓደኞቹ ያመልጣሉ ለጊዜው። - ጺወኔን ቢሆን ያፍዝ ያደንግዝ የደግሙባት ይመስል ተጠቅላበት እነበረው ቡልኮ ላይ እንደ ተቀመጠች ያገኟታል። - የባሻአገሯን ስትመለከት። - እመኪና መንገድ ዳር ይባባላሉ ሁለት ቄሶች፤ በርግጫና በጡጫ - የተሰረቀችውን የማርያምን ታቦት አጠገባቸው ቁጭ አርገው። - እንኳን አርማኒያ አዲባሳም ወስደህ አትተክላት የኛን ማርያም እያለ ትንፍስ ትንፍ ይላል አንደኛው ቄስ። - ከገበያ የምትመለስ ሴት ቆም ብላ ነገራቸውን ታዳምጥና የተሸከመችውን የሸመታ እህል አውርዳ ጥላ በቦታው ታቦቷን እዝል አድርጋ ቁልቁል ትመነጠቃለች....... ወደ ተሰረቀችበት ቀበሌ «እንዴታ! የማንን ማርያም ማን ይሰርቃታል!» እያለች። - ቄሶቹ በባዶ ሜዳ ይፍረመረማሉ። -

## ፵፱

## አደፍርስ

«አይ እ.......!» ይላል ያምሳ አለቃው ለወይዘሮ አሰጋሽ ሲያወራ «ይኸው ሚካኤል ምስክሬ ነው...... የርስዎን ልጅ ለመጥለፍ ማሰቡን አጫውቶኝ ቢሆን ኖሮ.......

«እረዳው ነበር እንዳትለኝ........!!

«ወንድ ነውኮ ጐርፉ! ባለ ሱሪ ነው! ዋይ ነዶ! ምን ይሆናል ብቻ......... ሰኔና ሰኞ......

«አንድ ገዳይ ተሰቀለ አሉ ዛሬ - ደብረ ሲና የምናውቀው ሰው ይሆን....... ሰምተህ እንደሁ? አዎን አዎን....... ምንድነው የሚከነክነኝኮ ብያለሁ....... ዋናውን ነገር ረስቼው፤ ጠላ መጠጫችሁን.......» ሁለት ብር የያዘ እጃቸውን ዘርጋ አድርገው «እንካልኝ ወንድሜ......

«አፈር ልጠጣ...... ደሞ የምን ጠላ...... ደሞ የምን ጠላ......!» ሰውነቱ ልውጥውጥ ይላል ያምሳ አለቃው «አፈር ልጠጣ....... አፈር ልጠጣ!!

«ምነው ያምሳ አለቃ! ግዴታ የለብህምኮ....... እኔ በሰጠሁ ያንተ መንገሽገሽ......

«አፈር ልጠጣ አልኩዎት.......!

«የሚጥምህን የምታውቀው ራስህ ነህ...... እንዴ! አሰጋሽ ነኝኮ! ማን መሰልኩህ.......? ግዴለህም ፉከራ ፈርቶ ሀብቱን የሚበትን የለም....... ለወደፊቱ እንጠነቀቅበታለን...... ደግሞም አሰጋሽ ወንድ ብርቋ አይምሰልህ - ስንቱን ጀግና ነው የምታስረግደው። - ስንቱን ስንቱን ጀግና......

«ኧረ እባክዎ የትና የት! ወንድ ቢባል እንድ አይደለም...... ጥይት እንደ ዝናብ ሲወርድ ግምባሩን የማይመስል ነው ጐርፉ...... በራሳ ነቀልቃል.....

«እባክህ ምነው ያምባ ገነን ጨዋታህን አታምጣ የመንግሥት ወታደር ሆነህ...... የወንድ ልጅ ሙያው በልቡ ነው..... የምን ሥራ ነው ደሞ ሥራ ቤት ይመስል....... ጌታውን ተከትሎ የወረደ ሁሉ ወግ ነው ይኸ.....

«አከላፋ ሆንበቲኮ! ጀምበር ሳትጠልቅ ያገኙት ነበር የወድን ልክ......

«ለወደፊቱ እንጠነቀቅበታለን....... ፍልውሃ ብሎ ነገር...... ባፍንጫዬ ይውጣ..... በቀዬውም አታያት ሁለተኛ አሰጋሽን.....

«ምን ይሆናል ብቻ...... ቀረ........!

«አትድከምኮ አልኩህ...... ትርፍ ነገር አትናገር...... ቀማኛ አጥፉ እንጂ ቀማኛ አበረታታኮ አላሉህም ንጉሡ...... ላቶ ጥሶ ነው ወጥቼ የምነግርልህ ቆይ.....

«ቀረ ነገር...... ብቻ....... ምን ያረጋል......

«የሮቢን ዘብጥያ አብራችሁ ነው የምትገቡባት፥ አርፈህ ካልተቀመጥህ......

«እሳት ውስጥም በገባሁ...... እሳት ውስጥ እልዎታለሁ...... የልቡን አድርሶ በሆነና.....

«በሚካኤል ይዘሃለሁ....... በኃይለ ሥላሴ....... በቃህ....... ይበቃሃል......... አትናገረኝ....... አትናገረኝ.....

ጺወኔ ቡልኮውን አጣጥፋ እድብኝት ውስጥ ታስቀምጠዋለች። - የተለጠፈችበትን። -

## ፺

# አደፍርስ

የቀኑን ሁኔታ የሚያሰላስሉ ይመስል ሦስቱም በአርምሞ ይቆዩና -

«እናት ለልጅዋ መድኅኒት ስታጠጣ መጀመሪያ ራሷ መድኅኒቱን ቀምሳ ነው። አልታመመችም። - የመድኅኒትም ቀመሳ ቅንጦት የለውም። ለምን ይመስልሃል እንዲያ የምታደርገው.......?» በማለት ይጀምራሉ አቶ ጥሶ። -

«ራሷን በማታለል ልጁም የተታለለ ስለሚመስላት.......» ይመልሳል አደፍርስ ቶሎ ይነቃና። -

«የለም ራሷን አላታለለችም፤ ዐውቃ የምታደርገው ድርጊት ትሊያ ሊሆን አይችልም...... ሳታቀው ብታደርገው ነበር ራሷን አታለለች ልንል የምንችለው። - ልጁም ቢሆን፥ ተተታለለ። - መድኅኒቱ በሽታውን እንደሚያድነው ታውቃለች። - ስለዚህ ዐውቆ ያልተቀበለውን በሽታ ሳያውቅ አስወገደው እንጂ አልታለለም.....

«እናቲቱ ባትቀምሰው ኖሮ፥ ልጁ መድኅኒቱን አይጠጣም ነበር ማለት ነው፤ ወይስ እናቲቱ በመቅመሷ ልጁ የማይጥመውን መድኅኒት ይጠጣል ለማለት ነው ያሁኑ ሐሳብ.......?

«ሁለቱም ጥያቄዎችህ ለማለት የምፈልጋቸውን ጥቃቅን ነቁጦች ይዘዋል...... ለማለት ወደምፈልገው ግን በሙሉ አይመሩም። - እናቲቱ በትቀምሰውም ልጁ መጠጣቱ አይቀርም፤ ግን እየፈራ እያንገፈገፈው የተጨነቀ አንዳንዴም እያለቀሰ ነው የሚጠጣው። - እናቲቱ አስቀድማ በመቅመሷ ግን ፍራት አይኖርበትም፤ አይጨነቅም፤

አያለቅስም...... ቢያንገፈግፈውም እንኳ፥ እናቱን ስትንገፈገፍ ስላላያት ይችለዋል። - ሳትታመም ታምማ መድኀኒቱን የቀመሰችለት የናቱ ፍቅር ጥንካሬን ይሰጠዋል.......

«ሳትታመም መታመሟን ያውቀዋል ማኣልት ነው ልጁ......?

«ልጁ ምናልባት የሚያውቀው ነገር ቢኖር እንደሱ....... የታመመች መሆኗን ነው......

«ስለዚህ ታዲያ፥ በስሕተት መንገድ መራችው ማለት ነዋ......!

«አልመራችውም....... የታመመች በመምሰል ከልጅዋ ጋር ያላትን የመንፈስና የድርጊት አንድነት ገለጸች እንጂ ወደ ስሕተት መንገድ መራችው ለማለት አንችልም...... ለልጅዋ እሱ ባለበት ሁኔታ ላይ ያለች ሆና በመታየት እናታዊ ፍቅሯን ገለጸች እንጂ ወደ ስሕተት መንገድ አልመራችውም.....

«እንደምሰማውኮ አሁን፥ በአንተ አስተያየት የማልፈልገውን የማይጥመኝን ነገር ለፍቅርና መስሎ ለመታየት ስል ማድረግ የለብኝ ማለት ነው......

«ለፍቅርና እምነትን ለማትረፍ፥ አንድነትህን ለማሳየት ማድረግ ይኖርብሃል......

«ዛሬ በምሳ ሰዓት ያደረገውን ብትሰማ አባዬ......» ትናገራለች ፍሬዋ ክርክራቸውን ስታዳምጥ ትቆይና......

«ምን አደረግሁ፤ ምሳዬን አያስበላኝም አሁን እርጐ አልጠጣም ማለት ነውር ነው.......?

«የበላይ እናትኮ ናቸው...... እንዴት ይመስልሃል አባዬ፥ አንጀታቸው ቁርጥ ያለው። - ልጄ እያሉ እንዲያ ሲለምኑት ምሳዬን አያስበላኝም ብሎ እምቢ ብሏቸው ሄደ...... ደግሞ ስለጨሊያቸውስ ያመጣኸው ክርክር.....

«ጨሌ በማጥለቃቸው ተቆጥተህ ይሆናል......» አቶ ጥሶ ቀስ ብለው ይጠይቃሉ። -

«መቆጣት አንድ ቃል እንዲያውም እርጐ አልጠጣ ያለው በጨሌው ምክንያት ተቆጥቶ መስሏቸው እሳቸው.....

«ብጠጣ ኖሮ መቆጣቴ አይታወቃቸውም ማለት ነው ባንቺ ቤት......

«አይታወቃቸውም፤ ወዲያውኑ ነበር የሚረሱት.....

«.......ዛሬ የየከተማውስ ልጆች ያነግቱት የለም ጨሌውን......?» ብለው በመጠየቅ ይጀመራሉ እንደ ገና አቶ ጥሶ።

«ታዲያ እነሱ ቢያነግቱት ለጌጥ እንጂ ለአምልኮት አይደለም......» ይመልሳል አደፍርስም በጀመረው መንገድ። -

«ምን ማለትህ ነው ለአምልኮት አይደለም ስትል....... እግዚአብሔር በጌጥ በውበት አይገለጥም.......?

«ማለቴ ሣር ጐዝጉዘው ገንፎ አንገፍተው ድፍን ቡና ቆርጥመው አይማጠኑትም.......

«ምኑን ነው የማይማጠኑት.........?

«ጨሌውን!

«.......ጽዱ ለብሰው ሽቶ ተቀብተው ጨሌውን፥ በአንገታችው ብቻ ሳይሆን በጃቸውም ዙሪያ አድርገው ቤተክሲያን የሚሰሙ አላየህም......?

«ጨሌውን እንደ ጌጥ በማሠራት አድርገው ቤተክሲያን የሚስሙ አይቻለሁ.......

«ጌጣቸውን ይመስልሃል እምነታቸው ብዙ ሕዝብ ወደሚሰብበት ቤተክሲያን የሚሰባቸው.......?

«የሚሰባቸው ስትል ምን ማለትህ ነው........?

«የሚመራቸው ማለቴ ነው......

«እንግዲያው ጌጣቸውም እምነታቸውም ነው እላለሁ ወደ ቤተክሲያን የሚመራቸው.......

«በተለይ ሴቶች ጌጣቸውን ውበታቸውን ለማሳየት የሚጥሩ አይመስልህም.......?

«ያው ነው፤ ወንዶችም ቢሆኑ ይጥራሉ......

«ጥሩ ነው፤ ወንዶችም የማሳየት ፍላጐት ይኑራቸው እንበል...... አያጣላንም...... ብቻ እንግዲህ ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች የማሳየት ፍላጐት አላቸው ማለት ነው......

«አዎ፥ አላቸው.......

«.......ጌጣቸውም ወይም ውበታቸውን ወይንም ሁለቱንምን የማሳየት ፍላጐት ካላቸው ዘንድ ይህን ፍላጐታቸውን ለማርካት ሲሉ ቤተክስቲያን መሄዳቸውን ስታይ ጌጡ እነሱ ካሰቡት በላይ ዋጋ ያለው አይመስልህም.......?

«ሰው እተሰበሰበበት ቦታ እንዲሄዱ በማድረግ ቤተክሲያን ስላሳማቸው...... አዎ፥ ይኸን እንደ ዋጋ ከቆጠርከው...... ካሰቡት በላይ ሊሆን ይችላል......

«ታዲያ እነዚህ ሰዎች ጌጡን አይማጠኑትም......

«አይማጠኑትምኮ ብያለሁ.......

«ባላሰቡትም መንገድ ቢሆን ወደ እግዚአብሔር ደጅ አድርሷቸው ማለት ነው ግን.......

«አድርሷቸዋል፤ ግን የልብን የሚያውቅ አምላክ በርግጥ የሄዱበትን ስለሚያውቀው፥ እብዚህ አይደለልም......

«ቤተክሲያን እየሄዱ በሙሉ ልባቸው ገብርኤል ሚካኤል አንተ ታውቃለህ የሚሉትንም ጭምር እግዚአብሔር ይከፋባቸዋል ማለትህ ነው........?

«ለምን ይከፋባቸዋል፤ ገብርኤል ሚካኤል ማለት አምልኮ ባዕድ አይደለም.......?

«ለምን አይደለም? ቤተክሲያን ሄደው እግዚአብሔርን በማመስገን ፈንታ ገብርኤልንና ሚካኤልን ሲያመሰግኑ.......? እኔ አምላካችሁ ቀናተኛ ነኝ ብሎ የለም እንዴ.......?

«እግዚአብሔር የልባቸውን ያውቀዋል። - ከአክብሮታቸው የተነሣ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በመላእከቱ በኩል እንጂ ቀጥታ እንዳይማጠኑ ያደረጉ መሆኑን ያውቀዋል......

«ስለዚህ እግዚአብሔር በሰው ዘንድ ሙሉ ልብ መስሎ ከሚገመተው በላይ ነው...... የልብ ልብ ሕልማችንን ጥረታችንን ዓላማችንን ያውቀዋል ማለት ነው......

«አዎ ያውቀዋል......

«እግዚአብሔር ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በልጁ በየሱስ ክርስቶስ ታውቋል ብለን እናምናለን......

«አዎ፥ እናምናለን........

«በራሱ ፈቃድ፥ ሊገባን በሚችል በተወሰነ ነገር ባይገለጽ ኖሮ...... ዘመን ሳይቆጠር ዓለም ሳይፈጠር የነበረን ወደፊትም የሚኖር እግዚአብሔርን እንዲህ ነው ብለን ለመገመት ባልተቻለንም ነበር.......

«አንችልም ነበር......

«ወሰን የሌለው ሐሳብ፥ በመጠኑ በቃላት እንደሚገለጽ ሁሉ መጀመሪያና መጨረሻ የሌላው እግዚአብሔርም መጀመሪያና መጨረሻ ባለው በየሱስ ተገልጾ...... ፎርም የሌለው በፎርም ታወቀ......

«ይኸ ሁሉ እርግጥ ነው...... ማለቴ ይገባኛል......

«ጥሩ እንግዲያው....... እስካሁን ጨሌ፥ ወደ ቤተ እግዚአብሔር የሚመራ ጌጥ፥ ቤተ እግዚአብሔር ወደ እግዚአብሔር የሚመራ ቦታ በመሆኑ ተስማምተናል......

«አዎ፥ ተስማምተናል......

«የበላይ እናት፥ በጨሌ በቤተ እግዚአብሔር በእግዚአብሔር እንደሚያመልኩ ነግረውታል ብላኛለች ፍሬዋ......

«አዎ ነግረውኛል......

«ታዲያ ጨሌው በቅርብ ቤተ እግዚአብሔሩ በሩቅ ወሰን የለሹን እግዚአብሔርን ወስኖ ለማወቅ የሚያደርጉት ጥረት ላለመሆኑ ምን ማስረጃ አለህ? ደግሞስ ወሰን የሌለው እግዚአብሔር በብዙ ጥቃቅን ወሰን አለሽ ነገሮች መገለጹ ለምን እንግዳ ነገር ይሆንብሃል? እግዚአብሔር የልብ ልብን ያውቃል ብለናል...... ካወቅነው ዘንድ በጨሌው እንጂ በኔ አላመለኩም ብሎ የሚከፋው ይመስልሃል? እርግጥ እግዚአብሔር ከዘመንና ከወሰን ውጪ ነው። - ነገር ግን ለሙሴ በእሳት ምላስ ተገልጿል። - ለአብርሃም - በተራራ በግ ተመስሎ መከራና ጭንቁን አሳልፎለታል። - ለሐዋርያት ከድንግል አምርያም በመወለድ ሰው ሆኖ የሰውን ልጅ ኅጢአት ዋጅቷል - ዛሬም በዘመናችን የሰው ልጅ በሚሠራው አስደናቂ ፈጠራ እየተገለጸ እናያለን........ ስለዚህ ወሰን የሌለው እግዚአብሔር ቁጥር በሌላቸው ውሱኖች ሲገለጥ...... ወሰን ያለውና ወሰን የሌለው ፎርም ያለውና ፎርም የሌለው ሆኖ ዘለዓለማዊነቱን አጽንቶ ይኖራል.......

«ስለዚህ በጨሌ ማመንን ትደግፋለህ ማለት ነው......?

«ቆይ አስጨርሰኝ......! ስለዚህ፥ ማንኛውም ሰው እንደ ተፈጥሮ ችሎታው...... ወሰን የሌለውን ወሰን ባለው - ወይም ጣጣ ፈንጣጣ ሳያበዛ እግዚአብሔርን በወሰን የለሽነቱ የማምለክ መብቱ ያለው ይመስለኛል.......

«እኮ፥ በጨሌ ማምለክም በተወሰነ ነገር እንደ ማምለክ ስለሆነ ይደገፋል ማለት ነው......

«ባልደግፈውም አልቃወመውም። - የኔ በወሰን የለሽነቱ እግዚአብሔርን ማመን ከነሱ በውሱኑ ነገር እግዚአብሔርን ለማግኘት መሞከር ይበልጣል ወይም ይሻላል ብዬ አልናገርም......

«ካልተቃወምከው እንዴት አድርገህ ወደ ተሻለው መንገድ ልትመራቸው ትችላለህ.......?

«አንደኛ ነገር እኔን የኔው መንገድ ይሻላል አላልኩም ሁለተኛ ማንም ሰው ቢሆን ራሱ ለራሱ እንዲመራመር እንጂ የኔን መንገድ እንዲከተል አልፈልግም......

«ታዲያ እንግዲህ በዚህ ዓይነት የጥንታውያኑን አድራጐት ብቻ እያደነቅን ከተቀመጥን - እንዴት ልንሻሻል እንችላለን....... ባሁኑ ጊዜ የኛ ትግል ከዘመኑ ጋር የሚስማማውን መምረጥ ሲሆን በየጊዜው በሆነ ባልሆነ ተጠየቅ ወደ ኋላ ብንመለስ ምን ያህል የሚጨበጥ ነገር እናገኛለን.......?

«ሰማሆይ አደፍርስ! ከዘመኑ ጋር የሚስማማውንማ ሁሉ እንምረጥ ካልን ስብእናችንን ድራሹን አጠፋነው ማለት ነው። ደግሞስ ያለፈውን አልፏል በማለት ብቻ እንዴት ልንረሳው እንችላለን? ባለፈው ጊዜ እውነት የነበረ ነገር ሁሉ ዛሬው እውነት መሆኑ እንዴት ይካዳል? እውነት አያረጅም አይጠፋም አደፍርስ፤ እውነት ዘለዓለማዊ ነው። - እንኳን እውነት እውነት ያለው ሰውም አያረጅም አይሞትም...... እምነቱ እውነቱ በልጅ ልጆቹ ነቅቶ ሕያው ሆኖ ይኖራል.......

«ታዲያ ቢሆንስ እንዲያው አልባሌ ነገር ውስጥ ሁሉ ሁሌ እውነትና እምነት አሉዎይ እያልን የኋሊት በመመልከት መከራችንን ከምናይ ለምን እኛ፥ የእምነትና እውነት ትውልዶች በምናደርገው ድርጊት ሲገለጽ አይታይም........?

«.......ትናንሹን እውነት ከናቃችሁ ትላልቁን ለማክበራችሁ ምን ዋስትና ይኖረናል......? በተወሰነው ተግባራችሁ ጥሩ ነገር ካልታየ በወሰን የለሽ ሐሳባችሁ ፋይዳ ትሠራላችሁ እምነትና እውነትን ታበሥራላችሁ ብለን እንዴት ዝም ብለን እንያችሁ? ስማኝ አደፍርስ....... የእምነትና የእውነት ውጤቶች ነን ከማለት ይልቅ ከጥቃቅኑ

ድርጊታችሁ ጀምሮ የሆናችሁ መሆናችሁን የሚያሳይ ምስክር እንዲኖር ያስፈልጋል.......» እያሉ ብድግ ብለው ወደ ቤት ውስጥ ይገባሉ። - አደፍርስም ይከተላቸዋል - ተዋሥኦቱ እንዲቋረጥበት ያልፈለገ በሚመስል ሁኔታ። -

## ፵፩

## አደፍርስ

«ለመሆኑ ጋሼ ጥሶ አንድ ነገር ልጠይቅህ...... መቼም ባህላችንን ከመረመርን ጥሩ ጥሩ እውነትና እምነት ይገኝባቸዋል የሚል አስተሳሰብ ስላለህ - ምናልባት መልስ ይኖርህ ይሆናል.......» እያለ። -

«አይ፥ መልስም ባይኖረኝ እውነት ያጣሉ ብዬ አላምንም......

«እሺ የኢትዮጵያ ነገሥታት የሰሎሞን ዘሮች ናቸው በሚለው ታሪክ ትስማማለህ? ታምንበታለህ.......?

«እንዴታ...... መስማማቴን ተወውና በርግጥ አምንበታለሁ። - የሰሎሞን ዘር?! ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ለሰሎሞን ያልተገለጸ ጥበብ እንዳልነበረ አታውቅም እንዴ......?

«እኮ፥ ስለ ንግሥተ ሳባ...... ስለ ቀዳማዊ ምኒልክ....... ስለ......

«ምን አስዘረዘረህ? አትድከም፤ አምንበታለሁ ብየሃለሁ.......

«ምክንያት እንዳለህ ልትነግረኝ ትችላለህ........?

«ምክንያት? አዎ ምክንያት አላጣም.......? ለእምነት ምክንያት አያስፈልግም ብዬ ባላምን....... ብቻ በመላ ምቴ ከተስማማህ......

«መላ ምትህ ምንድን ነው........?

«ከዚህ በፊት አብዛኛው የምናምንበት ነገር በራሳችን በኛ በሰዎች የተፈጠረ ነገር ነው በሚለው ሐሳብ ተስማምተን ነበር ይመስለኛል......

«አዎ፥ ተስማምተናል......

«ዛሬ ኢትዮጵያ የምንላት ባንድ ዘመን የትልቋ ኢትዮጵያ አካል ነበረች......

«ዐውቃለሁ......

«ዛሬ ኢትዮጵያ የምንላት በተለይ የሳባ ሳብዓይ የናምሩድ ተከታይ በነበረው በኩሽ ልጅ፥ በአቢስ ስም አቢስኒያ በመባል የታወቀች ነበረች........ እስከ ቅርብ ጊዜም የምትታወቀው በዚሁ ስም ነበር.......

«ዐውቃለሁ.......

«ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የሰፊዋን ጥንታዊት ኢትዮጵያ ስም ክፍሏ የሆነችው አቢስኒያ ወረሰች.....

«እርግጥ ነው......

«ዛሬ፥ ኢትዮጵያ ከሷ በፊት ታላቅና ሰፊ ኢትዮጵያ እንደነበረች ብትዘነጋና ባትቀበል አይገርምም.....

«አይገርምም.....

«ግሪኮችም ሐዋርያትም የጻፉት ሁሉ፥ ስለ ዛሬዋ ስለ አዲሲቱ ኢትዮጵያ ቢመስላት አያስገርምም..... አያስነውርምም......

«ባለማስገረሙ እስማማለሁ፤ ግን የመላዋን ኢትዮጵያን ዝናና ታሪክ ክፍሏ የነበረችው የዛሬዋ ኢትዮጵያ መውሰዷ የሚያስነውር ይመስለኛል......

«እንዴት ያስነውራል? እግር ሄዶ፥ እጅ ሠርቶ ያተረፈውን ዝናና ታሪክ እጅና እግር አብረን እገኘነው ብለው ቢያወሩ ወይም እያንዳንዳቸው አስገኘሁ - አስገኘሁ ቢሉ ባይሆን አብሮነታቸውን በመዘንጋታቸው ይወቀሳሉ እንጂ እያንዳንዳቸው ለግቡ መድረሻ ድርሻ ድርሻቸውን ማከናወናቸውና ታሪክ ማስቀረታቸው ይካዳል.......?

«እና ትልቋ ኢትዮጵያ ስትጠፋ አካሏ የሆነችው ትንሿ አቢሲኒያ ስሟን ወረሰች...... ተገቢ መብቷ ነው የምትለኝ.......

«ትልቋ ኢትዮጵያ አካሏ በነበረችው አቢስኒያ እንደ ገና ታደሰች እንጂ ጠፋች አልወጣኝም...... የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከጥንታዊቷ ኢትዮጵያ የወረሰችው ስሟን ብቻ ሳይሆን ታሪኳን ዝናዋንም ጭምር ነው። - ከኑቢያ አንሥቶ እስከ ሕንደኬ መንግሥት ከሜሴፖታሚያ እስከ ሱዳን ግርጌ ድረስ የተዘረጋው ታሪክ የዛሬይቱም ኢትዮጵያ ጭምር ነው......... ምዳኒት ስላነሰ አያሽርም አይባልም......

«ስለዚህ የሰሎሞንና የሳባም ታሪክ የአዲሲቱም ኢትዮጵያ ታሪክ ነው የምትለኝ......

አዎን ያዲስቲቱም ኢትዮጵያ ታሪክ ነው.....

«የሶሪያም - የኑቢያም - የሱዳንም......

«አትዘርዝረው ግዴለህም...... ለማለት የፈለግኸው ገብቶኛል....... ለታሪኩ ብቁ ሆነው ከተገኙ፥ ታሪኩ፥ የዘረዘርካቸው ሀገሮችና የሌሎችም ያልዘረዘርካቸው በጥንታዊት ኢትዮጵያ ውጽጥ የተመለከቱ ሀገሮች ሁሉ ታሪክ ነው........

«ለታሪኩ ብቁ ሆኖ መገኘት ስትል ምን ማለትህ ነው.......?

«የዚያን ዓይነት ባለ ታሪኮች ነን የሚሉት እንዲህ ያእል አሳፋሪ ነገር የሚሠሩ ናቸው ከመባል ያልደረሱ ሆኖ መገኘት......

«ታዲያ እንግዲህ ለታሪኩ ብቁ ሆና የተገኘችው አዲሲቱ ኢትዮጵያ ብቻ ነች ማለት ነው........?

«በታሪኳ የማታፍርበት ኢትዮጵያ ነች አልኩ እንጂ የጥንታዊቷን ኢትዮጵያን ስም ለመውረስ ብቁ እሷ ብቻ ነች አልወጣኝም.......

«ታዲያ በጥንታዊቱ ኢትዮጵያ ታሪክ አለማፈር የጥንታዊቷን ኢትዮጵያን ታሪክ ለመውረስ በቂ ሆኖ ይገኛል.......?

«እሱንማኮ የመለስኩልህ መስሎኛል...... ስለ እጆችና እግሮች ሥራ በመጥቀስ......... ካልተደማመጥንኮ ክርክራችን ዞሮ ዞሮ፥ መዝጊያው ጭራሮ ዓይነት ይሆናል......

«አዎ አዎ፤ መልሰህልኛል....... እሺ ሌላ ጥያቄ አለኝ። - ታሪክ ስትል ምን ማለትህ ነው.......?

«የጥንታዊቷን ኢትዮጵያን ባህል - ወግ ልማድና ቅርስ ፍልስፍናና ሃይማኖት አነሣሥና ውድቀት የሚያሳይ የቃልም ሆነ የጽሑፍ ቅሪት ነው......

«እና ይኸንን ቅሪት አጥብቀን የያዝነው እኛ ብቻ ነን ነው የምትለው.......

«ሳንሆን አንቀርም ነው ያልኩት.......

«ሰሎሞንና ሳባም ከቅሪቱ ውስጥ ናቸው ነው የምትለው......

«አዎን ናቸው......

«ቀዳማዊ ምኒልክ ከሰሎሞን መወለዱ ይነገራል......

«በርግጥ.......!

«በቅሪቱ ውስጥ ነው......

«ጥርጥር የለውም......

«ስለዚህ የኢትዮጵያ ነገሥታት የሰሎሞን ዘሮች ናቸው........

«ብለን እናምናለን......

«እኔ አልቀበለውም........!

«ለምን አትቀበለውም? የምናምንበት አብዛኛው ነገር ራሳችን የፈጠርነው በመሆኑ ደጋግመን ተስማምተናል...... ስለዚህ እንኳን ታሪክ ያቆየውንና ድንገትስ ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ እንደ ሰደድ እሳት፥ የሕዝብን መንፈስ ያዳረሰ መሆኑን ከተመለከትህ አንተ ብቻ የማትቀበልበት ምን ምክንያት አለህ.......?

«የሌላው ሰው እምነት እኔን እንዳምንበት የሚገፋፋኝ ምክንያት ሊሆን አይችልም......

«አንደኛ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪክ የኛም ታሪክ ቢሆን እኔ አልቀበለውም......... ሁለተኛም አብዛኛው የምናምንበት ነገር የራሳችንም ፈጠራ ቢሆን በዚህኛው ፈጠራ አላምንም........ ኅሊናዬ አልተቀበለውም ነው የምትለው......?

«አዎን ኅሊናዬ አልተቀበለውም...... ኅሊናዬም ስላልተቀበለው እምነት ሊኖረኝ አልቻለም........

«ለምን እንደ ሆነ አላውቅም ብቻ አልተቀበለውም........

«ለመቀበል ስላልፈለግህ ነው......

«ለምን አልፈልግም......

«የባዕድ ተጽእኖ የሚገዛህ ስለሚመስልህ...... በራስህ ስለማትተማመን ስለምትፈራ...... ስለዚህ ነው ለመቀበል የማትፈልገው...... ስማኝ! እስኪ አንድ ነገር ልጠይቅህ.......?

«ጠይቀኝ፤ የምችለው ከሆነ እመልሳለሁ......

«ዘመናዊ ሥልጣኔ - እንደ ጋንዴ፥ እንደ ኬኔዲ፥ እንደ ኪንግ ያሉ የፖለቲካ መሪዎች...... እንደ የሱስ፥ እንደ ሞሐመድ እንደ ቡድን ያሉ የሃይማኖት መሪዎች....... እንደ ናፖሊዎን እንደ ደጐል ያሉ ጀነራሎች ለማፍራት እንደጣረች ነች ሁል ጊዜ......

«አዎ እንደ ጋሊሊዎ፥ እንደ ኒውተን እንደ ኤንስታይን ያሉ የሳይንስ ሊቆች..... እንደ ቤቶቨን እንደ ሞዛርትን እንደ ዮሐንስ ስትራውዝ ያሉ ሙዚቀኞች....... እንደ ሊዎናርዶ ዳቪንቺ እንደ ራፋኤል እንደ ሚካኤል አንጀሎ ያሉ ኬንያት...... እንደ ዶስቶቪስኪ እንደ ፎክነር እንደ ሼክስፒር ያሉ ደራስያን........ እንደ ፎክፌለር......

«ጥሩ ነው ጥሩ ነው........ በዘማናዊ ሥልጣኔ ዓላማ ተስማምተናል ማለት ነው። በዚህ ዓላማ ከተስማማን ዘንድ እንግዲህ ኢትዮጵያ በበኩሏ ከሆነላት እንደ ሰሎሞን ዓይነት ጠብብ መሪ ማግኘት አርማ ማድረጓ እንዴት አዲስ ነገር ሊሆንብህ ቻለ? ደግሞስ በሙሉ ልባችንና አእምሯችን ካመንንበትና ከፈለግነው ሰሎሞንን መሰል መሪ በኢትዮጵያ መሬት ላይ የማይበቅልበት ምን ምክንያት አለ.......?

«ምክንያቱን አላውቅም፤ በቅሎባት ግን አላየሁም ከዚህ በፊት......

«ተሳስተሃል እንግዲያው የኔ ልጅ...... ብዙ ጠቢባን ብፁዓን ቆራጥና፥ ኮምጫጫ የሆኑ ሰዎች በቅለውበታል ኢትዮጵያ...... እንደ ኤዛና እንደ ላሊበላ እንደ ምኒልክ ያሉ ጠቢብ መሪዎች...... እንደ ዐምደ ጺዎን እንደ ቴዎድሮስ እንደ መኰንን ያሉ የወታደር መሪዎች......

«በቅለውባት ይሆናል......

«እሺ........! የበቀሉባት ከመሰለህ ዘንድ ታዲያ፥ በርግጥ ባርማችን ካመንን ታላላቅና ብፁዓን ሰዎች የማንፈጥርበት ምን ምክንያትችን የድንገተኛ ስሜት ጉዳይና ጉንጭ አልፋ ሆኖ ከቀረ፥ በስም ብቻ መኖር፥ ለሮማውያንም ሆነ ለግሪኮች ወደ ፊትም ላሜሪካኖችና ለመስኮቦች የሚበጅ አይሆንም። - ምድር በሰው መሰል ዲያብሎሶች እንደ ተመራች ትቆያለች...... ሥጋን ወደ መርዝ በረከትን ወደ መርገም በሚለውጡ...... መሪነታቸውን በመጥፎ ተግባራቸውን ብቻ የምናውቅላቸው....... ውለታቸውን ወህኔ ቤት በመጣል የምንከፍላቸው መሪዎች። እምነታችንም መሽቶ እንደሚጠፋ ጥላ ቆይቶ እንደሚበተን አቧራ ይሆናል......

«እና አርማው ምንም ይሁን እምነታችን ነው ዋናው መሣሪያ ነው የምትለው......

«አዎ እምነታችን ነው ዋናው መሣሪያ - ዛፍ እፍሬው ውስጥ እንደሚደበቅ የምንፈልጋቸው ሰሎሞኖች ጻድቃንና ሰማዕታት - ኢትዮጵያ ፍላጐታችንና ዓላማችን ውስጥ ይደበቁ እንጂ መውጣታቸው አይቀርም.......

«መቼ ነው ታዲያ የሚወጡት? እነዚህ ሰሎሞኖች፥ ጻድቃንና ሰማዕታት........?

«አትቸኩል ይወጣሉ - ነበሩን አሉን ይኖሩናል። - ባርማችን በእምነታችን ውስጥ ስለተደበቁ የሌሉ አይምሰልህ........! ፍራት የለሽ ስስት የለሽ ፍርድ አያዛቤ፥ የጥበብ ምንጮች የሚሆኑን........ ሐዘንን ደምሳሽ ብስጭትን አጥፊ - ሕይወታቸው የየሱስን መንገድ የተከተለ....... በማጣት የማይጨነቁ በማግኘት የማይፎክሩ በጠቅላላው ለዓለማዊ ድሎት የማያፈችሉ....... ጽኑ ብሩህ፥ ታጋሽ፥ ርጉ ሰሎሞኖቻችን ጻድቃናችንና ሰማዕታታችን ይወጣሉ ከየፍሬዎቻችን....... ከእኛ የሚፈለገው በእምነታችን ብቻ ጸንቶ መገኘቱ ነው.......

«መቼም ተስፋ ስለሰጠኝ ያሸነፍከኝ መሰለኝ.......

«እኔ ምን ተስፋ እሰጥሃለሁ....... ምናልባት ራስህ ለራስህ ተስፋ መስጠት ጀምረህም እንደሁ አንድ ነገር ነው...... ደግሞስ ምን ዋጋ አለው ብለህ አንተ ወይ እኔ በክርክር ብናሸንፍ...... ያንተ ወይም የኔ በኩል ክርክር ለጊዜው እውነት ወይም ውሸት መስሎ ቢታይ? ዋናው ነገር ይልቅ በኅሊናህ ያለው የምታምንበት ነገር....... ዋናው ነገር ራስህ ችሎታ ያለው ድኅና አድርጐ የጸደቀው እምነትህ......

## ፶፪

## አደፍርስ

ወይዘሮ አሰጋሽ ከሮቢት ወደ አርማኒያ እንደ ተመለሱ ወዲያው ወደ ደብረ ሲና አልወጡም። - የሮማን ሠርግ መዳረሱ ስለ ነበረ ሥራው ፋታ አልሰጣቸውም - ጌሾ ማስቀርጠፉ ከየጉድጓዱ እህል ማስወጣቱ ብቅል ማስበቀሉ ወደየውሃ ወፍጮው እየላኩ ማስፈጨቱ ያሯሩጣቸው ነበር። -

ሮማን በበኩሏ ከጺወኔ መጠለፍ ወዲህ ዕረፍት አልነበራትም። - ወዴትም ይሁን ብቻ ካርማኒያ የምትወጣበትን መንገድ ነበር የምትፈልገው። - ጴጥሮስ ይዤሽ እጠፋለሁ ብሎ ተስፋ በሰጣት መሠረት ከዛሬ ነገር ይቆርጣል እያለች ብትጠብቀው ማመንታት ብቻ ሆነ። - ከማትፈልገው ሰው ጋር መጠመጃዋ ቀን እየተቃረበ ሄደ። -

ሳምንት ያህል ቀረ ለሠርጓ። - አንድ ቀን ማታ ትጠፋና ደብረ ሲና ገብታ ታድራለች።
-

‹ሸጋው ካቲካላ ያገር ተወላጅ

በእምብርክ ያስኬዳል እንደ ሕፃን ልጅ› እያሉ እበራቸው ደፍ ላይ ቁጭ ብለው ሲዘፋፍኑ የምታገኛቸው አንዲት የካቲካላ ነጋዴ ሴትዮ፥ ትለምናቸውና ያሳድሯታል። - በማግስቱ ጧት ሞቅታቸው ሲበርድላቸውና ሮማንንም በደንብ ለማየት ሲችሉ፥ ጠፍታ የመጣችበትን ምክንያት ይሰሙና በማዘን ለጊዜው እቤታቸው እንድትሰነብት ይፈቅዱላታል። - ትውላለች ታድራለች። - በጋዴዋም ጠባያቸው አይለወጥም፤ መሸት ባለ ቁጥር ብቻ ሞቅ ሲላቸው ‹ሸጋው ካቲካላ ያገር ተወላጅ......› ነው እደፋቸው ላይ ቁጭ ብላ ‹በእምብርክ ያስኬዳል እንደ ሕፃን ልጅ......

# ፶፫

# አደፍርስ

አቶ ጥሶ ከነልጃቸው የሥራ ጊዜያቸውን ፈጽመው ወይዘሮ አካላት ከነአሽከራቸው ቤታቸውን በቅጥ አድርገው ከልጃቸው ጋር ለመክረም ሊመለሱ ወደ አዲስ አበባቸው ያመራሉ። - አደፍርስ አነስ ያለ ቤት አግኝቶ እስኪከራይ ወደ ደሴ እሚወስደው አውራ መንገድ ዳር እሚገኘው ሆቴል ይዛወርና ሥራን ይጀምራል። - ክብረትም አብሮት ቆይቷል ለጊዜው። -

«ሞትና ሕይወት ድንቁርናና ዕውቀት......! ባንተ አስተያየት እንግዲህ የሚያደርጉትን አያቁትም ማለት ነው ተማሪዎቹ....... ክፍል አንገባም ማለታቸው ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጋቸው ድንጋይ መወርወራቸው ብቻ ነው መሰለኝ የሚታይህ...... ጥሩው ሥራችወ ተውሰውሮብሃል......» ይናገራል አደፍርስ ከክብረት ጋር እሆቴሉ ቤት መዝናኛ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብሎ ሲያወጋ። -

«ማንኛውም ነገር ከመጠን ሲያልፍ አጉል ነው - ትምህርታችወን እንዲቀጥሉ ተደጋግሞ ተነገራቸው - በምክርም በግሥጻም....... እምቢ አሉ - ቤተ ሰቦቻቸውን አቃቱ...... ሕግ አስከባሪዎቹን የከተማ ፖሊሶች አቃቱ....... እና በመንግሥቱስ ለምን ትፈርዳለህ? - ወታደሮች ከደብረ ብርሃን መምጣታቸውን አልጠላሁትም......

«ምን ጠቀማቸው ታዲያ የባሰውን አም እሳቀላቸው እንጂ ተማሪዎቹ........?

«ይጥቀምም አይጥቀምም ለጊዜው ጸጥታን አግኝተናል....... እና ደሞ እናንተም መምህራኑ ብትረዱ አይከፋም.......

«ትቀልዳለህ ጋሼ ክብረት...... በውነት ነው የምልህ ትቀልዳለህ....... አንድ ነገር ልንገርህ በቀደም ቢል ያረገኝን በንዴት........ እንግዲህ እንግሊዝኛ አይደለም ማስተማር የጀመርኩት.......?

«ነግረኸኛል፤ ከሰላም ጓዱ ጋር የተጋጨኸውን አይደለም?

«መጋጨታችንንስ ነግሬሃለሁ........ ይኸው መከረሚያውን እንደምታየው እነዚያ ፍርፋሪ የሚያበላቸው ተማሪዎች እየተከታተሉ ይገላምጡኛል፤ ያሰቡትን እንግዲህ ማን ያውቃል.......?

«እስከዚህ ምን አደረግኸውና......

«እንግዲህ ምን ዐውቃለሁ........? ብቻ ያልነገርኩህ ነገ አለ....... በእንዴት ያለ መንገድ ቅኝ አገዛዛቸውን ሊቀጥሉ እንደሚፈልጉ ነጮች........

«አልነገርሽኝ ይሆናል.....

«.....እና ታዲያ አንድ የምንተኛ ክፍል ተማሪ ደብዳቤ ጽፎልሃል በእንግሊዝኛ ለ ‹Ethiopian Herald› ጋዜጣ....... እንዳርምለት አመጣው እኔ ጋ። - እኔም ቀስ ብዬ እንደ ተቻለኝ አረምኩለት እንግሊዝኛውን....... እንግዲህ አስበው እንግሊዝኛውን ብቻ ነው እኔ ያረምኩት - ሐሳቡን አልነካሁም። - ከዚያ በኋላ ለሰላም ጓዱ ደሞ ወስዶ አሳይቶት ይኖራል........ ቋንቋው ስለሆነ በተሻለ መንገድ እንዲያምርለት.......

«ብሔራዊ ቋንቋው እንግሊዝኛ የሆነ ሰው የተሻለ የሚያስተምረው አይመስልህም.......?

«ይሻልም አይሻል ገና ተጠንቶ አልታወቀም እንደህ ያለው ነገር - ብቻ እኔ ልነግርህ የፈለግሁት ይኸ ሰላም ጓድ ያደረገውን ነው...... የልጁን ደብዳቤ - ሰርዞ ሰርዞ ዐረፍተ ነገር በዐረፍተ ነገር - ድልዝና እመጫት አሽክሞ ይሰጠዋል። ሞኙ ተላሌው ተማሪ ሆዬ እቤቱ ወስዶ አሳምሮ ይገለብጥና - እንደ ገና ሊያሳየኝ መምጣት.......

«እሱ አደለም እባክህ......! ባነበው ጊዜ አብዛኛው የልጁ የነበረው ሐሳብ ጠፍቶ የሰላም ጓዱ ሐሳብ ሆኗል...... ሐሳብህኮ ተለውጥጧል ብዬ ነገርኩት ለተማሪው....... ያንተ ሐሳብ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች እንዲገባ እንዲህ መሆን አለበት ብሎ ነው የለወጠልኝ ብሎ መለሰልኝ......

«እኮ፥ ሐሳቡን አስተካከለለት ማለት ነው......

«የለም የተማሪውን ሐሳብ ደምስሶ የራሱን ሐሳብ ጻፈለት.......

«እና በቋንቋ ጥናት ውስጥ እንኳን ቢሆን የራሳቸውን ፕሮፓጋንዳ ነው የሚነዙት ነው የምትለኝ.......?

«እንዲያ ብቻ ሳይሆን - የራሳችንን ሐሳብ እያጐዘሉ የነሱን ሐሳብ ብቻ እንድናደንቅ ነው የሚፈልጉት ነው የምልህ......

«ታዲያ ምናለበት የራስህ ሐሳብ ያው የራስህ ነው...... የነሱንም ከነሱ የምትፈልገውን ወድደህ የምትቀበለውን እስኪታገኝ ድረስ የተቀበልክላቸው ምሰል......

«መምሰል ሳይሆን እየተለወጡ ሄዱ እንጂ ተማሪዎቻችን - ከነሱ የሚፈልጉትን እስኪያገኙ ዱሮ ተለውጠው ቁጭ ሆነዪ!! የራሳቸውን የሆነ ነገር ያስጠላቸው ጀመረ - በእንግሊዝኛ ቃል ያልተገኘለት ያማርኛ ቃል - በእንግሊዝኛ ለመግለጽ የሚያስቸግር ኢትዮጵያዊ ሐሳብ - በእንግሊዝኛ ቋንቋ የማይገለጽና የሌለ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ባህል ሁሉ ዋጋ እንደሌለው ተቆጠረ እንጂ - እንጀራውን ‹ብሬድ› ወጡን ‹ሱፕ› ጠይሙን ‹ብላክ› ጥቁሩን ‹ኔግሮ› እንዲሉ ተገደዱዪ - ምን አለፋህ ብቻ....... የኢትዮጵያውያንን ስብእና አጥፍተው የፈረንጁን ስብእና ተኩበት ነው የምልህ......

«የራስህ በሆነ ነገር ማፈር ስትጀምር የባዕድ ተገዥ መሆህን የማይጠረጠር ነው - ብቻ.......

«እምልህኮ አንድ ዐረፍተ ነገር በእንግሊዝኛ ትጽፋለህ...... ያንን ዐረፍተ ነገር የሰላም ጓዱ ይሰርዝና የተሻለው ይኸ ነው ብሎ የራሱን ይጽፋል። - አስተማሪህ ነውና ትቀበለዋለህ አንተም - ይቀጥላል እንዲሁ በየጊዜው - ትጽፋለህ ይሰረዛል - ትጽፋለህ ይሰረዛል - ከጊዜ በኋላ ትክክለኛ ዐረፍተ ነገር መጻፍ ጀምረሃል ብሎ ይመሰክርልሃል - የሱ ግልባጭ መሆንህን በትክክል ሲያረጋግጥ - ‹ቤብ› - ‹ሀይ!› እያልክ መዘባነን ነው አንተም ከዚያ ወዲያ። - እግሩን ሰብስቦ ተቀምጦ የሚለውን ዐረፍተ ነገር - ይኸማ ለሁኔታው አይበጅም - መዝናናቱ መታየት አለበት - ስለዚህ እግሩን እጠረጴዛው ላይ ዘርግቶ መባል አለበት...... ጥፍሯን አስተካክላና አሳምራ ቆርጣ የሚለውን - ይኸማ ያው ገልቱነትን ነው የሚያሳየው - ጥፍሯን አሳምራ አሳድጋና ቀለም ቀብታ መባል አለበት....... ወይም ከንፈሯ ሰው ሠራሽ ጌጥ ያልደባለቀ፥ በተፈጥሮ ውበቱ የሚያጓጓ የሚለውን - ከንፈሯን ዓይኖችህን እንዲያብለጨልጩ የሚያደርግ ሮዝ ከንፈር ቀለም ቀብታ....... ምናለፋህ ብቻ ቀስ በቀስ እግርህን እጠረጴዛው ላይ በመዘርጋት ጥፍርህን

በማሳደግ ከንፈርህን ቀለም በመቀባት ዓይነት መንገድ የተሻሻለ በመሰለህ ሐሳብህ ውስጥ ዘቅጠህ ትቀራለህ ነው የምልህ........ እነ አቶ ጥሶ ልማድ ወግ፥ ቅርስ የሚሏቸው ሁሉ ድራሻቸው ይጠፋል ነው የምልህ....... አንተም ዱሮ መሬትህ ነበር በቅኝ አገዛዝ የሚያዘው ዛሬ ሰውነትህን ስብእናህን ለቅኝ ገዥዎች ሰጥተህ ትቀራለህ ነው የምልህ...... ለምሳሌ አሁን የጥንቱን የተመለከትህ እንደሆነ ስብእናቸው በቅኝ ገዥዎች ያልተያዘ ስለ ነበረ መሬታቸውም ቢያዝ ለማስመለስ ችለው ነበር። - ዛሬ ግን እንዳያዘችን መሬታችን ቢያዝ እንኳ በየትኛው ስብእናችን እናስመልሰዋለን........? ደግሞስ ስብእናችንን እያጣን ከሄድን መሬታችንንስ ጭምር እያጣን ላለመሄዳችን ምን መተማመኛ አለን? ተመልሶ የኛ የመሆን ተስፋ በሌለው አኳኋን........! በየትኛው ስብእናችን ልናስመልስ.......? እኛንም መሬታችንንም እንዴት አድርገን የምንችል ይመስልሃል ከቅኝ አገዛዝ ሥር ለማውጣት.......? ሌላው ቢቀር እንደ አበው እንደ ጥንታውያኑ ያህል እንኳ ስብእናቸው ያልተነካ ኢትዮጵያውያን ካልተነሡ.......

«ያንን እዚያ እግርግዳዋ ላይ የተሣለ ሥዕል ትመለከታለህ.......?» ይጠይቀዋል ድንገት አደፍርስን ከብረት - አዲስ ነገር እንደ ተከሠተለት ዓይነት «መጀመሪያ ዛፉን ተመልከት፤ አምስት ቅርንጫፎች አሉት። - ወደ ቀይ የሚያደላ ሮዝ ዓይነት ቀለም ነው የተቀባው ግንዱ ደሞ። - የቅጠሎቹን ደሞ ትንንሽነት ትመለከትልኛለህ........? እሺ........! በነጭ ወረቀት ላይ በጥቁር ቀለም የተሣለ ሰው ሥዕል ነው ያ ደሞ....... እቅርንጫፎቹ መካከል የተለጠፈው - ከሌላ ዘንድ ቆርጠው አምጥቶ ነው የለጠፉት...... እሺ........! እሥሩ ደሞ...... እንዲሁ ከሌላ ዘንድ ቆርጠው አምጥተው የለጠፉትን የኮካኮላ ማስታወቂያ ታየዋለህ.......? ወንድና ሴት ኮካኮላ ከኮካኮላቸው ጨብጠው እኮላቸው ውስጥ ብራቸውን ሰክተው - አንጋጠው - በኀይል ስቀው ወደ ዛፉ ላይ ሰው ሲመለከቱ። - ከተሰቀለበት ዛፍ ወርዶ የማያመልጣቸው በመሆኑ ተማምነው የተደሰቱ ይመስል። - እዙሪያቸው እግርግዳው ላይ ደሞ የተምቦጫረቀውን ቀለም ትመለከተዋለህ.......? ይኸ ምንድነው ስሙ...... ለምጨቅ ነው ሮንቂ......? ይኸ ረግረግ የሆነ የሚዋልል መሬት ላይ የተቀመጡ እንደሚመስል። - እዳሩ ላይ ደሞ ከወደ ግራ በኩል አባት ነፍጠኛን ትመለከታለህ......? ጥቁር ጸጉራቸው ቀይ ማሠሪያ ካለው ነጭ ባርኔጣቸው ሥር ብቅ ብሎ - ፊታችውና እግራቸው ሮዝ ተቀብቶ - ቀይ ጥለት ያለው ሸማ ለብሰው - አረንጓዴ ሱሪ ታጥቀው - ጨበጥ አርገው የያዙትን ቀይ ጐራዴ አገንድረው...... በነጭ ግርግዳ መሣላቸው ደሞ በጅቷቸዋል........

አቅራቢያቸው ቆማ ታዳምጣቸው የነበረች አሳላፊ የቢራቸውን ተጠጥቶ ማለቅ ታይታ «የብሩታዊትና የባለ ክንፉ ዘንዶ ምሳሌ ነው ሥዕሉ......» እያለች ሁለት የጊርጊስ ቢራ ታመጣና መክፈት ትጀምራለች። -

«ባለ ክፍኑ ዘንዶ ታዲያ የታል.......?» ይጠይቃታል ከብረት። -

«አይታይም እሱ....... ተሰውሯል...... ጋኔል አይደለም እንግዲህ?! ሊሰወር ይችላል.......» ትመልሳለች አሳላፊዋ ሳቅ ሳቅ እያለች -

## ፵

# አደፍርስ

ወይዘሮ አሰጋሽ ሮማንን በየገጠሩም በየከተማውም ቢያስፈልጉ ሳትገኝ በመቅረቷ በመግመን በመጬስ ላይ እንዳሉ፥ አማላጅነት የተላኩ ሦስት ሽማግሌዎች ይመጣሉ እቤታቸው...... ሲፈሩ ሲቸሩ.......

«.......ባልና ሚስት ካንድ ባሕር ይቀዳል ነው የሚባለው...... እኛም መቼም ደፍረን የመጣነው አባቱ ያባቷ እናቱ የናቷ አብሮ አደግና በችግርም ሆነ በደስታ ያልተለያያችሁ በመሆናችሁ፥ ልጆቻችሁም የእናንተ ፈር ተከትለው እንዲተኩ በማሰብ ነው......» እያሉ የመጡበትን ጉዳይ በልዩ ልዩ ዓይነት መንገድ በመደጋገም ይናገራሉ አንጋፋው ሽማግሌ። - ወይዘሮ አሰጋሽ በዝምታ ይዳምጣሉ። -

«ልጁ መቼም አላጠፋም አንልም.......» ይለጥቃሉ ሌላው። -

«አዎ እውነት ነው። - እኔም አባትሽ ብሆን፥ ይኸው አሁን ሊቀ መልአኩ ነው፤ ለሌላ ሰው ቢሆን እደጅሽ ድርሽ አልልም ነበር - በዛሬው ጊዜ ማን ይታመናል? ይኸው ሮማን እንኳን እንዲህ አሳፍራን ጠፍታለች። - እና ታዲያ....... ልሮማንስ የተደገሰው ድግስ ለምን መና ይቅር.......? አዎ ይኸንን ሁሉ አስቤ ነው.......» ይናገራሉ ያዳምጡ ያዳምጡና አባ አዲሴ።

«እድነሱ እንኳ አይናገሩ አባቴ! የኔ ልጅ በሮማን ድግስ አታግባም....... የምታገባም ቢሆን...... ሁለት ሦስት ሙቶ ጋን ጠላ...... አምስት ስድስት ፍሪዳ፥ ሦስት አራት ሰቀላ.......» ድንገት ቱግ ይላሉ ወይዘሮ አሰጋሽ። -

«ወዴት ወዴት ወሰድሽብኝ? ምን ቢያገደኝ የኔ ልጅ! ያንችን የልጄን ምግባር አጣሁትና......

«.........አዎ ድፍን ይፋትን ጠርቼ አምቦዝቡዝበታለሁ የሮማንን ሠርግ ድግስ ቢሆን...... ጐርፉ ግን ወደ መጣችሁበት ቁም ነገር ልመለስና አከባሪዬ ልጅ ነበር....... ምን ይሆናል! በሰው አገር ደፍሮኛል። - አቅሜን ሴትነቴን አይቶ......

«ጥፋቱኮ ጥፋት አያህልም፤ አላጣነውም...... ኋላ አፋችንን ያስተሣሥሰረው ምኑ ነው......? አይ ጥፋቱ ጥፋት ነው። እንደመቤታችን ተማምነንብሽ የመጣነው ይቅርታሽ አይለየንም ብለን ነው እንጂ ጥፋታችንማ መቼ ታጥቶን። - የኔ ልጅ ለስንቱ ለስንቱ በዳይሽ ነው ይቅር የምትይው ልበ ሰፊ ነሽ...... አሁን በቀደም አንድ አኮሪዶ የሚጫወት ልጅ ሮማንን ቢደፍርባት....... ሰው እንዴት ጋብዞ ያመጣውን አስቀይሞ ያባርራል? ብላ የተሠራውን ሥራ ሁሉ ልቤ እያወቀው - አምንሃለሁ! ጥፋቱ ያንተ አይደለም ብላ - ጉዱን ሁሉ ሸፋፍና - ከዚያ ኋላ ደሞ አውላ አሳድራ በደስታ አልሸኘችውም.......? ይቅር ማለት ብቻኮ አይደለም...... ጉዱ ከግቢዋ አልወጣም። - ምግባሯ ነው ያኖራት........ ምግባሯ የኔን ልጅ.......

«አሁን ታዲያ ቀን ቢወስኑልን.......!» ይጠይቃሉ አንጋፋው ሽማግሌ። - «እስከ አሥራምስት ቀን ድረስ እስቲ ከልቤ ጋር እመክርና ለማንኛውም - ቁርጡን እነግራችኋለሁ........ አዎ፥ አንድ ልጅን ያህል መስጠት ቀላል ነገር አይደለም......

«ጐርፋስ ቢሆን ያው የርስዎ አይደለሞይ........ ምን ለየው.......?

«ጐርፋም የኔ ነው፥ ቢሆንም....... ቢሆንም......

ሽማግሌዎቹ እጅ ነሥተው ይወጣሉ። - ጺወኔ አማላጅነት የመጡበትን ካሸከሮች ትሰማለች። -

## ፶፫

## አደፍርስ

ነጋዴዋ ሴትዮ የሮማን ጉልበት እየጣማቸው ስለሄደ እንድትቆይላቸው ይለማመጣሉ በየቀኑ። - ሮማንን ቢሆን አይደላትም - ትከሳለች፤ ትጠቁራለች፤ በጥቂት ቀኖች ውስጥ ያ የሚያምረው ወዛም ሰውነቷ ይመጠጣል። - ከጧት እስከ ማታ የካቲካላ ድፍድፍ ሲቀቅሉ መዋልና ማምሸት ቀላል ሥራ አልነበረም። -

ለሠርጓ የተዘጋጀውን ድግስ ቢሆን ‹ድፍን ይፋትን› ሳይጋበዙበት ይቀራሉ ወይዘሮ አሰጋሽ። - ጺወኔም ትገነግናለች በዚህን ጊዜ። - ጐርፉ የላካቸው ሽማግሌዎች የተቀጠሩት እንደ ነገ ሊሆን ማታውኑ ጠፍታ ደብረ ሲና ትገባለች። - አጐቷ ቤት ድረስም ሄዳ ተደብቃ ትጠብቅና በላይን ታገኘዋለች። - በላይ የፈለገውን እርዳታ ያደርግላታል። - ይወስድና ለብቻቸው ቤት ተከራይተው እየኖሩ ከሚማሩ ሁለት የትምህርት ቤት ልጃገረድ ጓደኞቹ ጋር ያስቀምጣታል ስድስት ቀን ያህል። -

በሰባተኛው ቀን ግን፥ በምንም ዓይነት መንገድ ቢሆን አደፍርስን ካላገኘሁና ካላነጋገርሁት ሞቼ እገኛለሁ ብላ ስላስቸገረችው አደፍርስን ይጠራታል። -

## ፶፮

## አደፍርስ

አደፍርስ የጺወኔን ሁኔታ በሰማበት ወቅት አሁን ጊዜም የለኝ የሚልበት ዩንቨርስቲ የሚያዘውን የአንድ ዓመት አገልግሎቱን የጀመረበት አፋላ የሥራ ወራቱ ነበር፤ ከወዲያ ወዲህ ያሯሩጠዋል። - ሆኖም የበላይ ጉትጐታ ስለ በዛበትና ለጺወኔም አንዳንድ ጠቃሚ ምክር ቢሰጣት የምትመለስ ስለመሰለው ይሄድና ያነጋግራታል

«.......ጺወኔ መኮብለል አልነበረብሽም፤ በጣም አጥፍተሻል...... በጣም ነው የምልሽ.......! እናትሽ ምን ይሉ.......? በሐዘን የሞቱ እንደሁ ጉዳቱ የማን ይመስልሻል.......? አዙረሽ አትመለከችም?» እያለ ይጀምራል ግሠጻውንና ምክሩን እበላይ ፊት «ሮማን ይኸው እንደ ጠፋች አልተገኘችም....... ከሷ ምክንያት የደረሰችባቸውን ኪሳራና ንዴት ሳይወጡት ደሞ ያንቺ መጨመር! እውነቴን ነው የምልሽ በጣም ነው የሚያናድደኝ እንዲህ ያለ ነገር...... እኔኮ የማይገባኝ....... እንዴት አዙረሽ አትመለከችም........? እሺ ይሁን ደሞ ከኔም ጋር ተነጋግረሽ በሆነ........

«ሆዴ አልችል አለኝ...... የምትጨክንብኝ አልመሰለኝም........ የማስቸግርህ አልመሰለኝም ነበር ደሞ....... እግርህን አጥቤ እንኳን ብቀመጥ.......

«ሞትና ሕይወት! እግር ማጠብ...... እግር ማጠብ......! እኔ እግር አጣቢ አልፈልግም! እፈልጋለሁ ወጣኝ?! የት ቦታ...... የት ቦታ ወጣኝ እግር አጣቢ እፈልጋለሁ....... ራሴ የራሴን እግር አጥበዋለሁ....... የራሴን እድፍ....... እግር አጥቤ?!

«ሮማን የምትሠራው አያቅተኝ....... ያ....... ልከው....... ማንኛውም ሥራ ቢሆን.......

«ስሚኝ ልንገርሽ ጺወኔ! እኔ ለራሴ ይኸን ዓመት ስጨርስ ወደ ዩኒቨርስቲ ተመላሽ ነኝ። - እዚያ አንድ ዓመት እቆያለሁ። - ከዚያ በኋላ ደሞ ምኑ ይታወቃል? ወይ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ወዳጅ ሀገር እሄዳለሁ....... ወይ ሥራ እይዛለሁ...... እምልሽ ብቻ ነፃ...... ነፃ ለመሆን ነው የምፈልገው...... በምንም ዓይነት ነገር እንድታሠር አልሻም.......

«እኔ ታዲያ ምን ይብጀኝ......?

«የሚበጅሽ ወደናትሽጋ መመለሱ ነው....... አዎ ሳትውዪ ሳታድሪ...... ምናልባት ቢያስፈልግ አቶ ወልዱን አማላጅ ጨምረሽ.......

«ጕርፉን እንዳገባ ተመልሼ.......?!

«ምናልባት?! ጥሩ ልጅ ነው። - እወደዋለሁ ብለሽኛል ደግሞ....... የባላገሩንም ኑሮ ለምደሽዋል........

«ምነው ልቡሰ ጥላሽ ካልገጠመ አጉል ነው ብለኸኝ........? ምነው.......

«ነገርኩሽ.......! ስለ ልቡሰ ጥላ ብዙ ብዙ የማይገባሽ ነገር አለ። - ከፍ ያለ ትምህርት ያስፈልግሻል....... እሱ እንዲገባሽ........!

«አታስተምረኝም ታዲያ........?

«እምልሽ የሁለተኛ ደረጃ፥ የዩኒቨርስቲ ትምህርት......

«ጕርፉን በጭራሽ አላገባም....... እዚሁ ደብረ ሲና - አንተ ፊት ደሜ ይፈሳታሊ........!

«አብደሻል መሰለኝ ጺወኔ! የምለው ነገር የገባሽ አይመስለኝ.......

«የሮማንን ያህል እንዴት መሥራት ያቅተኛል........? ለሷ ሥራ እፈልግልሻለሁ ብለሃታል...... ለምን ለኔስ አትፈልግልኝም.........?

«አብዬ ወልዱንማ መቼ አጣሁት....... የፈለግሁት አንተን ሆነዪ....... አንተን ባመንሁ - ስንቀዠቀዥ መጣሁ እንጂ.........?

«አሁንም ልትመለሽ ትችያለሽ......

«ልብ ወደ ኋላ ከቀረ፥ በጁ ይላል......?

«በጁ እንዲልሽ ማድረግ......

«.......ከማዬም - ካባዬም - ከጕርፉም...... ከማንም ከማንም አብልጨ የምወደው አንተን ብቻ ነው......... እባላገር ብመለስ ርግጠኛ ነኝ እሞታለሁ....... እንዴት እንዴት ትጨክናለህ በኔ ስሞት ዝም ትላለህ........?» በላይ ሹልክ ይልና ይወጣል «የትም አትተወኝ....... አትተወኝ........ አትተወኝ....... ይዞሽኝ ሂድ...... የትም አትተወኝ...... አትተወኝ...... አትተወኝ........ ይዘሽም ሂድ...... የትም ጅብ ይብላኝ ካንተ ጋር ሄጄ.......» እያለች እጪማው ላይ ዘፍ ትላለች። - ሰውነቷን ሁሉ እንደ ሰደቻ ይመታታል። - ከሙጥኟም መንጭቆ የሚወረውራት ኀይል የተነሣ ይመስል አንድ እግሩን ጥርቅም

አድርጋ ትይዛለች። - መጀመሪያ እያንዘረዘረ ቀጥሎ እያንሰቀሰቀ ከዚያም በየትዝታው እየቆነጣጠረ እያለሳለሰ መምቦልቦል ይጀምራል እንባዋ። - ብዙ ጊዜ ታፍኖ የቆየና በልብ ውስጥ የሚግፈጠፈጥ ዳፈን አውጥቶ የሚያበድርና ሐዘንና ሥቃያትን የሚያሰጥም ይመስል። - እያለሳለሰ...... እያለሳለሰ...... ይወርዳል......... ይወርዳል....... ቀስ በቀ - ህቅታው...... ስርቅታው ሁሉ እየቀረ....... ድምፅ የሌለው ውርደት....... ይወርዳል...... ጽናትና ፈውስን ያገኘችበት ይመስል በፊቷ ላይ ባበጀው መንገድ ፍልቅ ፍልቅ እያለ....... ብድግ ስትል እንዳቋረ አሸንዳ ይጀጅራል። - አደድርስን አልተመለከተችውም። በሩቁ ከፍታ ልትወጣ ስትል ቁቁታው ይቀልጣል - እውጪ። - ወይዘሮ አሰጋሽ ወንድማማቸውን አቶ ወልዱንና ሁለት ፖሊሶች አስከትለው ይደርሳሉ። - በላይ ራቅ ብሎ ተከትሏቸዋል። -

## ፶፲

# አደፍርስ

ጺወኔና አደፍርስ ተይዘው ፖሊስ ጣቢያ ይሄዳሉ። ቃል ያሠረችውን ልጃገረድ ከትውልድ አገሯ አስኮብሎ በማጉደፍ ወንጀል ይከሰሳል አደፍርስ። - ጺወኔ ቃሏን ትሰጣለች። -

«ለመሆኑ ምን አደርግልሻለሁ ቢልሽ የሞቀ ቤትሽን ጥለሽ ኮብለልሽ?» ይጠይቃታል ፖሊሱ።

«ምንም አደርግልሻለሁ አላለኝ!» ትመልሳለች ጺወኔ። -

«እሱ ነው ግን ያስኮበለለሽ........?

«አላስኮበለለኝም.......

«እውነቱን ተናጋሪ ኋላ አንቺ መድረሻ ቢስ!» እያሉ ይንጐራደዳሉ ወይዘሮ አሰጋሽ። - ፖሊሱ ከቢሮው ያስወጣቸዋል። -

«ቃል ያሠርሽ ልጃገረድ ነሽ?» ይጠይቃታል ፖሊሱ። - አሰጋሽ እንደገና ወደ ቢሮው በራፍ ይመጣሉ። -

«ቃል አላሠርኩም!» ትመልሳለች ጺወኔ። -

«እንዴት አባሽ ብለሽ......!» ይጮሃሉ ወይዘሮ አሰጋሽ ውጪ እንደቆሙ «እንዴት ብትፏንኒ ትዋሻለሽ.......! ጐርፉ ምንሽ ነው በይ......? ምንሽ ነው? ከጐርፉ

ጋር አልተፈጣጠምሽም? አልተፈጣጠምሽሞይ.......?» ዘለው ሲጨቡዷት ዓይነት ይሻቸዋል፤ በኀይል ይይዝና ያቆማቸዋል በር ላይ የቆመው ፖሊስ። -

«ፊርማም ምንም የለ?» ይጠይቃል ፖሊሱ እንደገና። -

«ምነው የሽማግሌ ቃልስ ቢሆን? የምን የወረቀት ቅርንጥ ነው ደሞ........? እኔ አሰጋሽ ከወረቀት እበልጣለሁ........!» ቀጥለዋል ወይዘሮ አሰጋሽ። -

«ፊርማ የለሽሞይ ነው የምልሽ?» ይጠይቃል ፖሊሱ። -

«የለኝም!» ትመልሳለች ጺወኔ።

«ድግስም ፍጥምጥምም አልነበራችሁ.......?

«አልነበረንም.........?

«እንዴት አባሽ ብለሽ.......! የተደገሰው ድግስ እንኳ ተበልቶ ሳያልቅ.........» ጣልቃ ይገባሉ እያከታተሉ ወይዘሮ አሰጋሽ። -

«አሁን የምጠይቅሽን ጥያቄ ተጠንቅቀሽ መመለስ አለብሽ........» ያስገነዝባል ፖሊሱ «አደፍርስ የሚባለው ሰው ክብረ ድንግልናሽን ደፍሯል? አልደፈረም.......!

«አልደፈረም!

«እምልሽኮ! ምናልባት አርማኒያ በሰነበተበት ጊዜ.......

«በጭራሽ.......!

«እዚሁ ቤት ነው ማለት ነው ከመጣሽ........!

«አዎ እዚሁ ቤት ነው.........

«ተማሪዎቹ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱለት........

«እንደ መጣሁ እዚሁ ነው ያረፍኩት.......

«አገባሻለሁ በሚል ተስፋ ደልሎሽ እንደሁ.......

«ከመጣሁ ጀምሮ ዛሬ ገና ነው........

«ፍቅር መቼም የማያሠራው ሥራ የለ....... እና...... ምናልባት ከውዴታሽ የተነሣ.......» አንገቷና ቀርቀር አድርጋ መሬት መሬቱን ትመለከታለች - አትመልስለትም ጺወኔ። -

«ትወጂዋለሽ አትወጂውም አደፍርስን.......» ይጠይቃታል ፖሊሱ የጀመረውን በሌላ ዓይነት መንገድ። - አትመልስለትም እሷ ግን «መቼም እዚህ የመጣሽበት አንድ ምክንያት አለ....... ይልቅ ነግረሽን.......» ይቀጥላል ፖሊሱ። -

«ቁርዝ መሳይኮ ቢኖር እኔው ራሴ ባናገርኳት....... ዋይ ልቅ ነገረሽን.......» ይቀጥላል ፖሊሱ። -

«ቁርዝ መሳይኮ ቢኖር እኔው ራሴ ባናገርኳት....... ዋይ ነዶ!» ይናገራሉ ወይዘሮ አሰጋሽ ከበር ውጪ እንደ ቆሙ። -

«እንግዲያው ለምን ኮበለልሽ?!» ይጠይቃታል ፖሊሱ የቁጣ ጅመራ በሚመስል አንደበት። -

«ጐርፉን ማግባት ስላልፈለግሁ.......» ትመልሳለች ጺወኔ ቀስ ብላ። -

«እንዲያ ነው እንጂ.......! ተፈጣጥመሽ ነበር ማለት ነዋ....... ገብቶኛልኮ ከቅድሙም እውነት እንዳልተናገርሽ...... እንዲያ ነው...... እንዲያ ነው.......!

«ማለቴ...... በሮማን ሠርግ ሊድሩኝ.......

«እኮ ሠርግሽ መድረሱን ሲያይ፥ በጐን መጣና አቶ አደፍርስ.......

«እሱ በጐን የመጣበትም ነገር የለ......

«ጥሩ ጥሩ በቀጥታ አባብሎ አስኮበለለሽ እንበል......

«እንዴት ብዬ ልንገራችሁ.......

«ግዴለም ግዴለም ገብቶናል....... ካስኮበለለሽ በኋላ ደሞ፥ እዚህ ቤት አስቀመጠሽ...... ከተማሪዎቹ ጋር.......

«እኔው ራሴ ነኝ እዚህ....... ከበላይ ጋር......

«የተያዘ እንደሁ ከልጃገረዶች ጋር ነው ያኖርኳት ለማለት.......

«በላይ ነው እዚህ ያስቀመጠኝ ነውኮ የምለው.......

«በላይ? በላይ.......?» ወደ አቶ ወልዱ መልከት ይልና

«ግዴለም ግዴለም አያጣላንም ይኸ....... ብቻ አሁን ዋናው ነገር ክብርሽን የደፈረው......

«አልደፈረም ብያለሁኮ ቅድም.......

«አሃ! ክብርናሽ አልተደፈረም እንበላ ታዲያ.......?» መልስ ከመስጠቷ በፊት ብዙ ጊዜ ትቆያለሽ። -

«ሌጊዎን እንኳን አልደፈራትም የኔን ልጅ......!» ይላሉ ወይዘሮ አሰጋሽ ወደ በሩ እንደ መምጣት ይሉና። -

ወይዘሮ አሰጋሽ ወደ በሩ እንደ መምጣት ይሉና።

ፖሊሱ እንደ ገና መጠየቅ ይጀምራል እየተስፋፋ «ሕግሽ አልተደፈረም ማለት ነው.......

«ይመለጥ መስሏት በዚህ ብቻ....... ምናሳባለን ነው የማመጣት....... ጉዷን የምታወጣውን......» ጮክ እንደ ማለት በልው ደሞ «ይመለጥ መስሎሻል በዚህ! ምናሳባለን ነው የምናመጣት.......! ጉድሽን የምታወጣውን......

«አልመሰለችልንምኮ ገና.......!» ወደ እሷ መለስ ይልና «ምነዋ.....! ቀላል ነውኮ ጥያቄው...... ክብርናሽ ተገሷል አልተገሰሰም.......? አጭር መልስ ነው የምፈልገው...... ተገሷል አንድ ቃል.......አለ.....

«ተገሷል......!» ትመልሳለች ድክም ባለ አንደበት። -

«የዶቃቂት ሚካኤል ያለህ!!» ይጮሀሉ ወይዘሮ አሰጋሽ። - አደፍርስ ሰውነቱ ይለዋወጣል። - ጺወኔ ቀና ብላ ታየውና የተናገረችውን ትደግማለች። -

«ክብርናዬ ተገሷል......!»

«እና ታዲያ ለምን ትዋሻለሽ? አቶ አደፍርስ ነው ማለት ነው የገሰሰው.......» ይናገራል ፖሊሱ ሳቅ ሳቅ ለማለት እየቃጣው። - አደፍርስ ጣቶቹን ይጨብጥ ይዘረጋል። - ጥርሶቹን እንደ ማፋጨትም ይሞክረዋል «አቶ አደፍርስ ነው ማለት ነው፥ ቃል ያሠርሽውን ልጃገረድ አስኮብሎ አምጥቶ ሕግሽን የደፈረው?» ይጠይቃል ፖሊሱ ያስተካክልና። -

«አቶ አደፍርስ አላስኮበለለኝም....... ሕጌንም አልደፈረ!» ትመልሳለ ጺወኔ። -

«ግዴላችሁም ምናልባት በኃይል አንቆ ፈጽሞት እንደሁኮ ድርጊቱን ጭንቅላቷም ተነክቶ ሊሆን ይችላል.......» አስተያየት ያቀርባል ፖሊሱ ወደ አቶ ወልዱ መለስ ይልና። - አቶ ወልዱ ምንም አይናገሩም። -

«እኔ ጭንቅላቴ ደኅና ነው..... ስለ ክብሬ ነው ማወቅ የፈላጋችሁት...... አርማኒያ ነው ያስወሰድሁት። - እውሃ መቅጃ። - እናቴ ትቆጣኛለች ብዬ ፈርቼ ነው ከቤትም የኮበለልሁት....... አቶ አደፍርስ ምንም ያደረገው ነገር የለ......

«አይደረግም.......! አይደረግም........! የኔን ልጅ የሚደፍራት የለም አርማኒያ! ሴጊዎን እንኳን ቢሆን.......! ባኮሪዶ ተጭኖ የመጣ ካሆነ በቀር!! አይደረግም! የኔን ልጅ የሚነካት የለም አርማኒያ...... ሴጊዎን እንኳን ቢሆን...... ሴጊዎን እንኳን ቢሆን.......» ራሳቸውን እንደ መሳት ያደርጋቸዋል ወይዘሮ አሰጋሽን «........ቀበርኋ! ቀበርኋ! ቀበርሁ ልጄን...... ለሴጊዎን ሰጠሁ ልጄን...... ከእንግዲህ ወዲያ ምን ልጅ አለኝ! ምን ልጅ አለኝ? ቀበሪያለሁ ማለት ነው። - ቀበሪያለሁ ማለት ነው። - ምን ልጅ አለኝ! መካን! መካን! ሴጊዎን ሲሳይ....... ዓይንሽን አያሳየኝ ሊቀ መልአኩ....... ሬሳዬ ዳር እንኳ እንዳትደርሺ....... እሾህ ሆኖ ይወጋሻል...... አጥንታቸው የናት ያባቴ! እሾህ ሆኖ ይወጋሻል...... እሾህ ሆኖ...... እሾህ ሆኖ.......» አቶ ወልዱ ብድግ ይሉና እየደጋገፉ ይዘዋቸው ይሄዳሉ እኅታቸውን። - ፖሊስ ጣቢያው አደፍርስን ያሰናብተዋል። - ውሃ የጠጣ የወይራ ጉርማጅ በመምሰል ላይ ያለውን ፊቱን በይበልጥ አቀጭሞ አፉን አሆምጥጦ ዓይኖቹን በማለቅ ላይ ሆኖ ሁለት በመቅረዝ ሊዋጡ የደረሱ የሻማ ጉጦች አስመስሎ -

«ባንቺ ሰውነት ውስጥ........ እንዲህ - እንዲህ - እንዲህ....... እንዲህ ያለ ነገር....... አለ ብዬ አላስብም ነበር!» ይላትና ተመናጭቆ ወጥቶ ይሄዳል። - ጥርዥ ብርዥ እንደሚል ናፍታው ሊያልቅ እንደ ደረሰ ኩራዝ ዓይኖቿን ለመግለጥ እየሞከረች ከፖሊስ ጣቢያው ስትወጣ...... በላይ ቶሎ ይልና ደገፍ ያደርጋታል። -

## ፶፰

## አደፍርስ

አደፍርስ ቤት ያገኝና ይከራያል። - እናቱ ወይዘሮ አካላትና ገረዳቸው አጣሁ ወሮታም ካዲስ አበባ ተመልሰውለታል። - እተመደበበት አብዬ ትምህርት ቤት አማርኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎችን ማስተማሩን ቀጥሏል። - ከሥራው እቤቱ ሆኗል ፕሮግራሙ። - ካለፍ አገደም......... ያውም ከክብረት ጋር የሆነ እንደ ሆነ...... ካርታ ለመጫወትም ሆነ ቢራ ለመጠጣት መኪና መንገድ ዳር አለው ሆቴል ዘንድ ካልወጣ በስተቀር። - ሮማን አደፍርስን ፈልጋ በማግኘት ደጋግመው ከተወያዩ በኋላ፥ ለጊዜው ራቅ ብላ ሄዳ በተመቻቸ ጊዜ እንድትመለስ ይመከራትና የካቲካላ ነጋዴዋን ቤት ለቃ

ደብረ ብርሃን ሄዳ ቡና ቤት ትቀጠራለች። - በላይ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናውን ያልፍና ዩንቨርሲቲ ይገባል። ጒርፉ፥ ጺወኔ እንዳጫወተችው ሁሉ አደፍርስን አምናአው አብራው ተኝታ ያጐደፋት ይመስለውና ቂምና በቀል ልቡን እንዳነደደው ተነሥቶ ጠባሴ ይወጣና ወታደርነት ይመስላል። ወይዘሮ አሰጋሽ እዚያው አርማኒያቸው ተመልሰዋል። - ብቸኝነትና እርጅና እየተጫናቸው ቢሄድም ልባቸው ገና አላረጀም። - አሁንም ቢሆን ፈቃዳቸው አይጣስም። - አሁንም ቢሆን የፈለጉትን ከማድረግ ወደ ኋላዬ አይሉም። - አቶ ወልዱን፥ ይቅር እንዲሏት የምትነከረውን መጽሐፍ ዓይነት ስላላገኙት፥ ሁለዜ ያጠያይቃሉ...... ያወጣሉ ያወርዳሉ።-

## ፶፱

# አደፍርስ

ጺወኔ ከአጐቷ ጋር ተቀምጣለች። - ከፖሊስ ጣቢው ሁነት ወዲህ ምድራዊ የሰው ኑሮ ያስጠላት ይመስላል። - ከመንፈሳውያን ሰዎች ጋር መነጋገር ቤተ ክርስቲያን መሳም ማዘውተር ሆኗል ሥራዋ። - አደፍርስን ከእናቷ ጥላቻና መራራ ንግግር ያወጣችው መስሏት ሕጓ፥ ሳይደፈር፥ ተደፍሯል ብላ የሰጠችው ቃሏ ኅሊናዋን እንደ ወቀሰው አለ። - የብዙ ጊዜ ሱባዔና ጸሎት እንኳን የሚዋጀው መስሎ አይታያትም። - እንዲያውም አንዳንድ ጊዜማ የመኝታ ክፍሏን እየዘጋች ማልቀስ ነው ሥራዋ...... በተለይ አደፍርስ በርግጥ ክብርናዋን አስወስዳለች ብሎ አምኖ ያመናጭቃትና የጠላት መሆኑን ባሰበችው ጊዜ....... ማልቀስ ማልቀስ ነው ሥራዋ። - ቤቱንስ ፈልጌ ብደርስበት...... ከክብሬስ ነኝ ብለው...... እንዴት አድርጐ ያምነኛል......? ያሁኑስ ነገሬ፥ ውሸት ያለመሆኑን በምን ያውቀዋል........? አምላኬ! አምላኬ! የሚበጀውን መንገድ አሳየኝ...... በበትረ መንግሥትህ አትርሳኝ........ እያለች። - አንዳንዴ ደግሞ የራሷን ክብር ለሱ ክብር ስትል ተገፋ ያሳየችው ተጋድሎ ያልገባው መሆኑን ስታስበው ለወደፊቱም ቢሆን ያደረገችለትን መሥዋዕትነት ያውቀው ይሆናል የሚል ተስፋዋ እየመነመነ መሄዱን ስታየውና ሞታ እንኳን ቢሆን በትዝታው የመኖር መጽናናት እንዳልነበራት ስትገነዘበው የሡራ አካላቷን ያቃጥላትና እንደ እብደት ዓይነት ስሜት፥ ብረሪ ብረሪ የሚል አጣድፊኝ ነው የሚነዛባት። - አልፎ አልፎም ቢሆን ብቅ ያሉ እንደሆን ነው አባ ዮሐንስ ትንሽ ወደሷነቷ የምትመለሰው። - የሚናወጸው መንፈሷ የሚረጋጋላት........ሰውነቷን የሚያስጨንቀው ንዚት የሚነሣላት -

«.......አንዳንዱ ለምድራዊ ኑሮ እንደሚስማማ ሆኖ ይፈጠራል...... ከባላባት መካከል ተወልዶ ባላባት ይሆናል። - በሰው ልጅነት አጥንቱ በባላባትነት ንብረቱ

ይንደላቀቃል፡፡ - ችግርና መከራ የሚያገኙት አይመስለውም፡፡ - አፋሽ ከንፋሹ፥ ጠብ ርግፍ ባዩ ዙሪያውን ይከበዋል፡፡ - ሲናገር እውነት እውነት ሲጣራ አቤት አቤት ባዩ ግቢውን ይሞላዋል፡፡ - ያዩት ሁሉ ይጨነቁለታል፡፡ - ይርበተበቱለታል፡፡ - ገና ከሩቅ ብቅ ሲል ይነሡለታል፡፡ - ቆይቶ ሲሄድ ተሽቆጥቁጠው ይሸኙታል፡፡ - ያለም ጠርዟ እሱ ቤት የተወሰነች ይመስለዋል፡፡ - ከርሱም ኑሮ የተሻለ ኑሮ ይኖራል ብሎ ለመፈለግ አይነሣም ‹.......ገመል አንተ ስቁረተ መርፍእ እምባዕል በዊአ መንግሥተ እግዚአብሔር......› ባለጸጋ መንግሥተ ሰማያትን ከመውረስ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብትወጣ ይቀላታል - ተብሎ የተነገረለት ዓይነት ሰው ይሆናል ማለት ነው ባጭሩ.............................

........................................................................

......................................................

....................................

.......................

..........

እያሉ በመደሳሰስ ሲያጫውቷት በሌላው ዓለም ተሰፋ፡፡ - ወይም ደግሞ -

፳

# አደፍርስ

........‹ቀደስኩከ እምከርሠ እምከ› - ገና ከናትህ ማሕፀን መርጬሃለሁ እንደ ተባለው ገና ሲፈጠር ለእግዚአብሔር የሚመረጥ አለ....... እንደ ጻድቃኑና እንደ ሰማዕታቱ....... ምንም እንኳ ከባላባት ወገን ቢሆንም የተወለደው ባካባቢው የሚያያቸው ድሪያ ዝሙት፥ ስካር፥ መጋደል በጌጣጌጥ መብለጭለጭ፥ መከዳዳት ምቀኝነት፥ ተንኮልና ኩራትን የመሳሰሉት የኑሮ ተውሳኮች ሁሉ ያስጠሉትና በምግበ ሥጋ በምግበ ነፍስን ተክቶ በሚያልፈው ዓለም ምትክ የማያልፈውን ዘለዓለማዊ ዓለም ለማግኘት ይነሣል፡፡ - ዘመድ አዝማዱን ጐጆ ንብረቱን ትቶ፥ ዳባ አስኬማ መቋሚያ የመቁነን መቀበያ ቅልና ቆሬውን ብቻ ይዞ፥ ይወጣል፡፡ - ቁር እሚጋገርበት ወይም ሐሩር እሚያቃጥልበት ቦታ ሄዶ...... ቅጠላ ቅጠል ፍራፍሬና የዱር እንስሳት ወተት ብቻ እየተመገበ፥ በጾመ በጸሎት ተወስኖ...... የጌታ አገልጋይ ሆኖ ለመኖር ቆርጦ ይመንናል...... አንቺ የኔ ልጅ እንግዲህ ገና ስትፈጠሪ ለጌታ አገልጋይነት የተመረጥሽ

ሰማያዊ መንግሥቱን ሊገልጽብሽ ያቀሸ ነው የምትመስይኝ። - የደረሰብሽም ፈተና እንኳን ቢሆን ያልሆንሽውን ሆኛለሁ ብለሽ የወደድሽውን ሰው ክብር ለመጠበቅ ስትይ ያሳየሽው ሰማዕትነት የጌታን መስቀል መሸከምሽን ነው የሚያሳየው። - ወደፊትም ቢሆን ይኸን የመሳሰለ ብዙ ፈተና ይገጥምሻል። - እና ዋናው ነገር ብቻ ወዲያ ወዲህ ሳትይ ዓይንሽን አቅንተሽ፥ እጆችሽን አንሥተሽ ልብሽን ለሱው ላንድ አምላክ ማደሪያ አድርገሽ ‹አቤቱ አቤቱ የሚበጀውን መንገድ አሳየኝ፤ በበረት መንግሥትህ አትርሳኝ›ን ጸሎትሽ ማድረጉ ነው....... አዎ በበትረ መንግሥትህ አትርሳኝ ዋና ጸሎት ነው። - የኔ ልጅ የምድራዊ ፍቅር የምድራዊ ጋብቻና የመውለድ የመክበድ ሰው አይደለሽም። - የለም አይደለሽም። - እና ታዲያ ካልሆንሽ ዘንዳ፥ ከሴቶች ሁሉ ተመርጠሽ ክርስቶስ ሠምራን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስን ቅድስት እማሙዝን ብትሆኚ....... እንግዳ ጌጥ ሊሆንብሽ እንዴት ይችላል.......? እንግዳ ጌጥ ሊሆንብሽ አይችልም...... ‹ቀደስኩኪ እምከርሰ እምኪ› ብሎሻል እላለሁ እኔ አባትሽ ፈጣሪሽ። - ምነው ዛሬምኮ ቢሆን እግዚአብሔር በሰው አድሮ ይናገራል...... በሰው አድሮ ይናገራል.................................

.................................................................................................

.....................................................................

..............................................

........................

........

ወይም ደግሞ.........

# ፳፩

# አደፍርስ

............

..............................

....................................................

..........................................................................

.............................................................................................

.......ኀዲገ አብያትንና መንኖ ጥሪትን ዮሐንስ አፈወርቅ የሰጠው አንድ ጻድቅ ሰው፥ ከዚህ ዓለም ሐሳብ ድኖ በዕረፍት ይኖር ነበር። - ከዕለታት አንድ ቀን እከብር ባይ ልቡና እቤቱ እንግድነት ያድርና እንደምን ትኖራለህ ይለዋል? ጻድቁም ኀዲገ አብያትንና መንንኖ ጥሪትን ካገኘሁ ወዲህ ከዚህ ዓለም ጣጣ አርፌ እኖራለሁ ይለዋል። - እንግዳው ሰውዬ በዚህን ጊዜ፥ ሞኙ ተላላው፥ ‹ዐባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል›...... እንዳንተ ያለ ሰው ከተማ ገብቶ ተሾሞ ተሸልሞ ቤት ሠርቶ ንብረት ገዝቶ ለተራብ አብልቶ ለተጠማ አጠጥቶ እያስተማረ ይኖራል እንጂ እንዴት እዚህ ይቆራመዳል.......? እነዚህን ያልካቸውን የኋላ ኋላ አታጣቸውም....... ደግሞስ ከመነነና ከመነኮሰ፥ የሰጠ የመጸወተ እንዴት እንደሚሻል ሳታውቅ ቀረህ እያለ በሆነ ባልሆነው ነገር ግራ ያጋባውና...... ለንጉሥ ላሳድርህ ብሎ ይጠይቀዋል። - ጻድቁም ዲያብሎስ መቼ አንዴ ከደጁ ደርሷልና...... ነገሩስ ደግ ነበር፤ ነገር ግን ኀዲገ አብያትንና መንኖ ጥሪትን ተከተሉኝ ብላቸው እሺ ብለው ወደ ከተማ አይሄዱልኝ...... ማንን አስከትዬ እሄዳለሁ ይለዋል። - እደጅ የደረሰ ዲያብሎስ መቼም ተዘጋጅቷልና ፈቲው የሚባለውን አሽከሩን፥ አንተ ተከትለህ እያዘገምህ እኔ ዘንድ ይዘኸው ና...... እኔ ቀድሜ ቦታ አዘጋጅቼ እጠብቃችኋለሁ ይለውና ይሄዳል...... አቶ ዲያብሎስ ተንዘራፍጦ ቦታውን ይይዛል...... አቶ ጻድቅም መጠጣት መስከር መዳራት መጋደል...... ምኑ ቅጡ፥ በያይነቱ ኀጢአት አለበት ከተማ ይገባዋል...... የዚህ ዓለም ነገር....... እንደ ጕርፍ ውሃ እያሳቀ እንደ ቆንጆ ሴት ወይዘሮ እየደለለ..............................................................................................

...........................................................................................................

..........................................................................................

.......................................................................

.........................................................

...................................

...............

## ፳፪

# አደፍርስ

አጐቷ አቶ ወልዱ ደሞ በበኩላቸው የራሳቸው ዓይነት ድግግሞሽ ነበራቸው...... ማታ ማታ ገብታ ከፍ ካለ በኋላ አብረዋት ቁጭ ሲሉ -

......ሁሉ ነገር እንዳስቀመጡት አይገኝም። - እንዳሰቡት አይሳካም....... የሁሉ ነገር ውዴታ አይዘልቅም....... ይለዋወጣል........ ይቋረጣል። - ምን አለ ብለሸዋል የዚህ ዓለም ኑሮ? እንዳደረጉት ነው። - ሳትደሰች ተደስተሽ........ ምንም ነገር ሳትሆኚ ተከፍተሽ የምትኖሪበት ዓለም.......................................

..................................................................................................................

..............................................................................................

........................................................................

...................................................

................................

............

ወይም ደግሞ........

# ፳፫

# አደፍርስ

........

............................

................................................

....................................................................

........................................................................................

.........................................................................................................

........................................................................................................................

.......እናትሽ የምትቆጨው የምትናደደው ለማ ክብር ለማ መታወቅ ይመስልሻል? ለአንቺው ነው። - ቆላና ደጋ የምትረግጠው፥ የምትጥረው የምትግረው ለማ ይመስልሻል? ለአንቺው ነው። - የለም የለም ጺወኔ! መንገድ ፈልገን መታረቅ አለብሽ አሁንስ ከናትሽ። - ያባትሽን ሀብት እንኳን መሰብሰቡስ ቀላል ነገር ይመስልሻል? በጽሑፉም በምኑም ብትረጃትኮ ከድካም አዳንሻት ማለት ነው። - እስኪ ተመልከች የጊዜውን አካሄድ....... ከአራት ወር በላይ መሆኑ ነው እንግዲህ ከኛ ጋር ከተቀመጥሽ። - እርግጥ ማለፊያ እንድትለያት አትሻም። - እኔም ብሆን አጉል ልማድ አስለምደሽኛል ማታ ማታ፥ ቁጭ እያልን ማውራት...... ከማን ጋር አወጋ ነበር አንቺ ባትኖሪ? የማለፊያን ነገር ታውቂዋለሽ፤ ከማድ ቤት አትወጣ - እንደ ተርመጠመችው ይመሽላታል..........................

................................................................................................................

............................................................................................

......................................................................

....................................................

................................

................

# ፳፬

# አደፍርስ

ወይም ደግሞ አንዳንድ ታሪክ በማውራት.......................................................

.......................

.............................................

.......................................................................

...................................................................................................

........................................................................................................................

.........በቁስጥንጥንያ ከተማ አንድ ወሮበላና ፈታል የሆነ ሰው ይኖር ነበር። - ጥሩ ጩልፋትና የፈታልነት ሥራውን አጣርቶ የሚያውቅ ስለ ነበረ አገሬው ወሮበሌ፥ ወይም ፈታሌ ይሉት ነበር። - እሱ ግን ሥራው ስለ ነበር እምብዛም ሰዎቹ ከሰሙ ጋር አዛምደው የሚያስቡት አጉል መልኩ አይታየውም ነበር። - ነውርነቱንም የተገነዘበው ሰው አይመስልም ነበር ባኳኋኑ። - ሲጠሩት አቤት፥ ሲልኩት ወዴት ጩልፋትነቱን በርግጥ ያስመሰክር ነበር በድርጊቱ። - እያደር ግን በተለይ በፈታልነት ሥራው መበለቶችንና ባል የለሾቹን ብቻ ሳይሆን ባለትዳሮችም ጭምር እያቃጠረ፥ ከተማውን አጉል ስም ስላሰጠው አገሬው በተለይ ረጋ ያለ የተደላደለ ኑሮ ለመኖር የሚፈልገው ጠላው። - እንዲያውም ካንድ፥ ሁለት ጊዜ በጥይት ሊገድሉት ፈልገው ሳቱት። - በቁስጥንጥንያ ከተማ ለመኖር አልቻለም። - ወደ አሜሪካን አገር ተሰደደ። - አሜሪካ - በዚያው በለመደው ሥራው ቀጠለ። - እና በጥቂት ዓመታት ውስጥ የሱኑ ዓይነት ሥራ ይሠሩ ከነበሩት ካገሬው ሰዎች ይበልጥ ታወቀ። - ሀብት አገኘ። በለጸገ። - ነገር ግን ባለጸጋ ብርቅ ባልሆነበት ባሜሪካ የሱ ብልጽግና ከሌሎች በልጦ ሊያሳውቀው አልቻለም። - የሰበሰበውን ሰብስቦ ወደ ትውልድ ሀገሩ መመለስ ግድ ሆነበት። - ምን አለ አልሸው? የሰው ተፈጥሮ! ገንዘብ ሲገኝ ሹመት ሹመት፥ ሲገኝ መታወቅና መግነን - ምናለ ብቻ - ክብረት በሰው አገር አይደምቅምና ሀብቱንና ብልጽግናውን ይዞ ወደ ቁስጥንጥንያ ተመለሰ። -

ከዕለታት አንድ ቀን አምሮና ተሽትሮ፥ ፒታውን አፉ ላይ አጉጦ፥ እግሩን እብነ በረድ ጠረጴዛው ላይ አሳርፎ ጋዜጣ ሲያነብ የተመልካቾችን ዓይኖች ስቦ ስለ ነበር በየቦታው ስለ እሱ መውራት ጀመረ። - አንዳንዱ በርግጥ ፈታሌ ወሮበሌ መሆኑን

ዐወቀ። ሌላው ከሀብቱ ትልቅነት የተነሣ ስለተጠራጠረ በምንም ዓይነት ሁኔታ እሱ እስከዚህ አድጐ ሊመጣ አይችልም በማለት እሱነቱን ካደ። - ደፍሮና ቀርቦ ሊጠይቀው የመጣ ሰው ግን አልነበረም። - የሱን የሀብታም ልብስ፥ እነሱ ከለበሱት ጋር በማወዳደር ለመጠጋት አሳፍሯቸው። - ጊዜው ይሄዳል...... እና ከመቆየት መቼም አስፈሪና አስደንጋጭ ነገር ሁሉ ገራም መስሎ ይታያል። - አንድ ቀን አንድ አብሮ አደጉ የነበረ ሰው ተጠግቶ ያነጋግረዋል...... እንዴት ዋሉ ጌታዬ......! ኧረ ዐውቅዎ ይመስለኛል...... ይለዋል። - ሀብታሙም እንዴታ ከማወቅም ማውቅ፥ አብሮ አደጌ ነበርህ እንዲያውም ይመልስለታ። - በመቀጠልም ምነዋ ስሜን ረሳኸው እንዴ? ይለዋል። - አብሮ አደግም ፍራት ፍራት እያለው አዎን፥ ጌታዬ ይቅር ቢሉኝ ስምዎን ዘንግቼዋለሁ ይመልስለታል። - ስሜንስ አልዘነጋኸውም፤ ታውቀዋለህ...... እዚያ ከሰዎቹ ጋር ቆእምህ ስትተማሙብኝ ሰምቻለሁ...... እና መፍራት አያስፈልግም...... በዚያው በምታውቀው ስሜ ጥራኝ..... ግዴለም! ዴለም አትፍራ ይለዋል። - ትዝም አይለኝ፤ በፍጹም ዘንግቼዋለሁ እያለ እንደማሰብ የከጅለዋል። - ከዚያም የጥንቱ ስምህ የሚጀምርበት ፊደል አቶ ወ..... ወይም አቶ.... ፈ..... እንዲህ ይመስለኛል ባልሳሳት ብሎ ተናግሮ ሳይጨርስ..... አዎን! ልክ ነው። - አይዞህ አትፍራ! አቶ ወሮበሌ አቶ ፈታሌ በለኝ። - እኔ ተጠሪው ሳላፍር አንተን ጠሪውን ምን አሳፈረህ? እኔ ያ ወሮበላ ያ ፈታል የምባለው ሰው ነኝ። አንተ ቆሸሽህና ደህይተህ ስትጠብቀኝ እኔ አምሬና ከብሬ ተመለስሁ ይለዋል። - በዚህን ጊዜ ይናደዳል ጓደኛው..... ከአንተ ማማርና መክበር የኔ መልካም ስምን ይዞ በድህነት መኖር ሳይሻል ቀርቶ? ድህነት ነውር ሆነና ትሰደብኛለህ? ሞሽላቃ ሌባ፥ ወሮበላ ፈታል ምናምንቴ ነውረኛ እያለ እያከታተለ ይሰድበዋል....... ሀብታሙ ግን ከምንም ሳይቆጥረውና ሳይናደድ..... ደስ እንዲለኝና የሰበከኝን ስድብ እንዳልዘነጋው አልፊ አግዳሚውም እንዲያነበውና እንዲያውቀው በዚህ በቀለም እዚህ እነጩ እብነ በረድ ላይ በአጉል ጻፈው ይለዋል። - ጓደኛውም እንደታዘዘው ይጽፈዋል። - በዚህን ጊዜ ሀብታሙ ተኩሱ የባንክ ኖቱን መዘዝ መዘዝ አድርጐ ስድቡ በተጻፈበት እብነ በረድ ጠረጴዛ ላይ በሙሉ ይዘረጋበትና እስቲ እሳዳቢው ጓደኛዬ አሁን አንብበው ይለዋል። - ተሳዳቢውም አሁንማ በባንክ ኖት ሸፈንከው እንዴት ላንብበው ብሎ ይመልስለታል። - አያ ቂሎ ይኸውልህ ገንዘብ እንደዚህ ነውርን ይሸፍናል። ያንተን ድምፃዊ ስድብ የኔ ድምፅ የለሽ ባንክ ኖት ሸፈነው ብሎ አሰናበተው......... እየተባለ ሲወራ እሰማ ነበር ፓሪ በነበርኩበት ጊዜ እልሻለሁ። - እና....... ስለገንዘብና ስለ ሀብት ያለሽ አስተያየት ጤነኛ አይመስለኝም ነው የምልሽ አንቺንም። - በኋላ ይጭሻል.....

«ሀብታሙ በኖት ቢሸፍነው ድሃው የጻፈው ካልለ ከቃሉ አያነብለትም.......?» በማለት መንገድ ትጀምራለች ጺወኔ።

«ምን ለማለትኮ ይመስልሻል.........?

«እኔም ብሆን ድህንትን እመርጣለሁ እንዲያ ሆኖ ሀብት ከማግኘት......

«ያንቺ ሀብት በእንዲያ የተገኘ አይደለማ?!

«ያንቺ ሀብት በእንዲያ የተገኘ አይደለማ?!

«ቢሆንም......! ሀብት......? ሀብት.......? የእንዲህ የእንዲህ ዓይነቱ...... ሀብት.......!» ይቀጥላል በእንዲህ ዓይነት...... ልዩ ልዩ ዓይነት ቀለም እየተቀባ..... ልዩ ልዩ መልክ እያወጣ። - ሰልቸታ አይታይባትም። -

## ፵፱

## አደፍርስ

ጺወኔ ከአጐቷ ጋር ተቀምጣለች። - ከፖሊስ ጣቢው ሁነት ወዲህ ምድራዊ የሰው ኑሮ ያስጠላት ይመስላል። - ከመንፈሳውያን ሰዎች ጋር መነጋገር ቤተ ክርስቲያን መሳም ማዘውተር ሆኗል ሥራዋ። - አደፍርስን ከእናቷ ጥላቻና መራራ ንግግር ያወጣችው መስሏት ሕጓ፥ ሳይደፈር፥ ተደፍሯል ብላ የሰጠችው ቃሏ ኅሊናዋን እንደ ወቀሰው አለ። - የብዙ ጊዜ ሱባዔና ጸሎት እንኳን የሚዋጀው መስሎ አይታያትም። - እንዲያውም አንዳንድ ጊዜማ የመኘታ ክፍሏን እየዘጋች ማልቀስ ነው ሥራዋ...... በተለይ አደፍርስ በርግጥ ክብርናዋን አስወስዳለች ብሎ አምኖ ያመናጭቃትና የጠላት መሆኑን ባሰበችው ጊዜ....... ማልቀስ ማልቀስ ነው ሥራዋ። - ቤቱንስ ፈልጌ ብደርስበት...... ከክብሬስ ነኝ ብለው...... እንዴት አድርጐ ያምነኛል......? ያሁኑስ ነገሬ፥ ውሸት ያለመሆኑን በምን ያውቀዋል........? አምላኬ! አምላኬ! የሚበጀውን መንገድ አሳየኝ...... በበትረ መንግሥትህ አትርሳኝ........ እያለች። - አንዳንዴ ደግሞ የራሷን ክብር ለሱ ክብር ስትል ተገፋ ያሳየችው ተጋድሎ ያልገባው መሆኑን ስታስበው ለወደፊቱም ቢሆን ያደረገችለትን መሥዋዕትነት ያውቀው ይሆናል የሚል ተስፋዋ እየመነመነ መሄዱን ስታየውና ሞታ እንኳን ቢሆን በትዝታው የመኖር መጽናናት እንዳልነበራት ስትገነዘበው የሥራ አካላቷን ያቃጥላትና እንደ እብደት ዓይነት ስሜት፥ ብረሪ ብረሪ የሚል አጣድፊኝ ነው የሚነዛባት። - አልፎ አልፎም ቢሆን ብቅ ያሉ እንደሆን ነው አባ ዮሐንስ ትንሽ ወደሷነቷ የምትመለሰው። - የሚናወጸው መንፈሷ የሚረጋጋላት........ሰውነቷን የሚያስጨንቀው ንዚት የሚነሣላት -

«.......አንዳንዱ ለምድራዊ ኑሮ እንደሚስማማ ሆኖ ይፈጠራል...... ከባላባት መካከል ተወልዶ ባላባት ይሆናል። - በሰው ልጅነት አጥንቱ በባላባትነት ንብረቱ ይንደላቀቃል። - ችግርና መከራ የሚያገኙት አይመስለውም። - አፋሽ ከንፋሹ፥ ጠብ ርግፍ ባዩ ዙሪያውን ይከበዋል። - ሲናገር እውነት እውነት ሲጣራ አቤት አቤት ባዩ ግቢውን ይሞላዋል። - ያዩት ሁሉ ይጨነቁለታል። - ይርበተበቱለታል። - ገና ከሩቅ ብቅ ሲል ይነሡለታል። - ቆይቶ ሲሄድ ተሽቆጥቁጠው ይሸኙታል። - ያለም ጠርዟ እሱ ቤት የተወሰነች ይመስለዋል። - ከርሱም ኑሮ የተሻለ ኑሮ ይኖራል ብሎ ለመፈለግ አይነሣም ‹.......ገመል አንተ ስቁረተ መርፍእ እምባዕል በዊአ መንግሥተ እግዚአብሔር......› ባለጸጋ መንግሥተ ሰማያትን ከመውረስ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብትወጣ ይቀላታል - ተብሎ የተነገረለት ዓይነት ሰው ይሆናል ማለት ነው ባጭሩ............................

........................................................................

.......................................................

.....................................

......................

..........

እያሉ በመደሳሰስ ሲያጫውቷት በሌላው ዓለም ተስፋ። - ወይም ደግሞ -

## ፰

## አደፍርስ

........‹ቀደስኩከ እምከርሠ እምከ› - ገና ከናትህ ማሕፀን መርጬሃለሁ እንደ ተባለው ገና ሲፈጠር ለእግዚአብሔር የሚመረጥ አለ....... እንደ ጻድቃኑና እንደ ሰማዕታቱ....... ምንም እንኳ ከባላባት ወገን ቢሆንም የተወለደው ባካባቢው የሚያያቸው ድሪያ ዝሙት፥ ስካር፥ መጋደል በጌጣጌጥ መብለጭለጭ፥ መከዳዳት ምቀኝነት፥ ተንኮልና ኩራትን የመሳሰሉት የኑሮ ተውሳኮች ሁሉ ያስጠሉትና በምግበ ሥጋ በምግበ ነፍስን ተክቶ በሚያልፈው ዓለም ምትክ የማያልፈውን ዘለዓለማዊ ዓለም ለማግኘት ይነሣል። - ዘመድ አዝማዱን ጐጆ ንብረቱን ትቶ፥ ዳባ አስኬማ መቋሚያ የመቁነን መቀበያ ቅልና ቆሬውን ብቻ ይዞ፥ ይወጣል። - ቁር እሚጋገርበት ወይም ሐሩር እሚያቃጥልበት ቦታ ሄዶ...... ቅጠላ ቅጠል ፍራፍሬና የዱር እንስሳት ወተት

ብቻ እየተመገበ፥ በጾመ በጸሎት ተወስኖ...... የጌታ አገልጋይ ሆኖ ለመኖር ቆርጦ ይመንናል...... አንቺ የኔ ልጅ እንግዲህ ገና ስትፈጠሪ ለጌታ አገልጋይነት የተመረጥሽ ሰማያዊ መንግሥቱን ሊገልጽብሽ ያቀሽ ነው የምትመስይኝ። - የደረሰብሽም ፈተና እንኳን ቢሆን ያልሆንሽውን ሆኛለሁ ብለሽ የወደድሽውን ሰው ክብር ለመጠበቅ ስትይ ያሳየሽው ሰማዕትነት የጌታን መስቀል መሸከምሽን ነው የሚያሳየው። - ወደፊትም ቢሆን ይኸን የመሳሰለ ብዙ ፈተና ይገጥምሻል። - እና ዋናው ነገር ብቻ ወዲያ ወዲህ ሳትይ ዓይንሽን አቅንተሽ፥ እጆችሽን አንሥተሽ ልብሽን ለሱው ላንድ አምላክ ማደሪያ አድርገሽ ‹አቤቱ አቤቱ የሚበጀውን መንገድ አሳየኝ፤ በበረት መንግሥትህ አትርሳኝ›ን ጸሎትሽ ማድረጉ ነው....... አዎ በበትረ መንግሥትህ አትርሳኝ ዋና ጸሎት ነው። - የኔ ልጅ የምድራዊ ፍቅር የምድራዊ ጋብቻና የመውለድ የመክበድ ሰው አይደለሽም። - የለም አይደለሽም። - እና ታዲያ ካልሆንሽ ዘንዳ፥ ከሴቶች ሁሉ ተመርጠሽ ክርስቶስ ሠምራን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስን ቅድስት እማሙዝን ብትሆኚ....... እንግዳ ጌጥ ሊሆንብሽ እንዴት ይችላል.......? እንግዳ ጌጥ ሊሆንብሽ አይችልም...... ‹ቀደስኩኪ እምከርሰ እምኪ› ብሎሻል እላለሁ እኔ አባትሽ ፈጣሪሽ። - ምነው ዛሬምኮ ቢሆን እግዚአብሔር በሰው አድሮ ይናገራል...... በሰው አድሮ ይናገራል................................

..........................................................................................

..................................................................

............................................

.......................

........

ወይም ደግሞ.........

# ፳፩

# አደፍርስ

............

..............................

.....................................................

..........................................................................

.............................................................................................

.......ጎዲገ አብያትንና መንኖ ጥሪትን ዮሐንስ አፈወርቅ የሰጠው አንድ ጻድቅ ሰው፥ ከዚህ ዓለም ሐሳብ ድኖ በዕረፍት ይኖር ነበር። - ከዕለታት አንድ ቀን እከብር ባይ ልቡና እቤቱ እንግድነት ያድርና እንደምን ትኖራለህ ይለዋል? ጻድቁም ጎዲገ አብያትንና መንንኖ ጥሪትን ካገኘሁ ወዲህ ከዚህ ዓለም ጣጣ አርፌ እኖራለሁ ይለዋል። - እንግዳው ሰውዬ በዚህን ጊዜ፥ ሞኙ ተላላው፥ ‹ዐባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል›...... እንዳንተ ያለ ሰው ከተማ ገብቶ ተሾሞ ተሸልሞ ቤት ሠርቶ ንብረት ገዝቶ ለተራበ አብልቶ ለተጠማ አጠጥቶ እያስተማረ ይኖራል እንጂ እንዴት እዚህ ይቆራመዳል.......? እነዚህን ያልካቸውን የኋላ ኋላ አታጣቸውም....... ደግሞስ ከመነነና ከመነኮሰ፥ የሰጠ የመጸወተ እንዴት እንደሚሻል ሳታውቅ ቀረህ እያለ በሆነ ባልሆነው ነገር ግራ ያጋባውና...... ለንጉሥ ላሳድርህ ብሎ ይጠይቀዋል። - ጻድቁም ዲያብሎስ መቼ አንዴ ከደጁ ደርሷልና...... ነገሩስ ደግ ነበር፤ ነገር ግን ጎዲገ አብያትንና መንኖ ጥሪትን ተከተሉኝ ብላቸው እሺ ብለው ወደ ከተማ አይሄዱልኝ...... ማንን አስከትዬ እሄዳለሁ ይለዋል። - እደጅ የደረሰ ዲያብሎስ መቼም ተዘጋጅቷልና ፈቲው የሚባለውን አሽከሩን፥ አንተ ተከትለህ እያዘገምህ እኔ ዘንድ ይዘኸው ና...... እኔ ቀድሜ ቦታ አዘጋጅቼ እጠብቃችኋለሁ ይለውና ይሄዳል...... አቶ ዲያብሎስ ተንዘራፍጦ ቦታውን ይይዛል...... አቶ ጻድቅም መጠጣት መስከር መዳራት መጋደል...... ምኑ ቅጡ፥ በያይነቱ ኀጢአት አለበት ከተማ ይገባዋል...... የዚህ ዓለም ነገር....... እንደ ጐርፍ ውሃ እያሳቀ እንደ ቆንጆ ሴት ወይዘሮ እየደለለ...............................................................................................

.......................................................................................................................

.........................................................................................

.....................................................................

.......................................................

..................................

...............

# ፳፪

# አደፍርስ

አጐቷ አቶ ወልዱ ደሞ በበኩላቸው የራሳቸው ዓይነት ድግግሞሽ ነበራቸው...... ማታ ማታ ገብታ ከፍ ካለ በኋላ አብረዋት ቁጭ ሲሉ -

......ሁሉ ነገር እንዳስቀመጡት አይገኝም። - እንዳሰቡት አይሳካም....... የሁሉ ነገር ውዴታ አይዘልቅም....... ይለዋወጣል........ ይቋረጣል። - ምን አለ ብለሽዋል የዚህ ዓለም ኑሮ? እንዳደረጉት ነው። - ሳትደሰች ተደስተሽ........ ምንም ነገር ሳትሆኚ ተከፍተሽ የምትኖሪበት ዓለም......................................

.................................................................................................................

............................................................................................

......................................................................

..................................................

...............................

............

ወይም ደግሞ........

# ፳፫

# አደፍርስ

........

............................

................................................

.....................................................................

......................................................................................

.........................................................................................................

.........................................................................................................................

.......እናትሽ የምትቆጨው የምትናደደው ለማ ክብር ለማ መታወቅ ይመስልሻል? ለአንቺው ነው። - ቆላና ደጋ የምትረግጠው፥ የምትጥረው የምትግረው ለማ ይመስልሻል? ለአንቺው ነው። - የለም የለም ጺወኔ! መንገድ ፈልገን መታረቅ አለብሽ አሁንስ ከናትሽ። - ያባትሽን ሀብት እንኳን መሰብሰቡስ ቀላል ነገር ይመስልሻል? በጽሑፉም በምኑም ብትረጃትኮ ከድካም አዳንሻት ማለት ነው። - እስኪ ተመልከች የጊዜውን አካሄድ....... ከአራት ወር በላይ መሆኑ ነው እንግዲህ ከኛ ጋር ከተቀመጥሽ። - እርግጥ ማለፊያ እንድትለያት አትሻም። - እኔም ብሆን አጉል ልማድ አስለምደሽኛል ማታ ማታ፥ ቁጭ እያልን ማውራት...... ከማን ጋር አወጋ ነበር አንቺ ባትኖሪ? የማለፊያን ነገር ታውቂዋለሽ፤ ከማድ ቤት አትወጣ - እንደ ተርመጠመችው ይመሻላታል..........................

................................................................................................................

.............................................................................................

.......................................................................

.....................................................

.................................

................

# ፳፬

# አደፍርስ

ወይም ደግሞ አንዳንድ ታሪክ በማውራት.......................................................

.......................

.............................................

......................................................................

...............................................................................................

.......................................................................................................................

.........በቁስጥንጥንያ ከተማ አንድ ወሮበላና ፈታል የሆነ ሰው ይኖር ነበር። - ጥሩ ጩልፋትና የፈታልነት ሥራውን አጣርቶ የሚያውቅ ስለ ነበረ አገሬው ወሮበሌ፥ ወይም ፈታሌ ይሉት ነበር። - እሱ ግን ሥራው ስለ ነበር እምብዛም ሰዎቹ ከሰሙ ጋር አዛምደው የሚያስቡት አጉል መልኩ አይታየውም ነበር። - ነውርነቱንም የተገነዘበው ሰው አይመስልም ነበር ባኳኋኑ። - ሲጠሩት አቤት፥ ሲልኩት ወዴት ጩልፋትነቱን በርግጥ ያስመሰክር ነበር በድርጊቱ። - እያደር ግን በተለይ በፈታልነት ሥራው መበለቶችንና ባል የለሾቹን ብቻ ሳይሆን ባለትዳሮችም ጭምር እያቃጠረ፥ ከተማውን አጉል ስም ስላሰጠው አገሬው በተለይ ረጋ ያለ የተደላደለ ኑሮ ለመኖር የሚፈልገው ጠላው። - እንዲያውም ካንድ፥ ሁለት ጊዜ በጥይት ሊገድሉት ፈልገው ሳቱት። - በቁስጥንጥንያ ከተማ ለመኖር አልቻለም። - ወደ አሜሪካን አገር ተሰደደ። - አሜሪካ - በዚያው በለመደው ሥራው ቀጠለ። - እና በጥቂት ዓመታት ውስጥ የሱኑ ዓይነት ሥራ ይሠሩ ከነበሩት ካገሬው ሰዎች ይበልጥ ታወቀ። - ሀብት አገኘ። በለጸገ። - ነገር ግን ባለጸጋ ብርቅ ባልሆነበት ባሜሪካ የሱ ብልጽግና ከሌሎች በልጦ ሊያሳውቀው አልቻለም። - የሰበሰበውን ሰብስቦ ወደ ትውልድ ሀገሩ መመለስ ግድ ሆነበት። - ምን አለ አልሽው? የሰው ተፈጥሮ! ገንዘብ ሲገኝ ሹመት ሹመት፥ ሲገኝ መታወቅና መግነን - ምናለ ብቻ - ክብረት በሰው አገር አይደምቅምና ሀብቱንና ብልጽግናውን ይዞ ወደ ቁስጥንጥንያ ተመለሰ። -

ከዕለታት አንድ ቀን አምሮና ተሸትሮ፥ ፒታውን አፉ ላይ አጉጦ፥ እግሩን እብነ በረድ ጠረጴዛው ላይ አሳርፎ ጋዜጣ ሲያነብ የተመልካቾችን ዓይኖች ስቦ ስለ ነበር በየቦታው ስለ እሱ መውራት ጀመረ። - አንዳንዱ በርግጥ ፈታሌ ወሮበሌ መሆኑን

ዐወቀ። ሌላው ከሀብቱ ትልቅነት የተነሣ ስለተጠራጠረ በምንም ዓይነት ሁኔታ እሱ እስከዚህ አድጐ ሊመጣ አይችልም በማለት እሱነቱን ካደ። - ደፍሮና ቀርቦ ሊጠይቀው የመጣ ሰው ግን አልነበረም። - የሱን የሀብታም ልብስ፥ እነሱ ከለበሱት ጋር በማወዳደር ለመጠጋት አሳፍሯቸው። - ጊዜው ይሄዳል...... እና ከመቆየት መቼም አስፈሪና አስደንጋጭ ነገር ሁሉ ገራም መስሎ ይታያል። - አንድ ቀን አንድ አብሮ አደጉ የነበረ ሰው ተጠግቶ ያነጋግረዋል...... እንዴት ዋሉ ጌታዬ......! ኧረ ዐውቅዎ ይመስለኛል...... ይለዋል። - ሀብታሙም እንዴታ ከማወቅም ማውቅ፥ አብሮ አደጌ ነበርህ እንዲያውም ይመልስለታ። - በመቀጠልም ምነዋ ስሜን ረሳኸው እንዴ? ይለዋል። - አብሮ አደግም ፍራት ፍራት እያለው አዎን፥ ጌታዬ ይቅር ቢሉኝ ስምዎን ዘንግቼዋለሁ ይመልስለታል። - ስሜንስ አልዘነጋኸውም፤ ታውቀዋለህ...... እዚያ ከሰዎቹ ጋር ቆእምህ ስትተማሙብኝ ሰምቻለሁ...... እና መፍራት አያስፈልግም...... በዚያው በምታውቀው ስሜ ጥራኝ..... ግዴለም! ዴለም አትፍራ ይለዋል። - ትዝም አይለኝ፤ በፍጹም ዘንግቼዋለሁ እያለ እንደማሰብ የከጅለዋል። - ከዚያም የጥንቱ ስምህ የሚጀምርበት ፊደል አቶ ወ..... ወይም አቶ.... ፈ..... እንዲህ ይመስለኛል ባልሳሳት ብሎ ተናግሮ ሳይጨርስ..... አዎን! ልክ ነው። - አይዞህ አትፍራ! አቶ ወሮበሌ አቶ ፈታሌ በለኝ። - እኔ ተጠሪው ሳላፍር አንተን ጠሪውን ምን አሳፈረህ? እኔ ያ ወሮበላ ያ ፈታል የምባለው ሰው ነኝ። አንተ ቆሸሸህና ደህይተህ ስትጠብቀኝ እኔ አምሬና ከብሬ ተመለስሁ ይለዋል። - በዚህን ጊዜ ይናደዳል ጓደኛው..... ከአንተ ማማርና መከበር የኔ መልካም ስምን ይዞ በድህነት መኖር ሳይሻል ቀርቶ? ድህነት ነውር ሆነና ትሰደብኛለህ? ሞሽላቃ ሌባ፥ ወሮበላ ፈታል ምናምንቴ ነውረኛ እያለ እያከታተለ ይሰድበዋል....... ሀብታሙ ግን ከምንም ሳይቆጥረውና ሳይናደድ..... ደስ እንዲለኝና የሰበከኝን ስድብ እንዳልዘነጋው አልፊ አግዳሚውም እንዲያነበውና እንዲያውቀው በዚህ በቀለም እዚህ እነጩ እብነ በረድ ላይ በአጉል ጻፈው ይለዋል። - ጓደኛውም እንደታዘዘው ይጽፈዋል። - በዚህን ጊዜ ሀብታሙ ተኩሱ የባንክ ኖቱን መዘዝ መዘዝ አድርጐ ስድቡ በተጻፈበት እብነ በረድ ጠረጴዛ ላይ በሙሉ ይዘረጋበትና እስቲ እሳዳቢው ጓደኛዬ አሁን አንብበው ይለዋል። - ተሳዳቢውም አሁንማ በባንክ ኖት ሸፈንከው እንዴት ላንብበው ብሎ ይመልስለታል። - አያ ቂሎ ይኸውልህ ገንዘብ እንደዚህ ነውርን ይሸፍናል። ያንተን ድምፃዊ ስድብ የኔ ድምፅ የለሽ ባንክ ኖት ሸፈነው ብሎ አሰናበተው......... እየተባለ ሲወራ እሰማ ነበር ፓሪ በነበርኩበት ጊዜ እልሻለሁ። - እና....... ስለገንዘብና ስለ ሀብት ያለሽ አስተያየት ጤነኛ አይመስለኝም ነው የምልሽ አንቺንም። - በኋላ ይጭሻል.....

«ሀብታሙ በኖት ቢሸፍነው ድሃው የጻፈው ካልለ ከቃሉ አያነብለትም.......?» በማለት መንገድ ትጀምራለች ጺወኔ።

«ምን ለማለትኮ ይመስልሻል.........?

«እኔም ብሆን ድህንትን እመርጣለሁ እንዲያ ሆኖ ሀብት ከማግኘት......

«ያንቺ ሀብት በእንዲያ የተገኘ አይደለማ?!

«ያንቺ ሀብት በእንዲያ የተገኘ አይደለማ?!

«ቢሆንም......! ሀብት......? ሀብት.......? የእንዲህ የእንዲህ ዓይነቱ...... ሀብት.......!» ይቀጥላል በእንዲህ ዓይነት...... ልዩ ልዩ ዓይነት ቀለም እየተቀባ..... ልዩ ልዩ መልክ እያወጣ። - ሰልቾታ አይታይባትም። -

## ፷፫

## አደፍርስ

ሮማን ከደብረ ብርሃን ተመልሳለች። - የማርያምን ቤተክሲያን ልትስም ሄዳ ኖሮ ጂወኔንም እዚያው ታገኛትና አብረው የመኪና መንገዱን ዳር ዳር ይዘው ወደየቤታቸው ሲመለሱ አደፍርስና ክብረት አርፈውበት እነበረው ሆቴል ውስጥ ቁጭ እንዳሉ ያይቸዋል። - አደፍርስ ነው ባንዴ ያወቃቸው -

«.......ይቺ ምናምንቴ! በሷ ቤት አልታየችም....... ደጋግሜ ባልነግራት ደሞ በሆነ......» ብሎም ባንዳፍታ እሳት የሚሆነው። -

«አንተ እስከዚህ ምንቸገረህ? ለምን እንዳትገጥም ትከለክላታለህ.......? ጂወኔ አብሮ አደጓ እኅቷ ነች......» ይጠይቀዋል ክብረት።

«በምንም ዓይነት መንገድ ቢሆን፥ ከሷ ጋር እንዳይበላሽ ብያታለሁ...... በምንም ዓይነት መንገድ.......!

«መቼስ ከደብረ ብርሃን ከመጣች ይኸው እንግዲህ አሥራምስት ቀን ሊሆናት ነው። - እና ፈልጋት አልሄደች...... እንዳጋጣሚ ቤተክሲያን ስታያት መጥታ አነጋግራት ይሆናል.......

«ደሞ እሷ ብሎ ቤተክሲያን ሳሚ! ማን እንድትሄድ ፈቀደላት ቤተክሲያን.......?! ቤተ ክስሪያን ሳሚ.......! የትም ስትናዝር ቆይታ.......!

«እውነቴን ነው የምልህ አደፍርስ፤ የምትናደድበት ምክንያት አይታየኝም.....

«ቃሌ አለመጠበቁ......! ቃሌ አለመጠበቁ.........! ከዚህ የበለጠ ምን ያናደኝ.......?!

«እኮ ለምን.......?

«ከቤት እንድትወጣ አልፈልግም....... በተለይ ከጺወኔ ጋር ተገናኝታ እንዳያት.....

«ምናልባት ስላንተና ስለራሷ ግንኙነት የምታዋእራ መስሎህ እንደሁ.......?

«አሄሄ! እማባቷ መሬት ላይ ቆማ.......? አታደርገውም........ ደግሞስ ምኔ ነች...... እሷ...... ገረድ ነች.......! በቃ....... ገረድ.......!

«ወይዘሮ አካላት አብረውህ ናቸው። - በዚያ ላይ አጣሁ ወሮታ አለች - ሦስተኛ ደሞ - ሮማን.......? እኔ እምልህ ወርዶፉ የልጁን አንተ ዘንድ መቀመጥ ሲሰማ.......

«ይስማ! በግድ አስቀምጫታለሁ እንዴ እኔ.........

«ከበፊቱም ያስኮበለልካት አንተስ የመሰልከው እንደሁ......

«ይምሰለዋ!

«እጁን አጣምሮ ይቀመጥ ይመስልሃል ታዲያ? የጉድባውን ታሪክ ረሳኸው?!

«ካልክስ ያየሁት መሰለኝ ያለችም መስሎኛል - ጴጥሮስን ሮማን...... ብቻ ለሁሉም - እስቲ እንርሳው - እንነጋገርበት አሁን ጋሼ ክብረት...... ዝም ብለን እንጠጣ ቢራችንን...... ሌላ ሌላ ነገር እየተጫወትን.....

በስተግራ በኩል ተማሪዎች ተሰልፈው ይመጣሉ እየዘመሩ። በወፋፍራም ወረቀት ላይ የተጻፈ አቤቱታ አልፎ አልፎ ተሸከመው........ ወታደሮች በየቦታው በተን በተን ብለው ይጠብቋቸዋል። -

## ፳፮

## አደፍርስ

ጺወኔ ወደ አጐቷ ቤት ትመለሳለች «......ዓመት ሙሉ ስጠብቀው አንድ ቀን እንኳን እንዴት ዋልሽ ያለለኝ አደፍርስ...... ለካስ ፍቅሩ ለሮማን ቢሆን ኖሯል.......? ከመጀመሪያውም ቢሆን ጨርሶ አይወደኝም ማለት ነው...... ሮማንን ነው

የወደደው........» እያለች ስትብሰለሰል እቤተክሲያን በሩቅ ያየቻት ጊዜ - በፊለፊቷ ባርኔጣዋን ወደ ታች ቀልበስ አርጋ - የጥላው መሥመር ልክ እከፈንሮቿ ገደማ እንደሚቆም ሆኖ ፊቷን ከፀሐዩ አጥልቶላት - ያደረገችው ታኮ ጫማ ቁመቷን ጨምሮላት - የለበሰቻቸው አጫጭር ዘመናውያን ልብሶች አምረውና አሳምረዋት - የማነች ቆንጆ በማለት ደጋግማ የተመለከተቻት በተጨማሪ ይታሰባትና የባሰውን ብስጭትጭት ትላለች። - እቤቷ እንደ ደረሰች ሮጣ ትገባለች ወደ መኝታ ክፍሏ «.......እሷን ነው ማለት ነው ከመጀመሪያውም የወደዳት...... እሷን ነው ማለት ነው የሚወዳት......» መኝታዋ ላይ ቁጭ እያለች «እሷን የሚወዳት......! እሷን - እሷን! እሷን! እሷን!.......» ትራሷን ትመታታዋለች በጡጫዋ። - እንባዋ አይመጣላትም። የባሰ ትበሳጫለች። - በስንት ትግል ትንሽ ታለቅሳለች። - አይበቃትም። - እንደ ገና ደግሞ ትንሽ ታለቅሳለች። - አይበቃትም አሁንም። - እንደሚንቀሳቀስ ከባድ ሸክም የሚሰማትን ልቧን፥ የመነዘለውን ሥቃይና ሐዘኗን ጭር ጭር በሚል አልፎ አልፎ እየወረጨ በሚወርድ እንባዋ ልታሰጠምው አልተቻላትም። - የመጽናናት ኀይል አላገኘችበትም። - የመተንፈስ የመገላገል እፎይታ ሊሰጣት አልቻለም። - ከክፍሏ ሳትወጣ ካንድ ጐኗ ወደ ሌላ ጐኗ እንደ ተገላበጠች ይመሽላታል። -

## ፳፯

# አደፍርስ

መኪና መንገድ፥ የተማሪዎች ሰልፍ ሕጋዊ ያልሆነ መንገድን ይከተላል። - ከወታደሮች ጋር ድንጋይ መወራወር ይጀምራሉ። - ሰላማዊ ሰው ይመትታል። - ይቆስላል። - ጩኸትና ቁቁታ ይነሣል። - አደፍርስና ክብረት ከነበሩበት ሆቴል ይወጡና እተማሪዎቹ ማህል ይገባሉ። - እንዲያቆሙ ለማድረግ ይሞክራሉ ውርወራውን። - ከወዲያ ወዲህ እየተሯሯጡ። - የድንጋይ ውርጅብኝ እየበዛ እየበረከተ ይሄዳል። - ውርወራውን አላፊ አግዳሚው ሁሉ ሳይቀር ይገባበታል። አደፍርስ እጭንቅላቱ ገደማና እደረቱ ላይ በኀይል ይመታና ይወድቃል....... ክብረትም አንዴ ሁለቴ ያርፍበታል፤ አይጐድዳም ግን እሱ፤ አይወድቅም። - ሦስት ጥይት ያህል ወደ ሰማይ ይትተኮሳል። - ተማሪዎች ይበታተናሉ። - አደፍርስን «.......የኛ ድንቁርና ይሻላል ጌታዬ፥ የኛ ድንቁርና...... ዕውቀት ብሎ ነገር ደሞ....... የምን ዕውቀት? ባፍንጫችን ይውጣ....... ዕውቀት........?» እያለ ከሚያነበንብ አንድ ምልክት አሥር አለቃ ወታደር ላይ ተቀብሎ ደገፍ ያደርገዋል ክብረት «ሞትና ሕይወትን ላያራርቁ...... ዕውቀት ብሎ ነገር......» ይቀጥላል ወታደሩ። - ክብረት ገንገን ይልና ቀና ብሎ ያየዋል። - ወዲያውኑ

በጥድፊያ ያነሡታል አደፍርስን፤ የሣንሳ ይሸከሙታል - ወደ ክሊኒክ ያመራሉ «.......ሞትና ሕይወት...... ድንቁርናና ዕውቀት...... ላያራርቁ.......» የሚሉት ቃላት እያቃጨሉበት ኋላ ኋላ እያለ ክብረት። ማታ ሦስት ሰዓት ገደማ ይሞታል አደፍርስ። -

በማግሥቱ ጧት፥ ያሏትን ሁለት ሦስት ቀሚሶች ለማጣጠብ ትዘገጃጃለች እውጪ - ጺወኔ። - የወይዘሮ ማለፊያን በመቀነት የታጠፈው ብቻ ለሷ ቀሚስ ሊወጣው የሚችል ረጅም ቀሚስ ለብሳ...... አራት ሰዓት ገደማ ያደፍርስን መሞት ትሰማለች። -

## ፳፰

## አደፍርስ

ሸንተረሩን ገመገሙን ተራራውን ጋራውን ኮረብታውን ጋራውን ኮረብታውን ተረተሩን ጉባውን ሸጡን ሸለቆውን፥ ድሬ በሉውን ፋልማውን...... ብጫ አፈርቻ፥ አረንጓዴ ቀይ ቀለሞች ተምቦራጭቀውበታል - የደረቀው የተቆረጠው የታጨደው የተሰበሰበው የተወቃው የተከመረው....... ድንጋዩ ሽኮቴው መረሬው...... ማሽላው ባርማሽላው..... ዘንጋዳው...... የተመነጠረው የታሠረው የተጨፈለቀው - እብቁ ቆረቆንዳው ግቻው አገዳው ቃርሚያው ቆረኑ ቆረኑ ቃርሚያው አገዳው አገዳው - አገዳው ቃርሚያው....... ሾላው ዋንዛው እንዶዱ ወይባው ጀንፎቁ አለንቋጣው ወደል አስፈሱ አገሩን አልብሰውታል። - እየዳሁ እየተጥለመለሙ ጉርጓዳቸውን እየለቀቁ፥ ትሎች - እየጋጡ እየቀነጠቡ፥ ጋጣቸውን በረታቸውን እየዘነጉ እንስሶች - እየተንሳፈፉ እየመጠቁ ጐጆዋቸውን እየተዉ ወፎች - እየቦጨቁ እየወጉ ጐሪያቸውን እየለቀቁ አውሬዎች - እያሸተቱ እየቀመሱ ቀፎቻቸውን እየከፈቱ ንቦች - እየጮሁ እየገዘፉ ከተማቸውን መንደራቸውን ቤታቸውን እየዘጉ ሰዎች - ሁሉ አዲስ ሆኖባቸዋል -

‹የት ትሄዳለህ የት ትሄዳለህ፥

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ

እናት አባትህን ታሳዝናለህ

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ\

የት ትሄዳለህ የት ትሄዳለህ

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ

ወዳጅ ዘመድህን ታስለቅሳለህ

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ

የት ትሄዳለህ የት ትሄዳለህ

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ

ውዷን አገር ታጕላታለህ

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ?

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ?

ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ......?› እያሰኘ ያስደልቅ ያስናድል ያስገዝፋቸዋል። - በቆሙበት ቦታ ሁሉ። - ከሞትም ከሕይወትም ይሞቦለቦላል ውደቱ - ከጣኑም ካዝርእቱ። - የዳአዊት መዝሙሮች ይንዶቀዶቃሉ - መቶ ኀምሳ አንዱም እስኪፈሱ - በሰባት ጊዜ ቁመት። የወይዘሮ አካላት ዘመድ የሆነ «ጉዞ ፍታት የከፈልነውኮ ለቀልድ አይደለም!» እያለ በጥንቃቄ ይከታተላል...... አንዲቷ እንኳ መዝሙር እንዳትሰግር። -

ራሳቸው ወይዘሮ አካላት ደረታቸውን ጥለዋል። - ከንፈራቸው ያለረፍት ይንቀሳቀሳል፤ አንዳንዴ በመሐረባቸው አበስ እየተደረገ። - እንባ ቢሆን አይወርዳቸውም። - አቶ ጥሶ ያለቅሳሉ በለኆሳስ። - ሮማን ታለቅሳለች ላርጋጅ ለቀባሪው አስቸግራ። - ጺወኔ ታለቅሳለች የሥዕል አልቃሽ ሆና - ያስቋርጥ እንባዋ፤ የሕይወት ምልክት እንጂ - ሕይወት ያለባት ያለመምሰል። - እጕን እጕና እያለ ጕርፉ -

«......ምን ላርግ ትይኛለሽ? ላድነው ነበርኮ የሮጥሁት - ምን አስቤ ደሞ.......! እሱስ ደሞ እጁን ያዝ ሳደርገው የዘነጋኝም መሰለኝ - ሊመነጭቀኝም ፈለገ - መንፈቅ እንኳን አልሆነን - ይኸ የወታደር ልብስ ሌላ አስመስሎኛል መሰለኝ......? የነሱው ተማሪ የሆነ ነውኮ ድንጋዩን የወረወረው - ለኔ ይመስለኛል ድንጋዩ - ርግጠኛ ነኝ አስተማሪውን ሊመታ አልወረወረም - አያድርስ ነው መቼም ሰኔና ሰኞ የሚሉት ነገር...... ጺወኔ አትናገርም። - ያለማቋረጥ የሚፈሰው እንባዋ ግን እያደር ተግታ ያገኛል....... አገሬን ለቀቅሁ ይኸውልሽ እኔም - ምን ላድርግ ትይኛለሽ.......? መቼም እውነቱን ልንገርሽ፥ እንዲህ አጠገብሽ ታስቆሚኛለሽ ብዬ በውኔ ቀርቶ በልሜ

አላሰብኩትም - ያው ያነዬ አገሬው ሁሉ ሳቀብኝ - እንቿንም አጉላልቼ - ሳይሳካልኝ! ምን ይደረግ ቀረ........ ይኸ መሳይ ልጅ - ጥሩ ልጅ ነበር አደፍርስ - እጄ ላይ ነውኮ የወደቀው ሲሙቱት - እኔ ደሞ ምን ይሞት ብዬ - ሐኪሙ እንኳ ከተናገረ በኋላ አላመንኩም - ይገርምሻል - ትኩር ብሎ ያየኝ ነበር እጄ ላይ ሲወድቅ - ከንፈሩ ሁሉ ይላወስ ነበር....... የሰው ነገር እንድዋሉ መቅረት - ደሙ ከፊቱ ላይ ሲጠፋ ሳየው እንኳ አለመጠርጠሬ.......! እንደዚሁ ዓይነት ሁኔታ ወደዚህ ወደ ተጉለት ውስጥ ሽፍቶች አስቸግረው የሄድኩ ጊዜ፥ ሰው ሲሞት አይቼ ነበር - ትዝ ይለኛል - እንዲሁ ደሙ ሲሠርግ ይታይ ነበር ሊሞት ሲል ሹመቴ አልገረመሽም.......? ምክትል አሥር አለቃኮ ሆኛለሁ - ያነዬ ነው ይኸውልሽ የሆንኩት - ሁለቱንም ሽፍቶች ገደልናቸው - ማሾሽላ ዓይነት መልክ እያወጣች ትሄዳለች ጺወኔ...... አንድ ጩልፋት አንደኛውን እኔ ነኝ የገደልሁት ብሎ ተጫውቶብኝ ነበር - ጉድ ሠራሁት ግን እኔ፤ አስመርሰክርሁበት - ስንት ያገሮቻችን ልጆች ያሉ መሰለሽ? - አብረውኝ - ይገርምሻል! ጥቃት የሚወጡ፤ እሳት ውስት የሚገቡልኝ እኔ ከፈለግሁ...... አንች ግን አልተወጥሽም - እናትሽን? እንዴት ናቸው? መቼስ እርጅና ሳይጫጫናቸው አይቀርም - ካዲሳባ በወሯ ተመልሳ - ሰምተሻል ይኸን ጨዋታ........? ወካው ምነዬ አደገ እንዳለችው እንዳታደርጊኚ - አንችም በጣም ያማርሽና የተለዋወጥሽ ነው የመሰለኝ - አላወቅሽም ነበርኮ መጀመሪያ - የማን ጉታታ ቀሚስ ነው የለበሽው? ያሮጊት ልብስ የመስለ - አያስጠላብሽም ግን - ያምርብሻል - ያንቺ ቀሚስ አደለም ርግጠኛ ነኝ - መቀነቱስ ምንኛ አርጅቷል - ያምርብሻል ግን - እውነቴን ነው - ሰውነትሽን ሁሉ ደብቆታል....... በሞተር እንደሚሄድ ነገር ምንጥቅ ብላ ትወጣና ከለቃስተኛው ማህል ወደ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ወደሚወስደው መንገድ ትገባለች...... ምነው ወዴት ትሄጂ? ቀብሩኮ አረጋይ ነው - ልከተልሽ? እምልሽ ወዴት ነው የምትሄጂውው......? አመመሽ ልበል.....?» እያለ ይከታላታል ጉርፉም። - አባ ዮሐንስ ከጉርፉ ኋላ ኋላው ለጥቀዋል.....

«.....አየህልኝ ይን ታምር.....» እያሉ «ይኸን ታምር - የሚገርምኮ ነገር ነው፤ እንደ ጥይት ነውኮ ተስፈንጥራ የወጣችው - ስታጽናናት ነበር ይመስለኛል - ለሷ ምኗ ነው? እውነቷን ነው - ሙቶች ሙታቸውን ይቅበሩ - ጌታ ያለው የፈቀደው ሲፈጸምኮ ነው? ለራሱ ያእልውን ማን ይወስድበታል ዱሮስ? ለራሱ አገልጋይ የመረጣት ልጅ - ለራሱ የፈጠራት - ለሥርዐተ ምንኩስናዋ እግዚአብሔር በደኅና ያድርስና......! የሚገርም ነገር - እፊቷ ላይ የታየኝ መለስ ስትል - በአምሳለ ርግብ መልክ እንደ ጥላ ጀበብ ብሎ ሲርገበገብ - ባናቷ ላይ ሲያበራ - ምን ይሳነዋል ለሱ.....? የዘለዓለም ቤቷን አስመለከታታ.......! ምን ይሳነዋል.......? ፍጥነቱን እየጨመረ ይሄዳል ርምጃዋ፥ የጺወኔ - ባይነቱ ይከተላታል ጉርፉ። - አባ አዲሴም ከጉርፉ ኋላ ኋላ። - እየጨመረ -

እየጨመረ - እየጨመረ - ይሄዳል - እርምጃዋ። - እንደሷ ለመፍጠን ከጀል - ከጀል - ከጀል ያደርገዋል ጐርፉም። - አንዴ ሁለቴ ጀመር ጀመር አድርጐ - ያባ ዮሐንስ መከታተል ገንፈል ያደርገውና ይቆማል፤ ያመነታታል - ወደ ለቃስተኛው ይመለሳል። - ለሥርዐተ ምንኩስናዋ....... ቢያቆየኝ...... የኔ ልጅ....... ሥርዓተ....... ምንኩስናዋ...... ቢያቆየኝ...... ዱሮም...... ብያ....... ለሁ.......» ቅትት ቅትት እያሉ በመጣደፍ እሷ ዘንድ ለመድረስ ይታገላሉ፣ አባ ዮሐንስ...... ግርማዊ ሞገሳዊ መንፈሳዊ የሆነ የደወል ድምፅ ማስተጋባት ይጀምራል በቀዬው - ከሩቅም ከቅርብም እየመሰለ - የጺወኔን እርምጃ - እያስቀረ - እያስቀረ - እያስቀረ - ከአረጋዊ ደብር ላይ ነጫጭ ጐሴዎች ያስነሣና - አንዴ ደረታቸውን አንዴ ጀርባቸውን ለአቆልቋይዋ ፀሐይ አስሰጥቶ - ነጭ - ደብዛዛ - ብጫ - ብጫ - ብጫ - ወርቅማ - ወርቅማ - ወርቅ እያስደረገ - ለዛዛ ዓይነት ማዕበል ፍራቻ ድንጋጤ በሰውነት እየነዛ - እያቋረጠ - እየቀጠለ - እያቋረጠ - እየቀጠለ....................................................................................................................................



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ዳኛቸው ወርቁ በ፲፱፳፰ ዓ.ም. ደብረሲና ተወለዱ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በዚያው በደብረሲና አጠናቀቁ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተምረዋል፡፡ በ፲፱፵፫ ዓ.ም. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የከፍተኛ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል፡፡ በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸውም በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ የተቃውሞ ግጥሞችን ይጽፉ ነበር፡፡ ይህንንም በተመለከተ ስብስብ ሥራዎቻቸውን "እምቧ በሉ ሰዎች" በሚል ርዕስ መጽሐፍ አሳትመዋል።

ዳኛቸው ወርቁ በአዲስ ዘመንና በየዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጦች ላይ ስለተለያዩ ጉዳዮች ይጽፉ ነበር፡፡ የተለያዩ ተውኔቶችን ጽፈዋል፡፡ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንደምትቀላቀል በሚነገርበት ጊዜ "ያላቻ ጋብቻ ትርፉ ሐዘን ብቻ" የሚል ተውኔት ደርሰዋል፡፡ ከዳኛቸው ሥራዎች መካከል በ፲፱፷፪ ዓ.ም. ለኅትመት የበቃው "አደፍርስ" የተሰኘው መጽሐፋቸው በብዙዎች ዘንድ አድናቆትን ያተረፈ ነው፡፡

በጊዜው የነበረውን የመኳንንቱንና የባላባቱን የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም ስለ ሃይማኖት በሰፊው ይገልጻል፡፡ "አደፍርስ" የታሪኩ ባለቤት ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመሆን ከአዲስ አበባ ወደ ባላገር በመሄድ በአንድ ላይ ቤት ተከራይተው መኖራቸውን በመተረክ በከተማውና በባላገሩ መካከል ያለውን ከፍተኛ የአስተሳሰብ፣ የልማድና የመሳሰሉትን ልዩነቶች በጉልህ ያሳያል፡፡

## የደራሲው ሥራዎች

1. አደፍርስ(**ልብወለድ**)
2. እምቧ በሉ ሰዎች (**ግጥምና ቅኔ**)
3. ሰቀቀንሽ እሳት(**ተውኔት**)
4. ሰው አለ ብዬ(**ተውኔት**)
5. ትበልጫ(**ተውኔት**)
6. ያላቻ ጋብቻ ፥ትርፉ ሐዘን ብቻ (**ተውኔት**)

7. ማሚቴ (**ልብወለድ**)
8. Shout It from the Mountain Top ያልታተመ (**ልብወለድ**)
9. የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ (**ምርምር**)

NIGUSS DIGITAL LIBRARY